

# አጤ ምኒልክ

ከጳውሎስ ኞኞ

# ዳግማዊ አጤ ምኒልክ

ከጳውሎስ ኞኞ

የመጀመሪያው መጽሐፍ
በየካቲት ወር 1984 ዓ. ም. ታተመ

@BOOKALEM
ቡክአለም የቀረበው መጽሐፍ

# ማ ው ጫ


ትውልድ .............. .................. .. 11
ከመቅደላ ማምለጥ ...... .................. 19
የግዛት መስፋፋት .......................... 26
አርሲ .................................. 29
ወለጋ .......... ......................... 30
ከፋ ..... ................................. 30
ወላይታ ................................. 36
የሐረርጌ ጦርነት ............................ 39
የሥልጣን ትግል ........................... 46
የእንባቦ ጦርነት ........................... 63
ከንጉሥነት ወደ ንጉሠ ነገሥትነት ............... 94
የረሃብ ዘመን ............................. 126
አድዋ ................................... 131
የውጫሌ ውል ............................ 139
የአድዋ ጦርነት ........................... 159
አምባላጌ ............................... 167
የመቀሌው ምሽግ ........................... 172
አድዋ .............. ................. 195
የአድዋ ምርኮኞች ........................ 219
የኢትዮጵያ እድገት ......................... 236
ትምህርት ... ........................ 242
ባቡር .................................. 248




@BOOKALEM

# ማውጫ


ስልክ ........................ 258
ፖስታ ........................ 266
ኤሌትሪክ ........................ 270
አውቶሞቢል ........................ 271
ባሕር ዛፍ ........................ 293
ቧንቧ ውሃ ........................ 297
ሕክምና ........................ 302
ሆስፒታል ........................ 309
የመድኃኒት መሸጫ ሱቆች (ፋርማሲ) ........................ 311
ባንክ ........................ 316
ገንዘብ ........................ 321
ማተሚያ ........................ 326
ጋዜጣ ........................ 326
ሆቴል ........................ 328
ሰንደቅ ዓላማ ........................ 330
ፖሊስ (ዘበኛ) ........................ 330
ሰዓት እላፊ ........................ 332
ፎቶግራፍ ........................ 335
የጽሕፈት መኪና ........................ 336
ሲኒማ ........................ 336
ወፍጮ ........................ 337
ጫማ ........................ 338
ድር ........................ 339
የሙዚቃ ትምህርት ........................ 340
የሙዚቃ ሸክላ ........................ 340
ፍልውሃ ........................ 341




@BOOKALEM

## ማውጫ

ላስቲክ ........................ .. 343
ትምባሆ ........................ . 344
መንገድ ........................ . 345
አራዊት ........................ . 353
ጥይት ........................ . 355
ብስክሌት ........................ 355
ቀይ መስቀል ........................ 356
አረቄ ........................ . 358
ሥራ ማቆም ........................ . 358
የሚኒስትሮች መሾም ........................ 359
የውጭ አገር ሰዎች ........................ . 369
አስተዳደር ........................ .... 387
ጠባይና ሰውነት ........................ 432
ሕመምና ሞት ........................ 454
የምኒልክ ሐውልት ........................ 499
በምኒልክ ታሪክ ውስጥ ያሉ አስደናቂ ታሪኮች ........ 502
ዋቢ መጽሐፍት ........... .... ....... 506



@BOOKALEM

ለአሥራ አምስት ዓመት ጥሩ ጐረቤቶቻችን ለወይዘሮ ሊንዳ ዱካስ

እ ና

ለባለቤቷ ለአቶ ጥላሁን ወልደየስ

ይድረስ ለመጽሐፌ አንባቢዎች

የተላከ ከጳውሎስ ኞኞ

እኔ ደህና ነኝ ። ይህን መጽሐፌን በማቅረቤ በጣም ደስ ብሎ ኛል ። እናንተንም ቢያስደስትልኝ የበለጠ እደሰታለሁ ።

ጠቅላላውን የኢትዮጵያን ታሪክ ስንመለከት የኢትዮጵያ ነገሥ ታት ሁሉ በየዘመናቸው የየዘመኑን የውጭ ጥበብ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ያልተመኘ ንጉሥ የለም ።አብዛኛዎቹም ከውጭ አገር የሚጠይቁት ጥበባዊ ሥራ የጥይትና የመድፍ መሥሪያ ነው ። ይህም ከውጭ የሚመጣውን ጠላት ለመከላከል ፣ ወይም ደግሞ ያገር ውስጥ ተቀናቃኙን ለመደምሰሻ ነው ።

ምኒልክ በጦር መሣሪያ ፍለጋ ብቻ የተገቱ ሳይሆኑ በዘመና ቸው በውጭ አገር የነበረውን ጥበባዊ ሥራ ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡ ሰው ናቸው ። አሁን በአገራችን የምናየው ወይም የምንገለገልበት በኋላኛው ዘመን ከተፈለሰፉት አዳዲስ ግኝቶች በስተቀር በምኒልክ ጥረትና ዘመነ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ናቸው ። እነኚህንም ጥንታዊ ሥልጣኔዎችን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ምኒልክ ምን ያህል ችግርና ፈተና ደርሶባቸው እንደነበር ከመጽሐፉ ውስጥ ገባ ስንል እናገኘዋለን ። ምኒልክ ያን ሁሉ ችግር ያለፉና ኢትዮጵያን መሥርተው በእግርዋ ያቆሙ ሰው ናቸው ።

በመጽሐፌ ውስጥ እኔ በምተችበት ጊዜ እሮሮ እያልኩ ጽፌ አለሁ ። ግን ካንዳንድ የድሮ መጽሐፍት በተረጐምኩት ፣ ወይም በገ ለበጥኩት ፤ ወይም ከደብዳቤዎች ላይ ባገኘሁት ያው የበፊቱ ሰው እንዳለው ‘ጋላ’ ብያለሁ ።

ይህ መጽሐፍ በ1982 ዓ. ም. አጋማሽ ላይ ታትሞ ሊወጣ ሲል ባንዳንድ ጥቃቅን የሳንሱር ምክንያት ተይዞ ቆየ ። አሁን የመጻፍ ነፃነት ከታወጀ በኋላ ተቋርጦ የነበረው ሥራው እልቆለት ለመታ ተም በቃ ።

ደህና እንሁን

# ትውልድ

ምኒልክ በ1836 ዓ.ም. ነሐሴ 12 ቀን ቅዳሜ ዕለት ተወለዱ ። አባታቸው ኃይለ መለኮት ሣህለሥላሴ ሲሆኑ እናታቸው ወይዘሮ እጅጋየሁ ለማ አዲያሞ ይባላሉ ።

የምኒልክ እናት ወይዘሮ እጅጋየሁ የንጉስ ሣህለ ሥላሴ ሚስት የወይዘሮ በዛብሽ ገረድና የልጆች ሞግዚት ነበሩ ። እጅጋየሁ የግር ድና ሥራ የጀመሩት በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቤት አልነበረም ። ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቤት ከመቀጠራቸው በፊት የአንኮበር ቤተ ክርስቲያን አለቃ የነበሩት የመምህር ምላት ገረድ ነበሩ ። በአለቃ ምላት ቤት ግርድና ተቀጥረው ሳለ አንድ ቀን ጧት ለጓደኞቻቸው "....ዛሬ ማታ በሕልሜ ከብልቴ ፀሐይ ስትወጣ እየሁ...." ብለው ተናገሩ ። ሥራ ቤቶች የሰሙት ወሬ መዛመቱ አይቀርምና ወሬው ከጌትዮው ከአለቃ ምላት ዘንድ ደረሰ ። አለቃ ምላትም "እንግዲያው ይህ ከሆነ ወደላይ ቤት ትሂድ" አሉ ። የላይ ቤት የሚባለው የአንኮበሩ የን ጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቤተ መንግሥት ከኮረብታ ላይ በመሆኑ አገሬው በተለምዶ "ላይ ቤት" ይለዋል ።

እጅጋየሁ እንደተመከሩት ከንጉስ ሣህለ ሥላሴ ቤት ሔደው ተቀጠሩ ። የእጅጋየሁ የሕልም ወሬ ተዛምቶ ንጉስ ሣህለ ሥላሴም ቤት ገብቶ ስለነበረ የንጉስ ሣህለ ሥላሴ ባለቤት ወይዘሮ በዛብሽ ያ በሕልም የታየው ፀሐይ ከልጃቸው እንዲወለድ ፈለጉ ። ወይዘሮ በዛብሽ ከልጆቻቸው ሁሉ አብልጠው ሰይፉ ሣህለ ሥላሴን ይወዱ ታል ። ስለዚህ ሰይፉ ከእጅጋየሁ ልጅ እንዲወልድ ማታ እጅጋየ ሁን ወደሰይፉ መኝታ ቤት ልከው ያን ጕረምሳ እንድትጠብቅ አደ ረጉ ።

የልጅ ሰይፉ አሽከሮች የእጅጋየሁን መላክ እንዳወቁ ለጌታ ቸው ለልጅ ሰይፉ ተናገሩ ። ሰይፉ የሚወዳት ሌላ ሴት አለችው ። የአዲሲቱን የእጅጋየሁን መምጣት እንደሰማ ተናዶ እንዳያባርራትም እናቱን ፈርቶ ከወንድሙ ከኃይለ መለኮት ዘንድ ሔዶ "እባክህ ሌላ ሴት ከሌለህ እሜቴ የላኳትን ያቺን ገረድ ውሰድልኝ" አለ ። ኃይለ መለኮትም እሺ ብሎ ከእጅጋየሁ ጋር ባደረጉት ግንኙነት ልጅ ተፀነሰ ።

እናትዮዋ ወይዘሮ በዛብሽ የእጅጋየሁን መፀነስ እንዳዩ ከሰ ይቶ ያረገዘች መስሏቸው ተደስቱ ። በኋላ ግን ከሌላው ልጃቸው ከኃ ይለመለኮት ማርገዝዋን ሲሰሙ ተናደው እጅጋየሁን በእግር ብረት አሠሩዋት ። ቆይቶም በአማላጆች ተፈታች ። ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ይህን ወሬ ሰሙ ። ልጃቸው የንጉስ ልጅ ሆኖ ገረድ በማፀነሱ ተናደው ወሬው እንዳይሰማ እጅጋየሁን ከርስታቸው ከአንጐለላ ሔዳ እንድት ቀመጥ አደረጉ ።

እጅጋየሁ የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ወንድ ልጅ ወለደች ። የእ ጅጋየሁን መውለድ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ሲሰሙ የልጁን ስም "ምን ይልህ ሸዋ በሉት" ብለው ስም አወጡ ። ምን ይልህ ሸዋ ያሉበት ምክንያት የኔ ልጅ ከገረድ በመውለዱ ሸዋ ምን ይል ይሆን ? ለማ ለት ነው ። በኋላ ግን በሕልማቸው ከምን ይልህ ሸዋ ጋር አብ ረው ቆመው ከእሳቸው ጥላ የልጁ ጥላ በልጦ ፡በእግር የረገጡትን መሬት ሲያለካኩ እሳቸው ከረገጡት ልጁ የረገጠው ረዝሞ አዩ ። ይህን ሕልም ካዩ በኋላ "ምኒልክ የኔ ስም አይደለም ። የሱ ነው ። ስሙን ምኒልክ በሉት" ብለው አዘዙ ።

እዚህ ላይ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ "....ምኒልክ የኔ ስም አይደ ለም የሱ ነው...." ያሉት በጥንት ጊዜ "ምኒልክ በሚል ስም የሚ ነግሥ ንጉሥ ኢትዮጵያን ታላቅ ያደርጋታል" የሚል ትንቢት ስለ ነበረ ሣህለ ሥላሴ ሲነግሡ "ስሜ ምኒልክ ይሁን" ብለው ነበር ። ምኒልክ በሚለው ስም ሣህለ ሥላሴ ለምን እንዳልነገሱ ክብረ ነገ ሥት ውስጥ ብንመለከት "....የሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ፣ ምኒልክ በሚባል ስም ሲነግሱ ሲሉ አንድ መነኩሴ በዚህ ስም አትንገሥ ። መጥፎ አጋጣሚ ያመጣብሃል ። ይህ ስም የሚስማማው ከመጀመሪ ያው ወንድ ልጅህ ከኃይለ መለኮት ለሚወለደው ነው ።ይህም ስም የሚወጣለት የልጅ ልጅህ ኢትዮጵያን አንድ የሚያደርግ ትልቅ ንጉሥ ይሆናል አላቸው...." ይላል ። ስለዚህ ነው የልጁን ስም ምኒልክ ያሉት ።

ይሄው ከድሃ መወለድ በዘመኑ እንደነውር ተቆጥሮ ፣ ምኒልክ በሣህለ ሥላሴ ቤተ መንግሥት ውስጥ እንዳያድጉ ተደርጓል ። ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ እየፈሩ ከፃፉት ብጠቅስ "....ስለ ሕዝብ ዕረፍትና ጤና ፣ የተወለደው ምኒልክ በአንጐለላ መቅደላ ኪዳነ ምሕ ረት ክርስትና ተነስቶ ጠምቄ በሚባል አገር በሞግዚት እኖሩት...." ብለዋል ። አንጐለላ ደብረ ብርሃን ከሚባለው ከተማ አጠገብ ያለ መን ደር ነው ። መንዝ ውስጥ ባለው ጠምቄ በሚባለው አምባም ከእናታ ቸው ጋር ሰባት ዓመት ተቀመጡ ።

ፈረንሣዊው ሄንሪ አውደን በ1872 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ነበር ። ስለምኒልክ ትውልድ ሲተርክ "....ምኒልክ በተወለዱ ጊዜ መስፍኑ (ኃይለ መለኮት) ልጁን አልቀበልም ብለው ካዱ ። በነገሩ መሀል ወይዘሮ በዛብሽ ገብተው ሌሎቹንም ዘመዶቹን ሰብስበው ልጁ የኃይለመለኮት መሆኑን አምነው ተቀበሉ ።...." ይላል ።

ብዙ ታሪክ ፀሐፊዎች እንደሚሉት ወይዘሮ እጅጋየሁ ውብና ከደሀና ቤተሰብ መወለዳቸውን ይገልፃሉ ። የአባታቸውን ስም ግን የሚገልጽ የለም ። ለማ አዲያሞ ይባላሉ ። ይህን ሲተነትኑም አንዳንዶቹ ከጉራጌ አገር የተማረኩ ባርያ ናቸው ይሏቸዋል ። ባርያ ማለት በገንዘብ የሚሸጥ ብቻ ሣይሆን በጦርነት የሚማረክ ሁሉ ባርያ ይባላል ።ይህ ሁሉ ይቅርና ዋናው ቁም ነገር ታሪክ መሥራት እንጂ ትውልድ አይደለም ። ታላቁ ናፖሊዮን እንደዘመኑ አፃፃፍ ወደላይ የሚቆጠር አልነበረውምና ታሪኩን የሚጽፈው ፀሐፊ ቀርቦ "የትውልድ ታሪክዎን ከየት ልጀምር ?" ቢለው "ያለፈውን ትተህ ከኔ ጀምር" አለ እንደሚባለው ነው ።

ምኒልክ በእናታቸው ሞግዚትነት አደጉ ። አያታቸው ሣህለ ሥላሴ ሲሞቱ የሸዋውን አልጋ ልጃቸው ኃይለ መለኮት ወረሱ ። አጤ ቴዎድሮስ ኃይለ መለኮትን ለማስገበር ወደ ሸዋ በዘመቱ ጊዜ ኃይለ መለኮት በሕመም ስለሞቱ ልጅየውን ምኒልክን ማርከው ይዘዋቸው ሔዱ ። አጤ ቴዎድሮስ ወደሸዋ የዘመቱበት ዋናው ምክንያት እንዲህ ነው ።

አጤ ቴዎድሮስ ከራስ አሊ ጋር ተዋግተው ራስ አሊ ድል ከሆኑ በኋላ ሸሽተው ከደራው ገዥ ዋቆዲቦ ዘንድ ተጠግተው ተቀመጡ ።ዋቆዲቦ የደጃች ካሣን (በኋላ ቴዎድሮስ) ጦር ስለፈራ "ራስ አሊ ከኔ ዘንድ ናቸው" ብሎ ለደጃች ካሣ ላከ ። ይህን ነገር ራስ አሊ ሲሰሙ "እምኜው ብመጣ ዋቆዲቦ ለጠላቴ አሳልፎ ሊሰጠኝ ነውና ታደገኝ፣ አውጣኝ" ብለው ለሸዋው ገዥ ለኃይለመለኮት ላኩ ። ኃይለመለኮትም ጦር አዘጋጅተው ደራ ላይ ዋቆዲቦን ወግተው ራስ አሊን አወጧቸው ። ራስ አሊም ወደ የጁ ሄዱ ። ከዚያም ራስ አሊ ስለፈሩ ራያ በረሃ ወርደው ዋሻ ውስጥ ገብተው ተቀመጡ ። ደጃች ካሣ ይህን ነገር ሰምተው ተናደዱ ።

ደጃች ካሣ ወደሸዋ ለመዝመት ሲያስቡ ደብረታቦር ላይ እንዳሉ አቶ ሺናሽ አብጠው የሚባል አሽከራቸው "እምባ ቢጠበው ሰንሰለት ቢያንሰው፣

እንድ አድርጐ አጓዘው የጐጃምን ሰው ።
ብሩን ጨው አድርገህ ከመነዘርከው፣

ውቤን ጫማ አድርገህ ሸዋን ከፈተው” ብሎ አቅራራ ። ደጃች ካሣም በቅድሚያ ደጃች ውቤን በ1845 ዓ.ም. ወግተው ደጃች ውቤን ማረኩ ። ከዚህ በኋላ ደጃች ካሣ ስማቸውን አጤ ቴዎድሮስ ብለው ነገሡ ። አጤ ቴዎድሮስ ይንገሡ እንጂ የመጀመሪያው ጠላታቸው ራስ አሊ በሸዋው ንጉሥ በኃይለ መለኮት እየተደገፉ ስላልተያዙ ሸዋም አልገብርም ስላለ በነገሡ ባመቱ በ1846 ዓ. ም. በጥቅምት ወር ትግራይንና ወሎን አስገብረው ሸዋ ገቡ ።

አጤ ቴዎድሮስ ሸዋ ገብተው ግሼ ሲደርሱ የግሼው ሹም አቶ ሀብተማርያም ተዋግተዋቸው ሀብተ ማርያም ድል ሆኑ ። መንዝ ሲደርሱ የግድምና የይፍራታ ሰው ሁሉ ስለፈራ ሳይዋጋ ለቴዎድሮስ ገበረ ።ጉር ሥላሴ ሲደርሱ ግን ሕዝቡ ተዋግቶ ብዙ ሰው ጨረሰባቸው ።ይህ ከሆነ በኋላ የምኒልክ አባት ኃይለመለኮት ከከተማቸው ከአንኮበር ወጥተው ቶራ መስክ ላይ ጦራቸውን አዘጋጅተው ቴዎድሮስን ይጠብቁ ጀመር ። አጤ ቴዎድሮስም ደብረ ብርሃን ሲደርሱ አቶ በዛብህ የተባሉ የሸዋ ሰው ብዙ ሰው ጨረሱ ። ቴዎድሮስና ኃይለ መለኮት ከመጋጠማቸው በፊት ኃይለ መለኮት ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ጥቅምት 30 ቀን 1848 ዓ.ም. አርብ ሌሊት ሞቱ ። አንዳንድ ሰዎች “ኃይለ መለኮት የሞቱት ከአጤ ቴዎድሮስ የተላከ መልክተኛ መርዝ አብልቷቸው ነው” ይላሉ ። በአንኮበር የነበሩ የውጭ አገር ሰዎች እንደፃፉት ግን ኃይለመለኮት የሞቱት በንዳድ በሽታ ነው ።

የሸዋ ሰዎች መሪያቸውን ኃይለ መለኮትን ቀብረው የዐሥራ አንድ ዓመት ልጅ የሆኑትን ምኒልክን ይዘው ሸሹ ። ይህን የሰሙት ቴዎድሮስም ከደብረ በግዕ ተነስተው ጠራ ገቡ ። ጠራን ካስደበደቡ በኋላ ምኒልክን እያባረሩ ወደ መገዘዝ እንደደረሱም ራስ እንግዳ የሚያዙትን ጦር ወደ በረከት ሰደው ቴዎድሮስ ወደ ምንጃር ተሻገሩ ። ሕፃኑን ምኒልክን ይዘው ይሸሹ የነበሩት የሸዋ ሰዎች ከአረርቲ ቆላ ቆላውን ሄደው ከስምን ተሻግረው በረከት ብቅ ሲሉ ከራስ እንግዳ ጦር ጋር ተጋጠሙ ።በዚያም ቦታ ጦርነት ተደርጐ ከሁለቱም በኩል ብዙ ሰው አለቀ ።

በዚያን ጊዜም ከምኒልክ ጋር የነበሩት በድሮው በዘመኑ ማዕረጋቸው አቶ እንዳርጋቸው ከነልጆቻቸው ፣ አቶ ሸሸጉ ፣ አቶ በሀብቴ ፣ ልጅ አባየሬ ፣ አቶ በዛብህ ፣ አቶ አባውርጂ ፣ አቶ አቦዬ ፣ አቶ እንትን ይስጠኝ ፣ አቶ ወልደ ገብርኤል ፣ አቶ ገርማሜ ፣ አቶ ወልደ ጣዲቅ ፣ አቶ ናደው ፣ አቶ አባይነህ እና ሌሎችም ብዙ ነበሩ ። በዚያን ጊዜም በመኳንንቱ እንዲህ ተብሎ ተገጠመባቸው ።

ቁርጡን አወቁና አለመኖርህን ፣
በረከት አገቡት ጌታዬ ልጅህን ።

ከጦርነቱም በኋላ ምኒልክ ወደ ምንጃር ተመለሱ ። ምኒልክን ይዘው የሚሸሹት ሰዎች የአጤ ቴዎድሮስን ሠራዊት ብዛት ፣ የጦርነቱንም ብርታት አይተው ነበረና ምንጃር ሆነው ሲማከሩ ግማሾቹ ምኒልክን ይዘን ወደ ጋላ አገር እንሽሽ ብለው መከሩ ። ሌላው መካሪ ደግሞ ሕፃኑን አገር ላገር ከማንከራተትና አጤ ቴዎድሮስም ተከታትለው ከሚወስዱብን በፈቃዳችን ብንሰጣቸው ይሻላል ብለው መከሩ ። የጉባኤው ሀሳብ በሁለት በመከፈሉ ምንም ሕፃን ቢሆኑ የምኒልክን ሐሳብ እንጠይቅ ብለው "ወደ ጋላ አገር ከመሄድና ወደ አጤ ቴዎድሮስ ከመግባት ማናቸውን ይመርጣሉ" ብለው ቢጠይቋቸው ወደ ጋላ አገር ይዛችሁኝ ብትሸሹ ይሻለኛል ብለው ተናገሩ ።

ይህ በሚሆንበት ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ አንኮበር ላይ ሆነው አባት ያለህ ያባትህን እሰጥሃለሁና አባትህን መርቅ ። አባት የሌለህ ግን አባትህ እኔ ነኝና ደጅ ጥናኝ የሚል አዋጅ ስለ አናገሩ ብዙ የሸዋ ሰዎች ያባታቸውን አገርና ሹመት እናገኛለን በማለት ለአጤ ቴዎድሮስ መግባታቸው ተሰማ ። አቶ አንዳርጋቸውም ወደ ምኒልክ ቀርበው "ይህን የመሰለ አዋጅ ተነገረ ። ንጉሡ ቃል ኪዳናቸውን የማያፈርሱ ቆራቢ ናቸው ። አቡነ ሰላማም ደግ ጳጳስ ናቸው ይባላልና የአባትህን አልጋ አይነጥቁህም" በማለት ለምኒልክ አስረድተውና አባብለው ወደ አጤ ቴዎድሮስ ይዘዋቸው ገቡ ።

አጤ ቴዎድሮስም ምኒልክን በደስታ ተቀበሏቸው ። ነገር ግን ለቴዎድሮስ ያልገቡና በየዱሩ የተበታተኑ የሸዋ መኳንንት ስለነበሩ መጥተው ይወስዱብኛል በማለት ስለፈሩ ምኒልክንና አብረዋቸው የገቡትን በሰንሰለት አሠሩዋቸው ።

ምኒልክ በሰንሰለት በታሠሩበት ጊዜ እንቅልፍ ተኝተው አልሰሙም ነበርና ከእንቅልፋቸው ሲነቁ በሰንሰለት መታሰራቸውን አዩና አለቀሱ ። በማግስቱ አጤ ቴዎድሮስ ወደ ቤተክርስቲያን ሲያልፉ ያ ልጅ እንዴት አድሯል ? ብለው ጠየቁ ።ጠባቂዎቹም ሲነቃ ሰንሰለቱን ባየ ጊዜ አለቀሰ ብለው ነገሩዋቸው ። አጤ ቴዎድሮስም አዝነው ሰንሰለቱን ቶሎ አውጡለት ብለው አዘዙ ። ከዚያን ዕለት በቀር አልታሰሩም ይባላል ።

አጤ ቴዎድሮስ የሸዋን ግዛት ለሣህለ ሥላሴ ልጅ ለመርድ አዝማች ኃይለ ሚካኤል ሰጡአቸው ። አበጋዝነቱን ደግሞ ለአቶ አንዳርጋቸው ሰጥተው ሌላዎቹን ይዘው በሰላሌና በጃርሶ አድርገው ደብረ ታቦር ገቡ ። የምኒልክ እናት ወይዘሮ እጅጋየሁ ከልጃቸው ጋር ተማርከው ሲሄዱ የአባታቸው የኃይለመለኮት ሚስት ወይዘሮ ትደንቂያለሽ ግን ከባሌ ከኃይለመለኮት ወዲያ አለም በቃኝ ብለው ኢየሩሳ

ሌም ሄደው ከዚያው ሞቱ ። ምኒልክም በ1849 ዓ.ም. በጥር ወር መቅደላ ገቡ ።

ምኒልክ በአጤ ቴዎድሮስ ተማርከው ከተወሰዱ በኋላ እንደ እስረኛ ሳይሆን እንደ ልጃቸው አንከባክበው ያዙዋቸው ። የደጃዝማ ችነትም ማዕረግ ሾሙአቸው ። ጥቂት ቆይተው ልጃቸውን ወይዘሮ አልጣሽን በ1856 ዓ.ም. በጥር ወር በሚስትንት ዳሩላቸው ። አጤ ቴዎድሮስ ምኒልክን እንዴት እንከባከበው ይዘዋቸው እንደነበረ ካን ዳንድ ታሪክ ፀሐፊዎች ብጠቅስ እንዲህ ይላሉ ።

ጉሌልሞ ማሳያ "....ምኒልክ ከአጤ ቴዎድሮስ ልጅ ከመሸሻ ጋር አደጉ ። ቴዎድሮስ ምኒልክን እንደ ልጃቸው ያዩዋቸው ነበር ።.... ምኒልክም ሲያጫውቱኝ.... አጤ ቴዎድሮስ ፣ አባቴ ከሞቱ በኋላ ወደ ቤተ መንግሥታቸው ወሰዱኝ ። ልክ እንደ ልጃቸው አድርገው ይወ ዱኝ ነበር ። በታላቅ ጥንቃቄም አስተምረውኛል ። ከልጃቸው ሳይለዩ አሳድገውኛል ብለዋል...." ሲሉ ጽፈዋል ።

አለቃ ወልደ ማርያም ደግሞ "....ከሸዋ ከወጡ ዠምሮ ለአጤ ቴዎድሮስ እንደ ልጅ ሆነው መኳንንትም ሠራዊትም ሁሉ እጅ እየ ነሱ ያከብሯቸው ይወዷቸው ነበር ። በዘመናቸውም ሁሉ ከንጉሡ ልጅ ከመሸሻ ሳይለዩ በራስ ውቤ ጠባቂንት መቅደላ ብዙ ጊዜ ተቀ መጡ ።....ንጉሡም ሴት ልጃቸውን ሰጡ ።...." ብለዋል ።

አለቃ ገብረ ሥላሴም "....ምኒልክ ከአጼ ቴዎድሮስ ሠፈር ይኖር ነበር ።የሸዋ ሰው እኩሌታው መኳንንቱም ሠራዊቱም ከምኒ ልክ ፣ እኩሌታው ካቶ ዳርጌ ጋር እየሆን ካጤ ቴዎድሮስ ሠፈር ይኖር ነበር ።....ምኒልክንም....ደጃዝማች አሰኝተው ጭፍራ ሰጥተው በታ ላቅ ክብር አኖሩት ።....ምኒልክ አጤ ቴዎድሮስ ሠፈር እግዚአብሔር ሳይለየው ፣ ከጌትነት ሳይዋረድ ፣ መከራ ሳያገኘው ከአጤ ቴዎድሮስ መአት በኃይለ መንፈስ ቅዱስ ተጠብቆ አሥር ዓመት ኖረ ።.... በማለት ጽፈዋል ።

እንደተባለው ሁሉ ምኒልክ ቴዎድሮስን ይወዱ ነበር ። በኋለኛው ጊዜ የአጤ ቴዎድሮስን ሞት ሲሰሙ በጣም ማዘናቸውንና የመን ግሥት ሐዘን እንዲሆን ማወጃቸውንም ማሳያ ጽፏል ። ማሳያ ሲጽፍ "....የቴዎድሮስን ሞት በሰሙ ጊዜ ምኒልክ በጣም አዘኑ ። የመንግሥታቸው ሀዘን መሆኑንም በአዋጅ አስታወቁ ። በአዋጃቸ ውም ቴዎድሮስ ዳግማዊ አባቴ ስለሆኑ አዝኛለሁና እዘኑልኝ ብለው አወጁ ። እኔም ለምን እንዲህ ያውጃሉ ። በተከራካሪያ በቴዎድሮስ ሞት ምክንያት ተገላግለዋልና ታላቅ የደስታ በዓል ማድረግ ነበረብ

ዎት ብላቸው .... ሰውን ለማስደሰት እንዳልከው ባደርግ ጥሩ ነው ። ሕዝቡ እንዲደሰትም ካወጅሁ እኔ ወደ ዱር ሄጄ ብቻዬን አለቅሳለሁ ። አለጊዜአቸው የሞቱ ሰው ናቸው ። .... አስተማሪዬን አጣሁ ። ቴዎድሮስ እኔን በመልካም አስተዳደግ አሳድገውኛል ። ይሄ ልቤን ነክቶታል ። ....እንግሊዞች እንድረዳቸው ጠይቀውኝ ሳልረዳቸው ግዛቴን ሸዋን እየጠበቅሁ የቆየሁትም ለዚሁ ነው አሉኝ. . . .” ብሏል ።

ንጉሥ ኃይለ መለኮት





የዳግማዊ ምኒልክ አያት ወይዘሮ በዛብሽ ከፈረንሣይ ተጓዥ ብሮሼ በ1843 ዓ.ም. ሃተስ ጣቸውን ጃንጥላ ይዘው

# ከመቅደላ ማምለጥ

ምኒልክ ከመቅደላ የወጡበትን ዘመን አንዳንዶች 1858 ዓ. ም. ሲያደርጉት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ግን 1857 ዓ. ም. ነው ይላሉ ።

ሰኔ 24 ቀን መቅደላ ላይ ከባድ ዝናብ ጥሎ ነበር ። የመቅደላን በር የሚጠብቁ ዘበኞች ከዝናቡ ለመሸሽ ወደየጐጆአቸው ገቡ ። ዘቦቹ በየጐጆአቸው ውስጥ ተጠልለው ሳለ አንድ አንበሳ ከዱር ውስጥ መጣባቸው ። ወታደሮቹም አንበሳውን አይተው ሲጯጯሁና ሲተራመሱ አንበሳው ወደዱር ሄደ ። ወታደሮቹም በፈረስ እየሆኑ አንበሳውን ተከትለው ሄዱ ። ወታደሮቹ አንበሳውን ተከታትለው ፈልገው አጥተው ወደ ሠፈራቸው ሲመለሱ ቆቂት በር ክፍት ሆኖ አገኙት ።

በዚያ አንበሳ ግርግር መሀል ቆቂት በርን ማን እንደከፈተው አልታወቀም ። ቆቂት በር የተከፈተው ምኒልክ ከሃያ ተከታዮቻቸው ጋር ሲያመልጡ ነበር ። ምኒልክን ያስመለጡ የሸዋ ሰዎች ባቀዱት ፕላን መሠረት አብዛኛው ምኒልክን ይዞ ሲሄድ፣ ጥቂት ሰዎች ወደ ሌላ አቅጣጫ ተልከው በዚያም ምኒልክ ባልሄዱበት በሌላ አቅጣጫ በኩል ብዙ ጥይት ተኩሰው ተመልሰው ከምኒልክ ጋር ተገናኝተው ጉዞአቸውን ቀጠሉ ።

የዚያን ተኩስ ድምፅ የሰሙት አጤ ቴዎድሮስም "የምን ተኩስ ነው?" ብለው ቢጠይቁ "አንበሳ መጥቶ ስለነበረ አንበሳውን ለማ ባረር ብዙ ወታደር ወጥቷል ። እነኛ የወጡ ወታደሮች አንበሳውን አግኝተው የሚተኩሱት ነው" አሏቸው ። በማግሥቱ ምኒልክ ከመቅ ደላ ተራራ ላይ አልተገኙም ። ከተራራው ላይ ያልተገኙት ምኒልክ ብቻ ማይሆኑ እናታቸው ወይዘሮ እጅጋየሁና ሌሎችም የሸዋ እስረ ኞች ሁሉ ናቸው ። በዚህ ጊዜ የምኒልክ ዕድሜ 21 ዓመት ነበር ።

የምኒልክና የሌሎቹ እስረኞች መጥፋት እንደተረጋገጠ የሌሊቱ ተረኛ ዘብ የነበሩት ወታደሮች ቀኝ እጃቸውና ግራ እግራቸው በቴ ዎድሮስ ትእዛዝ እየተቆረጠ ተጣለ ። ወዲያውንም ፈረሰኛ ወታደር ታዞ ምኒልክን ከነሕይወቱ ወይም ሬሣውን እንዲያመጣ ተላከ ። የተላከው ወታደርም ለሊት የተኩስ ድምፅ በተሰማበት በኩል ፍለጋውን ቀጠለ ። ምኒልክ ግን ሊገኙ አልቻሉም ። እስተርን እ. ኤ. አ.

ሐምሌ 9 ቀን 1865 ዓ.ም. ለራሳም በየፈው ደብዳቤ ላይ ምኒልክ ከመቅደላ ያመለጡ እለት ከሰዓት በኋላ ወሎ ግዛት ገቡ ይላል ።

ምኒልክ ከአባታቸው ወዳጅ ከወሎዋ ገዥ ከወይዘሮ ወርቂት ግዛት መስቀላ ከሚባለው ተራራ መድረሳቸው ተሰማ ። ቴዎድሮስም በመቅደላ ያለውን እስረኛ ሁሉ አስወጥተው ምኒልክን በተቀበለ ችው በወርቂት ተናደው ነበርና ከእስረኞቹ መሀል "የወርቂት ልጅ የቱ ነው ?" ብለው ጠየቁ ። የወርቂት ልጅም የአጤ ቴዎድሮስ የክ ርስትና ልጅ ነበርና ሊምሩት ነው ብለው አቀረቡት ። ቴዎድሮስም ከዚሁ ልጅ ከአመዴ አሊ ሊበን ጋር አብረው የታሠሩ የወሎ መኳ ንንቶችን ፋሪስ ቃሲምንና አሊ ወዳጄን ፣ በጠቅላላው 24 የወሎ መኳንንት እጅና እግራቸውን በጐራዴ እያስቀረጡ ከገደል ጣሉዋ ቸው ። በዚያን ዕለት አጤ ቴዎድሮስ በጠቅላላው ገደል እያስጣሉ ያስገደሉዋቸው 41 ሰዎች ናቸው ።

ምኒልክ ከወይዘሮ ወርቂት ዘንድ እንደደረሱ በሰላም አልተቀ በለቻቸውም ። ከመቅደላ ያመለጡትን የምኒልክን ሰዎች በሙሉ በእ ስር ስም ያዘቻቸው ። የመቅደላዎቹ እስረኞች የወሎ እስረኞች ከሆኑ በኋላ ወይዘሮ ወርቂት "ምኒልክን እጁን ይገፔ ልስጥ ፣ ልጄን ይፍቱልኝ" ብላ ወደ አጤ ቴዎድሮስ የሐይቅን መነኮሳት አማላጅ ላከች ። እነዚያ መነኮሳት መቅደላ ሳይገቡ አሊ በር ሲደርሱ አጤ ቴዎድሮስ ተበሳጭተው ልጇዋን አስደብድበው ገደል ሰደዱት ፣ ሞተ ፣ የሚሉ ወሬ ስለሰሙ ተመልሰው ለወርቂት ነገሩዋት ። ወይዘሮ ወርቂትም የልጅዋን መገደል በሰማች ጊዜ "ይህ ሰው እግዚአብ ሔር ያልተለየው ነው ፣ ገንዘቡንም መልሱ ። እርሱንም በክብር እም ጡልኝ" ብላ ምኒልክ ወደታሰሩበት ወደ መስቀላ ላከች ። ምኒልክም ከመስቀላ ተነስተው ቦሩ ሜዳ በደረሱ ጊዜ በክብር ተቀብላ "የሸዋ ሰው አውራህ መጥቷልና ደስ ይበልህ ፣ ተቀበል" ብላ አዋጅ አስ ነግራ በደጃች ብርዬ የሚመራ አጃቢ አድርጋ መለከትና እምቢልታ ጨምራ ወደ ግዜ ድምበር ወደ አሊቡኮ ላከቻቸው ።

ግሪን ፊልድ እንደፃፈው "እንደሌላዎቹ ሸዋዎች ሁሉ ምኒልክ የጋላ ደም ስላለባቸው ወይዘሮ ወርቂት ይህን በእርግጥ ታውቅ ስለነበር ወደሸዋ እንዲገቡ አደረገች. . . . " ይላል ።

ምኒልክ በሰላም ከሸዋ ድንበር ቢደርሱም ሸዋ ለመግባት ግን አልተመቻቸውም ነበር ። የሸዋ ንጉሥ ነኝ ይሉ የነበሩት አቶ በዛ ብህ የሸዋን ሠራዊት ሰብስበው "ምኒልክ ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ውል አለው ። ውሉም እኛን አሳልፎ ለቴዎድሮስ ለመስጠት ነው ። ከቴዎድሮስ እጅ ከገባንም ይቀጡናል ይቆርጡናል" በማለት

አዋጅ አስነግሮ ሠራዊቱ ለጦርነት እንዲዘጋጁ አደረገ ። ከዚህ በፊትም አቶ በዛብህ ለወይዘሮ ወርቂት "....ምኒልክን እሠሪ ልኝ ብሎ ሁለት ሺ ብር ፤ ፈረስና በቅሎ ሰዶላት ነበር።...." ሲሉ አለቃ ገብረ ሥላሴ ጽፈዋል ።

ምኒልክ ሸዋ እንደደረሱ የግሼው ሹም ደጃች ወልዴና ያንጦኪያው ሹም ከሲል ነሚ ገቡላቸው ። የአቶ በዛብህ በር ጠባቂዎች እነ አቶ ሀብተየስ ሳይዋጉ በሩን ለቀው ወደ ይፍራታ ሸሹ ። በዚህ ጊዜ የምኒልክ ሠራዊት እየበዛ ሄደ ። ወይዘሮ ወርቂትም ሸኙ ብላ የሰደደቻቸው ሰዎች ለምኒልክ ሎሌ ሆነው አብረው ተጓዙ ።

ዳየር በሚባል ቦታ የአጤ ቴዎድሮስ አምባ ነበርና ምኒልክ ለአምባው ጠባቂ ግባ ብለው ቢልኩበት የቴዎድሮስን የጦር መሣሪያ ይዞ ለምኒልክ ገባ ። የይፍራታ ገዥ የነበሩት አቶ ሀብተየስ ለጦርነት መዘጋጀታቸው ሲሰማ ምኒልክ ጉላስ የሚባል የወታደር አለቃ ሀብተየስን እንዲዋጋ አዘው ጉላስ ድል አደረገ ። ጉላስም አቶ ሀብተየስን ይዞ ብዙ ጠመንጃ ፈረስና በቅሎ ማርኮ ለምኒልክ ግዳይ ጣለ ። ምኒልክ አንጾኪያና ኢፍራታን አሳምነው ግድም ሲደርሱ ሕዝቡ በደስታ ተቀበላቸው ።

የምኒልክን ወደ መሀል ሸዋ መግፋት የሰሙት አቶ በዛብህ ከምኒልክ ጋር ጦር ለመግጠም ጋዲሎ ከተባለው ቦታ ተሰለፉ ። በዚህ ጊዜም አንዲት ሴት

"ማነው ብላችሁ ነው ጋሻው መወልወሉ ፤
ማነው ብላችሁ ነው ጦራችሁ መሾሉ
ማነው ብላችሁ ነው ካራችሁ መሳሉ ፤
የጌታችሁ ልጅ ነው እረ በስማም በሉ" ብላ ገጠመች ።

ጦርነቱም በ1857 ዓ. ም. ነሐሴ 16 ቀን ሰኞ ዕለት ተጀመረ ። በጦርነቱም ምኒልክ ድል አድርገው አንድ ሺ ጠመንጃና አንድ መድፍ ሲማርኩ አቶ በዛብህ ግን አምልጠው ወደ አፍቀራ ሸሹ ።

ምኒልክ በአጤ ቴዎድሮስ ተማርከው ከመወሰዳቸው በፊት አቶ በዛብህ ብዙ ጀብዱ የሠሩ ሰው ነበሩ ። አጤ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ በመጡ ጊዜ "የጌታዬ ኃይለ መለኮት ልጅ ነፍሴ እያለች አይማረኩም...." ብለው ምኒልክን ይዘው ወደ በረከት ከሔዱት መኳንንት አንዱ ናቸው ። በረከት ከተባለው ሥፍራ ከቴዎድሮስ ሠራዊት ጋር በጀግንነት ተዋግተው በመጨረሻም ቆስለው በቴዎድሮስ ሠራዊት የተማረኩ ናቸው ።

ከአሥር ዓመታት በፊት ይህን ያደረጉ ሰው ከአሥር ዓመት በኋላ ደግሞ ጠላት ሆነው ምኒልክን አላስገባም ብለው ጋዲሎ ላይ መዋጋታቸውን ያየች ሴት ፤—

"የበረከት ለታ ከሸንጡ ተወግቶ ፣
ከሻንቅላ ጋራ አብሮ ተቆራኝቶ ፣
አገር ለምኒልክ እያለ ቆይቶ ፣
ሊወጋቸው ሔደ የሰው ነገር ሰምቶ ።
አንተም አደረግኸኝ የመነኩሴ ፈፉጅ ፣
የሙት ልጅ ሲቀበል እንዲህ ነወይ ወዳጅ" ብላ ገጠመች ።

ይህንን የጋዲሎን ከፍተኛ ድል የቀመሱት ምኒልክ ከብረት አምባ ከተባለው ሥፍራ የተከማቸ ሌላ አንድ ሺህ ጠመንጃና ሶስት መድፎች ስላገኙ የጦር ኃይላቸው እየተጠናከረ ሔደ ። በብዙ አጀብም ከአባታቸው ከተማ አንኮበር ገቡ ።

ምኒልክ አንኮበርን ትተው ከተማቸውን ልቼ ካደረጉ በኋላ እፍቀራ ምሽግ ገብተው የነበሩት አቶ በዛብህ የምኒልክን ሠራዊት መበርከት አይተውና አቅማቸውን ገምተው "ይማሩኝና ልግባ" ብለው ወደ ምኒልክ ላኩ ። ይህንን መልክት አቶ በዛብህ ወደ ምኒልክ ሲልኩ ከአቶ በዛብህ ጋር እፍቀራ ያለ አንድ ሰው ደግሞ በጕን "ይማሩኝ ማለቱ በከተማዎ ሆኖ ሠራዊትዎን እያባበለና እያሴረ የረጋውን አልጋዎን ሊያፈርስ ነው እንጂ ለእርቅ ብሎ አይደለምና እንዳይዘነጉለት ይሁን" ብሎ ለምኒልክ ላከባቸው ።

ከምኒልክ ዘንድ ያሉ መኳንንቶችም "ውሸቱን ነውና አይማሩት ። አልጋዎን ከማናወጥ አያርፍም" ብለው ቢያማክሩዋቸው "ከሆነም ወደፊት እየዋለሁና ምሬዋለሁ ፣ ይግባ"አሉ ። አቶ በዛብህም ነገር ማውጠንጠናቸውን ጀመሩ ።ውስጥ ውስጡን ሠራዊትና መኳንንቱን እያስማሉና እያስገዘቱ በምኒልክ ግልበጣ ላይ ያሴሩ ጀመር ።

ይህ የአቶ በዛብህ ሴራ ወሬው ተሰማ ። ምኒልክም አንዱን አሽከራቸውን ጠርተው "በአቶ በዛብህ ወዳጅ ባንዱ ስም የእከሌ አሽከር ነኝ ብለህ ሰልለኸው ተመለስ ...." ብለው ላኩት ። ያም አሽከር ከአቶ በዛብህ ዘንድ ሔዶ የወዳጅዎ የእከሌ አሽከር ነኝ ብሎ ነገራቸው ። አቶ በዛብህም እውነት መስሏቸው "....ቢሆንልኝ አልጋዬን አገኛለሁ ። ባይሆንልኝ ደግሞ ከጋላ አገር እገባለሁ ...." ብለው ለአሽከሩ ነገሩት ። ከምኒልክ የተላከው አሽከርም ይህን መልክት ለምኒልክ ነገረ ።

አጤ ምኒልክ ሕዝቡ የሚያወራው እውነት መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ አቶ በዛብህን አስያዙዋቸው ። አቶ በዛብህ ከተያዙ በኋላ ቤታቸው ሲበረበር ከዳታቸውን የሚናገሩ ከየመኳንንቱ ጋራ የተጣጣፉዋቸው ደብዳቤዎችም ተገኙ ። ችሎት እንዲደረግም ታዞ በችሎቱ ላይ ምኒልክ በደላቸውን ለችሎቱ ነግረው ደብዳቤዎቹንም አሳይተው ፍርድ ጠየቁ ። ችሎቱም በአቶ በዛብህ ላይ የሞት ፍርድ ፈረደባቸው ። የሞት ፍርዱን እንዲያፀኑ የመጨረሻው የውሳኔ ተራ ለምኒልክ ሲደርስ "....እንደምታውቁት በድሎኛል ። እሱ የሌለውን ፤ እኔ ባለኝ ባባቴ አልጋ ልቀመጥ ብል መንግሥቴን ማናወጥ ጀመረ ። አባቴ አገር ልግባ ብል አትገባም ብሎ ተዋጋኝ ። ደጋግሞ ቢበድለኝም ፤ ንስሐ ገብቶ ፣ ተጠጥቶ ለክፉ ቀን የሚሆነኝን በዛብህን የመሰለ ጀግና አልገለውም ምሬዋለሁ ። ዳግመኛ ግን እንዳያጠፋ ይመከርልኝ ። ከእርሱም ጋር ሆነው ያሴሩብኝን ሁሉ ምሬአቸዋለሁ" ብለው ያልተጠበቀ ፍርድ ፈረዱ ።

ምኒልክ አቶ በዛብህን ከማሩዋቸው በኋላ መኳንንቱ ተሰብስቦ "አቶ በዛብህ የሚመካው አፍቀራ ባለው ምሽግና መሣሪያ ስለሆነ እንዲያስረክብ ይታዘዝ" ብሎ ወሰነ ። በዚሁ ውሳኔ መሠረት አቶ በዛብህ አፍቀራ ያለውን ምሽጋቸውንና መሣሪያቸውን ሁሉ እንዲያስረክቡ ታዘዙ ። አቶ በዛብህም ምሽጋቸውን ለማስረከብ ወደ አፍቀራ ሔደው ሲመለሱ "ምሽጉን ለማስረከብ አሽከሮቼ እምቢ አሉኝ . . . ." ብለው ለምኒልክ ነገሩ ። ይህን የሰማው መኳንንትም "እሱ ራሱ እየመከራቸው ነው እንጂ ከልብ ቢይዛቸው መች እምቢ ይላሉ ? አሁንም እጁ ተይዞ አምባው በጦር ይሰበር" ብለው ወሰኑ ። አቶ በዛብህም ተይዘው ወህኒ ገቡ ።

የአፍቀራን ምሽግ ለመደምሰስም ጦር ተላከ ። በጦርነቱም ላይ ከሁሉም ወገን ብዙ ሰው አለቀ ። ጀግናው የጦር አለቃ የነበሩት አቶ ጉላስም በዚያ ውጊያ ላይ ሞቱ ። ድሉ ግን ለምኒልክ ሆነ ። ከዚህ በኋላ ሊቃውንቱና መኳንንቱ ይፍረዱባቸው ተብሎ አቶ በዛብህ እንደገና ከችሎት ቀረቡ ። በችሎቱም ላይ ስለምኒልክ ሆኖ የቆመው ተሟጋች የአቶ በዛብህን ወንጀል ከሥር ጀምሮ ያስረዳ ጀመር ።

"መጀመሪያ አቶ በዛብህ የማይገባውን በአባቴ አልጋ ተቀምጦ ከመቅደላ አምልጬ ብመጣ አላስገባ ብሎ ጋዲሎ ላይ ተዋጋኝ። ዳግመኛም ማረኝ ብሎ ከማርሁት በኋላ በከተማዬ ተቀምጦ ያሴርብኝ ጀመር ። በዚህም ምሬው አምባውን አፍቀራን አስረክበኝ ብለው ባሽከሮቼ እያመካኘ ሳያስረክበኝ ቀረ ። አምባውንም ለማፍረስ ብዙ ሰው ሞተበት ። ይህን ሁሉ አይታችሁ ፍረዱ" የሚል ክስ አቀረበ።

በችሎቱ የተሰበሰበው መኳንንትና ሊቃውንትም አቶ በዛብህ ለተከሰሱበት ወንጀል ምላሽ ሳይሰጡ እየተነሱ መፍረድ ጀመሩ ።

በዚያን ጊዜም ቢሆን እንደነበረው ሕግ መሠረት ችሎቱ የሚ ፈርደው አንድ ተከሳሽ ለተከሰሰበት ክስ መልስ ከሰጠ በኋላ ነበር ። ለአቶ በዛብህ ግን ይህ ደንብ አልተሟላላቸውም ። አቶ በዛብህ ችሎት ከመቅረባቸው በፊት ጧት ከእስር ቤት እንዳሉ ላንድ አጠገባቸው ላለ ሰው "ዛሬ ሌሊት በሕልሜ ክፉ ሕልም አይቻለሁና ፈርቻለሁ" ብለው ቢነግሩት ሰውየው "አይዝዎ ። ምንም የለብዎም ። አይፍሩ" እያለ አጥናናቸው ። አቶ በዛብህም "እንደምን አይዞህ ትለኛለህ ። ንጉሡ በውነት ምሬሃለሁ እንዳይሉ ልጅ ናቸውና የልባቸውን የሚ ያሠራቸው የለም ። ባጠገባቸውም ያሉት መኳንንቶች ብንለቀው ምን ያደርገናል የማይሉ ፈሪዎች ናቸው ። ስለዚህ ይገድሉኛል እንጂ ምንም አልተርፍም" ብለውት ነበር ። ስለዚህ ይሆን አቶ በዛብህ ለቀ ረበባቸው ክስ መልስ ሳይሰጡ መኳንንቱ ፍርድ የጀመረው ?

በችሎቱ ላይ የተሰበሰበው ሊቃውንትና መኳንንት ሁሉ እየተ ነሳ በአቶ በዛብህ ላይ የሞት ፍርድ ፈረደባቸው ። ከፈራጆችም መሀል አቶ ሠራዊቱ የሚባሉ ተነስተው በእግራቸው መሬቱን እየደበደቡ "....አንተ ያልሞትህ ማን ይሞት ኖርዋል ? ትሞታለህ" ብለው ተቀ መጡ ። አቶ ሠራዊቱ በጦርነት ላይ ፈሪ ናቸው እየተባለ የሚወ ራውን አቶ በዛብህ ያውቁ ነበርና ለአቶ ሠራዊቱ አነጋገር አቶ በዛ ብህ ሲመልሱ "እኔ ስሞት የአማራ ፣ የጋላ ፣ የእስላም ጀግኖች ተጨ ምረው ፈርደው እሞታለሁ እንጂ እንዳንተ ያለው ፈሪ ብቻ ፈርዶ እሞታለሁን ። አንተ የመግደያው ጦር ማመሙንና አለማመሙን ወዴት ታውቀዋለህ ?...." እያሉ አሳቁባቸው ። ሌላውም አነጋገር በችሎቱ የተሰበሰበው ፈራጅ ሁሉ ፈሪ ብቻ ነው ማለታቸው ነው ።

ከፈራጆቹ አንደኛው ግራዝማች ባዩ የሚባሉ ተነስተው ሲፈ ርዱ"....አቶ በዛብህ እንደኔ አድርጐ ያጠቃውና ያዋረደው ሰው የለም ። በአቶ በዛብህ ላይ ክፉ ቂም አለኝ ። ቢሆንም በዛብህን የመ ሰለ ጀግና ለክፉ ቀን የሚሆን ነውና ይሙት ብዬ በሱ ላይ አልፈር ድበትም" ብለው ተቀመጡ ። በመጨረሻው የሞቱ ፍርድ ጠናባቸው ። በጠመንጃ ጥይት እንዲገደሉም ተፈረዶባቸው ሲገደሉ ልብሳቸው በእሳት ተያይዞ ሬሳቸውም ተቃጠለ ።

አንዳንድ ሰዎች አቶ በዛብህ የተገደሉት ጧፍ የተነከረ ቀሚስ አልብሰዋቸው ስለሆነ ልብሳቸው በእሳት ተያያዘ ይላሉ ። ይሄ የማ ይመስል ነገር ነው ። አንድ ሙሉ ቀሚስ በጧፍ ከመንከር ይልቅ በእሳት ተቃጥሎ ይገደል ቢባል ይቻል የለ ? ብላቴን ጌታ ኅሩይ

ግን“ . . . . በዚያ ዘመን የነበረው ጠመንጃ በባሩድና በጨርቅ እየተደቀ ደቀ በካምሱር የሚተኮስ ነበርና ከባሩዱ ኃይልና ብዛት የተነሳ የለበ ሰው ልብስ ተያይዞ ስለነደደ ሥጋውና አጥንቱ ተቃጠለ . . . . ” ይላሉ ። የአቶ በዛብህ ወገኖችም የተረፈውን ለቃቅመው ደብረ ብርሃን ወስ ደው ቀበሩዋቸው ።

አልቃሽ “አንተም ጨካኝ ነበርክ ጨካኝ አዘዘብህ ፣
እንደገና ዳቦ እሳት ነደደብህ ።
ጋላም አርፈህ ተኛ እውልቀህ ጀባህን ፣
አማራውም ተንፍስ እራግፍ ኮርቻህን ፣
በእሳት አቃጠሉት የሚያባንንህን” ብላ ገጠመችላቸው ።

ምኒልክም በ1858 ዓ. ም. ነሐሴ 24 ቀን በአጤ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት “ምኒልክ ንጉሠ ሸዋ” ተብለው ነገሡ ።



# የግዛት መስፋፋት

ምኒልክ የተወለዱት ደብረ ብርሃን አቅራቢያ በሚገኘው አንጐለላ ውስጥ ነው ። ያደጉትም ከሸዋ ኦሮሞ ልጆች ጋር እየተጫወቱ ነው ። ከመቅደላ አምልጠው ሸዋ ሲገቡም ለመጀመሪያ ጊዜ ያረፉት ከቢሸፍቱ ደቡብ ባለው ከአዳው ኦሮሞ ከቡታ ቤተሰቦች ዘንድ ነው ። በሸዋም ላይ ሲነግሱ የረዱዋቸውና ሸዋን ያስተባበሩላቸው አብሮ አደግ ጓደኞቻቸው ኦሮሞው ጐበና ዳጨ ናቸው ። ጐበና የቱለማ ኦሮሞ መሪ የዳጨ ልጅ ናቸው ። ጐበናም የምኒልክን ግዛት ያዘጋጁና ያመቻቹ ታላቅ ሰው ናቸው ።

ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው ሸዋ በገቡ ጊዜ ሸዋ የሚባለው፥ አንኮበርን ጨምሮ መንዝና አካባቢው ነበር ። ምኒልክ በእነዚህ ቦታዎች ላይ ያሉትን ባላባቶች አስገብረው ራሳቸውን ንጉሥ ሸዋ ካሉ በኋላ "የአባቴን ግዛት መልሼ መያዝ አለብኝ" ይሉ ጀመር ። የምኒልክ አያት የሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ሲሞቱ ወዲያውኑ የሸዋ ግዛት በየባላባቱ ተከፋፍሎ እያንዳንዱ ለማንም የማይገብር ራሱን የቻለ መንግሥት ቢጤ ሆኖ ነበር ።

ምኒልክ የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑትን አቶ ጐበናንና ሌሎቹንም ረዳቶቻቸውን አማክረው የሸዋን ግዛት ለማስፋፋት ተስማሙ ። የዚያን ጊዜ የሸዋን ግዛት ለማስፋፋት ወይም እንደነበር ለማድረግ የተነሱበት አንዱ ምክንያት ኢትዮጵያን ዙርያዋን የከበቡ ቅኝ ገዢዎች ለእያንዳንዱ ባላባቶች ስጦታ በመስጠትና በማባበል የኢትዮጵያን ግዛት እየቀረሱ ወደራሳቸው ቅኝ ግዛትነት ይደባልቁ ስለነበር እነኚያን ቅኝ ገዢዎች ለማቆም ነበር ።

ምኒልክ ከመጀመሪያው ጀምረው አብዛኛው ሥራቸው፥ ነገሮችን በሰላም መጨረስ ይወዱ ስለነበር በሸዋ አካባቢ ላሉት ለተከፋፈሉት የኦሮሞ ባላባቶች "ያሳደጋችሁኝ ልጃችሁ፥ አብረን ያደግን ባልንጀራችሁ ነኝና በአባቴ አልጋ ከተቀመጥሁ በፍቅር ተገዙልኝ" እያሉ መልክተኛ ይልኩባቸው ጀመር ። ከድሮ የልጅነት ጓደኞቻቸው አንዳንዶቹ በአሁኑ ጊዜ በሞቱት አባቶቻቸው ምትክ የባላባትነቱን ቦታ ይዘዋል ። የቅርብ ጓደኞቻቸው ከነበሩት አንዳንዶቹም ለምኒልክ ገብተው እነጐበናን የመሳሰሉት የቱለማ ባላባት ልጆች አብረው ይኖራሉ ።

የአቶ ጐበና ሚስት ደግሞ የሰላሌው የኦሮሞ ባላባት የቢሩ ነገዎ ልጅ ናቸው ። አንዳንድ ፀሐፊዎች ግን የቢሩ ነገዎ እህት እንጂ ልጅ አይደሉም ይላሉ ። ሁሉም ቢሆን የባላባት ዘር ናቸው ። ይሆን በመሳሰለው መቀራረብ ምኒልክና ጐበና እሺ ያለውን በፍቅር ፡ እምቢ ያለውን በጦር ለማስገበር ተስማሙ ። በወዳጅነት እንዲገቡ ከተላከባቸው የኦሮሞ ባላባቶች አንዳንዶቹ የምኒልክ አገዛዝ እንዴት እንደ ሆነ ጐበናን ይጠይቁ ጀመር ። ጐበናም ከምኒልክ ጋር በምክር የጨረሱትን "ግዛታችሁና ባላባትነታችሁ አይነካም ። ግን ለመሀከለኛው ለምኒልክ መንግሥት በያመቱ ግብር ትከፍላላችሁ ። የተበታተነው ኦሮሞ አንድ ሆኖ ይተዳደራል" እያሉ ይነግሩ ጀመር ።

ቹሩሊ እንደ ፃፈው ለመጀመሪያ ጊዜ የሚታው ባላባት ቢራቱ ጐሌ በምኒልክ አሳብ ተስማምቶ ገባ ። ምኒልክም ቢራቱ ጐሌን ሸልመው ግዛቱን መረቁለት ። የጉለሌው ባላባት ቱፋ ሙና አልገባም ። አልገብርምም ብሎ እምቢ አለ ። ቀደም ብለው በገቡት በአቢቹና በቢራቱ ቢመከርም እምቢ ስላለ ጦርነት ገጥሞ በጦርነት ተገደለ ። በውድ ሳይሆን በግድ የጉለሌው የባላባት መንግሥት ከቀረ በኋላ ለጉለሌ ባላባትነት የሚገባውን ከዚያው ከሕዝቡ አስመርጠው ሾሙ ። የሸዋ ኦሮሞም "እንደ ቴዎድሮስ ይቆርጣሉ ብለን ነው እንጂ ግዛታችን ከኛ የማይመጣ ከሆነ እንገባለን" እያለ ብዙው በሰላም ገባላቸው።

የሸዋ ኦሮሞን ከያዙ በኋላ የጐበናን ፈረስ አስቀድመው ይጓዙ ጀመር ። በ1866 ዓ. ም. በጥቅምት ወር መራቤቴን ፡ ጐመሮንና ቸሃን አስገበሩ ። በ1873 ዓ.ም. ጥሙጋንና አዳልን (አፋር) አዘሎ ድረስ ያለውን አገር በጦር ኃይል አስገብረው እንደ ጥንቱ የኢትዮጵያ ግዛት እንዲሆን በሸዋ ሥር አደረጉት ። ይሁም ቢሆን የፈረንሣይ ፡ የኢጣሊያ ፡ የግብጥና የእንግሊዝ መንግሥታት አፋርን ለመያዝ እርስ በራሳቸው እየተሻኰቱ ስብከታቸውን አላቆሙም ነበር ። ይህን ጉዳይ የሚያውቁት ምኒልክ ለእነኚህ ለተጠቀሱት መንግሥታት በሙሉ ለእያንዳንዳቸው "አባቶቼ ይገዙት የነበረውንና በኋላ ጊዜ የከዳውን የአዳልን ግዛት መልሼ በእጄ ስላደረግሁት ደስ ብሎኛልና እርስዎም ወዳጄ ስለሆኑ ደስ ይበሎት" እያሉ ደብዳቤ ፃፉላቸው ። ይህም ግዛቱ የኢትዮጵያ መሆኑንና ገዢውም እሳቸው መሆናቸውን ለማሳወቅ ሲሆን በሌላው በኩል እነኚህ ኤሮፓውያን የአፋርን ግዛት እንደ ተመኙት እንይዛለን ቢሉ ጦርነት የሚገጥሙት ከምኒልክ ጋር መሆኑን ለማሳወቅ ጭምር ነው ። ይህም አልቀረ በአድዋ ጦርነት ትረካ እንደገለጽኩት ከድቶ ለቅኝ ገዥዎች ሊገባ የነበረውን የአውሳን ባላባት እንደገና በጦርነት አስደበደቡት ።



ጐበና ዳጬ

## አርሲ

ደጃች ወልደ ገብርኤል አርሲን ለማቅናት ዘምተው አገሩን ቢይዙም የአርሲኡ ኦሮሞ አንገዛም እያለ በማስቸገሩ ምኒልክ በ1874 ዓ. ም. ዘምተው ነበር ። አብዛኛው የአርሲ ሕዝብ እሜን ብሎ ሲገ ብር አንዳንድ ባላባቶች አስቸግረው ነበር ። ምኒልክም በ1874 አር ሲን መትተው አስገበርኩ ብለው ተመለሱ ። የምኒልክን መመለስ ያወ ቀው የአርሲ ሕዝብ እንደገና በገዢው በደጃዝማች ወልደገብር ኤል ላይ አመፀ ።

ምኒልክ በ1878 ዓ. ም. እንደገና ወደ አርሲ ለመዝመት ግን ቦት 5 ቀን ከእንጦጦ ተነሱ ። በሶዶ ፡ በከንባታ ፡ በዙዋይ አልፈው ጭላ ሎን ፡ ሳቶን ፡ ዲጋሎን አስገብረው አልባሶ ሜዳ ሠፈሩ ። በዚህም ጊዜ ኮጂ የሚባለው የአርሲ ባላባት ለሊት ከደጃች ወልደ ገብርኤል ሠፈር ገብቶ አደጋ አደረሰ ። 700 ያህል ሰዎችም ገደለ ። ምኒልክ የሠ ፈሩት ከደጃች ወልደገብርኤል ሠፈር ራቅ ብለው ነበርና የአደጋውን መድረስ አልሰሙም ። በዚያው ለሊት አንዲት የሸሸች ሴት ከንጉሡ ሠፈር ገብታ የአደጋውን መድረስ ነገረች ። በማግሥቱም ምኒልክ ለደጃች ወልደገብርኤል ርዳታ ላኩ ። የእርዳታውን መድረስ ያላወ ቀው የአርሲ ሕዝብ እንደልማዱ ለሊት አደጋ ለመጣል ሲመጣ የም ኒልክ ሠራዊት ፈጀው ። ከዚህ በኋላ አንዳንድ ጥቃቅን ግጭቶች ከመ ደረጋቸው በስተቀር የአርሲ ሕዝብ ገበረ ። ንጉሥ ምኒልክም ለአርሲ አጐታቸውን ራስ ዳርጌን ሾሙ ።

የአርሲ ባላባቶች በገበሩበት ጊዜ የምኒልክ ሠራዊት ከአርሲ ሕዝብ ብዙ ሰው ማርኮ ነበር ። በዚያን ዘመን በየትም አገር ላይ እንደ ሚደረገው ሁሉ በጦርነት የተማረከ ለማራኪው ባርያ ይሆን ነበር ። የሸዋውም የምኒልክ ሠራዊት የማረከውን ሰው ባርያ አድርጐ ያዘ ። ይህን ያወቁት ምኒልክ በዚያው በአርሲ ውስጥ እንዳሉ ሠራዊታቸ ውን ሰብስበው አዋጅ አስነገሩ ። አዋጁም "....አሩሲን ከግራኝ ወዲህ የገዛውና ያስገበረው የለም ። እኛ ጥንትም የኛ ነው በማለት መጣን በት እንጂ እርሱ አልመጣብንም ። ባለማወቁ እከላከላለሁ ብሎ አለቀ ፡ ተጐዳም ። ግን ባርያ አድርገን ልንገዛው አይገባንም ። ወንድማችን ነውና የማረከውን የሰው ምርኮኛ ሁሉ ልቀቅልኝ ። በአዋጅ ከለመንሁህ በኋላ ወስልተህ የአሩሲን ሰው ባርያ አድርገህ የያዝህ ከተገኘህ እጣ ላሃለሁ ። ልቀቅ ብያለሁና ልቀቅ....ላምና ከብቱ ለስንቅህ ይበቃሃ ልና ሰዉን ልቀቅልኝ ።...." የሚል ነበር ። ከዚህ በኋላ የምኒልክ ወታደር የሚሸጠውም ሆነ የሚያሠራው ባርያ (ምርኮኛ) በማጣቱ ቢናደድም የያዘውን ሁሉ ለቀቀ ።

## ወለጋ

የጐጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ሠራዊታቸውን ወደ ወለጋ እየ ላኩ በግብር መልክ ሳይሆን በዝርፊያ ወለጋን አዳክመውታል ። የወ ለጋው ባላባት ሞረዳ ከንጉሥ ተክለሃይማኖት ጋር በውድም ሆነ በግድ ተወዳጅተዋል ። የእንባቦ ጦርነት በሚለው አርእስት ውስጥ እንደ ፃፍኩት የሸዋው ምኒልክና የጐጃሙ ተክለሃይማኖት በወለጋ ምክን ያት እንባቦ ላይ ተዋግተዋል ። ንጉሥ ተክለሃይማኖት የወለጋውን ባላባት ሞረዳን ሲይዙ ንጉሥ ምኒልክ ደግሞ ልጅየውን ኩምሳን በወዳጅነት ያዙ ።

ንጉሥ ምኒልክ በ1878 ዓ. ም. ጐበና ዳጨን ወደ ወለጋ ልከው ጐበና ከኩምሳ ጋር እንዲነጋገሩ አደረጉ ። ጐበናም የንጉሥ ምኒ ልክን አሳብ ለኩምሳ ሲናገሩ “. . . . በሰላምና በፍቅር ብትገቡ መሬት የናንተ ነው ። በወለጋም ከኩምሣ በላይ የሚሾም ሰው የለም ። አገሩ ንም የምታስተዳድረውና የምታስገብረው አንተው ባላባቱ ኩምሣ ነህ ። ለምኒልክ መገዛትህን የምታስታውቅበት በየዓመቱ ለምኒልክ ትገብ ራለህ. . . . ከዚህ በተረፈ በበላይነት እንጂ በውስጥ ግዛታችሁ አንገ ባም. . . .” ብለው በዚህ ከተስማሙ በኋላ ባላባቱ ኩምሳ ገቡ ። ንጉሥ ምኒልክም ኩምሣን ክርስትና አስነስተው ስማቸውን ገብረ እግዚአ ብሔር አሏቸው ። ከዚያም በኋላ የደጃዝማችነት ማዕረግ ሰጥተው የወ ለጋ ገዥ ብለው ሾሟቸው ።

በ1880 ዓ. ም. ደርቡሾች ወለጋን ወረሩ ። ምኒልክም በጐንደር በአምባ ጫራ በኩል የመጣውን የደርቡሽ ጦር ለመውጋት ሄደው በአጤ ዮሐንስ ትእዛዝ ተመልሰው እንጦጦ መግባታቸው ነበርና በወለጋ በኩል የገባውን የደርቡሽ ጦር እንዲወጉ ራስ ጐበናን አዘዙ ዋቸው ። ራስ ጐበናም ሔደው ተዋግተው ድል አድርገው ተመለሱ ። ለአጤ ምኒልክም ግዳይ ጣሉ ። ምኒልክም ፈረስ ከነወርቅ መጣብሩ ፣ ባለወርቅ ጋሻ ፣ ባለወርቅ ጫሚ ጐራዴ ፣ ማለፊያ ጠበንጃ ፣ የወርቅ ዝናር ፣ ባለወርቅ ለምድ ፣ ወርቅ ኮፊያ ፣ ግምጃ ሱሪ ፣ ግምጃ መታ ጠቂያ ፣ቀጭን ድርብ ሸለሙዋቸው ።

## ከፋ

የከፋም ታሪክ ከወለጋው ጋር የተያያዘ ነው ። ጐጃሞች ወለጋ ንም ፤ ከፋንም ያስገብሩ ነበር ። ምኒልክም ከፋና ወለጋ የሸዋ ግዛት ስለ ሆነ አትግቡብኝ እያሉ ለንጉሥ ተክለሃይማኖት ቢልኩም ንጉሥ

ተክለ ሃይማኖት በራስ ደረሶ የሚመራ ጦራቸውን ወደ ከፋ በመ ላክ ኃይላቸውን አጠናከሩ ።

በ1874 ዓ. ም. ምኒልክ ሱሉልታ ሠፍረው ታሪካዊ ቦታዎችን እያስቆፈሩ በማስወጣት ላይ እንዳሉ ጐጃሞች አባጆቢርን የጉማ ውን ገዥ ድል አድርገው ገደሉት ። አገሩንም አጠፉት የሚል መልክት መጣላቸው ። ንጉሥ ምኒልክም ይህን እንደሰሙ ራስ ጐበ ናን ጠርተው በማማሥቱ ወደ ከፋ እንዲዘምቱ አዘዙዋቸው።ጐበና ወደ ከፋ ሲዘምቱ ምኒልክ ወደ አርሲ ዘመቱ ። ምኒልክ ከአርሲ ዘመቻ ተመልሰው አዋሶ ላይ ሲደርሱ ከራስ ጐበና የተላከ “. . . . ከራስ ደረሶ ጋር ጉማ ላይ ተገናኘን ። ያስገበሩትንም ገንዘብ ሁሉ ተቀበልናቸው ። እንግዲህ አጤ ምኒልክ ከሰጧችሁ አገር እንዳታልፉ ብለን አስምለን አስገዝተን ተራርቀን ወደ አገራቸው ተመለሱ ። እኛም መጣን . . . .” የሚል ደብዳቤ ደረሳቸው ።

ጐጃሞች ከጐበና ጋር በእርቅ ከተስማሙ በኋላ በዚያው ዘመን ውላቸውንና መሀላቸውን አፍርሰው ንጉሥ ተክለሃይማኖትን ይም ጡልን ብለው ልከው ራስ ጐበናን ለመውጋት ተጓዙ ።ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ተነሡ የሚል መልክተኛ ከራስ ጐበና ተልኮ ወደ ንጉሥ ምኒልክ መጣ ። ይህም በተሰማ ጊዜ ከተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብለው ከእንጦጦ ከተማቸው ተነሱ ።

ምኒልክ አዋሽን ተሻግረው ጥቁር መሬት ሲደርሱ ከአባ ጂፋር ተልኮ የመጣ ነጋዴ ጐጃሞች ጉማንና ወለጋን ሁሉ አጠፉት ብሎ ነገራቸው ። ከዚያም በፍጥነት ተጉዘው ኖኖ ላይ ለጋ እናን በተ ባለ ቦታ ከራስ ጐበና ጋር ተገናኙ ። በዚህ ጊዜ ጐጃሞች ሱጴ ላይ ሠፍረው ነበርና ከራስ ደረሶ ሰዎች ፊታውራሪ ይመር ተልከው ወደ ንጉሥ ምኒልክ መጡ ። ንጉሥ ምኒልክም ፊታውራሪ ይመርን ድንኳ ናቸው ውስጥ ተቀብለው “. . . . ከአባይ ወዲህ ምን ግዛት አላችሁ ? እኔ በፍቅር ስለወዳጅነት አሞሩን ፥ ሆሮን ፥ ጉድሩን ፥ ግንደበረትን የቀዲዳን አገር ለንጉሥ ተክለሃይማኖት ብሰጠው እያለፋችሁ ሌላ ውን አገር ትወጉ ጀመር ። ተጠማኝ ቢሰነብት ባለርስት ይሆናል የሚ ሉት በእናንተ ደረሰ ። አሁንም የሰጠሁትን አገሬን ወስጃለሁ ። እናን ተም አባይን ተሻግራችሁ ወደጌታችሁ ሂዱ ። ጌታችሁ ግን አገሩን ከወሰዱብኝ እዋጋለሁ ብሎ የመጣ እንደሆነ ከጌታችሁ ጋር እንድት መጡ ፈቅጄላችኋለሁ” ብለው ላኩዋቸው ። ከዚህ በኋላ የእንባቦ ጦር ነት ተነስቶ ንጉሥ ምኒልክ ድል አደረጉ ። ይህንንም የእንባቦ ጦር ነት በሚለው አርእስት ሥር ጽፌዋለሁ ።

የጂማው ሡልጣን ዳግማዊ አባጂፋር ፣ ለምኒልክ እንገብራለሁ ካሉ በኋላ ዛንዚባር ካሉ አረቦች ጋር በመላላክ ወዳጅነት ፈጥረው ነበር ። አባጅፋር የአባታቸውን የጐሞልን ዙፋን የወረሱት በ1870 ዓ. ም. ነው ። በግዛቱ ውስጥ መነጋገሪያው ቋንቋ አረብኛ እንዲሆንና የአረብኛ ትምህርት እንዲሰጥ ታወጀ ነበር ። በኢትዮጵያ ያለው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የተሻለ ኑሮ ለመመሥረት ወይም ለንግድ ከሸዋ ፣ ከወሎ ፣ ከጐጃም ፣ ከጐንደር ወደ ጂማ የሚገባውን ሰው ሁሉ እያስያዙ በግድ በእስልምና ሃይማኖት እንዲገቡ ያደርጉ ጀመር ። ይህን የሰሙት ንጉሥ ምኒልክ “ . . . . አገሩን የአረብ አገር ማድረግህ እንደሆነ ቁርጡን ንገረኝና ውላችን ይፍረስ . . . .” ብለው ላኩባቸው ። አባጅፋርም መልስ ሳይሰጡ ዝም አሉ ። ምኒልክም በትግስት ጠበቁ ።

ንጉሥ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ከተባሉ በኋላ በ1882 ዓ. ም. ሕዳር 9 ቀን አባጅፋር ግብር ለመገበር ወደ ምኒልክ ዘንድ መጡ ። አጤ ምኒልክም “. . . .ካገርህ የገባውን ክርስቲያን ሁሉ ሰብስበህ አምጣ . . . .” ብለው አባጂፋርን በወህኒ አዛዥ ወልደጻዲቅ እጅ አስጠበቋቸው ። አባጂፋርም ባገራቸው ውስጥ ያለውን ክርስቲያን ሁሉ ለቀቁ ። ከዚህ በኋላ አገራቸውን መልሰው ሰጥተው ሾመው ሸልመው ሰደዱዋቸው ።

አባጂፋር በአባታቸው ሥልጣን ሥርና ራሳቸውን ችለው ከ1861 ዓ. ም. ጀምሮ እስከ 1934 ዓ. ም. ድረስ ጂማን የገዙ ባላባትናቸው ። አባጅፋር ለምኒልክ ገብረው የምኒልክ ወዳጅ ሆነዋል ። ጂማንም ቢሆን በንግድ የታወቀች አገር አድርገዋታል ። በተለይ በባርያ ንግድ አገሪቱ እውቅ በመሆንዋ ምኒልክ ይህን የባርያ ንግድ እንዲተዉ በ1902 ዓ. ም. የካቲት 8 ቀን በተፃፈ ደብዳቤ አስጠንቀቋቸው ።

ይድረስ ካባ ጅፋር

ይህንን የደንብ ወረቀት ጽፈንልሃል ።

ከጃንጀሮ ወዳንተ አገር የመጣውን ጋላ እንግዲህ ከጂ ከገባ ልኝ ብለህ ጭቡ አድርገህ ባርያዬ ነህና አንተንም ልበድልህ ፣ልጅህንም አምጣና እንደከብት ልሽጠው ፣ ልለውጠው አትበል ። ይህን ያህል ዘመን አባቶቻቸው ከአባቶችህ ፡ ልጆቹ ካንተ ጋር አብረው ኑረው ባርያ ሊባሉ አይገባም ። ባደባባይም ባርያዬ ነው እያልክ አትሟገት ። የሰው ባርያ የለውም ። ሁላችንም የእግዚአብሔር ባርያዎች ነን ። እግዚአብሔር መርጦ ፡ ከሰው አልቆ ሲያስገዛ ጊዜ በሰው መጨከን አይገባም ። ለሰው ቢያዝኑ ዕድሜ ይሰጣል ።



አባጂፋር

ከኔም ጋር በእግዚአብሔር ቸርነት ጕንደሬ ሁሉ ተሰብስቦ እዚህ ሸዋ መጥቶ ተቀምጧል ። አገሬ ልግባ ያለ እንደሆነ ባርያ ነህ ተብሎ ሊያዝ ነውን ።

ደግሞም እወደደበት እተመኘው ቦታ ላይ ይቀመጣል እንጂ ካንተ አገር ተነስቶ ወደ ጃንጀር ቢሄድ ፥ ወደሌላ ወደ ወደደው አገር ቢሄድ የኔ ዜጋ ነው ብለህ ልትይዝ አይገባም ። የጃንጀሮው ሰው ፥ የሌላም አገር ሰው አንተን ወዶ ወዳንተ አገር ቢገባ የጃንጀሮም ገዢ ፥ ሌላውም ገዢ ሁሉ የኔ ዜጋ ነው ብሎ አይያዝ ። ድሀው እወደደው እተመቸው ቦታ ይደር ።

የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፪ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ ።

ምኒልክ ይህን ደብዳቤ ለአባ ጅፋር ከመፃፋቸው ሁለት ዓመት በፊት በመላው ኢትዮጵያ የባርያ ንግድ እንዲቀር አውጀው ነበር ። አዋጁም "....የባርያ ነገር አትሸጥ ፥ አትግዛ ብዬ ከዚህ ቀደም ባዋጅ አስከልክዬ ነበር ። አንተ ግን ውስጥ ለውስጥ መሸጥክን መግ ዛትህን የማትተው ሆንክ ። ይልቁንም በዳር በዳር ያለው ሚስቱንም፥ ልጁንም ይሸጥ ዠመር ማለት ሰማሁ ። አሁንም በዳር አገርም በሌ ላም አገር ቢሆን ባርያ መሸጥና መግዛትክን ተወኝ ።

"እንግዲህ ግን ባርያ ስትሸጥ ፥ ስትገዛ የተገኘህ ሰው እስከ ዘመ ድህ እያሰርሁ ሥራ ለሚሠራ ሰው እሰጥሃለሁ ።

የካቲት ፳፱ ቀን ፲፱፻ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ።

የጕማው ባላባት አባቦቃና የእናርያው ባላባት አባ ጕምቦሌ ለምኒልክ ለመገዛት ገበሩ ። በተለይ አባ ጕምቦሌ በሰላም በገበረ ጊዜ ምኒልክ ልጁን ክርስትና እንስተው ሮሙን ገብረ ሥላሴ ብለው የፊ ታውራሪነት ማዕረግ ሮጡት ። እልገብርም ብሎ ያስቸገረው የጃንጀ ሮው ባላባት አባ ባጊቦን ራስ ወልደ ጊዮርጊስ በጦር ኃይል ለ"ገስገ በር ሲዋጉ አባባጊቦ ድል ከሆነ በኋላ አምልጦ ጕራጌ አገር ገባ ። ጕራጌዎችም "የምኒልክ ጠላት ነህና ካገራችን ውጣ" ብለው ሲያባ ርሩት ወደ አዲስ አበባ ሄዶ ይቅርታ ጠየቀ ። ምኒልክም ይቅርታ አድ ርገውለት ልጁን ክርስትና እንስተው ስሙን ገብረ መድኅን አሉት ።

ይህ ሁሉ ቢሆንም የዛሬው የከፋ ክፍለ አገር በብዙ ባላባቶች የተከፈለ ስለነበር ግማሹ በሰላም እንገብራለሁ ሲል ግማሹ ደግሞ አንገብርም እያለ አስቸግሮ ነበር ። ደጃች ደምሰው መሀሉን ተጕዘው ጌራን ፥ ጕጀብን እስከ ጊሚራ ድረስ አስገበሩ ። ደጃች ተሰማም የማቅ ናት ሥራቸውን ቀጥለው ጊሻን ፥ ቢጣንን ፥ ጨናን አስገብረው ወሰ

ናቸውን ከደጃች ደምስው የጊሚራ ወሰን ጋር አገናኙ ። ራስ ወልደ ጊዮርጊስም ብኩሎ በኩል አድርገው እስከ ቦንጋ ድረስ አስገበሩ ። የዚያን ጊዜ የከፋ ዋና ከተማ ቦንጋ ነበር ።

የጋሊቶ ግዛት የነበረው ከፋ የተመሠረተው በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው ። የከፋ ዋና ከተማ ቦንጋም የነጋዴ አገር ሲሆን ገበያዎቹ ግን በሁለት የተከፈሉ ነበሩ ። ቦንጋ ከተማው የክርስቲያ ኖች ገበያ ሲሆን ቃያ (ካያ) ደግሞ የእስላሞች ገበያ ነበር ። የከፋን ታሪክ ገብረ ሥላሴ እንዲህ ብለው ይተርኩታል ። ". . . . ከፋ የሚባለው አገር ምሽጉም ፤ ጉድባውም እጅግ የከፋ ነው ። የከፋውም ንጉሥ ቅጣ ቱም ፤ ሥራቱም የጠነከረ ነው ። ሕዝቡም ጌታውን ያፍራል ፤ ይወዳል ። ሥራቱም እንዲህ ነው ። ብርቱ ኃጢአት የተገኘበት እንደሆነ ከነዘ መዱ ይሸጣል ። እንኳን ሌላ የንጉሥ ግብር (ምግብ) ሲገባ ደወል ምልክት አለው ። ያንኑ በሰማ ጊዜ እንኳን ከቤት ያለው ሰውና በከ ተማም ያለው ሠራዊት ሰውም አይነጋገር ። ወዲያ ወዲህም አይል ። ይህ የተደረገበት ቀድሞ ንጉሣቸው እህል ሲበላ ትን ብሎት ስለ ሞተ ነው ። ስለዚህ ነገር ይህንኑ ሥራት አድርገውት ቀርቷል ። አሳላ ፊውም ለንጉሡ ካሳለፈ በኋላ እጁን ከከረጢት ከትቶ ይኖራል ። በቀኝ እጁ አሳስቶት ሌላ ሥራ ሲሰራበት ሲበላበት የተገኘ እንደሆነ እጁን ይቆረጣል . . . ." ብለዋል ።

የከፋው ንጉሥ (ባላባት) ጋቂ ሲርቦ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ዘጠኝ ወር ሙሉ ከተዋጋ በኋላ ነሐሴ 29 ቀን 1889 ዓ. ም. በራስ ወልደ ጊዮርጊስ ሠራዊት ተማረከ ። በተማረከበትም ጊዜ ዘውዱ ፤ የወርቅ ወንበሩ ፡ እንደ ጉማሬ ያለ የወርቅ አለንጋው ፤ አንዱ የብር ፤ አንዱ የናስ የሆኑ ነጋሪቶቹ ሁሉ አብረው እንዳሉ ተያዙ ።

ጋቂ ሲርቦ ከተማረከ በኋላ ወልደ ጊዮርጊስ እጁን በወርቅ ሰን ሰለት አስረው ወደ ሸዋ ይዘውት ሲመጡ ከጉጀብ ድልድይ ላይ ሲደርስ ከድልድዩ ላይ በቅሎውን አቁሞ በጣቱ ላይ ያለውን የንጉ ሥነት መለያ የወርቅ ቀለበቱን አውጥቶ "የከፋ መንግሥት አለቀለት ። ከእንግዲህ ወዲያ በከፋ ንጉሥ አይኖርም ። ስለዚህ የነገሥታት መለያ የሆነችው የወርቅ ቀለበት ከወንዙ ሥር ከመደቡ ትረፍ" ብሎ ጣላት ። ከምኒልክ ዘንድ ደርሶም ለእስር ወደ አንኮበር ሊላክ ሲል ምኒልክ ይበደላልና ወሎ ሄዶ ከራስ ሚካኤል ጋር ይቀመጥ ብለው አዘዙለት ። በልጅ ኢያሱ ዘመነ መንግሥትም አዲስ አበባ መጥቶ ጥቂት እንደቆየ በ1911 ዓ. ም. ሞተ ።

በሃድያው ባላባት በነጊታ ይመራ የነበረው ከምባታም ገበረ ። ገኒ ጉምቴ ትመራው የነበረው ጌራም በ1879 ዓ. ም. በምኒልክ ሠራ

ዊት ተያዘ ። ነገር ግን ጉምቱ እጤ ምኒልክ የሚለብሱትን ኩታና ጋቢ እየ ፈተለች የምትልክ እውቅ ባላባት ነበረች ። ምኒልክ ጥር 4 ቀን 1899 በፃፉላት ደብዳቤ "....የሰደድሽልኝ መተያያ አንድ ድርብ ፡ አንድ ኩታ ደርሶኛል ። እጅግ ማለፊያ ነው ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ። እማር ስበት በሬ ያልሺውንም ከአባ ጅፋር ዘንድ አስር በሬ ዳርጌሻለሁ" ብለዋል ። ይህም ምን ያህል ወዳጅ ሆነው እንደነበር ያሳያል ።

## ወላይታ

የወላሞው ንጉሥ ጦና አልገብርም ብለው አስቸገሩ ። እንዲያ ውም የገበረውን አገር ሁሉ እየወጉ እንደገና እንዲከዳ ያደርጉ ጀመር ። በዚህ ምክንያት ራሳቸው አጤ ምኒልክ በ1887 ዓ. ም. ኅዳር 7 ቀን ከአዲስ አበባ ተነስተው ወደ ወላይታ ጉዞ ጀመሩ ። ከወላይታ የግዛት ወሰን ሾኔ ከሚባለው ቦታ ሲደርሱም መልክተኛ ለጦና ላኩ ባቸው"....ሰውንም አታስፈጅ ፡ አገርህንም አታስጠፋ ። ግብርህን ይዘህ ግባ ።...." አሉ ።

ንጉሥ ጦናም ምኒልክ ለላኩባቸው መልእክት "....ባገሬ ክርስ ቲያን አይገባበትም ። ገፍተውም ከመጡ እዋጋለሁ እንጂ ለክርስቲ ያን መንግሥት አልገብርም ።...." ብለው መለሱ ። ፈረሰኛው የምኒልክ ጦር እንዳያልፍም መሬቱን በሙሉ ጉድጓድ ብቻ አድር ገው አስቆፈሩት ። የምኒልክን ሠራዊት እንዲያውክም ሠራዊታቸው እንጨት እያሾለ በሜዳው ሁሉ ተከለበት ። አጤ ምኒልክም ይህን ድርጊት እንደሰሙ ራስ ሚካኤልን ፣ ደጃች ኃይለማርያምን ፣ ፊታው ራሪ ገበየሁንና ሊቀመኳስ አባተን ጠርተው ሠራዊታቸውን ይዘው ጉድባውን እንዲያስደለድሉና የተተከሉትንም ሹል እንጨቶች እንዲ ያስነቅሉ አዘዙዋቸው ።

የታዘዙትም ሥራቸውን ከጨረሱ በኋላ ምኒልክ ሠራዊታቸውን እየመሩ ኅዳር 23 ቀን ቆንጦላ ሠፈሩ ። ምኒልክ ቆንጦላ እንደሠፈሩ እጅግ በጣም የበዛ የጦና ሠራዊት ሊዋጋ መጣ ። ምኒልክ ጦሩ እንዲ ዋጋ ከማዘዛቸው በፊት ጥቂት ሰዎች ወጥተው ጦርነት ገጠሙ ። በዚያም ከምኒልክ ሠራዊት 75 ሰዎች ተገደሉ ። ምኒልክ ይህን እንደ ሰሙም ሊቀመኳስ አባተንና በጅሮንድ ባልቻን ጠርተው ተዋጊውን አባረው የነሱን ሠራዊት እንዲመልሱ አዘዙዋቸው ። አባተና ባል ቻም የጦናን ሠራዊት አባረው የምኒልክን ሠራዊት ወደ ሠፈር መለሱ ።

ይህ ከሆነ በኋላ ምኒልክ በሰላም ተጉዘው ከጦና ዋና ከተማ ደልቦ ላይ ኅዳር 27 ቀን ሠፈሩ ። ጦና ግን ከዚያ ቦታ አልነበሩምና ካሉበት ድረስ መላክተኛ ልከው “ . . . .አገር ከጠፉ በኋላ ሲያቀኑት ያስቸግራል ። ገንዘብም በግድ ካልሆነ በቀር በፈቃድ የሰጡት እያልቅም ። አገርህን አታስጠፉ ። ግብርህን ይዘህ ግባ” ብለው ላኩባቸው ። እሳቸው ግን አልገባም ብለው ቀሩ ።

አጤ ምኒልክ ዳሞት ተራራ ላይ ወጥተው ጦራቸውን ካሰለፉ በኋላ በለው ብለው አዘዙ ። የታዘዘውም ሠራዊት ባንድ ጊዜ ወላይታን በሙሉ ያዘ ። ጦናም ከወላይታ ወጥተው ወደ ቦረዳ ሸሹ ። የምኒልክ ሠራዊትም እስከ ቦረዳ ድረስ ተከታትሎ ጦናን በጥይት አቁስሎ ያዛቸው ። ጦናም ተይዘው ምኒልክ ዘንድ ከቀረቡ በኋላ ምኒልክ “እወይ ወንድሜን እንዲያው በከንቱ ሕዝብ አስጨረስክ” ብለው ወቅሰው የቆሰለው ቁስል እንዲታጠብና እንዲታከም አደረጉ ። ሠራዊቱም በጣም ብዙ ከብት ማርኮ ነበርና የተማረከው ከብት በሙሉ ለባላገሩ እንዲመለስ አዋጅ አስነገሩ ። የባላገሩ ከብት እስኪመለስና ጦናም እስኪያገግሙ ጥቂት ቀናት ከርመው ጦና ካገገሙ በኋላ የወላይታን ሕዝብ ሰብስበው “ .... እንግዲህ ወዲያ የሚያስተዳድርህ ልጁ ወዳጄ ጦና ነውና ተገዛለት ። አውቆ ሳይሆን ሳያውቅ እኔን የበደለ መስሎት ሰው አስጨረሰ እንጂ ከድሮም ከአያቶቻችን ቂም የለንምና መልሼ እሱኑ ሾሜልሃለሁ ። . . . . ከእንግዲህ ወዲያ ብታምፅ በራስህ እወቅ ። ግብሬን አግባ ። ....” የሚል አዋጅ ፣ ካነገረው የወጉዋቾችውን ጦናን ሾመው ጥር 11 ቀን አዲስ አበባ ገቡ ።

በመሳፍንት ተከፋፍላ የነበረችውን ኢትዮጵያ፣ አጤ ቴዎድሮስ እንደነበረች ለመመለስ ቢያስቡም ኀይሳካላቸው ቀረ ። ቴዎድሮስ ሳይሳካላቸው የቀረው የኃይል ሥራ ይሠሩ ስለነበረ ፈርቶ ገበርኩ የሚለው ሁሉ ራቅ ሲሉለት መልሶ ይከዳ ነበር ። በዚህ ምክንያት የመሀከለኛው መንግሥት የሚያስተዳድረው ግዛት ጠብቦ ሁሉም በየቦታው ራሱን ንጉስ እያለ ያውጅ ነበር ። አጤ ቴዎድሮስም በየቦታው መዝሙቱና መምታቱ አድክሟቸው ነበር ። ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ግን ብዙውን በፍቅር ሲይዙ እምቢ ባዩንም በጦር ኃይል አስገበሩት ።

ምኒልክ ከነበራቸው ጠባይ ዋንኛው የዲፕሎማሲ ዘዴ ስለነበረ ከባላባቱ ጋር ተዋግተው ዋናውን ባላባት ሲማርኩ በቦታው መልሰው የሚሾሙት ያንኑ የድሮውን ባላባት ተማራኪውን ወይም የተማራኪውን ልጅ ነበር ። ያለዚያም ሕዝቡን እየሰበሰቡ በማስመረጥ ሕዝቡ የመረጠውን ይሾሙለታል ። ምኒልክ የአገሩን ተወላጅ በአገሩ ላይ ቢሾሙም ፣ ተሿሚው የሚሾመው ለውስጥ አስተዳደሩ ብቻ ነው ። ጠቅላላ የጦሩ ኃይል በምኒልክ እጅ በመሆኑ ሌላም የቅኝ

ገዥ እንዳይገፉ ለአገሩ ጥበቃ የጠሩን ኃይል ለማዘዝ የሚሾመው ከመሀከለኛው መንግሥት ነበር ። ምኒልክም ከዚያ ለአስተዳደር ከሾሙት ባላባት ላይ በያመቱ የሚገብረውን ግብር ብቻ ይፈልጋሉ እንጂ ተሿሚው ፡ ሕዝብ ካልበደለ በስተቀር በውስጥ አስተዳደሩ አይገቡበትም ነበር ።

እስከ ሩዶልፍ ሐይቅ ድረስ የተጓዘው ዊልቤ በ1893 ዓ. ም. ባሳተመው መጽሐፉ " . . . . በጠረፍ ያሉት ሰዎች ምኒልክ ጥሩ ሰው እንደሆነ ያውቃሉ ። ምኒልክ ሁሉም ሰው በሃይማኖቱ ይደር ስላለና በሕዝቡ መሀል አድሎና የኃይል ሥራ ስለማይሠራ ይወዱታል ። . . . . ሲያጠሩም እንደሴሎቹ ንጉሶች መስሎን ሸሽተን ነበር ። በኋላ ይቅርታ እየጠየቅን ተመለስን ። . . . .ያኔ ተታለን ነበር ይላሉ ። . . . . አሁን ግብራቸውን እየገበሩ በሰላም ይኖራሉ ። . . . . " በማለት ስለወላይታ ሕዝብ ጽፍዋል ።

በጅሮንድ ተክለሐዋርያት በሕገ መንግሥት ንግግራቸው "አጤ ምኒልክ በቅድመ አያቶቻቸው መንግሥት ፣ በሙሉ ኢትዮጵያ ለመግባት በቁ ። ገብተውም ጋላ ቀምቶን የነበረውን የጥንት ግዛታችንን ሁሉ መልሰው እጅ አደረጉና ጋላውንም ከሸዋ ጋር አስማምተው አዛምደው በትዳር የተሳሰረ አንድ ሕዝብ አደረጉ . . . . ብለዋል ።

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴም ሲተርኩ ". . . . ከጥንት የኖረ በሸዋ ብርቱ ሥርዓት ነበረ ። ጥፋት የተገኘበት ሰው ገንዘቡን ተወርሶ ፣ እጁን ታሥሮ ፣ መሬቱ ይሸጥ ነበር ። ነፍስ የገደለ ሰውም ራሱ ቢያመልጥ ዘመዱ እስከ ሶስት ትውልድ ድረስ መሬቱን ይነቀል ነበር ። ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ግን የፍትሐ ነገሥት ሥራት ተመልክተው በ1883 ዓ. ም. በጥር 23 ቀን ከዋያት በመለስ አዋሽ ድረስ ያለውን የጋሻ መሬት ሁሉ እንደመንዝ ርስት አድርጌልሃለሁ ። ምንም ብታጠፋ ገንዘብህ ይወረስ እንጂ መሬትህ አይነቀል ብለው አዋጅ ነገሩ ። . . . ." ካሉ በኋላ በሌላ ምዕራፍ ደግሞ ". . . . በሸዋ የጋላ ባላባት የተነቀለበትስ ምክንያት እንደምን ነው ቢሉ ካጤ ማህለ ሥላሴ ጀምሮ አገር ሲቀና የክርስቲያኑን አገር እየወረረ ቤተክርስቲያኑን እያቃጠለ ፣ በጋላው አገር የተሾመውን አላስገዛ እያለ እየተዋጋ ፣ ክርስቲያኑን እየገደለ ርስቱን ተነቅሎ ነበር ። ደግሞም አገሩ መቅናት ከጀመረ በኋላ የጋላው ባላባት ጉልበት እያነሰው ያባቱን መሬት ላማራ እያወረሰ መሬቱን ለቆ ይኖር ነበር ። አጤ ምኒልክ ግን ልጁ ተነቅሎ መቅረቱ አሳዝኗቸው እኔ ያባቱን አገር ስገዛ ባላባትም ልጁ ተነቅሎ አይቅር ብለው ከአባቱ መሬት ካማራ ተካፍሎ እንዲበላ አዘዙለት ። . ." ብለዋል ።

# የሐረርጌ ጦርነት

“ . . . . እነኚህ የአበሻ ሕዝቦች ሰፊ ግዛት አላቸው ። ከቀይ ባህር ዳርቻ ከምፅዋ ፣ ከሱአኪንና ከአርቂቆ ተነስቶ ግዛታቸው እስከ መቃዲሾና ሶፋላ ይደርሳል ። በምዕራብም በኩል ግዛታቸው የሚዋሰነው ከኑባውያንና ከሌሎችም ሕዝቦች ጋር ነው ። . . . .”

አልፎንሶ አልቡ ከርክ 1503 ዓ. ም.

“ . . . . የአበሾች ግዛት ሰፊ ነው ። ቀይ ባሕር ዳርቻ ካለው ከትልቁ ወደባቸው ከቢሊ ተነስቶ ወደ ውስጥ ሲጓዝ በአዳል ምድር አልፎ ሐድያ ሁሉ የነሱ አገር ነው ። ወደ ሕንድ ውቅያኖስ አቅጣጫም እስከ መቃዲሾ ይደርሳል ። . . . . አበሾቹ በጣም ሰፊና ሀብታም አገር አላቸው ። . . . . እነዚህ ሕዝቦች ወሰናቸውን ለማስከበር ወደዳር አገር ወይም ወደ ወሰናቸው በሚጓዙበት ጊዜ የሚጓዙት ዛፍ እየቆረጡና መንገድ እየሠሩ ነው ። . . . .”

ፍራንቼስኮ አልቫሬዕ 1520 ዓ. ም.

“ . . . . አበሾች ዙርያቸውን በአረመኔዎችና በብዙ ጠላቶቻቸው የተከበቡ ሕዝቦች ቢሆኑም ግዛታቸው ሰፊ ነው ። ከነኩዋቸው ተዋጊ ሕዝቦች በመሆናቸው ዙሪያቸውን የከበቡዋቸው ጠላቶች በተነሱባቸው ጊዜ ከጠላቶቻቸው ጋር እየተዋጉና እያሸነፉ ይኖራሉ ። የአበሻ ሰዎች ለማንም ባእድ አንገዛም እያሉ ራሳቸውን ችለው የሚኖሩና አገራቸውን ከማንኛውም ባዕድ ገዥ እየተከላከሉ የሚጠብቁ ሕዝቦች ናቸው ። . . . . ግዛታቸውም ቀይ ባህርን ተሻግሮ እስከ አረብ አገር ድረስ ነው ። . . . .”

1521 ዓ. ም. ካርታ ዳስ ኖቫስ

“ . . . . ቱርኮች በኔ ላይ ክፉ ነገር በመሥራት ወሰኔን እየገፉ አጠገቤ ደርሰዋል ። . . . . ሐረርን ወሰዱት ። ከዚያም አልፈው ኢቱ ጋላንና በረሃውን ሁሉ ሊይዙት ነው ። ነገሩ እንዲህ ከሆነ ከነሱ ጋር

ለመዋጋት መሄዴ ነው ። የኤሮፓ ነገሥታት ሁሉ እኔን እንደጠላት ስላዩኝ የተገፋሁ ሰው በመሆኔ ግብጾችን ለመውጋት ለመዝመቴ እር ስዎ ምስክር ይሆኑኛል ። . . . .” ምኒልክ በግንቦት ወር 1876 ዓ. ም. ለኢጣሊያ ንጉሥ ከፃፉት ደብዳቤ ።

“. . . . ሐረር . . . . ከአያት ከቅድመ አያቶቼ ጀምሮ የሸዋ ግዛት ነው ። . . . . ” ምኒልክ ግንቦት 27 ቀን 1877 ዓ. ም. ለኢጣሊያ ንጉሥ ከፃፉት ሌላ ደብዳቤ ።

ግብጾች ሐረርጌን የያዙት በ1867 ነው ። ኢትዮጵያ በመሳፍንት አገዛዝ ተከፋፍላ ሁሉም የዕለት ጥቅሙን ያሳድድ በነበረበት ጊዜ ክፍት በር ያገኘው በራኡፍ ፓሻ የሚመራው 1200 ወታደሮች ያለ በት የግብጽ ጦር በቀላሉ ሐረር ገባ ። በዚያን ጊዜ በሐረር ከተማ 5000 ቤቶችና 2,000 ጐጆዎች ነበሩባት ። የሕዝቡም ብዛት 35,000 ነበር ። ሐረር ከተማ ዙሪያዋን በግንብ ተከባ ወደ ከተማዋ የሚገ ባውም ፤ ከከተማዋ የሚወጣው በአምስት በሮች ብቻ ነው ። እነዚህም በሮች የተለያየ ስም ሲኖራቸው ታላቁ መግቢያ አስበዲን በር ይባላል ። ይህ መድፍ ተጠምዶ የተቀመጠበት በር የጨርጨር ሰዎች መግ ቢያ ነው ። 2ኛው ሱቅጣጥ በር ይባላል ። ይህ በር ደግሞ ያርሲዎችና የጋራሙለታ ሰዎች የሚገቡበት ነው ። 3ኛው አርጐባ በር ይባላል ። የፊዲሶች ፤ ያርጐቦች መግቢያ ነው ። 4ኛው አሱም በር ይባላል ። አሱም በር እንደ አስበዲን በር ሁሉ መድፍ የተጠመደበት ሲሆን የኢሶች መግቢያ ነው ። 5ኛው በር የረር በር ይባላል ። የየረሮች መግቢያ ነው ። እነዚህ በሮች ሁልጊዜ በሚገባና በጥንቃቄ ይጠበቃሉ ። ማታ ሲሆን በሮቹ ይቆለፉና የቁልፎቹ መፍቻዎች ለአሚሩ ይሰጣሉ ። ከዚያ በኋላ ነግቶ በሮቹ እስኪከፈቱ ድረስ የሚገባም ሆነ የሚወጣ የለም ።

ኢጣሊያኖች ሐረርጌን ከመቃዲሾ ጋር ፣ እንግሊዞችም ከበርበራ ጋር ደባልቀው ለመያዝ አሳብ ነበራቸው ። እንግሊዞች አንግሎ ኢጂፕ ቲያን በተባለው ከግብጽ ጋር በነበራቸው ስምምነት መሠረት የግ ብፅ ጦር ከሐረርጌ ወጥቶ ሐረርጌን ለእንግሊዞች ለማስረከብ ተስማም ተዋል ። ይህን ስምምነት የሰማው የኢጣሊያ መንግሥት ደግሞ ሐረ ርጌን ከእንግሊዝ ቀድሞ በኃይልም ሆነ በፍቅር ለመያዝ እስቦ በሐ ረርጌ ያለውን የግብጾች ጦር የሚሰልሉ ሰላዮች በየጊዜው ወደ ሐረርጌ ይልክ ነበር ።

እንግሊዞች ከግብጾች ጋር በነበራቸው ስምምነት መሠረት ግብ ጾች ከሐረርጌ እንዲወጡ አደረጉ ። ምናልባት የኢጣሊያ መንግሥት ገፍቶ የመጣ እንደሆነ በማለትም ከግብጾች ቀጥሎ ሥልጣን ለያዘው ለሐረርጌው አሚር አብዱላሂ እንግሊዞች የሰለጠኑ ወታደሮች ፥ 400 ያህል ጠመንጃና ጥቂት መድፎችን ሰጥተው ጀልዴሳና ሐረር ላይ ምሽጉን እንዲያጠናክር አደረጉት ።

አሚር አብዱላሂ ሥልጣኑን በሚገባ ከያዘ በኋላ የግብፅን ገንዘ ቦች አሽራፊ እና መሀለቅ የተባሉትን አስገብቶ በሐረርጌ ገበያዎች ላይ እንዲውሉ አደረገ ። የእነዚህን ገንዘቦች መግባት ያየው የሐረርጌ ኦሮሞና የሱማሌ ብሔረሰቦች ገንዘቦቹን አንቀበልም በማለት በአሚሩ ላይ ጥላቻ አሳድረው ገበያ ጠፋ ። በገበያው መጥፋት ምክንያት የአሚር ወታደሮች ችግር ላይ ወደቁ ። አብዱላሂ በዚህ ብቻ ሳይሆን በሚያወጣው አዋጅ ሁሉ በሕዝብ ዘንድ እየተጠላ ሔደ ።

በሐረርጌ የውጭ ሸቀጥ አስመጭና ያገር ውስጥ ንግድ ላኪ የነ በረው ኢጣሊያዊው ጋይታኖ ሲኮኒ በስለላ ተግባር ይጠረጠር ስለነበር የሐረሩ ኢማም አብዱላሂ ፥ ጋይታኖን ጠርቶ “ . . . . በእስልምና ሃይማ ኖት እመን ። የማታምን ከሆነ አገሬን ለቀህ ውጣ ። . . . .” አለው ። ጋይታኖም በእስልምና ሃይማኖት አላምንም ብሎ ከሐረር ተባሮ ወጣ ። ጋይታኖ ከሐረር ተባርሮ እንደወጣ ኢጣሊያ አገር ገብቶ ሚላን ላለው ለአፍሪካ የንግድ ማኀበር የደረሰበትን በደል አመለከተ ። ማኀ በሩ ለስም የተቋቋመ እንጂ ዋንኛ ሥራው የኢጣሊያን መንግሥት ሰላዮች ማስተባበርና መላክ ስለነበር ስምንት የታወቁ የኢጣሊያ ሰላዮችን በኢጣሊያ ንጉሥ ስም ስጦታ አስይዞ ወደ ሐረር ወደ አሚር አብዱላሂ ላከ ።

እነዚህ የኢጣሊያ መልእክተኞች ሚያዝያ 1 ቀን 1878 ዓ. ም. የሐረርጌ ግዛት ከሆነው ጀልዴሳ ደረሱ ። ከዚያም ሆነው “የተከበሩ ታላላቅ ስጦታዎችን ይዘን መጥተናልና እንዲቀበሉን ፈቃድ እንጠ ይቃለን” ብለው ለአሚር አብዱላሂ ላኩ ። አብዱላሂም ክርስቲያኖቹ ኢጣሊያኖች ወደ ግዛቱ በመግባታቸው ተናዶ እንዲገድሏቸው ወታ ደሮች ላከ ። የተላኩትም ወታደሮች ሰባቱን ኢጣሊያኖች አርደው ገደሉዋቸው ። አንደኛው ግን በፈረስ አምልጦ ዘይላ ገባ ። ኢጣሊያኖ ቹን የገደሉት ወታደሮች የመጣውን ስጦታ ይዘው ለአሚር አብዱ ላሂ አቀረቡ ። አብዱላሂ ከኢጣሊያ ንጉሥ መጥቶለት የነበረውን ስጦታ ተቀብሎ ኢጣሊያኖቹን የገደሉትን ወታደሮች አሰራቸው ። አብዱላሂ ይህን ማድረጉ ኢጣሊያኖቹ የተገደሉት በስህተት ስለሆነ ወንጀለኞቹን አስሬአለሁ ለማለት ያህል ነበር ። ይህ ከሆነ በኋላ ኢጣ

ሊያኖች ሐረርጌን በጦር ኃይል ለመያዝ ጥሩ ሰበብ አገኙ ። "በሐረ ርጌ የተገደሉብን ወገኖቻችንን ደም እንበቀላለን" የሚል መግለጫ ማውጣታቸውንና ሐረርን ለመያዝ ማሰባቸውን የሸዋው ንጉሥ ምኒ ልክ ሰሙ ። ወዲያውም ለአሚር አብዱላሂ ደብዳቤ ጻፉለት ።

"....ቀድሞም ቢሆን ሐረርጌ ከኢትዮጵያ ውጭ ተገዝቶ አያው ቅም ። ከኢትዮጵያ አውራጃዎች አንዱ መሆኑን አንተም በታሪክ ሰም ተኸው ይሆናል ። .... ለአራት መቶ ዓመታት ያህል ያለማቋረጥ ግብ ሩን ለአያቶቼ ሲገብር ኖርዋል ። አሁንም ነገሩን በሰላምና በወዳጅነት ለመጨረስ ግብርና እንደ አባቶቻችን ወዳጅ እንሁን ...." የሚል ደብ ዳቤ ለአሚር አብዱላሂ ላኩለት ። አሚር አብዱላሂ ደብዳቤውን ከተቀበለ በኋላ "....በውኑ በዚህ ዓለም ላይ ከቱርክ የሚበልጥ መንግሥት አለን? ...." ብሎ ለመኳንንቱ ተናገረ ።

ምኒልክም ለመጀመሪያው ደብዳቤያቸው መልስ ያለመምጣቱን እንዳዩ ዳግመኛ "ብትገብር ይሻልሃል" የሚል ደብዳቤ ላኩለት ። የምኒልክ ሁለተኛው ደብዳቤ ሲደርሰው አሚር አብዱላሂ ሳቀ ። ለም ኒልክ ደብዳቤ መልስ ሲመልስ ".... በእስልምና ሃይማኖት ገብተህ የሰለምክ እንደሆነ ጌትነትህን እቀበላለሁ" ብሎ እስላሞች የሚያሸ ርጡትን ሸርጥ ፣ እስላሞች በራሳቸው ላይ የሚጠመጥሙትን ጥምጥ ምና የጸሎት ጊዜ መስገጃ ምንጣፍ ላከላቸው ። ይህን መልስ ያገኙት ምኒልክ "....ወደ ሐረር እመጣለሁ ። በዚያ ያለውን መስጊድም ወደ ቤተክርስቲያን እለውጠዋለሁ ። ጠብቀኝ ።" የሚል ደብዳቤ ልከውለት ይዘጋጁ ጀመር ። ወዲያውም በእስቸኳይ ተዘጋጅተው በአጤ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ኅዳር 4 ቀን 1879 ዓ. ም. ከእንጦጦ ከተማ ተነሱ ።

የምኒልክን ከእንጦጦ መነሳት የሰማው አሚር አብዱላሂ በሐረ ርጌ ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ከሐረርጌ እንዲወጡ አዋጅ አስነገረ ። በሃ ይማኖት ሳቢያ ይረዳሉ ብሎ ኤሮፓውያንንም ጠርጥሮ ስለነበር ፤ ካገር አልወጣም ያለ ማንኛውም ክርስቲያን የሆነ ፈረንጅ ሁሉ ከቤቱ እን ዳይወጣ አዘዘ ። ጠባቂም በየበራቸው ላይ አደረገ ። በዚያን ጊዜ በሐ ረር የነበረው እንግሊዛዊው ፔቴን በጻፈው ማስታወሻ ".... በከተማዋ ውስጥ እንደ እስረኞች ነን ። ደብዳቤ የመላክና የመቀበልም ነፃነት የለ ንም ። ከሐረር ከግንቡ ውጭ እንኳ እንዳንወጣ ክልክል ነን ። ...." ብሏል ።

የገና በዓል ደርሶ ነበርና ንጉሥ ምኒልክ ጨለንቆ ላይ ሠፍረው የገ ናን በዓል ለማክበር ወሰኑ ። በዚያምሠፈር እድርገው ሳለ ምኒልክ መኳ ንንቶቻቸውን ሰብስበው ".... ይህ አሚር አብዱላሂ እኛ ክርስቶስ ተወ ለደ ስንል እሱ አልተወለደም የሚልበት ቀን ነውና የልደት ዕለት

ጦርነት መግጠሙ አይቀርም'' ብለው ተናገሩ ። ከዚህም በኋላ "....ግሳ ፤ እኔ ላንተው ነው እንጂ የመጣሁት አገር ለማጥፋት አልመጣሁም ። ተገባህ ፣ ተተገዛህ አገር አልነሳህም ። ኋላ ይቆጭሃል'' ብለው ላኩበት ። አሚር አብዱላሂ ግን የፈሩት መስሎት የተላኩትንም መልእክተኞች አሠራቸው ።

ኮንቲ ሮሲኒ ሲጽፉ "…. ገብር የሚለው የምኒልክ ደብዳቤ ለአሚር አብዱላሂ እንደ ደረሰው የሕዝቡን አስተያየት ለማወቅ ሕዝቡንና ወታደሮቹን አሰብስቦ የምኒልክን ጥያቄ አሰማቸው ። ሕዝቡም በሃይማኖታችን ላልገባና በእስልምና ሃይማኖት ለማያምን አንገብርም ። እንዋጋለን ። ቢያሸንፉን ሐረርን ይውሰዱ ። ያንጊዜም የሚፈልጉትን ግብር እንገብርላቸዋለን ብለው መለሱለት ። ...." ይላሉ ።

የሐረርጌ ሽማግሌዎች ግን አሚር አብዱላሂ ዘንድ ሂደው ጦርነቱ እንዲቀርና እንዲገብር መከሩት ። አብዱላሂም "…. ስለምኒልክ ሠራዊት እንድትነግሩኝ አልፈልግም ። እንድትነግሩኝ የምፈልገው መጽሐፋችን ለካፊር እጃችሁን ስጡ ይላልን ...." ብሎ አማካሪዎቹን አሠራቸው ። ካፊር ማለት በእስልምና የማያምን ነው ። ከዚያም በኋላ የጅሃድ ጦርነት አወጀ ። ሊያስገብሩት ሄደው የነበሩትን የደጃች ወልደገብርኤልን ሠራዊት በጥቂት መሣሪያ በማባረሩ ፣ የምኒልክ ሠራዊትም እንደዚያው በቀላሉ ይሸሻል ብሎ አሰበ ። ከዚህ በኋላ ሠራዊቱን አስከትሎ የምኒልክን ጉዞ ለማስቀረት ወደ ጨለንቆ ተጓዘ ።

ቀኑ የክርስቶስ የልደት በዓል ስለነበር የምኒልክ ሠራዊት እየበላ ፤ እየጠጣ ይጫወታል ። ንጉሥ ምኒልክ ከድንኳናቸው ደጃፍ ተቀምጠው አሽጋጋሪውን ኮረብታ በመነጥር ሲመለከቱ የአሚር አብዱላሂ ሠራዊት ሲመጣ አዩ ። ምኒልክ ሠራዊቱ እንዲሰበሰብ አድርገው "ሂደህ በለው'' ብለው አዘዙ ።

ከቀኑ 5 ሰዓት ሲሆን የአሚር አብዱላሂ መድፎች በሸዋ ሠራዊት ላይ ይተኮሱ ጀመር ። የሸዋ ሠራዊትም በአስደናቂ ፍጥነት የአብዱላሂን ሠራዊት ወርሮ መድፎቹን ማረከ ። በተማረኩት የአብዱላሂ መድፎችም የአብዱላሂ ሠራዊት ይመታበት ጀመር ። ጦርነቱ ብልጭ ብሎ ጠፋ ። የአሚር አብዱላሂ ሠራዊት ሩብ ሰዓት ያህል ከተዋጋ በኋላ ሸሸ ። አብዱላሂም በፈረስ ሆኖ ወደ ሐረር ሸሽቶ አመለጠ ። ከአሚር አብዱላሂ ሠራዊትም አንድ ሺህ ያህል ወታደሮች ተገደሉ ። ታህሣስ 29 ቀን 1879 ዓ. ም. የሐረርጌው የአብዱላሂ ጦር ድል ሆነ ። ይህን የአብዱላሂን ጦር ድል መሆን የሰሙት እቴጌ ጣይቱ አዲስ

በመሠረቱት አዲስ አበባ ሆነው "የሚገዘው ሰንጋ የሚነዳው ሽህር ለልደት ባይደርስ ፣
እሱ ላም አርዶ ዋለ የሸዋው ንጉሥ" ብለው ተቀኙ ። አንዳንድ ያገራችን ታሪክ ፀሐፊዎች "እስላም አርዶ ዋለ" ብለው ቅኔውን በመ ተርጐም ጽፈዋል ። እንዲያ ከሆነ ቅኔነቱ ይቀራል ።

ምኒልክ ድል ካደረጉ በኋላ የኢጣሊያ መንግሥት ሐረርጌን ለመያዝ እጅግ በጣም የተንሳሳ ጉጉት ስለነበረው እዚያው ጨለንቆ እንደሆኑ ለኢጣሊያው ንጉሥ ለኡምቤርቶ ". . . . ኢጣሊያኖችን የገደ ለው አሚር አብዱላሂ በፈረስ አመለጠኝ ። ግን እግዚአብሔር ይመስ ገን ሰዎቹን ፈጀሁበት ። ሰንደቅ ዓላማዬንም በአገሬ ላይ አቆምኩ ። ወታደሮቼንም አገባሁ ። ኢጣሊያኖቹን ለመርዳት ስል ። ተደርጐ የነበ ረውን አደጋ በብዙ ሬሣዎች ተበቀልኩ ። ከዚህ ደብዳቤ በኋላ ሁኔታ ውን በሰፊው የሚያስረዳ መልእክት እሰዳለሁ ። . . . . " የሚል ታህ ሣሥ 30 ቀን ፣ ማለት በጦርነቱ ማግስት የተፃፈ ደብዳቤ ላኩ ። ምኒ ልክ ይህን ደብዳቤ የፃፉት ሐረርጌ የኢትዮጵያ ግዛት መሆኑን ለኤ ሮፓ ነገሥታት ለማሳወቅና አሮፓውያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ባላ ቸው አሳብ መሠረት ወደ ሐረርጌ ጦር ቢልኩ ውጊያው ከምኒልክ ጋር መሆኑን ለማሳወቅ ጭምር ነበር ።

ምኒልክ አብዱላሂን ለመያዝ ወደ ሐረር ከተማ ገሰገሱ ። ጥር 1 ቀን አማሬሳ ሲደርሱ አብዱላሂ የሸዋ ጦር እንደደረሰበት ስላወቀ "ልግባና ልገዛ ። አገርዎን አያጥፉት" ብሎ ላከ ። ምኒልክም "እሺ ግባ ምሬሃለሁ" ብለው ላኩበት ። አብዱላሂ ግን ፈርቶ ለሊቱን ሚስ ቱንና ልጆቹን ይዞ ወደ ጅጅጋ ሸሸ ። የአብዱላሂን መጥፋት ያወቁት ሐረርጌዎች ማለት የአሚር አብዱላሂ አጐት አሊ አቡበከር ፣ የሱፍ በርከሌ ፣ ቃዲ አብደላና ሌሎች ሽማግሌዎች ሆነው ወደ ምኒልክ ዘንድ መጥተው ". . . . አሚር አብዱላሂ ሌሊት ጠፋብን ። ግብርዎን ይቀበሉን ። ሕዝቡንም አያጥፉት ንጉሥ ሆይ . . . ." ብለው አመለከቱ ። ከመልክተኞቹም ጋር እስረኞች የነበሩትን ሁለት ግሪካውያንና ሌሎ ችንም ፈትተው ወደ ምኒልክ ላኩ ። ንጉሥ ምኒልክም መልክተኞቹን ተቀብለው ". . . . ከዚህ በፊትም ብያለሁ ። እኔ የእስልምናን ሃይማኖት ለማጥፋት አልመጣሁም ። ሁሉም ሰው እንደየእምነቱ ያድራል ። እናን ተም ለሰላምና ለእርቅ ስለመጣችሁ በሰላም ወደ ሐረር እስከመጣ ይህንኑ ለሰዉ ነግራችሁ ከዚያው ቆዩኝ . . . ." ብለው መልእክተኞ ቹን መለሱ ። ከመልክተኞቹም ጋር በጅሮንድ አጥናፌ ከተማውን ለመረከብ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይዘው እንዲሔዱ አደረጉ ። የሻቃ ተክሌን ፣ ባላምበራስ ዳምጠውን ፣ የሻቃ አድነውን ፣ የሻቃ ገበየሁን የከተማውን በሮች እንዲጠብቁ አዘዙ ። እነኚህም ታዛዥች

እንዲታዘዙ ሐረር ከተማ በሰላም ገብተው ፈረስ መጋላ በሚባለው አደባባይና በአምስቱም በር ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሰቀሉ ። ሰንደቅ ዓላማውን መስቀል ብቻ ሳይሆን የሐረር ከተማ ሕዝብ እንዳ ይዘረፍም በየቤቱ በራፍ ዘብ አቁመው ያስጠብቁ ጀመር ።

በዛሬው በጂቡቲ ውስጥ አቦክ ከተማ የነበረው ታውሪን እ. ኤ አ ፌብሩዋሪ 3 ቀን 1887 ዓ. ም. ወደአገሩ በፃፈው ደብዳቤ “ . . . ከተማዋ የተያዘችው አበሾች ድል ሲያደርጉ እንደሚይዙት ዓይነት አይደ ለም ። . . . . ያለምንም ደም መፋሰስና ዝርፊያ ድል አድራጊው የሸዋ ጦር ከከተማዋ ገባ ። . . . . ” ብሏል ። ንጉሥ ምኒልክ አንድ ወር ያህል በሐረር ከቆዩ በኋላ ባላንበራስ መኰንንን ደጃዝማች ብለው ጥር 18 ቀን 1879 ዓ. ም. የሐረርጌ የበላይ ገዢና የወታደር ሹም ብለው ሾሙዋቸው ። 3000 ወታደሮችም ሰጡዋቸው ። ለሕዝቡ ግን እንደ ባህ ሉና እንደሃይማኖቱ እንዲያስተዳድሩ የአሚር አብዱላሂን አጐት አሊ አቡበከርን ሾሙ ። የካቲት 1 ቀን ወደ ሸዋ ለመመለስ ከሐረር ተነሱ ። ከሐረርጌ ጦርነትም 3000 ጠመንጃ ፣ 600.000 ጥይትና አራት መድ ፎች ማርከው ይዘው መጡ ።

ንጉሥ ምኒልክ የካቲት 28 ቀን እንጦጦ ከተማቸው ሲገቡ ከዚያ በፊት ያልታየ አቀባበልና ሰልፍ ታየ ። የዚያን ጊዜ የምኒል ክን ሰልፍ ድንቅ ያደረገው በሐረር የነበሩ የአሚር አብዱላሂ ግብ ፃውያን ሙዚቀኞች ስለተማረኩ ከሰልፉ ፊት ቀድመው ሙዚቃ (ማርሽ) በማሰማት ይጓዙ ስለነበር ነው ። ከዚህም ሌላ ከግብፅ የመጡ የኤሮፓ ውሾችንና በያይነቱ ቀለም ያላቸውን የርግብ ለማዳዎችን ሌላም አውሬ ሁሉ ይዘው ገቡ ። የዚያን ጊዜ ዘፋኞችም “የምኒልክ ነገር ይመስለኛል ተረት ፣

አሞራው በቀፎ ውሻው በሰንሰለት ፣” እያሉ ዘፈኑ ።



# የሥልጣን ትግል

አጤ ቴዎድሮስ በኃይለኛ አገዛዛቸው ምክንያት መሳፍንትን ሲጥሉ ፡ መሳፍንት እየተነሱ አስቸገሩዋቸው ። ለቴዎድሮስ አንገብርም ካሉ መሳፍንትም አንዱ የሸዋው ምኒልክ ነበሩ ። ምኒልክ ገና አጤ ቴዎድሮስ በሕይወት እያሉ ራሳቸውን ንጉሠ ነገሥት ብለው ሰየሙ ። ኤደን ለነበሩት ጉሌልሞ ማሳያ በጻፉት ደብዳቤ "የተላከ ከንጉሠ ነገ ሥት ምኒልክ" ይላል ። ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያም ፡ ለኤደኑ የእ ንግሊዝ ቅኝ ገገርም የፃፉዋቸው ደብዳቤዎች ሁሉ "የተላከ ከንጉሠ ነገ ሥት ምኒልክ" የሚሉ ነበሩ ።

አጤ ቴዎድሮስ ከጳጳሱ ከአቡነ ሰላማ ጋር ተጣልተው ጳጳሱን መቅደላ አስረዋቸው በነበረ ጊዜ አቡነ ሰላማ እባክህ አውጣኝ ብለው ለምኒልክ ላኩ ። ምኒልክ ያላቸውን ኃይል ለማሳየት ጭምር 30.000 ወታደር ይዘው ሄደው ኅዳር 21 ቀን 1860 ዓ.ም. ዳርዳሩን አስፈራር ተው ተመለሱ ። በመቅደላ ላይ የታሠረውም ሆነ የቴዎድሮስ ወታደር የምኒልክን ሠራዊት አይቶ አደነቀ ። ጳጳሱ አቡነ ሰላማ ግን ምኒልክ የሔዱ ጊዜ ሞተው ነበር ።

በመቅደላ ያለው እስረኛ ሁሉ ኤሮፓውያኖቹም ሆኑ ኢትዮጵ ያውያኖቹ ምኒልክ የመቅደላን አምባ በጦር ኃይል ሰብረው ነጣ ሊያ ወጡን ነው እያሉ ሲደሰቱ ፡ ምኒልክ ግን ጥቂት የጥይት ተኩስ አሰ ምተው ተመለሱ ። ምኒልክ የተመለሱበት ምክንያት ስንቅ አለቀ በሚል ሰበብ ነበር ። የሠፈሩት ከወዳጃቸው ከወርቂት ግዛት ስለነበር የስንቅ ችግር አይደርስባቸውም ። ግን በተኮሱት የጥይት ድምጥ መቅ ደላ ባለመሸበሩና ፀጥ በማለቱ ፡ ጳጳሱም መሞታቸውን ስለሰሙ ዱጋፌ ማጣታቸውን አውቀው ወደሸዋ የተመለሱ ይመስላል ። ወይም ደግሞ ምኒልክ ፤ ቴዎድሮስን ደህና አድርገው እንደሚያውቋቸው ቴዎ ድሮስ በድንገት አደጋ የመጣል ችሎታ ስላላቸው ፈርተውም ሊሆን ይችላል ። ወይም ደግሞ ቴዎድሮስ በዚያን ጊዜ ጠላት በዝቶባቸው ስለነበረ ምኒልክ የሁሉም ኃይል እስቲዳከምና ቁርጡ እስቲታወቅ ሊጋ የሆነውን ጦራቸውን ላለማስጨረስም ብለው ይሆናል ። በማን ኛው እንደሆነ አይታወቅ እንጂ የስንቅ ማለቅ ምክንያት ሊሆን አይችልም ። የቴዎድሮስ ሚስት እቴጌ ጥሩነሽም ለመዋጋት ተሰልፈው ይጠብቋቸው ስለ ነበርም አቅማቸውን ገምተውም ይሆናል ።

ምኒልክ ኢትዮጵያን አጠቃለው ለመያዝ ቢያስቡም ነገሩን ሁሉ ሰላማዊ ሰው እየመሰሉ በሰላም ለመጨረስ ፈለጉ ። ሠራዊታቸውም እንዳይጐዳባቸውና እንዳይወድቁ አቅማቸውን እያመዛዘኑ መኖር ጀመሩ ። ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ ሆነው ከእንግሊዞች ጋር ወዳጅነት መሥርተው ነበርና እንግሊዞች አጤ ቴዎድሮስን ለመውጋትና እሥረኞቻቸውን ለማስለቀቅ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ባሰቡበት ጊዜ ምኒልክን ከጐናቸው እንዲሰለፉ ጠይቀዋቸው ነበር ። ምኒልክም እንግሊዞችን ቢረዱ አጤ ቴዎድሮስ ያሸነፉ እንደሆን እንደሚወጓቸው ስላወቁና እንግሊዞችም ቢያሸንፉ ከደጃች ካሣ (በኋላ አጼ ዮሐንስ) ጋር የጠበቀ የወዳጅነት ውል እንግሊዞች ተዋውለው ስለነበር እንግሊዞች ከካሣ ጋር ሆነው ይወጉኛል በማለት ለሁለቱም ወገኖች ወዳጅ መስለው በዝምታ ቆዩ ። በተደጋጋሚ ከእንግሊዝ መንግሥት ለተላከባቸው መልክትም "....የምትመጡት ኢትዮጵያን አስገብሮ ለመያዝ ከሆነ በነገራችሁ አልስማማም ። ...." የሚል መልስ ብቻ ላኩ ።

በኤደን የእንግሊዝ ቅኝ ገዥም ለምኒልክ ደብዳቤ ሲመልስ "....እኛ ኢትዮጵያን ለመውረር አንመጣም ። በግዛታችን ሥር ለመደባለቅም አይደለም ። ወደ ኢትዮጵያ የምንዘምተው ቴዎድሮስ ያሠሩዋቸውን ወንድሞቻችንን ለማስፈታት ነው ። አጤ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ቢሸሹ ወይም የሸዋው የርስ መንግሥት ቢረዳቸው ግን የኛ ወታደሮች የሸዋን ወሰን አልፈው የሚዘልቁ መሆናቸውን ይወቁት...." በማለት ጻፉላቸው ። ይህ ደብዳቤ በአባ ጉሴልም ማሳያ እጅ በደረሳቸው በማግስቱ ምኒልክ ወደ ወሎ ሄደው ከወሎዋ ገዢ ከወይዘሮ ወርቂት ጋር ወረሂመኑ ላይ ንግግር በማድረግ ቆዩ።በዚያም እንዳሉ ወደ ኢትዮጵያ የዘመተው የእንግሊዝ ጦር አዛዥ የነበረው ናፒር "....ሊረዱን ስለመጡ እናመሰግናለን ። አሁንም እኛ በምንደርስበት ጊዜ ጦርዎን ወደ መቅደላ እንዲያስጠጉ ይሁን" ብሎ መልክተኛ ላከባቸው ። ምኒልክ ግን ለተላከው መልክተኛ "ፋሲካ ስለደረሰ ፋሲካን የምውለው አገሬ ነው" የሚል መልስ ሰጥተው ወደ ሸዋ ተመለሱ ።

ናፒር ጦሩን እየመራ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ ከትግራዩ ገዥ ከደጃች ካሣ ጋር ስብሰባ አድርገው ሲወያዩ ፥ ደጃች ካሣ ለእንግሊዝ ወታደር የሚሸጥ ቀለብ እያቀረቡ የእንግሊዝን ወታደር በሰላም ካሳለፉ ፥ ከመቅደላ መልስ የጦር መሣሪያ እንደሚሰጥ ቃል ገባላቸው ። በዚህ ስምምነት መሠረት እንግሊዞች መቅደላ ዘምተው እስረኞቻቸውን አስፈትተው ሲመለሱ 12 መድፍ ፥ 280 የመድፍ ጥይት ፥ 900 ጠመንጃ ፥ 349.000 የጠመንጃ ጥይት ፥ 3.200 የሽጉጥ ጥይት ለደጃች ካሣ ሰጡዋቸው ። ይህንንም ስጦታ ምኒልክ በሰሙ ጊዜ በእንግሊዞች ላይ

ቂም ያዙ ። ለራሳቸውም የጦር መሣሪያ እንዲሰጣቸው ወደናፒር መል ክተኛ ላኩ ። ናፒርም "....የፈታናቸው እስረኞቻችሁ ይበቃሉ ። በቴዎ ድሮስ እጅ ታስረው የነበሩትን የሸዋን መኳንንት ፣ ከዘመዶችዎም ዳርጌን ጭምር ፈትተን ልከንልዎታል" የሚል መልስ ላከላቸው ።

በእንግሊዞች መልስ የተናደዱት ምኒልክ ከኢጣሊያኖችና ከፈረ ንሣዮች ጋር በመዋዋል የጦር መሣሪያ ወደ ሸዋ ማስገባት ጀመሩ ። አጤ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ ሥልጣን የያዙት ዋግሹም ጐበዜ ንጉሠ ነገሥት ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው ነገሡ ።አሁን ትግሉ ከቴዎ ድሮስ ጋር መሆኑ ቀርቶ ወደ ተክለ ጊዮርጊስ ዞረ ።

አጤ ተክለ ጊዮርጊስ ሸዋን ለመውጋት በ1861 ዓ.ም. በመስከ ረም ወር ጨጨሆ በርን አልፈው ዘቢጥ ላይ ሠፈሩ ።ግብሬን ይዘህ ግባ ብለው ወደሸዋው ምኒልክ ላኩ ። ምኒልክም መኳንንቱን ሰብስ በው እንዋጋ ወይስ እንገብር ብለው ምክር ጠየቁ ። ምክሩ እንዲያው ለይስሙላ የቀረበ እንጂ ምኒልክ ያንጊዜም ተክለ ጊዮርጊስን የመው ጋት አቅም አልነበራቸውም ። መርድ አዝማች ኃይሌና መሸሻ ሰይፉ የምኒልክ ተቃዋሚ በመሆን ገና አልገበሩላቸውም ። የሸዋም ሕዝብ ተከፍሎ ከእነሱ ጋር ነው ። ከዚህም ሌላ የሸዋ ኦሮሞዎች እስከ ደብ ረብርሃን ድረስ እየሔዱ እየዘረፉና እየገደሉ ያስቸገሩትን እንኳ የምኒ ልክ ሠራዊት ሊቋቋማቸው አልቻለም ። ይህን ሁሉ የሚያውቁት ምኒልክ ለተሰበሰበው ጉባኤ መገበሩ እንደሚሻል አስረድተው ለግ ብር የሚሆን ብዙ ፈረስና በቅሎ በጉበና ዳጨ እጅ አድርገው የተክለ ጊዮርጊስን ግብር ዘቢጥ ድረስ ላኩ ። አጤ ተክለጊዮርጊስም በደስታ ግብራቸውን ተቀብለው ተመለሱ ። የትግራዩ ደጃች ካሣ (በኋላ ዮሐንስ) ለአጤ ተክለጊዮርጊስ አልገብርም ብለው በሚ ዋጉበት ጊዜ ምኒልክ በበጌምድርና በወሎ እየተዘዋወሩ የዘመኑን ባለጉልበታሞችና በጋብቻ የተሳሰሩትን ዘመዳሞች ውጊያ ያዳምጡ ጀመር ። የሁለቱ ተዋጊዎች መዳከም ለምኒልክ ጉልበት ማበጀት ይረዳ ስለነበር ነው ። በጦርነቱም ደጃች ካሣ ድል ስላደረጉ ጥር 13 ቀን 1864 ዓ.ም. በአቡነ አትናቴዎስ እጅ ተቀብተው ዮሐንስ 4ኛ ተብ ለው በአክሱም ጽዮን ነገሡ ።

ምኒልክ ወደ ጐንደር በሄዱበት ጊዜ በእጃቸው የነበረው ወሎ ከድቶ በአባዋጠው ተያዘ ። ምኒልክም ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ወሎ ዘም ተው ይማሙን አባዋጠውን መስቀላ በር ላይ ተዋግተው ድል አደ ረጉት ። ከጦርነቱ ቦታ ሸሽቶ ያመለጠው አባ ዋጠውም ይማሩኝ ብሎ ወደ ምኒልክ ላከ ። ምኒልክም በዚያ ጠላት በበዛበት ዘመን ወዳጅ ማብዛቱ ይጠቅም ስለነበር ከነእናቱ እንዲገባ ምሬአችኋለሁና ግቡ

ብለው ላኩባቸው ። አባ ዋጠውም ከእናቱ ከወይዘሮ መስታወት ጋር ለምኒልክ ሊገብሩ ታርቀው ገቡ ። ምኒልክም ሁለቱንም ሸልመው ልጁን ከአባቱ አገር ሾመው ደስ አሰኝተው ሰደዱት ።

አጤ ዮሐንስ ከነገሡ በኋላ ምኒልክ በ1868 ዓ.ም. ከወሎ ተነ ስተው ከዋና ከተማቸው ልቼ ገቡ ። በዚህ ጊዜ በቀረበው የክረምት ወራት ምክንያት ንጉሥ ምኒልክ ከሸዋ የማይመለሱ መስሎት አባ ዋጠው ወሎን በሙሉ አስከዳባቸው ። ምኒልክም እንደገና ወደ ወሎ ተመልሰው ሰኔ 29 ቀን 1868 ዓ.ም. የጁ ላይ ካባ ዋጠው ተዋግ ተው ድል አደረጉ ። ተማራኪውን አባዋጠውን አስረው ለየጁ ደጃች ወሌን ሾመው ወረኢሉ ገቡ ።

አጤ ተክለ ጊዮርጊስና ደጃች ካሣ ተዋግተው ተክለጊዮርጊስ በቀላሉ በመሸነፋቸው የምኒልክ ሠራዊት ተደናግጧል ። ካሣም በነበራ ቸው መሣሪያና ወታደር ላይ ከተክለጊዮርጊስ የማረኩት መሣሪያና የገባላቸው ወታደር በመብዛቱ ምኒልክ በነገሩ ያስቡበት ጀመር ። አጤ ዮሐንስም ቢሆን በጌምድርንና ጐጃምን ከያዙ በኋላ ወደሸዋ ለመዝመት አስበው ነበር ። ግን ንጉሥ ምኒልክ ብዙ ፈረሰኛ ሠራዊት ከመሣሪያ ጋር ስለነበራቸው ለጥቂት ጊዜ ጉዳዩን ቸል ብለው የምኒልክ ኃይል የሚዳከምበትን ዘዴ ይፈጥሩ ጀመር ።

የዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት መባል በውጭም ሆነ በውስጥ ያለ ውን ይዞታቸውን (ፖለቲካ) እንዳበላሸባቸው ምኒልክ ገብቷቸዋል ። የሚያዋጣው መንገድ ሠራዊት ማብዛት መሆኑን አውቀው ሰበካ ያዙ ። በዋና ከተማቸው በልቼም ለሶስት ቀን የቆየ ግብር አግብተው ሕዝቡን አስደሰቱት ። ስለዚያ ግብር ሁኔታ ማሳኘ ሲጽፉ "....የተሠ ራው አዳራሽ ትልቅ ነበር። ....በአዳራሹም ለምግብ ማቅረቢያ 150 ረጃጅም ገበታ ተዘርግቶ ነበር ።ወታደር፣ ሲቢል፣ መኳንንት፣ ቄስ፣ የልቼና ያካባቢዋ ታላላቅ ሰዎች ሁሉ ተጠርተው ነበር ። ከጐጃም፣ ከጐንደር፣ ከትግራይና ከመላው ኢትዮጵያ ታላላቅ ሰዎች መጥተው ነበር ።አንድ የቤተ መንግሥቱ ሰው እንደ ነገረኝ ንጉሥ ምኒልክ ለዚያ ግብር 15.000 ማርትሬዚያ ብር ወጭ አድርገዋል ። በዚህ ዘመን ይህ ገንዘብ በጣም ብዙ ነው ። ምኒልክም በግብሩ ላይ ለሚወ ዷቸው ሰዎች ሲያጫውቱ ። ....ካሣ ....ተክለጊዮርጊስን በመድፍ አሸ ነፈ ። እኔ ደግሞ እሱን በብር፣ በጠጅና በብርንዶ እዋጋለሁ ። በዚህም ደግሞ እንደማሸንፍ እርግጠኛ ነኝ....ብለዋል ።...." በማለት ጽፈዋል።

ምኒልክ እንዳሉት በጠጅና በብርንዶአቸው (ጥሬ ሥጋ) እየተ ወደዱ ሄዱ ። ሌላም የመወደጃ ዘዴ ነበራቸው ።አጤ ዮሐንስ በኢትዮ ጵያ ውስጥ የእስልምና ሃይማኖት እንዳይኖርና ያሉትም ሰዎች እንዲ

ጠመቁ ብለው ሲያውጁ ፣ ምኒልክ የዚያን ተቃራኒ ፈጠሩ ። አባዋጠውን ድል ካደረጉ በኋላ የወሎውን ኢማም መሐመድ አሊን (በኋላ ሚካኤል) ለወሎ ገዢ አድርገው ሾሙ ።በዚህ ሹመት ጊዜም ምኒልክ ለኢማም መሐመድ አሊ ደስታ ታላቅ ግብር አዘጋጁ ። ይህን ግብር መዘጋጀት የሰማው ክርስቲያኑ ሠራዊታቸው ከእስላም ጋር አብረን ልንበላ ነውን እያለ አጉረመረመ ። ምኒልክም መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው "....የወሎ ሰው ዛሬ እስላም ቢሆን እስከ ዓመት ፣ ባይሆንም እስከ ሁለት ዓመት በጥምቀት ፣ በቁርባን የሚተባበሩን ወንድሞቻችን ናቸው ። እግዚአብሔር አሁን የሰጠንን ዓለም አብረውን የሚገዙ ፣ በኋላም በርሱ ቸርነት መንግሥተ ሰማያት አብረውን የሚገቡ ናቸውና አትጥሉብኝ ። እናንተ ፍሪዳውን እያቀረባችሁ ስጧቸው ። እነዚያ እያረረ ይብሉ ። የወሎን ሰው በትህትና በፍቅር እየሳብሁ አሁን ለዚህ ዓለም ግዛት ፣ በኋላም በክርስቶስ ቸርነት ለመንግሥተ ሰማያት ለማብቃት ነው እንጂ ለመዝረፍ ፣ ለማጥፋት አልመጣሁም ። አሁንም ልጆቼ ከቤታችን እስላም ገባበት ብላችሁ አትጠየፉ ። ....ዘወትር አሳቤ በጐ ነገር ነውና አትከፉ ። ሳሳድጋችሁ፣ ስሾማችሁ ፣ ስሰጣችሁ አላሳፈርኳችሁምና እናንተም እንግዳዬን በመሸኘት አታሳፍሩኝ...." ብለው መከረው አዘዙ ። ሠራዊቱም ደስ ብሎት እንደታዘዘው አደረገ ።

በግብሩ ጊዜ በአዳራሹ ውስጥ ንጉሥ ምኒልክና መሐመድ አሊ በአንድነት ተቀምጠው ለሕዝብ ታዩ ። ሕዝቡ ፣ ክርስቲያኑ ምኒልክና እስላሙ መሐመድ አሊ አብረው ተቀምጠው ሲበሉ በማየቱ ተደነቁ ። በዚያን ዘመን እስላምና ክርስቲያን ባንድ መሆን እንደታላቅ ኃጢአት ይቆጠር ነበር ። ሲበላ ፣ ሲጠጣ ከርሞ ግብሩ ካለቀ በኋላ አዋጅ ተነገረ ። "ከዋያት እስከ በሽሎ ፣ ከአባይ እስከ አዘሎ ፣ ለልጄ ለይማም መሐመድ ሰጥቻለሁ" ብለው አዋጅ አስነግረው ተሰነባበቱ ። ይህን የተመለከተው የወሎ ሕዝብ በፍቅር አሜን ብሎ ለምኒልክ ገበረ ።

በ1868 ዓ.ም. የግብፅ ጦር በአስመራ በኩል በገፋ ጊዜ አጤ ዮሐንስ ክተት ሲያውጁ "....ክርስቲያን የሆንክ ሁሉ ቄሶች ጭምር ወደመጣው ጠላት እንድትዘምቱና እስላሞችን እንድታጠፉ ።...." በማለታቸው በወሎም ሆነ በሌላ ቦታ ያለው የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ዮሐንስን እየጠላ ምኒልክን ወደደ ።

ምኒልክ በሰው ቢደራጁም አጤ ዮሐንስ ደግሞ በመሣሪያ በኩል እየደረጁ ሄዱ ። አጤ ዮሐንስ ጉንዲት ላይ ከግብጾች ጋር ባደረጉት ጦርነት 2.500 ጠመንጃና 20.000 ብር ማረኩ ። ይህን የሰሙት ምኒልክ "እንኳን ደስ አለዎት" ብለው አንድ መቶ ፈረስ

ስጦታ ለአጤ ዮሐንስ ላኩላቸው ፡፡ እንደገና አጤ ዮሐንስ ጉርአ ላይ ባደረጉት ጦርነት 13.000 ያህል ጠመንጃ ፣ 16 መድፍና እጅግ በጣም ብዙ ጥይት ማረኩ ፡፡ በዚህ ጊዜ ጉሌልሞ ማሳዣ እንደፃፉት ".... የም ኒልክ ጥላንና ተስፋ እንደ ጭስ በኖ ጠፋ...." ፡፡

በአሁኑ ሰዓት ምኒልክ የነበራቸው ወታደር በቁጥር 40.000 ይሁን እንጂ የያዘው መሣሪያ አሮጌና አይነቱም የተለየ ነበር ፡፡ ምኒ ልክ ፣ አባ ሚካኤልን ከፈረንጆች ጋር አድርገው ወደ ፈረንሣይና ኢጣ ሊያ ስለመሣሪያ ሽያጭ እንዲነጋገሩ ላኩዋቸው ፡፡ የኢጣሊያን ንጉሥ ዳግማዊ አማኑኤል መልክተኞቹን ተቀብለው በጉዳዩ እናስብበታለን በሚል መልስ አሰናበቱዋቸው ፡፡ እነአባ ሚካኤልም ሮም ውስጥ ካለው የኢጣሊያ የጂኦግራፊ ማኅበር ጋር ተገናኝተው ስለምኒልክ በመን ገር ፍላጐታቸውን አስረዱ ፡፡ ማኅበሩም ወደ ኢኳቶሪያል አፍሪካ አንድ ቡድን ለመላክ በማሰቡ ሁሉንም ነገር በሸዋ ለመጨረስ ተስፋ ሰጠ ፡፡ በዚህ መሀል አሌክሳንድሪያ የነበረው ፒየር አርኑክስ እና ሌሎ ችም ወደሸዋ መጥተው ከምኒልክ ተገናኙ ፡፡

እነኚህን አዲስ መጪዎች ወታደሮቻቸውን እንዲያሰለጥኑላቸው ምኒልክ ጠየቁ ፡፡ አርኑክስም አንድ መቶ የሚሆኑ ወታደሮችን አሰ ልጥኖ ካርባይን አሲዞ በማሰለፍ ሰልፉን ለምኒልክ አሳየ ፡፡ ምኒልክም ሰልፉን ካዩ በኋላ" . . . . እንዲህ ያሉ አስር ሺህ ወታደሮች ቢኖሩኝ ኖሮ . . . . " ሲሉ የሰማው አርኑክስ መሣሪያ ለማግኘትም ሆነ ለማሰ ልጠን ጉዳዩ ቀላል መሆኑን ለምኒልክ አስረዳ ፡፡

አርኑክስ ሰኔ 29 ቀን 1868 ዓ.ም. 100.940 የፈረንሣይ ፍራ ንክ የሚያወጣ ዕቃ ይዞ በለውጡ የጦር መሣሪያ ለመግዛት ከሸዋ ተነሳ ፡፡ ይህን የሰሙት አጤ ዮሐንስ የአርኑክስን ጉዞ ለማሰናከል የም ሥጢር መልእክተኛ ልከው ዘይላ ላይ የዘይላው ገዥ አባቡርቃ የአር ኑክስን ዕቃ ወረሰው ፡፡ ዕቃው እንደተወረሰ እነ አባ ሚካኤል ሮም ከተማ ውስጥ ያነጋገሩት የጂኦግራፊያ ማኅበር በማርቼዚ ኦራዚዮ አንቲኖሪ የሚመራ ቡድን ወደ ሸዋ ልኮ ከምኒልክ ጋር ተገናኘ ፡፡ የመሣሪያ ማግኘቱ ጉዳይ በእንዲህ ያለ ሁኔታ ላይ እንዳለ አጤ ዮሐ ንስ የምኒልክን ሰዎች ለማስከዳት ማባበልና መሻረክ ጀመሩ ፡፡ ከእነ ኚህም አንደኛዋ ለንጉሥ ምኒልክ እንደ ሚስት የነበሩት ወይዘሮ ባፈና ነበሩ ፡፡

ወይዘሮ ባፈና ቆንጆ ይሁኑ እንጂ ለምኒልክ ሚስትነት የሚ ገቡ አልነበሩም ፡፡ ባፈና ፣ ምኒልክን የእናት ያህል በዕድሜ ይበልጡዋ ቸዋል ፡፡ ወይዘሮ ባፈና በሸዋ የቴዎድሮስ ሹም የነበሩትን መርድ አዝ ማች አቦዬን ፣ አፈ ንጉሥ መድኅኔንና ሌላም ባል አግብተው ከፊቱ

በኋላ ምኒልክን በ1858 ዓ.ም. በወዳጅነት ያዙ ። ወይዘሮ ባፈና ምኒ ልክን ከያዙ በኋላ ወንድ ልጆቻቸውን ደህና ደህና ቦታ አስያዙ ። ከሴት ልጆቻቸው እንዷቷን ለምኒልክ ቱርክ ፓሻ (የጠመንጃ ያዥ አዛዥ) ሲድሩ ሌላዋን ደግሞ ለመሸሻ ሰይፉ ለምኒልክ አጐት ልጅ አጭተዋት ነበር ።ባፈና ከልጆቻቸው አንዱ በሸዋ እንዲነግስ ወይም የነገሰውን በሴት ልጃቸው ለማጥመድ ይፈልጉ ነበር ።

አጤ ዮሐንስና ወይዘሮ ባፈና ጥሩ ምሥጢራዊ ወዳጅነት መስር ተዋል ።ከአጤ ዮሐንስ ጋር የጠበቀ ወዳጅነት በመመሥረታቸውም ዘዴዎቻቸውን ለውጠው ያን ጊዜ አለሁ ይል የነበረውና በምኒልክ ዘንድ የሚወደደው ለዘውድም ቅርብ የሆነው መሸሻ ሰይፉ ስለነበር ወይዘሮ ባፈና "ባርያ ብሎ መሸሻ ሰደበኝ" ብለው ከምኒልክ አጣ ሉት ። ምናልባት ሥልጣን የያዘ እንደሆነ ብለው እጮኛ አድርገ ውለት የነበረችውን ልጃቸውንም ለሌላ ለመስጠት ወሰኑ ።

መሸሻንም ምኒልክ ተቀየሙዋቸው ። ከሹመታቸውም ስለሻሩዋ ቸው ወደደጃች ጐበና ዘንድ ሄደው ተቀመጡ ። ሰው ይወዳቸው ስለ ነበር ብዙ ተከታይ አገኙ ። መሸሻ ለአጐታቸው ለደጃች ዳርጌ ነግ ረው ፥ በእሳቸውና በባፈና መሀል ያለው ጉዳይ በዳኝነት እንዲታይላ ቸው ጠየቁ ። የሁለቱን ጉዳይ እንዲያጣራ የተሰየመውም ጉባኤ መሸሻ ምንም ጥፋት እንዳላጠፉ ወሰነላቸው ። ባፈናም በውሳኔው ሳይስማሙ ምኒልክን ለምነው መሸሻ እንዲታሰርላቸው ስላስወሰኑ ታህሳስ 5 ቀን 1869 ዓ.ም. መሸሻ ለእርጐባው ገዥ ተሰጥተው ታሠሩና ወደ ጉንጮ ተላኩ ። ምኒልክም ለሴት ብለው አጉል ፍርድ በመፍረዳቸው ሠራዊታቸው ሁሉ ታዘባቸው ።

አጤ ምኒልክ ወደ በጌምድር ሄደው ሳለ ፥ወይዘሮ ባፈና መርድ አዝማች ኃይለ ሚካኤልን በመገፋፋት እንዲሸፍቱ አደረጉ ። ምኒልክ ወደ በጌምድር ከመሄዳቸው በፊት ታህሣስ 7 ቀን ደጃች ገርማሜ የሸዋ እንደራሴ እንዲሆኑ ሾመዋቸው ነበር ። የምኒልክን መራቅ ያዩት በባፈና የተገፋፉት መርዕድ አዝማች ኃይለ ሚካኤል አንኮበር ገብተው ራሳቸውን ንጉሥ ሸዋ ብለው ሾሙ ። የሸዋው እንደራሴም ደጃዝማች ገርማሜ ፣ መርድ አዝማች ኃይለሚካኤልን አዛዥ ወልደ ጻዲቅ እንዲወጉዋቸው አዘዙ ። አዛዥ ወልደጻዲቅም ሉዊስ ፖቲየር ያሰለጠናቸውን 50 ወታደሮችና የራሳቸውን 200 ወታደሮች ከጥ ቂት ፈረሰኞች ጋር ይዘው ዘምተው ሚያዝያ 24 ቀን 1869 ዓ.ም. ጋራቤላ ላይ ተጋጥመው የአዛዥ ወልደጻዲቅ ጥቂት ወታደሮች በመ ርድ አዝማች ኃይለሚካኤል ወታደሮች ተውጠው ድል ሆኑ ። አዛዥ ወልደጻዲቅ ለጥቂት ሲያመልጡ የምኒልክ ወታደር አሰልጣኝ የነበ ረው ፖቲየር በጦርነቱ ላይ ተገደለ ።

መርድ አዝማች ኃይለሚካኤልም ወደ አንኮበር ተመልሰው በአል አደረጉ ። የሸዋ መኳንንትም እከተማቸው ድረስ እየመጣ ግብር እንዲገብር አዋጅ ነገሩ ። እንደራሴው ደጃች ገርማሜም የአዛዥ ወልደጻዲቅን ድል መሆን እንደሰሙ በፍጥነት ወደ አንኮበር ገሰገሱ ። መርድ አዝማች ኃይለሚካኤልም ሚጣቅ አፋፍ ላይ ይጠባበቁ ነበርና ሁለቱ ወገኖች ተጋጥመው ጦርነቱ ተጀመረ ። በጦርነቱም ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ ። በጦር መሣሪያ ካለቀው ይልቅ ገደል እየገባ የሞተው ይበልጣል ። መርድ አዝማች ኃይለሚካኤልም ቆስለው ተያዙ በሰንሰለት ታስረውም ወደ እንዋሪ ተላኩ ።

ወይዘሮ ባፈና በዚህ በኩል ያለው ውጥናቸው እንደፈረሰ ሲያ ውቁ ሌላ ብልሃት ፈጠሩ ። "በሸዋ ውስጥ የተነሳው ብጥብጥ ደህና ገዥ በማጣቱ ስለሆነ እንደራሴነቱን ለኔ ሰጥተውኝ እርስዎ እስኪ መለሱ እኔ ላስተዳድረው" ብለው ምኒልክን በደብዳቤ ለመኑ ። ምኒል ክም በፊት የሾሚቸው ደጃች ገርማሜ እንዲያስተዳድሩ በማለት የባ ፈናን ጥያቄ አልቀበል አሉ ። ባፈናም እየደጋገሙ በመወትወት ስላስ ቸገሩ ምኒልክ የሸዋ እንደራሴነቱን ባፈና እንዲይዙ ፈቀዱላቸው ። ባፈናም ይህን ሹመት እንዳገኙ ይህንኑ መሾማቸውን ለደጃች ገርማ ሜና ለአዛዥ ወልደጻዲቅ ቢገልፁላቸው ሁለቱም ሹማምንት የባፈ ናን መሾም አናውቅም አሉ ። ባፈናም ይህንኑ ለምኒልክ አስታወቁ ። የባፈናን መሾም በደብዳቤ አድርገው በማህተም አትመው ላኩላቸው ። ከዚህ በኋላ ደጃች ገርማሜ የሸዋ እንደራሴነት ሥልጣናቸውን ለቀው በባፈና ሥር ዋሉ ።

ወይዘሮ ባፈና የሸዋ እንደራሴነት ሥልጣናቸውን እንደያዙ የመ ጀመሪያ ሥራቸው ያደረጉት ብዙ ሰው የሚወደውን እስረኛውን መሸሻ ሰይፉን በነፃ መልቀቅ ነበር ። መሸሻ ሰይፉ ከእስር እንደተ ለቀቁ ባፈና በመሸሻ ሠራዊት እንዳይዋጡ ስለሰጉ መጀመሪያ ያጬ ላቸውን ልጃቸውን ለመሸሻ ዳሩላቸው ።ወይዘሮ ባፈና ፡መሸሻ ሰይ ፉን በሴት ልጃቸው ከያዙ በኋላ በታሞ ፥ በአንኮበር ፡ በልቼና በፍ ቅር ግንብ ያለውን የጦር መሣሪያና ምሽግ ሁሉ በቁጥጥራቸው ሥር አደረጉ ።

መሸሻ ሰይፉም ታሞ ከሚባለው ቦታ መሽገው ወታደር መሰብ ሰብ ጀመሩ ። የሸዋን መበጣበጥ የሰሙት የወሎው መሐመድ አሊም ከምኒልክ ጉያ ወጥተው የምኒልክን ከተማ ወረይሉን አቃጥለው ሸፈቱ ።ይህን ሁሉ ምኒልክ ጐጃም ላይ ሆነው ሰሙ ። እንደሰሙ መሸሻ ሰይፉ ካለበት እንዳይወጣና አገር እንዳይዘርፍ ወታደርም እንዳይሰበስብ በፍቅር ግንብ በኩል ራስ ዳርጌን ፥ በዶባ በኩል ደጃች ወልደሚካኤልን አዝዘው ተከበው እንዲቀመጡ አደረጉ ።

መሸሻ ሰይፉን ካስከበቡ በኋላ ሐምሌ 2 ቀን መሐመድ አሊን ለመያዝ ወደ ወሎ ዘመቱ ። ወረኢሉ ሲደርሱ መሐመድ አሊ(በኋላ ንጉሥ ሚካኤል)ሸሹ ። የምኒልክ ሠራዊትም እያባረረ በመሐመድ ሠራዊት ላይ ብዙ ጉዳት ቢያደርስም መሀመድ አመለጡ ። ምኒል ክም ወደ ወረኢሉ ተመልሰው የፈረሰ ከተማቸውን በማሠራት ላይ እንዳሉ የእናታቸውን የወይዘሮ እጅጋየሁን ሞት ተረዱ ። ከዚህ በኋላ ወደ ሸዋ ተመልሰው ልቼ ከተማቸው ገቡ ።ወይዘሮ እጅጋየሁ የሞ ቱት ነሐሴ 21 ቀን 1869 ዓ.ም. ነው ።

ምኒልክ ሸዋ እንደተመለሱ ጠላት እንደበዛባቸው አወቁ ።የጐ ጃሙ ራስ አዳል ፥ ምኒልክን እንዲወጉ በአጤ ዮሐንስ ቢታዘዙ "እር ስዎ ካልረዱኝ ብቻዬን ልወጋው አልችልም" ብለው ለአጤ ዮሐንስ በመመለሳቸው አጤ ዮሐንስ ፥ራስ አዳልን ለመርዳት ወደ ጐጃም ተጉዘዋል ። የወሎው ወዳጃቸውና ገብረው የነበሩት ኢማም መሐመድ ለአጤ ዮሐንስ ለመግባት ሸፍተው በአሁኑ ጊዜ መስቀላ ላይ ምሽ ጋቸውን አጠናክረው ሠራዊት ሰብስበዋል ።የንጉሥ ሳህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ መሸሻ ሰይፉ በሸዋ እንደሸፈቱ ናቸው ። አጤ ዮሐንስም የምኒልክን ታማኝ ደጃች ወሌን ማባበል ጀምረዋል ። አጤ ዮሐንስ ደጃች ወሌ ወደ እሳቸው ቢገቡ "ከጨጨሆ በላይ ያለውን አገር እሰጥሃለሁና ወደኔ ና ። እኔ እሻልሃለሁ" ብለው ላኩ ። ደጃች ወሌም ክረምቱ ጠብቶ በጋው ሲወጣ እመጣለሁ እያሉ ቆዩ ። አጤ ዮሐን ስም የማታለያ ቃል መሆኑን ባወቁ ጊዜ ከደብረ ታቦር ተነስተው ወደ ጨጨሆ ተጓዙ ። በዚህም ጊዜ የየጁ ሰው በሙሉ የዮሐንስን ጦር በመፍራት ከደጃች ወሌ ጋር ተነስቶ ወደሸዋ ተሰደደ ።

ይህን ሁሉ የተመለከቱት ምኒልክ ሁሉን ባንድ ጊዜ መግጠም እንደማያዋጣቸው አውቀው ወዳጅ ማብዛትና የሰላም መንገድ ይፈ ልጉ ጀመር ። የደብረ ሊባኖስን ፥ የጀር የዜና ማርቆስን መነኮሳትና የመሸሻ ሰይፉ አስተማሪ የነበሩትን አባ ማሳያን ጨምረው ነገሩን በሰላም ጨርሰው እንዲያስታርቋቸው ወደ መሸሻ ሰይፉ ላኩዋቸው። መሸሻ ሰይፉም ታርቀው ሲገቡ ምኒልክ የደጃዝማችነት ማዕረግና ግዛት ሰጥተው ሾሙዋቸው ። ይህን ሁሉ መዘዝ ያመጡባቸውን ባፈና ንም የቁም እስር አደረጉዋቸው ።

አጤ ዮሐንስ ከባፈና ጋር ያደረጉት ንግግር ሁሉ በባፈና መያዝ ምክንያት መፍረሱን ስላወቁና ራስ ወሌም አምልጠው ሸዋ ስለገቡ በጌምድርን ትተው መሐመድ አሊን ለመርዳት በጥር ወር ወሎ ገቡ ። ከዚያም ከመሐመድ አሊ ጋር በመሆን ወደ ሸዋ ጉዞ ሲጀምሩ በበ ረሃ የነበሩ መነኮሳት አባ ገብረጻዲቅና አባ አኑን የሚባሉ ወደ ንጉሥ

ምኒልክ መጡ ። እነኚህም መነኮሳት ከአጤ ዮሐንስ ጋር እንዲታረቁ ምኒልክን ለመኑዋቸው ። ምኒልክም“ .... እርቅ እምቢ ብዬ የክርስቲያን ደም በከንቱ አላፈስም ። አጤ ዮሐንስ ግን እርቅ አልፈልግም ያሉ እንደሆነ እግዚአብሔር ለተገፋ ይርዳ . . . . ”ብለው መነኮሳቱ ደክ መው ነበርና በቅሎ ሰጥተው አንድ አሽከር ጨምረው በሳይንት በኩል ወደ አጤ ዮሐንስ ሰደዱዋቸው ።

እነዚህም መነኮሳት ኅዳር 27 ቀን ከአጤ ዮሐንስ ሠፈር ቀበሮ ሜዳ ደረሱ ። ከአጤ ዮሐንስም ዘንድ ገብተው ደም ሳይፋሰስ ከምኒልክ ጋር እንዲታረቁ ለመኑዋቸው ። አጤ ዮሐንስም በእርቁ ተስማምተው በጅሮንድ ለውጤን ከመነኮሳቱ ጋር አድርገው ወደ ምኒ ልክ ላኩዋቸው ። መልክተኞቹም ታህሳስ 12 ቀን 1870 ዓ.ም. ምኒ ልክ ሠፍረውበት ከነበረው ጋርዳ ከተባለው ቦታ ከምኒልክ ጋር ተገ ናኙ ። ለእርቅ ከምኒልክ ወገን የተመረጡት ፊታውራሪ ናደው ነበ ሩና ከምኒልክ በኩል ያለውን የእርቅ ድርድር ይዘው ወደ አጤ ዮሐ ንስ ዘንድ ሄዱ ።

በእርቁም ድርድር አጤ ዮሐንስ ከበሽሎ ወዲህ ያለውን አገር በሙሉ ለምኒልክ እንዲለቁ ነበርና ይህ ሐሳብ ቢቀርብላቸው አጤ ዮሐ ንስ “....መልቀቁን ከበሽሎ ወዲያ ያለውን አገር እሺ እለቃለሁ። ነገር ግን ለማንኛውም ቢሆን ተገናኝተን ቃል በቃል ካልተነጋገርን እርቁ አይጸናምና ይህንኑ ንገሩት” ብለው በጅሮንድ ለውጤንና ፊታ ውራሪ ናደውን መልሰው ሰደዱዋቸው ። አጤ ዮሐንስ እኔን ለመገና ኘት ምኒልክ አይወጡም ብለው ይጠራጠሩ ነበርና በጅሮንድ ለውጤን ከሰደዱ በኋላ በየካቲት ወር በ1870 ዓ.ም. ተከታትለው መጥተው መንዝ ደረሱ ።

የአጤ ዮሐንስ ጉዞ የጐጃሙን ራስ አዳልንና የወሎውን መሐ መድ አሊን ግንባር ቀደም መሪ በማድረግ ነበርና ቀኝና ግራ እየወ ረሩ የሕዝቡን ከብት እየማረኩ መጡ ። ወደራ ላይ በሰፈሩበት ቀን የወይዘሮ አትሞች ሆኖን ከተማ ሰላድንጋይን አቃጠሉት ።

ምኒልክ እርቅ መታረቁን ቢፈልጉም አጤ ዮሐንስ ግን እን ታረቅ እያሉ ወደፊት እየገፉ በመምጣታቸው ምኒልክ ተናደዱ ። እንጐለላ ላይም ሠራዊታቸውን ሁሉ ሰብስበው በማስለፍ የወታደራ ቸውን ብዛትና ጥራት አይተው አሳዩ ።በዚያም ቀን የሸዋ መኳንን ቶች ሲፎክሩ ለአምስት ሰናድር እገሌ ተዋሰኝ ፣ ለአሥር ሰናድር እነሌ ተዋሰኝ እያሉ ይናገሩ ነበር ።

ሰናድር ጠመንጃ አመጣለሁ እያሉ ሸዋዎች መፎከራቸው ከዚያ አስቀድሞ በንጉሥ ምኒልክ ሠራዊት እጅ የነበረው ጠመንጃ በባሩ

ድና በጨርቅ እየተደቀደቀ በከምሱር ወይም በቋድ የሚተኮስ ነበር ። በአጤ ዮሐንስ ሠራዊት እጅ ያለው ግን በዘመኑ ማለፊያ የሚባለው ሰናድር ጠመንጃ ነበር ። ሰናድር ጠመንጃ እየማረክን እናመጣለን ማለታቸው ነው ።

ምኒልክ ግን አቅማቸውን ገምተው ከጦርነት ይልቅ እርቁን ፈልገው ነበርና ከእንኮበር አለቃ ስነ ጊዮርጊስን ፣ አለቃ ምላትን ፣ አለቃ እሴቱን ፣ ከሚጣቅ አለቃ ሐሤቱንና ሌሎችንም መነኮሳት ጨምረው ወደ አጤ ዮሐንስ ላኳቸው ።እነዚህም ሊቃውንቶች ከአጤ ዮሐንስ ጋራ ወደራ ላይ ተገናኝተው የዕርቁን ውል ተነጋግረው ጨረሱ ። ውሉም ሁለት ነገሮች ላይ ብቻ ያተኮረ ነበር ። አንደኛው ንጉሥ ምኒልክ ወደ አጤ ዮሐንስ ሄደው እንዳይገናኙ ፣ በአጤ ዮሐንስም ላይ ጠላት ቢነሣ ፣ ንጉሥ ምኒልክ የጦር አበጋዛቸውን እየ ላኩ መርዳት እንጂ ራሳቸው ወደ ዘመቻ እንዳይሄዱ የሚል ነበር ። ይህም በሁለቱ መሀል ምን ያህል መጠርጠር እንደነበር ያሳያል ።

2ኛው በሃይማኖት አንድ ሊሆኑ ፣ አባ ማስያስ የሚባሉትን የካቶ ሊክ ጳጳስ ምኒልክ ከሸዋ አስወጥተው እንዲሰዱ የሚል ነው ። ሌላው ግን ጥቃቅን ነገሮችን የያዘ ነው ። እነዚህም አስታራቂዎች ወደ ምኒ ልክ ተመልሰው የእርቁን ሐሳብ ገና ሳይናገሩ የአጤ ዮሐንስ ሠራ ዊት ወራሪው ጦር የበሬሣን ወንዝ ተሻግሮ ብቅ አለ ።በዚህ ጊዜ የምኒልክ ሠራዊት በተለይ የፈረስ ዘበኛው ወጥቶ ጦርነት ተጋጥ መው ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው ሞተ ።

የንጉሥ ምኒልክ የአክስታቸው ልጅ የሆኑት በሻህ አቦዬ ብዙ ሰዎች ገድለው ብዙ ሰናድርም ማርከው እየፎከሩ ተመልሰው ነበ ርና ሸዋዮች "ለአምስት ሰናድር ፣ ለአስር ሲናድር ዋስ የጠራችሁ ፣

በሻህ አቦዬ ከፈለላችሁ ።" ብለው ገጠሙላቸው ።

ከዚህም በኋላ አጤ ዮሐንስ የእርቁን ውል ለማጽናት ሲሉ "ከወንድሜ ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ታርቄአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አገር ያጠፋህ ፣ ከብት የዘረፍህ ወታደር ትቀጣለህ" የሚል አዋጅ ነገሩ ። ወታደሩ ግን ያዋጁን ቃል እምቢ ብሎ ከብት እየዘረፈ ሲመጣ ባዩት ጊዜ እያስያዙ በጠመንጃ አስደበደቡት ። አንዳንዱንም እጁን ቁረጡት ብለው ካዘዙ በኋላ ፊታውራሪ ናደው ለጊዜው በዚያው ነበ ሩና "ጃንሆይ ወታደር መብሉን እንጂ ሞቱን አያስብምና በግርፋት ይቀጣ እንጂ መቆረጡን ይማሩት"ብለው አማልደው እየተገረፉ ተለቀቁ።

አጤ ዮሐንስም የእርቁን ነገር ጨርሰው ደብረ ሊባኖስ ለመሳ ለም ሔዱ ።አጤ ዮሐንስ ወደደብረ ሊባኖስ የሔዱት ከምኒልክ ጋር

በመላክተኛ ታርቀው እንጂ ተገናኝተው አልተጨዋወቱም ነበርና ተፀፅተው"... ,ተገናኝተን ተነጋግረን በፍቅርና ባንድነት ብንኖር መል ካም ነው ።" የሚል ቃል ጽፈው መስቀልና ሥዕል ጨምረው በደጃ ዝማች ዋህድና በመምህር ግርማ ሥላሴ እጅ ወደ ንጉሥ ምኒልክ ልከው ወደፊት ይጓዙ ጀመር ።

የተላኩትም መልክተኞች ከደጃዝማች ጉበና ፣ ከደጃዝማች መን ገሻ አቲከምና ከሊቀ ካህናት ኪዳነ ወልድ ጋር ደብዳቤውን ለንጉሥ ምኒልክ ባስረከቡ ጊዜ "ከመኳንንቶቼ ጋር መክሬ ምላሹን እነግራችኋ ለሁ" ብለው አሳደሩዋቸው ። በማግሥቱ መልክተኞቹ እየተጠሩ ገብ ተው ከተመከረ በኋላ "....አጤ ዮሐንስ በእኔ ላይ ክፉ ሥራ ላይ ሰሩ የማሉና የተገዘቱ እንደሆን ምላሹን ስትልኩብኝ ሔጄ እገናኛ ቸዋለሁ" ብለው ለአጤ ዮሐንስ ባለወርቅ አልጋና ባለወርቅ ወንበር ፣ ለእጨጌ ቴዎፍሎስም ባለወርቅ ወንበር ገጸ በረከት ጨምረው ሰደ ዱዋቸው ።

አጤ ዮሐንስ ወደ ሸዋ የመጡት ንጉሥ ምኒልክ ለእኔ አይገብ ርም ብለው በመጠራጠር ነበር እንጂ ከገበሩላቸው ኃይል ሥራ ለመ ሥራት አሳብ አልነበራቸውምና ንጉሥ ምኒልክ የጠየቁትን የመሀላ ቃል እሺ ብለው ተቀበሉ ። አጤ ምኒልክም የአጤ ዮሐንስ መልስ ከመጣላቸው በኋላ መጋቢት 12 ቀን ከልቼ ከተማ ተነስተው አጤ ዮሐንስ ወዳሉበት ጉዞ ጀመሩና ጅጅጋ ላይ ተገናኙ ።ጂጂጋ አጋዴን ያለው ሳይሆን በሸዋ ክፍለ ሀገር ሰላሌ ውስጥ ያለቦታ ነው ። የምኒልክን መምጣት አጤ ዮሐንስ እንደሰሙ ዋግሹም ብሩና ደጃዝ ማች ማሩ ፣ ደጃዝማች ተሰማና ደጃዝማች ዋህድ ለመቀበልና እጅባ ለመምጣት ተልከው ሄዱ ። አጤ ዮሐንስም ልብሰ መንግሥት ለብ ሰው ፣ ዘውድ ጭነው ፣ በትረ መንግሥት ይዘው ፣ ወታደሩን ቀኝና ግራ አሰልፈው መድፍ እያስተኮሱ ፣ እምቢልታና መለከት እያስነፉ በታላቅ ክብር ተቀበሏቸው ። ከዚህም በኋላ ሁለቱም በባለወርቅ ዙፋን ተቀምጠው ቃል ለቃል እየተነጋገሩ ከቆዩ በኋላ ምኒልክ ተሰናብተው ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ ። በማግሥቱ ተገናኝተው ወደራ ላይ የተደረገውን የእርቁን ውል ተነጋግረው ጨረሱ ። ከዚህ በኋላ በሁለቱም መካከል ትልቅ ደስታ ሆኖ ሰነበተ ።

ምኒልክ የአጤ ዮሐንስን ሠራዊት እንዲጎበኙ ተጋበዙ ። በዚያም የምኒልክ ጉብኝት ጊዜ ያጤ ዮሐንስ ሠራዊት 70.000 እግረኛ ፣ ከነ ዚህም ውስጥ 15.000 ዘመናዊውን ሬምግተን ጠመንጃ የያዘና 4.000 ያህል ፈረሰኛ ነበር ። ከዚህ ሌላ 20.000 የራስ አዳል ወታደሮችና 5.000 የመሀመድ አሊ ፈረሰኞች በዚያው ቦታ ነበሩ ።

መጋቢት 18 ቀን አጤ ዮሐንስ ታላቅ ድግስ አስደግሰው የምኒ ልክ የዘውድ በዓል ቀን እንዲከበር አደረጉ ። በዚያም ዕለት ሕዝብ በተሰበሰበበት አጤ ምኒልክ ንጉሠ ሸዋ መሆናቸው በአዋጅ ተነግሮ አጤ ዮሐንስ የንጉሥነቱን ዘውድ ለምኒልክ ሰጡ ። ይህ ከሆነ በኋላ ምኒልክ ለአጤ ዮሐንስ መገበር ጀመሩ ።ለምሳሌ ያህል በ1872 ዓ.ም በታህሳስ ወር 50.000ጠገራ ብር ፣600 ፈረስና በቅሎ ፣ 80.000ያህል የተለያዩ ሸማዎች ገበሩ ። በዚያው ዘመን በግንቦት ወር ደግሞ 10.000 ብር ፣ 30.000 ዳውላ እህል ፣ 10.000 የቀንድ ከብት ፣ 2000 መስፈሪያ ዱቄትና 400 እንስራ ቅቤ ለአጤ ዮሐንስ ሰጡ ።

እስከ እርቁ ቀን ድረስ አጤ ምኒልክ ይባሉ ነበር ። በደብዳቤም ላይ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ እያሉ ያትሙ ነበር ። አጤ ዮሐንስ ወደ ሸዋ መጥተው ንጉሥ ብለው የንጉሥነት ዘውድ ከሸለሟቸው በኋላ ግን አጤ ምኒልክ በእርቁ መሠረት አጤ መባላቸው ቀረና ንጉሥ ምኒል ልክ ይባሉ ጀመር ።

በዚያን ጊዜም አዝማሪ "እንዴት ያለ ሩቅ ነው ጭንቅ ያለ መንገድ ፣

እሻቅቦ ወጥቶ ወደ ታች መውረድ"ብሎ ገጠመባቸው ።

በወደራ በተደረገው አንድ እምነት ይኖረናል በሚለው የእርቅ ውል መሠረት የተለየ እምነት ያላቸው በደብረ ሊባኖስ የሚኖሩ ክር ስቶስ ሶስተኛ ልደት አለው የሚሉ ዋልድቤ እንግዳና ዙራምቤ እንግዳ ፣ተክለ አልፋም እጃቸው ተያዘ ። አጤ ዮሐንስም በመጋቢት 25 ቀን ከደብረ ሊባኖስ ተነስተው በፍቼ አድርገው በደራ በኩል ወደ ወሎ ለመሄድ ጉዞ ጀመሩ ። ንጉሥ ምኒልክም እስከ ታርጳ ሸኝ ተው ተመለሱና በነዋሪ በኩል ልቼ ከተማ ገቡ ። ከመለያየታቸውም በፊት በሌላ ጊዜ ቦሩ ሜዳ ላይ ተገናኝተው የሃይማኖት ጉባኤ እን ዲደረግ ወሰኑ ።

ንጉሥ ምኒልክ በልቼ ከተማ አንድ ወር ያህል ከቆዩ በኋላ የሸ ዋን ሊቃውንትና ካህናት በአዋጅ አሰባስበው በግንቦት 18 ቀን 1870 ዓ. ም. ከልቼ ተነስተው ወደ ወሎ ተጓዙ ። ከአጤ ዮሐንስም ጋር ቦሩ ሜዳ ላይ ከተገናኙ በኋላ የሃይማኖት ጉባኤ ተደርጐ ክርክር እንዲጀመር ታዘዘና ክርክሩን ለመስማት ሁለቱም ነገሥታት ቀኝና ግራ በተዘረጋላቸው ዙፋን ተቀመጡ ።በጉባኤውም የነበሩ ትልልቅ ሰዎች እጨጌ ቴዎፍሎስና ራስ አዳል ፣ ገና ክርስትና ያልተነሱት ይማም አባዋጠውና መሐመድ አሊ ነበሩ ። ከሸዋውም ወገን እነደጃ ዝማች ወልደ ሚካኤልና እነ ፊታውራሪ ናደው ሌሎችም ብዙ መኳ ንንቶች ነበሩ ።

ከሁለት ልደት ወገን አፈ ጉባኤው መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ፣ ከሶስት ልደት ወገን አለቃ ወልደ ሃና ሆነው ቆሙ ። የሁለት ልደት ወገን አፈጉባኤ የጥያቄ ቃል እያመጡ መላልሰው ከጠየቁ በኋላ የሶስት ልደት ወገን አፈ ጉባኤ ደግሞ በተራቸው ጥያቄ ሲጠይቁ እየመላለሱ በመጠየቃቸው አጤ ዮሐንስም መኳንንቱም ለተጠየቅኸው ነገር አጕራህ ጠናኝ ወይም አገባ በል እንጂ ተጠየቅ ማለት አይገባህም አሉ ።

በዚህም ጊዜ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ተነስተው "ጃንሆይ ፣ በእኛ በሸዋ ሥርዓት ከሳሹ ተጠየቅ እያለ ከተሟገተ ፣ ተከሳሹም በተራው ተጠየቅ እያለ ለመሟገት አይከለከልም" ብለው ስለ ተናገሩ አለቃ ወልደ ሐና ተጠየቅ እያሉ እንዲከራከሩ ተፈቀደላቸው ።

በክርክሩ ክርስቶስ ሶስተኛ ልደት አለው የሚል ከቅዱሳት መጻሕፍት ምስክር ስላልተገኘ ሁለት ልደት አለው የሚሉት ሲረቱ ሶስት ልደት አለው የሚሉት ወገኖች ተረቱ ። በዚህም ምክንያት በጉባኤው የነበረው ሰው ሁሉ ሃይማኖቴ ሁለት ልደት ነው እያለ ከዚያ ላይወጣ ተገዘተ ። ከደብረ ሊባኖስ እየተያዙ የሄዱት ዋልድቤ እንግዳና ዘራምቤ እንግዳ ፣ ተክለ አልፋ የሚባሉት ግን ለክርስቶስ ሶስት ልደት አለው ማለታችንን አንተውም አሉ ።በጉባኤው ከተቀመጡትም አንዱ ተነስቶ "አሁን ይህን የኑፋቄ ሃይማኖት ይዛችሁ መንግሥተ ሰማይ ልትገቡ ነውን" ቢሏቸው ዋልድቤ እንግዳ የሚባሉት የማይፈሩ ተናጋሪ ነበሩና "ምናልባት ያን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ አጤ ዮሐንስ ፣ ሊጋባው አሉላ ይከለክሉን ይሆን" ብለው በድፍረት ተናገሩ ። በዚህም አነጋገራቸው ምላሳቸውን ይቆረጡ ተብሎ ተፈረደና የሶስቱንም ምላሳቸውን እየቆረጡ ቀጧቸው ። ዋልድቤ እንግዳ ያን ጊዜውን ሞቱ ። ዘራምቤ እንግዳና ተክለ አለፋ ግን ከቦሩ ሜዳ ጉባኤ በኋላ ብዙ ዘመን ኑረው ሞቱ ።

አጤ ዮሐንስ ቦሩ ሜዳ ላይ በተደረገው የሃይማኖት ክርክር ሶስት ልደት የሚሉትን ወገኖች ምላሳቸውን በማስቆረጣቸው የውጭ አገር ሰዎች የክርስቲያን ተግባር አይደለም እያሉ በጋዜጣ ጽፈውባቸው ነበር ። አጤ ዮሐንስ ይህን ተግባር እንዲፈጸም ያደረጉት ባንዳንድ መነኮሳትና ቀሳውስት ግፊት እንጂ በራሳቸው ፈቃድ እንዳልሆነ ይታወቃል ። አጤ ዮሐንስ በሃይማኖታቸው ፅኑ መሆናቸውን የሚያውቁ ሰዎች "ሶስት ልደት የሚሉትንና እስላሞችን የአካል ቅጣት ቢቀጡዋቸው ይፀድቃሉ እንጂ አይኮነኑም" እያሉ ስለመከሩዋቸው እውነት መስሏቸው ይህን ከፉ ተግባር ፈጸሙ ።

ከቦሩ ሜዳ ጉባኤ በኋላም እስላምና ያልተጠመቀ ሁሉ እንዲጠመቅ የሚያስገድድ አዋጅ በ1870 አጤ ዮሐንስ አሳውጀው እሳቸው

የቦሩ ሜዳን ቤተ ክርስቲያን ማሠራት ጀመሩ ። በዚህም በተነገረው አዋጅ በኢትዮጵያ ያለ የእስላም ሃይማኖት ተከታይ ሁሉ ከፋው ። ከእስላሙ ወገንም በሃይማኖቱ የፀናውና ጉልበት ያለው ወደ መተማ እየተሰደደ ከደርቡሾች ጋር ተደባለቀ ። ሌላውም ወደ ሐረር ፣ ወደ ዋቤና ጂማ ተሰደደ ። የሚደርሰውን መከራ የፈሩት የእስልምና ሃይማኖት አማኞችም በእርግጥ ሳይሆን በአፋቸው ብቻ አምነናል እያሉ ተጠመቁ ። አገር ውስጥ ሆነው አንጠመቅም ያሉትም በእሥራት ፣ በመወረስ ፣ በሞትም ጭምር ተቀጡ ።

ከኢትዮጵያ እየወጡ የተሰደዱትም ካይሮ ድረስ በመሔድ የደረሰባቸውን ግፍና መከራ ለየባለሥልጣኑ ይነግሩ ጀመር ። ይህም የእስላሞች አቤቱታ በካይሮ ምድር እየበዛ በመሔዱ ገገርው ፣ የእስክንድርያውን ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስን አስጠርቶ“. . . .በቀድሞ ዘመን አይሁድና ክርስቲያኖች ባንድነት ሆነው በአረብ አገር የሚኖሩትን እስላሞች ባስጨነቋቸው ጊዜ መከራ የደረሰባቸው እስላሞች ወደ ኢትዮጵያ እየተሰደዱ ገቡ ። በዚያ ዘመን የነበረው የኢትዮጵያ ንጉስም ስደተኞቹን ተቀብሎ ማረፊያ እየሰጠ በደስታ ማኖሩን በታሪክ ሰምተናል ። ያሁኑ የኢትዮጵያ ንጉሥ አጤ ዮሐንስ ግን ባገሩ ውስጥ በሚኖሩ እስላሞች ላይ መከራ እያመጣ ስላስጨነቃቸው ይህ ነገር እንዲቀር የአደራ ደብዳቤ ጽፈው ይላኩ . . . . ”ብሎ አዘዛቸው ።

አቡነ ቄርሎስም “ . . . .ልጄ ሆይ ባገርህ ውስጥ የሚኖሩት እስላሞች በወደዱት ሃይማኖት እንዲኖሩ አድርግልኝ . . . .” የሚል ቃል ያለበት ደብዳቤ ጽፈው ወደ አጤ ዮሐንስ ላኩ ። አጤ ዮሐንስም ይህ ከአቡነ ቄርሎስ የተጻፈው ደብዳቤ ከደረሳቸው በኋላ ሁኔታውን ለምኒልክ ለማሳወቅ ብለው የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉላቸው ።

መልእክተ ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ።
ንጉሠ ጽዮን ፣ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።
ይድረስ ከንጉሥ ምኒልክ ።

በአማን እሥራኤላዊ ዘአልቦ ጸልሁት ሰላም ለከ ። ወሰላም እግዚአብሔር የኃሉ ምስሌከ ። እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት ፣ በእምነ ጽዮን አማላጅነት ፣ አምላክ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ደህና ነኝ ። ምህረቱ ለዘላለም ነውና ።

ይህ እስላም ኃይል ቢያጣ ነው እንጂ ተንኮሉን አልተወም ። ይህም ሊታወቅ የምስሩ ከደዊ ሊቀ ጳጳሳቱን ጠርቶ ምነው የእናንተ ልጆች እስላሙን ፣ ሃይማኖትህን ትተህ በኛ ሃይማኖት ግባ እያሉ ካለ

ፈቃዱ ያስቸግሩታል ብሎ ነግሮአቸው ኑሮ ሊቀ ጳጳሳቱ ምነው ልጁ ብትተውልኝና በወደደው ሃይማኖት ቢኖር ። በዚህ ያለነው አባቶችህ እንዳንቸገር ብለው ላኩብኝ ። እንደዚህም ማለታቸው የወዲያኛዎቹን እስላሞች ነገር ፈርተው ነው እንጂ እስላሙ ወደ ክርስትና ቢመለስ ጠልተው አይደለም ።

እኛም እንግዲህ ይህ ስለሆነ የተመለሰውም እንዲጸና ፣ ያልተመ ለሰውም እንዲመለስ በረቂቅ እያደረግን ሥራችንን እንዳንፈታ ይሁን ።

ተጽሕፈ በአሥመራ ከተማ አመ ፱ ለሚያዝያ በ፲፰፻፸፩ ዓ.ም.

በዚህ ደብዳቤ ላይ እንደምናየው አጤ ዮሐንስ እስላሙን በማስ ገደድ ተግባር ላይ ጨክነዋል ። የአቡነ ቄርሎስን አማላጅነት ለማክ በር ያህል ብቻ በይፋ መሆኑ ቀርቶ ውስጥ ውስጡን በዘዴ እንዲካ ሔድ ማዘዛቸውን "በረቂቅ" የምትለዋ ቃል ታስረዳለች ። ንጉሥ ምኒልክ ይህ የማስገደዱ ተግባር እንዲቀር የምክር ደብዳቤ ቢጽፉላ ቸውም "ግራኝ መሀመድ በአገራችን የእስልምናን ሃይማኖት ያስፋ ፋው በሰይፍ አይደለምን ። አሁንስ ቢሆን ደርቡሾች ጐንደር ድረስ እየገቡ ክርስቲያኑን ሕዝብ በሰይፍ እየቆረጡ ወደ እስልምና ሃይማ ኖት እንዲገባ ያደርጉ የለምን . . . . እኔም ሃይማኖቴን በሰይፍ አስከብራ ለሁ. . . .ያለፈውንም ደም እበቀላለሁ . . . ." የሚል መልስ ላኩላቸው።

በዚህም መልስ ላይ አጤ ዮሐንስ ባንዳንድ ባልተማሩ ቀሳው ስት ምክር መመራታቸውን እናያለን ።ምክንያቱም የክርስትና ሃይማ ኖት ፍቅርና ሰላምን እንጂ ሰይፍን አያዝምና ነው ። ያልተማሩ ቀሳ ውስት የተማሩ መስለው ቀርበው ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ይጥፋ በሚ ለው በኦሪት ሕግ በመመራት ሰይፍ በመዘዘ ላይ ሰይፍ ምዘዝበት እያሉ በማስተማራቸው ሃይማኖተኛው አጤ ዮሐንስ እውነት መስሏ ቸው በተግባር ላይ አዋሉ ። አጤ ዮሐንስ ፍጹም ሃይማኖተኛ ሰው እንደነበሩ የሚያስረዳ ሊነግሱ አክሱም በሔዱ ጊዜ ቀሳውስቱ ተሰብ ስበው "ሚስት ሳይኖርዎት እንዴት እናነግስዎታለን ?" ቢሏቸው "ሐዋርያው ጳውሎስ የጻፈውን አላነበባችሁምን ። ሚስት ያለው በሙሉ ልቡ እግዚአብሔርን ሊያገለግል አይችልም ብሎ የለምን. . . ." ብለው ያለሚስት ብቻቸውን ነገሡ ። እስከ መጨረሻውም ለሃይማኖታቸው ሲሉ ተሰዉ ።

ይህንኑ የአጤ ዮሐንስን አድራጐት የሰሙ የውጭ አገር መንግሥ ታትና ነገሥታት ሁሉ ተቃውመው ነበር ። ለምሳሌ የጀርመኑ ንጉሥ

ነገሥት ዊልሔልም ይህንኑ ጉዳይ አስመልክተው ለጻፉላቸው ደብዳቤ አጤ ዮሐንስ ሕዳር 1 ቀን 1872 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ መልሱን ሲመልሱ "....ሸዋ ዘምቼ ሳለሁ ። እኛ በኛ ክርስቲያኖቹ በሃይማኖት ተከራክረን፣ እረተን፣ በእስክንድርያ ሃይማኖት አገባናቸው ። እስላም ሁሉ አይቶ ሰምቶ ለኛስ አባት መጽሐፍ የለንም ። ያጥምቁን ። ክርስትና ያስነሱን ብሎ ለመነኝ ። እሺ ከፈቀድህስ ፤ ከወደድህስ ክርስትና ግባ ብየው የኢትዮጵያ እስላም ሁሉ ወዶ በፈቃዱ ክርስቲያን ሆነ ። አንድ ነገር በኃይል ያደረግሁት የለኝም ። ወዶ በፈቃዱ ነው እንጂ የገባ..." በማለት አስተባብለዋል ።በፍቃዳቸው ወደ ክርስትና የገቡ እነሸህ ዘካርያን የመሰሉ ጥቂት ሰዎች ናቸው እንጂ በሌላው ላይ ግዴታ እንደነበረበት ብዙ ተራኪዎች ጽፈዋል ።

ንጉሥ ምኒልክም ከወሎ ተመልሰው አንኮበር ከገቡ በኋላ የአጤ ዮሐንስን ትእዛዝ ለመፈጸም ሲሉ የይፋትና የአርጎባን እስላም ፣ የአብዩንና የገላንን ሰው በግድ እንዲጠመቅና እንዲቆርብ አደረጉ ። ይልቁንም ካህናቱ ሕዝቡን ካልተገረዘ አናጠምቅም እያሉ እምቢ በማለታቸው ኦሮሞው እንደ አባቶቹ ሕግ ገዳ የሚባለው የሚገረዝበት ዘመን ሳይደርስ በመገረዙ ትልቅ ጭንቅ ሆኖበት ነበር ።

ራስ አዳልም በበኩላቸው እንደ ንጉሥ ምኒልክ የአጤ ዮሐንስን ትእዛዝ ለመፈጸምና ደስ ለማሰኘት ሲሉ በጐጃም ያለውን እስላም በግድ ማስጠመቅ ፣ ቅብአት የሚባለውንም ሃይማኖት የያዙትን ሰዎች ማስገዘት ጀመሩ ።በዚያ ዘመን በኢትዮጵያ እስላምና እረመኔ በነበረው ሕዝብ ላይ የደረሰበትን መከራ በቀላሉ መገመት ይቻላል።

# የእንባቦ ጦርነት

ምኒልክ ታማኝ መስለው ቢገብሩም ለአጤ ዮሐንስ አልተኙላቸውም ። አጤ ዮሐንስም ቢሆኑ የምኒልክን ኃይል ለማድከም ጥረት ያደርጋሉ ። አጤ ዮሐንስ የወሎውን ኢማም መሀመድ አሊን (በኋላ ሚካኤል የተባሉትን) ክርስትና ቢያነሱ ፣ ንጉሥ ምኒልክ ደግሞ ሌላውን የወሎን ኢማም አባዋጠውን (በኋላ ኃይለ ማርያም የተባሉትን) ክርስትና በማንሳት በወሎ በኩል ምኒልክ ተመጣጣኝ ኃይል አገኙ ። ይህን የተገነዘቡት አጤ ዮሐንስ ከጐጃም ሌላውን ጀግና መለመሉ ። ይህም ጀግና የምኒልክ እኩያ እንዲሆን በማሰብ በጐጃም ታሪክ ውስጥ የሌለውን የንጉሥነት ማዕረግ ለመስጠት ወስነው ጉዳዩን ለምኒልክ በደብዳቤ አሳወቁ ።

መልእክተ ዘሥዩም እግዚአብሔር ዮሐንስ ፣
ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ከንጉሥ ምኒልክ ። በአማን እስራኤላዊ ዘሀልቦ ጸልሁት ሰላም ለከ ።ወሰላም እግዚአብሔር የሃሉ ምስሌከ ። እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት በእምነ ጽዮን አማላጅነት አምላክ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ደህና ነኝ ።ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ።

ራስ አዳልን የጥምቀት ዕለት የምሾመው የማነግሰው ነኝ ። ሲሆን ቢሰላ አብረን ሆነን መሾም ይገባን ነበር ።ቀኑ የሚያጥር የማያዳርስ እንደሆነ አንድ ደህና ሰው ሁኔታውን ሁሉ የሚያይ ገስግሶ ለጥምቀት እንዲገባ ይሁን ። እኔ ይሄን ማለቴ ንጉሠ ነገሥት ተብዬ እኮራለሁ ብዬ አይደለም ። አንድ ጊዜ ስሙ ወጥቶልኛል ። የእግዚአብሔር ሃይማኖት እንዲፀና ፣ እንዲስፋ ፣ አሕዛቦች እንዲጠፉ ብዬ ነው ። የኢትዮጵያ ምቀኛዋ ብዙ ነውና ጠላቶቻችን እንዲደክሙና እንዲያፍሩ ብዬ ነው ።

ደግሞ ይህን ጉዳይ ካደረግን በኋላ ወደ አምናችን የምመጣ ነኝና መምጣቱ የሚቸግር እንደሆነ ከዚያው እንድንገናኝ ይሁን ። የኢጣሊያ ንጉሥ አምና በረከት ሰዶልኝ ነበር ።ዕቃውን እኑሮ ስዎ

ቹን መልሶ ወሰዳቸው ። ፍቅር ጀምሮ ሰዎቹን መልሶ መውሰድ ብል ሃቱ ጠፍቶኛል ። የዚህ ነገሩ ወደርስዎ ይገኝ ይሆን ።

ተጻሐፈ በአምባጫራ ከተማ አመ. ስሙኑ ለታህሣሥ በ፲፰፻፸ ወ፫ ዓ. ም.

ንጉስ ምኒልክም ይህ ያልታሰበ ነገር የሚገልጸው ደብዳቤ እንደተ ጻፈላቸው "….. ይህማ ትልቅ ነገር አይደለምን ። እንደምን አድርጌ እቀ ራለሁ….." ብለው በግስጋሴ ወደ ደብረ ታቦር ሔዱ ። አጤ ዮሐንስም ከአምባጫራ ወደ ደብረ ታቦር ሔደው ጥር 11 ቀን 1873 ዓ. ም. ራስ አዳልን ንጉስ ተክለሃይማኖት ብለው በጐጃም ላይ አነገሱዋቸው። ምኒልክ ማቅናት የጀመሩትን የከፋንም ንጉሥነት ጨመሩላቸው ። ለሽልማት ብለውም ስምንት ሺህ ጠመንጃ ሰጥተዋቸው አጤ ዮሐንስ ወደ መቀሌ ተመለሱ ።

በማዕረግ የምኒልክ እኩያ የሆኑት ንጉስ ተክለ ሃይማኖት የከፋ ግዛትም በተጨማሪ ስለተሰጣቸው ከፋን ለማቅናት ሐሳብና ሥራ ጀመሩ ። ከፋንም ለማቅናት ራስ ደረሶ ተላኩ ። ራስ ደረሶ ኦሮሞው ውስጥ ገብተው ወለጋን ፣ ነቀምቴን ጉማን ፣ አሞሮን ፣ ሐሮን ፣ ጉድሩን ፣ ግንደ በረትን ፣ ጂማን አስገብረው ያዙ ። ንጉስ ምኒ ልክ ነገሩን ሳይሰሙ ቆይተው በኋላ "….. የጐጃም ጦር አዛዥ ራስ ደረሶ ከጉማው ባላባት ከአባ ጆቢር ጋር ተዋግተው አባ ጆቢርን ገደሉዋቸው….." የሚል ወሬ ሰሙ ። ምኒልክም ራስ ጐበናን በአስቸ ኳይ ወደ ከፋ ልከው እሳቸው ወደ አርሲ ዘመቱ ።

ራስ ጐበናም ብዙ አገሮችን አስገብረው ሊሙ ሲደርሱ ራስ ደረሶ ከየአገሩ የሰበሰቡትን ዝባድና የዝሆን ጥርስ ሊሙ አስቀም ጠው ከፋን ሊያስገብሩ ሄደው ነበር ። ራስ ጐበና ሊሙ እንደደረሱ ራስ ደረሶ የሰበሰቡትን የዝሆን ጥርስና ዝባድ አግኝተው እጅ አደ ረጉ ። ወዲያውም "እነ'ዚህ ጐጃሞች በምን ይስቃሉ ፣

ጥርሳቸውን ሊሙ ጥለውት ሄዱ አሉ" ተብሎ ተገጠመ ። የራስ ጐበናን ነገር ደረሶ በሰሙ ጊዜ ከከፋ ተመልሰው አገሬን ለቀህ ውጣ ብለው ለጐበና ላኩባቸው ። ራስ ጐበናም ጦርነት ላለ ማንሳት "በዮሐንስ አምላክ ተዳኝ" ብለው ከአጤ ዮሐንስ ነጋዴዎች ዳኛ አደረጉ ። ዳኞቹም ጠብ እንዳይፈጠር ሁለቱንም ወገኖች አቆሙ ። ራስ ደረሶና ጦሮች ይመር ግን ጦርነት አምሮአቸው ነበር ። ግን በዮሐንስ አምላክ ስለተባሉ ጠብ ለማንሳት አልደፈሩም ። የዚህ ጊዜም የራስ ደረሶ አዝማሪ

"እገዛለሁ ብሎ ከእንጦጦ ገስግሶ ፣
በዮሐንስ አምላክ አሰኘው ደረሶ" ብሎ ዘፈነ ።

ራስ ደረሶ ወደ ጐጃም ተመልሰው ጉዳዩን ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ነገሩ ። ራስ ጐበናም ለምኒልክ ደብዳቤ ጻፉ ። ንጉሥ ምኒልክ አርሲን ድል አድርገው ሲመለሱ አዋሽ ላይ ከራስ ጐበና የተጻፈው ደብዳቤ ደረሳቸው ። ደብዳቤውም "…. ከራስ ደረሶ ጋር ጉማ ላይ ተገናኝተን ከባላገር በግብር የተቀበሉትን ከብት ሁሉ አስመለስናቸው። ወደፊትም ንጉሥ ምኒልክ በፈቃዳቸው ከሰጧችሁ አገር በቀር ወደ ሌላ እንዳታልፉ ይሁን ብለን አስምለንና አስገዝተን ሰደናቸዋል ። እኔም ወደዚያው ወደ ንጉሥ መምጣቴ ነው …." የሚል ነበር ። ንጉሥ ምኒልክም ነገሩ አላምር ብሎአቸው ምናልባት ሁለቱ ጀግናች ራስ ጐበናና ራስ ደረሶ ጦርነት የተጋጠሙ እንደሆነ የብዙ ሰው ደም ሳይፈስ አይቀርም እያሉ ሲሰጉ ነበርና ነገሩ ያለ ጦርነት በመ ጨረሱ ደስ ብሎአቸው ወደ እንጦጦ ከተማ ተመለሱ ።

አጤ ዮሐንስ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደሚያግዙና ምኒል ክን ለመጣል እንደሚተባበሩባቸው ንጉሥ ምኒልክ ያውቃሉ ። ተባ ብረው ይገ ሉኛል እያሉም ይሰጋሉ ። ስለዚህ ምኒልክ በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መበደላቸውን አስቀድመው ፍርድ እንዲታይላቸው ወደ አጤ ዮሐንስ ደብዳቤ ጻፉ ።አጤ ዮሐንስም የሚከተለውን ደብዳቤ ለምኒልክ ጻፉላቸው ።

መልእክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ፡

ንጉሠ ጽዮን ፡ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ከንጉሥ ምኒልክ ። በአማን እስራኤላዊ ዘአልቦ ጸልሑት ። ሰላም ለከ ወሰላም እግዚአብሔር የኃሉ ምስለከ ። እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት ፡ በእምነ ጽዮን አማላጅነት ፡ አምላክ ቅዱስ ይክበር ይመስገን ደህና ነኝ ። ምህረቱ ለዘላለም ነውና ። ደብዳቤውም ደረሰኝ ። ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከዚህ በፊትም ልኬአለሁ ። እንግዲህም እሺ እልካለሁ። ደግሞ ለየራሳችሁ አንዳንድ ሰው አለመስደዴም ወደሸዋ የሄደው ለሸዋ። ወደ ጐጃም የሄደውም ለጐጃም ያደላልና ነገሩ አያምርም ብዬ ነው ። ነገር ግን አንድ ጳጳስ ፡ ሶስት ኤጲስ ቆጶሳት አራት ሆነው ሲመጡ ፡ በኢትዮጵያ ተደርጐ የማያውቅ አዲስ ነገር ሲደረግ ፡ የረከሰ በሚቀደ ስበት ፡ የተጣላ በሚታረቅበት ጊዜ እላንተ ትጣላላችሁ ። እኔም ለሠራ ዊቱ ስንቅ አስይዝ ብዬ ነው እንጂ ምን አደርጋለሁ ይኸው መጣሁ ፡ ተነስቻለሁ ። ሲሆን ወይ ከዋድላ ወይ ከቤጌምድር ላይ ከእኔ ስንገናኝ አለያያችኋለሁ ። አትቸኩሉ ፡ እስከመጣ ድረስ ቆዩ ።

የቸኮላችሁ እንደሆነ ግን ካለሁበት ድረስ እየራሳችሁ የሚለ

ያይ አንድ አንድ ሰው ሰደዱ ። የሚመጣው ሰው ግን በጥንተ ውሉ ተጋጥሞ የሚለያይ ነው ።

ተጻሐፈ በመቀሌ ከተማ እመ ፳፰ ለኅዳር በ፲፰፻፹፱ ዓ.ም.

ምኒልክ ይህ ደብዳቤ እንደደረሳቸው ለአጤ ዮሐንስ መልስ ጽፈዋል ። ምኒልክ የጻፉትን ደብዳቤ ባላገኘም አጤ ዮሐንስ በጻፉላቸው የመልስ ደብዳቤ ላይ ሁኔታው ሊታወቅ ይችል ይመስለኛል ። አጤ ዮሐንስ ደግመው የጻፉት ደብዳቤ ቀጥሎ ያለው ነው ።

መልእክተ ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ፣
ንጉሠ ጽዮን ፡ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ከንጉሥ ምኒልክ ። በአማን እስራኤላዊ ዘአልቦ ጸልሁት። ሰላም ለከ ወሰላም እግዚአብሔር የሃሉ ምስለከ ። እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት ፡ በእምነ ጽዮን አማላጅነት ፡ አምላክ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ደህና ነኝ ። ምሕረቱ ለዘላለም ነውና ።

ደብዳቤውም ደረሰኝ ። ከዚህ በፊትም የሁለታችሁን መልእክት ደብዳቤ አመላለስሁ ። አትጣሉብኝ፡ተፋቀሩልኝ ፡ እንደ ሽማግሌ ፣ እንደ እናት ፡ እንደ አባት እመክራለሁ ፣ እገላግላለሁ እንጂ እንደ ንጉሥ ይህ ይሁን ብዬ ያዘዝሁት ነገር የለኝም ። አሁንም የእሕዛብና የሰይጣን መሳለቂያ እንዳንሆን ከባህር ወዲህ ፡ ከባህር ወዲያ ብዙ ጠላት ሳለን ፣ እርስ በርሳችን ብንዋጋ የክርስቲያን ደም በከንቱ ቢፈስ ለክርስቶስ ደስ አይለውም ። አሁንም የሁለታችሁ ጦር አይገናኝ ። ከተገናኘ ዘንድ ከመዋጋት ይደርሳል ። እኔ እስከመጣ ድረስ ታገሡልኝ ። ጦራችሁ በያለበት ይቆይ ። ደግሞ እኔ ፊቴን ወደ ትግሬ ብመልስ በወረባብ፡ ባርጉባ ፡ በወሎ ብዙ ነገር ይደረጋል ። ማተቡን ይቆርጣል ሲሉ እሰማለሁ ። ከቀድሞም ያጠፋ ያባ ዋጠው ምክር ይሆንን ብዬ ነበር ። አሁንም ቢመከርበት ይሻላል ። ነገር ግን እኔ ባጠፋው ቸግሮኝ አይደለም ። ከወንድሜ ጋራ እንዳልከፋፋ ብዬ ነው እንጂ ።

ተጻፈ ባጭኔ ሰፈር እመ ፰ ለጥር ፲፰፻፹፱ ዓመተ ምሕረት ፣

አጤ ዮሐንስ ደብዳቤ የጻፉት ለምኒልክ ብቻ አይደለም ። የጎጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ተበዳይ ነኝ ብለው ለጻፉላቸው ደብዳቤ አጤ ዮሐንስ መልሱን ልከውላቸው ነበር ። ደብዳቤውም ቀጥሎ ያለው ነው ።

መልእክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ፣
ንጉሠ ጽዮን ፣ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።
ይድረስ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ በአማን እስራኤላዊ ዘእልቦ ጽልሁት ።

ሰላም ለከ ወሰላም ፣ እምላከ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ደህና ነኝ ። ምህረቱ ለዘለዓለም ነውና ።

ደብዳቤውም ደረሰኝ ። እኔም የሁለታችሁን ነገር እየሰማሁ መከራ እየተቀበልኩ ተቀምጫለሁ ። ነገር ግን ኢትማእ ለእኩይ በእኩይ አላ በገቢሩ ሠናይ ነው ። እንኳን በቅርብ ያለውን ጠላቴን በሩቅ እንኳን ያለውን ጠላቴን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጐዳልኛል እንጂ እኔ አልጐዳም ። አሁንም መጣፋት ክፉ ነው እንጂ የተገፋ ሰው ምን ተጐድቶ ያውቃል ። ለሁሉም እኔ ወደዚያው መጣሁ ። ሁሉም ስንገናኝ ይሆናል ።

ተጻሐፈ በአድዋ ከተማ አመ ፲፰፻፸፬ ዓመተ ምሕረት ።

የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መልክተኞች የአጤ ዮሐንስን ደብዳቤ ይዘው ወደ ጐጃም ሲመለሱ አጋም ውሃ ሲደርሱ ደስታ ኃይሉ የሚባል ተንኰለኛ ሽፍታ ነበረ ። ከሞጣ ነጋዴ ገንዘብ እየቀማ ስለለመደ መልእክተኞቹን ከመንገድ ይዞ አስሮ የአጤ ዮሐንስን ደብዳቤ ቀምቶ ቀዶ ጣለው ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም የደስታ ኃይሉን ተንኰል ሳያውቁ የአጤ ዮሐንስን መልስ ሲጠብቁ ከረሙ ።

እንደ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ አጻጻፍ ግን "...ራስ ደረሶ ደብዳቤውን ከመልክተኛው ተቀብለው ባዩት ጊዜ አትዋጋ የሚል ሆኖ ስላገኙት ንጉሱ ደብዳቤውን ያዩ እንደሆነ ከጦርነቱ ይቀራሉ በማለት ሳያሳዩዋቸው ቀርተው ነበር ። ...." ይላሉ ። አለቃ ተክለ ኢየሱስ ግን ሽፍታው ተይዞ እንደተፈረደበት ሁሉ ይገልጻሉ ። የንጉሥ ምኒልክ ሥራ ቤቶችም —

"ሴቶች ተሰብሰቡ እንውቀጥ ዳሂራ
ከርከር አይቀርም ከራስ አዳል ጋራ ።
ይታመሳል አሉ ከፋና ቦረና ፤
አማን አይደሉም ወይ እነ ራስ ጐበና"

እያሉ ይዘፍኑ ጀመር ። ጥቂት ቆይቶም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለዘመቻው አዋጅ ማወጃቸው ተሰማ ።

ንጉሥ ምኒልክም የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ጦር ማወጅ በሰሙ ጊዜ እርሳቸውም በበኩላቸው የጦር አዋጅ አውጀው በመጋቢት 13

ቀን 1874 ዓ.ም. ከእንጦጦ ከተማ ተነሱ ። ራስ ጐበናም ከአገር አገር ወዲያና ወዲህ እየተዘዋወሩ አገሩን ያቀኑ ነበርና በመንገዱ ርቀት ምክንያት ወሬአቸው ጠፋ ። ንጉሥ ምኒልክ ጥቁር መሬት ሲደርሱ ከጅማ የመጣ አንድ ነጋዴ ተገኝቶ ወሬ ሲጠየቅ "ራስ ጐበና ወደ ንጉሥ ለመምጣት ጊቤን ተሻግረዋል ። ከጐጃሞቹም ጋራ ጦርነት አልገጠሙም እንጂ ጐጃሞች አገሩን ሁሉ ማጥፋት ጀምረዋል" ብሎ ተናገረ ።

ኖኖ ሲደርሱም ራስ ጐበና መጥተው ከምኒልክ ጋር ተገናኙና ታላቅ ደስታ ሆነ ። ወዲያውም በርሳቸውና በራስ ደረሶ መካከል የሆነውን ነገር ሁሉ ያገሩንም አኳኋን እያስረዱ ከተናገሩ በኋላ ባንድነት ሆነው ወደፊት ጉዞ ጀመሩ ።

የወሎዋ ባላባት ወይዘሮ መስታወትም የወሎን ሠራዊት ይዛ እንድትመጣ ታዛ ነበረና ንጉሥ ምኒልክ ሊቃ ላይ ሲደርሱ በሰልፍ ገብታ የወሎን ሠራዊት አሳየች ። ምኒልክ ፥ ጐጃሞች ሳያስቡት በድንገት ሳሲ በሚባል ወንዝ ዳር መስፈራቸውን የጐጃም ጦር ስለሰማ ወደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መልክተኛ ላኩ ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ገና አባይን አልተሻገሩም ነበርና ከመኳንንቱ ጋራ ተማክረው ፊታውራሪ ይመር የሚባለውን አሽከራቸውን "ወደ ንጉሥ ምኒልክ ሄደህ ይህ አሁን እርስዎ ያሉበት አገር በአጤ ዮሐንስ ፈቃድ ያቀናሁት የኔ ግዛት ስለሆነ የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ ትተው ይመለሱልኝ ብለህ ንገር" ብለው ላኩዋቸው ። ፊታውራሪ ይመርም እንደተላኩት ለምኒልክ ቢነግሯቸው "ለንጉሥ ተክለሃይማኖት ከአባይ ወዲህ ምን ግዛት አለው ። እኔ ስለወዳጅነትና ስለፍቅር ብዬ አሞሩን ፥ ጠሮን ፥ ጉድሩን ፥ ግንደ በረትን ፥ የቀዲዳን አገር እንዲያቀና ብሰጠው እያለፈ ሌላውን አገር ሁሉ ይይዝ ጀመር ። አሁን ግን በፈቃዴ የሰጠሁትን አገር ወስጃለሁና ከአባይ ወዲህ ያለው የእርሱ ሠራዊት እየተመለሰ እንዲሻገር ይሁን" ብለው ለፊታውራሪ ይመር ነገሩዋቸውና መልክተኛው ተመልሰው ሔዱ ።

ከዚህም በኋላ ንጉሥ ምኒልክ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሠራዊት ባቀናው አገር ሹም ሽር አድርገው ወደ እንጦጦ ለመመለስ ኖኖ ሽሬ ከሚባል ስፍራ ሲደርሱ ግንቦት 21 ቀን የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መልክተኞች መጡ ። ንጉሥ ምኒልክ አስጠርተው "ደብዳቤ ይዛችሁ እንደሆነ ስጡኝ ። የቃል መልክትም እንደሆነ ንገሩኝ" ቢሏቸው "መኳንንቱ ሁሉ ካልተሰበሰቡ ለብቻዎ እንዳንናገር ታዘናል" አሏቸው ። ምኒልክም መኳንንቱን ሁሉ ሰብስበው ንገሩኝ አሏቸው።

"ጌታችን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ንገሩ ያሉን ቃል ይህ ነው ። ምነው እርስዎ እኔን ሁልጊዜ ያዋርዱኛል ። ከዚህ ቀደም በኃይል መጥተው አገሬን ጐጃምን አጥፍተውት ሄዱ ። አሁን ደግሞ ያቀናሁትን የጋላውን አገር እያጠፉ ሹም ሽር አደረጉበት ። ከእንግዲህስ ወዲህ መጣሁ ፣ አይሂዱ ። ከጉዱሩና ከሐሮ ፣ ከጅማና ከጨሊያ በወደዱት አገር የጠራ ሜዳ ይዘው ይቆዩኝ ። ይህንንም ቃል በደብዳቤ አለ መላኬ ደብዳቤውን ብቻዎን አይተው ቀደው ጥለው ሰምተው እንዳልሰማ ሆነው ሸሽተው ይሄዳሉ ። በቃል የሆነ እንደሆነ ግን ይህን ሰምተው ሲሸሹ አሽከርዎችዎ ይታዘቡዎታልና በቃል መላኬ ስለ ዚህ ነው ብለዋል" ብለው ተናገሩ ።

ንጉሥ ምኒልክም ይህን በሰሙ ጊዜ "ምንም ቢሆን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ይህን የመሰለ ኃይለ ቃል አይልክብኝም ። ቢልክብኝም በማኅተሙ ይልክብኝ ነበር እንጂ በቃል አይልክም ። ስለዚህ ሐሰተኞች ናችሁና ተይዛችሁ ቆዩ" ብለው አሲያዙዋቸው ። መልክተኞቹ ግን "ይህ ቃል የጌታችን መልክት ያልሆነ እንደሆነ በአካላችን እንቀጣ" እያሉ ከማሉና ከተገዘቱ በኋላ "እንግዲያውስ ከእናንተ አንዱ ሄዶ አዎን ልኬአችዋለሁ የሚል ባለ ማኅተም ደብዳቤ ይዞ ይምጣ ። እናንተ ግን እንደ ተያዛችሁ ቆዩ" አሉዋቸው ። ለሚሔደውም መልክተኛ "እኔ ለአንተ ጦር ሰግቼ ሸሽቼ አልሄድም ። ነገር ግን ከኔ ጋራ ለመዋጋት ከአጤ ዮሐንስ ፈቃድ አግኝተህ እንደሆነ ፈቃድ ማግኘትህን በደብዳቤ እንድትልክብኝ ብዬ ነው እንጂ ፣ ለጦርነትስ እዚያው አገርህ ደረቢ ሜዳ ላይም ቢሆን እመጣለሁና አንተን መንገድ አይምታህ ። ይህንንም በደብዳቤ አለመላኬ አንተ ደብዳቤውን ስትጠላው አይቼ ነው ብለህ ንገር" ብለውት ሄደ ።

ከዚህም በኋላ ንጉሥ ምኒልክ ደጃዝማች ወልዴን ጠርተው "ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለጦርነት መምጣቱ እውነትም ሐሰትም እንደሆነ በግስገሳ ሄደህ ወደ አባይ አፋፍ ዘልቀህ በመነጥር አይተህ አሳውቀኝ" ብለው ላኩዋቸው ። ደጃች ወልዴም በግስጋሴ ሔደው ሲመለሱ "ከአባይ ወዲህ ብዙ የድንኳን ሠፈር አይቻለሁ" ብለው ተናገሩ ። ይህን የሰሙት ምኒልክም ከሠፈሩበት ተነስተው ወደ ጉዱሩ ተጓዙ ። ይላላም በደረሱ ጊዜ በግንቦት 28 ቀን 1874 ዓ.ም. በጠራ ሜዳ ላይ ሠራዊታቸውን አሰልፈው ሰልፉን ሲያዩ ዋሉ ።

በግንቦት 30 ቀን በማለዳ ተነስተው ሲጓዙ እምባቦ ሜዳ ሲደርሱ የጐጃም ቀዳማዊ ጦር ታየ ። ንጉሥ ምኒልክ በፈረስ ሆነው ወዲያና ወዲህ እየተዘዋወሩ ወታደሩን በየአለቃው አሰልፈው ከቀኑ 5 ሰዓት ሲሆን ጦርነት ገጠሙ ። ጦርነቱም እንደተጀመረ የንጉሥ ተክለ

ሃይማኖት መድፍ መተኮስ ጀመረ ። ሁለት ጊዜ ያህል ተተኩሶ በሶስተኛው መንኮራኩሩ ተሰባብሮ ወደቀ ። የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሰዎችም ይህን ባዩ ጊዜ ደነገጡ ። መምህር ወልደ ጊዮርጊስ "የሸዋን ጦር ፈረስ አይችለውምና የኛ ሰው በእግር ብቻ ይሰለፍ" ብለው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን አማከሩ ። ምኒልክ ደግሞ የመስታወትን ሠራዊት የወሎን ፈረስ አሰልፈው በምስጢር አኖሩ ። ራስ ጐበናም የምኒልክ ዋና ጦር አዛዥ ነበሩ ።

ጦርነቱ ተፋፍሞ የጥይቱ ጭስ ጠሐይዋን ሲጋርዳት የንጉሥ ተክለሃይማኖት ሠራዊት እንደመናወጥ አለ ። ይህን የሠራዊቱን መበ ርገግ ያዩት የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የጦር አዛዦች ራስ ደረሶና ደጃዝማች ሥዩም በወደቀው ሬሳ ላይ እየቆሙና እየተራመዱ መዋ ጋት ሲጀምሩ ሠራዊቱም በርትቶ ይዋጋ ጀመር ። እንደገና ነገሩ ተገላ በጠና የምኒልክ ጦር በዘመኑ የፈሪ ውጊያ የሚባለውን መሬት ላይ ተኝቶ ይተኩስ ጀመር ። ይህም ቢሆን የጐጃም ጦር ቦታ አስለቀቀ። ወደፊትም ይገፋ ጀመር ።

ከኋላ የነበሩት ንጉሥ ምኒልክ የጐጃም ጦር ወደፊት መግፋ ቱን አይተው ዳኘው ከተባለው ፈረሳቸው ላይ ወጥተው ከውጊያው መሀል ሊያዋጉ ገቡ ። ወዲያውም የጐጃም ተኳሽ የምኒልክን ፈረስ በጥይት አቆሰለው ። የተያዘላቸውንም ግንጥላ በጥይት በጣጥሶ ጣለው። ከፊት ያለውን ግንጥላና ፈረስ ቀርቶ ከኋላ ያለውንም የምኒልክን ድንኳን በጥይት በሳሳው ። ድል ለመሆን ከጫፉ የደረሱት ምኒልክ ደብቀው ያስቀመጡትን የመስተዋትን ሠራዊት የወሎን ፈረሰኛ እንዲዋጋ አዘዙ ። እግረኛና ፈረሰኛ እኩል አይዋጋምና ብዛት ያለው የወሎ ፈረስ እግረኛውን የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ጦር ወረረው ። ብዙ ሰዎችንም ገደሉባቸው ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ጣታ ቸው ተላልጦ እስቲ ቆስል ድረስ ተኩሰው ከብዙ ቦታ ላይ ቆስለው ከውጊያው ወጡ ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከጦሩ መሀል እንደወጡ የምኒልክ አሽ ከር የሆኑት ጐጃሜው የዳሞቱ ባላባት መንገሻ አቲከም በፈረስ ሆነው ደረሱባቸው ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ቆስለው እንደ ወደቁ መን ገሻ አቲከምን በሩቁ ሲያዩ "ናውሰደኝ" ብለው ላኩባቸው ። መንገሻ አቲከምም በክብር እጅ ነስተው የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን እጅ በሻሽ አስረው ወደ ምኒልክ ወሰዱዋቸው ። እንደ ደንቡ አንድ የጦር መሪ ሲማረክ የሚታሰረው በሰንሰለት ወይም በእግር ብረት ሲሆን መን ገሻ አቲከም ግን በሻሽ ያሠሩበት ምክንያት ንጉሥ ተክለ ሃይማ ኖትን በማክበር ነበር ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከብዙ ቦታ ላይ እንደ ቆሳሰሉ ከምኒልክ ዘንድ ቀረቡ ። ምኒልክም ሰውን የመሳብ ኃይል ነበራቸውና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደመጡ ከዙፋናቸው ተነስተው አቅፈው ፣ ስመው "ወንድሜ እንኳን ክርስቶስ በሕይወት አገናኘን" አሉዋቸው። ወዲያውም እኔ ነኝ ቁስሉን የማከምለት ብለው ደማቸውን እየጠራረጉላቸው ውጊያው አልቆመም ነበርና "ሠራዊትህን አስተወኝ ። ያለፈው ይበቃል" አሏቸው ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም በምኒልክ አድራጎት ተደንቀው ነበርና እሺ ብለው ውጊያውን እንዲቆም አዘዙ ። የታዘዘውም ፈረሰኛ "የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሰው የሆንህ ተው ብለውሃል ፣ ንጉሣችሁ ተይዘዋል" እያለ ለፈፈ ። ይህን ልፈፋ ራስ ደረሶ ፣ ደጃዝማች ስዩምና መምህር ወልደ ጊዮርጊስ በሰሙ ጊዜ "ያለ ዮሐንስ ንጉሥ አናውቅም ፤ በለው ። በወሰደበት እጁ መልሶ ይሰጠናል" እያሉ ሲያዋጉ አመሹ ። ቢሆንም ድል የምኒልክ ሆንዋልና የማታ ማታ ራስ ደረሶ ፣ ደጃች ስዩምና መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ተያዙ ። ንጉ ሥ ተክለ ሃይማኖትም ሊቆስሉ የቻሉት ስመ ጥሩ ጀግና ነበሩና ደጀን ሆነው ያዋጉ ቢሏቸው አይሆንም ብለው እንደተራ ወታደር በፈረስ ላይ ሆነው መሐል ለመሐል ገብተው ሲያዋጉ ነው ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሁለት ሰዓት ያህል በጀግንነት እንደተዋጉ ነው ቆስለው የተያዙት ።

በተለይ በኋላ እጨጌ ሆነው የተሾሙት አባ (መምህር) ወልደ ጊዮርጊስ የተመዘዘ ሰይፍ ይዘው "የሸሸህ ገዝቼሃለሁ" እያሉ የጐጃምን ጦር ስላበረቱት ጦርነቱ እስከዘጠኝ ሰዓት ድረስ ቆየ ። በጦርነቱም ላይ ብዙ ሰዎች ሞቱ ። በማግሥቱ ንጉሥ ምኒልክ በጦርነት ላይ የሞተውን የሸዋውንም ፣ የጐጃሙንም ዋና ዋናውን እያስፈለጉ በማስቀበርና ፣ ቁስለኛውንም ሲያስነሱ ዋሉ ። የተሰበሰበውን የሁለቱንም ወገን ቁስለኞች ከሠፈር አሳድረው ከፊታውራሪ ቀዲዳ አገር እየተመራ እንዲታመምና እንዲድን አዘዙ ። ጦርነቱ በተደረገ በሶስተኛው ቀንም ምኒልክ ለጐጃም ምርኮኛ ሁሉ ራስ ጐበናን ባልደረባ ሰጥተው አባይ ድረስ በራስ ጐበና አሸኝተው ወደ አገራቸው እንዲገቡ አደረጉ ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ቁስላቸው የበረታ በመሆኑ በበቅሎ ላይ ተቀምጠው መሔድ ባለመቻላቸው ምክንያት ተኝተው በሰው ሸክም እየተጓዙ ወደ እንጦጦ መልስ ሆነ ። ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር እሳቸው የመረጡዋቸው መኳንንትና 3000 ያህል ወታደሮቻቸው አብረዋቸው እንዲጓዙ ተደረገ ። በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሕመም ምክንያት ጉዞው በቀስታና እየታረፈ ስለነበረ ጦርነቱ በተደረገ በወሩ ሰኔ 29 ቀን እንጦጦ ገቡ ። በጉዞውም ላይ የንጉሥ ተክለ ሃይ

ማኖትን ቁስል ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንደጻፉት "ንጉሥ ምኒልክ ራሳ ቸው በመድኃኒት እያጠቡ በሻሽ ያስሩላቸው ነበር ።...."

እንጦጦ ከደረሱም በኋላ በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እካል እየ ገባ የቀረውን ጥይት የሚያወጣ ሐኪም መጥቶ በአካላቸው ውስጥ የቀረው ጥይት እየተፈለገ ወጣላቸው ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ካረፉ በትም ቤት ምኒልክ በቀን ሁለት ሶስት ጊዜ እየተመላለሱ በመጠየ ቅና ስለምግባቸው ይዞታ እያዩና አብረውም እየበሉ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን በታላቅ ጥንቃቄ አዳኑዋቸው ። አንድ ቀን ራስ ደረሶ፣ ደጃዝማች ሥዩምና ሌሎችም የጐጃም መኳንንት ባሉበት በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ማረፊያ ቤት ግብር ተበልቶ ጠጅ እየተጠጣ ሲጫ ወቱ ምኒልክ የእንባቦውን ጦርነት ሁኔታ አንስተው ጐጃሞች በርት ተው በመዋጋታቸው ካመሰገኑ በኋላ "እንዲያው ለመሆኑ እኔን ብትማርኩኝ ኖሮ እንዴት ታደርጉኝ ነበር ?" ብለው ጠየቁ ። የጐጃም መኳንንቶችም "ቆራርጠን ለአሞራ ነበር የምናበላዎ" አሏ ቸው ። ምኒልክም "ከእናንተ ጭካኔ ከኔ ርህራሄ የቱ ይሻላል ታዲያ" ቢሏቸው "ሲዋጉ ጭካኔ ድል ሲያደርጉ ርህራሄ የሚገባ ነው" ብለው መለሱላቸው ። ምኒልክም በዚህ እውነተኛ መልስ ተደስተው "ከእንግ ዲህ ወዲያ የጐጃሜ እስረኛ የለኝም ። ቤቱ ቤቱ ነው ። አገሬም አገሩ ነው" ብለው አዋጅ አስነገሩላቸው ።

ምኒልክም ለምርኮኛው መኳንንት ሁሉ ለየራሱ የሚኖርበት ቤት ሰጡት ። ምግብና መጠጡም ከምኒልክ ቤተ መንግሥት እንዲ ላክ አዘዙለት ። ንጉሥ ተክለሃይማኖትንም ማለፊያ ሆኖ በተዘጋጀ ቤት አስቀምጠው የንጉሥነታቸው ክብር ሳይጐድልባቸው ቁስላ ቸው በሚገባ እስቲድን እንዲኖሩ አደረጉ ። ለሚፈልጉት ነገር ሁሉ የሚያስፈጽምላቸውም ሻለቃ ተክሌን ባልደረባ ሰጡአቸው ።

የሁለቱ ንጉሶች ውጊያ ቀላል አልነበረም ። አለቃ አፅሜ እንደ ጻፉት ከምኒልክ ሠራዊት 913 ሰዎች ሲሞቱ 1648 ሰዎች ቆስለዋል ። ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሠራዊት ደግሞ ግማሹ ያህል አልቋል ። ይህ ሁሉ ሰው ያለቀው በሶስት ሰዓት የጦርነት ጊዜ ውስጥ ነው ።

የንጉሥ ምኒልክንና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን መዋጋት ሲሰሙ አጤ ዮሐንስ ተናደዱ ። በተለይም ምኒልክ አሸንፈው ተክለ ሃይማኖት በመሸነፋቸው የባሰ ተበሳጩ ። ምክንያቱንም ብላቴን ጌታ ኅሩይ ሲገ ልጹ "አጤ ዮሐንስ በማናቸውም ቢሆን ንጉሥ ምኒልክን የሚወዱ ቸው በመፍራትና በሥጋት ፣ በመጠራጠርም ነበር ። ንጉሥ ተክለ ሃይ ማኖትን ግን ባለመፍራትና ባለመሥጋት ወገኔ በማለት ይወዷቸው ነበር ይባላል .... ።" ብለዋል ። ይህም በመሆኑ አጤ ዮሐንስ ምናልባት

የተክለሃይማኖት ኃይል ቢያንስ እርዳታ ለመስጠት "....እኔ ወደ ደብረ ታቦር ሳልዘልቅና ተዋጋ ብየ ሳላስታውቅህ ምንም ቢሆን ጦርነት እንዳትገጥም" የሚል ደብዳቤ ጽፈው ልከውባቸው ነበር ። ይህን ቃል የያዘው ደብዳቤ ግን ቀደም ብለን እንዳነበብነው ሽፍታው ደስታ ኃይሉ ወይም ራስ ደረሶ አስቀሩት የተባለው ነው ።

አጤ ዮሐንስ ከግብፅ አገር አራት ጳጳሳት አስመጥተው ስለነበረ ምኒልክና ተክለ ሃይማኖት እንዳይዋጉ ጳጳሳቱ የውግዘት ቃል እንዲልኩባቸው አዘው ጳጳሳቱ የላኩት የውግዘቱን ቃል የያዘው ደብዳቤ ዘግይቶ ከጦርነቱ በኋላ ደረሰ ። ንጉሥ ምኒልክም የጳጳሳቱን ውግዘት የያዘው ደብዳቤ ከደረሳቸው በኋላ ከእንጦጦ ከተማቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለጳጳሳቱ ጻፉ ።

ትብጻህ ኀብ ልዑላን ወኀሩያን በኀበ እግዚአብሔር አቡነ ጴጥሮስ ። ለአቡነ ማቲዎስ ። ለአቡነ ማርቆስ ። ለአቡነ ሉቃስ ዘኢትዮጵያ ። ብርሃናቲ ዓለም ወሐዋርያቲሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወወሉዱ ለማርቆስ ወንጌላዊ ።

የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ ። እዓመኀከሙ በአምሃ መንፈሳዊት በአኃሥሥ በረከትክሙ ከትረፍአ ለኩሉ ፍጥረት ። እነ ዳህን ወሰላም በጸጋሁ ለእግዚነ ፀባኦት ወበስዕለተ ለእግዚእትነ ወላዲተ ሕይወት ።

በሰኔ 2 ቀን የተጻፈ የውግዘት ደብዳቤአችሁ በተዋጋን በ20 ቀን ደረሰልኝ ። እኔም ንጉሥ ተክለሃይማኖትን ለመውጋት አልፈለግሁትም ነበር ። እርሱ ፎክሮ ከወደ ኋላዬ ገስግሶ ቢመጣብኝ አልሞት ባይ ተጋዳይ እንደሚባለው ዞሬ ተዋጋን ።

እኔ ግን ለመውጋት ፈልጌው እንደሆነ ያወገዛችሁትም ፣ የረገማችሁትም ይድረስብኝ ። ደግሞ ክርስቲያን ለክርስቲያን በመዋጋታችን ጃንሆይን አስቀይመን ይሆናል ። የጃንሆይም ልቡና እንዳይለወጥብኝ ስለሥላሴ ብላችሁ አስምሩኝ እንጂ በደለኛውንስ እኔ በዋቢ ስመጣ እዚያው ከጃንሆይ ፊት ታገኙታላችሁ ።

ሐምሌ ፩ ቀን ፲፰፻፸፪ ዓ. ም. ተጻፈ ።

አጤ ዮሐንስም ደብረ ታቦር ላይ ሳሉ ሁለቱ ንጉሦች መዋጋታቸውን ከሰሙ በኋላ መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው "ከክረምት በኋላ ወደ ሸዋ እንዘምታለንና ከብታችሁን እያጠነከራችሁ ክረሙ" ብለው አዘዙ ። ከመኳንንቱ የሚበዙት "ንጉሥ ምኒልክ እንኳን የጐጃምን

መሣሪያ ጨምረው ፣ እንዲያውም የሚያስፈሩ ሆነዋልና አሁኑን ቁስ ለኛው ሳይሽር ፣ የደከመው ሳይበረታ ፣ ገመምተኛው ሳይነሳና ሳይ ጠነክር ብንደርስባቸው ይሻላል እንጂ ክረምት ውጭስ አንችላቸ ውም'' ብለው ስለመከሩዋቸው ሰኔ ሲያልቅ ሐምሌ ሲገባ ከደብረ ታቦር ተነስተው በእማሐራ ሳይንት በኩል ተጓዙ ።

ሳይንት ሲደርሱ ንጉሥ ምኒልክ አስረው በአትርጎስ ማርያም ያስቀመጡትን ደጃች መሸሻ ሰይፉን ፈትተው እርሱን መንገድ መሪ አድርገው ለጋምቦንና ወሎን እያዘረፉ ወረይሉ ገቡ ። ደጃች መሸሻ ሰይፉን ከታሰረበት ፈትተው ማውጣታቸው የንጉሥ ምኒልክ ባላንጣ መሆኑን ያውቃሉና ማስፈራሪያ እንዲሆናቸው ነበር ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ግን ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ታርቀው ወዳጅ ሆኑ ።ምንም እንኳ ወዳጅ ቢሆኑ አጤ ዮሐንስ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ማድላታቸውን ስለሚያውቁ የተዋጉበትን ምክንያት አስቀ ድመው ለማሳወቅ ምኒልክ ወደ አጤ ዮሐንስ መልክተኞች ላኩ ። ምኒልክ የላኩዋቸው መልክተኞች የሚያመጡትን መልስ ሲጠብቁ አጤ ዮሐንስ በክረምቱ ወራት በውሃ ሙላት ወደ ወሎ መምጣታ ቸው ተሰማ ። ንጉሥ ምኒልክም በዚህ ሁኔታ ሲደነቁ ወደ አጤ ዮሐ ንስ የላኩዋቸው መልክተኛ ከአጤ ዮሐንስ ዘንድ ደብዳቤ ይዘው መጡ ።

መልእክት ዘሥዩም እግዚአብሔር ዮሐንስ ፣

ንጉሠ ጽዮን ፣ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ከንጉሥ ምኒልክ ። በአማን እስራኤላዊ ዘአልቦ ጽልሁት ሰላም ለከ ። ወሰላም እግዚአብሔር የሃሉ ምስሌከ ። እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት በእምነ ጽዮን አማላጅነት አምላክ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ደህና ነኝ ። ምህረቱ ለዘላለም ነውና ።

በጌምድር ሳለሁ ሁለቱ ነገሥታት ተዋግተው ድል ለንጉሥ ምኒልክ ሆነ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትንም ይዘው ወደ ሸዋ ተጓዙ ሲሉ ብሰማ እግዚአብሔር የፈቀደውን ሰርቷል ብዬ የክርስቲያን ደም በማይረባ ነገር በመፍሰሱ የእናንተን ደብዳቤ ስጠብቅ ደብረ ታቦር ላይ ወር ሙሉ ተቀመጥሁ ። ኋላ ግን ወሬያችሁ ቢጠፋብኝ ይህስ ነገር አለበት ብዬ ስመጣ ሳይንትን ሳልፈው የንጉሥ ወረቀት ደረሰልኝ ። ደብዳቤውንም አይቼ መዘግየቱ በመንገዱ ርዝመት እንጂ ሌላ ተንኰል አለመኖሩን ባወቅ ወደ በጌምድር ለመመለስ አሰብሁ ። ነገር ግን ክረምቱ ተጭኗልና ሠራዊቱ የሚጐዳብኝ ሆነ ።ስለዚህ

በወሎ እንድከርም ፈቃድ ይደረግልኝ ። እኔም አገር አልበድልም ። በጥቢ ተገናኝተን ሁሉንም ነገር ተማክረን ወደ በጌምድር መመለስ ይሻላል ብዩ ነው እንጂ ሌላ ጉዳይ ኖሮኝ አይደለም ።

ደግሞ ይህ የሚያሳዝን ነገር ቢሆን ፥ ተመልሼ ሠራዊቱ በውሃ ሙላት ፥ በጭቃ ያለቀው አልቆ የተረፈውን ይዤ መመለስ ይሻለኛል ።

ሐምሌ ፲ ቀን ፲፰፻፸፬ ዓ. ም. ።

ይህ የአጤ ዮሐንስ ደብዳቤ እንዲያው ለይስሙላ የተጻፈ እንጂ አንድ ንጉሠ ነገሥት ለበታቹ ወይም ለታዛዡ የሚጽፈው ደብዳቤ አይደለም ። አንደኛ ፥ የመላው ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነው በበታች ግዛታቸው በወሎ እንድከርም ይፈቀድልኝ ማለታቸው ፥ ሁለተኛ ፥ የማይፈቀድልኝ ቢሆን ሠራዊቱ በውሃ ሙላት ያለቀው እያለቀ ወደ በጌምድር እመለሳለሁ ማለታቸው ሲታይ የለበጣ ወይም የጊዜ ማሳለፊያ ይመስለኛል እንጂ አንድ ንጉሠ ነገሥት በገዛ ግዛቱ ውስጥ የመቆያ ፈቃድ መጠየቅ የለበትም ። ንጉሥ ምኒልክም ይህ የአጤ ዮሐንስ ደብዳቤ እንደደረሳቸው “.... ጃንሆይ መጥተው ወደ ወሎ ከቀረቡ ሳንገናኝ እንከርምምና ወደዚያው እመጣለሁ ። ከድንኳንም ቤት ይሻላልና ወረኢሉ ከኔ ቤት ገብተው ቢከርሙ ይሻላል” የሚል ደብዳቤ ሐምሌ 10 ቀን 1874 ዓ.ም. ጽፈው ለአጤ ዮሐንስ ላኩ ።

አጤ ዮሐንስ የሁለቱን ንጉሦች ጉዳይ ለማየት ምኒልክ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ይዘው እንዲመጡ ልከውባቸው ነበርና ንጉሥ ምኒልክ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ይዘው ሐምሌ 14 ቀን ከእንጦጦ ተነስተው በደብረ ብርሃን አድርገው ደጋ ደጋውን በመጓዝ ነሐሴ 6 ቀን ወረኢሉ ደረሱ ። አጤ ዮሐንስም ጠመንጃ እያስተኰሱ በታላቅ ክብር ተቀበሉዋቸው ።

ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከአጤ ዮሐንስ ዘንድ እንደደረሱ ተጣልተው በጦርነት የተፈታተኑ ባላጋራ መሆናቸው ቀርቶ ፍጹም የሚዋደዱ ፍቅረኞች ሆነው ታዩ ። አጤ ዮሐንስ ግን የሚጠብቁት ከሁለቱ አንዱ አንደኛውን ከሳሽ ሆኖ ፍርድ ለመጠየቅ ከፊታቸው የሚቀርቡ መስሏቸው ነበር ። ስለዚህ አጤ ዮሐንስ ሁለቱንም ንጉሦች አቅርበው ፥ “.... ቃሌን ጥሳችሁ ስለምን ተዋጋችሁ” ብለው በቁጣ ቃል ወቀሱዋቸው ።

ንጉሥ ምኒልክ “እምቢ ብሎ ገፍቶ መጥቶ ያለውድ በግድ ገጠመኝ” አሉ ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም “አሽከሮቼ ያቀኑትን አገር

ቀምተው ምርኮውን ሁሉ እጅ አድርገው ለጃንሆይ የላኩሁት ደብ ዳቤ መልሱ ቢቀርብኝ አገሬን ገንዘቤን አልሰጥም ስል ተዋጋሁ" ብለው ተናገሩ ። አጤ ዮሐንስም "አትዋጉ ብዬ የላኩትን ደብዳቤ ምን ወሰደው?" ብለው መልክተኞቹን ጠየቁ ። መልክተኞቹም "ደስታ ኃይሉ የሚባል ሽፍታ ከመንገድ አስሮ ደብዳቤውን ቀማን" አሉና መለሱ ። ከዚህ በኋላ የደስታ ኃይሉ ተንኮል ተገልጦ አጤ ዮሐን ስም "ማኅተም ቀምቶ ሕዝቡን ባስፈጀበት እቀጠዋለሁና ከተቀ መጠበት ቦታ እጁን አስይዝ" ብለው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን አዘዙ ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና ንጉሥ ምኒልክ ትእዛዝ ጥሰው በመዋ ጋታቸው ሠራዊቱን ባስፈጁበት መቀጫ ከንጉሥ ምኒልክ ወሎን ወስ ደው ለራስ አርአያ ሥላሴና ለራስ ሚካኤል ሰጡባቸው ። ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ደግሞ ሰባት ቤት አገውን ወስደው ለራስ አሉላ ሰጡ ። ከዚህም በቀር ንጉሥ ምኒልክ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር በተዋጉ በት በእንባቦ ዘመቻ ጊዜ የማረኩትን መድፍና መሣሪያ ሁሉ ለራስ አሉላ እንዲያስረክቡ አጤ ዮሐንስ አዘዙዋቸው ። ምኒልክም በዚህ ትእ ዛዝ በጣም ቢያዝኑም ቅር እያላቸው አስረከቡ ። ወዲያው ለንጉሥ ተክለሃይማኖት ሊመልሱላቸው ነው እየተባለ ስለተወራ የሸዋ መኳ ንንት ሁሉ ገና በወሬው አዘነ ።

ሁለቱ ንጉሶች ማለት ምኒልክና ተክለ ሃይማኖት ከአጤ ዮሐ ንስ ተሰናብተው በቶሎ ወደ አገራቸው ለመመለስ ፈለጉ ።ቀድመ ውም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወደ አጤ ዮሐንስ ዘንድ ገብተው "እባክዎ ጃንሆይ ፣ ወደ አገሬ እንድገባ ይፍቀዱልኝ" ብለው ቢለም ኑዋቸው "ወደ አገሬ ልግባ የምትለኝ መቼ ማርሁህና ነው ። አሁንም ስለጥፋትህ ሁሉ ምህረት እንዳደርግልህ ንጉሥ ምኒልክን አማላጅ ላክብኝና ከዚያ በኋላ አሰናብትሃለሁ" አሏቸው ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ይህንኑ ለንጉሥ ምኒልክ ነግረው "እባክዎ ከልብ ያስታርቁኝ" ብለው ለመኑዋቸው ። ንጉሥ ምኒልክም ጉዳዩ ሳይ ገባቸው እሺ ብለው ለአማላጅነት ወደ አጤ ዮሐንስ ዘንድ ገቡ ። ". . . . እባክዎ ጃንሆይ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ከልብዎ ይታረ ቁትና ወደ ሀገሩ ይግባ" ብለው ቢለምኗቸው "እኔ ባነግሰው እርሱ በጥጋቡ ለቆታልና መንግሥት አይገባውም ነበር ። ነገር ግን ንጉሥን አማላጅ ከላከ ምን ይደረጋል ።ትናንትም ንጉሥ አድርገን ዛሬ ብንሽ ረው ለኛም አያምርልንምና ምሬዋለሁ ። ዳሩ ግን ንጉሥ ሆኖ ያለ መሣሪያ በጆሌ ወታደር ታጅቦ ወደ ሀገሩ ቢገባ ውርደቱ ለኛው ነውና የተማረከበት መድፉም ፣ ነፍጡም እንዲመለስለት ይሁን. . . ." አሏቸውና ምኒልክ በድንጋጤ አዘኑ ።

ምኒልክ በደረሰባቸው ነገር ሁሉ ቢያዝኑም ያልተከፉ በመምሰል ከአጤ ዮሐንስ ጋር ቆይተው አቡነ ማቴዎስን ለሸዋ ጳጳስነት ተቀ ብለው የካቲት 2 ቀን 1875 ዓ. ም. ከቦሩ ሜዳ ተነስተው የካቲት 24 ቀን ልቼ ከተማቸው ገቡ ። ወደ ደብረ ብርሃንም ሄደው ልብሰ መንግሥት ለብሰው ፣ ዘውድ ጭነው ፣ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስም የጵጵስና ልብሳቸውን ለብሰው ታላቅ በዓል ተደረገ ።

ምኒልክ በግዛታቸው መቀነስ ተናደዱ ። ሆኖም አሳባቸውን በሆዳቸው ይዘው ሰላማዊ መስለው መታየት ጀመሩ ። አጤ ዮሐንስ አል በገር እያለ ያስቸገራቸውን የምኒልክን ኃይል በጋብቻ ለመተሳሰር አስበው ልጃቸውን ለልጃቸው እንዲድሩላቸው ጠየቁ ። ለጋብቻው አማላጅነትም ራስ አሉላ ፣ ራስ ገብረ ኪዳን ፣ ቢትወደድ ገብረ መስቀል ካጼ ዮሐንስ ተልከው ወደ አጤ ምኒልክ መጡ ። "ልጅዎን ወይዘሮ ዘውዲቱን ለልጄ ይስጡልኝ ብለዋል...." ብለው ነገሩ ። ንጉሥ ምኒልክም እምቢ ማለት ስለማይችሉ ጋብቻውን ፈቅደው የስድስት ዓመት ዕድሜ ያላት ዘውዲቱ ፣ 12 ዓመት ዕድሜ ላላቸው ለአርአያ ሥላሴ ተዳሩ ።

ዮሐንስና ምኒልክ በሥልጣን ሽሚያ ላለመፈላለግ በጋብቻ ቢተሳሰሩም የዮሐንስ ጫናና የምኒልክ የግልበጣ ሐሳብ አልቀረም ። ምኒልክ የጦር መሣሪያ ፍላጐታቸው አልገታ አለ ። ማሳዣ እንደጸፉትም በዓመት እስከ አንድ ሚሊዮን ብር ለመሣሪያ መግዣ ወጭ ያደርጉ ጀመር ። ይህን የምኒልክን የጦር መሣሪያ ፍላጐት ያለመገታት ያወቁት አጤ ዮሐንስም ምኒልክ ከውጭ መንግሥታት እንዳይገናኙና የጦር መሣሪያም ወደ ሸዋ እንዳይገባ በሩን ሁሉ ዘጉባቸው ።

ምኒልክ በእንዲህ ዓይነቱ ችግር መሀል ሲዋልሉ አለቃ ብሩ የተባሉ ሰው ከአጤ ዮሐንስ ከድተው ወደ ምኒልክ ዘንድ መጡ ። አለቃ ብሩ ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ከተገናኙ በኋላ የባህሩን በር ከያዙት ግብጾች ጋር ቢወዳጁ የበለጠ ጥሩ ውጤት እንደሚገኝ ምኒልክን መከሩዋቸው ። በአለቃ ብሩ ምክር የተስማሙት ምኒልክም ፣ የአባ ቡርቃ ፓሻን ልጆች ወደ ካይሮ ልከው ከከዲቩ ጋር ወዳጅነት መሠረቱ ። በኋላም አለቃ ብሩን ከሙዚንጀር ጋር ወደ ካይሮ ልከው ወዳጅነታቸውን አጠናከሩ ።

ምኒልክ ከባላንጣቸው ጠላት ከግብፅ ጋር ወዳጅ ይሁኑ እንጂ ከዚያ በፊት ግብጾች የኢትዮጵያን ክፍል ቆርሰው ይዘው ነበር ። በሰሜን በኩል ከአጤ ዮሐንስ ጋር እየተዋጉ ወሰን ቢገፉም ፣ በምሥራቅና በደቡብም ከኢትዮጵያ ቆርሰው ይዘው ነበር ። ለምሳሌ ንጉሥ ምኒልክ በ1868 ዓ.ም. ሰኔ 10 ቀን ከልቼ ከተማቸው ለግብፅ ኢስማኤል ፓሻ የጻፉት ደብዳቤ እንዲህ ይላል ። "....መልካም ሥራ

ትና ጥበብ ንግድም በአገሬ አገባለሁ ብዬ ዠምሬአለሁ ። ዳግመኛም ከጐረቤቶቼና ከአውሮፓ ነገሥታት ወዳጆቼ የፍቅር መገናኘትን ፣ ውልንም ላደርግ እፈልጋለሁ ። ይህም እስከ ባህር ድረስ መንገድን በመክፈት ነው ። የርስዎ መንግሥት ምክር ለኔ ሥራ በርን የሚደፍን መሰለኝ ። ጐረቤቶቼን ሊዋጉ የመጡ የርስዎ ወታደሮች በኢትዮጵያ ደቡብ በኩል አገሬን ተዋጉት ። ዛሬም አላረፉም ። ከኒያ የተከፈሉት ተጕሪን* ያዙት ። አውሳንም ጨዉንም ያዙት ። የሸዋ መንግሥት የጋ ላን አገር ይዞ የነበረ ፣ አዳሉም ፣ ሐረርጌም በእርስዎ ወታደሮች እጅ ሆነ ። ዛሬ ጦሩ ባጠገባችን ነው ። ሶስተኛ ጦር በነጭ አባይ መጥቶ በጋላ አገር ታየ ይሉናል ። በሐረርጌና በዘይላ የወጣው ከላይኛው ጦር ጋራ ጉራጌ ላይ እንዲገናኙ ተቃጥረዋል ይባላል ። ይህም ምስጢር አይደለም ። ጉራውጌውም የኔ ግዛት ነው ።

“አሁን ይህን ምን እንበለው ። የወታደሮችዎ ሥራና የወዳጅነት የፍቅር የሚያሳይ የደብዳቤ ቃል የተካከለ አይመስለኝም ። እጅግ የሚ ያስፈራ ነገር ነው ። በዚህም እጅግ አዝኛለሁ ። ነገር ግን እርስዎ እኔን ወዳጅዎን አለ ብልሃት ፣ አለ ሥልጣን መጥተው ይወጉኛል አይመስ ለኝም ። አገሬ ድረስ መጥተው ። ለጊዜው ብቻ አሳዘነኝ እንጂ ። ነገር ግን ኢትዮጵያ በእናንተ ጦር መከበብዋን ማሳየት ይገባናል ።

“ዛሬ በባህረ ኤርትራ ያሉ በርሮች ፣ በሕንድ ውቅያኖስም ያሉ በርሮች ወደኛ ከጨርቅ በቀር ሌላ እንዳይመጣ ከለከሉ ። ነፍጥና ባሩድ ፣ የወታደር መሣሪያ ሁሉ ለመጠባበቂያ የሚሆን ሁሉ በእውቅ ተከለከለ ።

“የግብጻውያን ጦር አገሩን ሁሉ ከበበው ። ጥቂት ቀይቶ አዋሽ ሊገቡ ነው ። ከኔ ግዛት ላይ ። ይህ የሆን እንደሆነ የፈራሁት ሁሉ ደረሰ። .... ለመንገዱ ፣ ለበሩ ሳንከለከል በተጕሪ አውራጃ ያለ መሀከለኛው መንገድ በመሀል እንዲኖርልን ። የንግድም ዕቃ ሁሉ ይህ ይቅር ሳይባል ከወዲያ የሚመጣ ሁሉ ከዚህም የሚሄደው ሁሉ መሄድና መምጣት እንዳይከለከልብን ። በበሩ ሁሉ ፣ በመንገዱ በወታደሮችዎም እጅ እንዳ ይያዝብን ። የኔ መልካም ፈቃድ ፣ መልካም ምኞት ማሰናከያ እንዳያ ገኝ .... ስለዚህ መልካም ፍሬ ከእርስዎ እንዲያገኝ ተስፋ አለኝ ....” የሚል ደብዳቤ ሲልኩ ማኅተማቸውም ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢ ትዮጵያ የሚል ነበር ።

የኢትዮጵያ መሳፍንት በእንዲህ ዓይነቱ የሥልጣን ሽሚያ በሚ ራኰቱበት ወቅት የሐማሴን መኳንንት ከሐማሴን ግዛት እየቀረሰ ለኢ ጣሊያ ይሰጥና ይሸጥ ጀመር ።

---

* ተጕሪ የሚለው—ታጁራን ነው ።

የንጉሥ ምኒልክ መኳንንቶች በዔታቸው መበደል ምክንያት በተለይም ከእንባቦ የተማረከው መሣሪያ በመመለሱ ይቆጩ ነበርና አንገብር እንዋጋ እያሉ ንጉሥ ምኒልክን ይወተውቱ ጀመረ ። ምኒ ልክ ግን የመዋጋቱ ሀሳብ ቢኖራቸውም አጤ ዮሐንስ ብዙውን መኳ ንንት በወዳጅነት ይዘውት ስለነበረ አቅማቸውን ገምተው መዋጋቱ እንደማያዋጣቸው አውቀው የመኳንንቶቻቸውን ምክር ሳይሰሙ ቆዩ ። አጤ ዮሐንስ እንደሚያደርጉት ሁሉ ንጉሥ ምኒልክም አጤ ዮሐንስ በወዳጅነት የያዙዋቸውን መኳንንቶች ለማላቀቅ ይጥሩ ጀመር። በመጀመሪያም በኃያልነታቸው የታወቁትን የጐጃሙን ንጉሥ ተክለ ኃይማኖትን ከአጤ ዮሐንስ ለማላቀቅ ሞከሩ ።

በ1880 ዓ.ም. የውጭ ጠላት በሁለት በኩል ኢትዮጵያን ከበበ። ባንደኛው በኩል ኢጣሊያኖች ሲሆኑ በሌላው በኩል ደግሞ ደርቡ ሾች ነበሩ ። አጤ ዮሐንስም ታላቁን የኢጣሊያን ጦር ለመው ጋት ወደ ሰሐጢ ሲሔዱ ፣ በጐንደር በኩል የመጣውን የደርቡሽ ጦር ደግሞ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወደ በጌምድር ሔደው እንዲጠባበቁ አዘዙዋቸው ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደታዘዙት ሠራዊታቸውን አስከትለው ወደ በጌምድር ሔደው በቀልት ከተባለ ቦታ ሆነው ይጠ ባበቁ ጀመር ።

የደርቡሾችም ጦር በዚያው ዘመን ደንቢያ ድረስ ገብቶ ጥር 10 ቀን ሣር ውሃ ከሚባል ሥፍራ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሠራዊት ጋር ጦርነት ገጠመ ። የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሠራዊትም በመጀመሪያ ድል ካደረገ በኋላ እንደገና የደርቡሽ ጦር በርትቶ በመዋጋቱ የን ጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ሠራዊት ድል አደረገው ። ንጉሥ ተክለሃይማ ኖትም ከልጃቸው ከራስ በዛብህ ጋር በፈረስ አምልጠው በደንገል አድርገው ጐጃም ገቡ ። ሌላው ልጃቸው ደጃዝማች በለው ደግሞ ጳጳ ሱን አቡነ ሉቃስን ይዘው በፎገራ በኩል ሸሽተው ጐጃም ደረሱ ። በዚህ ትርምሱ በወጣ ጦርነት ከአባቴ አልለይም ብለው አብረው ዘምተው የነበሩት የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሴት ልጅ ወይዘሮ ምን ትዋብ በደርቡሾች ተወሰዱ ። የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሠራዊትም አብዛኛው በሰይፍ እየታረደ ሲያልቅ የተረፈውም ሸሸ ። በሚሸሸው ላይም አባራሪው ደርቡሽ ሲደርስበት ሸሺው ከጣና ባህር እየገባ አለቀ ። በዚያ ጦርነት ደርቡሾች ስምንት ሺ ያህል ሰዎች ማረኩ ። ጐንደር ከተማ ገብተውም 47 አብያተ ክርስቲያናት አቃጠሉ ። ወደ ጐንደር በሚጓዙበት ጊዜም 200 ያህል ቤተ ክርስቲያን አቃጥለዋል ።

ይህ በሆነበት ጊዜ ንጉሥ ምኒልክ ወሎ ውስጥ ነበሩ "…. ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከደርቡሽ ጋር ተዋግተው ድል ሆነው ወደ አገራ

ቸው ጐጃም ተመለሱ ።....” የሚል ወሬ ምኒልክ እንደሰሙ እንደገና ደርቡሽ ተመልሶ እንዳያጠቃ የካቲት 7 ቀን 1880 ከቦሩ ሜዳ ተነስ ተው መጋቢት 1 ቀን ደብረ ታቦር ገቡ ። በደብረ ታቦር ከተማም ጥቂት ቀናት ቆይተው ወደ ጐንደር ተጓዙና እዘዞ ሲደርሱ ሚያዝያ 11 ቀን ሠራዊታቸውን በሙሉ አሰልፈው የተኩስ ትርኢት ተመ ለከቱ ። ምኒልክ ንጉሥ ከተባሉበት ጊዜ ጀምሮ ይሄን ያህል ሰልፍ አላሳዩም ይባላል ። የደርቡሽ ሰላዮችም ይህንኑ አይተው ለበላዮቻ ቸው ታላቅ ኃይል መምጣቱን አሳወቁ ። ምኒልክም እምባጫራ ወር ደው የደርቡሽን መምጣት ሲጠባበቁ ደርቡሾች ፈርተው መተማን ከማጠናከር በስተቀር ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ሳይገቡ ቀሩ ።

ንጉስ ምኒልክ እምባጫራ ሆነው ሲጠባበቁ አጤ ዮሐንስ ከሰ ሐጢ ጦርነት ተመልሰው መቀሌ ገብተው ነበርና “....የደርቡሽ መልክተኞች ጐንደር መጥተው ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ተገናኝተው በምስጢር ተነጋግረው ተመለሱ....” የሚል ወሬ ተነገራቸው ። አጤ ዮሐንስ ይህን ሲሰሙ ተናደዱ ። “በኔ ላይ ከኢጣሊያኖች ጋር መዋ ዋሉ አልበቃው ብሎት እንደገና ደግሞ ከደርቡሾች ጋር መመሳጠር ከጀመረ የንጉስ ምኒልክ ሐሳብ ከኔ ጋር ለመጣላት ሳይሆን አይቀ ርም” ብለው “.... ከእንግዲህ ወዲህ በመጣችሁበት መንገድ ወደ አገራችሁ ተመለሱ....” የሚል ደብዳቤ ለንጉሥ ምኒልክ ላኩባቸው።

ምኒልክ ይህ ደብዳቤ እንደደረሳቸው አጤ ዮሐንስ ለጠብ እንደ ፈለጉዋቸው ገባቸው ። ወዲያውም መኳንንቱን ሰብስበው ደብዳቤ ውን ካስነበቡ በኋላ በተደረገው ምክር አንዳንዶቹ እንደአዘዙን በመ ጣንበት በወሎ እንመለስ የሚል አሳብ አቀረቡ ። ምኒልክ ግን “በመጣ ሁበት መንገድ ስመለስ ገስግሰው መጥተው ቢቆዩኝሳ ፣ ዳግመኛ እጅ ልንሳ ? ያውም ለወቀሳ ፣ ለከሰሳ ። ይህስ የማይሆን ነገር ነው ። ....” ብለው በዘዴ ተለማማጭነታቸውን ለማሳየት ጭምር “....እባክዎ ጃንሆይ በጐጃም አድርጌ ወደ ሸዋ እንድመለስ ይፈቀድልኝ ....” የሚል ደብዳቤ ወደ አጤ ዮሐንስ ላኩ ።

አጤ ዮሐንስም ደብዳቤው እንደደረሳቸው መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው ተመከረበት ። በምክሩም “....በጐጃም አድርገው ወደሸዋ ለመመለስ ቁርጥ አሳብ አድርገው እንደሆነ በመጡበት ይመለሱ ብንላቸው አይመለሱልንም ። ብንገሰግስም እንደርስባቸውም ። በዚህም ላይ ሠራዊታችን በሰሐጢ ዘመቻ ተጐድቷልና አንችላቸውም ። ስለ ዚህ በጐጃም እንዲሄዱ ቢፈቀድ ይሻላል. . . .” ተብሎ ተመከረና በጐ ጃም ይሂዱ የሚል ፈቃድ ተጻፈላቸው ። ለንጉስ ተክለ ሃይማኖትም “....ንጉስ ምኒልክ በጐጃም ሲያልፉ መንገድ አትከልክሉ ። ስንቅም ስጥ....” የሚል ደብዳቤ ተላለፈላቸው ።

ንጉስ ምኒልክ እንደተፈቀደላቸው ተጉዘው ጐጃም ሲደርሱ ንጉስ ተክለ ሃይማኖት በቋፍ ነበሩና ምኒልክን ጠርጥረውና ፈርተው ሸሹ ። ምኒልክም በሰላም ለማለፍ መምጣታቸውን ከላኩባቸው በኋላ ንጉስ ተክለ ሃይማኖት መጥተው ከምኒልክ ጋር በፍቅር ተገናኙ ። ምኒልክም ሆኑ ተክለ ሃይማኖት አጤ ዮሐንስን ለመጣል ወዳጅ መስ ለው ይተባበሩ እንጂ ውስጥ ውስጡን እርስ በራሳቸውም አይተማመ ኑም ነበር ። ለምሳሌ ጄኔራል ባራቲየሪ ለኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒ ስቴር ፌብራዮ 3 ቀን 1895 በጻፈው ደብዳቤ "....ተክለ ሃይማኖት የምኒልክ የውስጥ ጠላት ነው...." ብሏል ።

ምኒልክ ጐጃም እንደገቡ ንጉስ ተክለ ሃይማኖት ታላቅ ግብር አዘጋጅተው ጋበዙ ።ግብሩ በሚበላበት አዳራሽ ውስጥ ከፍ ካለ ቦታ ላይ ሶስት ዙፋን ተዘርግቶ ነበር ።በአንደኛው ዙፋን ንጉስ ምኒልክ ሲቀመጡ በሌላው ደግሞ ንጉስ ተክለ ሃይማኖት ተቀመጡ ። ከመሀ ላቸው ያለው ሶስተኛው ዙፋን ግን በጣም አምሮና አጊጦ የአጤ ዮሐን ስ ዙፋን ነው ተብሎ ባዶውን ተቀምጦ ነበር ። ለመሰንበቻውም ዙፋኖቹ በዚሁ ሁኔታ ቆዩ ።

ምኒልክ በጐጃም ውስጥ በሚዘዋወሩበት ጊዜ በየደረሱበት ቦታ ሁሉ ሕዝቡ በሆታና በእልልታ እየተቀበለ አጤ መሆኛዎ ደረሰ እያለ ይዘፍንላቸው ነበር ። ሁለቱ ንጉሶች በአጤ ዮሐንስ ላይ ለማድ ረግ ያሰቡትን ነገር በምስጢር ተነጋግረው ሲጨርሱ ንጉስ ምኒልክ "....ከደርቡሽ ጋር ስትዋጋ የጦር መሣሪያህ ተማርኮብሃልና ስለ እርጥባን ነው ።...." ብለው ሁለት መድፎችና 250 ጠመንጃ ለንጉስ ተክለ ሃይማኖት ሰጡዋቸው ። ንጉስ ተክለ ሃይማኖትም ለመሰነባበቻ ብለው ለንጉስ ምኒልክ ግብር አበሉ ። ግብሩ በሚበላበት አዳራሽ ውስጥ በፊት ከነበሩት ሶስት ዙፋኖች እንደኛው ፣ መሀል ያለው የአጤ ዮሐንስ ዙፋን የተባለው ተነስቶ የሁለቱ ዙፋኖች ብቻ ተቀምጠው በመታየታቸው የጐጃምና የሸዋ ሰው ነገር እንዳለበት አውቆ በጉዳዩ ተደነቀ ። ምኒልክም በግንቦት መጨረሻ እንጦጦ ገቡ ።

ሁለቱ ንጉሶች ያደረጉት ስምምነትም አጤ ዮሐንስ መጀመሪያ ወደ ጐጃም የዘመቱ እንደሆን ንጉሥ ምኒልክ በቤጌምድር መጥተው በጀ ርባ ሊወጉ ፣ አጤ ዮሐንስ ወደ ሸዋ የዘመቱ እንደሆን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በቤጌምድር መጥተው በጀርባ ሊወጉ ተማምነው ነበር ። በዚህ ምክር ተስማምተው ከተለያዩ በኋላ ለአጤ ዮሐንስ አንገብ ርም ብለው ግብር ሳይከፍሉ ቆዩ ።

ይህን ምክርና የክዳት አድማ አጤ ዮሐንስ ሲሰሙ ተናደዱ ። ከምኒልክ ይልቅ አቅማቸው ዝቅ ያለውን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን

ለይቶ ለመምታት ደርቡሽን እወጋለሁ በሚል ሰበብ በ1880 ዓ.ም. በክረምቱ በነሐሴ ወር አጤ ዮሐንስ ወደ ጐጃም ዘመቱ ። የአጤ ዮሐ ንስን መዝመት የሰሙት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ለጦርነት ይዘ ጋጁ ጀመር ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ስንቃቸውንና መሣሪያቸውን አዘጋጅ ተው በጅብላና በመተራ ካሉ ምሽጐች ገብተው ተቀመጡ ። የጐጃሙ ጳጳስ አቡነ ሉቃስም አስታርቃለሁ ብለው አጤ ዮሐንስ ወዳሉ በት ጉሊት ሔዱ ። በዚያም በማስታረቁ ጉዳይ ሲጥሩ ከረሙ ። አጤ ዮሐንስ ግን ወደፊት መጥተው ጉዛምን ላይ ሠፈሩ ። መድፎቻቸ ውንም በጭምትና በማይ አፋፍ ላይ ጠመዱ ። ከዚያም ሆነው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ያሉበትን ምሽግ ለመስበር መድፎቹ ሲተኮሱ ጅብ ላን እያለፉ ይወድቁ ጀመር ። ቀላል መድፎች በቅርብ የሚመቱት ሲተኮሱም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ያሉበትን ምሽግ ገደሉን እየ መቱ ይቀሩ ጀመር ። የንጉስ ተክለ ሃይማኖት የመድፍ ተኳሾች አለቃ የሆነው ባሻ አስናቀ ግን ጅብላ ሆኖ ጭምት ላይ ከተጠመ ደው መድፍ አስተካክሎ ሲተኩስ ጥይቱ በመድፉ አፍ ገብቶ መድ ፉን በመገልበጡ የአጤ ዮሐንስም መድፍ ተኳሽ ተገደለ ። ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወገንም የተሰለፉት ባላንበራስ ጊዮርጊስ የተባሉት ግሪካዊ ከአጤ ዮሐንስ ብዙ ሰዎችን ገደሉ ። ከዚህ በኋላ አጤ ዮሐ ንስ ጭምት ላይ ያላቸውን የጦር ሠፈር አነሱ ። ባሻ አስናቀ በኢት ዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ መድፍ የሠራ ኢትዮጵያዊ ነው ።

በዚህ የተናደዱት አጤ ዮሐንስም ጐጃም በሙሉ እንዲዘረፍ አዘዙ ።ወታደሩም ከዳር እስከ ዳር በጐጃም ተሰማርቶ ከብቱንም ሀብቱንም ዘረፈው ። ከብትዋ የተዘረፈባት አንዲት የጐጃም አልቃሽም

"በላይኛው ጌታ በባልንጀራዎ ፤
በቅዱስ ሚካኤል በጋሻ ጃግሬዎ ፤
በጽላተ ሙሴ በነጭ አበዛዎ ፥
ጐጃምን ይማሩት ፈሪም አንልዎ" ብላ ገጠመች ።

ጐጃም ከተዘረፈ በኋላ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የጐጃም መበ ደልና መዘረፍ አሳዝኖአቸው ከአጤ ዮሐንስ ጋር ተላልከው ታርቀው ገቡ ። እልልታም ደስታም ሆነ ። አጤ ዮሐንስም ከጠፋው በቀር የጐ ጃም ገንዘብ ይመለስ ብለው አዋጅ አናገሩ ። ከዚህ በኋላ አጤ ዮሐ ንስ ንጉሥ ምኒልክን ሊወጉ ወደሸዋ ጉዞ ጀመሩ ። ምኒልክም ከተ ክለ ሃይማኖት ቀጥሎ በትሩ እንደሚያርፍባቸው ያውቁ ነበርና ራስ ዳርጌን በሰላሌ በኩል ፥ ደጃች መኰንንን በግንደበረት በኩል ፥ ደጃች ወሌን በወሎ በኩል አሰልፈው የዮሐንስን መምጫ ይጠባበቁ ነበር ። የጐጃምን መዘረፍ ከሰሙ በኋላ ግን የሸዋም ሕዝብ የዚያ ዓይነት

ዕድል እንዳያጋጥመው ከደብረ ሊባኖስና ከዙቃላ የተውጣጡ መነኮሳትን "አስታርቁኝ" ሲሉ ወደ አጤ ዮሐንስ ላኩዋቸው ። አጤ ዮሐንስም ምኒልክን ካስገበሩ በኋላ ወደ መተማ ሔዱ ።

አጤ ዮሐንስ ወደ ሸዋ መዝመታቸውን ቢተዉም የንጉሥ ምኒልክ ነገር ግራ ስላጋባቸው በምኒልክ አጐት በራስ ዳርጌ አማካይነት ነገሩ ሁሉ ተፈራርሞ ሰላም እንዲመሠረት በደብዳቤ ጉዳዩን የመጨረስ አሰቡ ።ለመጀመሪያ ጊዜም ኅዳር 18 ቀን 1881 ዓ.ም. ለሚከተለውን ደብዳቤ ለራስ ዳርጌ ፃፉላቸው ።

ይድረስ ከራስ ዳርጌ ።እንዴት ሰነበቱ ። እኔ ከሠራዊቱ ጋር እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። ፲፩ ዓመት ሙሉ በፍቅር ተጸምደን በሃይማኖት ፣ በምግባር አንድ ሆነን መንግሥታችንን አጽንተን እንኳን የኢትዮጵያ ሰው ፣ የወዲያ አገር ነገሥታት እንኳ እየቀኑብን ከእግዚአብሔር ፣ ከሰው ተስማምተን እስካሁን ተቀመጥን ።

አሁን ዲያብሎስ ጸላኢ ሠናያት ነውና የአህዛብ መሳለቂያ ሊያደርገን ከሁለታችን ከወንድማማቾች መካከል እንዲህ ያለ ነቅ አገባብን ።

ደግሞ ዝምድናችን እንዲጸና፣ እንድንበረታ ብዬ ምንም እግዚአብሔር ቢያሳፍረኝ ልጅ ከልጅ አጋባሁ ።ምክር መከርሁ ። ሃይማኖት አስተማርሁ ። ሥላሴ እንኳን የማያደርጉትን ከመንግሥቱ ከፍዬ ወንድሜን ለመንግሥት አበቃለሁ እንጂ እኔ በንጉሥ ክፉ ያደረግሁ አልመሰለኝም ነበር ።

አሁንም በትውልድ አባት ነዎ ። በዕድሜ ሽማግሌ ነዎ ። ሰይጣን ባልሆኑ ሰዎች አድሮ ነገር ሲያበላሽ እያዩ ምነው ዝም ይላሉ ። ምንም ፈቃዱ የእግዚአብሔር ስለሆነ እኔ አሣላፊ ነኝ ። አገሩን ኢትዮጵያ ሁሉ ከፍዬ ሰጥቼ ትግሬንና በጌምድርን ይዤ ብቀመጥ በቤጌምድር ሹም ሽር ተደረገበት ። በትግሬም የንጉሥ ደብዳቤ አልመጣ እንደሆነ ነው እንጂ የመኳንንቱ ደብዳቤ በሀገሬም በሠፈሩም ያልመጣበት ፣ በመልእክት ያልተባበለ ፣ ወርቅ ያልተቀበለ ሰው አይገኝም።

የመጣውንም ደብዳቤ ሎሌ ለጌታው ያየውን ፣ የሰማውን አይሰውርምና ከሰዎቹ እጅ ደብዳቤውን አግኝቼ ነው እንጂ ሳላገኘው በሐሰት አልጻፍኩም ።

እንግዲህ ግን ደርቡሽ ወጥቶ የክርስቲያን ደም ቢያፈስ ፣ ቤተ ክርስቲያን ቢተኩስ ፣ የዚህ ፍዳ ንጉሥ ምኒልክን ነው እንጂ እኔን አያ

ገኘኝም ፡፡ከልቤ እንኳ ብርቱ ምስጢር ቢኖር ከወንድሜ ከንጉሥ ምኒልክ ሰውሬ የማስቀረው አልነበረኝም ፡፡ በፊትም አብረን ሳለን እየ ተባበለ የትግሬ ጦር ሁሉ ሄደ ፡፡ አሁንም በኋላ አምባጫራ ወርዳችሁ ሳለ በደምቢያም ፤ በበጌምድርም ያለ ሁሉ ጃግናውም ፤ ደብተራውም ፤ ፈላሻውም ፤ ቤቱም የቀረ የለም ፡፡ እየተባበለ ከናንተ ጋራ ባንድ ሄደ፡፡

ሳይጠፋኝ ይህን ሁሉ እየሰማሁ ዝም ብል በመጨረሻም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን አባብላችሁ አስከዳችሁት ፡፡ ስለ ከዳ ግን አገሩ ጠፋ በት ፤ ተጐዳ እንጂ ፡፡አሁን እግዚአብሔር ምህረት አውርዶ ታርቆ ገባ ፡፡

ደግሞ እኔ የእግዚአብሔር የትህትና ደካማ ነኝ እንጂ የሰው ደካማ አይደለሁም ፡፡ የኔን አገር የሚገዛው የለም ፡፡

ይህን ሁሉ እያደረገ እናንተንና እኔን ሰይጣን ሆኖ የሚያፋጀን፤ መንግሥት ሲያፈርስ የሚኖር ፤ የአለሙን ሁሉ ቋንቋ ተምሮ የሰይጣ ናትን ቋንቋ ሲያጠና የሚኖር ፤ ነፍስ አባት አይሉት የሰው አገር ሰው ፤ በጌምድር መሸሻ ወርቄ የሚሉ መካር አበጅታችሁ የተንኰሉ ሁሉ ምንጭ እርሱ ነው እንጂ ከንጉሥም ፤ ከእናንተም ይህን ያህል ተንኮል እንደሌለ አውቃለሁ ፡፡አሁንም እኔ ግድ የለኝም ፡፡ እስ ተውላችሁ ብትመከሩት ይሻላል ፡፡ ደብዳቤውንም እርስዎ አይተው ወደ ልጅዎ ወደ ንጉሥ ስደዱት ፡፡

ተጽሐፈ በዳሞት ሠፈር አመ ፲፰ ለኅዳር ፲፰፻፸፮ ዓመተ ምህረት

ይህን የአጤ ዮሐንስን ደብዳቤ ራስ ዳርጌ ባዩ ጊዜ ደንግጠው ሁኔታውን እንዲያውቁት ብቻ ማይሆን በታዘዙት መሠረትም ለን ጉሥ ምኒልክ አቀረቡት ፡፡ ምኒልክም ይህን ወቀሳ የመላበትን ደብዳቤ ካዩ በኋላ በራስ ዳርጌ በኩል ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ወደ አጤ ዮሐ ንስ ላኩ ፡፡

ይድረስ ከሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ፤
ንጉሠ ጽዮን ፤ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፡፡
የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ ፡፡

ወደ ራስ ዳርጌ የመጣው የጃንሆይ ደብዳቤ ደረሰኝ ፡፡ ሰይጣናት በሰው አድረው በእኔና በጃንሆይ መካከል ንቁዕ ስለ አገቡብን ደብዳቤውን አይቼ እጅግ አዘንኩ ፡፡

እኔም ከመሥጋቴ በቀር ከያዝሁት መንግሥት በላይ ሌላ መንግሥት ፈልጌ እንደሆነ ፤ ጃንሆይንም ጠልቼ የጃንሆይ መንግ ሥት እንዲናወጥ አድርጌ እንደሆነ እግዚአብሔር ምስክሬ ነው ። ደግሞ እስካሁን በጃንሆይ ትእግሥት ፤ በጃንሆይ ልበ ጥሩነት ነው እንጂ ሠራዊቱማ የሚያወራብኝ ብዙ ነው ። ፊት ደርቡሽን አመጡ ተብዬ ነበር ። ኋላም ኢጣሊያ ቢመጣ ይህንኑ አሉኝ ። እኔ ግን ይህ ነን ሁሉ ቢያወሩ ግድ የለም ፤ ከጦርነቱና ከሞቱ የተለየሁ እንደሆነ ያን ጊዜ ሁሉም ይታወቃል ብዬ ሠራዊቴን አስከትቼ ብመጣ ጃን ሆይ ወደ ደርቡሽ አዘዙኝ ።

እኔም ደስ ብሎኝ እግዚአብሔር ኃይል ቢሰጠኝ የክርስቲያንን ደም እመልሳለሁ ፤ ብሞትም ሰማዕትነት እቀበላለሁ ብዬ ሄድሁ ። በእግዚአብሔር ቸርነት ፤ በጃንሆይ ሀብት ጠላታችን ሸሽቶ ቢሄድ ታርቀው ሄዱ እያለ ያወራል አሉ ።

ዳግመኛ ፤ ጃንሆይ ባዘዙልኝ ቃል ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መል ካም አድርጐ ቢቀበለኝ ደስ ብሎኝ ክርስቲያን ለክርስቲያን ፤ ወን ድም ለወንድሙ መርጠብ ይገባል መስሎኝ ሁለት መድፍ ፤ 250 ጠመንጃ ረጥቤው መጣሁ ። ይህ ነውር ሆኖብኝ ንጉሥ ተክለ ሃይማ ኖትን ያስከዱ ፣ ጐጃምን ያስጠፉ ንጉሥ ምኒልክ ናቸው ይሉኛል አሉ ።

ደግሞ የጃንሆይ ደብዳቤ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን አባብላችሁ አስከዳችሁት ይላል ።

ከእንግዲህ ወዲህ የዚህን ነገር ብናገር ሐሰት እንጂ እውነት አይመስልም ። ካልጠፋ መንገድ በጐጃም መምጣቴ ነው የሚያሳዝነኝ።

ነገሩንም እግዚአብሔር ባወቀ ይግለጸው ። እኔማ ወይሰበከ ወን ጌለ መንግሥተ ሰማያት ውስተ ኩሉ ዓለም ። ከመ ይኩን ሰምዓ ላዕለ ኩሉ አሕዛብ ያለው በጃንሆይ ጊዜ ሊደርስ ሊፈጸም ነው ብዬ ሳለሁ ፣የኛን አንድነት ሰይጣናት አፍርሰው የመሐመድ ቁራን በኢት ዮጵያ ሊነገርበት ይሆን ብዬ አዝኜ ነበርሁ ። አሁንም የፈራሁበትን ነገር ከምህረትዎ ጋራ ላባታችን ለአቡነ ማቴዎስ ነግሬአለሁ ። ለራስ ዳርጌም ጽፌአለሁ ።

በታህሣሥ ፲፩ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምህረት ከእንጦጦ ከተማ ተጻፈ።

ንጉሥ ምኒልክ ይህን ደብዳቤ ለአጤ ዮሐንስ እንዲያደርሱ ለራስ ዳርጌ ሰጡ ። ራስ ዳርጌም በፊት ለተጻፈላቸው ደብዳቤ ምላሹን ጽፈው ከንጉሥ ምኒልክ ደብዳቤ ጋር ወደ አጤ ዮሐንስ ላኩት ። ራስ ዳርጌ ለአጤ ዮሐንስ የጻፉት ደብዳቤ ቀጥሎ ያለው ነው ።

"ይድረስ ከሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ፤
ንጉሠ ጽዮን ፤ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ወደ እኔ የተላከው የጃንሆይ ደብዳቤ ደረሰልኝ ። እኔን ሽማግሌ አድርገው አስበው ስለላኩብኝ እግዚአብሔር በምህረት ልቡናው ያስብዎ ። ደብዳቤውንም እኔ አይቼ ወደ ንጉሥ ምኒልክ ሰደድሁት ።

ሰይጣን ፤ ባልሆኑ ሰዎች አድሮ ነገር ሲያበላሽ እያዩ ምነው ዝም ይላሉ ብለው የላኩብኝም ፤ ነገሩን ማወቁ ጃንሆይ ጉጃምን ከረገጡ ወዲህ ነው እንጂ ከዚያ በፊት የሰማሁት ነገር አልነበረም ።

ነገር ግን የጃንሆይ ልብ ጥሩ ነውና ይህን ደብዳቤ ስለላኩብኝ እጅግ ደስ አለኝ ። ከንጉሥ ምኒልክ የመጣልኝን ማኅተም ነገሩ የተን ኮል የክፋት እንዳልሆነ ባየው ከንጉሥ ሳላስፈቅድ ጃንሆይ እንዲ ያዩት ብዬ ይኸው ሰድጄዋለሁ ።

አሁንም ጃንሆይ ደህንነት ፣ምህረት ፣ልማድዎ ነውና ከልብዎ ይማሩት ። መግባቱን ግን ሥጋት ከሆነበት ጃንሆይ የሰይጣንን ክንፍ ይስበሩት ።

ኋላም ነገሩ እየተመረመረ እንደዚህ ቀደሙ ፍቅርዎ ስቦት ቶሎ እንዲገባ አውቃለሁ ።

እግዚአብሔር ምክሩን ጥበቡን ይግለጽልዎ ።

የተላከ ከራስ ዳርጌ ። ክርስቶስ ጤና ይስጥልኝ ብዬ እጅ እነሣለሁ ።

በታህሣሥ ፲፰ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምህረት ተጻፈ ።

እዚህ ደብዳቤ ላይ የምናየው የደብዳቤ አጻጻፍ ከአሁኑ አጻጻፍ የተለየ ሆኖ ይታያል ። ራስ ዳርጌ "የተላከ" ያሉት ፤ ሰላምታም ያቀረቡት ከደብዳቤያቸው መጨረሻ ላይ ነው ። በድሮው ጊዜ አንድ የበታች ሰው በሥልጣን የበላዩ ለሆነ ሰው ደብዳቤ በሚጽፍበት ጊዜ ሰላምታ የሚጽፈው ከደብዳቤው መጨረሻ ላይ እንጂ ከመነሻው አልነበረም ። አንድ በስልጣን የበላይ የሆነ ሰው ግን "የተላከ" የሚለውንና ሰላምታውን ሁሉ የሚጽፈው ከደብዳቤው መጀመሪያ ላይ ነው ።ይህን ካነሳን ንጉሥ ምኒልክ ለአጤ ዮሐንስ በጸፉት ቀደም ብለን ባነበብነው ደብዳቤያቸው ላይ "የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ" የሚለው ከደብዳቤው መጨረሻ መሆን ሲገባው ምኒልክ ግን ከመነሻው ላይ አድርገውታል ።ይህም የሚያሳየው ምኒልክ ንጉሠ

ነገሥቱን መናቃቸውን ወይም ደግሞ በኩርፊያ ጠብ ፍለጋ መጻፋቸ ውን ነው ። ምኒልክ እንደ አጤ ዮሐንስ ሁሉ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ በኋላ ግን ማንም መኳንንት ወይም ከሥራቸው ያለንጉሥ "የተላከ" የሚለውንና ሰላምታውን ከደብዳቤው መጀመሪያ አድርጐ የፃፈላ ቸው የለም ።

አጤ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ ምንም እንኳ አንዱ ለአንዱ አድራሻውን በትክክል አድርጐ ቢጽፍም በቀጥታ ለባለ አድራሻው ደብዳቤውን አይልኩም ነበር ። ሁለቱም የሚልኩት በራስ ዳርጌ በኩል ነበር ።ይህም በዚያን ዘመን በልቦናቸው የነበረውን ሀሳብ ባናው ቅም አጤ ዮሐንስ ጉዳዩን ሲጀምሩ መጀመሪያ ለራስ ዳርጌ የላኩ በት ምክንያት ራስ ዳርጌ የምኒልክ አጐት ስለሆኑ በምኒልክና በእሳ ቸው መሃል ያለውን ጉዳይ እንዲያውቁት ለማድረግ ያሰቡ ይመስ ላል ።የደብዳቤውም አድራሻ ለራስ ዳርጌ ይሁን እንጂ ጥፋቱ የተዘረ ዘረው የምኒልክ ነው ። ይህንኑ ጥፋታቸውን እንዲያውቁትም በማለት ራስ ዳርጌ የተፃፈላቸውን ደብዳቤ ካነበቡት በኋላ ለምኒልክ እንዲ ሰጡ አጤ ዮሐንስ አዘዋል ።

ንጉሥ ምኒልክ ለዚያ ለተፃፈው የወቀሳ ደብዳቤ መልስ ሲሰጡ ምንም እንኳ አድራሻው ለአጤ ዮሐንስ ቢሆንም ፥ደብዳቤው የተሰ ጠው ለራስ ዳርጌ ነበር ።ምኒልክ በቀጥታ ለምን ለአጤ ዮሐንስ አላ ኩም ? ብዙ ትንተና ሊኖረው ይችላል ።

አሁን በመጨረሻው ላይ ያነበብናቸው የንጉሥ ምኒልክና የራስ ዳርጌ ደብዳቤዎች ለአጤ ዮሐንስ ከደረሱ በኋላ አጤ ዮሐንስ ለም ኒልክ መልስ መፃፋቸውን ትተው እንደ መጀመሪያው ጊዜ ተበ ድያለሁ የሚሉበትን ሁሉ አሰባስበው ደብዳቤው በደረሳቸው ማግ ስት የፃፉት ለራስ ዳርጌ ብቻ ነው ። ምናልባትም ምኒልክ ነገሩን በም ስጢር ደብቀው ይይዙታል በማለት ወይም ደግሞ ራስ ዳርጌ በሁ ለቱ መሐል እማኝ ወይም ዳኛ እንዲሆኑ አስበው ይሆን ይሆናል ። ለሁሉም ነገር አጤ ዮሐንስ ለራስ ዳርጌ የጣፉት ደብዳቤ ቀጥሎ ያለው ነው ።

"መልእክት ዘሥዩም እግዚአብሔር ዮሐንስ ፥
ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።
ይድረስ ከራስ ዳርጌ ።

እንዴት ሰነበቱ ። እኔ ከሠራዊቱ ጋር እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። እመ ፲፰ ለታህሣሥ የተጻፈውም ደብዳቤ ደረሰልኝ ። ኢጣሊያ የመምጣቱ ወሬ የመጣልኝ በሐረርጌ በደጃዝማች መኰንን

በኩል ነው ። ኢጣሊያን ፣ ንጉሥ ምኒልክ አመጡት እያለ በደጅ ይጫወት እንደሆነ እንጂ በፊቴ ደፍሮ እንዲህ ያለ ነገር የሚናገር የለም ። ከዚያ በኋላም መምጣቴ ከታወቀ ወዲያ ፣ ጃንሆይ የጦሩ እለት እንዳልለይ ያድርጉኝ የሚል የንጉሥ ቃል በአቡነ ማቴዎስ መጣልኝ ። እሺ ብዬ ወደ ንጉሥ ላክሁኝ ።

ከዚያ ወዲያ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ድል ሆኖ ነበርና ዳግመኛ ሕዝበ ክርስቲያኑን ደርቡሽ ወጥቶ ይፈጀዋል ብዬ ቢያሳዝነኝ በእግ ዚአብሔር ፈቃድ ለኢጣሊያው እኛ እንበቃዋለን ፣ እምባጫራ ላይ ሆኖ እርሱን መጠበቅ ይሻላል ብዬ ወደ ንጉሥ ላክሁኝ ።ይህም ሆነ አልቀረም ። በምጥዋም በመተማም ያለውን ጠላታችንን እግዚአብ ሔር አሳፈረው ።

ንጉሥ ምኒልክ ከደርቡሽ ጋራ ተላልከዋል ብለው የደምቢያና የቤጌምድር ሰዎች ይጫወቱ እንደሆነ እንጂ ከእኔ መኳንንቶች አፍ እንዲህ ያለ ነገር አይወጣም ። እኔም መቅደላ እከርማለሁ ብዬ ሳለሁ ፣ ደርቡሽ መጣ ቢሉኝ ክርስቲያኑን ይፈጀዋል ብዬ ወደ በጌምድር ወርጄ አምራ ገደል ሰፍሬ ሳለሁ ፣ ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይ ማኖት አሲረው ከድተዋል ፣ ተማምለዋል ። ወደ ኢጣሊያም እኛና እና ንተ አንድ ነን ብለው ጽፈው ፣ አትመው ሰደዋል ። ጃንሆይ ነገሥታቱ ከድተዋችዋል ። በወዲያውም ደርቡሽ መጥቶባችዋል ። እንግዲህ ምን ኃይል አላቸው እያሉ ኢጣሊያኖች ይሳለቁብናል የሚሉ ወሬ ሰማ ሁኝ ።በዚህ ምክንያት ጐጃም ተሻገርሁ ።

በእኔም በድሃውም ኃጢአት እንደሆነ አይታወቅም አገሩን ሳ ጠ ፋው ከረምሁ ። ኋላም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ታርቆ ገባ ። ከገባ ወዲህ ይህንኑ ቃል እውነት ጽፋችሁ ልካችኋል ወይ ብዬ ብጠይቀው እዎ ልከናል አለኝ ።መከዳቱንስ እውነት ተማምላችሁ ከድታችሁኛል ወይ ብለው ፣ ከጃንሆይ ጋራ ውጊያ አልዋጋም ብያለሁ እንጂ መ ሀላ ውንስ እሺ ብዬ ምያለሁ ብሎ ነገረኝ ። ከዚያ ወዲያ ግን ወደ እር ስዎ ደብዳቤ የፃፍሁ ከዚህ የተነሣ ነው ።

የመተማመኑ ነገር ግን እኔ አልከዳሁ ፣ መሀላ አላፈረስሁ ፣ አፍ ርሼ እንደሆን ክርስቲያን አልባልም ። ዳግመኛ የምንተማመነው የፊቱን ማን አፍርሶት ነው ። በእኔም ፣ በንጉሥም ፈርሶ እንደሆነ ፣ ከዚህ ከእኔ ጋር ብዙ መኳንንት ፣ በወዲያም ብዙ መኳንንት እሉና በያሉበት ሆነው መርምረው እገሌ ከድቷል ፣ እገሌ መሀላውን አፍር ሰዋል ይበሉን ። ከዚያ ወዲያም ወደ ቁም ነገራችን እንሄዳለን ።

ተጽሐፈ በዳሞት ሠፈር ። አመ ፲፰ ለታህሣሥ በ፲፰፻፹፭ ዓ.ም.



ራስ ጎበና

ራስ ዳርጌም ይህን ደብዳቤ ካነበቡ በኋላ ለንጉሥ ምኒልክ አቅርበውላቸው ነበርና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በመካከላቸው የነበረውን ምሥጢር ለአጤ ዮሐንስ በማውጣታቸው ስለተናደዱ እርሳቸውም በበኩላቸው የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ምሥጢር እያወጡ ጽፈው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለአጤ ዮሐንስ ላኩላቸው ።

"ይድረስ ከሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ።
ንጉሠ ጽዮን ። ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።
የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እውነት ልትክዱኝ ተማምላችሁ ኑርዋልን ፣ ወደ ኢጣሊያስ ልካችሁ ኑርዋልን ብዬ ብጠይቀው ከጃንሆይ ጋራ አልዋጋም ብያለሁ እንጂ መሀላውንስ ተማምያለሁ አለኝ የሚል አገኘሁ ። መክዳቱን ከድቻለሁ ፣ መዋጋትን ግን አልዋጋም ማለት ይህ ስንፍና ነው እንጂ መቼ ትህትና ነው ። ነገሩም ሀሰት መሆኑ በዚህ ይታወቃል ።

መሀላ ተማምለን ነበር ፣ወደ ኢጣሊያ ተላልከን ነበር ያለውን ግን አሁን እኔ ብናገር እውነት አይመስልም ። ነገር ግን እልቦ ክዱን ዘኢያስተርኢ ። ወአልቦ ኅቡዕ ዘኢይትከሡት እንዳለ እግዚአብሔር ይግለጠው ።እኔ ግን የማልሁት መሀላ እንደዚህ ብዬ ነው ።

ካምባጫራ ተነሥቼ ፎገራ ስደርስ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፫ መነከሳት ላከብኝ ። የመጣችሁበት ነገሩ ምንድነው ብዬ ብጠይቃቸው ፣ባገሬ ላይ ሊመጡብኝ ነውና ንጉሥን አስታምኑልኝ ብለዋል ብለው ቢነግሩኝ ፣ ቀድሞ ጃንሆይ አማምለው አገዛዝተው አስታርቀውናል ።አሁን ደግሞ ከጠረጠረኝ መጥቶ አይገናኘኝ እንጂ ቢሻው አምባው ይግባ ፣ አለዚያም ከፈቀደው ቦታ ይቀመጥ ። እኔ ጃንሆይ ባዘዙኝ መንገዴን እሄዳለሁ ብዬ ለጊዜው ተቆጣሁ ። በኋላ ግን ነገሩ ይህ አይደለም ፣ የማጫውትዎት ብርቱ ምሥጢር አለኝ ። ይህን ለሰው እንዳያወጡብኝ አስታምኑልኝ ያሉት ስለዚህ ነው ቢሉኝ ለዚህማ ምን ከፋኝ ብዬ ታመንሁ ።ወዲያው ጉጃም ገባሁ ።

ከርሱ ከተገናኘን በኋላ ምን ጠርጥረኸኝ ነው ማል ተገዘት ብለህ መነኮሳት የላክህብኝ ብዬ ጠየቅሁት ። ራስ አርአያ ሥላሴ ፣ ደጃች ሥዩምን ይዞ እንደሰጠ እኔንም ጃንሆይ ይያዙት ብለዎ እን ደሆነ ብዬ ነው የሠጋሁት አለኝ ።

በምን ምክንያት ምን አጠፋሁና እንደዚህ ያለ ነገር ይደረጋል ፣ ይህስ እውነት አይመስለኝም አልሁት ።

እርስዎ ኢጣሊያን አመጡ ተብሎ ታምተዋል ። እኔንም የኢጣሊያ መንግሥትና የጐጃም መንግሥት አንድ ነው ብለህ ጽፈሀል ብለው ጠልተውኛል ። ከገባንም ሁለታችንንም አይተዉንም ፣ ይይዙናል አለኝ ።

ይህ በምን ይታወቃል ብለው አሁን መጥተው ጐጃም ይከርማሉ ። እኔም ከዚያ ከድንጋዩ ገብቼ እሞታለሁ እንጂ አልገባም አለኝ ። ሰይጣናት በፍቅር ይቀናሉ ፣ የኛን አንድነት ለመለየት ነው እንጂ ጃንሆይስ እንዲህ ያለ ነገር አያደርጉም ።

አሁንም ወደ ጐጃም የመጡ እንደሆን ነገሩ ተገልጦ እንዲምሩህ እንድትታረቅ ወደ ጃንሆይ ደብዳቤ እልክልሃለሁ ብየው መጣሁ ።

ወዲያው ደግሞ ንጉሥ ምኒልክ ፣ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መድፍና ብዙ ነፍጥ ሰጥተው ተማምለው መጡ ተብዬ ይህን ጃንሆይ ሰምተው ራስ አሉላ በሰሜን በኩል ተጓዙ ፣ ጃንሆይ መምጣታቸው ነውና ይጠንቀቁ ብሎ እዚያው ያለ ወዳጄ ላከብኝ ።

ወዲያው ደግሞ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለኔም ነግሮኛል ፣ ጃንሆይ ተናደው አገርዎን እንዳያጠፉት ብዬ ወደ ጃንሆይ ላክሁ ።

የዚህም ምላሽ ይልቅስ በእኛ በሁለታችን ሰይጣን አይግባብን ። እግዚአብሔር እንደሞቱትና እንዳሉት አድርጐ አይለያየን ። ባገሩም ጥፋት እግዚአብሔር በፈረደው ይፍረድ የሚል ደብዳቤ መጣልኝ ።

እንዲህ መታረቁ ሳይቀር ሰይጣን አበርዳለሁ ፣ አስታርቃለሁ ብዬ ብልክ የኔ ቃል ሳይሰማልኝ ቀረ ። ከዚያ ወዲያ ግን የሆነ ያልሆነውን ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጻፍሁለት ።

በታህሣሥ በ፳ ቀን በ፲፰፻፹፩ ዓ.ም. በእንጦጦ ከተማ ተጻፈ ።

ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በአጼ ዮሐንስ ላይ የሰሩት ሥራ ምንም ለየራሳቸው ጥቅም ቢሆን በመካከላቸው ጽኑ መሀላ መደረጉን ሁለቱም ወገኖች አምነዋል ። እነኚህን ደብዳቤዎች የሚያነበው የዛሬ አንባቢ ጉዳዩ ሁሉ በተራ ሰዎች መሀል የሚደረግ አሉባልታ ይመስላል ። ግን የምንረዳው አንድ ነገር አለ ። በዚያ ዘመን ንጉሠ ነገሥቱና ሁለቱ ንጉሶች ሶስቱም እርስ በራሳቸው ይፈራሩ እንደነበረ ነው ። አጼ ዮሐንስ ሁለቱንም ሽረው ሌላ ለመሾም ሙሉ ሥልጣን እያላቸው በደብዳቤ በመነጋገር እርቅ መፈለጋቸው ፣ ምኒልክም ሆኑ ተክለ ሃይማኖት በቂ ኃይል ያላቸው አስፈሪ ንጉሶች እንደ

ነበሩ እንረዳለን ። ሌላው ነገር ደግሞ አሁን አንዱ ያንዱን ጉድ ወይም ውጥን ወይም ሚስጥር እያወጣ ለንጉሠ ነገሥቱ ይናገር እንጂ ሁለቱ ንጉሶች በዮሐንስ ላይ ማደማቸው ግልጽ ነው ።የአጤ ዮሐን ስም ጥረት ሁለቱን አጣልቶ ለማለያየት መሆኑን ባሉባልታው ወሬ ማወቅ እንችላለን ። ምኒልክ እንደገና ተበድያለሁ የሚሉበትን ከደብ ዳቤው የረሱትን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ጽፈው በራስ ዳርጌ በኩል ለአጤ ዮሐንስ ላኩ ።

"ይድረስ ከሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ፣
ንጉሠ ጽዮን ፣ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።
የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ ።

ዳግመኛ የምንተማመን የፊቱን ማን አፍርሶት ነው ፣ በኔም በንጉሥም ፈርሶ እንደሆን ከዚህም ከእኔ ጋራ ብዙ መኳንንት ፣ ከወዲያም ከሸዋ ብዙ መኳንንት አሉ ። በያሉበት ሆነው መርምረው እገሌ ከድ ቷል ፣ እገሌ አፍርሷል ይበሉን የሚል ቃል አገኘሁ ። ነገር ግን መጀመ ሪያ የተማመን ጊዜ ካልተገናኘን ወሎን እወስዳለሁ ፣ የተገናኘን እንደሆን ግን ለሌላ ሰው አልሰጥም አሉኝ ።

እኔም ከጃንሆይ የምገባ ነኝ ብዬ ለሰዎቼ ባማክራቸው ከገባንም ከበ ሽሎ ወዲህ ላለ አገራችን አስታምነን እንግባ ቢሉኝ ለእጂ ብቻ ይታመኑልኝ እንጂ ከገባሁስ አጼ ቴዎድሮስ ሳይሞቱ ጀምሮ ያቀና ሁትን አገሬን ወሎን ይነሱኛል ብዬ አልጠራጠርም ፣ አላምልም ብዬ ገባሁ ።

ጃንሆይም በተናገሩት ቃል ከበሽሎ ወዲህ ሰጥቼሀለሁ ብለው አዋጅ ነግረውልኝ ደስ ብሎኝ ተቀምጬ ሳለሁ ፣ ወዲያው ደግሞ ራስ ሚካኤል ከፋኝ አለ ፣ ወረሂመኑን ልቀቁለት አሉኝ ፣ ለቀቅሁ ።

ደግሞ የማኖርበት ስፍራ ሳላጣ ፣ጃንሆይን በማመኔ ደጃች መሸ ሻን ሳይንት ላይ ባሥር ፈትተው ወሰዱብኝ ። ንጉሥ ተክለ ሃይማ ኖት አገሬ ላይ መጥቶ ቢወጋኝ እግዚአብሔር ረድቶኝ እርሱንም መኳንንቱንም ይዤ ብገባ ነፍጡን መልስለት አሉኝ ። እሺ ብዬ መለ ስሁ ። ደግሞ ወዲያው ወሎን ለኔ አደርገዋለሁ ፣ ሐዋርያ እሆንበታለ ሁና ልቀቅልኝ ቢሉኝ ፣ ለራስ ሚካኤል የሰጡብኝ እንደሆን ይከፋ ኛል እንጂ ለጃንሆይማ ከሆነ እሺ ብዬ ለቀቅሁ ። ኋላ ግን ለራስ አር አያ ሥላሴ ቢሰጡት ጥጃ ጠባ ፣ ከሆድ ገባ እንዲሉ ለልጂ ከሆነ ብዬ ደስ አለኝ ። ወዲያው አይስጡብኝ ላልሁት ለራስ ሚካኤል መልሰው ቢሰጡት ፣ እየኖረ ፍቅር እየተጨመረ ይሄዳል እንጂ ይጐድላልን ብዬ በዚህ ከፋኝ ።

እምነትና ፍቅር ፈረሰብኝ እለሁ እንጂ መሐላና ግዝትስ ፈረሰብኝ እላልሁም ። ባገሬም እኔ ባልገባ ተማምኜበት አልቆ ነበር ። ኋላ ግን ፍቅር እጨምራለሁ፤ወሎንም አገኛለሁ ብዬ ገባሁ ። አሁን ግን ቢቀርብኝ በቀድሞው ውሌ እለሁ ማለቴ ስለዚህ ነው ።

እኔስ ፡ ለጃንሆይ ሽማግሌ ምን አስፈልጐኝ ። ይህን ደብዳቤ በብሩህ ልቡናዎ ተመልክተው ይህ ያስከፋዋል ፣ ይህ አያስከፋውም ብለው ጃንሆይ ይፍረዱ ። ደግሞ ይህን ሁሉ መጻፌ የመድፈሬ አይደለም ። ጃንሆይ ከፈቀደልኝ ብዬ ነው እንጂ

በጥር ፲ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓ.ም. እንጦጦ ከተማ ተጻፈ ።”

አጤ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ እርቀ ሰላም ለማውረድ የመወቃቀሻ ደብዳቤዎቻቸውን ይላላኩ እንጂ በመሀከላቸው ልባዊ የሆነ ፍቅርና ሰላም አልተገኘም ። ራስ ዳርጌም ቢሆኑ ለወንድማቸው ልጅ ለምኒልክ ማገዛቸው ባይቀርም በአጤ ዮሐንስ አድራጐት ከሚናደዱት የሸዋ መኳንንት አንዱ መሆናቸው ግልፅ ነው ። በዚህ ምክንያት ደብዳቤ አመላላሽ ሆነው ቀሩ እንጂ አጤ ዮሐንስ እንዳመኑዋቸው ምኒልክንም ቢሆን ተቆጥተው ፣ አጤ ዮሐንስንም ቢሆን መክረው በመሀላቸው ወዳጅነት ሊፈጥሩ ይችሉ ነበር ።

አጤ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ እነኚህን ደብዳቤዎች በሚጻጻፉበት ጊዜ በኋላ ንግሥት የሆኑት ወይዘሮ ዘውዲቱ ምንም እንኳ ባላቸው የአጤ ዮሐንስ ልጅ ራስ እርእያ ሥላሴ ቢሞቱም የሚኖሩት ከዚያው ከአጤ ዮሐንስ ዘንድ ነበር ። የሁለቱን ማለት የሚቹ ባላቸው አባት አጤ ዮሐንስና ወላጅ አባታቸው ንጉሥ ምኒልክ የሚጻጻፉትን ደብዳቤ እየሰሙ ያዝኑ ነበርና አንድ ቀን “ባሌ ራስ እርእያ ባይሞቱ ፣ ጃንሆይና አባቴ ሳይታረቁ አይቀሩም ነበር” ብለው ተናገሩ ። አጤ ዮሐንስም ይህን ነገር ሲሰሙ ራስ እርእያ እንደሞቱበት ቀን መኳንንቱ ሁሉ ተሰብስቦ ትልቅ ለቅሶ ተለቀሰ ይባላል ። አጤ ዮሐንሲም ወይዘሮ ዘውዲቱን ከፍ ባለ ማዕረግ አሳጅበው ወደ አባታቸው ወደ ንጉሥ ምኒልክ ላኩዋቸው ።ከዚያ በፊት ግን እንደ መያዣ አድርገዋቸው ነበር ይባላል ።

# ከንጉሥነት
# ወደ ንጉሠ ነገሥትነት

ደጃዝማች ምኒልክ ከመቅደላ ከወጡ በኋላ የአጤ ቴዎድሮስ እስተዳደር እየተበላሸ ሄደ ። በፊትም ቢሆን ቴዎድሮስ የዋዛ ሰው እልነበሩምና ምኒልክ ከከዱ በኋላ ግን በብስጭት ምክንያት የኃይ ልና የጭክና ሥራቸው እየባሰበት ሄደ ። ቴዎድሮስ አንድ ቀን አዲስ ከመ ጡት ከሊቀ ጳጳሱ ከአቡነ ቄርሎስ ጋር ሲጫወቱ “ . . . . አባቴ ፣ በሀገርዎ ሳሉ የኔን ወሬ ይሰሙ ኖርዋልን” ብለው ጠየቋቸው ። እር ሳቸውም “ቸርነህ ፣ ጀግና ነህ ይሉሃል ። ነገር ግን የሾመውን የሸለመ ውን ያስራል ፣ ይገድላል ፣ ይቆርጣል ይሉሃል” አሉዋቸው ። አጤ ቴዎድ ሮስም ሲመልሱ “በሽፍትነቴ በረሃ ለበረሃ ስሄድ መነኩሴ አገኘሁ ። ያም መነኩሴ ትነግሳለህ ፣ ነገር ግን ያሳደግኸው ሰው ከቤትህ የወጣ ዕለት መንግሥትህ ያጥራል ብሎ ነገረኝ ። ይህን የማደርገው ስለዚህ ነው” አሉዋቸው ። አቡነ ቄርሎስም “እግዚአብሔር የሚያነግሰውን ሽፍኖ ይጠብቀዋል እንጂ አንተ መቼ ታገኘዋለህ ። ደግሞስ ሄሮድስ ያን ሁሉ ሕፃናት በከንቱ አስፈጃቸው እንጂ ክርስቶስን አገኘውን” አሉዋቸው ።

ምኒልክ ሸዋ ከገቡ በኋላ ነሐሴ 16 ቀን 1857 ዓ.ም. ራሳቸውን ንጉሥ ብለው ነገሡ ። ጉልበታቸው እየጠና ሲሄድም “ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት” የሚል ማኅተም አዘጋጅተው ራሳቸውን ንጉሠ ነገ ሥት አሰኙ ። ይህ ሁሉ እንዲያው በሥልጣናቸው ያደረጉት እንጂ የበላዮቻቸው በፊትም አጤ ቴዎድሮስ ፣ በኋላም አጤ ተክለ ጊዮር ጊስ አላፀደቁላቸውም ወይም አልሾሙዋቸውም ነበር ። በአጤ ዮሐ ንስ ዘመነ መንግሥትም ቢሆን ትልቁ ጠብ ምኒልክ ራሳቸውን ንጉሠ ነገሥት በማለታቸው ነበር ።

አጤ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ በብዙ አማላጆች ከታረቁ በኋላ አጤ ዮሐንስ መጋቢት 18 ቀን 1870 ዓ.ም. የምኒልክን ንጉሥነት አፅድቀው ዘውድ ሰጧቸው ። ይህንንም በአጤ ዮሐንስ የተሰጣቸውን የንጉሥነት ማዕረግ በይፋ ለማሳወቅ የዚያን ጊዜ ዋና ከተማቸው

ከነበረው ልቼ ሲገቡ ሥርዓተ መንግሥት ለማድረስና ግብር ለማብ ላት አስበው እንዲዘጋጅ አዘዙ ።

የግብር ማብያው አዳራሽና ግብሩ ከተዘጋጀ በኋላ ጥቅምት 3 ቀን 1871 ዓ.ም. ቅዳሜ ማታ ምኒልክ ከልቼ ወደ ደብረ ብርሃን ሔዱ። የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተክርስቲያን ካህናትም ማህሌት ቁመው አደሩ ። ሲነጋም ምኒልክ ልብሰ መንግሥታቸውን ለብሰው መምህር ገብረ ሥላሴና መምህር ግርማ ሥላሴ በተዘጋጀው ዙፋን ላይ አስቀ መጧቸው ። ምኒልክ በዙፋናቸው ላይ ከተቀመጡ በኋላ ዘውድ ተደ ፋላቸው ።

ዘውዱ ከተደፋላቸው በኋላ ሊቀመኳስ አጥናፍ ሰገድ ካባ ላንቃ ለብሰው ፣ ራስ ጉበና የራስ ወርቅ አስረው ከቤተ ክርስቲያን ወጡ ። በወርቅ መረሸት ያጌጠች በቅሎ ከቤተ ክርስቲያኑ ደጃፍ ስትቀርብ ምኒልክ ከበቅሎዋ ላይ ወጥተው ፣ በግራና በቀኝ ሰይፍ መዝዘው በያዙ መኳንንት ታጅበው ጉዞ ጀመሩ ። እጅግ በጣም በደመቀ አጀብ ታጅ በውም ከከተማቸው ልቼ ገቡ ።

ልቼ ገብተው አዳራሹ ውስጥ ከተዘጋጀው ዙፋን ላይ ሲቀመጡ ከውጭ የተጠመደው መድፍ 22 ጊዜ ተተኮሰ ። ከመድፉ ተኩስ ጋርም ሠራዊቱ ሁሉ ጠመንጃውን በመተኮስ በዓሉን እጅግ አደመ ቀው ። ጥቅምት 4 ቀን ሙሉ የግብር ቀን ሆኖ ዋለ ። ከዚያን ቀን ጀምሮ ለብዙ ቀናት ግብር ሲበላ ከረመ ።

አጤ ዮሐንስ ለንጉሥ ምኒልክ ዘውድ ከሰጡዋቸውና የሸዋን ንጉ ሥነት ካጸደቁላቸው ከ11 ዓመት በኋላ አጤ ዮሐንስ ሞቱ ። እስከዚህ ጊዜ ምኒልክ በራሳቸው ንጉሥነት 13 ዓመት ፣ በአጤ ዮሐንስ የንጉሥ ነት ሹመት 11 ዓመት በጠቅላላው 24 ዓመት በንጉሥነት ሸዋን ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል ። ግዛታቸው ስሙ ሸዋ ይሁን እንጂ በምሥ ራቅ እስከ ሐረርጌ ፣ በሌላውም አቅጣጫ እስከ ወለጋና ከፋ ድረስ ነበር ። አጤ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ መጋቢት 29 ቀን 1881 ዓ ም ወሎ ውስጥ ቦሩ ሜዳ ላይ እንዳሉ “ገኘሁ እኔ ነኝና ባለህ እርጋ” ብለው አዋጅ አስነገሩ ።

አጤ ዮሐንስ የሞቱት በሕመም ሳይሆን በጦርነት ላይ ነው ። ባጭሩ ሁኔታውን ለማስረዳት ያሀል ደርቡሾች እንደገና ጐንደርን

ለመውረር ይዘጋጃሉ የሚል ወሬ ለአጤ ዮሐንስ መጣላቸው ። እሳቸ ውም ደርቡሾች ሳይመጡ መተማ ድረስ ወርደው ለመምታት ወደ መተማ ጉዞ ጀመሩ ። አገው ምድርን አልፈው ወደ ደንቢያ ወርደው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና ደርቡሾች ከተዋጉበት ሣር ውሃ ከተባለው ቦታ ሲደርሱ በዚያ የወደቀውን የሰው አጥንት ብዛት አይተው ደርቡ ሾች በሠሩት ሥራ በጣም አዘኑ ።

ከዚያም በግስጋሴ ወደ መተማ ተጓዙ ። የዚያን ጊዜ የአጤ ዮሐ ንስ ሃሳብ መጀመሪያ መተማ ላይ ያለውን ደርቡሽ ከመቱ በኋላ እስከ አምዱርማን ድረስ ሔደው ጠላታቸውን ለመደምሰስ ነበር ። አብረዋቸው ትልቁ ራስ አርአያ ፣ ቢትወደድ ገብረ መስቀል ፣ ራስ ሚካ ኤል ፣ ራስ ኃይለ ማርያም ፣ ራስ አሉላ ፣ ራስ መንገሻ ፤ ራስ ሐጐስና ሌሎችም ነበሩ ። የዘመተው ሠራዊታቸው ቁጥር እስከ 150.000 ይደ ርስ ነበር ። ከዚያም ሠራዊት መሀል ሃያው ሺ ፈረሰኛ ነበር ። ይህ የአጤ ዮሐንስ ዘመቻም አምዱርማን ሲሰማ ታላቅ ድንጋጤን ፈጠረ ።

ባሁኑ ጊዜ በደርቡሾች በኩል የድሮ አዝማቻቸው ሐምዳን አቡ አንጃ ሞቶ በሱ ቦታ ዜኪ ቶማል የተባለ ተተክቶዋል ። እሱም የጦር አለቆቹን ሰብስቦ “....ጠላቶቻችንን እንዴት ሆነን እንቋቋማቸው ? በውጭ ወይስ በቅጥር ውስጥ ሆነን ብንቋቋማቸው ይሻላል....” ብሎ ምክር ጠየቀ ። ከተሰብሳቢዎቹ አንዱ ቃዲ አህመድ የሚባለው “....በሜዳ ተሰልፈን የቆየናቸው እንደሆነ ሐበሾች ፈረሰኞች ስለ ሆኑ አንችላቸውም ። ስለዚህ ምሽጋችን ውስጥ ሆነን ብንቋቋማቸው ይሻላል....” የሚል ሃሳብ አቀረቦ ሁሉም በዚህ ሐሳብ ተስማሙ ። በኢ ትዮጵያና በደርቡሾች መሀል ስላለው ጠብና መነሻ ወደፊት አሳ ትመዋለሁ ባልኩት ባጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ውስጥ እገልጠዋለሁ ።

ዜኪ ሠራዊቱን አስቆጥሮ 85.000 ወታደር እንዳለ ተረጋገጠ ። ይህም ብዛት እንደማይበቃ ተገምቶ በየገበያውና በየመንደሩ አዋጅ ነጋሪ ስዶ ነጋዴውም ሆነ ገበሬው በአዋጅ እንዲሰበሰብ አደረገ ። የተሰበሰበውንም ገበሬና ነጋዴ መሣሪያ እየሰጠ ለጦርነት አሰለፈው። ወደ ከሊፋ አብደላም መልክተኛ ልኮ “....እዘንልኝ ። ረዳትም ስደድ ልኝ ። ወደ አበሾች ሰላይ ልኬ ነበርና ብዛታቸው እንደሰማይ ኮከብ እንደ ባህር አሸዋ ነው ። ሲጓዙም ከብዛታቸው የተነሳ የምድሩ ትቢያ እንደደመና ሆኖ ጠሀይን ይከልላታል ብሎ ነገረኝ ። በዚህም ላይ

ደግሞ 'አበሾች ካርቱም ድረስ ይመጣሉ ። ፈረሶቻቸውም እስከ አንገታቸው ድረስ በሰው ደም እየተነከሩ በንጭ አባይ ዳር በበቀለው ዛፍ ይታሰራሉ' የሚባል ትንቢት አለና ይሄ ሁሉ ያስፈራኛል ....'' በማለት ላከ ።

አጤ ዮሐንስ ጀግናና አስፈሪ የሆነ ሠራዊታቸውን እየመሩ በየካቲት ወር ማለቂያ ላይ መተማ ደረሱ ። እንደደረሱም ለደርቡሾች ጦር አዛዥ ለዜኪ ''....መጣሁብህ ፣ ተዘጋጅተህ ቆየኝ ። እንደ ሌባ በድንገት መጣብኝ እንዳትለኝ ። የመጣሁትም የክርስቲያኖችን ደም ለመበቀል ነው ።....'' ብለው ላኩበት ። ይህ ከሆነ በኋላ ሁለቱም ወገኖች የጦር ዝግጅታቸውን አሟልተው ጨረሱ ።

መጋቢት 1 ቀን 1881 ዓ.ም. ጦርነቱ መተማ ላይ ተጀመረ ። ጦርነቱ እንደተጀመረ ከሠራዊቱ ብዛት የተነሳ አቧራው እንደደመና ሆኖ ሰውና ሰው ለመተያየት እስቲያቅት አስቸግሮ ነበር ይባላል ። ደርቡሾቹ ጠንክረው ከተዋጉ በኋላ የአጤ ዮሐንስ ሠራዊት ባንድ በኩል ምሽጉን ጥሶ ከመተማ ከእስላሞቹ ከተማ ገባ ። ከዚያም የከተማውን ሕዝብ አስወጥተው ከተማውን በእሳት አቃጠሉት ። በዚህ ታላቅ ውጊያ የአጤ ዮሐንስ ሠራዊት ጨርሶ ድል ለማድረግ ጥቂት ሲቀረው አጤ ዮሐንስ በጥይት ተመቱ ። የአጤ ዮሐንስም በጥይት መመታት ወሬው ተዛምቶ ከሠራዊታቸው መሀል ተዳረሰ ። በዚህ ጊዜ ውጊያው ተገላበጠና አባራሪ የነበረው የአጤ ዮሐንስ ሠራዊት ሸሺ ፣ሸሺ የነበረው ደርቡሽ በተራው አባራሪ ሆነ ።

አጤ ዮሐንስም ክፉኛ ቆስለው ነበርና አልጋ ወራሻቸውን ለመናዘዝ አስበው የወንድማቸውን የደጃዝማች ጉግሣን ልጅ ራስ ኃይለ ማርያምን አልጋወራሽ ለማድረግ ጳጳሱንና እጨጌውን ሌሎችንም በአጠገባቸው ያሉትን መኳንንት አሰባስበው ''ኃይለማርያምን ጥሩት'' አሉ ። ''በጦርነት ስለቆሰሉ ለመምጣት አይችሉም'' አሏቸው ። ቆሰለ ያሉት ቢሞት ነው ብለው አጤ ዮሐንስ በጣም አዘኑ ። ወዲያውም ''ወንድሙን ራስ መንገሻን ጥሩልኝ'' ብለው ተጠርተው ሲቀርቡ ''እኔ የሞትሁ እንደሆነ አልጋ ወራሼ ልጄ ራስ መንገሻ ነውና ለርሱ ተገዙ'' ብለው ተናዘዙ ። በማግስቱም አረፉ ። መኳንንቱም ያጤ ዮሐንስን ሬሳ በማጥን ከተው ወደ አትባራ ሸሹ ።

ደርቡሾችም በጦሩ ዕለት ወዲያውኑ በጦሩ ሜዳ ላይ የወደቀውን የኢትዮጵያውያንን የጦር አለቆች ራስ እየቆረጡ ለከሊፋ አብደላ የምሥራች እያሉ ላኩለት ። በማግስቱም ኢትዮጵያኖቹ ተመልሰው ይወጉናል በማለት ፈርተው ምሽጋቸውን በሚያጠናክሩበት ጊዜ ወደ

ኢትዮጵያውያን ሠፈር የተላከው ስላይ ወደ ወገኖቹ ሲመለስ "....ፊታ ቸውን ወደ አትባራ ወንዝ አድርገው ይሸሻሉ እንጂ አንድ መኰ ንን እንኳ ተዳፍሮ ወደኛ ወገን ፊቱን ያዞረ የለም...." ብሎ ተናገረ ። ይህን የሰማው የጦሩ አዛዥ ዜኪ ሠራዊቱን በሙሉ ሰብስቦ በፈረስና በግመል እየጋለቡ ኢትዮጵያውያኖችን ተከታተሉዋቸው ።

የአጤ ዮሐንስን ሬሳ ይዘው የሚሸሹት መኳንንት መጋቢት 3 ቀን አትባራ ወንዝ አጠገብ ሠፈር አድርገው ሳሉ የደርቡሽ ጦር በድንገት ደርሶ ተዋጋቸው ። የአጤ ዮሐንስ ወታደሮችና መኳንንቶችም ሬሳው ካለበት ድንኳን ዙሪያ ሆነው የጌታችንን ሬሳ አናስማርክም ብለው በታላቅ ጀግንነት ተዋጉ ።

የደርቡሾች አስተሳሰብ አጤ ዮሐንስን ለመማረክ ነበርና በድን ኳኑ በር ላይ በተደረገው ውጊያ ከሁለቱም ወገን የሚወድቀው ሠራ ዊት ሬሳው በሬሳ ላይ ተከመረ ። ከኢትዮጵያውያን መኳንንትም ትልቁ ራስ አርአያ ፣ ቢትወደድ ገብረ መስቀል ፣ደጃች ተድላ ፣ ብላታ ገብረ ማርያም ፣ አዛዥ ወንድም ሁነኝ ፣ አዛዥ ላዕከ ድራግ ፣ መም ህር ዘሚካኤል ፣ መምህር ወልደ አረጋዊ ፣ መምህር ክንፈ ኪሩብ ፣ ቄስ ገበዝ ሰላማና ሌሎቹም ሬሳቸው እየተነባበረ በድንኳኑ በር ላይ ወደቀ ።

ይህ ሁሉ እልቂት ከተፈፀመ በኋላ ደርቡሾች ድንኳኑ ውስጥ ገቡ ። እንደገቡም ተሽቀዳድመው ከሣጥኑ ዘንድ ሔዱ ። ሣጥኑ በሰም ተደ ፍኖ ስለነበር ገንዘብ ያለበት ሣጥን መስሏቸው ለመዝረፍ ነበር ። ቶሎ ብለው በሽሚያ ቢከፍቱት ከውስጡ ያለው ሬሳ እንጂ ገንዘብ አልነበረም ። በዚያው በድንኳኑ ደጅ ከተማረከው አንዱን ሰው ቢጠ ይቁት "የአጤ ዮሐንስ ሬሳ ነው" አላቸው ። ሬሳውን በያዘው ሣጥን አጠገብ በብሩና የተጻፈ ልባሱ (ገበታው) በባህር አረብና በወርቅ የተለበጠ አራቱ ወንጌል ፣ የዕለት ፣ የሣምንት ፣ የወርና የዓመት ቁጥር የሚቆጥር የወርቅ ሰዓት ፣ ትልቅ የሩቅ ማያ መነጥር ፣ በፈርጥ ያጌጠ መስቀልና ሌሎችም ዕቃዎች ተገኝተው ወሰዱዋቸው ።

ከሬሳው ላይ ያጤ ዮሐንስን ጭንቅላት ቆርጠው ለከሊፋ አብዱ ላሂ የምሥራች ብለው ላኩለት ። ከሊፋ አብዱላሂም የተላከለትን የአጤ ዮሐንስን ጭንቅላት ባየ ጊዜ በጣም ተደሰተ ። ወዲያውኑ መለ ከት እንዲነፋ አዝዞ ሕዝቡ ሲሰበሰብ የምሥራች ተነገረው ። ከሶስት ቀናት በኋላ የአጤ ዮሐንስ ጭንቅላት በእንጨት ላይ ተሰክቶ በግ መል ጀርባ ላይና በሰው ሸክም እየሆነ ገበያ ለገበያና መንደር ለመን ደር እየዞረ ለሕዝቡ ሲታይ ከረመ ።

አጤ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥትነታቸውን እንዳገኙ ብዙ ተቀናቃኝ አልተነሳባቸውም ። ግሼ አምባ ላይ ያጤ ዮሐንስን የጦር መሣሪያ ይጠብቁ የነበሩት "የንጉስ ዕቃ ለንጉስ ነውና ይረከቡን" ብለው ወደ አጤ ምኒልክ ላኩ ። ምኒልክም ደጃች ወልዴን ተረካቢ ፣ አቶ ወልደ ተክሌን የእምባው ጠባቂ አድርገው ፣ ከነበሩበት ከወሎ ወደ ሸዋ ጉዞአቸውን ጀመሩ ። ሐይቅ ሲደርሱ ደጃች ወሌን ራስ ብለው ከጨጨሆ በላይ ያለውን የየጁን ግዛት የበጌምድርንና የደንቢያን ቆራጭነት (የበላይነት) ሰጡዋቸው ። ለብሩ የዋግን ሹምነት ፣ ለዣንጥራር አስፋው እምባሰልን ፣ ለራስ ወልደ ሥላሴ ሰሜንን አደላድለው ግዛት ሰጡዋቸው ።

ከወሎ ወደሸዋ በሚጓዙበት ጊዜ ቋና ሲደርሱ ግንቦት 27 ቀን የጐጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ገቡላቸው ። ምኒልክም የቀድሞውን ቂማቸውን ትተው 41 ጊዜ መድፍ አስተኩሰው በደስታ ተቀበሉዋቸው ። በነበራቸው የቀድሞ ግዛታቸው ላይም ከፋን ጨመሩላቸው ። ደጃዝማች ነጋሽና ሌሎችም እየመጡ እጅ እየነሱ ተገዢነታቸውን ገለጡ ። የአጤ ቴዎድሮስ ልጅ ፣ ራስ መሸሻም ሲገቡላቸው የደንቢያን ግዛት ሰጧቸው ። የገባውን መኳንንት ሁሉ የያዘውን አገር እየመረቁለትና ግዛት ላነሰውም ግዛት እየጨመሩ ሁሉንም አስደስተው እንጦጦ ከተማቸው ገቡ ። የትግራይ መኳንንት ግን ራስ መንገሻን እናነግሳለን ብለው አንገባም አሉ ። ምኒልክም ከመኳንንቶቻቸው ጋር ተማክረው እነራስ መንገሻን ከማስገበራቸው በፊት ሥርዓተ ንግሥ እንዲፈጽሙ ተደረገ ።

ለመንገስ በተነሱበት ጊዜ ጳጳሳቱ አቡነ ማቴዎስና አቡነ ጴጥሮስ በኔ እጅ ይነግሳሉ እየተባባሉ ተጣሉ ። አቡነ ጴጥሮስ የአጤ ዮሐንስ ጳጳስ ሲሆኑ አቡነ ማቴዎስ ደግሞ የንጉሥ ምኒልክ ጳጳስ ናቸው። አቡነ ጴጥሮስ "ቀድሞም የንጉሠ ነገሥቱ ጳጳስ እኔ ነኝና ምኒልክ የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ መድፋት የሚገባቸው በኔ እጅ ነው" ሲሉ አቡነ ማቴዎስ ደግሞ "የንጉሠ ነገሥቱ ዕጣ ወደኔ ከደረሰ ምኒልክን የማነግስ እኔ ነኝ" በማለት ተጣሉ ። ምኒልክም ራሳቸው የፈለጉትን ጳጳስ መርጠው መንገስ ሲችሉ በሃይማኖት ጉዳይ ላለመጋባትና ሰላማዊ መፍትሔ ለመፈለግ ወደ እስክንድሪያው ሊቀ ጳጳስ ወደ አቡነ ቄርሎስ ደብዳቤ ጽፈው ውሳኔ እንዲሰጡላቸው ጠየቁ ። የእስክንድሪያው ሊቀ ጳጳስም "…. ንጉሠ ነገሥትነቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ አባ ማቴዎስ ዕጣ ከሄደ መቀባቱ ለአባ ማቴዎስ ይገባል" ብለው ላኩ ።

የንግሡ በዓል በ1882 ዓ.ም. ጥቅምት 25 ቀን በአዲስ አበባ እንዲሆን ተወሰነ ። ምኒልክም በዋዜማው ጥቅምት 24 ቀን ከእንጦጦ

ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሄደው አደሩ ። ለሊቱኑ ሥርዓተ ንግሡ ተጀምሮ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ጳጳሱ የወርቅ ሰይፍ ባርከው አስታጠቁዋቸው ። ከዚያም በወርቅ ሽቦ የታሸቡ ሁለት ጦሮች አስያዙዋቸው ። ቀጥለው የወርቅ ዘንግ ሰጡዋቸው ። ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ቅብዐ መንግሥቱን ቀብተው የወርቁን ዘውድ ጳጳሱ ደፉላቸው ። ከዚህ በኋላ ቅዳሴው ተጀምሮ ረፋዱ ገደማ ላይ አለቀ ።

የቅዳሴው ሥርዓት ከተፈፀመ በኋላ አጤ ምኒልክ በውጭ አገር በእውቅ በአምስት ሺ ብር የተሠራ ካባቸውን ለብሰው ፣ ባለወርቅ ጥላ ተይዞላቸው ፣ ዘውዳቸውን ደፍተው ፣ የወርቅ ዘንግ ይዘው ፣ የወርቅ ጫማ አድርገው ፣ ካህናቱ ከፊትና ከኋላ እያጠኑ ፣ በራሶችና ደጃዝማቾች ታጅበው ከቤተክርስቲያኑ ብቅ አሉ ። እጅግ በጣም በዝቶ የተሰበሰበው ሕዝብም የዘምባባ ዝንጣፊ እየያዘ "ሺህ ዓመት ያንግሥዎ" እያለ ደስታውን በእልልታና በሁካታ ገለጠ ።

ከቤተ ክርስቲያኑ ውጭ ለሕዝብ እንዲታዩ ከተዘጋጀላቸው ማረፊያ አልጋ ላይ ቁጭ ሲሉ "ከእንግዲህ ንጉሥህ እኔ ነኝ" ብለው ተናገሩ ። ወዲያውም "ዕዳ ያለብህ ነፃ ብየሃለሁ ። በዱር በገደልም ያለህ ምሬሃለሁ ግባ" የሚል አዋጅ ተነገረ ። አቡነ ማቴዎስም "ለንጉሠ ነገሥቱ ለምኒልክ ያልረዳ ፣ ከፈቃዱ የወጣ አውግዣለሁ" ብለው አወገዙ ።

አጤ ምኒልክ በአልጋቸው ላይ ጥቂት ጊዜ ተቀምጠው ለሕዝቡ ከታዩ በኋላ በቅሎዎች በሐር ለኮ ተስበው ቀረቡ ። በወርቅ ዘቦ ኮርቻ ፣ በወርቅ መረሸት እስከ ጉልበቷ የተሸፈነችው በቅሎ ተነጥላ ስትቀርብላቸው ልብስ ተጋርዶላቸው ካልጋ ተነስተው ከበቅሎ ሲወጡ እምቢልታና መለከት ተነፋ ።

ግምጃ ቀሚስ የለበሱ ፣ በወርቅ ዘቦ ያጌጡ ፣ ለምድ የደረቡ ግራና ቀኝ ሆነው ፣ የዝንብ መከላከያ ጭራ ይዘው ፣ወርቀዘቦ ቀሚስ የለበሱ ፣ ቀይ ከፋይ ለምድ የደረቡ ሰዎች ደግሞ ሰይፍ ይዘው ግራና ቀኝ ሲሄዱ ከእነሱ እልፍ ብለው ደግሞ በወርቅ ዘቦ ለምድ አጊጠው ራስ ወርቅ ያሠሩ ራሶች በወርቅ የተለበደ ጋሻና ጠመንጃ ይዘው ፣ ሁለቱ ሊቀመኳሶች ሊቀመኳስ አባተና ሊቀ መኳስ አድነው ቀይ ቀሚስ ለብሰው ፣ ካባ ላንቃ ደርበው ከምኒልክ ፊትና ኋላ ፣ ከፊተኛው ሊቀመኳስ ፊት ደግሞ ሊጋባው ባለወርቅ ቀሚስ ለብሰው ፣ የወርቅ ለምድ ደርበው የንጉሠ ነገሥቱን የወርቅ ዘንግ ይዘው

ይጓዙ ነበር ። በዚህ ሁሉ ዙርያ ደግሞ የሚያማምር የቤተ ክህነት ልብስ የለበሱ መነኮሳት ማጠንት ያጥናሉ ። እንዲህ ባለ አጀብ ታጅበው እልልታውን በሚያቀልጠው ሕዝብ መሀል እያለፉ ከቤተመንግሥታቸው ገቡ ።

ከቤተ መንግሥታቸው ውስጥ ከተዘጋጀው የግብር ማብሊያ ዳስ ገብተው ከተዘጋጀላቸው ዙፋን ላይ ሲቀመጡ 101 ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ። ከመድፎቹ መተኰስ ጋርም ጠቅላላው ሠራዊት የያዘውን ጠመንጃ በተኰሰ ጊዜ የጭሱ ብዛት እንደ ደመና ሆነ ። ከዚህ በኋላ የግብር ማብላቱ ሥርዓት ተጀምሮ እሁድ እስከ እኩለ ለሊት ድረስ ግብሩ ተበላ ። በማግሥቱ ሰኞም እንደዚሁ ሲበላ ዋለ ። አጤ ምኒልክ በነገሡ በሶስተኛው ቀን ማክሰኞ ዕለት እቴጌ ጣይቱ ሥርዓተ ንግሥ አድርሰው ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ ዘውዱን ከአጤ ምኒልክ እጅ ተቀብለው ደፉላቸው ።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ከማንኛውም የኢትዮጵያ ነገሥታት የተለየ የሚያደርጋቸው አንድ የንግሥ ነገር አለ ። ማንኛውም ንጉሥ በሚነግስበት ጊዜ የበፊት ስሙን ለውጦ ሲነግስ ምኒልክ ግን ስማቸውን ሳይለውጡ በዚያው በምኒልክ ነገሡ ።

አጤ ምኒልክ የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ጭነው ኢትዮጵያን መያዛቸውን ከተረዱት በኋላ ፥ ሕዝቡ በአጤ ዮሐንስ ዘመን የሚጠላውንና በግዴታ የተቀበለውን ነገር ሁሉ በአዋጅ በመሻር የመወደጃ መንገዳቸውን አበጁ ።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንደፃፉት "1ኛ. አጤ ዮሐንስ የተጠሉበት ዋና ነገር ባልተማሩ መነኮሳት ምክር እየተመሩ እስላሙን ፥ ፈላሻውን ፥ አረመኔውን ፥ ሳይማር እንዲያው በግድ ተጠመቅና ክርስቲያን ሁን እያሉ አዋጅ በመንገራቸውና አንጠመቅም ፥ ክርስቲያንም አንሆንም ያሉትን በሞትም ፥ በስደትም ፥ በእሥራትም ፥ በልዩ ልዩ መከራና ሥቃይም በመቅጣታቸው ነበር ። አጤ ምኒልክ ግን ተምሮ በፈቃዱ ተጠምቆ ክርስቲያን ካልሆነ በቀር እንደ አባቱ ሃይማኖት እንዲኖር እንጂ በግድ እንዳይጠመቅ አደረጉለት ።

"2ኛ. አጤ ዮሐንስ የተጠሉበት ዋና ነገር ማንም ሰው በመሬቱ ላይ ትንባሆ እንዳይዘራና እንዳይጠጣ አዋጅ በማናገራቸውና በመሬቱ የዘራ መሬቱን ይነቀል ። ባፉም የጉረሰ ከንፈሩን ይቆረጥ ። ሱረትም በአፍንጫው የጠጣ አፍንጫውን ይፎነን በማለታቸው ነበር ።

"አጤ ምኒልክ ግን ትምባሆ መጠጣት እንደ ጠላ ፣ እንደ ጠጅ ልማድ ነው እንጂ በመጽሐፍ የተከለከለ ፣ በነፍስም የሚያስኩንን አለመሆኑን አውቀው በትምባሆ ነገር ሰው ሁሉ እንደ ልማዱ እንዲኖር አደረጉለት ።

"3ኛ. አጤ ዮሐንስ የተጠሉበት ዋና ነገር ፣ ካንዱ አገር ወደ አንዱ አገር ሲዘዋወሩ ለወታደራቸው ሁሉ ነፃነት እየሰጡ በየባላገሩ ቤት ተሰሪ እየሆነ እየገባ የባላገሩን እንጀራውን ፤ ወጡን ፤ ጠላውን ፤ ሥጋውን ይህንም የመሰለውን ሁሉ በግድ እንዲወስድበት ስለአደ ረጉ ነበር ። አንዳንዴም የባላገሩን ሚስት በግድ እየያዘ በባልዋ ፊት ያስነውራት ነበር ይባላል ። አጤ ምኒልክ ግን ወታደር በቤትህ አይ ግባ ብለው አዋጅ ነገሩለት . . . . " ብለዋል ።

ምኒልክ ይህን የመሳሰለውንና ሌላም አዋጅ እያወጁ አብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል አሜን ብሎ ቢቀበላቸውም ትግሬዎች ግን በአጤ ዮሐንስ ሞት ምክንያት ፤ በመሀላቸውም በወራሽነት በተነሳው ብጥ ብጥ ለምኒልክ አንገብርም ብለው ተለዩ ። አጤ ዮሐንስ በመተማ ጦርነት ሰበብ ሲሞቱ ወራሻቸውን ራስ መንገሻን አድርገው ተና ዘው ነበር ። ይህ ኑዛዜ ገና ከመታወጁ በፊትም የትግሬ መኳንንት ከመተማ ጦርነት ሲመለስ እርስ በርሱ በሀሳብ ተለያይቶ ነበር ። ምክ ንያቱም አጤ ዮሐንስ ከሚቺ ከልዑል ራስ አርአያ ሥላሴ በቀር ልጅ አልነበራቸውምና የወንድሞቻቸው ልጆች ማለት የደጃች ጉግሣ መርጫ ልጅ ራስ መንገሻ ፣ የደጃች ማሩ መርጫ ልጅ ደጃች መሸሻ፣ የትልቅ ራስ አርአያ ልጅ ደጃች ቦጋለ አሊጋ ወራሽ እንሆናለን በማ ለት ገና አስቀድሞኑ እርስ በራሳቸው ይቀናኑ ስለነበር ነው ።

አጤ ዮሐንስ ከመተማው ጦርነትም በፊት ራስ መንገሻ ጉግ ሣን ከሁሉ አስበልጠው ይወዱ ስለነበር አሊጋ ወራሼ መንገሻ ነው እያለ ይናገሩ ነበር ። ይህን የሚያውቁ መኳንንት አጤ ዮሐንስ ሳይሞቱ ፣ ከሞቱም በኋላ ወደ ራስ መንገሻ ወገን ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ወደሌሎች እየሆኑ ተከፋፍለው ነበር ። ከመተማ ጦርነት መል ስም ላይ የነበረው ጉዞ በመለያየቱ ምክንያት የኩርፊያና የተነጣጠለ ጉዞ ነበር ።

ይህንንም ሁኔታ ለማጥፋትና ሠራዊቱን ለአንድ አላማ የተሰ ለፈ ለማድረግ ጳጳሱ አቡነ ጴጥሮስ ፤ እጨጌ ቴዎፍሎስ ፣ ራስ ሐጐስ ፣ ራስ ሚካኤልና ፊታውራሪ ለውጤ እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ በአን ድነት ተሰብስበው "የእነዚህ የጃንሆይ ዘመዶች አኳኋን እጅግ የሚ ያሰጋ ነው ። ራስ ወልደ ሥላሴ ከልጃቸው ከደጃች ነጋሽ ጋር በሰ ሜን ሆነው ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በጐጃም ሆነው ፣ ንጉሥ ምኒ

ልክ በወሎ ሆነው ይጠባበቁናል ። በዚህ ላይ ደግሞ በመካከላችን ስምምነት ካልተገኘ ወደ ሀገራችን ለመግባት እንኳ መቸገራችን አይቀርምና የአጤ ዮሐንስን የኑዛዜ ቃል በአዋጅ ብናስታውቅ ይሻላል ብለው ተማከሩ ።

ከዚህ በኋላ ሕዝቡንም መኳንንቱንም ሰብስበው በአዋጅ የራስ መንገሻን አልጋ ወራሽነት ተናገሩ ። የአዋጁን ቃል ደጃች ቦጋለና ደጃች መሸሻ አልተቀበሉም ። ያልተቀበሉበትም ምክንያት ለአጤ ዮሐንስ ሁሉም እኩል የሆነ ዝምድና አላቸው ። ሁሉም የአጤ ዮሐንስ የወንድም ልጆች ናቸው ። አጤ ዮሐንስ ዙፋናቸውን የሚወርስ በሕይወት ያለ ልጅ የላቸውም ። ስለዚህ "....በወንድም ልጅነት ከሆነ ሁላችንም እኩል ነንና አገራችን ከገባን በኋላ እግዚአብሔር ለሚሰጠው ይሰጠዋል" እያሉ ልብሳቸውን በአፍንጫቸው ላይ እያደረጉና እያጉረመረሙ ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ ።

በአጤ ዮሐንስ ወራሽ፣ በራስ መንገሻ በኩል እንዲህ ያለ የመለያየት ጥንስስ በመነሳቱ ለአጤ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት መሆን መንገድ ከፈተ ።የአጤ ዮሐንስን መኳንንት መለያየት ያወቀው ሌላው መኳንንትም ከሁሉ የተሻለ ኃይል ላላቸው ለምኒልክ ተገዢነቱን አምኖ ተቀበለ ። ከትግራይ መኳንንትም ቢሆን በራስ መንገሻ አልጋ ወራሽነት የከፋቸው ሁሉ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው እንደሚባለው መንገሻን ለመጉዳት ከምኒልክ ጋር እየሆኑ ያሴሩ ጀመር ። ራስ መንገሻም ከትግራይ መኳንንት ተከፍሎ ከምኒልክ ጋር ማበሩን እንዳዩ ምኒልክን የሚጐዱበትን ለመፈለግ ከውጭ እርዳታ ለማግኘት ሲሉ ከኢጣሊያ መንግስት ጋር ተወዳጁ ። ኢጣሊያኖችም ከዚህ በፊት በአጤ ዮሐንስና በንጉሥ ምኒልክ መሀል እየገቡ በነገረ ሰሪነት ያጣሉ እንደነበሩት ሁሉ አሁን ደግሞ በአጤ ምኒልክና በራስ መንገሻ መሀል ገብተው ለማጣላትና አለያይተው ለማዳከም ነገር ይሠሩ ጀመር ።

ራስ መንገሻ ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር መስማማታቸውን ምኒልክ እንዳወቁ እሳቸውም ከሌሎች ኤሮፓውያን መንግሥታት ጋር ለመወዳጀት አቀዱ ። የኤሮፓ መንግሥታት ሁሉ የኢጣሊያም መንግሥት ጭምር ምኒልክ በሙሉ ኢትዮጵያ ላይ መንገሣቸውን እንዲያውቁላቸው በነገሱ ባመቱ ቃሉ ተመሳሳይ የሆነ ደብዳቤ ለሁሉም ጻፉ ። ይህም ደብዳቤ የሚከተለው ሲሆን ያገኙሁትን ባለማህተሙን ለማውጣት ያህል ደብዳቤው ለጀርመን ንጉሠ ነገሥት የተፃፈ ነው ።



ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩ
መ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።
ይድረስ ኀበ ክቡር ወልብ ዴቱረ ሊዮፖል ንጉሠ
ነገሥት ዘበልግ ፡ አሌማኝያ ሰላም ለከ ይሁን
በልዑል እግዚአብሔር ፡ ሰኔ ፳ ቀን ከዘ፲ ተደርጎ
ከቡር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሀ ለነበሩት በኢጣ
ዮልያስ ዘፋሺ ሁሉ ጋር ዌቱ ንጉሠ ነገሥት በነ
ቡር እዮቱ ሆ በፀጋና ውል መካከል የሚደ ተቃጣ
ዎችና ወዳጅነት ሊኖሩበት ለም እንዲያገኙ ለዐል
ጠቅማቸው ንጉ ከቡር ወገኝ ጃንሆይ ለሌብልሉት ሰት
ፁዚ ሹመን ሁሉ እስካሁን ዘፈሩ ሀገሪቱ ከሌሎ
ዘረገብ ሊኖ እንዲደናቁ ተሰሩ እለዚ ብዙ ዐሊ
ሰላም ለግዛቱ ከተዙ ዘመን ፬ ዓመት ከዓሉ ለ
ደቂ በለዘ ፲ ከየዐ ሮፓ ነገሥታት ጋሬ ሠባቱ ፤ በ
ዝቀጭ ሆና ጋሉ ጋሉ ሁሉ እስከዓ ሳሊ መሰሪ ቀርቦ
ነበረ ፡ ግብርና ሥራ ሁኔታ ለውጥ እሬስ ሳና እናደተመ
ቱ እዩት እናዳ ሰላሪያቱ ሆተሻል ዐላ ሁሉ እሄሪ
ዘ ዲዳ ዓመት እያለ ዛሬ በፊት የየራሳቸው ነገሥታ
ት የቱሪ በሊ ሂድሮ ዳራሂ በደዞ እናጋቢ ለዲ
ላ ጉረቤቶች የሚገባዉ ወንድ ከና ባሌ በወዳጅነ
ት ለማንዳደርጉ ይሆናል ብለን ተሰሩ አቋርጦ
ሳለ ለዘ የባሕር ዳር የዘዉ ሲየቀጠ ጎኑ ሀ
ጠደጠርያ ለሬ ተዉ ግን ኛገ የመሮ ጠሰርያ በሌሳ
ሀ ቆያ እኛዊዳጎበ እንደ ፲ጣ ባለ፤ እርሰ በ፲ሰቁ
ው ጠቀቀል ሆኖ ዲጎጫ በኛዊሂ የሰ ወሰተቁ
ወሰናል ብለዉ ሳደሌክብኑ ጫከ ኢያቲኛጉ ዓይሰቱ

ውቀኖ ቀርተው በወሬ ውዉ ለውጪ ነው። የሰማነው
ግሰር፡ ሊሆኝ ከኛ ይሌቅ፡ ተወዳችትቶ ነበሩና እኝዴል
ቡ ሀ ጦር ወሰሌያ እጠሬ ቀዉ፡ ዘሬ፡ የተነሰ ብኛ፡ የማህ
ጁህ ወገኛ ሣይማዎትና እግር፡ የማያጠሩ/እሰለዉጅ፡
እነዚያ ግሰሮች፡ ያጠፉቀዉ፡ ትኛ፡ ወሰሪያ፡ ያዘዉ፡ ነዉ።
እባፉቾኛኛ የሚያበለ ሹ፡ ከብዙ ዘመኛ በፊት፡ ጀመ
ሮ እሰከዘሬ፡ ዱር ሰ፡ ቅዱሰ፡ ሃይማኖቶች ኛኛ ብቻ ቸ
ኛኛ፡ ጠብቀኛ ክርሰቲያኖ፡ ሕዝቦች ኛኛ መፍጀት ከሚ
ፈለጉ፡ እደ ናቸው፡ ከዚህም ቀዳሞ፡ ትልቅ ኛጉሠ ነ
ገሥታችኛ አጤ ዮሐኝሰ ጠፉ፡ ከርሰቶስ ግ፡ ሃፉ፡ በ
ዙሰዎች፡ ወደቀብኝ፡ እያሌ እግር ተዘረፈ ከፍ ዱ
ኛኛ አፉ ዩቱሃም ዘሬ ከግዱህ ያለ ከቶ ጦር በተነሣ
ግዜ ከኛ ያት እጅሬ፡ ዙፕ ጀ፡ ቅሌሉ፡ አሁኛ ማለ፡ እኛም
ይህ ኛ አይዙኛ ከየው፡ ሮፓ፡ ዊ ሉሌ ቅ ነገ ሠራ፡ ት
ሁሉ ዘኛዉ የብዩ ቢ፡ ሌከናሌ ያሌማኒያ ከቡ፡ ር ወኪ
ሉ ሠ፡ ት ኛ ሕዝቦቻ በወዩ ፎነት ሂሬ ዪ ናፊ ዩ ዘ ኛኛ
ወሉ ጀ የሚ ገበው ኛ ውሌ ሂቀ መ፡ ት ኛ ነገ ሠፉ ት ው
ሉ ኛ እፍርሰው፡ የጦር መሰሮያ ሁ፡ ሌ፡ በገሬ ቻኛ እ
ኛ ዊ ገበ ለማው ፈማ ቃግዙ ዊ ላ ቾ ሁ ዘ ለ ኘ፡ ዘሰ
ኣ፡ እየዩሮፓለኝ የዚህ ኝ ግሩ ሳ ሻ፡ እለ ተዐማሠት።
እኛ ጠብቃለን፡ በታኅሣሥ፡ በ፯ቀን፡፡
በ፲፱፻፳፬ ዓመተ፡ ምሕረት፡፡
በእንጦጦ፡ ከተማ፡ ተጻፈ፡፡

አጤ ምኒልክ ይህን ደብዳቤ ጽፈው ለየመንግስታቱ ሁሉ ላኩ ። ይህ የምኒልክ ደብዳቤ ኤሮፓ ውስጥ ክርክር አስነሳ ። አንዳንድ የኤሮፓ ምሁራን ኢትዮጵያ የነበራትን ወሰን በሰፊው አድርገው ሲያቀርቡ አንዳንዶቹ ደግሞ የምኒልክን መንገስ አፍርሰው ኢትዮጵያን ለመያዝ የፈለጉ እውነተኛ ያልሆኑ ለመንግሥታቸው የቆሙ ተከራካሪዎች ኢትዮጵያ አሁን ያላትም ወሰን ቢሆን ሲበዛባት ነው እያሉ እመሀል አፍሪካ ውስጥ ያለች ቁራጭ መሬት ቢጤ እያስመሰሉ አወሩ ። ይህን የሰሙት ምኒልክም ለኤሮፓ ነገሥታት ሁሉ የኢትዮጵያን ወሰን ለማሳወቅ አሁን የያዘችውንና በፊት የነበራትን ወሰን የሚያብራራ ፤ ቃሉ ተመሳሳይ የሆነ የሚከተለውን ደብዳቤ ለየመንግሥታቱ ሁሉ ጻፉ ።



ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብ
ሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፡፡
[illegible] ንጉሠ ነገሥት ዘሀገረ [illegible]
[illegible] ደብዳቤ [illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible] የኢትዮጵያ [illegible] ድንበር [illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible] ከኢጣሊያ ድንበር ፡ ባሕር ዳ
የኢትዮጵያ [illegible] ድንበር ይህ ነው [illegible]
ር [illegible] ፡ አፈፋ [illegible] ወደ ምዕራብ [illegible]
ሐይቅ [illegible] ይደርሳል ፡፡ ከ[illegible] እንስ
ቶ የመረብ ወንዝ [illegible] ወንዝ መገናኛ ይደርሳል ፡፡ ከመ[illegible]
[illegible] ወንዝ መገናኛ እንስቶ [illegible] ወንዝ [illegible]
ሬ ሰቲት ወንዝ ፡ መገናኛ [illegible] ከአበት [illegible] ይደርሳል
[illegible] እንስቶ [illegible]

ዩ ደርሳል ፡ ከካርቱም ፡ እንሱም ፡ ነጭ አባይ ፡ የሶባት ፡ ወንዝ መ
ገናኛ ፡ ይደርሳል ፡ ከነጭ ፡ አባይ ፡ ከሶባት ፡ ወንዝ መገናኛ ፡ እንሰማ
የሶባትን ወንዝ ፡ ይዞ እርቦሬ ጋላን ፡ [illegible] ፡ ሳምቡሩ ፡ ባሕር ፡ ደር
ስ ፡ ወደ ምሥራቅ ቦረን ጋላን ይዞ እሩሲን ሁሉ ፡ ይዞ እስከ ሶ
ማሌ ፡ ዳር ፡ [illegible] ፡ [illegible] ወደ ሰሜን ተመልሶ
ሐበር አዋልን ገዳቡርሲን ኢሳ ሶማሌን ይዞ ፡ አምቦስ ፡ ይደርሳል ፡፡
ከአምቦስ ፡ እንሶች ፡ ይደርሳል ፡ ባሕር ፡ ጨው ምድር ፡ የጥንቱ ፡ ዘጋችን ፡ የመሐመ
ድ ፡ አንፋሬን ፡ ግዛት ፡ ሁሉ ፡ ይዞ ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ እየሄደ አራፋሊ ፡ ይ
ደርሳል ፡ ይህንን ፡ ዛሬ ፡ የጻፍኩትን ፡ ድንበር ፡ ስለ ፡ ጻፍሁ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ እንደ ሰጠኝ ፡ ጉልበቴ ፡ ከሰጠኝ ፡ የጥንቱን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዳዛት ፡ እስከ
ካርቱም ፡ እስከ ፡ ኒያንሳ ፡ ባሕር ፡ ጋራ ፡ የተባለው ሁሉ ፡ ለማቅናት ፡ እፈልጋለ
ሁ ፡ ... ከ፲፬፻ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲ ፡ ክርስቲያን ፡ ደሴት ፡
በአረመኔ ፡ ባሕር ፡ ተከቦ ፡ ሲኖር ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ የመጣ ፡ መንግሥት ፡ እ
ፍሪቃን ፡ እንካፈላለን ፡ ሲል ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ ማየቴ ፡ አይታሰብም ፡፡
እግዚአብሔር ፡ ኢትዮጵያን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ እንደ ጠበቃት ፡ እንግዲህ
ም ፡ ወደፊት ፡ ይጠብቃታል ፡ ያሰፋታል ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ፡ እን
ጂ ፡ ሌሎች ፡ መንግሥት ፡ እካፈሏታል ፡ ብዬ ፡ አልጠረጥርም ፡፡
ቀድሞም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ድንበር ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ነበር ፡፡ የኢትዮጵያ
ጉልበት ፡ ሲደክም ፡ የረዳኝ ፡ ክርስቲያን ፡ ስናጣ ፡ የባሕር ፡ ድንበ
ራችን ፡ ከእስላሞች ፡ እጅ ፡ ገባው ፡ አሁንም ፡ የባሕር ፡ ዳር ፡ ድንበራ
ችንን ፡ በጉልበታችን ፡ እናገኘዋለን ፡ አንልም ፡፡ የክርስቲያን ፡ ነገሥታት ፡
ክርስቶስ ፡ አስተማራቸው ፡ የባሕር ፡ ዳር ፡ ድንበራችንን ፡ ተመል
ሰው ፡ ላይሰጡንም ፡ ከባሕር ፡ ዳር ፡ ፩፩ ቦታ ፡ ተሰጥኖ ያዩኛሉ ፡፡
ብለን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ፡፡ በሚያዝያ ፡ ፲፬ ቀን ፡፡
ባ፲፰፻፹፫ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡፡ ፡፡ ፡፡
ባዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ተጻፈ ፡፡ ፡፡ ፡፡

ምኒልክ ዝነኛ የሆነውንና እስካሁን ታሪክ ፀሐፊዎች የሚጠቅሱትን ይህን ደብዳቤ ጽፈው ኤሮፓውያን መንግሥታትን ዳኝነት ጠየቁ ። ከኢትዮጵያ ቆርሰን እንወስዳለን ወይም መላ ኢትዮጵያን እንይዛለን የማለት ሐሳብ የሌላቸው መንግሥታት ኢትዮጵያ በመቆራረስዋ እያዘኑ ምኒልክ ትክክለኛ ሐሳብ እንዳላቸው አወቁላቸው ።

ይህም ኢትዮጵያን ለመጥቀም ወይም ምኒልክን በእውነተኛው መን ገድ ለመደገፍ ብለው ሳይሆን ከፈረንሳይ ፣ ከኢጣሊያና ከእንግሊዝ መንግሥታት ጋር ቁርሾና ጥላቻ ስላላቸው ነበር ። ኢጣሊያና እንግ ሊዝ ፣ፈረንሳይም ጭምር ቢቻል እንዳቸው መላ ኢትዮጵያን ለመያዝ ፣ ባይቻል ግን ዙርያውን የያዙትን መሬት እየስፉፉ እያንዳንዳቸው ኢትዮ ጵያን ለመካፈል አሳብ ስለነበራቸው በየፊናቸው በምኒልክ ላይ ሴረ ኞችን ያበረታቱ ጀመር ።

ሌሎቹ መንግሥታት ያስነሱዋቸው ሴረኞች እምብዛም የማይ ጐዱ ነበሩ ። ኢጣሊያ ግን ቀደም ብዬ እንዳልኩት ራስ መንገሻን በመያዝዋ ኃይለኛ ባላጋራ በምኒልክ ላይ ቀሰቀሰች ። ባለፉት ገጾች በተገለጠው መሠረት በአጤ ምኒልክና በራስ መንገሻ መሀል ጠብ መነሳቱን ያዩት ኢጣሊያኖች “. . . .ከኢጣሊያ መንግሥት አንድ ነገር ቢፈልጉ በምጥዋ ወደ ሚኖረው አገር ገዢ እየፃፉ ቢያስታውቁ ለማግኘት ይችላሉ. . . .” የሚል ደብዳቤ ከኢጣሊያ ንጉሥ ከግርማዊ ኡምቤርቶ ለራስ መንገሻ መጣላቸው ። ራስ መንገሻም ይህ ደብዳቤ ከደረሳቸው በኋላ ከኢጣሊያ ጋር ወዳጅነታቸውን አጠናክረው አንድ የወዳጅነትና የፍቅር ውል ለመዋዋል ኢጣሊያኖችን ጠየቁ ። የአሥመ ራው ገዥ ጀኔራል ጋንዶልፊ የራስ መንገሻን ጥያቄ በሰማ ጊዜ ወዲ ያው ከወሰናቸው መረብ ድረስ ተገናኝተው ጉዳዩን እንዲጨርሱ ተስ ማምተው ሁለቱም በቀጠሮው መረብ ከወሰኑ ላይ ተገናኙ ። ማንኛ ውንም ነገር በቃል ከተነጋገሩ በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ውል ተፃ ጽፈው ተፈራረሙ ።

1ኛ. ውል የኢጣሊያ መንግሥት ራስ መንገሻን የሚጠላ ጠላቱ ነው ። ራስ መንገሻን የሚወድ ወዳጁ ነው ። ራስ መንገሻን ይወደዋል ፣ ያከብረዋል ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ልጅ እንደመሆኑም ያውቀ ዋል ። ራስ መንገሻን የሚያሳዝን ትንሽ ነገር ስንኳ ምንም እንዳያደ ርግ ምኗል ።

2ኛ. ውል ፣ ራስ መንገሻ የኢጣሊያን መንግሥት የሚጠላ ጠላቱ ነው ። የኢጣሊያን መንግሥት የሚወድ ወዳጁ ነው ። የኢጣሊያን መን ግሥት ይወደዋልና ያከብረዋል ። የኢጣሊያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን እንደመሆኑ ያውቀዋል ። የኢጣልያን መንግሥት የሚያሳዝን ትንሽ ነገር ስንኳ እንዳያደርግ ምኗል ።

3ኛ. ውል ፣ ከእንግዲህ ወዲህ በትግሬ ሰዎችና በኢጣሊያ ሰዎች መካከል ሰላምና ፍቅር ሆንዋል ። ከዚህ በቀር ሌላ የሚዋዋሉበት ነገር የለም ።

መረብ ላይ ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፰፻፹፪ ዓ.ም.



ራስ መንገሻ

ይህን ውል በሚዋዋሉበት ጊዜ አጤ ምኒልክ ደሴ ነበሩ ። ራስ መንገሻ ከኢጣሊያ ጋር መዋዋላቸውን አጤ ምኒልክ እንደሰሙ ደሴ ድረስ መጥተህ እንገናኝ ብለው ለራስ መንገሻ ላኩባቸው ። ራስ መን ገሻ ለጊዜው እሺ እመጣለሁ ብለው መልስ ላኩ ። ይህን ጥሪ የሰ ማው የትግራይ መኳንንት አጤ ምኒልክ ልጃቸውን ወይዘሮ ሸዋረ ጋን ለራስ መንገሻ ሊድሩላቸው ነው እያሉ የጥሩ ምልክት ወሬ ሲያ ወሩ ፤ ኢጣሊያኖች ግን ከኛ ጋር መዋዋልዎ ሳይሰማ አልቀረምና ወደ ደሴ የተጠሩት ሊታሠሩ ነው እያሉ ራስ መንገሻን ስለመከሩዋ ቸው ወደደሴ ሳይሄዱ ቀሩ ። በዚህም ምክንያት ራስ መንገሻ ከኢጣሊ ያኖች ጋር ማበራቸው ተረጋገጠ ። አጤ ምኒልክም በዚህ ጉዳይ አዘኑ። የትግራይ መኳንንት አስቀድመውኑ ልጃቸውን ሊድሩላቸው ነው እያለ ያወራው እውነት ነበር ። በኋላ ግን ራስ መንገሻ ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር መዋዋላቸው በመረጋገጡ ምኒልክ ተናደው ልጃቸ ውን ወይዘሮ ሸዋረጋን ለራስ ሚካኤል ድረው ለትግሬ መኳንንት የተሰናዳውን ሽልማት ለወሎ መኳንንት ሸልመው ወደ ሸዋ ተመ ለሱ ።

አጤ ምኒልክ ወደሸዋ ቢመለሱም በዚያን ጊዜ የኮሌራ በሽታ ተነስቶ ነበርና ከአዲስ አበባ ወደ እንጦጦ ፤ ከእንጦጦም ወደ አንኮ በር ሲሸሹ በሽታው እየተከታተለ ብዙ ሰው ጨረሰባቸው ። በአንኮ በር ከርመው በሽታው በረድ ሲል መስከረም 11 ቀን 1885 ዓ.ም. ከአንኮበር ተነስተው መስከረም 23 ቀን እንጦጦ ገቡ ። በሽታው ሲበ ርድ ደግሞ ሌሎች መንግሥት ገልባጮች ተነሱ ። ደጃች መሸሻ ወር ቁና አለቃ አድማሱ ዋና ነገር ጠንሳሾች ሆነው ሌሎችንም መኳን ንት ለማሳደም ተነሱ ። አድማውም ምኒልክን ገድለው የመርድ አዝ ማች ኃይሌን ልጅ ፊታውራሪ ጉልላቴን (ተክለማርያምን) ለማንገሥ ነበር ። እነዚህ ሰዎች እየተያዙ ሲጠየቁ ሁሉም አመኑ ። ለፍርድ ቀር በውም በሁሉም ላይ የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው ። አጤ ምኒልክ ግን የሞት ፍርዱን ለውጠው በእስራት እንዲቀጡ ስለፈረዱ ፊታውራሪ ጉልላቴ ለራስ ዳርጌ ፤ ደጃች መሸሻ ወርቄ ለደጃች ወልደ ጊዮርጊስ፣ አለቃ አድማሱ ለደጃች ወልዴ ተሰጥተው እንዲታሠሩ ሆነ ። ምኒል ክን ለመግደል የተስማማው የምኒልክ የእልፍኝ አሽከር አበበ የሚባ ለው ግን እጅና እግሩ ተቆረጠ ።

በዚሁ ዘመን ማለት በ1885 ዓ.ም. ራስ መንገሻ በትግራይ ውስጥ የንጉሥነት ማዕረግ መግለጫ የሆነውን ቀይ ጃንጥላ ያስይዙ ጀመር ። ይህንንም ያደረጉ ራስ አሉላ ናቸው ። ራስ አሉላ በዶጋሊ ጦርነት ምክንያት ከኢጣሊያኖች ጋር ፍቅር ባይኖራቸውም ፣ በአጤ ዮሐ ንስ ዘመን ምኒልክ ከኢጣሊያኖች ጋር ተወዳጅተው አጤ ዮሐንስን

ሲያናድዱ መኖራቸውን አሉላ ስለሚያውቁ ፡ አሁን ደግሞ ነገሩ ተገ ልብጦ አጤ ምኒልክን ለማናደድ ራስ መንገሻ ከኢጣሊያኖች ጋር ተዋውለው ወዳጅነት በመመሥረታቸው ራስ አሉላ ፡ መንገሻን ለማን ገስ ሕዝቡን ይሰብኩና ያነሳሱ ጀመር ። ራስ መንገሻም የራስ አሉ ላን ምክር በመቀበል በ1885 ዓ.ም. የትግራይን ሕዝብ ሐውዜን ላይ ሰብስበው ከአጤ ምኒልክ መከዳታቸውንና ለመንገሥም መነሳታቸ ውን አሳወቁ ። ሕዝቡም ለመንገሥ ማሰባቸውን እንዲያምን ቀይ ጃንጥላ አስይዘው ታዩ ። ወዲያውም ባለ አንበሳ ማኅተም አዘጋጅ ተው በደብዳቤ ራስጌ ማተም ጀመሩ ። እዚህ ላይ ነገሩን ግልፅ ለማድ ረግ በደብዳቤ ራስጌ ማኅተም የሚያደርግ ንጉሠ ነገሥት ብቻ እንጂ የንጉሥነት ማዕረግ ያለው እንኳ ቢሆን ማኅተሙን የሚያትመው ከደብዳቤ ግርጌ ወይም መጨረሻ ላይ ነው ።

ራስ መንገሻ መረብ ላይ ከኢጣሊያኖች ጋር የተዋዋሉት ፡ ምኒ ልክን ለማናደድ እንጂ ኢትዮጵያን ለመጉዳት አልነበረም ። ምኒልክን የመጣል እቅዳቸውን ከፍጻሜ ለማድረስ ኢጣሊያኖች የጦር መሣ ሪያ እንዲሰጡዋቸው ጠየቁ ። የኢጣሊያ መንግሥትም "ለመንገሻ የጦር መሣሪያ መስጠት ወላዋይ ሰው ስለሆነ ሊከዳ ስለሚችልና መልሶ እኛኑ ስለሚወጋበት አያስፈልግም" በማለት ከለከለ ። ራስ መንገሻ ደጋግመው ቢጠይቁ "በውላችን መሠረት ጠላትዎ ጠላታችን ነው ። እኛ እያለን እርስዎን የሚደፍር ባላንጣ ስለማይመጣ አይስጉ" በሚል መደለል ብቻ መሣሪያውን ከለከለ ። ኢጣሊያኖች መሣሪያውን የከለ ከሉበት ምክንያታቸው እውነትነት ያለው ነው ። ራስ መንገሻ ለጊ ዜው ባደረባቸው ንዴትና ቁጭት የምኒልክን ጠብ ለመወጣት መሣ ሪያ ይጠይቁ እንጂ ነገ ሲደላደሉ ኢጣሊያኖችን ከድተው መልሰው የሚወጓቸው ሰው ነበሩ ። እየቆዩም ነገሩን እራሳቸው ሲያስቡት አድ ራጐታቸው የአጤ ዮሐንስንና የትግራይን ሕዝብ ስም የሚያስጠፋ መስሎ ስለታያቸው በአድራጐታቸው ተፀፅተው ይማሩኝና ልግባ የሚል ደብዳቤ ጽፈው በ1886 ዓ.ም. በሹም አጋሜ ተስፋዬ እጅ ወደ አጤ ምኒልክ ላኩ ። አጤ ምኒልክም "ቀድሞውንም ቢሆን የኢት ዮጵያ ጠላቶች አስመስለው ቢነግሩት ይሆናል እንጂ እርሱ ከልቡ አቅንቶ ይህን ሥራ እንዳልሠራ አውቄዋለሁ" ብለው "ባለፈው ጥፋትህ ሁሉ ምሬሃለሁና ወደ አዲስ አበባ እንድትመጣ ይሁን. . . ." የሚል መልስ ላኩላቸው ።

ራስ መንገሻም በሚያዝያ ወር 1886 ዓ.ም. ከትግራይ ተነስ ተው በግንቦት አዲስ አበባ ገቡ ። አብረዋቸው ራስ አሉላ ፡ ራስ ሐጐስ፣ ሹም አጋሜ ተስፋዬና ሌሎችም መኳንንቶች ነበሩ ። በአዲስ አበባም አንድ ወር ያህል ቆይተው ከዘውድ በቀር ለንጉሥ የሚገባ ሽልማት

ተሸልመው ከሰነበቱ በኋላ ሰኔ 7 ቀን ከአዲስ አበባ ተነስተው ወደ ትግራይ ጉዞ ጀመሩ ።

ጉዳዩን ባጭሩ እናድርገውና ወደፊት እንደምናነበው ከኢጣልያ አገር ተልኮ የመጣው ዶክተር ትራብርሲ የውጫሌ ውል እንዳ ይፈርስና እንደፀና እንዲቆይ ከአጤ ምኒልክ ጋር ተነጋግሮ ሳይሳካለት ቀረ ። ይህንኑ ያለመሳካቱን ለኢጣልያ መንግሥት አስታውቆ በተ ሰጠው ትእዛዝ መሠረት ከራስ መንገሻ ጋር ለመነጋገር ወደ ትግራይ ሔደ ። ከዚያም ራስ መንገሻ ከኢጣልያ መንግሥት ጋር የጀመሩትን ወዳጅነት እንዲያጠናክሩና በውላቸውም መሠረት እንዲገፉበት ያባብል ጀመር ። ራስ መንገሻ ግን “. . . . መረብ ላይ ከእናንተ ጋር የወዳጅነት ውል መዋዋሉ . . . . ከጠብ ፍቅር ይሻላል ብዬ ነው እንጂ አገሬን ኢትዮጵያንና ንጉሤን ምኒልክን ከድቼ ከእናንተ ጋር ለመሆን የተዋዋልሁት ውል የለኝም . . . .” ብለው በኢጣሊያኖች ሐሳብ ያለመስማማታቸውን ቆርጠው ተናገሩ ። አንዳንድ ኢትዮጵያኖችም “....እርስዎ የአጤ ዮሐንስ ልጅ ሆነው ለአጤ ምኒልክ መገዛትዎ ትልቅ ውርደት ነው....” እያሉ ቢመክሩዋቸውም ራስ መንገሻ የሁሉንም ምክር አልቀበል አሉ ።

በዚሁ ሰሞን ደርቡሾች ከኢጣሊያኖች ጋር ለመዋጋት በከሰላ በኩል ጦራቸውን አሰለፉ ። ኢጣሊያኖችም ለጦርነቱ ይዘጋጁ ጀመር ። ራስ መንገሻም የሁለቱን ጦርነት ለማዳመጥና አሸናፊውም ወሰን አልፎ እንዳይገባ ለመጠባበቅ ከወሰን ላይ ሔደው ተቀመጡ ። በዚያም እንዳሉ ከሐማሴንና ከሠራዬ አውራጃዎች ከኢጣሊያ እየከዱ ብዙ መኳንንትና ሠራዊት ገባላቸው ። ወደራስ መንገሻ ብዙ የኢጣልያ ሠራዊት እየከዳ ቢገባላቸውም ከራስ መንገሻም በኩል ቢሆን እየከዱ ወደ ኢጣሊያ የገቡ ነበሩ ። ከእነዚህም አንዱ ደጃች ሐጐስ ተፈሪ ናቸው ። ደጃች ሐጐስ ከኢጣሊያ ዋና ጦር አዛዥ ከባራቲየሪ ዘንድ ሲደርሱም ታላቅ ደስታ የተሞላበት አቀባበል ተደረገላቸው ። ከዚህ በኋላ ባራቲየሪ ሌላውን ሁሉ ትቶ ወደ ትግራይ ዘምቶ ራስ መንገሻን ለመውጋት ወሰነ ።

የሠራዊቱን መክዳትና ያለመረጋጋት ያየው ባራቲየሪ ወደ ትግራይ መዝመቱ ቢሰማ መላው ሠራዊት እንደሚከዳው ስላወቀ ዘመቻውን እንዳይጠረጥሩ ሠራዊቱን ሰብስቦ “.... እኔ ራሴ ወደ አድዋ ሔጄ ከራስ መንገሻ ጋር ለመነጋገር እፈልጋለሁ ። የምንጋገረውም መረብ ላይ የተደረገው ውላችን ለምን እንደፈረሰ ተወቃቅሰን ለመታረቅና በውላችን ለመጽናት ነው ።....” በማለት ንግግር አደረገ ። ወዲያውም ራስ መንገሻ የባራቲየሪን መምጣት እንዳይቃወሙና ጦርን

ትም እንዳያነሱ ለማታለል ሲል "....እኔ የምመጣው መረብ ላይ ያደረግነውን ውል ማን እንዳፈረሰው ተወቃቅሰን እንድንታረቅ ነው ፡ የሚሻለንም መታረቁ ነው ። የሕዝቡ ደም በከንቱ ቢፈስ ጉዳት እንጂ ምን ጥቅም አለው?...." የሚል ደብዳቤ ጽፎ ላከላቸው ።

ጄኔራል ባራቲየሪ ሕዝቡንም ሆነ ራስ መንገሻን በቃላት ድለላ ለሱ እንደመሰለው ካረጋጋ በኋላ ታህሣሥ 19 ቀን 1887 ዓ.ም. ከሠራዬ ተነስቶ በሠራዊቱ ታጅቦ ወደ አድዋ ጉዞውን ጀመረ ። በዚህ ጊዜ ራስ መንገሻ ኢንትጮ ነበሩ ። ባራቲየሪ አድዋ እንደደረሰም የአድዋ ከተማ ካህናትና ሕዝብ ለወዳጅነት የመጣ መስሏቸው ታላቅ አቀባበል አደረጉለት ። ጄኔራል ባራቲየሪም ከአድዋ ሕዝብ መሀል እንደገባ ከፈረሱ ወርዶ በሰልፍ ከቆሙት ካህናት ዘንድ ተጠግቶ የያዙትን መስቀል ተሳለመ ። ወዲያውም ቀዳሚ ጦሩን ወደ አክሱም እንዲሔድ አዝዞ እዚያው አድዋ ውስጥ ሸብረብ ሲል በድንገት ሳይታሰብ የራስ መንገሻ ሠራዊት ዙርያውን ከብቦ ከጭንቅ ላይ ጣለው ።

ጄኔራል ባራቲየሪ ከፈረሱ ላይ ወጥቶ እብረውት የቀሩትን ወታደሮቹን ለማሰለፍና ቦታ ለማስያዝ ቢሞክርም የራስ መንገሻ ሠራዊት በቀላሉ የማይፈታ መሆኑ ገባው ። ስለዚህ የሚሻለውን መንገድ መርጦ ከፈረሱ ወርዶ ወደ ካህናቱና ቄሶች ዘንድ ቀረበ ። ለእነሱም "....እኔ የመጣሁት ለፍቅርና ለእርቅ ነው ። ለጦርነት አልመጣሁምና ቢሆን ከራስ መንገሻ ጋር አስታርቁኝ ። ለመታረቅ ፈቃዳቸው ካልሆነ ግን ለቀውኝ ወደ አሥመራ እንድመለስ እማልዱኝ ።...." ብሎ ለመናቸው ። እጨጌ ቴዎፍሎስ ለአቀባበል ወጥተው በሕዝቡ መሀል ነበሩና ድምፃቸውን ከፍ አድርገው "....እርሱ እንደዚህ እያለ የፍቅር ነገር ሲናገር እናንተ ለምን ጠብ ትፈልጉታላችሁ...." እያሉ በቁጣ ስለተናገሩ የራስ መንገሻ ሠራዊት ቃላቸውን ተቀብሎ "....አሁንኑ አገራችንን ለቅቆ ከሔደልን እሺ እንደ አባታችን እንደእርስዎ ቃል እንፈፅማለን...." ብሎ መለሰላቸው ። ከዚህ በኋላ ወዲያውኑ ባራቲየሪ በፈረሱ ሆኖ ሠራዊቱን ይዞ ወደ አዲኳላ ሔደ ።

ባራቲየሪ ሊለቀቅ የቻለው ካህናቱና ሕዝቡ በእርግጥ ለሰላም የመጣ ስለመሰላቸው ነው ። እጨጌ ቴዎፍሎስ ግን ባራቲየሪ ለሰላም ጉዳይ ያለመምጣቱን በእርግጥ ያውቁ ነበር ። ብላቴን ጌታ ኅሩይ ስለዚህ ጉዳይ ሲተቹ "....እጨጌ ቴዎፍሎስ እጅግ ተከብረውና ተፈርተው የሚኖሩበት የአጤ ዮሐንስ መንግሥት ወደ አጤ ምኒልክ በማለፉ ደስ አላላቸውም ነበርና የማታልፈውን ኢትዮጵያን ሳያስቡ አጤ ምኒልክን ብቻ የሚጐዱ ስለመሰላቸው የራስ መንገሻን መኳን

ንት አማልደው ጄኔራል ባራቲየሪን አዳኑት እንጂ የእርሱ አመጣጥ ለእርቅና ለሰላም አለ መሆኑን ፈፅመው ያውቁ ነበር ። ከዚያም አስ ቀድሞ ዋጋው እጅግ ብዙ የሆነ ባለወርቅ ጥልፍ ካባ ካስመራ ልኮላ ቸው እንደነበርና ወዳጅነትም ጀምረው እንደነበረ የአክሱም ካህና ትና በከተማውም የሚኖሩ ትልልቅ ሰዎች ሁሉ ያውቃሉ ....” ብለ ዋል ።

ጄኔራል ባራቲየሪ ወደ አዲኳላ ከተመለሰ በኋላ ብዙ ወታደሮች አዘጋጅቶ ራስ መንገሻን ለመውጋት ወደ ኩአቲት ሰደደ ። በአድዋ ያለው የራስ መንገሻ ሠራዊትም የኢጣሊያ ጦር ተደራጅቶ መም ጣቱን እንደሰማ እጨጌ ቴዎፍሎስን በግልጥ ያማርርና ይወቅስ ጀመር። ከእንግዲህ በኋላም ማማረሩ ዋጋ እንደሌለው ታውቆ ራስ መንገሻ ሠራዊታቸውን ለጦርነት አሰለፉ ። ራስ መንገሻ ለጦርነት ከተሰለፈው ሠራዊታቸው ፊት ቆመው ብላቴን ጌታ ኀሩይ እንደጻፉት “ ....ስለ አገራችን ነፃነት ተዋግተን ሲሆን ድል እናደርጋለን ። ባይሆንም ደማች ንን ረግጠ ይገባል እንጂ እንዲያው አይገባምና አትፍሩ ። የዮሐንስ ፣ የምኒልክ አምላክ ይረዳናል ....” እያሉ ሲናገሩ ሠራዊታቸው ግልብጥ ብሎ ፎከረላቸው ። ከዚህ በኋላ ወደ ኩአቲት ጉዞ ጀመሩ ።

ራስ መንገሻ ሠራዊታቸውን እየመሩ በተፈጥሮ ምሽግ የሆነውን ኩአቲትን ኢጣሊያኖች ሳይዙት ቀድመው በመግባት ያዙ ። ባራቲየ ሪም ሠራዊቱ ኩአቲትን ቀድሞ እንዲይዝ አዝዞ ስለነበር ኩአቲት በራስ መንገሻ ሠራዊት መያዙን ሲሰማ አዘነ ። ቢሆንም በሆነው መን ገድ ከራስ መንገሻ ጋር ለመዋጋት ጥር 4 ቀን ከተሰያት በኋላ ጦሩን አሰለፈ ። የኢጣሊያ ጦር በ66 መኰንኖችና በ105 ባለሌላ ማዕረግ ነጮች የሚመራ ሲሆን ከወታደሩ አብዛኛው ግን የቅኝ ግዛት ወታ ደር ነበር ።

ባራቲየሪ ስለዚያን ጊዜው ስለ ጥር 4 እና 5 ቀን ሁኔታ ሜሞ ሪ. ዲ. አፍሪካ በተባለው መጽሐፍ ላይ ሲገልፅ “ ....ማታ ጠላቶ ቻችን ከሜዳ ላይ በሚያነዱት እሳት የምድጃውን ብዛት መቁጠር እንችላለን ። ዙሪያ ከብ እየሆኑ ከመሀል እሳት ያነዳሉ ። ....በኛ ካምፕ ሲመሽ ፀጥታ ይሆናል ። ....በዚህ ምክንያት ጠላት ያለንበትን ቦታ ስለማያውቅ ለሊት ሊያጠቃን አይችልም ።....ከመንጋቱ ሁለት ሰዓት ቀደም ብሎ የጦር መኰንኖቼን ሰብስቤ ትእዛዝ አዘዝኩ ። መመሪያም ሰጠሁ ። የ4ኛው የጥቁር ብርጌድ አዛዥ ማጆር ቶዞሊ በቀኝ በኩል ፣ በመሀል ደግሞ የ3ኛው የጥቁር (ያገር ተወላጅ) ባታሊዮን አዛዥ ማጆር ጋሊያኖ ፣ ከጋሊያኖ በኋላ የሁለተኛው የእግር ተወላጅ ባታ ሊዮ አዛዥ ሂዳልጎ እንዲሆኑ አደረግሁ ። መድፎቻችን ግን በቶዞሊ ትእዛዝ ሥር እንዲሆኑ አዘዝሁ ።

"....ጠሀይዋ ወገግ ስትል የጠላት ቦታ ፈገግ ብሎ ታየን ፡፡ ጠላት ያለ ሐሳብ ተቀምጧል ፡፡ ከጧቱ ለ12 ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ጦርነቱን ጀመርን ፡፡ የቶዞሊ ባታሊዮን መድፍ ይተኩስ ጀመር ፡፡ በጋሊያኖ ውስጥ ያሉት ሳንጉኔቲ እና መቶ አለቃ ሙላዚኒ መሀል ለመሀል እየገፉ ሔዱ ፡፡ ለእነሱም ከኋላ ያለው የሂዳልጐ ባታሊዮን ሽፋን ይሰጣቸዋል ፡፡ ....ውጤታችን እያማረ ሔደ ፡፡....ሲነጋ የካፒቴን ቺኮዲ ኮላ መድፈኛ 1900 ሜትር የሚጓዝ የመድፍ ጥይቱን ጠላት ላይ ይጥል ጀመር ፡፡ እኔም የኢጣሊያን ባንዲራ አስይዤ ከመሀል ሆኜ አዛለሁ ፡፡....የ3ኛውና የ4ኛው ባታሊዮን ጠመንጃ ተኳሽም ወደፊት እየገፋ ሔደ ፡፡....በግራ በኩል ተጠቃን ፡፡....በቀኝ በኩልም ከባድ ጥቃት አደረሱብን ፡፡....በመሀልም ባለው ሠራዊት ላይ ከባድ ጥቃት ስላደረሱ የኛን ሠራዊት ወደኋላ እንዲያፈገፍጉ አደረጉት ፡፡ ...የ3ኛው ባታሊዮን አዛዥ ጋሊያኖ በስተግራ ዞሮ እንዲያግዝ አደረግሁ ..." ይላል ፡፡

ጋሊያኖ እንደታዘዘው በስተግራ በኩል ለመዞር ሲሄድ ኢትዮጵያኖቹ ከባድ ጉዳት አደረሱበት ፡፡ ከጧቱ ሶስት ሰዓት ተኩል ሲሆን ሂዳልጐ ፣ ካፒቴን ፓቬሲ እና ብራባንቲ በአዲስ ጉልበት ጠንክረው እንዲዋጉ ታዘው ከጦርነቱ መሀል ገቡ ፡፡ ራስ መንገሻ ደጅን ሆነው የጦር ነጋሪታቸውን እያስመቱ በለው ይላሉ ፡፡ ከኢጣልያ በኩል የሚወድቁት ቁስለኞች በዶክተር መቶ አለቃ ቢርዲያ ይታከማሉ ፡፡ ከኢትዮጵያውያን በኩል የሚወድቀው ቁስለኛ ግን ደሙ እንዳይፈስ ጨርቅ እንኳ የሚያስርለት ሐኪም የለውም ፡፡ ሐኪም ቀርቶ ጓደኛውም ቢሆን ወደፊት ጠላቱን እየመታ መግፋት እንጂ ጓደኛውን ለማንሳት አሳብ አልነበረውም ፡፡ ድሉ ለማን እንደሆነ ሳይታወቅ የጥር 5 ቀኑን ጦርነት ምሽት ገላገለው ፡፡

ባራቲየሪ ማታውኑ አዲስ ጦር ባስቸኳይ እንዲመጣለት ትእዛዝ አስተላለፈ ፡፡ ሲነጋጋ ጥር 6 ቀን የራስ መንገሻ ሠራዊት ጦርነቱን ከፈተ ፡፡ ኢጣሊያኖቹ የታዘዘው አዲስ ጦር እስኪመጣላቸው ድረስ በመከላከል ብቻ ቆዩ ፡፡ ባራቲየሪም ኢትዮጵያውያኖቹ ጥይታቸውን እንዲጨርሱ አስደርጉ እያለ ሠራዊቱን ስላዘዘ የኢጣሊያ ሠራዊት ለመዋጋት ሳይሆን ኢትዮጵያኖቹን ጥይት ለማስጨረስ ብቻ እየቆዩ ይተኩሱ ጀመር ፡፡ ወዲያውም አዲስ የታዘዘው ጦር በጄኔራል አሪሞንዲ እየተመራ ደረሰ ፡፡ ይህም አዲስ ጦር ብዙም ሳይዋጋ ጊዜው ስለመሸ ጦርነቱ ቆመ ፡፡

የኢጣሊያ ጦር ባካባቢው ያለውን ውሃ ይዞት ስለነበረ ኢትዮጵያውያኖቹ በውሃ ጥም ከባድ ድካም ደረሰባቸው ፡፡ ቢሆንም ተበረታ

ትተው ለሶስተኛው ቀን ዙር ውጊያ ሲዘጋጁ አንድ ወሬኛ ለኢጣሊ ያኖች ስንቅና ጥይት ለማቀበል የመጡትን ብዙ አጋሰሶች አይቶ ለኢጣሊያ ሊቆጠር የማይችል አዲስ ጦር መጣላቸው ብሎ በፉስ መንገሻ ሠፈር ስላወራ የራስ መንገሻ ጦር ተፈታ ። ራስ መንገሻም የሠራዊታቸውን መበታተን እንዳዩ የቀሩዋቸውን ጥቂት ወታደሮች አስከትለው ከምሽቱ በ4 ሰዓት ወደ ሰንአፌ ሔዱ ።

በማግስቱ የራስ መንገሻ ወደ ሰንአፌ መሔድ በኢጣሊያኖች ዘንድ እንደተሰማ በጄኔራል አሪሞንዲ የሚመራ ጦር በአስቸኳይ እንዲከታተላቸው ተደረገ ። ራስ መንገሻም በሰንአፌ ሜዳ ድንኳን አስተክለው ሠራዊታቸውን ግብር አስገብተው ሲያበሉ ኢጣሊያ ኖች በድንገት ደርሰው አምባ ታሪክ ከሚባለው ሥፍራ ሆነው መድፍ መተኮስ ጀመሩ ። ወዲያውኑም ባራቲየሪ ደርሶ መድፍ ተኳሾቹ በራስ መንገሻ ድንኳን ላይ ብቻ እንዲተኩሱ አዘዘ ። በዚህ ሳይታ ሰብ ድንገት በደረሰው አደጋ የራስ መንገሻ የተረፈ ሠራዊታቸው ተደናግጦ የተተከለውን ድንኳን እንኳ ሳይነቅል ሸሸ ። ኢጣሊያኖ ችም ከራስ መንገሻ የሰንአፌ ሠፈር ገብተው 17 ነጋሪት ፣ ጐራዴ ጋሻና ጦር ሌላም የጦር መሣሪያ ወዳድቆ ያገኙትን ሁሉ ወሰዱ። በተለይ ግን ኢጣሊያኖችን ያስደሰታቸው አጤ ምኒልክና ራስ መንገሻ የተጻጻፉዋቸውንና ራስ መንገሻ ከሐማሴን መኳንንት ጋር በኢጣልያኖች ላይ እየዶለቱ የተጻጻፉዋቸውን ደብዳቤዎች ማግኘ ታቸው ነበር ። በኮአቲትና በሰንአፌው ጦርነትም ለአገራቸው ክብር ሲዋጉ ከሞቱት መሀል ደጃዝማች ተድላ ፣ ደጃዝማች በየነ ፣ ደጃ ዝማች ካሣ ፣ ቀኛዝማች እንዳርጋቸውና ሌሎችም ይገኙበታል ። ከራስ መንገሻ ሠራዊት በጠቅላላ የሞቱት 1500 ሰዎች ያህል ሲሆኑ የቆሰሉት ደግሞ 2000 ይሆናሉ ። ከኢጣሊያኖቹ በኩል ሶስት ከፍተኛ መኰንኖች ያሉበት 95 ሰዎች ሲሞቱ ሁለት መኰንኖች ጨምሮ 299 ሰዎች ቆሰሉ ።

ኢጣሊያኖች ከራስ መንገሻ ጋር ባደረጉዋቸው ጦርነቶች በጠቅ ላላ 153.725 የጠመንጃ ጥይቶች እና 228 የመድፍ ጥይቶች ተተኩሰ ዋል ። በዚህ አስተሳሰብ ከራስ መንገሻ ሠራዊት 2000 ሰዎች ሞቱ ብንል እንኳ ኢጣሊያኖች አንድ ሰው ለመግደል 77 ጥይት ተኩሰ ዋል ማለት ነው ። ያውም የመድፉ ጥይት ባንድ ጊዜ የሚያደርሰውን እልቂት ሳንጨምር ነው ።

በዚህ ዘመን ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ወላሞ ዘምተው ስለነበረ የራስ መንገሻን ከኢጣሊያኖች ጋር የመዋጋት ወሬ ወዲያውኑ አልሰ ሙም ነበር ። ከወላሞ ዘመቻ ተመልሰው ጥር 11 ቀን 1887 ዓ ም አዲስ አበባ ሲገቡ የራስ መንገሻን ድል የመሆን ዜና ከራስ መንገሻ

መልክተኛ ሰሙ ። ወዲያውም ተከታትሎ ጄኔራል ባራቲየሪ ለአገር ጥበቃ ማጆር ጋሊያኖን በሰንአፌ ትቶ ፤ ከድተው የገቡለትን ደጃዝማች ሐጐስ ተፈሪን በአጋሜ ሾሞ እሱ አዲግራት ገብቶ መቀመጡ ተነገ ራቸው ። እንዲያውም መቀሌ ድረስ ዘምቶ ራስ መንገሻን አባርሮ ሊይዝ ነው እየተባለ ይወራ ጀመር ።

አጤ ምኒልክ ለራስ መንገሻ ደብዳቤ ጽፈው "እስክመጣ እንዳትዋጋ" የሚል መልክት ልከው የደከመ ጦራቸውን አሰባስበ ውና አዘጋጅተው በግንቦት ወር ወደ ትግራይ ጉዞ ጀመሩ ። አጤ ምኒ ልክ ወረኢሉ ሲደርሱ "....ኢጣሊያኖቹ የመጡባቸው መስሏቸው ሸሽተው ሔዱ ።...." የሚል መልክት ከራስ መንገሻ ደረሳቸው ። አጤ ምኒልክም ምናልባት ኢጣሊያኖቹ እንደ ገና የመ ጡ እንደሆን ብለው ቀኛዝማች ኃይለ ማርያምን ፤ ፊታውራሪ ንጉሤን ፤ ግራዝማች ኃይለ ማርያምን ፤ ባላምበራስ በየነን ከራስ መንገሻ ጋር ሁናችሁ አገር ጠብቁ ብለው ወደትግራይ ላኩዋቸው ። እሳቸው ግን ክረምቱን አዲስ አበባ ለማሳለፍ ብለው ሰኔ 29 ቀን አዲስ አበባ ገቡ ።

ኢጣሊያኖች የአጤ ምኒልክን መመለስ እንደሰሙ መቀሌ ሔደው ራስ መንገሻን ለመውጋት ወሰኑ ። ራስ መንገሻም የኢጣሊያኖችን እን ደገና ጦር ማዘጋጀት ሲሰሙ ከመቀሌ ወጥተው ወደ ሕንጣሎ ሔዱ ። ራስ መንገሻ ወደ ሕንጣሎ የሄዱበት ምክንያት 1ኛ ከአጤ ምኒልክ ሳያስፈቅዱ ለመዋጋት ባለመቻላቸው ፤ 2ኛ በፈቃዳቸው ጦርነቱን ቢገጥሙ እንዳለፈው ጊዜ ድል የሆኑ እንደሆን ለክብራቸው የማይ ገባ ውርደት መሆኑን በመገመት ነው ። ኢጣሊያኖችም ራስ መንገሻ መቀሌን ለቀው መውጣታቸውን እንደሰሙ ከአዲግራት ተነስተው ያለችግር መቀሌን ያዙ ። በመቀሌም ምሽግ መሥራትና መዘጋጀት ጀመሩ ። ራስ መንገሻን ግን ጄኔራል አሪሞንዲ እና ማጆር ቶዞሊ ተከ ታትለው እንዲወጉ ታዘዙ ።

ራስ መንገሻን እንዲወጉ የታዘዙት የኢጣሊያ ሹማምንት በግስ ጋሴ ወደ ሕንጣሎ ሔዱ ። ራስ መንገሻም የኢጣልያኖቹን መከታ ተል እንደሰሙ ሕንጣሎን ትተው ወደ ደብረ ኃይላ ተጓዙ ። ደብረ ኃይላም ከራስ መንገሻ ጋር የነበሩት መኳንንት ተሰብስበው "..... ከእንግዲህ ወዲህ መሸሽ አይገባንም ። እግዚአብሔር ኃይሉን ቢሰ ጠን ድል እናደርጋለን ። ድል ባናደርግም ስለሀገራችን ስለኢትዮጵያ እንሞታለን ። ራስ መንገሻ ግን ቢማረኩም ፤ ቢሞቱም ለሰዋቻውና ለሀ ገራቸው ውርደት ሲሆን ለኢጣሊያኖች ግን ትልቅ ደስታ ይሆናልና ከሸዋ ጦር እስቲመጣ ወደ ራስ ወሌ ግዛት ተጠግተው ቢቆዩ ይሻ ላል ።...." ብለው መክረው መኳንንቱ ሠራዊቱን ይዞ ሲቀር ራስ መንገሻ ወደ በላዋ ሄዱ ።

በማጆር አሜሊዮ የሚመራው ጦር ገስግሶ ራስ መንገሻን ለመ ያዝ ደብረ ኃይላ ሲደርስ ራስ መንገሻን አጣቸው ። በዚያ የቀረው የራስ መንገሻ ሠራዊት ከኢጣሊያኖቹ ጋር ጦርነት ገጥሞ ከሁለቱም ወገን ብዙ ሠራዊት ካለቀ በኋላ ኢጣሊያኖቹ ድል አደረጉ ። ከራስ መንገሻ መኳንንቶችም መሀል ቀኛዝማች ኃይለማርያም ብቻ ቆስ ለው ሲማረኩ ሌሎቹ እየተታኮሱ አመለጡ ። ቀኛዝማች ኃይለማር ያም ጀግንነታቸው በኢጣሊያኖች ዘንድ ሁሉ የታወቀ ነበርና ማራ ኪዎቹ ኢጣሊያኖች በክብር አንስተው በሚገባ አሳክመው ካገገሙ በኋላ ወደ አሥመራ ላኩዋቸው ።

ከዚህ በኋላ የኢጣሊያ ጦር ወደ አምባላጌ ሔደ ። በአምባላጌም ራስ መንገሻ አስረው ያስቀመጡዋቸውን ፣ ለኢጣሊያኖች የቀድሞ ወዳጃ ቸው የነበሩትን ራስ ስብሃትን ከነልጆቻቸው ፈትተው የምሥራች ብለው ወደ ጄኔራል ባራቲየሪ ላኩዋቸው ። ራስ ስብሃትም ከጄኔራል ባራቲየሪ ዘንድ ሲደርሱ ታላቅ ክብር የሞላበት የደስታ አቀባበል ተደረገላቸው ። ወዲያውም የእንደርታ አውራጃ ገዥ ብሎ ሾማቸው ።

ራስ ስብሃት የአጋሜው ባላባት የሰባጋዲስ የልጅ ልጅ ናቸው። ራስ መንገሻና ራስ አሉላ በነገር ሠሪ ምክንያት በተኮራረፉበት ጊዜ ራስ ስብሃትም ከራስ አሉላ ጋር በነገሩ አሉበት ተብለው ነበር ። በዚያውም ላይ ደግሞ የራስ መንገሻን ሁኔታና ይዞታ ሁሉ ለኢጣሊ ያኖች ያቀብላሉ እየተባሉ ይታሙ ስለነበረ ራስ መንገሻ ፣ ራስ ስብሃ ትን ከነልጆቻቸው አምባ ሰላማ ከሚባል ቦታ አስረው አስቀመጡ ዋቸው ። ራስ መንገሻ ከኢጣሊያኖቹ ጋር ኩአቲት ላይ ሊዋጉ ሲሉ ኢጣሊያኖች ፈትተው እንዳይወስዱዋቸው ወደ አምባላጌ አዛወሯቸው ። ራስ ስብሃት በአድዋ ጦርነት ጊዜ ለኢጣሊያኖችም ለኢትዮጵያው ያኖችም የተዋጉ ጀግና ናቸው ። ይህንንም በሥፍራው እናገኘዋለን

ራስ መንገሻ ኢጣሊያኖቹ እየተከታተሉና ሰላምም ስላሳጡዋቸው ለኢጣሊያው ንጉሥ ለቀዳማዊ ኡምቤርቶ የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉ ።

ለታላቁ ንጉሥ ቀዳማዊ ኡምቤርቶ
የተላከ ከጽዮን ንጉሥ ልጅ ፣ ከራስ መንገሻ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

እንደምን ከርመዋል ። እግዚአብሔር ይመስገን እኔ ደህና ነኝ ። ክፉ ሥራ ስለተሠራብኝ አዝናለሁ ። ጄኔራል ባራቲየሪ እኔ እንደጉዳ ሁት አድርጎ ያወራል ። በነገራችን መሀል ሰይጣን ገብቶ ክርስቲያን ሕዝቦች እርስ በራሳቸው ተላለቁ ።

ባለፈው የተደረገው ነገር የሰይጣን ሥራ ነው ። አሁን ሰላም እፈልጋለሁ ። አሁን እርስዎ እውነተኛ ሰው ልከው ከእኔና ከጄኔራል ማን እንዳጠፋ እንዲያጣሩ እጠይቃለሁ ። ይህንንም የምጠይቀው የጥንት ወዳጅነታችን እንደነበረ እንዲመሠረት ፈልጌ ነው ።

ተጻፈ የካቲት ፲፫ ቀን አዲ ኡምዳይ ።

በደብዳቤያቸው ላይ እንደምናየው ራስ መንገሻ አሁንም ቢሆን ራሳቸውን ንጉሠ ነገሥት እንዳሉ ናቸው ። ራስ መንገሻ ይህን ደብ ዳቤ ለኢጣሊያው ንጉሥ ከላኩ በኋላ ጄኔራል ባራቲየሪ ሐሳቡን እንዲሰጥና ከትትሉን ላላ እንዲያደርግላቸው ከኢጣሊያ መንግሥት ተጠየቀ ። ባራቲየሪም ለመንግሥቱ ጥየቃ መልስ ሲሰጥ “. . . .የሚታመኑ ስላልሆነ ጠቅለው ወደኛ ካልገቡ ሰላም የለም ። . . . . ” ብሎ መለሰ ። ከዚህ በኋላ የአድዋው ጦርነት ተጀመረ ።

በአድዋ ጦርነት ራስ መንገሻ ታላቅ ጀብዱ የሠሩና ያስመሰ ከሩ ጀግና ናቸው ። በአድዋው ጦርነት ብዙ ኢጣሊያኖችን ማርከው ከፍተኛ ድል አስገኝተዋል ። የአድዋ ድል በተገኘ ባመቱ ኀዳማ በ18 89 ዓ.ም. ራስ መንገሻ “ናፍቁአለሁና መጥቼ ዓይንዎን ልይ” ብለው ወደ አጤ ምኒልክ ልከው ካስፈቀዱ በኋላ በታህሳስ ወር አዲስ አበባ ገቡ ። በዚህ ጊዜ ራስ መንገሻ የእቴጌ ጣይቱን የወንድም ልጅ ወይዘሮ ከፈይን አግብተው ስለነበረ ለምኒልክ ቤተመንግሥት ቤተኛ ሆነዋል ። በአዲስ አበባም በታላቅ ክብርና ደስታ ከርመው ፣ ተሸል መው ፣ ለሠራዊታቸው ደሞዝም 60ሺ ብር ተቀብለውና ተሰናብተው ወደ ግዛታቸው ወደ ትግራይ ሄዱ ። ትግራይ ሲደርሱ እንደገና የመሸ ፈታቸው ወሬ ተሰማ ። ራስ መንገሻም “ከእንግዲህ ወዲህ የምንገና ኘው በጦርነት ነው” የሚል መልእክት በእነ ሊቂ ወልደየስ ላኩ ።

አጤ ምኒልክም ይህን መልእክት እንደሰሙ ከቤተ መንግሥት መምህር ዜናን ፣ መምህር ፈቃደን ፣ የወሎውን መምህር አካለወል ድን ፣ የሐይቁን መምህር አባ አምደ ሥላሴን ፣ የግሼኑን ግራጌታ ውቤ ንና አባ ወልደ ገብርኤልን መስቀል አስይዘው “. . . .የትግሬን አድባ ራት ሁሉ ይዛችሁ እኔ በድየህ እንደሆነ ማረኝ ፣ ይቅር በለኝ ብላችሁ መስቀሉን ተሸክማችሁ ውደቁና አስታርቁኝ. . . .” ብለው ላኩዋቸው ።

እቴጌ ጣይቱም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ላኩ ።

“ይድረስ ከልጄ ከወዳጄ ከራስ መንገሻ።የላኩሃቸው ሰዎች እነሊቂ ወልደየስ ለጃንሆይ የነገሩትን ነገር ሰምቼ አጥብቆ ገረመኝ ። ደነቀኝ ። የያዝነው ፍቅርና ወዳጅነት እንዲህ ባጭሩ ይቀራል አልመሰለኝም ነበር።

እኔስ የፍቅራችን ርዝራዥ ፣ እንኳን ባንተና በኛ ዕድሜ ፣ ቆይቶ ለልጅ ልጅ ያልፋል ይመስለኝ ነበር ። እነከሳለሁ ብየ በቅሎ ገዛሁ። ዓይኔ ይጠፋል ብዬ መሪ አበጀሁ ፣ ያላሰብኩት ጆሮዬ ደነቆረ ያለው ተረት በኔ ደረሰ ። እኛ ያንተን ቤት እንሠራለን ብለን ስንደ ክም የኛን ቤት አፈርሳለሁ ብለህ አሰብከውን ። ይህንን ነገር እግዚ አብሔር ይወደዋልን ።ሰይጣን ያደረበት ሰው እነሳስቶሃል እንጂ አን ተስ የክርስቲያን ልጅ ክርስቲያኑ ይህን ነገር አታደርገውም ። አሁ ንም ልጄ ስለመድኃኒዓለም ፣ ስለተሰቀለው ጌታ ፣ ስለወላዲት አምላክ እማጥኝሃለሁ ። ይህን ክፉ አሳብህን ተው ። የሰይጣናትን ክንፋቸውን ስበረው ።ከዚህም ቀደም ራስ አሉላና ራስ ሐጐስ ወንድማማቾቹ ቢያልቁ አንተን የማይወድ ሰው ሁሉ ደስ ይለዋል ብለን በዚህ አዘን ። ደግሞ ዛሬ ከዚህ የባሰ ነገር ሊመጣ ነው ። ጠላቱ ፣ ደመኛው ከኋላው ቆሞ እየጠበቀው ፣ ዙሮ ከወንድሙ ከወዳጁ ጋር የሚጣላ ሰው አለን ። ይህን ነገር አእምሮ የተሳለበት ሰው ያውቀዋል ። እኔም እናትህ ፣ ወዳጅህ በዚህ ባደረግኸው ነገር አጥብቄ አዘንሁ ። አጥብቄ አለቀስሁ ። እህል ለሰጠ አፈር ፣ወርቅ ለሰጠ ጠጠር ይመለሳልን ። እኔስ ቆሜም ተቀምጨም ባስበው አንተን ያደረግንብህን የሚያስቀ ይመውን ነገር አጣሁት ። አንተም በሰው አታመካኝ ። እገሌ እንዲህ ቢለኝ ነው ፤ እገሌ እንዲህ ቢለኝ ነው አትበለኝ ። ባንተና በኛ መካ ከል ገብቶ ክፉ ነገር የተናገረብህ ሰው የለም ። እግዚአብሔር ይጐዳ ሃል ። ደግሞስ ከአድዋ እንስቶ እስከ መረብ ድረስ የፈሰሰው የክርስ ቲያን ደም ወደ እግዚአብሔር ቢጮህ አያስጐዳህምን ። ደግሞ ሁለተኛ የሸዋና የትግሬ ሰው የወንድማማቾቹ ደም ይፍሰስን ። እኔም የእና ትነቴን መከርኩህ ። ደግሞ እግዚአብሔር ይጨመርበት" ብለው ላኩ። ከዚህ ከእቴጌ ጣይቱ ደብዳቤ ጋርም የደብረ ሊባኖስና በሸዋ ያሉ ገዳማት መምህራንና ሊቃውንትም የሚከተለውን ደብዳቤ ፃፉላቸው ።

ይድረስ ከራስ መንገሻ ። ወልዱ ለዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ፣ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።*—

የተላከ ከመምህራን ወሊቃውንት ዘደብረ ሊባኖስ ወኩሉ አድ ያሚሃ ለብሔረ ሸዋ ።

መሐሪ መመስተሣህል ፣ እግዚአብሔር ቸርነቱን አያርቅብዎ ብለን እጅ እንነሳለን ። ይህ የሰማነው ነገር እጅግ አሳዘነን ። የኛ ድካም የመንገዱ ርቀት ነው እንጂ እኛንም ሁላችንንም የሚያስመጣ ነበር ።

---

* ንጉሠ ነገሥት የሚለው አጤ ዮሐንስን ነው ።

እሁንም ይህን የፃፍንልዎን ወረቀት በንፁህ ልቦናዎ ይቀበሉን ። ቃሉም ይህ ነው ። ለጂ ፈራሁ ብለው ላኩ ማለትን ሰማን ። አጤ ምኒ ልክ እስዎን ግብር እምጡ ቢሉዎ አላስቀሩ ፣ ዘምተህ ይህን አገር ውጋ ቢሉዎ ከዘመቻ ወስልተው አልቀሩ ። ሰው የሚያውቀው ምን ክፉ በደል በድለው እጄን ይይዙኛል ብለው ጠረጠሩ ። በወዲያ አገር ያለ ሰው ሁሉ ዛሬ የሚመለከተው ኢትዮጵያን የኛን አገር ነው ። የውጭ ጠላት እንዳይገባባችሁ አገራችሁን መጠበቅ ይመስል እናን ተን አባትና ልጁን የሚያነቃቅፍ ምን ነገር ተገኘ ። ያን ጊዜ እንኳን ራስ መንገሻ ከዳ እያለ ቢያወሩብኝ መጣሁ ብለው ልብዎ ደህና ቢሆን ስተት ብለው ገስግሰው መጡ ።

ደግሞ በአጤ ዮሐንስ ጊዜ የትግሬ ሰው ፣ የበጌምድር ፣ የጐ ጃም ሰው ምኒልክ አጤ ዮሐንስን ከዱ እያሉ ከአጤ ዮሐንስ በተለ ያዩ ቁጥር ቢያወሩ የሰው ነገር አልሰማም እያሉ ሁልጊዜ ከመግባት አልተለያዩም ። ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ጋር የተዋጉ ጊዜ አጤ ዮሐንስ መሸሻ ሰይፉን ፈትተው እምባውን ሰብረው በዚያ በውሃ ሙላት ቢመጡብዎ [1] ወታደሩ ባላገሩ ሊያስርዎ ነው እያለዎ [2] እንኳ ሌላ ካጤ ዮሐንስ ሠፈር ያለው መኳንንቱ ሁሉ ሊያስርዎ ፣ ነው እያለ ቢልክብዎ [3] አንድ ጊዜ ምያለሁ ፣ ተገዝቻለሁ ፣ ከደጃፌ ድረስ መጥቶ ቢወጋኝ ጠላቴን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ወጋሁ እንጂ የበደልኳቸው ነገር የለ ። እንዳወቁ ያድርጉኝ እንጂ ምን አደር ጋለሁ ብለው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን በሰንሰለት እንኳ ሳያደርጉ ከነዘውዳቸው ይዘው ከልብዎ ውል ውል ነገር ባይኖርብዎ [4] ስተት ብለው ገቡ ። ነገር ግን አጤ ዮሐንስ የትግሬን ሰው ረግመውታል ሲሉ እንሰማለን ። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ከመተማ ከገባችሁ ወዲህ የትግሬ ሰው መኳንንቱም ፣ ወታደሩም ፣ ባላገሩም እርስ በርሱ ሲተላ ለቅ ኖረ ። ያው ያጤ ዮሐንስ ርግማን እስከዛሬ ድረስ ከትግሬ ሰው ላይ አልተነሳምና እርስዎን በጤና አላስገዛም ብሎ ነው እንጂ ሌባ ፣ ቀማኛ ፣ ወንበዴ በጠፋበት ጊዜ ፣ ሴት ወርቅ በራስዋ ላይ አድርጋ ብትሄድ በማትነካበት ፣ እህልና መሬት ፣ ሰውና እህል በተስማማበት ጊዜ ፣ ዳር እስከ ዳር አገሩ ሁሉ ጸጥ ብሎ በተገዛበት ጊዜ ፣ በስሜን፣ በበጌምድር ፣ በጐጃም ነቅዕ አልወጣ ፣ ደርቡሽ እንኳ አጤ ዮሐንስን ያህል ንጉሠ ነገሥት ገድሎ ዳግመኛ በእግዚአብሔር ቸርነት ባገራ

---

1. ቢመጡባቸው
2. እያላቸው
3. ቢልከባቸው
4. ባይኖርባቸው

ችን ብቅ አላለብንም ። እንደርስዎ ያለ ሰው የጌታ ልጅ መሠረተ ጌታ ለበጐ አርአያ እብነት ይሆናሉ እንጂ ከዚህ መካከል ራስ መንገሻ ሸፈተ ይባላሉን ። ለክፉ አርአያ መሆን መቼ ይገባል ።

ደግሞ አጤ ምኒልክ ራስ መንገሻ ከድቶኛል ፣ እሱ እንደከዳኝ እኔ አውቀዋለሁ ብለው አሉ ብሎ ሹም አጋሜ ተስፋዬ ነገረኝ ማለ ትዎስ አይመስለንም ። እንኳን ለእሽከርዎ ፣ ለወዳጅዎ ለሹም አጋሜ ተስፋዬ ፣ ለሌላውም ሰው ቢሆን እንዲህ ያለ ነገር አይናገሩም ። አጤ ምኒልክ ሰፊው እጅዎ[5] ነው እንጂ አፍዎ[6] ጠባብ ነው ። ዛሬ እንኳ ራስ መንገሻ ከዳኝ ብለው ባፍዎ[7] አያነሱትም ። እውነት አጤ ምኒልክ ራስ መንገሻን አስረዋለሁ ብለው በልብዎ[8] ሐልዮ እንደ ሌለ በሥጋው ፣ በደሙ ፣ በስዕል ፣ በመስቀል እንማል ፣ እንገዝት ። ጃን ሆይንም ያስታምኑ ።

ደግሞስ ያን ጊዜ ከኢጣሊያ ጋር ተዋግተን ስንመለስ በዚያ በጭንቀት ፣ በዚያ በረሃብ ፣ በሐምሌ በውሃ ሙላት ተዝካሬን ታወጣ ልኛለች የሚሏትን ልጅዎን[9] እቴጌ መስጠትዎ[10] ቤቱ ቤትዎ እንዲ ሆን ልቦናዎ እንዳይሰጋ ለመተማመን አልነበረምን ። ይህን ሁሉ ዘሎ እንደዔት ያለ ክፉ ነገር መጣ ። ራስ ዘውዴን እንኳ አንድያ ወታደር የነበረውን ከድህነት አውጥተው የሻለቃነት፣ ከሻለቃነት ፊታውራሪነት፣ ከፊታውራሪነት ራስነት ሰጥተው ራስ ወርቅ ባገልግል አድርገው ደብረታቦር ድረስ ሰደው ይሄን ሁሉ አድርገውለት ቢከዳዎ[11] ተይዞ ቢመጣ መሰቀል ፣ መደብደብ ፣ መቆረጥ ሲገባው በጅራፍ እንኳ ሳይገርፉ ክፉ ቃል ሳይናገሩ ማሩት ። አጤ ምኒልክ እንደ ፈጣሪዎ[12] ነቅዓ ምሕረት ነዎ.[13] እንጂ ክፉ ነገር መቼ በሰው ይሠራሉ ። ይህንን ሰይጣን ያነቃውን እናጥፋው ። ክንፉን እንሰበረው ። ስለተሰ ቀለው ጌታ ፣ ስለኩርዓተ ርእሱ ብለው ይተዉልን ።"

እነኚህን ሁለት ደብዳቤዎችና የአጤ ምኒልክን የቃል መልክት የያዙት መልክተኞች መቀሌ እንደገቡ ከትግራይ ፣ ጌታ ኃይሉን ፣ ጌታ

---

5. እጃቸው
6. አፋቸው
7. ባፋቸው
8. በልባቸው
9. ልጃቸውን
10. መስጠታቸው
11. ቢከዱቸው
12. ፈጣሪያቸው
13. ናቸው ።

ገብረ ጊዮርጊስንና ሌሎችንም መኳንንትና መምህራን ጨምረው ከራስ መንገሻ ዘንድ ገብተው "መማር የሚገባ ለኔ ነበር ። ግን አንተ ማረኝ ብላችሁ መስቀሉን ተሸክማችሁ ውደቁ ብለውናል" ብለው መስቀሉን በየቆባቸው እያደረጉ ወደቁ ።ራስ መንገሻ ግን ሳቁባቸው ።

አጤ ምኒልክ በ1891 ዓ.ም. በጥቅምት ወር ደሴ ሔደው ወረ ኢሉ ነበሩና ወደራስ መንገሻ የተላኩት መልክተኞች "እኛ አል ሆነልንም ። ጃንሆይ እንደሚያደርጉ ያድርጉ" ብለው ላኩባቸው ። ከዚህ በኋላ አጤ ምኒልክ በራስ መንገሻ ቦታ በትግራይ "ለልጄ ለወዳጄ ለራስ መኰንን በሐረርጌ ላይ ትግሬን ሰጥቼዋለሁ" ብለው ሾሟቸው ።ወዲያውም ቀጥሎ ያለው አዋጅ ታወጀ ።

ስማ የትግሬ ሰው

ራስ መንገሻ ፥ ፊት ደጃች ሥዩምን አስሬ እሱን ብሾመው ከዳኝ። አሁን ደግሞ እሹሁን ነቅዬ ፥ አደላድዬ ሹሜው ብመጣ እኔን አባቱን ከዳኝ ። የትግሬ ሰው አድባራቱም ፤ መኳንንቱም ፣ ራስ መንገሻ ሰወ ደው ጠልቶኛልና ግፌን እይልኝ ። እኔ ግን ያጤ ዮሐንስ ወረታ እመ ልሳለሁ ብዬ መኳንንትና ወታደር ሳይወደው በግድ ሹሜው ነበ ርና መሬት አሰናበተችው እንጂ እኔ በድየው አይደለም ። አሁንም የትግሬ ሰው ወዳጄ ነህ ። ራስ መንገሻ ከዳኝ ብዬ በሱ ተናድጄ አላጠፋህም ። እግዚአብሔር የሰጠኝን አገሬን በጄ አድርጌ አለማዋ ለሁ ። ደስ አሰኝሃለሁ ። እይዞህ ፥ ግባ ፥ በያባትህ እተክልሃለሁ ። አባትህን መርቅ ፥ አባትህን እርገም ። ልብህ ያሰበውን የሚያደርግ ልህን ፥ ለባሕርይህ የሚስማማህን ልጄን ወዳጄን ራስ መኰንንን ሰጥቼሃለሁ ። ከሐረርጌ ጋራ ትግሬን ማድረጌ አንተን እንዲያለማህ ፥ አንተን እንዲጠቅምህ ብዬ ነው ። የሱን ይሰጣችኋል እንጂ ከትግሬ የሚፈልገው ነገር የለም ። አራሽም እረስ ። ነጋዴም ነግድ ። ከዚህ ወዲህ ከመንገሻ ጋር የተገኘህ ሰው በነፍስህም ተገዝተሃል ። በሥጋ ህም እኔ እቀጣሃለሁ ። ርስትህን ፤ ጉልትህን እስከ ፫ ትውልድ እነቅ ልሃለሁ ።"

አጤ ምኒልክ ይህን ካወጁ በኋላ ምናልባት ራስ መንገሻ ጦር ነት ያነሱ እንደሆነ በማለት ከአዲሱ ተሿሚ ከራስ መኰንን ጋር ራስ ሚካኤልን ፥ ዋግሹም ጓንጉልንና ደጃዝማች አባተን አብረው እንዲሄዱ አዘዙዋቸው ። እነኚህም መኳንንቶች መቀሌ ሲደርሱ ራስ መንገሻ ከመቀሌ ወጥተው ኢጣሊያኖች ከሠሩት እዳጋሐሙስ ካለ ምሽግ ውስጥ ገቡ ። ከራስ መኰንን ጋር የሄደው ጦርም እዳጋ ሐሙ ስን ከብቦ ተቀመጠ ። ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ራስ መንገሻ በሰ

ላም እጃቸውን እንዲሰጡ እንደገና ይጠየቁ ጀመር ። በተለይም ራስ ሚካኤል ያጤ ዮሐንስ የክርስትና ልጅ በመሆናቸው ከራስ መንገሻ ጋር ልዩ ወዳጅነት ነበራቸውና "....እባክህ እኔ ላስታርቅህ ። ምን ሆንክና ነው ። ያንተን አገር የሚሸምብህ የለ ። አትታሰር ። ደርስህ አጤ ምኒልክን ፣ እናትህን እቴጌ ጣይቱን ትተህ ከደን ትገባለህ...." እያሉ ደጋግመው ደብዳቤ ፃፉላቸው ። ራስ መኰንንም እንደዚሁ እያባበሉ ደብዳቤ ቢጽፉላቸው ራስ መንገሻ የሁሉንም አልሰማ ብለው እምቢ አሉዋቸው ።

ከዚህ በኋላ ከራስ መኰንን ጋር ያሉት መኳንንት መክረው በመዋጋቱ ወሰኑ ። ወስነውም እነሱ በግንባር ፣ ከበስተኋላ በአጋሜ በኩል ደግሞ አራት ሺ ጠመንጃ የያዘ ሠራዊት አሰለፉ ። ለመሰለል የወጣ የራስ መንገሻ ጥቂት ሠራዊት በአጋሜ በኩል ከተሰለፉት ወታደሮች ጋር ተገናኝቶ ተኩስ ከፈቱ ። የራስ መንገሻም ሰዎች ተጐድተው የተረፉት ወደ ምሽጋቸው ገቡ ። ከዚህ በስተቀር ምንም ግጭት አልተደረገም ። ስለመጨረሻው ሁኔታ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በጻፉት ታሪክ እንዲህ ይላሉ ። "....የሰፈረበት ሠፈር ካጠገባቸው ያለ ተራራ፣ በሰማይ ደመና ሳይዞርና ዝናም ሳይኖር በጠራራ ፀሐይ ከቀኑ 6 ሰዓት ሲሆን ገደሉ ተናደበት ። የተቀመጡበት መሬት እንደከዳቸው ያንጊዜ አወቁት ። ገደሉም በተናደ ጊዜ እነራስ ሚካኤልም ፣ እነራስ መኰንንም ከሰፈሩበት ድረስ ተሰማ ። እነሱም ይህ ነገር የመድፍ ተኩስ ነውን ፣ ጦር መጣ ይሆን ብለው ታጥቀው ተሰልፈው እስኪወጡ ድረስ የመሬቱ ጩኸት ድምጡ ሲሰማ አንድ ሰዓት ያህል ቆየ.... እሱም ከዚያ ወዲያ ትግሬ አገራቸውን ለወደዱት ይሹሙበት ። እኔን ለጃ አስምሩኝ ብሎ እስተማምኖ ገባ ።...."

አጤ ምኒልክም ትግራይን ለሶስት ከፍለው ፣ ከወር ወንዝ ወዲያ ያለውን አገር ለደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ፣ ከወር ወንዝ ወዲህ ያለውን አገር ለደጃች አብርሃ ፣ አጋሜን ለሹም አጋሜ ደስታ ሰጡ ። ራስ መንገሻም አንኮበር ላይ ታሰሩ ።

ራስ መንገሻ በእስር ላይ ሆነው "....ጥፋት የለብኝምና እንደ ገና ፍርድ ይታይልኝ ። ጥፋተኛ ሆኜ ከተገኘሁ ግን ከዚህ ካለሁበት ከባሰ እስራት ልታሠር ።...." ብለው ወደ አጤ ምኒልክ ላኩ ። አጤ ምኒልክም የሚከተለውን ደብዳቤ መልስ ጻፉላቸው ።

ይድረስ ከልጄ ከወዳጄ ከራስ መንገሻ ።

ከድቼ ብገኝ አደባባይ አይቶት እንደገና ከብርቱ እስራት ልግባ ብለህ ላከብኝ ።አገርህንስ የተሻርክበት አንተስ እስካሁን ከኔ የተለየ

ሀበት ከፍቃዴ ብትወጣ ብትከዳኝ ነው እንጂ አለዚያማ በምን ምክ ንያት ይህ ሁሉ ተደረገ ። እኔም ይህን አደባባይ ይታይ እንዳልል ከዚህ ቀደም አደባባይ አይውጣ ፤ ፍትሐ ነገሥት አይታይ ብለህ ሰውን ሁሉ አማልክ ። ደግሞስ እነራስ ሚካኤል ፣ እነራስ መኰንን የዘመቱት ባንተ ክዳት ነው እንጂ ማንን ሊፈልጉ ሔዱ ።ደግሞም ደብዳቤም አለኝ ትላለህ አሉ ። አሁንም ደብዳቤውንም በተረፈ ነገ ሩም እኔን በውል እንዲገባኝ አድርገህ ሁሉንም ነገር ገልጠህ ለታ መነ ሰው ላክብኝ ። ከኔም ዘንድ ይሄውና በጅሮንድ ገድሌን ልኬል ሃለሁ ።

ሕዳር ፲፮ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ራስ መንገሻ በእስር ላይ እንዳሉ በተወለዱ በ42 ዓመታቸው በ1899 ዓ.ም. ሕዳር 6 ቀን በወጣትነት ዘመናቸው አንኮበር ላይ ሞቱ ።

በራስ መንገሻ ግዛት ትግራይን ተካፍለው የተሾሙት ደጃች አብርሃ ለጥቂት ዓመታት ከምኒልክ ጋር ወዳጅ ሆነው ከቆዩ በኋላ ከምኒልክ ከድተው ሸፈቱ ። ጦር ታዞም ድል ሆነው ደጃች አብርሃ ተይዘው ታሰሩ ። ይህን የተደጋገመ የከዳት በደል ያየው ሕዝብም በትግሬዎች ላይ ቂም ይዞ በያገኘበት ቦታ ሁሉ ይሰድብ ጀመር ። ይህንንም ድርጊት ምኒልክ እንደሰሙ የሚከተለውን አዋጅ በሕዳር ወር 1902 ዓ.ም. አወጁ ።

## አ ዋ ጅ

አንድ ሰው ደጃች አብርሃ ቢከዳ እዚህ የተቀመጠውን እኔን የሚወደኝን የትግሬን ሰው ሁሉ ታስቀይማለህ አሉ ። አባያ ወንድሙ ይታሠርበታል እንጂ ይታረዳልን ። አሁንም ዳግመኛ ባደባባይ ያለ ውን የትግሬን ሰው የሚያስቀይም ነገር የተናገርክ ትቀጣለህ ። አደ ባባይም ያለህ የትግሬ ሰው የሚያስቀይም የተናገረህን ሰው ተያይ ዘህ አምጣልኝ ። ዳኝነት ይታይልሃል ።

## የረሃብ ዘመን

ምኒልክ ባላንጣዎቻቸውን ለማረጋጋትና አገሪቱን ለማደላደል በሚራወጡበትና በሚደክሙበት ጊዜ በኢትዮጵያ ከባድ ረሃብ ደረሰ ። ይህ የረሃብ ዘመን ከ1880 እስከ 1884 ዓ. ም. ድረስ ለአምስት ዓመታት ያህል ቆየ ። በነዚህ ዘመናት ይህ ረሃብ ሊደርስ የቻለው የከብት በሽታ ገብቶ ከብቱን ስለጨረሰው ነበር ። የከብቱ በሽታ የመጣው ከሕንድ በመጡ ከብቶች ምክንያት ነው ። ኢጣሊያኖች ምፅዋን ይዘው መስፋፋት እንደጀመሩ አንድሬአሊ የተባለ ኢጣሊያዊ ብዙ ከብቶች ከሕንድ አገር አስመጣ ። ከብቶቹ በሾኬ ወይም ደስታ በሚባለው በሽታ የተለከፉ ስለነበሩ በሽታው ተስፋፍቶ ብዙ ከብቶችን ጨረሰ ። ከዚያ ወደ ትግራይ ፤ ቤጌምድር ፤ ላስታና ጐጃም ተላለፈ ። ቀጥሎም ወደ ሸዋ ገባ ።

በደረሰው የከብት ማለቅ ምክንያት ከዳር እስከ ዳር ያለው የእርሻ ተግባር ቆመ ። በገበያም ላይ የእህል ዘር አልታይ አለ ። ከረሃቡ በፊት ባንድ ማርትሬዚያ ብር 20 ቁና ስንዴ ይገዛ የነበረው አሁን ያውም በድብቅ ገበያ ባንድ ማርትሬዚያ ብር አንድ ቁና ተኩል ስንዴ ይሸመት ጀመር ። ድሮ ባንድ ማርትሬዚያ ብር 40 ቁና ገብስ ይሸመት የነበረው በአሁኑ ጊዜ ሁለትና ሦስት ቁና ሆነ ። ሕዝቡ ለማረስ ቢፈልግም የማረሻ በሬዎች ሁሉ በበሽታው ስላለቁ በሬ ጠፋ ። ቢገኝም ያንድ በሬ ዋጋ 80 ብር ደረሰ ። ድሮ ግን ዋጋው ከሁለት እስከ አራት ብር ነበር ። ድሮ ስድስት የበግ ሙክት ተመርጦ ባንድ ብር ይገኝ ነበር ። በረሃቡ ጊዜ የማይመረጥ አንድ ኮሳሳ በግ ዋጋው አራት ብር ሆነ ። ረሃብ ስለጠናም ሕዝቡ በብዛት ያልቅ ጀመር ። ረሃቡ በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሆነ የሕዝቡ እልቂትም በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር ።

ሕዝቡም "እህል በፊት ሲሸሽ በሬ ሲያባርር ፤
ሁሉም ተከታትለው ጠፉ አሉ ካገር ።
እህል ታሟል አሉ ሒደን እንየው ፤
የማይተርፍ እንደሆን እኛ እንቅደመው ።
እኔ ከእህል ጋራ ይቅርታም የለኝ ፤
ሲያልቁ ዘመዶቼ ይብላኝ ያላለኝ ።
እህል ኮበለለ ሒዶ በነፋስ ፤
ተከተለው በሬ እንዳይመለስ ።" እያለ ያለቅስ ጀመር ።

በምኒልክ ዘመን ስለደረሰው ረሃብ ብዙ ሰዎች ጽፈውለታል ። እንደዚያን ጊዜው ረሃብም የተፃፈለት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የለም ።ለማወቅ ያህል የዘመኑ ፀሐፊዎች እንዴት እንደጻፉ በመጠኑ እናንብብ ። ክሩዜት ሲጽፉ "....የከረን ሕዝብ የሚበላውም ሆነ የሚዘራው የለውም ።....ባካለ ጉዛይ አውራጃም ረሃቡ ከፉኛ ገብቷል.... ሕዝቡ ማንኛውንም የከብት ቆዳ በትናንሹ ቆራርጦ ያደርቀዋል ። ከደረቀ በኋላ በሙቀጫ ወቅጠው ፤ በወፍጮ ፈጭተው ያደቁና እንደ ዳቦ ጋግረው ይበሉታል ።...." ሲሉ ጽፈዋል ።

የአላዛሪስት ሚስዮን አባል የነበሩት ኩልቤክስ ደግሞ "....በየ ቦታው የሚገኘው ሁሉ የሚላወስ አጽምና የሞተ ሬሳ ብቻ ነው ። ከወደቀውም ሬሳ አብዛኛው በጅብ የተበላ ነው...." ሲሉ ኢጣሊያኑ ሳሊምቢኒ "....አድዋ ከተማ በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ነች ። አድዋ የመቃብር ሥፍራ እንጂ ከተማ አትመስልም...." በማለት በአድዋ ያዩትን ፅፍዋል ።

ሚስዮናዊው ሚካኤል አረጋዊ ለፍላድ በጻፉት ደብዳቤ "....በትግሬ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች አልቀዋል ። የገባው ረሃብ ከባድ በመሆኑ ድሆችም ፤ ሀብታሞችም በመሞት ላይ ናቸው ። .... ልጆቼ (ተማሪዎቼ) ከዱር ውስጥ ያገኙትን ፍሬ ሲለቅሙ ይውሉና ያገኙዋትን ያህል ቀቅቅለው ያቺን እንቀምሳለን ። የሞተ አውሬ ሲገኝ እንዳንድ ሰዎች ያን ሥጋ ይበሉና ይሞታሉ ። ይህ ረሃብ ያደረሰውን ነገር በሙሉ ልፅፍልህ አልችልም . . . ." ብለዋል ። ትራቢርሲ ደግሞ የአሞራና የአውሬ ሥጋዎች መበላቱን ገልፅዋል ።

ኮንት አንቶኔሊ ". . . . የከብት በሽታ በሸዋ ብቻ ሳይሆን በመላ ኢትዮጵያ በመዳረሱ ኢትዮጵያ ከባድ የኤኮኖሚ ውድቀት ደርሶባታል ። በትግራይ ፤ በጐንደር ፤ በበጌምድር ፤ በጐጃምና በሸዋ እጅግ በጣም ብዙ ከብት አልቋል ።. . . ." ይልና በ1881 ወደሐረር ሲሔድ በመንገድ ያየውን ሲገልፅ ". . . . ሀገሪቱ ያለ ሰው ቀርታለች ። በማሽላ ሰብልና በከብት መንጋ ተሞልቶ የነበረው ሥፍራ ሁሉ ዛሬ ባዶ ነው ። በሐረርና በጮርቃ መሀል ባሉት አገሮች ብቻ ሰውና ከብት ይታያል ። ምንጃር ውስጥማ ሰው የለም ። እርሻም አይታይም ። በዚያ በሚያምር ለም በነበረው ቦታ የሚታየው ቁልቋልና ሰንበሌጥ ብቻ ነው ። የኢቱ አገር ጨርጨር እንዳልነበረ ሆንዋል ።. . . . ብሏል ።

ፈረንሳዊው ሐኪም ውርዝ ደግሞ ". . . . በአገሪቱ ያሉ ከብቶች በሙሉ አልቀዋል ። ለምሳሌ ቡልጋ ያሉ ከብቶች የሞቱት በስምንት ቀን ውስጥ ነው ። በዚያም ምኒልክ የነበሩዋቸው ከብቶች አንድም ሳይተርፍ ሁሉም ሞቱ ። እንደሚነገረው ያለቁት የምኒልክ ከብቶች

250.000 ናቸው ይባላል ። በተለይ ጋሎች ብዙ ከብቶች ስለነበሩዋ ቸው እያንዳንዱ ጋላ ከ10.000 እስከ 12.000 የቀንድ ከብት ሞቶበ ታል. . . .'' ብለዋል ።

ኢትዮጵያዊው ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ሰው የጅብ ሥጋ መብላቱንና ባንዳንድ ክፍልም ሰው የሰው ሥጋ መብላቱን ፅፈዋል ። የምኒልክ ፀሐፊ ትእዛዝ የሆኑት አለቃ ገብረ ሥላሴ ". . . . ጥኑ ረሃብ ሆነ ። የፈረስ ሥጋ ፡ የአህያ ሥጋ ተበላ ። ሰውን ሰው በላው። ወሎም አንዲት ሴት ልጅዋን በላች ። እንሳሮ ከሚባልም አገር አንዲት ሴት ሰባት ሕፃናት በላች. . . . " በማለት ጽፈዋል ። ፀሐፊ በማጣት አይነገርለት እንጂ በመላ ኢትዮጵያ የገባው ረሃብ በሁሉም ቦታ ተመ ሳሳይ ድርጊት ያስፈፀመ ነበር ።

በዘመኑ በነበረው በሕዝብ አመላለክ መሠረት የምኒልክ መን ግሥ ገደ ቢስ ሆነ ። የምኒልክ አመራር እንኳን ሲያዘልቅ ላሁኑም አላዋጣ እያለ ሕዝቡ ያማ ጀመር ። ረሃቡን ያመጣው ግን የምኒልክ ገደ ቢስነት አልነበረም ። በዘመነ መሳፍንት ሕዝብ ሥራ ፈቶ እንዳ ንድ በጥባጭ መኳንንትን በመከተል ወዶም ሆነ ሳይወድ ወታደር ሆንዋል ። ይህን የመሣፍንት ብዛት ለማስጣል የተነሱት ቴዎድሮስም 15 ዓመት ሙሉ ሕዝቡን ጦረኛ አድርገውታል ። ይህም ብቻ ሳይሆን የተዘራ አዝመራ ከደረሰበት ቀበሌ በገቡ ቁጥር ዝሪቱን አህያና በቅሎ እንዲበላው ያዙ ነበር ። ባንድ ጀንበር ብቻ ደብረ ታቦር ላይ በትእዛዝ የታረደው ከብት የሚበላው ሰውም ሆነ አውሬ ጠፍቶ በከተማው በሽታ አስነስቶ ነበር ። በዚያን ዘመንም የገባው ረሃብ በጣም የጠና ነበር ።

ከአጤ ቴዎድሮስም በኋላ አጤ ተክለ ጊዮርጊስ ሲነግሡ ተቃዋሚዎ ቻቸውን ለማስገበር ገበሬውን ሁሉ ወታደር አደረጉት ። አጤ ዮሐን ስም እንደዚሁ ተቀናቃኞቸውን ለመጣል ወታደር ሲያበዙ ተቀናቃ ኞቻቸው ምኒልክና ተክለሃይማኖትም ወታደር ለማብዛት እያሰባሰቡ አራሽ ገበሬ ታጣ ። በዚያ ላይ አንዱ የአንዱን አገር በሚወርበት ጊዜ በደል የፈፀመው ተራው ገበሬ ይመስል አዝመራውንም ሆነ ከብቱን ፈፅሞ ይደመስሱና ያጠፉበት ነበር ። ይሄ ሁሉ ተጨማምሮ በምኒልክ ዘመን የበረታ ረሃብ ደረሰ ።

ይህ ረሃብ እንደደረሰ አጤ ምኒልክ ማንም ሰው የላም ሥጋ እንዳይበላ ወይም እንዳያርድ በአዋጅ አስከለከሉ ። በቤተ መንግሥ ቱም ቢሆን አንድም የቀንድ ከብት እንዳይታረድ ተከለከለ ። አብዛ ኛው የቤተ መንግሥቱ ግብርም ንፍሮና እንጀራ በእህል ወጥ ብቻ ሆነ ። ከቤተ መንግሥቱ ለሚጠጋው ረሃብተኛም ንፍሮ በብዙ

ጋኖች ተቀቅሎ እያደረ በነጋታው ምኒልክ ራሳቸው ለሕዝቡ በማደሉ ተግባር ይካፈሉ ጀመር ። በዚህ ላይ እንዳሉ ቅድም ያልናት እንሳሮ ውስጥ አንዲት ሴት ሰባት ልጆች በላች የሚሉ ወሬ ሰሙ ። በእስ ቸኳይ ተይዛ እንድትመጣ አዘው መጥታ ከፊታቸው ስትቀርብ "እውነት የሰው ሥጋ በላሽን" ብለው ጠየቋት ። እሷም "አዎን ጃንሆይ ። ቢርበኝ ሰባት ልጆች ይዤ በላሁ" አለቻቸው ። እሳቸውም "ከወዴት እየያዝሽ ፣ እንዴትስ እያደረግሽ ገደልሽና በላሻቸው" ብለው ቢጠይቋት "ከሚጫወቱበት ቦታ እያነቅሁ እየያዝሁ ነው" አለቻቸው ። በዚህ መልስ "እንዴት አገሬ ጠፋ ። ድሃዬ አለቀ" ብለው ማልቀሳቸውን ፕሮፌሰር አፈወርቅ ጽፈዋል ። ያቺንም ልጆች የበላችውን ሴት በቤተ መንግሥት እንድትቀመጥ ለአዛዡ ነግረው ከእሳቸው ዘንድ አስቀመጧት ። ይቺው ሴት የሌላ ሰው ልጆችን ትብላ እንጂ የነበራትን አንድ ልጅ አልበላችውም ነበርና ይህን ልጅዋን አቶ ሮባ እንዲያሳድጉት ሰጧቸው ።

ከብት አልቆ የሚታረስበት መጥፋቱን ያዩት አጤ ምኒልክ" .... የከብት ነገር ተፈፅሞ አልቋልና እግዚአብሔር ፊቱን እስኪመልስልን ድረስ እኔም አብነት ለመሆን ብዬ በጄ የምቆፍርበት ዶማ ፣ የምቆርጥበት መጥረቢያ አስበጅቻለሁና እናንተም እንደኔ ሁኑ ...." እያሉ ለየመኳንንቱ ደብዳቤ ፅፈው ለእያንዳንዱም አንዳንድ ትናንሽ ዶማና መጥረቢያ ላኩላቸው ። መጀመሪያ የተላከላቸው የጐጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ የወሎው ራስ ሚካኤልና የጐንደሩ ራስ ወሌ ነበሩ።

ምኒልክ ለአብነት እሆናለሁ ብዬ ባሉት ቃል መሠረት መሬት ለመቆፈር የወጡት ለመታየት ብቻ አልነበረም ። ፕሮፌሰር አፈወርቅ እንደፃፉት አንድ ቀን የየካን ዱር ሲመነጥሩ ጋሬጣና እሾህ እግራቸውን እየቀደደ ደም ብቻ አደረገው ። በዚያ የነበሩ መኳንንትም ከምኒልክ እግር ብዙ ደም ሲፈስ አይተው ተደናገጡ ። ወዲያውንም በየሸማቸው የምኒልክን ደም ለመጥረግ ሲሻሙ ምኒልክ ተቆጥተው "ተዉ ። አትንኩኝ ። ይልቅስ እኔ ለእናንተ እንዳሳየሁ እናንተም ከበታቻችሁ ላለው ሰው አሳዩ ። አስተምሩ ። ከዚያ ወዲያ ትርፋንና ጥቅሙን ታዩታላችሁ ...." አሏቸው ። ይህን ካሉዋቸው በኋላ መኳንንቱ ሁሉ ማጭድና መጥረቢያውን እየያዘ ዱሩን መመንጠር ጀመረ ።

ራስ መኰንን ከሐረርጌ 5000 በሬና 5.000 ላም ላኩ ። ምኒልክም እነኚህን ከብቶች እያከፋፈሉ በየአገሩ ለርቢ ሰደዱዋቸው ። ሕዝቡም ላምና በሬ በማየቱ እንደብርቅ እየተደነቀ እበቱን እየቆነጠረ እያሸተተ ይዞት ይሄድ ነበር ። ከዚህ በኋላ የረሃቡ ዘመን ተፈጽሞ የተድላና የደስታ የጥጋብ ዘመን ተጀመረ ። ያ ቀን አልፎ ሰብል መታየት

ሲጀምር ሕዝቡ "እህል ዱር አደረ ብቻውንም ዋለ ፣
ጠላት እንደሌለው ሰው እንዳልገደለ ።
እህል ዘምቶ ገባ እኛም አየነው ፣
አያሌ ሰው ቀረ ሳይገናኘው ።" እያለ ዘፈነ ።

# አድዋ

የአድዋን ጦርነት ከመናገር በፊት ኢጣሊያኖች ወደ ኢትዮጵያ ወሰን እንዴት እንደገቡና እንደተስፋፉ መናገሩ ለአንባቢ ግንዛቤ የሚሰጥ መሰለኝ ።

በሃይማኖት ስብከት ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ የገቡት አባ ጁሴ ፔ ሳፔቶ ከአሰቡ ባላባት ከሱልጣን ኢብራሂምና ከራሂታው ሱል ጣን ከሐሰን መሐመድ ጋር ተወዳጅተዋል ። ጁሴፔ ሳፔቶ ለማረፊያ ያህል የምትሆን መሬት እንዲሸጡላቸው ሱልጣኖቹን ጠየቁ ። ሱል ጣኖቹም የፈለጉትን ያህል መግዛት እንደሚችሉ ለጁሴፔ ሳፔቶ ቃል ገቡላቸው ። ጁሴፔም የሚገዙትን መሬት አይተውና ለክተው ከሱል ጣኖቹ ጋር ከተስማሙ በኋላ ሩባቲኖ ወደ ሚባለው የኢጣሊያ የመ ርከብ ኩባንያ ዘንድ ሔደው በኢትዮጵያ የቀይ ባህር ዳርቻ ወደብ እንዲመሠርት ከኩባንያው ጋር ተነጋግረው የመሬት መግዣ ገንዘብ ይዘው መጡ ።

አባ ጁሴፔ ሳፔቶ አሰብንና ሰባት ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለ ውን የባህር ዳርቻ በ1862 ዓ.ም. በ8100 ማርትሬዚያ ብር ከሱልጣ ኖቹ ላይ ገዙ ። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት አጤ ተክለ ጊዮርጊስ ነበሩ ። አጤ ተክለጊዮርጊስ ከቴዎድሮስ የተረከቡት የተ በጠበጠው የኢትዮጵያ ግዛት አልጠራላቸው ስለነበርና እረፍትም ስላላገኙ በኢትዮጵያ ዳርቻ ስለገባው የውጭ ኃይል ያሰቡበት አይመ ስልም ።

አባ ጁሴፔ ሳፔቶ አሰብን ገዝተው ገንዘቡን በከፈሉ ማግስት 28 ጊዜ መድፍ ተተኩሶ በዛሬው የአሰብ ምድር የኢጣሊያ ባንዲራ ተውለበለበ። የሩባቲኖ የመርከብ ኩባንያም ለአስራ ሁለት ዓመታት ያህል በወደቡ እንደመጠቀም እያለ ከቆየ በኋላ ወደቡ ምንም እንደ ማይጠቅመው በማወቁ በ1874 ዓ.ም. በአጤ ዮሐንስ ዘመነ መንግ ሥት በ417 000 ሊሬ ለኢጣሊያ መንግስት ሸጠው ። የኢጣሊያ መንግሥትም ሰኔ 19 ቀን 1874 ዓ.ም አሰብ የኢጣሊያ ግዛት መሆ ኑን በአዋጅ አሳወቀ ።

ኢጣሊያኖች ተሰብስበው ለመውደቅ የሚንገዳገደውን የኢጣሊ ያን መንግሥት በእግሩ ካቆሙ በኋላ አገራቸውን ወደ ጥንቱ የሮማ

አገዛዝ ደረጃ ለመመለስ ቅን ግዛት ይፈልጉ ነበር ። ማግኘቱ ግን ችግር ሆነ ። በሜዲቴራኒያን ባህር የሚዋሰኑ አገሮችን ለመያዝ እስ በው ፈረንሳዮች በቅድሚያ አልጄሪያንና ቱኒዚያን ይዘዋል ። ሞሮኮንም ቢያስቡ የሞሮኮው ሱልጣን የማይበገር ኃይል ያለው ሆነ ባቸው ።በሌላው አቅጣጫ ዞረው በቀይ ባህር በሕንድ ውቅያኖስ እካ ባቢ እስከ ዛንዚባር ድረስ ያፈላልጉ ጀመር ። ይህ ፍለጋ በተጀመረ ጊዜ የኢጣሊያ ፓርላማ አዳራሽና የውጭ መመላለሻ (ኮሪዶር) ሁሉ "ቀይ ባህር ለሜዲቴራኒያ ባህር ቁልፍ ነው ።" በሚል መፈ ክር ተሞላ ። በዚህ ጊዜ ነው ኢጣሊያኖች አሰብን ከሩባቲኖ ኩባንያ የገዙት ።

በዚያን ዘመን አፍሪካ በአብዛኛው ማለት ይቻላል በግልጽም ሆነ በስውር በእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ሥር ነበረች ። እንግሊዞችም ባህ ርና መንገድን በመቆጣጠር ሌላ የውጭ ኃይል ወደ አፍሪካ እንዳይ ገባ ይከላከሉ ነበር ። በ1875 ዓ.ም. ያ ታላቅ የእንግሊዝ መንግሥት በግብፅና በሱዳን ታላቅ ችግር አጋጠመው ። በየአገሮቹ ውስጥ ከተነ ሳው ችግር ሌላ የፈረንሳይና የጀርመን መንግሥትም ለእንግሊዝ መንግሥት የጐን ውጋት ሆነው ቀስፈው ያዙት ።

በንቀት ዓይን ይታይ የነበረው የኢጣሊያ መንግሥት የታላላቆ ችን መንግሥታት የፖለቲካ ሽኩቻ በመመልከት በአጋጣሚው ለመ ጠቀም አሰበ ። ይህን አጋጣሚ ሊጠቀምበት የተነሳው የኢጣሊያ መን ንግሥት በዘመኑ ችግር ውስጥ የገባውን የእንግሊዝን መንግሥት ለመርዳት ማሰቡን የሚገልጥ ጥያቄ አቀረበ ። የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ማንቺኒ ለእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለሎ ርድ ግራንቪል እንረዳዳ የሚል ደብዳቤ ጻፉ ። ሎርድ ግራንቪልም በኢጣሊያ መንግሥት ሐሳብ ተስማምተው ዲሴምበር 22 ቀን 1884 ዓ.ም. የኢጣሊያና የእንግሊዝ መንግሥት የወዳጅነት ውል ተዋዋሉ ። ከውሉም እንደኛው ክፍል ኢጣሊያ አንድ የወታደር ቡድን ወደ ኢት ዮጵያ ጠረፍ ወደ ምፅዋ ልካ ሱዳን ውስጥ እንግሊዝን የሚበጠብጠ ውን ኃይል ለመጠባበቅ እንድትችል የሚያደርግ ነው ። ምፅዋ በዚ ያን ጊዜ በግብጾች የተያዘ ስለነበረ እንግሊዝ ግብጾችን ከምፅዋ አስ ወጥታ ምፅዋን ለኢጣሊያ ለመስጠት ተስማሙ ።

ይህ ከሆነ በኋላ ጃንዋሪ 19 ቀን 1885 ዓ.ም. በኰሎኔል ሳሌታ የሚማሩ 40 መኰንኖች ያሉበት 800 የኢጣሊያ የወታደር ቡድን ከኔፕልስ በመርከብ ተሳፍሮ ወደ ምፅዋ ጉዞውን ጀመረ ። ቡድኑ ወደ ምፅዋ ጉዞ መጀመሩ ከተሰማ ምናልባት የፈረንሳይም ሆነ የጀርመን የጦር መርከቦች አደጋ እንዳይጥሉበት ስላሰጋ የኢጣሊያ ወታደሮች

የሚጓዙበት ጐታርዶ የሚባለው መርከብ በሁለት የጦር መርከቦች እንዲታጀብ ተደረገ ። ወታደር የጫነው ጐታርዶ የተባለው መርከብ አሜዴስ እና ጋሪባልዲ በተባሉ ሁለት የጦር መርከቦች ታጅቦ ጉዞ ውን ወደ ምፅዋ ጀመረ ። ፖርት ሳይድ ሲደርሱ አሜዴስ የተባለችው አጃቢ መርከብ ስለተበላሸች በምትኳ ቬስፑቺ የተባለች የጦር መር ከብ ለጥበቃው ተተካች ። እነኚህም አጃቢ መርከቦች የሚታዘዙት በአድሚራል ካይሚ ነበር ። በሚስጥር የተላከው የኢጣሊያ የወታደር ቡድን በ1877 ዓ.ም ጥር 28 ቀን ጧት ምፅዋ ገባ ።

አጤ ዮሐንስ የእንግሊዝን ጦር እየመራ የአጤ ቴዎድሮስን እስ ረኞች ለማስለቀቅ ከመጣው ከናፒር ጀምሮ ከእንግሊዞች ጋር ጥሩ ወዳጅነት አለኝ ብለው ነበር ። በእንግሊዞች በመተማመንም በእንግሊ ዞች ግፊት የሒወትን ውል ተዋውለው እንግሊዞችን እንደ ቅርብ ረዳት አድርገው ያስቡዋቸው ነበር ። አሁን ኢጣሊያኖች በእንግሊዝ እርዳታ ምፅዋን መያዛቸውን ሲሰሙ ግን እውነት ነው ብለው አላመ ኑም ነበር ።

ነገሩን ካረጋገጡ በኋላ የእንግሊዝ መንግሥት ሳያሳውቃቸው ወይም ሳያማክራቸው ምፅዋን ለኢጣሊያ በመልቀቁ ተደነቁ ። ጉዳ ዩን ለማጣራትና የሒወት ውል እንዴት እንደተሻረ ለማወቅ ሲሉ ለንግሥት ቪክቶሪያ ደብዳቤ ጽፈው ጉዳዩን ጠየቁ ። በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ የዚያን ጊዜ የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ከኢጣሊያ ንጉሥ ጋር ወዳጅ ነበሩና ምኒልክ ኢጣሊያኖች የገቡበትን ምክንያት ንጉሥ ኡምቤርቶን እንዲጠይቁ አዘዙ ። ዮሐንስ ደብዳቤ በመጻፍና ጉዳዩን በማጣራት ላይ እንዳሉ ኢጣሊያኖች በምፅዋም ሆነ በአሰብ ወደብ ምንም ዓይነት የጦር መሣሪያ ወደኢትዮጵያ እንዳይገባ ከለከሉ ።

ንጉሥ ምኒልክም ለኢጣሊያው ንጉሠ ነገሥት ኡምቤርቶ በጻ ፉት ደብዳቤ የኢጣሊያ መንግሥት ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጋር ጦርነት ለመግጠም አስቦ ምፅዋ መግባቱን በመስማታቸው ማዘናቸ ውን ገልፀው ጻፉ ። ንጉሥ ኡምቤርቶም ለምኒልክ ደብዳቤ መል ሱን አድሚራል ካይሚ እንዲሰጥ አዘዙት ። አድሚራል ካይሚም ለምኒልክ ደብዳቤ ሲመልስ ምፅዋ የገባነው በኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ፈቃድ ነው በማለት የቅጥፈት መልስ ሰጠ ።

ምኒልክም ይህንን የደረሳቸውን መልስ ለበላያቸው ለአጤ ዮሐ ንስ አሳወቁ ። አጤ ዮሐንስም ይህን የኢጣሊያኖችን መልስ እንደ ሰሙ አንድ የኢጣሊያ መልክተኛ ቡድን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ እንዲነጋገ ርና በሒወት ውል መሠረት ጉዳዩን ግልፅ እናድርገው ብለው ምኒ ልክ እንዲጠይቁ ደግመው አዘዙዋቸው ። ንጉሥ ምኒልክም ይህንኑ

ሐሳብ ለኢጣሊያው ንጉሥ ኡምቤርቶ በደብዳቤ አሳወቋቸው ። ንጉሥ ኡምቤርቶም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ማንቺኒ በአጤ ዮሐንስ ጥያቄ መሠረት እንዲፈፅም አዘዙት ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩም በፌራሪ የሚመራ የኢጣሊያ ቡድን ወደ ኢትዮጵያ ላከ ።

ከኢጣሊያ የተላከው ቡድን በሚያዝያ ወር አጋማሽ በ1877 ዓ. ም. ኢትዮጵያ ገብቶ ከአጤ ዮሐንስ ጋር ተገናኝቶ ንግግር ጀመረ። ቡድኑም “ . . . . ምፅዋ የገባነው የመሀዲስቶችን አገር የመያዝ ግፊት ልናቆምላችሁ ነው . . . . ” የሚል ሰበብ ሰጠ ። በዚያን ጊዜ እንደተባለውም መሀዲስቶች መተማን ይዘው ኢትዮጵያን ለመውረር ይዘጋጁ ነበር ። ስለዚህ ይሆን የመሀዲስቶችን ግፊት የሚያውቁት አጤ ዮሐንስ የኢጣሊያኑን የመልክተኞች ቡድን አመስግነው ሽልማትም ሸልመውት ተሰነባበቱ ። የኢጣሊያው መልክተኞች መሪ ፌራሪ ከአጤ ዮሐንስ ከመሰናበቱና ከመለያየታቸው በፊት ምፅዋ ካለው ከኰሎኔል ሳሌታ የተጻፈ አስቸኳይ ደብዳቤ ደረሰው ። ደብዳቤውም “ . . . . የምፅዋ በር ለኢትዮጵያ ክፍት ይሆናል ብለህ እንዳትዋዋል ። የጦር መሣሪያ ሊገባላት አይችልም ። አሁን እኔ ወታደሮቼን እየመራሁ አራፋሌንና ሕርጊጎን ይዘናል ። በቅርቡ ሰሐጢን ለመያዝ አሳብ አለኝ . . . .” የሚል ነበር ።

የኢጣሊያኖቹ ባታሊያ መጽሐፍ እንደሚገልጠው ኰሎኔል ሳሌታ እንዳለው ሰኔ 17 ቀን በዚያው ዘመን ሰሐጢን ኢጣሊያኖች ያዙ ። አሁን እንግዲህ ኢጣሊያኖች ከባህር ዳርቻ ወደ ውስጥ 50 ኪሎ ሜትር ያህል ወደ ኢትዮጵያ ዘልቀው አገር በመያዛቸው የአውራጃው የመረብ ምላሽ ገዥ ራስ አሉላ ለኢጣሊያኖቹ በሁለት ቃላት ብቻ ተቃውሞ አቀረቡ ። “ሰሐጢን ልቀቁ” የሚሉ ነበሩ ።

ኢጣሊያኖች አሰብንና ምፅዋን ልቀቁ አልተባሉም ። ሰሐጢን ልቀቁ በመባላቸው ብቻ ተናደውና ተበሳጭተው ጉዳዩ ለኢጣሊያ ፓርላማ ቀረበ ። በፓርላማው ላይ የኢጣሊያ የጦር ሚኒስትር ቀርበው እንዲያስረዱ ተደረገ ። የጦር ሚኒስትሩም ለፓርላማው ባደረጉት ንግግር “ . . . .እንዲህ ዓይነቱን ነገር ልናደርገው አንችልም ። ምክንያቱም የአገር ክብር ጉዳይ ነውና . . . .” በማለት አስረዱ ። በዚህ ጊዜ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱን ቦታ ከማንቺኒ ተረክበው ዲ ሮቢላንት ይዘው ስለነበር እሳቸውም የጦር ሚኒስትሩን አሳብና ንግግር በመደገፍ ለኢጣሊያ ፓርላማ ተናገሩ ። ፓርላማውም የአገር ክብር እንዳይነካ የምትሠሩ ከሆነ መልካም ነው ብሎ ወሰነ ።

ምፅዋ የገባው የኢጣሊያ ጦር በጄኔራል እንዲመራ ተወስኖ መስከረም 22 ቀን 1878 ዓ ም. ጄኔራል ጄኔ ተሾሙ ። ጄኔራል ጄኔም

ምፅዋ ገብተው በሕርጊጐና በእምኩሎ ያለውን ምሽግ አጠናከሩ ። ኩይሃንና ዙላንም ለመያዝ ይዘጋጁ ጀመር ። የሕርጊጐው ናኢብ መሀመድ አብደልራሂም ኢትዮጵያን የሚወድ ነበርና ኢጣሊያኖች ከናኢብነቱ ሽረው አባረሩት ። በሱም ቦታ ወንድሙን አብዱል ከሪምን ሾሙት ። አብዱል ከሪም በምፅዋ ለገቡት ኢጣሊያኖች ሥጋ ፣ አትክልትና ፍራፍሬ እያቀረበ የሚሸጥ ነጋዴ ነበር ። አብዱል ከሪም ለኢጣሊያኖች ታማኝ መስሎ ይታይ እንጂ ኢትዮጵያን የሚወድና ለአውራጃው ገዢ ለራስ አሉላም የቅርብ ወዳጅ ነበር ።

አጤ ዮሐንስ ከሙለርና ከሾጐት ጋር ባደረጉት የመሣሪያ ግዢ ስምምነት መሠረት አንድ ሺ ጠመንጃ ወደ ኢትዮጵያ መሀል አገር ለማስገባት ምፅዋ ደረሰ ። የዚህን መሣርያ ምፅዋ መግባት ራስ አሉላ ሰሙ ። የመሣሪያውን መድረስ በጉጉት ይጠባበቁ ነበርና መሣሪያው በቶሎ እንዲገባ መልክተኛ ላኩ ። ጄኔራል ጄኔ ግን መሣርያው ወደ ኢትዮጵያ መሀል አገር እንዳይገባም ወደመጣበትም እንዳይመለስ መጋዘን ውስጥ ቆልፈው አስቀመጡት ።

ራስ አሉላም በመሣርያው መያዝ ተበሳጩ ። ኢጣሊያኖች ኩይሃን ይዘው ምሽጋቸውን ማጠናከራቸውንም ሰሙ ። በዚህ ጊዜ “ . . . . እስከ ጥር 13 ቀን 1880 ኩይሃን እንድትለቅ ። ዙላን ደግሞ እስከዚህ ወር መጨረሻ ድረስ ለቀህ እንድትወጣ ። ይህ ካልሆነ በኛ መሐል ያለው ወዳጅነት እንደማይኖር እንድታውቀው” የሚል ደብዳቤ ለጄኔራል ጄኔ ላኩላቸው ። ለዚህ ደብዳቤ ጄኔ ሲመልሱ“ . . . . ወታደሮቻችን በኩይሃ ይቆያሉ” ብለው ለአሉላ ላኩባቸው ።

ጄኔራል ጄኔ ሰሞኑን አንድ ባታሊዮን ጦር ልከው ሰሐጢን አጠናከሩ ። በቦታውም በመድፍ የተጠናከረ የወታደር ኃይል አስቀመጡ ። ራስ አሉላ ይህን ሲሰሙ ለመዝመት ተዘጋጁ ። በአጠገባቸው የነበሩትንም አራት የኢጣሊያ መልክተኞችን ማለት እንጂነር ሳሊምቢኒን ፣ ማጆር ፒኖን 12 ዓመት ዕድሜ ካለው ወንድ ልጁ ጋርና መቶ አለቃ ሰቦይሩክስን አሠሩዋቸው ። ለጄኔራል ጄኔም “ . . . . ይህ ደብዳቤ በደረሰህ 3ኛው ቀን ድረስ ሰሐጢን እንድትለቅ ። ባትለቅ ግን በእጄ ያሉትን ኢጣሊያኖች ገድዬ ባንተም ላይ እንደምዘምት እወቀው” የሚል ደብዳቤ በፒኖ እጅ ላኩለት ።

ጄኔራል ጄኔ ይህ ደብዳቤ እንደደረሳቸው ጉዳዩን ወደ ሮም አሳወቁ ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሮቢላንት ለጄኔራል ጄኔ ጥያቄ ሲመልሱ “ . . . . ራስ እንዲህ እንደምትለው ዓይነት ጅል ስህተት እንደማያደርጉ ተስፋ አለኝ ። ካደረጉትም ደግሞ ምላሹን ያገኙታል ። ለአንተም የሚያጠናክርህ ማጠናከሪያ ስለተላከልህ ትምህርት አስተ

ምረው. . . . ” የሚል ቃል ላኩላቸው ። ትምህርት አስተምረው የሚ ሉት ራስ አሉላን ነው ። እኚሁ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጥር 18 ቀን ለኢጣሊያ ፓርላማ ንግግር ሲያደርጉም “ ....ጄኔራል ጄኔ ጠላትን መራራ ትምህርት ለማስተማር ችሎታ ያለው ሰው ነው ። . . . ” ብለዋል ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ይህን የሁለተኛ ጊዜ የፓርላማ ንግግራቸውን ያደረጉ ዕለት ራስ አሉላ ዶጋሊ ላይ ኢጣሊያኖችን ድል አድርገው መራራ ትምህርት አስተምረዋቸው ነበር ።

በዶጋሊው ጦርነት ራስ አሉላ 500 ኢጣሊያውያኖች ገድለ ዋል ። ፈፅመው ድል አድርገዋል ። ዶጋሊ ከምፅዋ የሚርቀው ሃያ ኪሎ ሜትር ያህል ነው ። ራስ አሉላ ዶጋሊ ላይ ኢጣሊያኖችን ድል ካደረጉ ለምን ቆልቆል ብለው ኢጣሊያኖችን ከምፅዋ አላስወጡም ? ለምንስ በየቦታው የተራረፉት ኢጣሊያኖች ምፅዋ ላይ እንዲከማቹ ቹል አሉዋቸው ? ለምንስ የኢጣሊያኖችን የቅኝ ግዛት የመፈልፈል ሐሳብ ከመነሻው እንቁላሉን አልሰበሩትም ? ምኒልክ ከአድዋ ድል በኋላ ለምን ወደ ኤርትራ ተሻግረው ኢጣሊያን አላጠፉም ? እንደ ሚለው ጥያቄ ዓይነት ነው ።

እኛ የማናውቀው አሉላ በጊዜውና በቦታው የሚያውቁት ሚስ ጥር ሊኖር ይችላል ። ምናልባት የዶጋሊው ጦርነት አጤ ዮሐንስ ሳይሰሙና ሳይፈቅዱ የተደረገ በመሆኑ ራስ አሉላ አጤ ዮሐንስን አክብረውና ፈርተው ተመልሰው ይሆናል ። ምናልባትም ደግሞ በም ፅዋ ያለው የኢጣሊያ ኃይል ከአሉላ ኃይል በመሣሪያ የበለጠ ማየ ሉን አውቀው ይሆናል ። ምናልባትም ደግሞ በአካባቢው በአሉላ ግዛት የሚሸፍተው መ ኳንንት በዝቶ ስለነበረ አሉላ ሌላውን ሽፍታ ለመቆጣጠር ተመልሰውም ይሆናል ። ምናልባትም ደግሞ በሰሐጢ ያለቀ ውን ጦራቸውን ገምተ ው ለአዲስ ዝግጅት መመለሳቸውም ይሆናል ። እኛ የማናውቀው ወይም በዘመኑ የነበሩት ታሪክ ፀሐፊዎች ምክን ያቱን ያላቆዩን ታሪክ በመሆኑ በጥያቄ ብቻ እንለፈው ።

ራስ አሉላ የዶጋሊውን ጦርነት ፈፅመው ከተመለሱ በኋላ ጦርነቱ በተደረገ አምስተኛው ሳምንት ምፅዋ ላይ የተያዘውን አንድ ሺ ጠመንጃ እንዲለቀቅላቸው ማጆር ፒኖን ላኩት ። ኢጣሊያኖችም በምፅዋ ያላቸውን አቅም ገምተው እስኪደራጁ ድረስ ጊዜ ለማግኘት የተያዘውን አንድ ሺ ጠመንጃ እንዲለቀቅ ፈቀዱ ።ራስ አሉላ የተያ ዘውን ጠመንጃ ቢያስለቅቁም አጤ ዮሐንስ ሳይፈቅዱ ከኢጣሊያ ጋር ጦርነት በማንሳታቸው የመረብ ምላሽ ግዛታቸው በአጤ ዮሐንስ ተያዘባቸው ።

ኢጣሊያኖችም ለዶጋሊው እልቂት ምክንያት የሆነው ጄኔራል ጄኔ ነው በማለት እሱ ተሽሮ በቦታው እንደገና ኰሎኔል ሳሌታን ሾሙት ። የዶጋሊ ጦርነት በተደረገ በሳምንቱ ማለት ፌብራዮ 3 እና 4 ቀን የተሰበሰበው የኢጣሊያ ፓርላማ የዶጋሊን ብድር ለመመለስ ለአዲስ ወታደሮች መቅጠሪያና ማጠናከሪያ አምስት ሚሊዮን ሊሬ ወጭ እንዲሆን ፈቀደ ። ሲኞር ክሪስፒም ለፓርላማው ባደረጉት ንግ ግር “ .... ምፅዋ ላይ ተዘግተን መቅረት የለብንም ። ለታላቅ ግብና ዓላማ ወደፊት ማንጣጠር አለብን ....” ብለው ተናገሩ ። በሰኔ ወርም የኢጣሊያ ፓርላማ 20 ሚሊዮን ሊሬ ምፅዋ ለገባውና ለሚገባው 20.000 የኢጣሊያ ወታደር በጀት አጠደቀ ።

ምፅዋ የኢጣሊያ ጦር መከማቻ ሆነች ። 814 መኰንኖች ያሉበት 17.700 ወታደሮች ፣ 138 መድፍ ፣ 28 መትረየሶች ፣ 3000 ፈረሶች ፣ 2000 በቅሎዎች 18.000 ግመሎች ምፅዋ ላይ ተከማቹ ። ወታደሩም በሙሉ ወተርሊይ የተባለውን የዘመኑን ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀ ነበር ። ጄኔራል ሳን ማርዛኖም ጠቅላይ አዛዥ ሆኖ ተሾመ ። ኢስቶ ሪያ ሚሊታሬ መጽሐፍ ውስጥ እንደተጻፈው ከምፅዋ የእምኩሉና የዶጋሊ የምድር ባቡር ሐዲድ ሥራው ተጠናቆ ባቡሩ ወታደር ማጓ ጓዝ ጀመረ ።

ይህን የኢጣሊያን ጦር መከማቸት አጤ ዮሐንስ ሰሙ ። ማይ ሚሽን ቱ አቢሲኒያ በሚባለው መጽሐፍ ላይ ፖርታል እንደሚገል ጠው አጤ ዮሐንስ የኢጣሊያን ጦር መከማቸት እንደሰሙ ከአስ መራ የራስ አሉላን 16.000 ወታደር ፣ ከከረን የራስ ሐጐስን 20.000 ወታደር ፣ ከወሎ የራስ ሚካኤልን 25.000 ወታደር ፣ የራሳቸውን 5.000 የክብር ዘበኞች ፣ የራስ መንገሻን 5.000 ያህል ወታደር ፣ ከዋድላ የራስ ኃይለማርያምን 16.000 ወታደር ፣ ከአድዋ 40.000 ወታደር ፣ የደጃች ተሰማን 32.000 ወታደር በድምሩ 159.000 ወታደር ይዘው ዘመቱ ።

አጤ ዮሐንስ ይህን ሠራዊት እየመሩ ሰበርጉማ ደረሱ ። በዚያም ሆነው ኢጣሊያኖችን ለመውጋት ሲጠባበቁ ኢጣሊያኖች ሰሐጢ ላይ ካዘጋጁት ምሽጋቸው አልወጣ አሉ ። ከመቆየት የተነሳም የወታደሩ ስንቅ እያለቀ ሔደ ። የስንቁ ማለቅም ብቻ ሳይሆን ቦታውም ሞቃት በመሆኑ የደጋው ወታደር የቆላውን ሙቀት ሊቋቋመው አልቻለም ። ከዚህም ሌላ በጐንደር በኩል የመሀዲ ጦር ገብቶ የጐጃሙን ንጉስ ተክለ ሃይማኖትን ድል በማድረጉ አጤ ዮሐንስ ሁለት ወር ከቆዩ በኋላ ኢጣሊያኖችን ትተው በጐንደር የገባውን የእስላም ጦር ለመ ውጋት መጋቢት 22 ቀን 1880 ዓ.ም. ሠራዊታቸውን እየመሩ ወደ ደጋው ተመለሱ ። አስመራ ሲደርሱም ራስ አሉላን ከመረብ ምላሽ ግዛታቸው ሽረው ሚያዝያ 15 ቀን ከአስመራ ተነሱ ።

አጤ ዮሐንስ ያደረጉትን ቹም ሽር የሰማው የኢጣሊያ መንግ ስትም ሳን ማርዛኖን ሽሮ በቦታው ጄኔራል ባልዲሴራን በምፅዋ ለነ ባው ጦር አዛዥ አድርጐ ሾመው ። ባልዲሴራም ሲሾም በታዘ ዘው መሠረት ከመረብ ምላሽ ግዛት የገባው የአጤ ዮሐንስ ሠራዊት መመለስና የራስ አሉላ መሻር ቦታውን ባዶ ስላደረገለት በአስቸኳይ ወሰኑን መረብ ምላሽ አደርጐ ያዘ ። የኢጣሊያ ባንዲራም ወሰኑ ላይ ተውለበለበ ። አጤ ዮሐንስ መተማ ዘምተው መሞታቸው እንደተሰ ማም በ1882 ዓ.ም. ኢጣሊያኖች መረብ ምላሽ ቅኝ ግዛታቸውን ኤርትራ ብለው ሰየሙት ።

አጤ ዮሐንስ ያን ሁሉ ሠራዊት ይዘው ወደ ምፅዋ ከዘመቱ በኋላ ጦርነት ሳያደርጉና ሳይሞካከሩ ለምን ተመለሱ ? እንደ ራስ አሉላ ሁሉ ይሄም አጠያያቂ ነው ። ምናልባትም በዘመኑ የከብት በሽታ ገብቶ ከብት አልቆ እህል ስለጠፋ ወታደሩ በመራቡ ሊሆን ይችላል ። ምናልባትም ደግሞ የኤርትራው ገዥ ማርቲኒ እንደጻፈው እነ አባ ገብረ እግዚአብሔር ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር የውስጥ ወዳ ጅነት አበጅተው ስበኩ በተባሉት መሠረት ክርስቲያኑን ኢጣሊያን ከመውጋት እስላሙን ደርቡሽን መውጋት ይሻላል በሚለው ስብ ከት አምነውበት ይሆን ? ምናልባትም ደግሞ የጐጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በደርቡሾች ድል ሆነው ከተመለሱ በኋላ የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ለእርዳታ ብለው ጐንደር ሔደው ስለነበር አጤ ዮሐንስ የሁለቱን ንጉሶች መገናኘት ጠርጥረው ጣልቃ ገብተው ለመለያየት ብለው ይሆናል ። አጤ ዮሐንስ ከምጥዋ የተመለሱበትን የመተማን ጉዞ አቋርጠው ጐጃም ገብተው የንጉሥ ተክለሃይማኖትን የደከመ ሠራዊትና ሕዝብ የወጉትም በዚሁ ምክንያት ነው ። አጤ ዮሐንስ ጐጃምን ካጠፉ በኋላ ወደሸዋ ለመዝመት ሲያስቡ ምኒልክ ጦራቸ ውን አባይ ወንዝ ዳርቻ አሰልፈው ስለቆዩዋቸው አጤ ዮሐንስ ሸዋን ሳይገጥሙ ስለተመለሱ ምኒልክ የጠላታቸው ጠላት ከሆነው ከኢጣ ሊያ ጋር የተወዳጁትም በዚህና በሌሎችም ምክንያት ነበር ።

የዛሬዋን ኤርትራ ኢጣሊያኖች በቅኝ ግዛትነት ሊይዙ የቻሉት ኢትዮጵያውያን መኳንንት በማዕከላዊው መንግሥት ላይ እየሸፈቱ ለወንድም ጠላታቸው ጠላት ለሆነው ለውጭ መንግሥት በመርዳታ ቸው ነው ። ከእነዚህም ዋቂቶቹ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ሰሎሞን የአካለ ጉዛይ ገዥ የነበሩት ፣ ደጃዝማች ደብብ አርአያና የከረን ገዥ የነበሩትና ባላንባራስ ክፍለ ኢየሱስ ናቸው ።

## የውጫሌ ውል

“ . . . .እኛ ግን እንኳን ለአልፍና ለሁለት እልፍ ሰው ፤ የኢጣሊያ አገር ሰው ሁሉ ቢመጣ የኢጣሊያን ጥገኝነት ይቀበላሉ ብለህ አት ጠርጥር ። . . . . ” ምኒልክ ነሐሴ 23 ቀን 1887 ዓ.ም. ኤሮፓ ለነበረው ለሙሴ ኢልግ ከጻፉት የግል ደብዳቤ ላይ ።

“ . . . . የውጫሌው ውል ከምፅዋ ባህር ገብቷል። . . . .” የኢጣ ሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለኢጣሊያ ፓርላማ ካደረጉት ንግግር ።

አጤ ዮሐንስ ሲሞቱ ራስ መንገሻ ዙፋኑን እንዲወርሱ በመናዘ ዛቸው ዘፋኑ ለራስ መንገሻ አይገባም የሚሉት የመንገሻ ተቀናቃኝ የሆኑት የትግራይና የሐማሴን መኳንንት መንገሻን ለመጉዳት በማ ለት ወደ ኢጣሊያ ገቡ ። እነኚህም ወደ ኢጣሊያ የገቡ ሰዎች ለኢጣ ሊያ መንግሥት ታማኝነታቸውን ለመግለፅ የመሬት ገፀ በረከት አቀረቡ ። ደጃዝማች ደብብ አሥመራንና አካባቢዋን ፡ ደጃዝማች ባህታ ሐጐስ አካላ ጉዛይን ፣ ባላንባራስ ክፍለ ኢየሱስ ከረንና ቦጐ ስን ለኢጣሊያ መንግሥት አስረክበው እነሱ ከኢጣሊያ መንግሥት ሥር ተገዢ ሆኑ ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው በየመኳንንቱ ዘንድ አማካሪ በመ ምሰል የተቀመጡት የኢጣሊያ ሰላዮች በሁሉም ዘንድ ወዳጅ ሆነው በመሰለል የኢትዮጵያን መኳንንት እርስ በርሱ አሻከሩት ። በአጤ ምኒልክ ዘንድ የነበረው አንቶኔሊ ለአጤ ምኒልክ መንግሥት ያሰበ በመምሰል አሥመራ ውስጥ በኢጣሊያኖች የተረቀቀውን ውል አምጥቶ ምኒልክ ከኢጣሊያ መንግስት ጋር እንዲዋዋሉ አደረገ ። አንቶኒሊ ውሉን ይዞ የመጣ ጊዜ ምኒልክ አዲስ አበባ አልነበሩም ። ወሎ ውስጥ እየተዘዋወሩ ያልረጋውን አገር ይጐበኙ ነበር ። በነገሩ የቸኮለበት አንቶኒሊ ምኒልክ ካሉበት ወሎ ድረስ ሔዶ ውጫሌ ላይ ሠፈር አድርገው አገኛቸው ። በዚያም ውሉን አቅርቦና ሰብኮ ውሉን ምኒልክ እንዲዋዋሉ አደረገ ። ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም. የተዋዋ ሉት ውልም በነበሩበት ቦታ ስም የውጫሌ ውል ተባለ ። የውጫሌ ውል የተፈረመው አሰብ በተያዘ ከሃያ ዓመት በኋላ ሲሆን ፤ ኢጣሊያ በሐማሴን ግዛትዋን አስፍታ ወሰንዋን አደላድላ ከያዘች በኋላ ነበር ።

የውጫሌ ውል በሃያ አንቀጾች የተከፋፈለ ሲሆን ለአድዋ ጦርነት መነሻ የሆነችው 17ኛዋ አንቀፅ ናት ። ይህቺም አንቀጽ ቀጥላ ያለችው ናት ።

## ፲፯ተኛ፡ ክፍል፡

የኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ከኤውሮፓ፡ ነገሥታት፡ ለሚፈልጉት፡ ጉዳይ፡ ሁሉ፡ በኢጣሊያ፡ መንግሥት፡ እጋዥነት፡ መላላክ፡ ይቻላቸዋል፡፡

የውሉም ረቂቅ በተነበበ ጊዜ አጤ ምኒልክ "17ኛው አንቀጽ ጥቅም ስለሌለው ምን ያደርጋል ። ይቅር" ቢሉ ኮንት አንቶኔሊ "ቢጨመርስ ምን ይጐዳል" በማለት አስፈረመ ። ውሉ በአማርኛው ጽሑፍ ላይ ከላይ እንደተነበበው ዓይነት ሲሆን በኢጣሊያንኛው ጽሁፍ ላይ ግን "የኢትዮጵያ መንግሥት ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግሥት አማካይነት ማድረግ ይገባዋል" ይላል ።

Articolo XVII.

S. M. il Re dei Re d'Etiopia consente di servirsi del Governo di S. M. il Re d'Italia per tutte le trattazioni di affari che avesse con altre Potenze o Governi.

በውሉ ውስጥ ያለው ሌላው ቁም ነገር ጉዳይ ስለኤርትራ ወሰን የሚናገረው 3ኛው አንቀጽ ነው ። እሱም "በእነዚህ በሁለቱ ነገሥታት ወሰን ጠብና ክርክር እንዳይነሳ እውቅ የተመረጡ ከሁለቱ ወገኖች ሁለት ሁለት ሽማግሌዎች ልከው በማይጠፋ ምልክት የግዛቱን ድንበር ይዋሰናሉ ። ከድንበሩ ወዲህ የሚጨመሩ አገሮች እነዚህ ናቸው ። የደጋው አገር ከኢትዮጵያና ከኢጣሊያ መሀል ወሰን ይሆናል። ከራፋሌ ጀምሮ ሐላይ ፣ ሰገነይቲ ፣ አሥመራ ሶስቱ የኢጣሊያ መንግሥት መንደር ይሆናሉ ። ዳግመኛ በቦጐስ በኩል ዐዲንፋስ ፣ ዐዲ ሞጐስ በኢጣሊያ ድንበር ውስጥ ይሆናሉ ። ከዐዲሞገስ መንደር ጀምሮ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ባቀና ይከፈላል" ይላል ።

ይህን ኢትዮጵያውያን ሲራኮቱበትና ለብዙ ዘመናት ደማቸውን ሲያ ፈሱ የኖሩበት የባህር በርን የሚዘጋውን ውል ምኒልክ ለምን ተቀ ዋሉ ? ማንኛውም የአሁኑ ኢትዮጵያዊ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው ። አጼ ዮሐንስ "ክርስቲያኑን ኢጣሊያን ከመውጋት፣እስላሙን ደርቡ ሽን መውጋት ይሻላል" ብለው ወደ መተማ ሲዘምቱ ኢጣሊያኖች ገስግሰው መረብ ድረስ ያዙ ። የአጼ ዮሐንስን ደግነትና የዋህነት በተለይም በሃይማኖታቸው በኩል የጠኑ መሆናቸውን ኢጣሊያኖች በሚገባ ያውቃሉ ። ወደ መተማ እንዲዘምቱ ያስደረጉም ኢጣሊያ ኖች ናቸው ። ሃይማኖተኛ መስለው ለገንዘብ የተገዙ መነኮሳትን አስ ባስበው ዮሐንስ ዘንድ በመላክ "ከክርስቲያኑ ኢጣሊያ ጋር ቢዋጉ ድል ቢያደርጉም በነፍስዎ ግን ይበደላሉ ። ከእስላሙ ከደርቡሽ ጋር ተዋግተው ቢሰዉ እንኳ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ" እያሉ ትን ቢት አስመስለው ስለነገሩዋቸው የዋሁ አጼ ዮሐንስም ይህንኑ አባ ባል ለመኳንንቶቻቸው ተናግረው ወደ መተማ ዘመቱ ። ነገሩ ግን ኢጣሊያኖች በር ለማስከፈት ያደረጉት ተንኮል ነበር ።

አጼ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ ኢጣሊያኖች የያዙት ወሰን እንዲረ ጋላቸው ከምኒልክ ጋር ውል ለመዋዋል ፈለጉ ።ይህንንም ውል ለማ ስፈፀም በኢትዮጵያ መኳንንት ዘንድ ወዳጅ የሆነውና በቤተ መንግ ሥቱም ተወዳጅ የነበረው ኮንት አንቶኔሊ ተመረጠ ። አንቶኔሊ ሸዋ ገብቶ መቀመጥ ከጀመረ ቆይቷል ። ከኢትዮጵያዊት ሴትም ሁለት ልጆች አስወልዷል ። በተለይ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር ጥሩ ወዳጅነት ስላ ለው ከውጭ አገር የፔርሺያ ጫማና የእግር ሹራብ ለጣይቱ ያስመ ጣላቸው ነበር ።ይህን የመሰለው ወዳጅነት ለማታለለም ሆነ ለመስ በክ አመችቶት ነበር ። የውጫሌ ውል የተባለውን ለማስፈፀም የተመ ረጠው አንቶኔሊ ብቻ አልነበረም ። እንደ አንቶኔሊ ሁሉ በኢትዮጵያ ውያን ዘንድ የታወቀው ሳሊምቢኒ የተባለውም ለአንቶኔሊ ረዳት ሆኖ ተመርጦ ነበር ።

ሳሊምቢኒም በሸዋ የቆየ ኢጣሊያዊ ነው ። ምኒልክ በውጫሌ ውል ስለኤርትራ ወሰን በሚናገረው በ3ኛው አንቀፅ አልስማማም ባሉበት ጊዜ ምኒልክን ያግባባ ሳሊምቢኒ ነው ። ሳሊምቢኒ በጻፈው ሐተታ ስለዚያን ጊዜው ምኒልክ አልስማማም ስላሉበት ስለ 3ኛው አንቀጽ ጉዳይ ሲያትት "እንዲህ አልኳቸው" ይላል ፡ " . . . .ጃንሆይ ። የኢጣ ሊያ መንግሥት ትግሬ ድረስ ልያዝ የሚለው ለክፋት አይደለም ። ወሰኑን ከትግራይ ጋር አድርጐ በዚያ መሀል ያሉትን ሽፍቶች ለማ ጥፋት ብሎ ነው ። 2ኛም የኢጣሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ ቀደም ብለው ለኢጣሊያ ፓርላማ ንግግር ሲያደርጉ ከኢትዮጵያ ጋር ያለው ወሰናችን መረብ ፤ በለሳና ሙና ነው ብለው ተናግረዋል ።

አሁን ይሄ አይደለም የተባለ እንደሆነ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ ትልቅ ሐፍረትና ውርደት ይሆናል ። 3ኛው ፣ የኢጣሊያ መንግሥት በእርስዎ ላይ ከሸፈተው ከትግራዩ ገዥ ከራስ መንገሻ ጋር በዚህ ወሰን ላይ የተዋዋሉ እንደሆነ የኢጣሊያ መንግሥት እርስዎን በመርዳት ፈንታ የሚረዳው ራስ መንገሻ ዮሐንስን ይሆናል ። ይህ ደግሞ ትልቅ መጥፎ ነገር ያመጣል ። ሸዋ ሁሉ በትግሬ ሥር ይወድቃል ። . . . . ይህ ወሰን የሚከለሉበት ሥፍራ ደግሞ የአውሬ መፈንጫና ሰው የማይደርስበት አስፈሪ ቦታ ነው ። አሁንም ቢሆን የጠቀመው ለሽፍቶች መደበቂያ እንጂ ሌላ ምንም ጥቅም የለው ። ይህ ቦታ ለሹማምንት ሁሉ ያስቸገረ ነው ። የኢጣሊያ መንግሥት ጉልበት ስላለው ይሄን ከትእዛዝ ውጭ የሆነውን ሽፍታ በኃይል ለመግራት ይችላልና እንዲያቀናው ቢፈቀድለት ይሻላል . . . . አልኳቸው ።

“ምኒልክም ሲመልሱልኝ ገና ታላቁ ንጉሥ አጤ ዮሐንስ ሳይሞቱ አንቶኔሊ ኢጣሊያ የምትፈልገው ለወታደሮችዋ ማሳረፊያ ከምፅዋ የምትዛወርበት ጥሩ አየር ያለበትን ቦታ ብቻ ነው ። ሌላ ምክንያት የለንም ብሎ አታሎ መቆናጠጫ ያዙ ። ንጉሱ ወደ ደርቡሽ ሲዘምቱም ኢጣሊያኖች ተስፋፍተው አገሩን ያዙ ። አሁን ደግሞ በኔ ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከሆንኩ ወዲህ ወሰናችን መረብ ድረስ ነው ብትሉኝ ፣ ትግሬን ሁሉ ከያዛችሁ ለኔ ምን ይቀረኛል ? ደግሞም ትግሬዎች ደማቸውን ያፈሰሱበትን መሬት እመልሳለሁ እንጂ እንዴት በዚያው እርጉ እላለሁ ? ሲሉ ጣልቃ ገባሁና ጃንሆይ በዚህስ አይታለሉ ። አበሻን የከበቧት እስላሞች በመሆናቸው ሁሉም ጠላቶች ናቸው ። የኢጣሊያ መንግሥት ግን ክርስቲያን ስለሆነ ትረዳዳላችሁ እንጂ በክፉ አትተሳሰቡም አልኳቸው . . . . ” ሲል ዛጊ ባሳተመው መጽሐፍ ላይ ተንትኖዋል ።

አቶ ግርማይ ገብረ ጻዲቅ የካቲት 20 ቀን 1980 በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ “ . . . . በአጤ ዮሐንስ ሞት ምክንያት የኢትዮጵያ መኳንንት በሥልጣን ይገባኛል ሲራኮቱ አጋጣሚው ይበልጥ ለጠላት አመችቶ እነሱን ጭምር በመሣሪያነት በመጠቀም ባሕረ ነጋሽን ኤርትራ ብሎ በመሰየም ወደ ትግራይ ሲዘልቅ ለአዲሱ ንጋሲ ለምኒልክ ታላቅ የራስ ምታት ሆነ ።

“የኢጣሊያ ጦር መረብን ተሻግሮ ትግራይን ሲወር ፣ አባዳኘው ከነገሡ መንፈቅ እንኳ ስላልሞላቸው አስተማማኝ ኢኮኖሚያዊ መሠረትና ኃይል አልነበራቸውም ። ታላላቆቹ ያገሪቱ መሣፍንትም ጀርባቸውን በመስጠት ከጠላት ጋር ተሰልፈው ሊወጉዋቸው እያሴሩባቸው ነበር ። በሌላ በኩል ደግሞ አገሪቱ በታሪኳ ውስጥ አጋጥሞአት በማ

ያውቅ "ታላቅ ረሃብ" ውስጥ ነበረች ። በአገሪቱ በሞላ ሕዝቡና ጥሪቱ አብሮ እንደቅጠል በመርገፍ ላይ ነበር ። እናም "ምን ተይዞ ጉዞ" ሆነና ምኒልክ ጠላቶቻቸውን የሚወጉበት ስልት ከመለወጥ ሌላ የተሻለ አማራጭ አልነበራቸውም ። በመሆኑም ምኒልክ ያለ ተከላካይ እንደፈረሰኛ ጐርፍ እየጋለበ ወደ መሃል አገር ይገሰግሥ የነበረውን ጠላታቸውን ውጫሌ ላይ በፈረሙት ውል አማካይነት ከመረብ ፣ በለሳ ፣ ሙና መሥመር እልፍ እንዳይል በማድረግ ለማይቀረው ጦርነት ሁለገብ ዝግጅት ማድረግ ጀመሩ ። ብዙ የታሪክ ፀሐፊዎች እንደ ተስማሙበት ምኒልክ በዚህ ወቅት የተጠቀሙበት ስልት ፣የዲፕሎማሲ ብስለታቸውን ፣ አርቆ አሳቢነታቸውን ፣ ተጨባጭ ሁኔታ የማመዛዘንና የመገምገም ችሎታቸውን ፣ የአመራር ብቃታቸውን በሚገባ አረጋግጧል ። . . . ." በማለት ጽፍዋል ። ሌላው ውል ደግሞ ከአድዋ ድል በኋላ አለ ።

ኢጣሊያኖች ይህን የውጫሌ ውል ከተዋዋሉ በኋላ ለአሥራ ሁለት ኤሮፓ መንግሥታትና ለዩናይትድ እስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ጥምር አክቶበር 11 ቀን 1889 ዓ ም በተፃፈ ደብዳቤ "ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ሥርነች" እያሉ አሳወቁ ። በትምህርት ቤት መማርያ ደብተሮችም ላይ ሁሉ ፣ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ጥገኝነት ሥር ናት የሚል ታተመ ።

አጤ ምኒልክ በኢጣሊያ በኩል ያለው የውጫሌ ውል ጉዳይ አልገባቸውም ነበርና በኢትዮጵያ ላይ መንገሳቸውን ለማሳወቅ ለጀርመኑ ንጉሥ ነገሥት የጻፉት ደብዳቤ ለውጫሌ ውል ብጥብጥ መነሻ ሆነ ። ምኒልክ የጻፉትን ደብዳቤ የጀርመኑ ንጉሠ ነገሥት በቀጥታ በመቀበላቸው ውዝግብ ተነሳ ። የኢጣሊያ አገር ጋዜጦች ". . . .በውጫሌ ውል ላይ ኢትዮጵያ የኢጣሊያን ጥገኝነት ተቀብላ ውል ከፈረመች በኋላ የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ከኢትዮጵያ የሚላከውን ማንኛውንም ደብዳቤም ሆነ ጉዳይ በኢጣሊያ መንግሥት በኩል መቀበል ሲገባቸው በቀጥታ ከምኒልክ የተጻፈውን ደብዳቤ ተቀብለዋል. . . ." እያሉ የጀርመኑ ንጉሠ ነገሥት የሁለቱን አገሮች ውል እንዳፈረሱ ያህል ተቆጥረው ተጸፈባቸው ።

በዚያን ጊዜ ልዑል ራስ መኰንን በኢጣሊያ አገር በጉብኝት ላይ ነበሩና በኢጣሊያ አገር ስዕል እንዲማሩ ተልከው የነበሩት ልጅ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ (በኋላ ፕሮፌሰር የሆኑት) በጋዜጣ ያነበቡትን ለራስ መኰንን ነገሩዋቸው ። ራስ መኰንንም አስጐብኚያቸው የነበረውን አንቶኔሊን ስለዚህ ጉዳይ ቢጠይቁት ". . . ያ ደደብ ኢትዮጵያዊ ተማሪ ትርጉሙ ስላልገባው ነው" ብሎ ተሳደበ ። ራስ መኰንንም ተቃውሞአቸውን ለኢጣሊያ መንግሥት ከነገሩ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ የውሉን መበላሸት ለአጤ ምኒልክ አሳወቁ ።

ወዲያውንም አከታትሎ የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ለዳግማዊ ምኒልክ የጻፉላቸው ደብዳቤ ደረሳቸው ። የጀርመን ንጉሠ ነገሥትም ሆኑ መንግሥታቸው ከኢትዮጵያ ጋር ለመወዳጀት መፍቀዱን ይገል ፅና ፣ ለመወዳጀትም ሆነ ለሌላ ጉዳይ መነጋገር የሚቻለው በቀጥታ ሳይሆን በውጫሌ ውል መሠረት በኢጣሊያ መንግሥት አማካይነት መሆኑን የሚገልፅ ነበር ።ይህንንም ደብዳቤ ቢሆን የጀርመኑ ንጉሠ ነገሥት በቀጥታ ለምኒልክ አላኩም ። ደብዳቤው የተላከው በኢጣ ሊያ መንግሥት አማካይነት ለምኒልክ እንዲደርስ ተብሎ ስለነበር ኢጣሊያኖች ተደስተው የበላይነታቸውን ለማሳወቅ በጀርመንኛ የተ ጻፈውን የንጉሠ ነገሥቱን ደብዳቤ በኢጣሊያንኛ ተርጉመው ወደ ምኒልክ ላኩት ።

ወዲያውኑ ደግሞ የኤሮፓ ኃያላን መንግሥታት የባርያ ንግድን ለማስቀረት በ1882 በብሩሴል ጉባኤ ባደረጉ ጊዜ የኢጣሊያ መን ግሥት መልክተኛ "ኢትዮጵያ በኢጣሊያ መንግሥት ጥገኝነት ሥር ስለሆነች ዛሬ በጉባኤው ላይ የተገኘሁት የኢትዮጵያንም መንግሥት ወክዬ ነው" ብሎ ንግግር በማድረጉ ጉባኤው ለጥቂት ጊዜ ታወከ ። የእንግሊዝና የጀርመን መልክተኞች የኢጣሊያው መንግሥት መልክ ተኛ ያደረገውን ንግግር ተስማምተውበት "ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ጥገኝነት ሥር ናት" በሚለው አቋም ረጉ ። የጅቡቲ ቅኝ ግዛቱን ለማ ስፋት ምኞት የነበረው የፈረንሳይ መንግሥት መልክተኛ የመንግሥ ቱን አቋም ሲገልፅ "ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ጥገኝነት ሥርናች የሚለ ውን አባባል አልቀበልም"ብሎ አመለከተ ።የሩሲያው መልክተኛም "አንድ ለብዙ ዘመን ነፃ ሆኖ በክርስቲያን ንጉሥ የሚገዛውን ነፃ አገር በጫና መያዝ ስለማይገባ የኢጣሊያኑ መልክተኛ የኢትዮጵያ ተወካይ ነኝ የሚሉትን ንግግር አንቀበልም"አሉ ።የቱርክ መንግሥት ተወካይም በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የመንግሥታቸውን የመስፋ ፋት ምኞት ስለሚያውቁ ለኢትዮጵያ አሳቢ መስለው የኢጣሊያኑን መልክተኛ ንግግር እንደሚቃወሙ ገለጡ ። ኦስትሪያና የቤልጅግ መን ግሥታት መልክተኞች ግን "በውጫሌው ውል መሠረት ለዚህ ጉባኤ የኢጣሊያ መንግሥት ለኢትዮጵያ ተወካይ ቢሆን እንቃወ ምም" በማለታቸው ጉዳዩ በድምፅ ብልጫ ተወስኖ ኢጣሊያ ኢትዮ ጵያን ወከለች ።

ይህን ሁሉ ጉዳይ ምኒልክ በወዳጆቻቸውም ከጠላት ወዳጆ ቻቸው ሁሉ ሰሙት ። በዚያ በደካማ አቅማቸው ምንም ለማድረግ ስለማይችሉም ትርፋቸው ንዴት ብቻ ሆነ ። ነገሩንም በሰላም መንገድ ለመጨረስ አስበው የተበላሸው የውጫሌ ውል እንዲሻሻል በማለት ለኢጣሊያው ንጉስ ለቀዳማዊ ኡምቤርቶ በመስከረም ወር 1883 ዓ.ም. የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉላቸው ።

ለወዳጃችንና ወንድማችን ግርማዊ ንጉሠ ኡምቤርቶ ።
የኢጣሊያ ንጉሥ ።
ሰላም ለርስዎ ይሁን

በንግሤ ምክንያት ወዳጆች ለሆኑት የአውሮፓ መንግሥቶች ከንጉሠ ነገሥት ዙፋን ላይ መውጣቴን ባስታውቃቸው በመጣልኝ ምላሽ ውስጥ መንግሥቴን የሚያኮስስ ነገር አገኘሁበት ። የዚህ መሠረትም የሚገኘው ውጫሌ ላይ በሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓ ም በተደረገው ውል 17ኛው አንቀጽ ውስጥ ነው ። ይህነን አንቀጽ ደህና አድርገን ከተመለከትነው በኋላ ፤ የአማርኛው ምንጭና የኢጣሊያንኛው ትርጉም የማይገጣጠሙ መሆናቸውን አረጋገጥን ።

እኔ ለኢጣሊያ ስለወዳጅነት ብዬ ይህን ውል ስገባ ምሥጢራችን ተጠብቆ እንዲኖር ፤ ጉዳዮቻችንም እንዳይበላሹ በማለት በየአውሮፓ ለሚሆኑ የንግድ ጉዳዮቻችን በወዳጅነት በኢጣሊያ ንጉሥ መንግሥት ረዳትነት ሊደረጉ የሚችሉ መሆኑን ተናገርኩ እንጂ ለዚህ የሚያስገድደኝ ውል አልገባሁም ።

ግርማዊ ንጉሥ አንድ የሌላ መንግሥት ጥገኛ ያልሆነ መንግሥት ፣የሌላውን መንግሥት ረዳትነት በወዳጅነት ብቻ እንደሚፈልገው ይገባዎታል ። ከዚህም በቀር የውሉን 19ኛ አንቀጽ በሁለቱም ቋንቋዎች የቃሉ አሳብ የተስማማ እንደሆነ ብቻ ውልነታቸው የሚጸና መሆኑን የሚያመለክተውን ልብ አድርገው ይመልከቱት ።

በአማርኛ የተጻፈው 17ኛው አንቀጽ የሚለው ከሌሎች መንግሥቶች ጋር ለሚደረገው ጉዳይ በኢጣሊያ አማካይነት ላደርገው እንደምችል ይናገራል ። ነገር ግን ከአውሮፓ መንግሥቶች ሁሉ ጋር በማደርገው የንግድ ጉዳይ ሁሉ በኢጣሊያ አማካኝነት ላደርገው መፍቀዴን አይናገርም ።

ውሉን ለመጨረስ ከአንቶኔሊ ጋር ስንነጋገር እርሱን በምር ጠየቅሁትና እንዲህ ብሎ መለሰልኝ ። ቢያሰኝዎ የእኛን አማካይነት ይቀበላሉ ። የተመቸ ሆኖ ባይታይዎ ግን ሊተዉት ይችላሉ አለኝ ። እኔም እንደዚህ አልኩት ። ይህ ጉዳይ የወዳጅነት ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ለምን ብዬ ጉዳዬን በሌላ በኩል ልፈጽም ። ግን እኔ በዚያ ጊዜ የተመቸኝን ከማድረግ የሚያግደኝ ውል አልገባሁም ። ዛሬም ቢሆን በእንዲህ ያለ ግዴታ የምገባ ሰው አይደለሁም ። እርስዎም እንደዚሁ ተቀበል አይሉኝም ።

አሁን እርስዎ ለወዳጅዎ ክብር ብለው በ17ኛው አንቀጽ የተደረገውን ስህተት እንዲቀና እንዲያስደርጉትና ይህን አንቀጽ ላስታወቋቸው መንግሥቶች ስህተቱን እንዲገልፁላቸው እመኛለሁ ።

ረጅም ዕድሜ እንዲሰጥዎና ወዳጅነታችን ከማናቸውም መታ
ወክ እንዲጠበቅ እግዚአብሔርን እለምናለሁ ።"

ምኒልክ ደብዳቤ መጻፍ እንጂ የጻፉትን ደብዳቤ ከኢትዮጵያ
ውጭ መላክ አይችሉም ነበር ። ምክንያቱም የኢጣሊያ መንግሥት
የምኒልክን ደብዳቤ ከኢትዮጵያ እንዳይወጣ ከፍተኛ ቁጥጥር በማድ
ረግ እየያዘ ያስቀርባቸው ስለነበር ነው ። ይህ ስለሆነ ምኒልክ በካይሮ
ተቀማጭ የሆነ ፓሪሲስ የሚባል ግሪካዊ ወዳጅ አላቸው ። ደብዳቤያ
ቸውን ጽፈው ነጋዴ በሚመስሉ መልክተኞቻቸው ዘይላ ድረስ ይል
ኩና ከዘይላ በፖስታ ቤት በኩል ለፓሪሲስ ይላክል ። ፓሪሲስም የምኒ
ልክን ደብዳቤ በየአድራሻው ያደርስ ነበር ።

ምኒልክ አሁን ያነበብነውን ደብዳቤ ለኢጣሊያው ንጉሠ ነገ
ሥት ለኡምቤርቶ እንዲደርስ አደረጉ ። የኢጣሊያ መንግሥት የምኒ
ልክ አዝማሚያ አላምር ስላለው የውጫሌውን ውል ጉዳይ የጀመረ
ውና ውል አስፈርሞ የጨረሰው ኮንት አንቶኔሊ ስለሆነ በጉዳዩ እን
ዲነጋገር ወደ አዲስ አበባ ተላከ ።

አሁንም ቢሆን ኮንት አንቶኔሊ በዋና መልክተኛነት ተላከ
እንጂ ሳሊምቤኒ ደግሞ የውጫሌን ውል ጉዳይ ባለበት እንዲያቆይ
ታዞ ነበር ። ስለዚህ ጉዳይ ሳሊምቤኒ በያዘው ማስታወሻ ላይ ሲጽፍ
" . . . . የኢጣሊያ መንግሥት አንድ ሺህ ብር ጉቦ ለግራዝማች ዮሴፍ
ንጉሤ እንድሰጥና ዮሴፍም ምኒልክ የውጫሌን ውል እንዲቀበሉ
እንዲያደርግ አድርግ ተብዬ አደረግሁ ። . . . ." ይላል ። ግራዝማች
ዮሴፍ እንደ ሳሊምቤኒ አጻጻፍ ሺውን ብር ጉቦ ተቀብለው እንደሆነ
ኢጣሊያኖችን አታለዋቸዋል ። ምክንያቱም ሺህ ብራቸውን ተቀብ
ለው የተገላቢጦሽ ምኒልክ በውጫሌ ውል መፍረስ እንዲጠኑ ይመ
ክሩ ነበርና ነው ።

ኢጣሊያኖች ጉቦ የሰጡት ወይም ለመስጠት የፈለጉት ለግራ
ዝማች ዮሴፍ ብቻ አይደለም ። ሩሲያዊው ሊዎንቲቭ በዚያን ጊዜ
ለአጤ ምኒልክ የቅርብ ወዳጅና አማካሪ ስለነበር እሱንም አባብለ
ውት ነበር ። ሊዎንቲቭ ወዳገሩ ወደ ፔትስበርግ ሄዶ በነበረ ጊዜ
በዚያ ከኢጣሊያ አምባሳደር ጋር ተገናኙ ። አምባሳደሩም "ይህ ከም
ኒልክ ጋር ጭቅጭቅ ያስነሳውን ነገር በሰላም እንዲጨረስ ብታደርግ ፥
ሁለት ሚሊዮን ሩብል እንሰጥሃለን" ብሎ የኢጣሊያ አምባሳ
ደር መለመኑን ሊዎንቲቭ ለልዑል ሉባኖቭ ገልጾላቸዋል ። ይህንንም
ታሪክ ራሱ ሊዎንቲቭ በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ በሰፊው ጽፎታል ።
ወደ ኮንት አንቶኒሊ አመጣጥ እንመለስ ።

ኮንት አንቶኔሊ ከምኒልክ ችሎት ቀርቦ "ኢጣሊያ 17ኛው አንቀጽ ተበላሽቷል ወይም ተሳስቷል የሚባለውን አትቀበልም ። በዚህም ጉዳይ ማንም ኃያል መንግሥት ሊያስገድዳት አይችልም ። ምክንያቱም ክብሯን የምትጠብቅ ታላቅ መንግሥት ናት" አላቸው ። ይህን በሚናገርበት ጊዜ እቴጌ ጣይቱ በዚያው በችሎቱ ላይ ስለነ በሩ ወዲያውኑ የኮንት አንቶኔሊን ንግግር አቋርጠው "ያ አንቀጽ የሚ ለውን ነገር እኛም ለኃያላን መንግሥታት አሳውቀናል ። በአማርኛ ቋንቋ የተፃፈው ምን እንደሚልም ነግረናል ። እንደ እናንተ ሁሉ እኛም ክብራችንን እንጠብቃለን ።እናንተ የምትመኙት ኢትዮጵያ በእናንተ ሥልጣን ሥር እንድትሆን ነው ። ይህ ለምን ጊዜም የማይ ሆን ነገር ነው" አሉት ። አንቶኔሊም " . . . .የተዋዋልነው ውል ለአም ስት ዓመት ብቻ ነው ። አሁን ይኸው ካምስቱ ዓመት ሁለት አለፈ ። እንግዲህ ሶስት ዓመት ብቻ ነው የቀረንና ከፋም ጥሩም ሆነ ይኸው ውላችን እንዳለ ሶስት ዓመት ይለፍ" አለ ። አጤ ምኒልክ ግን "ነገሩ ሳይጐላ እንዲህ ባንጉል እንኳን ሶስት ዓመት ፣ ሶስት ቀንም ቢሆን አያድርምና ይልቁንስ አሁን ቶሎ ይለቅ" ብለው ወጥረው ያዙት ።

ኮንት አንቶኔሊ እየደጋገመ "ላጭር ጊዜ ብለን እንጣላ ። አም ስቱ ዓመት ሲያልቅ ውሉ እንደገና ይሻሻላል ስለሚል በውሉ መሠረት ያን ጊዜ አስፈላጊ ከሆነ ይህን አንቀጽ ልናሻሽለው እንችላለንና አሁን 17ኛው አንቀጽ አይነሣ ይቅር" አለ ። አስተርጓሚውም አቶ ዮሴፍ የልጥ ማረፊያው ነበሩና ነገሩን ባጭሩ አድርገው ሲተረጉሙ "17ኛው አንቀጽ አይነሣ ፣ ይቅር" ብለው ተረጐሙ ። አጤ ምኒልክ ይህን ቃል ሲሰሙ "እኔስ እስከዛሬ የተናገርሁት አሥራ ሰባተኛው ክፍል ያለው ቃል እንዲቀር አልነበረምን ።አሁንም እሺ ወዲያ ይቅር ይሰረዝ"አሉ ።

በዚህ አባባል ሁለቱም ወገኖች ተደሰቱ ። ጉዳዩም እንደገና እን ዲፃፍ ተደርጎ ተፃፈ ። የተፃፈውም ጽሑፍ "17ኛው አንቀጽ ተሠር ዟል" የሚል ነበር ። ይኸው ቃል ባማርኛ ብቻ በሁለት ወረቀት ተጽፎ አንዱ ለኮንት አንቶኔሊ ተሰጠው ። አንዱ ከምኒልክ ቤተ መንግሥት እንዲቀመጥ ተደረገ ። ኮንት አንቶኔሊም የተሰጠውን ወረቀት ይዞ እየተደሰተ ሄደ ። በማግሥቱ ኮንት አንቶኔሊ ያን ጽሑፍ ወደ ኢጣሊ ያንኛ ሲያስተረጉመው "17ኛው ክፍል የነበረው ቃል ተሠርዟል ። ለመቼውም ተፍቋል" የሚል ሆኖ አገኘው ። በዚህም ጽሑፍ ደንግ ጦና ተናዶ ወደ ቤተ መንግሥት ሄደ ። ከዚያም ምኒልክና ጣይቱ ፣ መኳ ንንቱም ካሉበት እልፍኝ ገብቶ ለምን ተሠርዟል የሚል ቃል ተፃፈ ? ብሎ ጠየቀ ። አጤ ምኒልክ "ሁለታችን ተነጋግረን አንተው ወደህ የተጣፈ ነው እንጂ እኛ የጨመርንበትም የቀነስንበትም ነገር የለም ።"

አሉት ። አንቶኔሊም "ለጊዜው አሁን አይነሳ አልኩ እንጂ ጨርሶ ይሰረዝ አላልኩም" አለ ። አጤ ምኒልክም "ባስተርጓሚ በነገርከን ቃል መሠረት የተጣፈ ነው ። አሁን ለምንድነው የጸጸተህ?" ሲሉት ኮንት አንቶኔሊ ባስተርጓሚው ዮሴፍ ላይ አፍጥጦ "ይሄን ሁሉ ነገር የምታበላሽ አንተ ነህ ። ቀጣፊ" ብሎ ተሳደበ ።

ኮንቱ አንቶኔሊ ዮሴፍን ሲቆጣ የሰሙት ጣይቱ "አጥፍቶስ ቢሆን አሽከራችንን በሚገባ እኛ እንቆጣለን እንጂ አንተ እንዲህ አላግባብ በኛ ፊት አሽከራችንን መሳደብ አይገባም" አሉት ። ኮንት አንቶኔሊም አፍሮ ይቅርታ ጠየቀ ። እቴጌ ጣይቱም "በውጫሌው የተ ዋዋልንበት ወረቀትም ቢሆን ፣ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ውስጥ ታድራ ለች የሚል ቃል ታማርኛው አይገኝበትም ። እንዲህ ያለ ቃል ተጽፎበ ታል የምትል እንደሆን ተሆነልህ አሳየን ። በትላንትናውም ነገር የሆነ እንደሆነ አንተው ወደህ የአሥራ ሰባተኛ ክፍል ነገር ይቅር አይነሳ ብትል ይኸው ተጣፈ ። አሁን ለምን ነው መጠጠትህ ። ከመ ጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ጃንሆይ ከተናገሩት ሁሉ አን ድም ቃል አልተዛባም ፣ አልተዛነፈም" ብለው ተናገሩት ።

አንቶኔሊም ውጫሌ የተዋዋልንበት ወረቀት በፈረንሣይ ቋንቋ የተጣፈው ይታይልኝ ብሎ አመለከተ ። እቴጌ ጣይቱም "እኛ እምና ውቀው በአማርኛ የተጣፈውን ነው እንጂ የፈረንጅ ቋንቋ አናው ቅም ። አንተ ግን የኛን ቋንቋ ታውቃለህና ባማርኛ የተጣፈውን እየው"አሉት ። ከዚህ በኋላ ኮንት አንቶኔሊ ተናዶ ያን ትናንት የተጣ ፈውን ወረቀት ቀዳዶ ጥሎ ውሉን የኢጣሊያ መንግሥት በጦር ኃይል እንደሚያስከብር ተናገረ ። ይህን የሰሙት እቴጌ ጣይቱም ስቀው "የዛሬ ሣምንት አድርገው ። በዚህ የሚደነግጥልህ የለም ። ሂድ የፎከርክበትን አድርግ ። እኛም የመጣውን እናነሳዋለን ። እግሩን ለጠ ጠር ፣ ደረቱን ለጦር ሰጥቶ አገሩን የማያድን ሰው በዚህ የሌለ አይም ሰልህ ።የገዛ ደሙን ገብሮ ለገዛ አገሩ መሞት ጌጥ ነው እንጂ ሞት አይባልም ። አሁንም ሂድ ፣ አይምሽብህ ፣ የፈከርክበትን በፈቀድህ ጊዜ አድርገው ። እኛም ከዚህ እንቆይሃለን ።" አሉት ።

ሳሊምቢኒ በያዘው ማስታወሻ 23 ዲሴምበር 1890 በሚለው ላይ አንቶኔሊ የውሉን ማሻሻያ ቀድዶ በጣለው ጊዜ እቴጌ ጣይቱ " . . . . እኔ ሴት ነኝ ። ጦርነት አልወድም ። ግን እንዲህ መሳዩን ውል ከመቀበል ጦርነት እመርጣለሁ አሉ ። . . . ." ሲል ጽፍዋል ።

ትራቢርሲ ደግሞ የዕለቱን ሁኔታ እየመዘገበ ለኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያስተላልፍ ነበር ። ኦገስት 26 እና 29 ቀን በጣፈው " . . . ምኒልክ የአስተርጓሚውን መሰደብና የደብዳቤውን ከፊታቸው

መቀደድ ባዩ ጊዜ አንቶኔሊን ለመደብደብ ከመቀመጫቸው ተነሱ ። በዚያ ያሉ መኳንንትና በተለይ እቴጌ ጣይቱ ገላግለው አንቶኔሊን ከመደብ ደብ አዳኑት. . . .'' ብሏል ። በአገራችን ባንዳንድ መጽሐፍትና ጋዜጦች ኮንት አንቶኔሊ በምኒልክና በጣይቱ ፊት የቀደደውን ወረቀት የውጫሌ ውል ነው እያሉ ጽፈውታል ። ግን አይደለም ። የውጫሌ ውል የተቀደደው በመድፍ ነው እንጂ በአንቶኔሊ እጅ አይደለም ።

አንቶኔሊ ከስብሰባው ሲወጣ ምኒልክ ለጋሲዮኑ ድረስ የሚሄድ በት በቅሎ ስጡት ብለው ተሰጠው ። አንቶኔሊ በቅሎ ለሰጠው አሽ ከር አንድ መቶ ብር ሰጠ ። አሽከሩም የተሰጠውን ብር ይዞ አዳራሽ ገብቶ ለምኒልክ ነገረ ። ራስ መኰንን ከዚያው ነበሩና ''ጉርሻ ከሆነ ይበዛል ። ጃንሆይ ለሰጡት በቅሎ ዋጋ ከሆነም ያንሳልና ይመለስ'' አሉ ። ምኒልክም ስቀው ለአሽከሩ ''ጉርሻ ነውና ውሰደው''አሉት ።

ከዚህ በኋላ በጉዳዩ የተናደዱት አጤ ምኒልክ የውጫሌውን ውል በተዋዋሉ በ4ኛው ዓመት ለኤሮፓ ኃያላን መንግሥታት ሁሉ አድራሻው እየተለዋወጠ ቃሉ አንድ ዓይነት የሆነውን የውጫሌን ውል ያፈረሱበትን ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጻፉ ።



ሞዓ፡አንበሳ፡ዘእምነገደ፡ይሁዳ። ዳግማዊ ምኒልክ፡ሥዩመ፡እግዚአ

ብሔር፡ንጉሠ፡ነገሥት፡ዘኢትዮጵያ። [illegible]

[illegible]

ይህ የምኒልክ ደብዳቤ የደረሳቸው ነገሥታትና መንግሥታት ሁሉ በሁለት በኩል ተከፈሉ ። ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ሐሳብ የሌላቸውም ሆኑ ያላቸው መንግሥታት ኢጣሊያ ባላት ኃይል ኢትዮጵያን እንደምትጐርሳት አሰቡ ። አዘኑ ። የቅኝ ገዢነት ምኞት የነበራቸው ያዘኑበት ዋናው ምክንያት ኢጣሊያ ከሁሉም ቀድማ ኢትዮጵያን ለመያዝ የሚያስችላት መንገድ ስለተጠረገላት ነበር ። የምኒልክ ወዳጅ የነበሩ መንግሥታት ግን ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በቀላሉ መያዝ እንደምትችል አወቁ ። ምናልባትም የኢትዮጵያን መንግሥት ባለበት ሁኔታ ማለት ባገሩ ሰው የውስጥ አስተዳደሩን እየመራ እንዲቆይ ለማድረግ የተሻለው ዘዴ ፤ ኢትዮጵያ የኢጣሊያን ጥገኝነት ተቀብላ በውጫሌው ውል እንድትረጋ የሚያስፈልግ መሆኑ ተሰማቸው ። ይህንኑም በመግለፅ የእንግሊዝ መንግሥት ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር በተዋዋሉት ኮንቬንሽን ኦፍ ሮም በተባለው ውል መሠረት ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ጥገኛ መሆንዋን አውቆ ስለነበር የእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ ለምኒልክ በጻፉት ደብዳቤ በኢጣሊያ ጥገኝነት ሥር እንዲቆዩና ለኢትዮጵያም የሚሻለው ዘዴ ይሄው መሆኑን ገለጡላቸው ።

የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ደግሞ በኢጣሊያ ጥገኝነት ሥር መቆየቱ ለኢትዮጵያ የሚበጅ መሆኑን በመግለጥ ነገሩን እንደገና እንዲያስቡበት የሚመክር ደብዳቤ ለምኒልክ ጣፉላቸው ። ምኒልክም ደብዳቤዎቹን ሁሉ አጣርተው ከመረመሩ በኋላ አሁንም እንደገና ቃሉ አንድ ዓይነት የሆነውን አድራሻውንና ማዕረጉን ብቻ እየለዋወጡ ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያና ለጀርመን ንጉሠ ነገሥት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ላኩ ።



ሞዓ፡ አንበሳ፡ ዘእምነገደ፡ ይሁዳ፡ ዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ ሥዩመ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ።

ይድረስ፡ ወደ፡ ክቡሩ፡ ወደ፡ ታላቁ፡ ዊልሄልም፡ ፪ተኛ፡ የነምሳ፡ ንጉሠ፡ ነገ
ሥት፡፡ ሰላም፡ ለርስዎ፡ ይሁን፡፡ በሰኔ፡ በ፲፯ቀን፡ በ፲፰፻፺፯፡ የተጻፈ፡
ክቡር፡ ደብዳቤዎ፡ ደረሰልኝ፡ ሰለኛ፡ ነገር፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ያሰቡትን፡
መልካም፡ ሐሳብዎን፡ ባደረጉት፡ ደስ፡ ብሎ፡ የል፡ ለኛ፡ ላገራችን፡ አስበው
መልካም፡ የፍቅር፡ ምላሽ፡ ለአሳዩን፡ እግዚአብሔር፡ ያመስግንዎ፡
ለንጉሠ፡ ነገሥት፡ ይወደዱ፡ በአዶሚራል፡ ዝደ፡ ባ፲፰፻፺፬ ልውጤ ሊ ላይ
የተደረገውን፡ ውል፡ ማፍረሳችን፡ በዚህ፡ ውል፡ ያለውን፡ ፲፯ተኛውን፡
ክፍል፡ ሳንመለከት፡ ያደረግነው፡ አለመሆኑን፡ እንደነበረ፡ በዚህ፡ የተ
ነሳ፡ የክቡር፡ ንጉሥ፡ ዑምቤርቶ፡ ምላሽ፡ በመንግሥት፡ እንደተቀበሉ፡ ቃ
ሉ፡ እስከ፡ ብለው፡ የክቡሩ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ አማክሮኝ፡ እሱንም፡ ለለ
ክፍል፡ መለወጥን፡ ተቀን፡ ጭራሽ፡ ያፈረሰንበትን፡ ምክንያት፡ እን
ቆርሳዩም፡ ይቆተዲልን፡ ይህን፡ ውል፡ በመዋዋሌ፡ ስንዋዋል፡
ከኢጣሊያ፡ መንግሥት፡ ጋራ፡ ብዙ፡ ቀን፡ የሆነውን፡ ፍትሬ፡ ተገን፡
እንመነከራል፡ ለሕዝባችን፡ ለኢጣሊያ፡ ሕዝብ፡ ጥቅም፡ እንደ
ቀረበ፡ ብለን፡ ማውረዳችንን፡ የክቡሩ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ያውቃሉ፡፡
ይህ፡ ውል፡ ከተቀመጠ፡ ከጥቂት፡ ቀን፡ በኋላ፡ በዚህ፡ ውል፡ ውስጥ፡ ያለ
ው፡ ፲፯ተኛው፡ ክፍል፡ በኛ፡ ቋንቋ፡ የተጻፈው፡ ተለወጠ፡ ኢትዮ
ጵያ፡ መቸም፡ መቼም፡ ጥግነት፡ ያልፈለሳትውን፡ በኢጣሊያ፡ ቋ
ንቋ፡ ተለውጦ፡ ተጽፎ፡ አገኘነው፡ እኛም፡ ሬጥየ፡ ይህን፡ ነገር፡ መ
ሳሳቱን፡ ለኢጣሊያ፡ መንግሥት፡ አስታወቅን፡፡ ጣምርኛና፡ በኢ
ጣሊያ፡ ቋንቋ፡ ተከክል፡ ሆኖ፡ ተገልብጦ፡ ሲያበቃ፡ የታመነ፡ ም
ስክር፡ ይሆናል፡ ተብሎ፡ ባለዘኛው፡ ክፍል፡ እንደተጻፈ፡ ፲፯ተኛ
ው፡ ክፍል፡ በኢጣሊያ፡ ቋንቋ፡ ተለወጦ፡ የተጻፈው፡ እንደሩቱልን፡

እጅግ፡ በብርቱ፡ ይከመጋበት፡፡ ሆኖም፡ እኛ፡ ብንገበረት፡ የኢጣሊያ፡
መንግሥት፡ እውነተኛውን፡ የሚገባንን፡ ጩኸታችንን፡ አልሰማ
ም፡ አሉን፡፡ ይኸው፡ ፳፫፡ በዚህ፡ ውል፡ ሁለታችን፡ ተስማምተን፡ በ
ኢትዮጵያና፡ በኢጣሊያ፡ መንግሥት፡ መካከል፡ ያለውን፡ ድምበር፡
ወሰንን፡ ነበር፡፡ ነገር፡ ግን፡ ሆኖም፡ ብንጠብቅ፡ ውሉም፡ ብፕሮግራ፡
የኢጣሊያ፡ መንግሥት፡ ወታደሮች፡ ድምበሩን፡ አልፈው፡ እያሉ
አገር፡ ያዙ፡፡ አገሩ፡ የውሮፓ፡ ሌጋቱ፡ በነገሥታቱ፡ ሁሉ፡ መካከል፡
ያለውን፡ ሕግ፡ አፍርሰው፡ ድምበር፡ እንጂ፡ ከሰል፡ የሌ ክሶውን፡
መልክተኞችን፡ አስረው፡ አዋረዱት፡፡ ይህ፡ ብቻ፡ ውሉን፡ ለማፍ
ረስ፡ ይበቃ፡ ነበር፡፡ ነገር፡ ግን፡ እኛ፡ ተእግሥት፡ ይሻላል፡ ብለን፡
ቻልን፡ ደግሞ፡ ፲፫፡ በዚህ፡ ውል፡ ያለውን፡ ክፍል፡ ሁሉ፡ ቀተው፡
ምጥቀም፡ እስመልክቶ፡ ላይ፡ አለፍርዱ፡ ያለ ቀቀ፡ ዜጎች፡ የውሮ
ፓ፡ ሁሉ፡ ያውቃል፡፡ ከዚህም፡ ሌላ፡ በዚህ፡ ደብዳቤ፡ ያልተጻፈ፡ በዚ
ህ፡ ውል፡ ውስጥ፡ ያለ፡ ብዙ፡ ክፍል፡ ፈርሶብናል፡፡ ፬ኛም፡ የኢጣ
ሊያ፡ ደጃዝማቾች፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ሳይማከሩ፡ ሳያስታውቁኝም፡ በ
ሰሜን፡ በኩል፡ ካሉት፡ ሹማምቶቼ፡ ጋራ፡ ለመዋዋል፡ ሞከሩ፡፡
ስለዚህ፡ ሁሉ፡ ምክንያት፡ ይህም፡ ውል፡ ሁለቱን፡ ሕዝብ፡ ማፋ
ቀሩ፡ ቀርቶ፡ ዘወትር፡ የጠብ፡ ምክንያት፡ መሆኑን፡ ብናይ፡ ደግሞ፡
የኢጣሊያ፡ መንግሥት፡ በመጠንቀቅ፡ ይህን፡ ውል፡ ያዙ፡ እያሉ፡ እ
ኛን፡ ያስቸግራሉ፡፡ እነዚያ፡ ግን፡ እንዲን፡ ተጠንቀቀው፡ ውሉን፡ ይ
ጸዱቁና፡ ውል፡ ያለን፡ አስሰመሰሉትም፡፡ ይህን፡ ሁሉ፡ ብናይ፡ ው
ሉን፡ ለማፍረስ፡ ጨክነንበት፡፡ ለነገሥታቱም፡ ሁሉ፡ አስታወቅን፡፡
ከየውሮፓም፡ ፍርድ፡ እንደናገኝ፡ ግን፡ ተስፋ፡ አለን፡፡ ለዚህም፡
ነገር፡ የከበረ፡ ጌታ፡ ነገሥታትን፡ እየምነዎታለን፡፡ ከኢጣሊያ
ም፡ መንግሥት፡ ጋራ፡ ከፍቅር፡ በቀር፡ ጦርነት፡ አለመፈለጋችንን፡
በርግጥ፡ እንነግረዎታለን፡ ይመኑን፡፡ ነገር፡ ግን፡ ነፃነታችንን፡ ለመጠበ
ቅ፡ መከላከላችን፡ ይህንም፡ ነፃነት፡ ለመጠበቅ፡ ከብዙ፡ ዘመን፡ ጀ
ምሮ፡ እግዚአብሔር፡ እንደረዳን፡ እኛም፡ ከነገሥታት፡ ወዳጅ፡ እን
ደረደን፡ እንጠረጥርምም፡፡ የኢውሮፓ፡ ነገሥታት፡ ሁሉ፡ ካፍሪቃ፡
መሬት፡ መልካም፡ ሥራትና፡ ብልሃት፡ እንዲገባ፡ መፈለጋቸውን፡
እናውቃለን፡፡ እኛም፡ ይህን፡ መልካም፡ ሥራ፡ ለማቆየት፡ ባገራችን፡ የ
መጡቀን፡ የጃንጣሬ፡ መንገደኞች፡ በሚገባ፡ ሸኘን፡፡ የየውሮፓ፡ ነ
ጋዴዎችም፡ አለሥጋት፡ እንደነጋዴ፡ መንገድን፡ አቀናን፡፡ በብዙ፡ ያረ
ሙኒ፡ አገር፡ የክርስቲያን፡ ሃይማኖት፡ እየሰፋለን፡ ብለን፡ የወታደር
ፎቻችን፡ ደግሞ፡ እራሳሰጋበቅ፡፡ ከየውሮፓ፡ ነገሥታት፡ ጋራ፡ ተዋውለ

ን፡ ፱ምንወዳቶን፡ ካይማምት፡ ጠላት፡ ደርቡሽን፡ ለማጥፋት፡ ተስፋ፡ አድርገን፡ ነበር፡፡ በመንግሥታችን፡ ሁሉ፡ ብዙ፡ ዘመን፡ የኖረ፡ ልማድ፡ ተተን፡ የባሪያን፡ ንግድ፡ እስከልከለናል፡፡ ይህ፡ ሁሉ፡ ማድረጋችን፡ የውሮፓ፡ ካፍሪቃ፡ ያሰቦችውን፡ መልካም፡ ፍቃድ፡ ለመስፈጸም፡ ብለን፡ ነው፡፡ እንግሊችንም፡ የመልካም፡ ሥራት፡ የተርፍ፡ ጥቅም፡ እንዲያገኝልን፡ ነው፡፡ እስከዛሬ፡ ድረስ፡ የውሮፓን፡ እምነት፡ ወዳጅ፡ አድርገን፡ የኖርነውን፡ ከእንግዲሀ፡ ወዲህ፡ የነፃነታችንንና፡ የእፉቶችን፡ በየውሮፓ፡ ጠላት፡ አናገኝበትም፡፡ እንዲሀ ካለው፡ አሳብ፡ እግዚአብሔር፡ ያውጣንና፡ ላገርዎ፡ ደኅንነትዎ፡ ለንጉሠ፡ ነገሥት፡ ጤና፡ የምልመነውን፡ ደሉት፡ እግዚአብሔር፡ እንዲሰማኝ፡ ተስፋ፡ አድርጌ አለሁ፡፡

በ[illegible] ቀን፡፡ ባዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ ተጻፈ፡፡
፲፰፻፹፫ ዓመተ፡ ምሕረት፡፡

ምኒልክ ከየነገሥታቱ የሚደርሷቸው ደብዳቤዎች ሁሉ ለኢጣሊያ መንግሥት የሚያግዙና ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ሥር ትተዳደር እያሉ የሚመክሩዋቸው በመሆናቸው ተበሳጩ ። ኤሮፓም ባንድነት ተባብሮ ኢትዮጵያን ለመውጋት እንደሚነሳ ገባቸው ። በዚህ ምክንያት “. . . . በአገሬ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ኢጣሊያኖች ሁሉ እየወጡ ካገሬ ይሂዱ ። . . . .” ብለው ለየመኳንንቶቻቸው ሁሉ አሳወቁ ። ለኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም “. . . .ወደፊት ማንኛውም የኢጣሊያ ሰው ወደአገሬ እንዳይመጣብኝ ይሁን. . . .” ብለው በደብዳቤ ገለፁ ።

የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳግማዊ አጤ ምኒልክ ደብዳቤ እንደደረሰው ነገሩ በሙሉ መበለሻሸቱ ስለገባው ስለዚህ ስለውጫሌ ውል እንዲነጋገር ዶክተር ትራቨርሲን ሁለት ሚሊዮን ጥይት ገፀ በረከት አስይዞ እንደገና ወደ ኢትዮጵያ ላከው ። አጤ ምኒልክም ከዶክተር ትራቨርሲ ጋር በተገናኙ ጊዜ “. . . . እኔ በማናቸውም ቢሆን ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር የጀመርሁትን ወዳጅነት ለመተው አሳብ አልነበረኝም ። እናንተ ግን አሳባችሁ ሁሉ ለጠብ እንጂ ለፍቅር አለመሆኑን ሥራችሁ ይመሰክራል ።

"የሠራችሁትም አድራጐት መጀመሪያ ስለወሰን ነገር በውጫሌ ውል በ3ኛው ክፍል የተጻፈውን ከኮንት አንቶኔሊ ጋር ተስማምተን ካደስነው በኋላ የታደሰውን ውል አፍርሳችሁ እስከ መረብና እስከ ሙና እስከ በለሳም መጥታችሁ ሰንደቅ ዓላማችሁን አቆማችሁ ።

"ሁለተኛም ፤ በዚያው በውጫሌ ውል በ17ኛው ክፍል የተጻፈውን እንለውጣለን ካላችሁ በኋላ ምክንያት እያበዛችሁ ነገ ከነገ ወዲያ እያላችሁ እስካሁን አቆያችሁት ።

"ሶስተኛም ፤ ከሁሉ የሚብስና የሚከፋ ነገር ጄኔራል ጋንዶልፊ እኔን ለማሳዘን ሲል ወደ መረብ ወጥቶ እኔ ሳልሰማ ከራስ መንገሻ ጋር የወዳጅነት ውል ተዋዋለ ። ይህም የጠላትነት እንጂ የወዳጅነት ሥራ አለመሆኑ የታወቀ ነው ። . . . . "በማለት ነገሩት ። በመጨረሻውም" . . . . ከኢጣሊያ አገር ድረስ ያመጣሽውን ጥይት አልቀበልም ብዬ ብመልሰው ግርማዊ የኢጣሊያ ንጉሥ ወዳጅነታቸውን የጠላሁ መስሏቸው እንዳያዝኑብኝ ስል ተቀብያለሁ ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ" ብለው አሰናበቱት ።

በዚህ መሀል በ1887 ዓ.ም. በጄኔራል አሬሮ የሚመራው የኢጣሊያ ጦር አድዋ ገብቶ አገሩን ያዘ ። አዲግራትና መቀሌም መጋቢት 16 ቀን ተያዙ ። እስከ አክሱም ዘልቆም ለሕዝቡ ልብስና ማባበያ በመስጠት "ከምኒልክ አገዛዝ ነፃ ላወጣችሁ ነው" እያለ ይሰብክ ጀመር ። አጤ ምኒልክም ይህን ነገር ወደ ኢጣሊያው ንጉሥ ቢያስታውቁ ነገሩ የተፈፀመው በስህተት ነው የሚል የውሸት መልስ አገኙ ። በስህተትም ቢሆን አገር መያዝ እንደማይገባ የሚገልጽ ለሁለተኛ ጊዜ ለዋናው ጦር አዛዥ ለጄኔራል ባራቴየሪ ደብዳቤ ፃፉ ።

## ይድረስ ከጄኔራል ባራቲየሪ

በ፲፰፻፹፯ የተፃፈ ደብዳቤ ደረሰልኝ ። እኔም በጥር በ፳ ቀን በ፲፰፻፹፯ የላኩልህ ደብዳቤ ደርሶህ ይሆናል ብዬ ተስፋ አለኝ ።በዚህ ደብዳቤ እንዳየኸው ራስ መንገሻና እናንተ መዋጋታችሁ በመሳሳት እንደሆነ እወቀው ። እኔ ከጐረቤቶቼ ጋር በፍቅርና በሰላም መኖር እንድፈልግ በጣም ታውቃለህ ። ነገር ግን አንተ በመዠመሪያ ተቀድመህ ወተህ ከሰው ከተማ መግባትህ ጥቃት አይሆንምን ። ራስ መንገሻ አጥፍቶ ተገኝቶ እንደሆነ ወደኔ መላክ ነበር እንጂ ጦር ይዘህ አድዋ ድረስ መምጣት አይገባም ነበር ። አሁንም በትግሬ መሬት ላሉት ለኔ ሹማምንቶች ለራስ መንገሻ እንዲህ ያለ ጦርነት ሁለተኛ እንዳያነሱ ልኬ

አለሁ ። ለንጉሥ ኡምቤርቶም ምጥዋ ያሉትን ሹማምንቶችዎን ይቆጡልኝ ብዬ ልኬባቸዋለሁ ። አሁንም ይህን በመሳሳት የተደረገውን ጠብ በሥራት ለማስማማት አይቸግረንም ብዬ ተስፋ አለኝ ።

በመጋቢት በ፭ ቀን ፲፰፻፹፮ ዓ.ም አዲስ አበባ ተፃፈ ።

የምኒልክ ወዳጅና ረዳት የነበሩት የሩሲያው ንጉሠ ነገሥት ሞተው ስለነበረም ምኒልክ በኃዘን ላይ ኃዘን ተጨመረባቸው ። ወዲያውኑም ከአዲሱ የሩሲያ ንጉሠ ነገሥት የተላኩ መልክተኞች ወደ ኢትዮጵያ መጡ ። መልክተኞቹ ከአዲሱ ንጉሠ ነገሥት የተላኩትን መልክት አድርሰው ወደ አገራቸው በሚመለሱበት ጊዜ ዳግማዊ ምኒልክ ለአዲሱ ለሩሲያ ንጉሠ ነገሥት የደረሰባቸውን በደል የሚዘረዝር ደብዳቤ ጥፈው ስጦታም ጨምረው በፊታውራሪ ዳምጠው የሚመራ ቀኛዝማች ገነሜ ፣ መምህር ገብረ እግዚአብሔርና ሌሎችም ሰዎች ያሉበት የመልክተኞች ቡድን ወደ ሞስኮ ላኩ ። ምኒልክ ለአዲሱ የሩሲያ ንጉሠ ነገሥት የጻፉት ደብዳቤ የሚከተለው ነው ።

ይድረስ ፣ ወደከበሩ ፣ ወደታፈሩ ፣ ከፍ ያሉ ቄሳር የመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ኒኮላዎስ ።

ሰላም ለርሶ ይሁን ። የመስኮብ መንግሥትና የኢትዮጵያ መንግሥት በሃይማኖት ፣ በፍቅር ተስማምቶ የኖረ መንግሥት ስለሆነ ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ መንግሥትና በኢጣሊያ መንግሥት የተደረገውን ውል መፍረሱን ለከበሩ ላረፉት አባትዎ ልኬ ነበር ። መላኬም የርስዎ መንግሥት የክርስቲያን ነፃነት እንዲወድ ባውቅ ፣ የኢትዮጵያን መንግሥት ከጥንት የነበረ ፣ ራሱን የቻለ ፣ ባለነፃ መንግሥት መሆኑን ያውቃሉና ከኤሮፓ ነገሥታት ጋራ በፍቅር መኖር እንጂ የማንም ጥግነት አልፈልግም ስል ላክሁ ። እኔ እስካሁን ድረስ በመልካም ሥራትና በመልካም ሃይማኖት እንደሚኖሩ የክርስቲያን ነገሥታት አገሬን እየጠበቅሁ አረመኔውን እያቀናሁ በሰላም በፍቅር ከኤሮፓ ነገሥታት ጋር ልኑር ብል የኢጣሊያ መንግሥት እኔ ስዘምት እያሰለሉ በኋላዬ ብዙ ግፍ ይሠሩብኝ ጀመር ። ይህ የተደረገውን ግፍ ለወዳጄ ለፈረንሲስ መንግሥት እንዳስታወቅሁ ለርሶም ለወዳጄ ማስታወቅ ይገባል ብዬ ላኩብዎ ።

በግዛቴ በደቡብ በኩል ጉዳይ አግኝቶኝ ስዘምት አስቀድሞ የትግሬ ገዥ ራስ መንገሻ ከኢጣሊያ ጦር ጋር ወደ ደርቡሽ ልዝመት ይፍቀዱልኝ ብሎ ቢልክብኝ ክርስቲያን ለመርዳት ከሆነ ብዬ እሺ አልኩት ። የኢጣሊያ ሹማምንት እንደሚሠሩብኝ ተንኮል ቢሆንፈቃድ

መስጠት አይገባኝም ነበር ። እነዚያ ግን ከከተማ መራቴን ፥ መዝመቴን በሰሙ ጊዜ ጦር አስከትተው አድዋን ትልቁን ከተማ ዘረፉት ። ስለ ዚህ የክርስቲያን ደም አለውል ፈሰሰ ። ፊትም አለውል በተያዘው አገሬ ለኤርፖ ነገሥታት እያሰማሁ መኖሬን ሰምተውታል ። ይህ የተ ደረገ ግፍ በክርስቲያኖች ፥ በብልሃተኞች ሕዝብ መካከል የሚደረግ አይደለም ።

የራስ መንገሻ ሠራዊት ግን ይህን ግፍ ባየ ጊዜ ያለመጠን ተቆ ጭቶ የማይታገድ ቢሆን ከኢጣሊያኖች ጦር ጋራ ተዋጉ ። ይህ ጦር ነት እርግጥ መሆኑን ማወቄ ከዘመቻ ተመልሼ ከተማዬ ስገባ ከጄ ኔራል ባራቲየሪ የተላከ ደብዳቤ ቢደርስልኝ ነው ። በዚህ ደብዳቤ ጀኔራል ባራቴሪ ይህ ነገር ካለመስማማትና ከመሳሳት የተነሣ ነገር ነው እንጂ ኢጣሊያንና ኢትዮጵያን በጭርስ የሚያጣላ ነገር የለበ ትም እያለ ያመካኛል ። እኔ ግን እርቅና ሰላም ስለወደድሁ ይህን የም ክንያት ቃል በትእግስት እንደ እውነት ተቀበልኩ ። ዳሩ ግን ያገሬን አንድነትና ነፃነት ለመጉዳት ዘወትር የኢጣሊያ መንግሥት ሹሞች የሚሠሩትን የተንኮል ሥራ መርሳት አልችልም ። ይህን ሁሉ ለርስዎ ማሳየቴ ቅንነትዎንና ወዳጅነታችንን አይቼ የክርስቲያን ደም አለ ውል ፈሷልና በቅንነትዎ ይመልከቱት ።

እነዚህ ሰዎች በያለበት የሚሠሩብኝ የተንኮል ሥራ ከልክ አልፎ ድንገት ከጦርነት ያደረሰኝ እንደሆነ ፥ የኤርፓ ነገሥታት ሁሉ ይልቁንም ወዳጆቼ ሁሉ መዋጋቴ ስለ አባቶቼ ርስትና ስለመንግሥቴ ነፃነት መሆኑን እወቁት ። ዳሩ ግን እኔም ከዚህ የምደርሰው የእርቅን ነገር ሁሉ ፈትኜ ሳበቃ ነው ። እናንተም ስለ ክርስቲያን እርቅና ሥራት ፥ ስለወዳጅነትም ፍቅር አግዙኝ ። ፍርዳችሁን እንጠብቃለን ።

በመጋቢት በ፳ ቀን በ፲፰፻፹፯ ዓ. ም. አዲስ አበባ ተፃፈ ።

ኢጣሊያኖች አድዋንና አክሱምን እንደያዙ ወዲያው እየገፉ አጋ ሜንና እንደርታን አምባላጌን ሁሉ ያዙ ። ምንም እንኳ በአገሪቱ ላይ አምስት ዓመት የቆየ ከባድ ረሃብ የደረሰ ቢሆንም ያንኑ ረሃብተኛ ሕዝብ ለማዝመት ምኒልክ ቀጥሎ ያለውን የክተት አዋጅ አወጁ ።

"እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስ ፍቶ አኖረኝ ። እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ ። እንግ ዲህ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና ስለኔ ሞት አላዝንም ። ደግሞ እግዘ አብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም ። እንግዲህም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራ ጠርም ።



አንቶኔሊ



ጂያኮሞ



ሳሊምቤኒ



Nel disegno che riproduciamo, la scena della rottura diplomatica tra il conte Antonelli e Menelik, così come la narra il cronista etiopico Afework. In realtà la vicenda fu un poco diversa. (Dis. di W. Molino)

የውጫሌ ውል ማኘኘያው ሲቀደድ

"አሁንም አገር የሚያጠፋ ፥ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት ፥ እግዚአብሔር የወሰነልንን የባህር በር አልፎ መጥቷልና እኔም ያገሬን ከብት ማለቅ ፥ የሰዉን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር ።

"አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም ። ያገሬ ሰው ፤ ካሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም ። አንተም እስካሁን አላስቀየምኸኝም ። ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ ። ጉልበት የሌለህ ለልጅህ ፥ ለምሽትህ ፥ ለሃይማኖትህ ስትል በሀዘን እርዳኝ ። ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ ። አልተውህም ። ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም ። ዘመቻዩ በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረይሉ ከተህ ላገኝህ"

በአዋጁ ላይ እንደምንመለከተው አጤ ምኒልክ ላገራቸው ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት ሲሉ በጦር ሜዳ ለመሞትም ቢሆን ቁርጠኛ መሆናቸውን ያስረዳል ። ሌላው ነገር ደግሞ የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን በባህር የተከለለ እንደሆነም ይናገራል ።

## የአድዋ ጦርነት

" ....በጥጋባቸው አድዋ ላይ ተዋግተው ድል ሆኑ ። እኔ ግን በድንቁርናቸው ብዛት የእነዚያን ሁሉ ክርስቲያን ደም በከንቱ መፍሰሱን እያየሁ ድል አረግኋቸው ብዬ ደስ አይለኝም. . . . " ምኒልክ ለሙሴ ሽፍኔ መጋቢት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. ከፃፉት ደብዳቤ ።

" ....ሃያ ሺህ ያህል ወታደሮች ያሉበት የኤሮፓ ጦር በአፍሪካ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ተሸነፈ ። በኔ እምነት መሠረት በዘመናችን ታሪክ ውስጥ እንደ አድዋው ያለ ጦርነት የለም ። በእልቂቱ በኩል 25.000 ሰዎች በአንድ ቀን ጀምበር የሞቱበትና የቆሰሉበት ነው ። ፖለቲካና ታሪክ አበቃ ። በአፍሪካ ውስጥ ታላቅ የተወላጆች ኃይል መነሳቱ ታወቀ ። የአፍሪካ ተወላጆች ታሪክ ተለወጠ ። ጥቁሩ ዓለም በኤሮፓውያን ላይ ሲያምፅና ሲያሸንፍ የመጀመሪያው መሆኑ ነው ። አበሾች አደገኛ ሕዝቦች መሆናቸው ከአራት ዘፍጥረት ጀምሮ ተጽፎላቸዋል ። የኛ ዓለም ገና ቶር እና ኦዲዮን በሚባሉ አማልክት ሲያመልክ በነበረበት ጊዜ አበሾች የክርስትናን ሃይማኖት የተቀበሉ ናቸው ።. . . . አሁን የሁሉንም ፍላጐት አድዋ ዘጋው. . . " ቤርክሌይ ።

ወደ አድዋ የዘመተው የኢትዮጵያ ጦር ብዛቱ በትክክል አይታወቅም ። ብዙ ታሪክ ፀሐፊዎችም የፃፉት የተለያየ ቁጥር ነው ። ቶኪ የተባለው ፀሐፊ የኢትዮጵያ ወታደር ከ70.000 እስከ 80.000 ይደርሳል ይልና ከነዚህ ውስጥ ጠመንጃ ያላቸው 25.000 ሰዎች ናቸው ብሏል ። አንቶኔሊ ደግሞ ከ110.000 እስከ 120.000 ነው ሲል ባራቲየሪ እንደፃፈው ደግሞ ከ75.000 እስከ 80.000 ይደርሳል ብሏል ። ኢልግ 150.000 ነው ሲል ቄልቤ ደግሞ በምኒልክ ጥሪ የተሰበሰበው 200.000 ሰው ነው ይልና "ይህ ሠራዊት በሙሉ ከጦርነቱ ቦታ አልደረሰም ። ሠራዊቱ በከፊል ገና በጉዞ ላይ እንዳለ ጦርነቱ አለቀ" ይላል ። ዌልዴ የተባለው ፀሐፊ ደግሞ 120.000 ኢትዮጵያውያን በጦርነቱ ተካፍለዋል ሲል የምኒልክ መድፍ አስተኳሽ የነበረው ፈረንሣዊው ካፒቴን ክሎቼቱ 150.000 እንሆናለን ሲል ጽፏል ።

የኢትዮጵያ ወታደሮች አሰልጣኝ የነበረው ሊዮንቴፍ 107.000 ወታደሮች ነበሩ ይላል ። በርከት ያሉ ፀሀፊዎች የተስማሙበት የዘማቹ ዝርዝር ግን የሚከተለው ነው ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አጤ ምኒልክ | 30.000 | እግረኛ | 12.000 | ፈረሰኛ |
| እቴጌ ጣይቱ | 3.000 | " | 6.000 | " |
| ራስ መኰንን | 15 000 | " | | |
| ራስ መንገሻ ዮሐንስ | 12.000 | " | | |
| ራስ ሚካኤል | 6.000 | " | 10.000 | ፈረሰኛ |
| ራስ አሉላ | 3.000 | " | | |
| ራስ መንገሻ አቲከም | 6.000 | " | | |
| ራስ ወሌ | 10.000 | " | | |
| ራስ ወልደ ጊዮርጊስ | 8.000 | " | | |
| አዛዥ ወልደ ጣዲቅ | 3.000 | " | | |
| ደጃች ተሰማ ናደው | 4.000 | " | | |

ራስ ዳርጌ ፣ ግራዝማች በንቲና ቀኛዝማች መኰንን 20.000 እግረኛ ወታደሮች አሰልፈው ነበር ።

በኢጣሊያ በኩል የቅኝ ግዛት ወታደር ሳይጨምር 17.000 ኢጣሊያውያን ከ56 መድፎች ጋር ተሰልፈው ነበር ። በኢጣሊያ በኩል የተሰለፈው ወታደር እጅግ ዘመናዊ የሆነና የሰለጠነ ወታደር ነበር ። የኢትዮጵያኑን ቁጥር ያበዛው ግን የተከታዩ ጀሌ ጦር ብዛት ነው ። ይህንንም ካፒቴን ሞልቴዶ የተባለ የዘመኑ የኢጣሊያ ጋዜጠኛና መድፈኛ ከፃፈው ለመረዳት እንችላለን ። የጋዜጠኛው መድፈኛ እንዲህ



ለአድዋ ዘመቻ ሠራዊቱ ከአዲስ አበባ ተነሳ ።



ምኒልክ ለአድዋ ዘመቻ ጉዞ ጀመሩ ።

ይላል “. . . .ከፓውሴቲ ጋር ተገናኝተን እንዳጫወተኝ የአበሾች ጦር ፣ ወረራ እንጂ ጦርነት አልነበረም ። ሕዝቡ ከሁሉም ብሔረሰብ ተውጣጥቶ ቀርቧል ። የሚዋጋው ደግሞ ፈረሱ ፣ በቅሎው ፣ አህያው ሁሉ ባንድነት ከሰዎቹ ጋር ተደባልቆ በመሆኑ ግራ ገብቶን ነበር ። ጦርነቱን ከወታደሮች ጋር ብቻ አልገጠምንም ። በጦርነቱ ውስጥ ሴቶች ፣ ሽማግሌዎች ፣ ሕፃናት ፣ ቄሶችና ቆማጦችም ሳይቀሩ ወጉን ብሎኛል ።. . . .” ሲል ጽፏል ።

በአድዋው ጦርነት ጊዜ በምኒልክ በኩል የነበሩት መድፎች ብዛት 42 ሲሆን እነዚህም የኢጣሊያን ዘመናዊ የተራራ መድፍ የማይወዳደሩ ነበሩ ።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ጥቅምት 2 ቀን 1888 ዓ. ም. ሠራዊታቸ ውን አስከትለው ወደ ትግራይ ለመዝመት ከአዲስ አበባ ጉዞ ጀመሩ ። ጉዞው እንዴት ነበር? ፓውሴቲ እንዲህ ይላል ። “. . . .ሲጓዙ በደንብ ተመልክቻለሁ ። ዳገቱን ሲወጡ ፣ ቁልቁለቱን ሲወርዱ ፣ ሸለቆውን ሞልተው ሲሄዱ እየተጯጯሁ ነው ። ለውጊያ የሚሄዱ አይመስሉም። ሴቶች ፣ ሽማግሌዎች ፣ አንካሶች ፣ ሕፃናት ፣ ቄሶች ፣ ቆማጣዎች ሁሉ ሳይቀሩ አብረው ባንድነት ይጓዛሉ ። እኔ እንዳሰብኩት ለጦርነት የሚ ሄዱ የጦር ወታደሮች አይመስሉም ። ሕዝቡ በሙሉ ተነቅሎ ለወረራ የሚሔድ ይመስላል ።. . . .” ብሏል ።

ሞልቴዶ ደግሞ“. . . .አህያው ፣ በቅሎው ፣ ፈረሱ ፣ ሰዉ ሁሉ ባንድነት ይጓዛል ። መንገዱ ሲጠብ. . . .መንገድ ይሠራሉ ። ባንድ ጊዜ በግራ ወይም በቀኝ ይሠማሩና የጠበበውን መንገድ ይሠራሉ ። ሠራ ዊቱ ባለፈበት መንገድ እርጥብ የሣር ዘር እንኳ አይገኝም ። ምክ ንያቱም በመቶ ሺ የሚቆጠር እግር ረጋግጦ ስለሚያጠፋው ነው ። ዳገት ላይ ሲደርሱ በመጠኑ እርምጃቸውን ቀንሰው ይጓዛሉ ። ጉዞው እርምጃውን በሚቀንስበት ጊዜ አንዳንድ ጐበዝ ከመሀል ብቅ ይልና ፈጥኖ ይራመዳል ። በዚህ ጊዜ ሁሉም ያን ጐበዝ ተከትለው እርምጃ ቸውን ያፋጥናሉ ።ያን ጊዜ ወደኋላ የሚቀሩ አህያና በቅሎ ነጂዎች ናቸው ።. . . .የአህያና የበቅሎውን አካሄድ ወደኋላ የሚያስቀረው የየተ ራራው ግራ ቀኝ ድንጋይ ነው ። ጉዞአቸው ከየተራራው ድንጋይ ጋር ግራና ቀኝ እየተጋጩ በመሆኑ ነው ።

“. . . .የንጉሡ ሠራዊት መንገድ ሰሪ ክፍል አለው ። መንገድ ሰሪ ዎቹ ሲሰሩ አይቻለሁ ። መንገድ ሠሪዎች በሺህ የሚቆጠሩ ናቸው ። መንገድ ሲሰሩ በጐራዴያቸው የዛፉን ቅርንጫፍ ይቆርጣሉ ። ግማሹ በቆንጨራ ቁጥቋጦውን ሁሉ እየቆረጠ ይጥላል ። ግማሹ በማጭድ ሣሩን ያጭዳል ። ግማሹ ድንጋይ እየተሸከመ ያነሳል ። ግማሹ ትንንሿን

ተክል ሁሉ እንዳታደናቅፍ እየነቀለ ይጥላል ። ....አበሾች የሚጓዙት እንደ ደርቡሾች በለሊት ጨረቃ ጠብቀው ሳይሆን ፣ ለሊቱን አርፈው አድረው ቀን ሲሆን ይጓዛሉ ።. . . .” ብሏል ።

ቤርክሌይም ስለጉዞው ጽፏል ። “. . . .በሠራዊቱ መሀል አዝማሪዎችም አብረው ይዘምታሉ ። በዚያ ሁሉ ሁካታ አዝማሪዎቹ ዘማቹን እያጫወቱ ይሄዳሉ ። አብሮአቸው የሚጓዘው ሠራዊትም ለአዝማሪዎቹ ግጥም ይነግሩዋቸዋል ። አዝማሪዎቹም የደከመውን በግጥም እያበረታቱ ይጓዛሉ ። ለምሳሌ ከሚገጥሙት ግጥም የሚከተለውን እንመልከት ። ወንድሜ ራበህ ወይ ? ወንድሜ ጠማህ ወይ

አዎን የናቴ ልጅ እርቦህ ጠምቶሃል ።

ታዲያ የናቴ ልጅ አዳኝ ወፍ አይደለህም ወይ ?

ግፋ ፣ ብረር ፣ ወደፊትህ ሂደህ ጠላትህን አትበላም ወይ ?

ግፋ ወደፊት ከበዓሉ ቦታ ፈጥነህ ድረስ ።

የምታርደውን ሥጋ የማቀራርጥልህ እኔ ነኝ ።

ግፋ የናቴ ልጅ ውሃ ጠምቶሃል ።

ጠጅ ብታጣ ደሜን እንድትጠጣ እሰጠሃለሁ ። ግፋ ። ይላሉ ።. . .” ብሏል ።

የአድዋ ጦርነት ከመጀመሩ በፊት ባራቲየሪ በእረፍት ሰበብ ከኤርትራ ወደ ኢጣሊያ ሄዶ ነበር ። ካሚራ ከሚባል ከተማ ሉልዮ (ሐምሌ) 26 ቀን 1895 ሲገባ ከፍ ያለ አቀባበል ተደረገለት ። የከተማው ሕዝብ በሙሉ ወጥቶ ተቀበለው ። ገና ሳይዋጋ “ታላቁ ድል አድራጊው ጀግና” እያለ ሕዝቡ ጮኸለት ። ባራቲየሪም ለሕዝቡ ንግግር ሲያደርግ “. . . .በቅርብ ቀን ምኒልክን በቀፎ ውስጥ አስሬ ሮማ አመጣዋለሁ. . . .” ብሎ መናገሩን ኤሊትስ እና ሮሲ ጽፈውታል ።

የኢጣሊያ ሹማምንትና ሕዝብ ድል በማድረጉ ተማምኖ በየቦታው በሚፈነጭበት ጊዜ በአዲስ አበባ ምኒልክ የሚሠሩትን ሲሰሩ ፣ ጣይቱ ደግሞ በየአገሩ ያለውን ሸክላ ሰሪ ሁሉ አሰባስበው የእንጀራ መጋገሪያ ምጣድና የወጥ መሥሪያ ድስት ሲያሰሩ መክረማቸውን ከሪስ ጽፋለች ።

አጤ ምኒልክ ኢጣሊያን ለመውጋት ወደ ትግራይ ከመዝመታቸው በፊት አብዛኛው የኢትዮጵያ መኳንንት በኢጣሊያ ሰላዮች ስብከት ተጠምዶ ነበር ። እውግስቶ ሳልምቢኒ ጐጃም ውስጥ ተቀምጦ የንጉሥ ተክለሃይማኖት ረዳትና አማካሪ በመምሰል ፣ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ከኢጣሊያ ጋር ቢያብሩ የኢጣሊያ መንግሥት ባላን

ጣቸውን ምኒልክን ጥሎ እሳቸውን እንደሚያነግሳቸው እየነገረ ልባቸ
ውን ይገነትት ነበር ።

በትግራይ በኩል ጂያኮሞ ናሬቲ እና ሌሎችም በአጤ ዮሐንስ
ጊዜ የዮሐንስ ቤተ መንግሥት ባለሟል የነበሩትና የምኒልክ ባለ
ሟል የነበረው አንቶኔሊ አጤ ዮሐንስንና ንጉሥ ምኒልክን ነገር እየጐ
ነጐኑ ሲያጣሉ እንደነበሩት ሁሉ ባሁኑም ዘመን አጤ ምኒልክ ዙፋ
ኑን የያዙት በግፍ መሆኑን ለራስ መንገሻ በመንገር ራስ መንገሻ
ከኢጣሊያ ጋር ቢተባበሩ በግፍ የተወሰደባቸውን ዘውድ አስመል
ሰው በዮሐንስ ዙፋን ላይ እንደሚያስቀምጧቸው ቃል በመግባት
እስከ ማስከዳት ደርሰው ነበር ።

በሐረርጌ የራስ መኰንን ወዳጅና የኢጣሊያ ሰላይ የነበረው
ፌልተር ራስ መኰንን በኢጣሊያ ጉብኝታቸው ጊዜ በኢጣሊያ አገር
ስላዩት የጦር መሣሪያ ብዛትና ዘመናዊነት እያስረዳ ኢትዮጵያ ከኢ
ጣሊያ ጋር ከመዋጋት ይልቅ የኢጣሊያን ጥያቄ መቀበሉ የሚያዋጣ
መሆኑን እየነገረ በመኰንን ልብ ውስጥ ፍርሐት ለመንዛት ሞክሯል ።

እ.አ.አ. ፌብሩዋሪ 3 ቀን 1895 ዓ.ም. ጀኔራል ባራቴሪ ለኢጣ
ሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በፃፈው ደብዳቤ “ . . . . ራሶች ሁሉ
ተለያይተዋል ።ሁሉም የሚሠራውና የሚያስበው የየግሉን ጉዳይ ብቻ
ነው ። የጐጃሙ ንጉሥ ፣ ለምኒልክ የውስጥ ጠላት ነው ። መንገሻ እሁ
ንም በማንገራገር ላይ ነው ። ራስ ሚካኤል ከኛ ጋር እየተነጋገረ ነው ።
መኰንንም ጦርነቱ እንዳይካሄድ የተቃውሞ ተንኰል እየሠራ ነው ።
ጦርነቱ ሲጀመርም በንጉሡ ላይ ይሸፍታል ። . . . .” በማለት አሳው
ቋል ። ባራቲየሪ ነገሩ እውነት ይምሰለው እንጂ አንድም ከልቡ ምኒ
ልክን ወይም አገሩን የከዳ መኳንንት አልነበረም ። ሁሉንም ነገር መኳ
ንንቱ እየነገሩዋቸው ምኒልክ ሁሉንም ነገር ያውቃሉ ። ዋናው ምክን
ያት ሁሉም የኢጣሊያ ወዳጅ እየመሰለ ምስጢር ለማግኘት ነበር ።

ለኢጣሊያ ሰላዮች ያልተበገሩት ራስ አሉላ ናቸው ። ራስ አሉላ
በዮሐንስም ጊዜ ቢሆን የኢጣሊያን ሰላዮች በራሳቸው ሰላዮች እያስ
ያዙ በማሰርና ካገር በማስወጣትም ይቀጡ ነበር ። እንዲያውም ራስ
አሉላ የኢጣሊያን ሰላዮች ሲያስሩ አጤ ዮሐንስ በትእዛዝ ስለሚፈቷ
ቸው ራስ አሉላ በዮሐንስ አድራጎት ይበሳጩ ነበር ። ራስ አሉላ የሚ
ይዙት ፣ የሚያስሩት በትግራይ ውስጥ ያሉትን ሰላዮች ብቻ ሳይሆን
በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ሁሉ እየለቀሙ ነበር ። አንድ ጊዜ
በጐጃም በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ዘንድ ተወዳጅ የነበረውን የኢጣ
ሊያን ሰላይ ሳሊምቢኔን ራስ አሉላ ይዘው ሲያስሩት አጤ ዮሐንስ
ፍታ ብለው ስላስፈቱዋቸው አሉላ ተበሳጭተው የራሳቸውን ግዛት ብቻ

ወደ መጠበቁ ተመለሱ ። ቤርክሌይ እንደፃፈው በዚህ በአድዋው ጦርነት ዋዜማ ጊዜ እጤ ምኒልክና ራስ አሉላ ሲጫወቱ ራስ አሉላ ለአጤ ምኒልክ ". . . . ጃንሆይ ፣ እነኚህ ኢጣሊያኖች ዓይናቸው ታውሯል ልበል ? እኔንም እኮ አባበሉኝ ። . . . ." ብለው መናገራቸውን ጽፏል ። ይህም ቢባል የኢጣሊያን ማባበል እየተቀበሉ ወደ ኢጣሊያ ለመ ሆን ያሰቡም ፣ የሆኑም ነበሩ ።

የእቴጌ ጣይቱ ወንድም ራስ ወሌና የላስታው ዋግሹም ብሩ ከኢጣሊያ ጋር መነጋገራቸው ተደርሶባቸው ራስ ወሌ የጣይቱ ወን ድም በመሆናቸው ማስረጃ አልተገኘባቸውም በሚል ሲለቀቁ የላስ ታው ዋግሹም ብሩ ታሰሩ ። ኢጣሊያኖች የወሎውን ራስ ሚካኤልን "እንደገና ወደጥንት ሃይማኖትዎ ተመልሰው የእስላም ሃይማኖት ንጉሥ ይሆናሉ" ብለው ስለሰበኳቸው ወደ ኢጣሊያ ሊገቡ በቋፍ ነበሩ ። የአውሳው ባላባት ከኢጣሊያ ጋር ከጐኑ እንደሚሰለፍ ውል ተዋውሎ ስለነበር ምኒልክ ፣ራስ ሚካኤል የአውሳውን ባላባት እንዲ ወጉ ቢያዟቸው አልወጋም ብለው እምቢ አሉ ። በካፒቴን ፔርሲኮ ስብከት ኢትዮጵያን ከድቶ ከኢጣሊያ የተስማማው የአውሳው ባላ ባት ሼክ ጧላ በምኒልክ ጦር ከተደበደበ በኋላ አምልጦ ወደ ኢጣሊ ያኖች ገብቶ አላጌ ላይ 350 ዘመናዊ ጠመንጃ በያዙ ወታደሮቹ የኢት ዮጵያን ሠራዊት ወግቷል ። አንዳንዶቹም ሰዎች የኢጣሊያን ገናናነት ለምኒልክ በመንገርና የኢጣሊያን ዘመናዊ መሣሪያ ለመግጠም ያለመ ቻሉን በሚያስተማምን ማስረጃ እያቀረቡ ኢጣሊያ በሚለው መን ገድ እንታረቅ ይሉ ነበር ።

ይህን በመሳሰለው ግርግር ግራ የተጋቡት አጤ ምኒልክ መኳንን ቱን ሰብስበው ". . . . .አንፍራ ። እኔ እንደሆንሁ መዝመቴን አልተውምና ስለኢጣሊያ ዘመናዊ መሣሪያና ገናናነት አትንገሩኝ ። ኃይል የእግዚ አብሔር ነውና እጋጠማለሁ ። ብትዘምቱም ፣ ብትቀሩም ፊሣዬን ከጦር ሜዳ ፈልጉት ። ጠላትን በኋላ አስቀምጦ መዝመት አይቻልምና በየግ ዛታችሁ ያሉትን ኢጣሊያኖች አባርሩ. . . ." ብለው አዘዙ ። ራስ መኰ ንንም ብዙዎቹን ኢጣሊያኖች ሲያስወጡ ዋና የኢጣሊያ ሰላይ የነበ ረውን ወዳጃቸውን ፌልተርን አስቀሩ ። ይህም ሰው በአምባላጌው ጦርነት ጊዜ በሁለቱ ወገኖች መሐል እየተመላለሰ ለኢጣሊያ ከፍ ያለ ሥራ ሠርቷል ።

የኢጣሊያ ጦር አድዋን ይዞ በሰላም አለቅ በማለቱ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ሠራዊታቸውን አስከትተው ወደ አድዋ ዘመቱ ። አጤ ምኒልክ ወደ አድዋ ለመዝመት ገና በጉዞ ላይ እንዳሉ የአውሳው ባላባት መሐመድ አንፋሪ ከኢጣሊያ ጐን ለመሰለፍ መወሰኑን ሰሙ ።



ንጉሥ ሚካኤል

መሐመድ አንፋሪን ከወገኖቹ ከኢትዮጵያውያን አስከድቶ ወደ ኢጣሊያ ሠራዊትነት ያስገባው የውጫሌን ውል ያጣመመው አንቶኔሊ ነው ። አጤ ምኒልክ ይህንን በሰሙ ጊዜ ወደ ትግሬ ሊዘምቱ የነበሩት ራስ ወልደ ጊዮርጊስና ደጃዝማች ተሰማ ካገራቸው መራቅ የተነሣ ወደ ኋላ ቀርተው ነበርና ወደ አውሳ እንዲዘምቱ እንዲህ ብለው ላኩባቸው ። "ከኔ ጋር ያለው ሠራዊት ብዙ ነው ። ልክና መጠን የለውም ። እግዚአብሔር ካልተለየን በትግሬ በኩል ላለው ጦር ይበቃል ። እናንተም ወደ አውሳ ዝመቱ" ብለው አዘዙዋቸው ። እነዚህም ሁለት መኳንንቶች ከአንኮበር አዛዥ ወልደ ጣዲቅን ጨምረው ወደ አውሳ ዘመቱ

መሐመድ አንፋሪም ድል ሆኖ ሚስትና ልጆቹን ይዞ አመለጠ ። እንዲህ መሳሳዩ አገር ከሃዲ ቢያናድድም እንደ ደጃዝማች ጓንጉል ዘገየ አይነቱ ደግሞ ደስ የሚያሰኝ ታሪክ አለው ። ደጃዝማች ጓንጉል ዘገየ በአጤ ምኒልክ ላይ ሸፍተው ከምኒልክ ጭፍሮች ጋር በጦርነት የተፋታተኑ ሰው ናቸው ። በዚህም በትግራይ ዘመቻ ጊዜ በምኒልክ ላይ እንደ ሸፈቱና በረሃ እንደገቡ ናቸው ። ምኒልክ ኅዳር 24 ቀን መርሳ ላይ ሠፍረው ሳሉ የደጃዝማች ጓንጉል መልክተኛ ከአጤ ምኒልክ ዘንድ መጣ ። መልእክተኛውም "ጃንሆይ ፣ ከእርስዎ ተጣልቼ በረሃ ገብቻለሁ ። አሁን ግን በአገሬ ላይ የውጭ ጠላት ስለመጣባት የርስዎና የኔ ጉዳይ ቀርቶ ይማሩኝና መጥቼ ከእርስዎ ከጌታዬ ጋር ሆኜ ያገሬን ጠላት ልውጋ ብለዋል"ብሎ ተናገረ ። አጤ ምኒልክም ተደስተው "ይምጣ ምሬዋለሁ" ብለው ላኩ ። ደጃዝማች ጓንጉልም መጥተው ካጤ ምኒልክ ጋር ተገናኙ ። ሠራዊቱም መኳንንቱም በእንደ ዚህ ያለ ጊዜ መጥቼ ከጌታዬ ጋር ልሙት በማለታቸው እጅግ ተደነቁ ።

## አምባላጌ

በፊታውራሪ ገበየሁ ተክሌ አበጋዝነት (አዝማችነት) የሚመራው የኢትዮጵያ ሠራዊት አምባላጌ ደረሰ ። ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ ጋር ተጣልተው ለኢጣሊያ ገብተው የነበሩት ራስ ስብሀት 350 ዘመናዊ ጠመንጃ ከኢጣሊያ ተቀብለው ፋላጋ ኮረብታ ላይ እንዲሆኑ የአምባላጌው ጦር አዛዥ ቶዜሊ አዞአቸው መሽገዋል ። በመሀል ፋሊጋ ኮረብታ አጠገብ በካፒቴን ኤሴል የሚመራው ጦር ፣ አላጌ ላይ በመድፈኛ ጦር አዛዥ በካፒቴን ፔርሲኮ የሚመራው የመድፍ ክፍልና ራሱ የጦሩ አዛዥ ቶዜሊ ተሰልፈዋል ። ካፒቴን አንጌራ አራት መድፎች ያሉበትን ጦሩን ይዞ በጉናቸው ሆነዋል ። በስተቀኝ በመቶ

አለቃ ቮልፒቼሊ የሚመራው ጦር ፤ በሱ ጎን ደግሞ ቶጉራ ኮረብታ ላይ ከኢትዮጵያ ከድቶ ለኢጣሊያ የገባው ሼክ ጢላ 350 ዘመናዊ የኢጣሊያ ጦር ይዞ መሽጓል ።

የኢትዮጵያ ጦር አምባ አላጌ እንደደረሰ ራስ መኰንን "....ይሄ ነገር አይሆንም ። እኔ ነገሩን በሰላም ለመጨረስ በያዝኩበት ጊዜ የእ ናንተ ከዚህ መሰለፍ የእርቁን ድርድር ስለሚያበላሽ ወደኋላ ተመ ለሱ ።...." ብለው ኅዳር 26 ቀን ለቶዜሊ ደብዳቤ ላኩለት ። ቶዜ ሊም "....ወደኋላ መመለሱ የማይታሰብ ነው ። እስከ አሸንጌ ሐይቅ ድረስ እገዛለሁ ። ከእናንተ በኩል አንድ ሰው ወደፊት አንድ እርምጃ ቢራመድ ግን ጦርነቱ መከፈቱን ይወቁት ...." ብሎ መለሰላቸው ።

ኅዳር 28 ቀን 1888 ዓ.ም. ከንጋቱ 12 ሰዓት ተኩል ሲሆን በኢጣሊያኖች ሠፈር "ጠላት ተንቀሳቀሰ" የሚል ድምፅ ተሰማ ። ቴኔንቲ (መቶ አለቃ) ማዜይ የሚያዘው ጦር ተኩስ ከፈተ ። የኢትዮ ጵያም ጦር በስተግራ ቡታ በሚባለው ኮረብታ በኩል ወደፊት ተጠጋ ። በቡታ ኮረብታ በኩል የተጠጋውን በራስ ወሌ የሚመራውን የኢትዮጵያን ጦር ፤በራስ ስብሀትና በደጃች አሊ የሚመራው የኢጣ ሊያ ጦር አላራምድ አለው ። በሌላም በኩል በኢሴል እና በካኖቬቲ የሚመራው የኢጣሊያ ጦር በኃይል ይዋጋ ጀመር ። የኢጣሊያ ጦር በመሸገው ምሽግ ውስጥ ሆኖ የኢትዮጵያን ሠራዊት በኃይል ይዋ ጋው እንጂ የኢትዮጵያ ጦር ከኢጣሊያ ምሽግ ድረስ እየሄደ ብዙ ጉዳት አደረሰ ።

የኢትዮጵያ ጦር ለጠላት አመቺ እየሆነ ቢታኰስም ፤ጦርነቱ በተጀመረ በሁለት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ሁለት የኢጣሊያ መኰንኖች ተገደሉ ። በግራ በኩል የኢጣሊያ ጦር አዝማች የነበረው ሜዘይ ቆስሎ ወደቀ ። የመጀመሪያዋ ጥይት ከተተኮሰች ከሁለት ሰዓት ተኩል በኋላ ማለት ከጧቱ 3 ሰዓት ሲሆን ካፒቴን ሪቺ ጦሩን ወደፊት እን ዲገፋና መቶ አለቃ ማንፍሬዲኒ ደግሞ ያለውን መድፍ ሁሉ እንዲያ ስተኩስ ቶዜሊ አዘዘ ።

ለአራት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን የራስ መንገሻና የራስ አሉላ ሠራዊት ቮልፒቼሊ ባለበት በኩል እየገፋ ተጠጋ ። የግንባር ጦሩ አዛዥ ቮልፒቼሊም "....በኛ በኩል ጠላት ገፍቷል ። ያሉት መድፎ ችም በቂ ስላልሆኑ ተጨማሪ መድፍ በኛ አቅጣጫ የመጣውን ጠላት ይደብድብልን ...." በማለት ጠቅላይ የአምባ አላጌን ጦር አዛዥ ቶዜሊን ጠየቀ ። በጠየቀው መሠረት በፔርሲኮ እና በአንጌራ የሚመሩት መድፈኛ ብርጌዶች ታዘው አራት ሰዓት ሲሆን በኢትዮ ጵያ ሠራዊት ላይ በሩቅ የመድፍ ጥይት ያዘንቡበት ጀመር ። ምሽ

ግም ሆነ ዘመናዊ የጦር ትምህርት የሌለው የኢትዮጵያ ወታደር ፣ ባለ ምሽጐቹን ኢጣሊያኖች ከምሽጋቸው ድረስ እየሄደ ባለው እርጌ ጠመንጃና ጥይት ይቆላው ጀመር ።

ኢጣሊያኖች የሚቆስሉባቸውን ሰዎች ወደ መቀሌ ማጓጓዝ ጀመሩ። ቆስለው ወደ መቀሌ ከተወሰዱት ውስጥ አንዱ በጉይዶ ሞልቲዶ ሥር ያለው የጥቁር ጦር አዛዥ የነበረው አሊ አጋ መቀሌ እንደደረሰ "....ጦርነቱ ዋጋ ያለው አይመስለኝም ። መድፎቻችን ያለማቋረጥ ይተኮሳሉ ። በየጊዜው በአንድ አካባቢ ብቻ ቢያንስ አራት አራት የመድፍ ጥይቶች ይወድቃሉ ። .... ጠላቶቻችን ሲወድቁም ፣ ሲሞቱም ፣ ሲቆስሉም እናያለን....ግን ብዛታቸው ሳይቀንስ እንዳሉ ሆነው ወደ ፊት በመግፋት ይመጡብናል ። እጅግ በጣም ብዙ ናቸው ። በዚህ ሁኔታ ጦርነቱን ያለመቀጠሉ የተሻለ ነው ።....የጠላት ጦር ከግራ እስከ ቀኝ እንደቀለበት ከቦናል ።...." ብሎ ተናገረ ።

ከዚህ በኋላ ዶጀን የነበረው የአርሞንዲ ጦር ወደፊት እንዲሄድና በአሸጋጋሪ በመድፍ የኢትዮጵያን ሠራዊት እንዲደበድብ ታዘዘ። ከቀኑ አምስት ሰዓት በኋላ ያለው ጊዜ ለኢጣሊያ ሠራዊት አልቂትና የቶዜሊ የጭንቀት ጊዜ ነበር ። የጨነቀው ቶዜሊ የአርሞንዲ መድረስ ስለዘገየበት ሌተና ባዛኒን ልኮ አርሞንዲ ቶሎ እንዲደርስ ስለት አደረገ ። ያልተነካው የአርሞንዲ ትኩስ ሠራዊትም 6 ሰዓት ተኩል ሲሆን ደርሶ የኢትዮጵያን ሠራዊት በተጨማሪ መድፍ መደብደብ ሲጀምር የኢጣሊያ ሠራዊት ትንፋሹ መለስ አለ ። የራስ እሉላ ጦር ግን አልበገር ብሎ ሼክ ጧላን ደምስሶ የሼክ ጧላን ምሽግ ያዘ ። የሼክ ጧላ ምሽግ በመያዙም የኢጣሊያኖች ሥቃይ እየበዛ ሄደ ። ወደ መቀሌ የመሸሻ መንገዳቸውም ተዘጋ ።

ማንፍረንዲኒ መድፎቹን በአሸጋጋሪ እየተኮሰ ሽፋን እንዲሰጥ ተደርጎ ኢጣሊያ ከአምባላጌ ወደ መቀሌ መጓዙን ጀመረ ። ዕቃ የተጫኑ በቅሎዎች ፣ የቆሰሉ ሰዎች ሁሉ ከያሉበት ኮረብታ በእንቆቅቅ እየወረዱ በካፒቴን ብሩዚ እና በማንፍሬዲኒ የተኩስ ከለላ መሀል እየሾለኩ ወደመቀሌ ይጓዙ ጀመር ። ኢትዮጵያውያኖችም የሚሸሸውን ሠራዊት እየተከታተሉ ይፈጁት ጀመር ። በዚህ የጭንቅ ጊዜ ኢጣሊያኖቹ አንዲት መንገድ ብቻ ከፍት ሆና በማግኘታቸው ቁስለኛውም ፣ ፈረሱም ፣ በቅሎውም ፣ ጤነኛውም በዚያች መንገድ እየተተረማመሰና እየተጋፋ ሲሸሽ ለኢትዮጵያውያኖቹ ማነጣጠር የማያስፈልገው ጦርነት ሆነላቸው ። ሞልቴዶ "....ራስ አሉላ እንዳያመልጥህ እያሉ በማዘዛቸው ብዙ የጭነት እንስሳትና ሰዎች አለቁ ።...." ብሎ ሲፅፍ ቤርክሌይ ደግሞ "ከአምባላጌ እስከ መቀሌ ርቀቱ 35 ማይል

ይሆናል ። የሚሸሸው የኢጣሊያ ሠራዊት መሄጃ መንገድ እያጣ መቀሌ የደረሰው ከስድስት ቀን ጉዞ በኋላ ነው ። . . . .” ብሏል ።

የኢጣሊያ ሠራዊት ሽሽት እንዴት ነበር ? የኢጣሊያኑ ጋዜጠኛና መድፈኛ ከነበረው ሞልቴዶ ከፃፈው መጽሐፍ ጥቂት እንስማ ። “. . . . መሐመድ የሚባለው ሱማሌው ወታደራችን ሲያጫውተኝ. . . . ጦርነቱ ተጀመረ ። . . . .ተኩስ እሰማለሁ ። ግን የማየው ነገር የለም ። ወጥቤት ነኝና ቁርስ ለማዘጋጀት ተነስቼ ጉድ ጉድ ስል አምስት ሰዓት ሲሆን መቶ አለቃ እስካላ በብቅሎ ተቀምጦ መጣ ። ምን ታደርጋለህ ? አለኝ ። . . . .ምግብ አዘጋጃለሁ አልኩት ። ተወው ፤ ዛሬ ምግብ አንበላም ። ሁሉን ነገር እዚያው ተውውና በቅሎ ጭነው ከሚሄዱት ሰዎች ጋር ተገናኝ አለኝ ። . . . .ተደባልቄ ስንጓዝ ካንድ ሰርጥ ገባን ። እዚያም አበሾቹ በጥይት ተቀበሉን ። በየድንጋዩ ኋላ አበሾቹ ተደብቀው ኖርዋል ። ከበላያችን ይተኩሳሉ ፤ ከፊታችንም ይተኩሳሉ ፤ ከጐናችንም ይተኩሳሉ ። መድረሻ አሳጡን ። በዚያ ላይ ደግሞ የሚሸሸው የኛ ወታደር ይገፋናል ። . . . .በቅሎዎች እየረጋገጡን ያልፋሉ ። ይጋፋሉ ። በግራም በቀኝም ሬሣና ቁስለኛ ብቻ ተከምሯል ። የቆሰሉት ሰዎቻችን እርዱን እርዱን ይላሉ ። የሚሰማቸው የለም ። በየትም ቦታ በየትም አበሾቹ እየተከታተሉ ይተኩሱብናል ። በነሱም ላይ ቢሆን የኛ መድፍ ይተኮስባቸዋል ። የኛ መድፍ ተኳሾች ከኔ ጋር ሲሸሹ ሳይ ጊዜ ተስፋ ቆረጥሁ ። መንገዱን ተውኩና ጫካ ውስጥ ገባሁ ። አንድ ቦታም ተደብቄ ራሴን አዳንሁ ። . . . .በጉዞዬ ላይ የኛን መኰንኖች አላየሁም ። አሁን ከዚህ ከሌሉ ሁሉም ሞተዋል ማለት ነው . . . .አለኝ. . . .” ብሏል ።

ሞልቴዶ በመጽሐፉ ካወጣቸው የአምባላጌ ታሪኮች ሌላው ደግሞ እንዲህ ይላል “....ከመቀሌ ምሽጋችን ውስጥ እንዳለሁ አንድ የቆሰለ ወታደር መጣ ። እሱም “ሰላም ሌቴናቴ .... አበሾቹ ደርሰዋል ። እዚህ እኋላዬ ናቸው ። .... የአራተኛው ባታሊዮን ወታደሮች በሙሉ ተገደሉ ።....ሁሉ ሞቱ ።....አለኝ....የዚህን ጊዜ ይህን የሰሙ በምሽጋችን ውስጥ የነበሩ የወታደር ሚስቶች በሙሉ ተሰበሰቡ ። ጠጉራቸውን ነጩ ፤ በእግራቸው መሬቱን ይደበድባሉ ። እየጮሁም ማልቀስ ጀመሩ ። ሚስቶችም ፣ እህቶችም ባንድነት ሆነው ለሞቱት ባሎቻቸውና ወንድሞቻቸው ያለቅሱ ጀመር ።....የእነሱም ጩኸትና ለቅሶ እኔንም እምባዬን አመጣብኝ ። . . . .በተለይ ባሎቻቸው የሞቱባቸው የሱዳን ሴቶች የበለጠ አዘኑ ። ጩኸታቸውም ከሌሎቹ የበለጠ ነበር ። የአባሻ ሴቶች የባሎቻቸውን ጠርቡሽ (ባርኔጣ) ራሳቸው ላይ እያደረጉ ያለቅሳሉ. . . .” ብሏል ።

ሊብሮ ቤርዴ ወይም አረንጓዴ መጽሐፍ ፣ የኢጣሊያን መንግ ሥት ብዙ ሪፖርቶች አውጥቷል ። በማንፍሬዲኒ ውስጥ መድፍ ተኳሽ የነበረ አንድ ብሉቅባሽ ስለ አምባላጌው ጦርነት የተናገረው ቃልም ከዚያው ውስጥ ታትሞ ወጥቷል ። ብሉቅባሹ እንዲህ ይላል "....ቶዜሊን አይቼዋለሁ ። ከኛ ጋር ይሸሽ ነበር ። ከጥይት ያስጥለው ይመስል እጁን ለመከላከያ ራሱ ላይ አድርጐ ቀስ እያለ በዚያች ጠባብ መንገድ ሲያልፍ አይቼዋለሁ ።. . . .አብረውት ከነበሩት መኰንኖች መሀል አንጌራ ፣ ፔርሲኮ ፣ ቦድሬሮ ፣ ፒጂላ እና ሌሎች ታማኝ መኰ ንኖችም አብረውት ይሸሹ ነበር ። ....ተኩሱ ግን ይተኮስባቸዋል ። መጀመሪያ አንጌራ ወደቀ ። ቀጥሎም ፔርሲኮ ወደቀ ። እንደምንም ከዚያም ጭንቀት ወጥተን አንጣሎ መንገድ ስንደርስ ቶዜሊ ፣ ቦድሬ ሮን ጠራና እባክህ የምትችል ከሆነ አርሞንዲ የት እንደደረሰ ፈል ገው አለው ። ቦድሬሮም ሰምቶ እንዳልሰማ ነፍሱን ለማዳን ወደፊት ጉዞውን ቀጠለ ።. . . .አሁን እነሱ ያሉት ቤት ማርያም ናቸው ። ቶዜሊ በጣም ደክሞ ምንም መንቃነቅ አይችልም ። ቦድሬሮም አልታዘዝ ብሏል ። ቶዜሊን ትሄድ እንደሆን ተነስ እንሂድ ቢለው ቶዜሊ ሲመ ልስ ከዚህ ቦታ አንድ እርምጃ መራመድ አልችልም ። ከእንዲህ ዓይ ነቱ ጉዞ መሞቴን እመርጣለሁ ዞር በልልኝ ፤ አበሾቹ መጥተው ይግ ደሉኝ ብሎ ግንባሩን ለአበሾቹ ማነጣጠሪያ አመቻችቶ ተቀመጠ ...." ይላል ። አንዳንድ ፀሐፊዎች ቶዜሊ በዚያች ቦታ ተገደለ ሲሉ አንዳ ንዶቹ ደግሞ ከሌላ ቦታ ነው ይላሉ ።

የአምባላጌው ጦርነት ተፈፀመ ። በአምባላጌው ጦርነት 1300 የኢጣ ሊያ ጥቁር ወታደር ፤ ሃያ የጦር መኮንኖች መገደላቸውን ራሳቸው ኢጣሊ ያኖቹ አምነዋል ። አምባአላጌ መሽጐ የነበረው ጠቅላላው የኢጣ ሊያ ጦር ተበታትኖ ከሞት የተረፈው ከ15 ቀናት በኋላ መቀሌ ላይ ተሰበሰበ ። መቀሌ ላይ ከተሰበሰበው መሀልም "....አንዳንዱ በሰይፍ ራሱ የተገመሰ ፣ ትከሻው የተቀረጠ ነው ። አንዳንዱ በጥይት የቆሰለ ነው ። እንደ እነኚህ ዓይነቶቹ ተርፈዋል የሚባል ከሆነ ከጠቅላላዎቹ መድፈኞች የተረፉት 35 ሰዎች ብቻ ናቸው ። በቶዜሊ ሥር ይመራ ከነ በረው ከ4ኛው ብርጌድ 579 ሰዎች ብቻ ሕይወታቸውን አድነዋል ። ከእነኚህም ውስጥ ሃያዎቹ ቁስለኞች ናቸው ። ሲዘምቱ ግን ከሺህ በላይ ነበሩ ።. . . .ከአበሾቹም ቢሆን 3000 ያህል ሰዎች እንደሞቱ ይገ መታል ።. . . ." ሲል ቤርኬሌይ ጽፏል ።

የአምባላጌ ጦርነት በተፈፀመ ጊዜ ምኒልክ ገና በጉዞ ላይ ስለነ በሩ ጉሊማ ላይ ሠፍረው ነበር ። " . . . .አላጌ ከጦሩ ሜዳ የነበረ የራስ መንገሻ መልእክተኛ ደብዳቤ ይዞ መጣ ። . . . .መልእክተኛውም ደብዳ ቤውን ይዞ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ገባ ። ወሬውንም ተናገረ ።

ቃሉም ይህ ነው ። . . . .ሰዉ የመድፉንም የነፍጡንም ተኩስ ቁም ነገር አላለውም ። እጅ ለጅ ተያይዘው ወጥቶ እዐብ ድንቅ ተብሎ የተመ ሰገነ ውጊያ ተዋግቶ ድል አድርጐ ፈጀው ። ፊታውራሪ ገበየሁ ግን ታሞ ሰንብቶ ነበርና በበቅሎ ተቀምጦ መሣሪያ ሳይዝ ዘንግ ብቻ ይዞ እይዞህ ፤ እይርም ያለቀብህ በጉራዴ በለው እያለ ሲያዋጋ ዋለ . . . .። ለጦሩም ሹም ሆኖ የመጣው ማጆር ቶዞሊ የሚባለው የኢ ጣሊያ ሹም ከዚያው ከጦሩ ላይ ሞተ ። እሱ ግን እሸሻለሁ ብሎ መንገድ ጀምሮ ነበር ። የኢትዮጵያ ሰው ፈጣን ነውና ለማምለጥ አልተቻለውም ብሎ መልእክተኛው ይህን ቃል ተናገረ ። . . . .” በማለት ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽፈዋል ።

እዚህ ላይ አንድ ነገር ለመጨመር ፡ የአድዋ ጦርነት የተካሄ ደው በገናና በሁዳዴ ጾም ጊዜ ነው ። ክርስቲያኑ ዘማች በዚያን ጊዜ እንደነበረው አጿጿም ራቱን በልቶ እስከ ሚቀጥለው ጀምበር መጥ ለቅ ድረስ ምንም አይቀምስም ። ውሃ እንኳን አይጠጣም ነበር ። ይህን የተገነዘቡት አጤ ምኒልክ ጳጳሱን አቡነ ማቴዎስን “. . . .ጦርነት ላይ መሆናችንን ያውቃሉ ። ሠራዊቱ በጦርነቱም ፡ በጠሙም ተደራራቢ ጉዳት እንዳይደርስበት ያገኘውን እየበላ እንዲዋጋ ይፍቱት ። ቢያስፈ ልግ ከጦርነት መልስ ይጾማል ።. . . .” ቢሏቸው አቡኑ ግብፃዊ ነበሩና የኢትዮጵያ ጉዳይ ጉዳያቸው ስላልሆነ “አልፈታም” ብለው እምቢ አሉ ። ምኒልክም በዚህ አዝነው “እግዚአብሔር የየዋህ አምላክ ይር ዳው” አሏቸው ። አቡኑ ድል ካደረገው ጋር ነዋሪ በመሆናቸው ፤ ያለበለዚያም በክብር ወደ አገራቸው የሚመለሱ ስለሆኑ የኢትዮጵያ ውድቀትም ሆነ እድገት ለእሳቸው የሚያመጣው ለውጥ አልነበረም። ደግሞ በጦርነት ጊዜ ሕዝቡ እንዳይጾም የሚታወጅለት አዲስ ነገር ሳይሆን የተለመደ ነበር ። ለምሳሌ ግራኝ መሐመድ የተነሣ ጊዜ አጤ ገላውዴዎስ ሲዋጉ ጊዜው የሁዳዴ ጦም ስለነበረ ጦሙ በአዋጅ ተሽ ሯል ።

## የመቀሌው ምሽግ

ከአምባላጌ ጦርነት የተረፈው የኢጣሊያ ሠራዊት ወደ መቀሌ እየሸሸ መቀሌ ምሽግ ውስጥ ታጐረ ። መታጐር ብቻ ሳይሆን የመቀ ሌው ምሽግ ተጠናክሮ እንዲሠራ በመታዘዙ ኢጣሊያኖች ከአምባ ላጌው ውድቀታቸው በ3ኛው ቀን የመቀሌን ምሽግ አጠናክረው መሥራት ጀመሩ ። የመቀሌው ምሽግ አሠራር እንዲህ ነበር ። በደቡብ በኩል 3 ሜትር ስፋት ያለው ግንብ እየሆነ ተገነባ ። ምሽጉ ዙርያ

# Le Petit Journal

SUPPLÉMENT ILLUSTRÉ

Huit pages : CINQ centimes



S. M. TAÏTOU

Impératrice d'Abyssinie

ለፔቲት ጋዜጣ ከመቀሌው ድል በኋላ እቴጌ ጣይቱን በመጀመሪያ ገፁ ላይ አወጣ ።



የድሮይቱ መቀሌ ከተማ

ከቡን ካለው ጥብቅ አጥር ሌላ ከግንቡ 30 ሜትር ያህል ራቅ ብሎ በጣም የሾሉ እንጨቶች በምሽጉ ዙሪያ በብዛት ተተክሉ ። ካንዱ ሹል እንጨት እስከ አንዱ ሹል እንጨት ያለው ርቀትም 20 ሣንቲ ሜትር ያህል ነበር ። እነኚያ ሹል እንጨቶች ከመሬት በላይ ያላቸው ከፍታ 30 ሣንቲ ሜትር ነው ። እንዲህ ሆኖ መተከሉም ምንም ነገር እንዳያልፍ ተብሎ ለመከላከል ነው ። ቲኒንቴ (መቶ አለቃ) ሉቺዮ እና ቲኒንቲ ፓኦሌቴ እንደተናገሩት ። . . . . በእነዚያ ሹል እንጨቶች መሀል ማለፍ የሚቻለው ቀስ ብሎ እግሩን እያሰላ በዘዴ የሚረግጥ ሰው ብቻ ነው ። እንዲህ አድርጎ እንዳያልፍ ደግሞ እኛ ከፊት ለፊቱ እንተኩስበታለን ። አደናቅፎት እንኳ በእነኛ ሹል እንጨቶች መሀል ከወደቀ ተመልሶ መነሳት አይችልም ። እጅግ በጣም ጠብቀው ከመሬት ውስጥ የተተከሉ በመሆናቸውም ማንም እንደፈ ለገው ሊነቅላቸው አይችልም ። . . . .'' ብለዋል ።

የመቀሌው የኢጣሊያኖች ምሽግ ከውስጥ 3 ሜትር ስፋት ባለው ግንብ ታጥሮ ፣ ከግንቡ በ30 ሜትር ስፋት በብዛት በተተከሉት በእ ነኛ ሹል እንጨቶች ብቻ ተደራጅቶ አላበቃም ። ከሹል እንጨቶቹ አልፎ ደግሞ እሾካማ ሽቦ እየተድበለበለ በምሽጉ ዙርያ እየተተከለ ተከምሯል ። እንኳን ሰው ፣ ወፍ አትሾልከውም ። ይህ ሁሉ የምሽግ አመሻሸግ በወታደሮች ዘንድ ያለ ነው ። የዚያን ጊዜዎቹ የመቀሌ ኢጣሊያኖች ግን ዘዴ ፈጥረው ነበር ።

ኢጣሊያኖች አምባላጌ ምሽጋቸው ላይ ጉድ የሆኑት የኢትዮ ጵያ ሠራዊት እምሽጉ ድረስ እየገባ በመዋጋቱ ነበር ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ለእግሩ ጫማ እንደሌለው ኢጣሊያኖቹ ያውቃሉ ። የግራር እሾሃማ አጥር ሲያጋጥመውም ጋሻውን አንጥፎ እንደሚያልፈው ያውቃሉ ። ለዚህ ነው ሽቦውን ጋሻውን አንጥፎ቎ ቢያልፍ ፣ እነኚያ ሹል እንጨቶች እየዘነጠሉ ያስቀሩታል ተብሎ የተተከሉት ። ከግንብ አልፎ ሹል እንጨት ፣ ከሹል እንጨቶች አልፎ ባለእሾሃማ ሽቦ እየተ ድበለበለ ከተደረገ በኋላ ፣ አሁንም ኢጣሊያኖቹ ፍርሐቱ ስላልለቀ ቃቸው ከሽቦው ውጭ ደግሞ ጠርሙስ እየተሰበረ እንዲነሰነስ ተደ ረገ ። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሠራዊት ለእግሩ ጫማ ስለሌለው እየ ወጋና እየቆረጠው እንዲያስቀረው ነው ። ቤርክሌይ እንደ ጻፈው "…. ኢጣሊያኖቹ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ፋሽኮና ጠርሙሶችን እየሰበሩና እያሾሉ ደረደሩ ። የኢጣሊያ መኰንኖች አዲስ ነገር መፈልሰፋቸው ነው ። በኔ ግምት ግን ትልቅ ስህተት ነው ። በነኚያ ሁሉ ፋሽኮና ጠርሙሶች ውሃ ሞልተው ቢይዙባቸው ይሻል ነበር ። በመጨረሻዎቹ 11 ቀናት ለአንድ ወታደር የተሰጠው የውሃ ራሽን በቀን ግማሽ

ሊትር ውሃ ነበር ። በዚህ ግምት አንድ ጠርሙስ ውሃ ለአንድ ወታደር ለሁለት ቀን ይሆነው ነበር ። ....” ብኋል ።

ጋሊያኖ ለመድፈኛው አዛዥ ለሞልቴዶ ትእዛዝ ሰጠው ። ትእዛዙም “....ምሽጉን ዙርያውን ፈንጂ ጥመድበት ። የምትጠምደውም ፈንጂ ከመሣሪያ ግምጃ ቤት ዋሻችን ጋር የተያያዘ ይሁን ። የማስጠንቀቅህ ነገር አበሾቹ ምሽጋችንን ሰብረው ለመግባት ቢሞክሩና ከምሽጋችን ቢገቡ ፣ የመጀመሪያ ሥራህ ፈንጂዎቹን በሙሉ ማፈንዳት ነው ። ....” አለው ። ይህን የጥብቅ ጦር አዛዡን የጋሊያኖን ትእዛዝ የሰሙ የኢጣሊያ መኰንኖች “.... ፈንጂው ሲፈነዳ እንዴት እንሆናለን ?” ቢሉት ጋሊያኖ ሲመልስ “በመጨረሻ ጊዜ ሁላችንም ባንድነት በአየር ላይ እንንሳፈፋለን” አላቸው ።

ከታህሳስ 5 ቀን ጀምሮ እስከ ታህሳስ 10 ቀን እንደር ወዳጁ የትግራይ ሕዝብ ሳይታዘዝ በራሱ ፈቃድ እየወጣ በኢጣሊያኖቹ ላይ ሲተኩስ ከረመ ። ታላቅ ጉዳት ግን አላደረሰም ። እዚያ ምሽግ ውስጥ ምን ጉዳት ይደርሳል ?

በዚህ መሀል ታህሳስ 4 ቀን ከራስ መኰንን የተፃፈ ደብዳቤ ኢጣሊያኖቹ ደረሳቸው ። ደብዳቤውም ራስ መኰንን ወደ አዲግራት መዝለቃቸውን የሚነግር ነበር ። በዚህ መሠረት ታህሳስ 7 ቀን የኢጣሊያ ታማኝ መኰንኖች ወደራስ መኰንን ሄደው እንዲነጋገሩ ተወሰነ ። በዚያ በመቀሌ ምሽግ ውስጥ ያሉት መኰንኖች ወጣቶች በመሆናቸው ነገር ያደፈርሳሉ ተብለው ስለተፈሩ ፣ ይሻላል የተባለው ቴኔንቲ ፓርቲኒ ወደ ራስ መኰንን ተላከ ። በራስ መኰንን ዘንድም መልካም አቀባበል ከተደረገለት በኋላ በአምባላጌው ጦርነት ቆስሎ ከተማረከው ከመድፈኛው አዛዥ ከአስካላ ጋር እንዲያድር ተደረገ። በዚያም ለሊት አስካላና ፓርቲኒ በኢትዮጵያ ላይ ሲመክሩና ሲጠነስሱ አድረው በማግስቱ ፓርቲኒ ከአስካላ የተነገረውን ብዙ ምስጢር ይዞ ወደ ወገኖቹ ሄደ ። ፓርቲኒ የአስካላን ታሪክ ለአለቆቹ ከነገረ በኋላ ፣ የሚጣራ ነገር ስላለ ፓርቲኒ ለአስካላ ልብስና መድኃኒት አቀብላለሁ ብሎ ተመለሰ ። ራስ መኰንንም በደስታ ተቀብለው እንዲሰጥ አደረጉት ። አስካላም በምስጢር ለቀረበለት ጥያቄ አስፈላጊውን መልስ ለፓርቲኒ ነግሮ ወደ ወገኖቹ ላከ ።

የመቀሌው ጦርነት ታህሳስ 18 ቀን ተጀመረ ። ጦርነቱን የጀመረው የኢጣሊያ የመቀሌ ምሽግ የመድፈኛ ክፍል አዛዥ የሆነው ቴኔንቲ ሞልቴዶ የመጀመሪያውን መድፍ በማስተኮስ ነው ። ተኩሱ ሲጋጋል የኢትዮጵያ ሠራዊት በብዛት ሆኖ ወደፊት ተጠጋ ። እንዳየሱስ ኮረብታ ላይ ያለው የኢጣሊያ ጦር በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ

መድፉን አርከፈከፈበት ። ፈረሰኛውና እግረኛው የኢትዮጵያ ጦር ወደ ምሽጉ በሩጫ ሲጠጋ ምሽግ ውስጥ ያሉት የኢጣሊያ ወታደ ሮች በመትረየስ ጥይት ይቀበሉት ጀመር ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ምንም ማድረግ አልቻለም ። እስከ ታህሳስ 29 ቀን ድረስ ከባድ ትግል ቢያደርግም ከእልቂት በስተቀር ውጤት የለም ። ይህ ሁሉ ሲሆን ምኒልክ ገና በጉዞ ላይ ናቸው ። ታህሳስ 29 ቀን ምኒልክ መቀሌ ደረሱ ። ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ መቀሌ እንደደረሱ ጣይቱ የቀደሙትን መኳንንት እነ ራስ መኰንንን ሰብስበው "…. ይህ ነው ለአቀባበል ያዘጋጃችሁልን ግብር? አንድ የኢጣሊያ ሹም እናንተን ሁሉ ንቆ እንዲህ እስቲመሽግ ድረስ ዝም ብላችሁ መቆየታችሁ አፈርኩባችሁ ።…." አሏቸው ። ከዚህ በኋላ ራስ መኰንን "…. ያሠራሁትን ምሽግ እኔ አፈርሳለሁ…." ብለው ጦርነት ገጥመው ከኢትዮጵያኖች በኩል ብዙ ሰው አለቀ ።

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ሲጽፉ ምኒልክ ከደረሱ በኋላ "… በዚያም ቀን ኢጣሊያኑ ያለበትን እርዱን ፣ ካቡን ፣ መኳንንቱም በመነጥር ፣ ሠራዊቱም አሻግሮ ባየ ጊዜ እንደእሸት የሚቅመው ፣ እንደ ጥህሎ የሚውጠው መሰለው ። ነገር ግን እጤ ምኒልክ የጉድባውን ብርታት አይተውታልና ሠራዊቱ ወደ እርዱ እንዳይሄድ አስከለከሉት። ሠራዊቱም በየሠፈሩ ድንኳን ሲተክል የተራገፈች የወታደር በቅሎ ነጥቃ የኢጣሊያ ወገን ከተሠማራበት ተደባለቀች ። በቅሎይቱን ለመ መለስ አንድ ሰው ሮጠ ። ከካቡም ውስጥ ያሉት ኢጣሊያኖች ያ ሰው ሲሮጥ ባዩ ጊዜ መድፍ መተኮስ ጀመሩ ። እጤ ምኒልክ ….የመድፉ ተኩስ በበዛ ጊዜ ሊቀመኳስ አባተንና በጅሮንድ ባልቻን ሄዱ ተኩ ሱበት ብለው አዘዙ ።…." ብለዋል ።

በኢጣሊያኖቹ በኩል ደግሞ እንደፃፉት "…. ከጧቱ 4 ሰዓት ድንኳኖች ሲተከሉ አየን ። ከመሀል ቀይ ድንኳን ተተከለ ። የምኒ ልክ መሆኑን አወቅን ።…. በዚያ የበዓል ቀን ኢትዮጵያውያን ጦር ነት ያደርጋሉ ብለን አላሰብንም ነበር ። ጥቂት እንደቆዩ ግን ፈረሰ ኛው ቀድሞ ፣ እግረኛ እየተከተለ ሲመጣ አይተን የቴኔንቲ ባሲሊ ሰዎች በ4 ሰዓት ተሩብ ተኩስ ሲከፍቱ መላው ሠራዊታችን ተኩስ ከፈተ…." ብለዋል። የአንድ በቅሎና ያንድ ሰው ሩጫ ብዙ መስኋቸዋል። በዚያን ቀን ኢጣሊያኖቹ በኢትዮጵያውያን ላይ 174 የመድፍ ጥይት ተኩሰዋል ። ግን አብዛኛው ጥይት ግማሹ ከኢትዮጵያውያን በማለፍ፣ ግማሹም በመቅረት የተተኰሰ ነበር ። የእለቱን ግጥሚያ ምሽት ገላገለው ።

"ምሽትም በሆነ ጊዜ" ይላሉ ጸሐፊ ትእዛዝ "ሊቀመኳስ አባ ተና በጅሮንድ ባልቻ ተጠሩ ። እንግዲህ ከዚህ ጉድባ ውስጥ ያሉትን ኢጣሊያኖች ሳላወጣ ወዲያና ወዲህ አልልም ። እናንተም አረር እንዳይመታችሁ መታኮሻችሁን አብጁ ብለው አዘዙዋቸው ። ሊቀመ ኳስ አባተም ካሽከሮቹ ጋር ሆኖ የኢጣሊያውን ዘበኛ አባሮ በስተ ግራ በኩል ካቡን ክቦ ፣ መድፎቹን ፣ መትረየሱንም አልቦበት ነበር ። ደግሞ በስተቀኝ በኩል በጅሮንድ ባልቻም እንደዚሁ ለሊቱን ሲክብ አድሮ መድፎቹን ፣ መትረየሱንም አለበበት ። ኢጣሊያኖቹ ጦሩ እንደ ቀረባቸው ባዩ ጊዜ መድፋቸውን ነፍጣቸውንም ጠንክረው ይተኩሱ ጀመር ። ሊቀ መኳስ አባተም ብልህ ዓይነጥሩ ነፍጠኛ ነውና ኢጣሊያኖች ታቦተ ኢየሱስን አውጥተው የገቡበትን ቤተ ክርስቲያን በመነጥር እያየ እየመዘነ መስኮቱን በመድፍ ይመታው ጀመር ። የመድፋቸውንም መንኮራኩር በመድፍ ሰበረው...." በማለት ጽፈዋል ።

ሊቀመኳስ አባተ መድፉን በመድፍ መስበራቸውን ኢጣሊያኖቹ ራሳቸው በፃፉት ታሪክ ውስጥ ገልፀውታል ። የኢጣሊያ ክርስቲያን ወታ ደሮች የኢየሱስን ቤተ ክርስቲያን ምሽግ አድርገን እንዋጋም ብለው እምቢ አሉ ። ኢጣሊያኖቹም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑትን ወታ ደሮች አስገብተው መታኮስ ጀመሩ ። ውጊያው በተፋፋመበት ጊዜ ሊቀመኳስ አባተ የተኰሱት መድፍ እንዳየሱስ አረፈ ። ቤርክሌይ እንደፃፈው "....ያ ቀን መጥፎ ቀን ነበር ። እንዳየሱስ ያለው ምሽግ አደገኛና ለአደጋ የተጋለጠ ሆኖ ዋለ ። ከየአቅጣጫው የሚተኰሰው መድፍ ያለማሳሳት ይመታዋል ።.... አንዷ የተተኰሰውም የመድፍ ጥይት የኢጣሊያን መድፍ መንኰራኩር ሰባብሮ ጣለው ። ተኳሾቹ ሁለት ወታደሮች ቆሰሉ ። እሳትም አስነስቶ ጥቂት አፈር የተሞሉ የምሽግ ዶንያዎች ተቃጠሉ ።...." ብሏል ።

እንዳየሱስ ኮረብታ 2225 ሜትር ከፍታ ያለው ነው ። ኢጣሊያኖ ችም የመቀሌን ምሽግ በሚያጠናክሩበት ጊዜ እንዳየሱስ ኮረብታ ለውጊያ አመቺ ሥፍራ መሆኑን ስላዩ ከዚያ ላይ ጦር ለማስቀ መጥ አሰቡ ። ከእንዳየሱስ ኮረብታ ላይ ወጥተው "....ጦርነቱ ሲያ ልቅ ቤተ ክርስቲያኑን በጥሩና በታላቅ ሕፃን እናሠራዋለን ። አሁን ግን አስፈላጊያችን ቦታ ስለሆነ ልቀቁልን ....' ብለው ለቄሶቹ አንድ ሺ ብር ሰጡ ። በዚህ ውል መሀል አንድ 50 ዓመት የሚሆን ዕድሜ ያለው ቄስ በምንም ነገር አንለቅም ብሎ በመከራከሩ ወዲያ ውኑ ተገደለ ። ከዚህ በኋላ በቤተ ክርስቲያኑም ሆነ በአምባው ኢጣሊያኖች ያዙበት ጀመር ። ወደ ትረካችን እንመለስ ።

በዚያን እለት ሊቀ መኳስ አባተ ብቻ ሣይሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያን መድፈኞችም የጠላትን ጦር ግራ አጋብተውት ነው የዋሉት ። የኛን ሰው ምስክርነት ትተን ራሳቸውን ኢጣሊያኖችን እናስመስክራቸው ። መቶ አለቃ ፓርቲኒ እንዲህ ይላል ። "…. የመቀሌው ውጊያ ከተጀመረ 74 ሰዓት አለፈው ። 74 ሰዓት ሙሉ ምንም ረፍት አላገኘንም ። …. በምሥራቅ በኩል የቆፈርነውን ጉድጓድ አበሾች አስለቀቀውን ይዘውብናል ። በዚያም ምሽግ ውስጥ ያሉት ጠላቶች አስቸግረውናል ። ጀናዮ 8 ቀን (በኛ ታህሳስ 30) ጧት 8 ሰዓት ተሩብ (በኛ 2 ሰዓት ተሩብ) ሲሆን የመትረየስ ተኩሳቸው ጨዋታውን ጀመረ። 8 ሰዓት ከ45 ሲሆን ፤ በደቡብ አቅጣጫም ተጠቃን ። ከፍተኛ ቦታ ላይ የተጠመደው የጠላት መድፍ ምሽጋችንን ያዘንብበት ጀመር ። በዚያ ላይ የጠላት ፈረሰኛና እግረኛ ሥር ሥሩን ያዋክቡናል ። …. የኛ መድፎችም ሆኑ መትረየሶቻችን የሚተኮሱት ወደ ምሽጋችን በሚመጣው ጠላት ላይ በመሆኑ ፤ የራቀውን የጠላት መድፍ ፤ መድፎቻችን ሊያስታግሱልን አልቻሉም ።….

"በየቀኑ ባራቲየሪ ይደርስልናል እያልን እንጠባበቃለን ። ባራቲየሪ ግን በመቀሌ ምሽግ ያለነው ወታደሮች በቀላሉ ጠላትን እንደ ምናሸንፍ ነግሮን ነበር ። ከሌሊቱ 11 ሰዓት (በኛ 5 ሰዓት) እግረኛው ጠላት እምሽጋችን ሽቦ አጥር ድረስ ተጠግቶ አጠቃን ። እኛም ተበረታትተን መለስነው ። ጥቂት አረፍ እንዳልን እንደገና ከለሊቱ በአንድ ሰዓት (በኛ አቆጣጠር ከሌሊቱ 7 ሰዓት) ሲሆን ጠላት እንደገና ሽቦ አጥራችን ድረስ መጣ ። እኛም መለስነው ። ከዚያ በኋላ ጥቂት ረፍት አገኘን …." ብሏል ።

ኢጣሊያኖቹ እንዳሉት ከኢትዮጵያውያን በኩል መቀሌ ምሽግ ላይ የተጣለው የመድፍ ጥይት 500 ነው ። ከኢትዮጵያውያን በኩል የተተኮሰው የመድፍ ጥይት ያንያህል ነው? አይደለም? ብለን ባንከራከርም ኢትዮጵያውያን የመቀሌን ምሽግ ለመስበር ከባድ መስዋዕትነት መክፈላቸውን አንጠራጠርም ። ኢትዮጵያውያን በሙሉ ልብ የመቀሌን ምሽግ ለማስለቀቅ ቢደክሙም እንኳን ፤ በዚያ ሁሉ ትግል መሀል ያደረሱት ጉዳት ቀላል ነበር ። ኢጣሊያኖቹ ባወጡት መግለጫ በዚያ የመቀሌ ምሽግ አንድ ኢጣሊያዊ ሲሞት አራት ኢጣሊያኖች ቆሰሉ ። ከጥቁር አሽከሮች 3 ሲሞቱ 9 ቆሰሉ ብለዋል ። በዚህም በኩል አነሰ ብለን አንከራከርም ። የመቀሌው ምሽግ እጅግ በጣም ጠንካራና ከባድ ጥሩ መከላከያ የነበረው በመሆኑ ነው ።

በማግሥቱም እንደገና ጦርነቱ ቀጠለ ። ኢትዮጵያውያኖቹ እያጠቁ ምሽጉ ድረስ ይሄዱ ጀመር ። ከምሽጉ በሚጠጉበት ጊዜ የጠር

ሙሉ ስባሪ አላስኬድ አላቸው ። "…. ጋሻዎች እያነጠፉ ሲመጡብ ንም ፤ ለመትረየሳችን ኢላማ ምቹ ይሆኑልን ጀመር …." ብሏል ሞል ቴዶ ። ኢትዮጵያውያኖች ያን የጠርሙስ ስብርባሪ ቦታ ጋሻቸውን እንጥፈው ሲያልፉ ፣ያ ድብልብሉ እሾሃማ የሽቦ አጥር ያቆማቸዋል ። ከዚያም የሽቦ አጥር ላይ የብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ሬሣ እንደወፍ ሬሣ እየተንጠለጠለ ቀረ ። የመቀሌ የጠላት ምሽግ በወንዶቹ ጀግን ነት አልፈታ አለ ። ከዚህ በኋላ የሴት ብልሃት ተተካ ። የመቀሌውን እልቂትና ትግል ጣይቱ በየቀኑ ይመለከቱ ነበር ። የጣይቱ ማዘንም ሆነ ወንድን ማበረታታት ትርፉ እልቂት እንጂ ውጤት አልሰጠም ። በዚህ የተናደዱት ጣይቱ ፤ ዘዴ ፈጠሩ ። የጣይቱን ዘዴ ከፀሐፌ ትእ ዛዝ ገብረ ሥላሴ መጽሐፍ እንስማው ።

"…. ንግሥቲቱም እቴጌ ጣይቱ ከድንኳን ብቅ ብለው ግምጃ ውን አጥር አስገልጠው ሲመለከቱ አዛዥ ዛማኔል አጠገባቸው ቆሞ ነበርና ወደሱ አይናቸውን ዞር አድርገው ተናገሩ ። አንተ ሂድና ውሃ ውን ለመያዝ ይመች እንደሆነ ስፍራውን ሰልለው ። ለሊቀ መኳስ አባተም አማክረው ብለው አዘዙ ። ሊቀመኳስ አባተም ሥፍራው ጕድጓዳ ነው ፤ ለኢጣሊያኖችም ቅርባቸው ነው ። የውሃውና የምሽጉ ርቀት 150 ክንድ ይሆናል ። ነገር ግን እኔ በመድፍ በሩን እጠብቀዋለሁ። ዘበኛውም ለዓይን ሲነሳ ገብቶ ከወንዙ ይተኛል ብሎ ላከ ። ይህም ነገር በእቴጌ ዘንድ የተወደደ ሆነ ። ለንጉሠ ነገሥቱም አመለከቱ ። አጤ ምኒልክም እሺ እንዳልሽ አሉዋቸው ።

"እቴጌም አሽከሮቻቸውን እንዲህ ብለው አዘዙ ። እናንተ ከጉ ድባ ገብተን ካልተዋጋን እያላችሁ ስትመኙ ነበር ። ነገር ግን ለብዙ ሠራዊት ጥቂት ሥፍራ አይበቃውምና ከኢጣሊያው ነፍጥ ይልቅ እና ንተ እርስ በርሳችሁ ትተላለቃላችሁ ። ከውሃው ተኝታችሁ ውሃ እን ዳይቀዳ ጠብቁ ። ከጉድባቸው ሄደን እንዋጋለን ያላችሁ ከሜዳው ላይ ሞት እንዳትፈሩ ተስፋ አለኝ ። በሕይወት ያለውንም ባዘዝኳችሁ ነገር እሸልመዋለሁ ። የሞተውንም ተዝካሩን አወጣለሁ ። ልጁን አሳድጋለሁ ። እግዚአብሔር ከናንተ ጋራ ይሁን ብለው አሰናበቷቸው። እነሱም እምረው ተሰልፈው ፤ የተቆጣ ነብር መስለው ከማታው በ11 ሰዓት ወደ ወንዙ ወረዱ ።

"እቴጌም ለሊቱን ሙሉ በጭንቅ በኀዘን …. ሲያለቅሱ አደሩ። ከሌሊቱ 11 ሰዓት በሆነ ጊዜ የእልፍኝ አሽከሮችም[1] ተነሱ ። ስማቸውም ገብረ ጊዮርጊስ ፣ ድልነሴ ፤ ሽዋዬ ይባላሉ ። እነዚህም አሽከሮች የ300

1 አሽከሮቻቸው



ጣይቱና ምኒልክ



ራስ አባቱ



ደጃዝማች ባልቻ

የ300 ነፍጥ ሹሞች ናቸው ። ከነሰዋቸው ተሰልፈው ወደ ወንዙ ወረዱ ። መታኮሻቸውን አደራጁ ። ውሃውንም ደፈኑት ።.... እንደ አዳራሽ ፥ እንደ እልፍኝ አመቻችተው ወንዙን ተቀመጡበት ።

"ኢጣሊያኑም ውሃውና ካቡ ቅርብ ነበርና ውሃው ይያዝብኛል ብሎ አላሰበም ነበር ። ነገር ግን የውሃውን መያዝ ቁርጡን ባወቀ ጊዜ መድፉን ጉትቶ ፥ ነፍጡን ሰልፎ ፥ ሐሙስ ማታ በ3 ሰዓት አደጋ ጣለባቸው ። እነዚያም ጠንክረው ተታኩሰው መለሱአቸው ። ኢጣሊያኖችም እኩሌታው ሸሽቶ ሲገባ ፥ እኩሌታው እኔ እሻላለሁ ብሎ ይመጣ ነበር ። ሲመልሷቸው ግን ወደ እርዱ ለመግባት በራቸው ይጠባቸው ነበር ። እንዲህም እየሆነ ኢጣሊያኑም ባሽባዙቁም እያሌ ሞተ ።

"....እቴጌ ጣይቱም ውሃውን ለሚጠብቁ ዘበኞች ጠጁ በብዙ ቀንድ እየተሞላ ፥ በማለፊያ ወጥ እንጀራ እየተፈተፈተ በመሶብ ሆኖ ፥ ፍሪዳው ታርዶ ሥጋው በእንቅብ እየሆነ ከሌሊቱ በዘጠኝ ፥ በ10 ሰዓት ይሰዱላቸው ነበር ። የጠገበ ሰው ሁሉን ይደፍራልና እነሱም ነፍሳቸውን ለጌታቸው ፥ ለመንግሥታቸው ለውጠውታልና ትዋቃቸውን ሳይፈቱ ፥ እንቅልፍ ሳይተኙ ፥ በአንድ ቀን የሚያስመርረውን ጦርነት 15 ቀን ሙሉ ሌሊትና ቀን እየተዋጉ ውሃውን ከልክለው በጭንቅ ኢጣሊያኑን ከእርዱ ውስጥ እንዲወጣ አደረጉት ።

"ደግሞ አንድ ቀን እንዲህ ሆነ ። በጥር በ3 ቀን የራስ መኰንን ሰዎች ዘብ ይጠብቁ ከነበረው ውሃ ወጥተው የመቀሌን ግንብ እናፈርሳለን ብለው የሽቦውን አጥር ቆርጠው ፥ ከካቡ ሥር ተዋግተው ከሌሊቱ በ11 ሰዓት ጀምረው እስከ 8 ሰዓት ድረስ ሲታኮሱ ዋሉ ። ከራስ መኰንን ሰው 150 የሚሆን ሞተ ። ከእርዱም ውስጥ ካለው ከፈረንጁም ፥ ከባሽባዙቆችም እያሌ ሞተ ። ነገር ግን ካቡን ለማፍረስ አማይመቻቸው ሆኖ ተመለሱ ። ...." ብለዋል ።

የመቀሌ ምሽግ በሰው ኃይል ወይም በመሣሪያ ብዛት የሚፈታ አልነበረም ። የመቀሌን ምሽግ የፈታውና ድል ያስገኘው የጣይቱ ዘዴና የውሃው መያዝ ነው ። ውሃውን ከበው የያዙትም ወታደሮች ብዛታቸው 900 ያህል ነበር ። ጣይቱ ውሃውን እንዴት እንዳስያዙና ውሃውን ለያዙት ወታደሮች ከመኳንንቱ ምግብ ፍትፍት እያስፈተፈቱ በየለሊቱ በመላክ እንዴት ያበረታቱ እንደነበር ከፀሐፌ ትእዛዝ መጽሐፍ አወቅን ። በኢጣሊያኖችስ ዘንድ እንዴት ነበር ? የውሃው መያዝስ በኢጣሊያኖች ላይ ምን ችግር ፈጠረ ?

ሊቀ መኳስ አባተ መድፉቸውን ማስተኮስ የጀመሩት ከሌሊቱ 7 ሰዓት ተኩል ሲሆን ነው ። በዚያም ሰዓት የኢጣሊያ ምሽግ በአ

ባተ መድፍ ቢኃይል ተደብድቦ ለጥቂት ጊዜ መድፉ ዝም አለ ። እንደገና ከሌሊቱ 8 ሰዓት ተኩል ሲሆን የአባተ መድፍ መቀሌ ምሽግ ላይ ዘንቦ እርጭ አለ ። በምሽጉ ውስጥ የነበሩት ኢጣሊያ ኖች እንቅልፍ ገርስሷቸው ጥቂት ሸለብ ሲያደርጋቸው ከሌሊቱ 10 ሰዓት ላይ የአባተ መድፍ ቀስቅሷቸው ለሩብ ሰዓት ያህል ተተኮሰባቸው ። በመጨረሻው በ11 ሰዓት ተኩል መተኮስ የጀመረው የሊቀ መኳስ አባተ መድፍ እስከ ጧቱ 4 ሰዓት አላባራም ።

ኢጣሊያኖቹ ጥርጣሬ ገባቸው ። ለምን ለሊት መድፍ ሲተኮ ስብን አደረ ለሚለው ጥያቄያቸው መልስ ይፈልጉ ጀመር ። ውሃው መያዙን አወቁ ። ወዲያውም በአንድ ሙንጣዝ (50 አለቃ) የሚመራ ቡድን ወደ ውሃው ሂዶ ውሃውን እንደገና ነጥቆ እንዲይዝ ላኩ ። ቡድኑም በታዘዘው መሠረት ከውሃው በስተደቡብ ሂዶ ውሃው በ 500 ኢትዮጵያውያን መያዙንና ለማስለቀቅም ያለመቻሉን አሳወቀ ። ከዚህ በኋላ ሜጀር ጋሊያኖ ተናዶ ፣ ያለው ኃይል ሁሉ በውሃው አቅ ጣጫ እንዲዋጋና ውሃውን እንዲያስለቅቅ አዘዘ ። ወዲያውም የውሃ ችግር እንደሚደርስ ስላወቀ አንድ ወታደር በቀን ግማሽ ሊትር ውሃ ብቻ እንዲሰጠውና የኢጣሊያ ነጮች ግን የሚሰጣቸውን ቢኖ ብቻ እንዲጠጡ እንጂ ውሃ እንዳይሰጣቸው ጥብቅ ትእዛዝ ሰጠ ።

ቀን የፀሐዩ ግለትና አቧራው ውሃ ያስጠማል ። የውሃው ራሺን ለሁለት ቀናት ያህል ከተሞከረ በኋላ የምንጩ ውሃ እያያዝ የሚለ ቀቅ መስሎ ስላልታየ አንድ ወታደር በቀን እንዲት ብርጭቆ ውሃ ተሰፍራ እየተሰጠችው በዚያች ጉሮሮውን ሲያርስ እንዲውል ተደ ረገ ። ከዚህ ትእዛዝ አንድ ሁለት ቀን በኋላ በምሽጉ ውሃ ማጠራቀ ሚያ ገንዳ ውስጥ የነበረው ውሃ መልኩ ቢጫ ሆኖ ወደ ድፍርስ ነት ተለውጦ ለመጠጣት የማይቻል ሆነ ።

ፈረስና በቅሎዎች ውሃ ከጠጡ ሶስት ቀን ስለሆናቸው ምሽ ጉን ሰብረው ለመውጣትና ወደውሃው ለመሄድ እያሉ ከባድ ችግር አደረሱ ።የአብዛኛው ወታደርም ሥራ ፈረስና በቅሎዎቹ ከምሽጉ እን ዳይወጡ መከላከል ሆነ ።

በመቀሌ ምሽግ ያለውን የኢጣሊያ ሠራዊት እጅግ በጣም ያስ ቸገረው የውሃው መያዝ ቢሆንም ፣ የራስ መኰንንና የራስ አሉላ ሠራዊት ደግሞ በጥይት ይቆላቸው ነበር ። የኢትዮጵያ ሠራዊት የመቀሌን ምሽግ ስብርባሪ ጠርሙሱን አልፎ ድብልብሉን የሽቦ አጥር መበጣጠስ ጀመረ ። እንዴት እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም እንጂ ኢጣሊያኖቹ እንደፃፉት የራስ መኰንን ሠራዊት ያን የሽቦ አጥር የበጣጠሰው በጐራዴው ነው ይላሉ ።

ሞልቴዶ ስለዚሁ ጉዳይ ሲጽፍ "....የኛ ወታደሮች ያለ እረ ፍት ይተኩሳሉ ። ወታደሮቻችን የሚተኩሱት በጥርሳቸውና በግራ እጃቸው ጥይት ይዘው ነው ። ይህም ፈጥነው ጠመንጃቸውን ለማጉ ረስ እንዲመቻቸው ብለው ነው ።.... ከጠላት ወገን ከሚተኰሰው ጥይት የሚወጣው ጭስ በንፋስ እየተገፋ እየመጣ ምሽጋችን ላይ ያንዣብባል ። ወታደሮቻችን ፣ ባንዲራ ለመምራት ገድ አለው ብለው ባንዲራችንን ወደ አምባአላጌ አቅጣጫ ተከለውታል ።.... ምሽጋችን በመሬት ላይ ያለ ሳይሆን ሲኦል ሆኖብናል ።.... መቶ አለቃ ፍራን ኮኒ መሸነፌ ነውና እርዳታ ይላክልኝ ይላል ። ማን ይሰማዋል ? ...." ብሏል ።

ኢጣሊያኖችን በአንድ ቀን ድል ከመሆን ያዳናቸው የምሽጋቸው መጠንከር ነበር ። ኢትዮጵያኖቹ የጠርሙሱን ስባሪ ድራሹን አጥፍ ተው ድብልብሉን እሾካማውን የሽቦ አጥር ለማለፍ መሰላል ሠር ተው በመሰላል ለመሻገር ቢፈልጉም ከምሽግ ውስጥ ያለው የኢጣ ሊያ ሠራዊት በጥይት ይመታቸው ጀመር ። በሽቦ አጥሩ ዙርያም ብዙ መሰላሎቹ ቆመው ሲታዩ መሰላሎቹን ይዘው የሄዱት የኢትዮጵያው ያን ሬሣም በአጥሩ ሽቦ ላይ ተከምሮ ነበር ። ኢጣሊያኖቹ ራሳቸው እንደፃፉት አንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር ያን የሽቦ አጥር ሲያልፍ ገላው ሁሉ ተበሳስቶ ደሙን እያዘራ ከግንቡ አጠገብ ደርሶ ነበር ። ከግንቡ ሥርም ሆኖ ግንቡን አፍርሶ ለመጣል የግንቡን መሠረት ሲቆፍር ተገደለ ። እንዴት ያለ ጀግንነት ነው ?

በመቀሌ ምሽግ ውስጥ የውሃው ነገር እያከተመ ስለሄደ ክርስ ቲያን የሆኑ ጥቁር ወታደሮች ከራሺናቸው ግማሽ ብርጭቆ ውሃና ሩብ ብርጭቆ ቢኖ እየተሰጣቸው እያደባለቁ ጉሮሮአቸውን እንዲያ ርሱ ታዘዙ ። ለእስላሞች ግን በቀን አንድ ብርጭቆ ውሃ እንዲሰጣ ቸው ተደረገ ። በዚህ ጊዜ ውሃ ሳይቀምሱ የቆዩት ፈረሶች ፣ በቅሎዎ ችና የቀንድ ከብቶች መሞት ጀመሩ ። በሕይወት ያሉትም እንስሳት የውሃ ማጠራቀሚያውን ገንዳ ከበው ውሃ ማስቀዳት ከለከሉ ። ይህን ሁኔታ ያየው የጦሩ አዛዥ ጋሊያኖ ተበሳጭቶ "....ሄዱ ። ውጡና ጠጡ የሚሆነውን ነገር እግዚአብሔር ያውቃል ።...." ብሎ አዘዘ ። ውሃው በጣይቱ ወታደሮች በጥብቅ ይጠበቅ ነበርና ማን ይድረስ ?

ሞልቴዶ ስለውሃው ችግር ሲገልጽ "....እኛ መኰንኖቹ ለሰባት ቀናት ፊታችንን የታጠብነው የሴሊቱን ውርጭ ጤዛ በሮጣችን እየ ጠረግን በዚያ በማበስ ነበር ። ከአዲግራት የሚመጣው ጦር ያድነናል እያልንም እንጠባበቅ ነበር ።.... የውሃው ኃላፊ የውሃ ራሺን በሚሰ ጥበት ጊዜ እያንዳንዱን ሰው ወንዱንም ሴቱንም በስሙ ይጠራል ።

የተጠሩትም ሲቀርቡ መልካቸውን በደንብ እየተመለከተ ድጋሚ ጠብታ ውሃ እንዳይወስዱ እየተቆጣጠረ ይሰጣል ። .... የአንድ ሱዳን ሚስት ልጅ ወለደችና ለልጅዋ ማጠቢያ ውሃ ብትለምን ተከለከ ለች ። ....'' ይላል ።

ሹምባሽ መሐመድ ወደ መቀሌው ጦር አዛዥ ጋሊያኖ ዘንድ ሄዶ ፣ ዛሬ ለሊት በሕልሜ ነቢ መሐመድ መጥቶ ከምሽጋችሁ መሀል ጉድጓድ ብትቆፍሩ ውሃ ሊወጣላችሁ ይችላል ብሎ ነገረኝ ። የኔ ሕልም ደግሞ አይስትም ብሎ ነገረው ። ጋሊያኖም የፈለገ ሰው ይቆ ፍረው ። ምናልባትም ይገኝ ይሆናልና ሞክሩ አለ ። በቡድን የተከፋ ፈለ ቆፋሪ ተቋቋመ ። ቁፋሮውም ተጀመረ ። እምሽጉ ውስጥ ያለው ወታደር ሁሉ እግዚአብሔር በትክክል ለሚያምነው ለማንኛውም ሰው ሚስጥር ይገልጽለታል እየተባባለ ቁፋሮውን ቀጠለ ። ሁለት ቀንና ሁለት ለሊት ከቆፈሩ በኋላ ቁፋሮው አለት ድንጋይ ላይ ደረሰ ። ቆፋሪው ቡድን አለቱን መስበር ሲጀምር ካፒቴን ሞልቴዶ ሳቀባቸው ። "ሲኞር ቴኔንቲ ፣ ሳቅ ብቻ ። የእናንተ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ ተአ ምር አይገልጽላችሁም ። እኛ ግን አሁን በቅርቡ ውሃ እናወጣለን አሉኝ'' ይላል ሞልቴዶ በመጽሐፉ ።

የውሃ ነገር አከተመ ። የሹምባሹም ሕልም እንደቅዠት ተቆጥሮ ጉድጓድ ቆፋሪዎች የቁፈራ ሥራቸውን አቆሙ ። በቢርካ ወይም በገ ንዳ ያለችውን ውሃ የሚቆጣጠረው ፋሬሬ ፓትሮና በምሽጉ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ሰብስቦ "ዛሬ የሚታደላችሁ ውሃ ለመጨረሻ ጊዜ ነው ። ይቺን ዛሬ የምንሰጣችሁን ውሃ በጥንቃቄ ያዟት ። አንዷት ጠብታ ከመሬት ጠብ እንዳትል ተጠንቀቁ'' ብሎ አዘዘ ። ሞልቴዶ ስለ ውሃው ሁኔታ ሲገልጽ "....ይሸታል ፣ በጣም የቆሸሸ ውሃ ነው ። መልኩም ቢሆን ወደቢጫነት ተለውጧል ። ውሃው ይሆን መሳይ ይሁን እንጂ ወታደሩ ራሺኑ ሲታደለው ብርቅና ድንቅ የሆነ ውሃ ያገኘ ይመስለዋል ። ራሺን የሚሰጣቸው ወታደሮች ውሃ ጥም ሲይ ዛቸው አንዴ ፉት ይሉለታል እንጂ በርከት አድርገው አይጠ ጡም ።....'' ብሏል ።

"ከዚህ በኋላ''ይላሉ ፀሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ።....ከዚህ በኋላ ሙሴ ፊልተር የሚባለው የኢጣሊያ ሰው ተልኮ መጥቶ ነበርና ከአጤ ምኒልክ ገብቶ እንዲህ ብሎ ተናገረ ። የናንተስ ሰው ከምሽግ ዳር እየሄደ እየተታኮሰ ለምን ይሞታል ? እነዚያስ ከእርዱ ውስጥ ያሉት ኢጣሊያኖች በውሃ ጥም ለምን ያልቃሉ ? እኛም የምንፈል ገው ፍቅርና እርቅ ነው ። በፍቅር እንኳን የመቀሌን እርድ እስከ አዲግራትም ድረስ ለቀን እንሄዳለን ብሎ ቢናገር እሺ ይሁን ። እሁ

ንም እርቅ ከፈለጋችሁ ሂደህ የዚያን ነገር ጨርስህ ምላሹን አምጣ ብለው በጥር በ9 ቀን ሰደዱት ።

"እሱም መቀሌ ያሉት ኢጣሊያኖች በውሃ ጥም መጨነቃቸውን ልከውበት ነበርና የሶስቱን ቀን ጉዳና ባንድ ቀን አዲግራት ደርሶ ስልክ አስመትቶ ከኢጣሊያ መንግሥት ልቀቁ የሚል ምላሽ መጥቶለት ባለማኅተም ደብዳቤ ይዞ ተመለሰ ። በ3ኛው ቀን አጤ ምኒልክ ሠፈር ገባ ። ከዚያም ያመጣውን ደብዳቤ መቀሌ ላሉት ኢጣሊያኖች ሰደደላቸው ። እነዚያም ጉድባውን ለቃችሁ ውጡ የሚል ባለማኅተሙን ደብዳቤ ባዩ ጊዜ ተድላ ደስታ አደረጉ ። ...." ብለዋል ።

ፒየትሮ ፌልተር ጉዳዩን በእርቅ እጨርሳለሁ ብሎ የተመላለሰው በእርግጥ ለእርቅ አልነበረም ። ባራቲየሪ በኋላ ጊዜ እንደገለጠው ከኢጣሊያ የተነሣው አዲሱ ተጨማሪ ጦር እስኪደርስ ድረስ እንጉታ ረቅ እያለ ቢያንስ ለሃያ ቀናት ነገሩን እንዲጕትትና ለመቀሌው ምሽግ ውሃ እንዲያስገኝ ነበር ። ፌልተርም ራሱ በመጽሐፉ ይህን ጉዳይ ቢገልጽም ከጸሐፌ ትዕዛዝ ለየት ያለ ፌልተር የገለፀው ነገር ደግሞ አለ ። እንዲህ ይላል ። . . . .ምኒልክ አስጠርተውኝ ከድንኳናቸው ገባሁ ። እንደገባሁም እንዲህ አሉኝ ። ....እናንተ እኛን ለማሸነፍና ድል ለማድረግ መጥታችኋል ። የኢትዮጵያንም ሕዝብ ከባርያነት አገዛዝ ነፃ እናወጣሃለን ትላላችሁ ። ነገር ግን እንኳ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፣ እነኚያን በምሽጋቸው ውስጥ የታፈኑትን ምስኪን ሰይጣን ወገኖቻችሁን ለማውጣት አልተቻላችሁም ። የእኔም ደካማነት እንደ እናንተ ከሆነ ፣ እነኚያ ሰዎቻችሁ በውሃ ጥም እንዲሞቱ አደርጋለሁ ። ይሄን ለባራቲየሪ ንገረው ። ቅዱሳን መላእክት ግን ጠላቶቻችንን እንድንወድ ይነግሩናል ። እኔ ክርስቲያን ነኝ ። የአረመኔ ሕዝብም ንጉሥ አይደለሁም ። ስለዚህ እነኚህ ክርስቲያኖችም አይሞቱም ። የሚመሩዋቸው ሰዎች ላኩና ይውሰዷቸው ። ልትወጉን የምትፈልጉ ከሆናችሁ ባንድነት ሁኑና ጠብቁኝ እመጣለሁ ....አሉኝ ...." ይላል ። በማግስቱም 30 በርሜል ውሃ በምሽጉ ያሉ ኢጣሊያኖች እንዲቀዱ ተፈቀደላቸው ።

ጸሐፌ ትእዛዝ እንዳሉት መቀሌ ምሽግ ውስጥ ያሉት ኢጣሊያኖች ምሽጉን ልቀቁ የሚለው ደብዳቤ ሲደርሳቸው ተድላ ደስታ ያድርጉ እንጂ ምሽጉን በሰላም ለመልቀቅ ገና ከአጤ ምኒልክ ፈቃድ አልተሰጣቸውም ነበር ። የተለፋበት የመቀሌ ምሽግ እንዲለቀቅ የኢጣልያ መንግሥት ባዘዘ ጊዜ ፣ በኢጣልያ ያሉት ጋዜጦች በኢጣሊያ መንግሥት ላይ ተቃውሞአቸውን ይጽፉ ጀመር ። አንዳንዶቹ ጋዜጦ

ችም "እምባላጌ ላይ ተዋርደን በጦር ኃይል ተሸንፈን ለቀቅን ፡፡ ታላቅ ምሽግ ነው የተባለውን የመቀሌውን ምሽጋችንን ደግሞ በውሃ ሰበብ ለቀቅን ፡፡ ይህ የኢጣሊያን መንግሥት ውድቀት ስለሚያሳይ መንግሥታችን ድል መሆኑን አምኖ ከአበሻ ምድር መውጣት አለበት" እያሉ ሲጽፉ ፣ ሌላዎቹ ደግሞ "በመላ ዓለም መሳቂያ የሆን ውን ስማችንን ሳናድስ ሠራዊታችን ከኢትዮጵያ መውጣት የለበ ትም ፡፡ ቢያንስ አንድ ጊዜ ድል አድርጐ ከዚያ በኋላ ብንታረቅ ይሻ ላል" እያሉ ፃፉ ፡፡

መቀሌ ምሽግ ውስጥ ያሉት ኢጣሊያኖችም ምሽጉን ልቀቁ የሚለው ደብዳቤ እንደደረሳቸው ምሽጉን ጥለው ወደ ውሃው ለመ ውጣት ሲሉ በአዋጅ እንዳይወጡ በአለቆቻቸው ተከለከሉ ፡፡ እንደ ሞልቴዶ አገላለጥ ". . . . ባራቲየሪ አንድ ደብዳቤ ልኮ ጋሊያኖ ደርሶት ሲያነበው ዓይኑ እንባ አቀረረ ፡፡ ደብዳቤውም በንጉሥ ኡም ቤርቶ ስም የመቀሌን ምሽግ ለአበሻው ንጉሥ አስረክቡ የሚል ነበር. . . ." ይላል ፡፡ ከምሽጉ መውጣት የሚቻለው ነጭ ባንዲራ ሲሰቀል መሆኑም ተነገራቸው ፡፡ ከበፊቱ ይልቅ አሁን ውሃ ጥሙ ባሰባቸው ፡፡ ". . . . አጤ ምኒልክ ኢጣሊያኖችን በማሩዋቸው ጊዜ" ይላሉ ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ "በጅሮንድ ባልቻን ልከው ሰዉም ፣ ከብቱም ውሃ ይጠጣ ብለው ዘበኞቹን አዘዙ ፡፡ ኢጣሊያ ኖችም ይህን በሰሙ ጊዜ ወደ ውሃው ሲወጡ ዘመዱን ለመገና ኘት የናፈቀ ሰው ይመስላሉ እንጂ ጠላት ወዳለበት የሚሄዱ አይመ ስሉም ፡፡ ከብቱም ውሃ ከጠጣ በኋላ ብዙ አለቀ ፡፡ እንዲቱም ውሻ በሩ ሲከፈትላት ሩጣ ወጥታ ከውሃው ደርሳ ዘበኞቹ 3 ጋሻ ውሃ አጠ ጧት ፡፡ ውሃውንም ከጠጣች በኋላ ሁለት ሙት ወልዳ ከዚያው ላይ ሞተች ፡፡

"ከዚህ በኋላ በጅሮንድ ባልቻ መቀሌ በእርዱ ውስጥ ገብቶ የኢትዮጵያን ባንዲራ ተከለበት ፡፡ ኢጣሊያኖችም ከመቀሌ ከእርዱ ውስጥ እቃቸውን አንስተው ወጥተው ከሠፈር ዳር ከሜዳ ሠፈሩ ፡፡ ነገር ግን ከእርዱ ውስጥ ከብታቸው በውሃ ጥምና በመድፍ ፣ በመት ረየስ አልቆባቸው ዕቃቸውን የሚያነሱበት ከብት አጥተው ነበርና አጤ ምኒልክን ለመኑ ፡፡ አጤ ምኒልክም በቸርነታቸው ከእንደርታ ከነጋዴ ውና ከባላገሩ 500 ግመልና በቅሎ በየዋጋው እየገዙ ጭነው እንዲ ሄዱ አዘዙላቸው ፡፡ ለማጆር ጋሊያኖም ማለፊያ መርገፍ የተጫነች በቅሎ ሰጡት ፡፡ . . . ." ብለዋል ፡፡

ከመቀሌ ምሽግ 20 ከፍተኛ መኰንኖች ፣ 13 ዝቅተኛ መኰን ኖች ፣ 150 ባለሌላ ማዕረጐችና አንድ ሺ ጥቁር ወታደሮች ወጡ ፡፡

ከእነሱም ጋር ቀደም ብለው ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ሁለት ኢጣሊያውያንና 3 ግሪኮች አብረው ከጦሩ ጋር ወጡ ። ከአምባላጌ እየቆሰሉ ከተመለሱት ጋርም 200 ቁስለኞች በቃሬዛ ወጡ ።

ኢጣሊያኖቹ ወደ መቀሌ ምሽግ ሲገቡ 200.000 ጥይት ይዘው ነበር ። በመቀሌ ምሽጋቸው 80.000 ጥይት ተኩሰው ፥ 120.000 ጥይት ይዘው ወጡ ። ከሰላሳ ሺ ጠመንጃቸው 3.000 ብቻ ይዘው ወጡ ። ሃያ ሰባት ሺ ተማረከ ። ኢጣሊያኖቹ መቀሌ ምሽግ ሲገቡ 860 የመድፍ ጥይት ይዘው ገብተው ፥ ሲወጡ 600 የመድፍ ጥይት ይዘው ወጡ ። ይህም 260 የመድፍ ጥይት በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ተኩሰዋል ማለት ነው ።

የንጉሥ ኡምቤርቶ ቃል እንደደረሳቸው ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ለፊልተር ደብዳቤ ፃፋለት ። ደብዳቤውም እንዲህ ይላል ።

ይድረስ ከሙሴ ፊልተር ።

ከአዲግራት የመጣው የመንግስት ደብዳቤ ደረሰልኝ ። እንዳ ኢየሱስም ያሉ ሰዎች ክፉ ነገር ሳያገኛቸው በደህና እንዲሄዱ ንጉሥ ኡምቤርቶ እንደተመኙ ራስ መኰንን ተያዥ ይሁን ብዬ አዝዣለሁ ።

በጥር በ፲፪ በመቀሌ ሠፈር ተፃፈ

በዚህ ደብዳቤ አማካይነት ራስ መኰንን አስረካቢ ፥ ፊልተር ተረካቢ ሆነው በመቀሌ ምሽግ ውስጥ የውጥር ተይዘው የነበሩት ኢጣሊያውያን ተለቀቁ ። ኢጣሊያኖቹ ተለቀው በራስ መኰንን ጥበቃ ሥር እንዳሉ ዳግማዊ ምኒልክ ለኢጣሊያው ንጉሥ ኡምቤርቶ የሚከተለውን ደብዳቤ ፃፉ ።

ይድረስ ከንጉሥ ኡምቤርቶ ።

ፍቅርና ሰላም መፈለግዎን ጀኔራል ባራቲየሪ በስልክ የመጣለትን ቃል ቢያስታውቀኝ እኔም ደስ ብሎኝ የሚገባ የክርስቲያን ሥራችንን ለማስታወቅ እንዳ ኢየሱስ ከእርድ ውስጥ በመከራና በጭንቅ በውሃ ጥም ተይዘው ፥ ተከበው ፥ በእግራችን ተረግጠናቸው የነበሩትን ወታደሮችዎን አውጥቼ ከነመሣሪያቸው እርስዎ እንደተመኙት በራስ መኰንን እጅ ሸኝቼ ሰድጃለሁ ። አሁንም የእርቁን ነገር ተነጋግሮ የሚጨርሰውን ሰው ቶሎ ቢያስታውቁኝ መልካም ነው ። ከኔም ለሚጨርሰው ሰው ትእዛዝ ሰጥቼ ቶሎ ቢጨረስ እወዳለሁ ።

በጥር በ፲፮ ቀን በዶሎ ሠፈር በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም. ተፃፈ ።

ይህ የዳግማዊ ምኒልክ ደብዳቤ ለንጉሥ ኡምቤርቶ ከመድረሱ በፊት የኢጣሊያ ሚኒስትሮች ስብሰባ አድርገው ነበር ። ሚኒስትሮቹ የተሰበሰቡት መቀሌ ላይ ስለተያዙት ኢጣሊያኖች ጉዳይ ሲሆን በስ ብሰባው ላይ እነኚያን ኢጣሊያኖች ለማስለቀቅ ነገሩን በሰላም መጨ ረስ አለብን ተብሎ ተወሰነ ። ይህን ውሳኔ ለመፈፀም ኢጣሊያ ከሮማ ኢትዮጵያ ድረስ ወታደሮችዋን አዝምታ በሁለት ግጥምያ ድል ሆና ልታረቅ ማለቱ አሳፋሪ ነገር ሆነባቸው ። በዚያ ላይ ደግሞ የኢጣሊያ ጋዜጦች አሳፋሪ ተግባር እያሉ መንግሥታቸውን ይወቅሱና ሕዝቡን ይቀሰቅሱ ስለነበር ለኢጣሊያ መንግሥት ማጣፊያው ያጠረ ተግባር ሆነበት ። ሕዝቡም በየአደባባዩ እየተሰበሰበ“. . . . ሁለት ጊዜ በጥቁ ሮች በመሸነፋችን ታላቁ የኢጣሊያ መንግሥት በዓለም ፊት ተዋ ረደ ።. . . . ክብራችን ይመለስ ። እንዋጋ . . . . ”እያለ ይጮህ ጀመር ።

የኢጣሊያ መንግሥት እንደ ሕዝቡ ፍላጐት ወደፊት ግፋ እን ዳይል የኢትዮጵያው ጦር የማይጨበጥ የእሳት አሎሎ ሆነበት ። ነገ ሩን በሰላም እንዳይጨርስና ወታደሮቹን እንዳይመልስ የሕዝቡ ጩኸ ትና ሁካታ ለመንግሥቱ የሚያስጋው ሆነ ። በዚህ ምክንያት ለሕ ዝቡ ሰበብ ለመስጠት በሚያስችል መንገድ እርቅ እንዲፈፀም የኢጣ ሊያ ካቢኔ ወሰነ ። የመታረቂያውን አሳብ ወደ ምኒልክ ከመላኩ በፊት በየቦታው የተበታተኑትና ከመቀሌ ምሽግ የወጡት ኢጣሊያኖች ተጠቃለው አዲግራት እንዲገቡና ከዚያ በኋላ የእርቁ ንግግር እንደ ሚጀመር ዳግመኛ ፊልቴር ተልኮ መጥቶ ጥር 28 ቀን ለዳግማዊ ምኒልክ ነገረ ።

ባራቲየሪ “. . . . ስለ እርቁ ከምርኮኛው ከማጆር ሳልሳ ጋር ለመነ ጋገር ስለምፈልግ ይመለሳልና ይላኩልኝ. . . . ” ብሎ በፊልተር መላክ ተኛነት በጠየቀው መሠረት ማጆር ሳልሳ ወደ ባራቲየሪ ተላከ ። ሳልሳ ከመሄዱ በፊት የመመለሻው ቀን ተወስኖለት ለመያዣም አሥር መኰንኖች ከምኒልክ ዘንድ ቀርተዋል ። ሳልሳ ከሄደ በኋላ በመመለ ሻው ቀን ሳይመለስ ቀረ ። ምኒልክም መያዣቸውን እንደያዙ በትእግ ሥት ሲጠብቁ የቀጠሮው ጊዜ አስር ቀን አለፈው ።

ያቺን ጊዜ የኢጣሊያ ተራኪዎች እንዲህ ይሏታል ። “. . . .የሳልሳ የመመለሻ ጊዜ አስር ቀን ካለፈ በኋላ ፌብራዮ 3 ቀን እነኛ አስሩ መኰንኖች ወደ ምኒልክ ድንኳን ተጠሩ ። ድሮውንም እንገደላለን እያሉ ሲፈሩ ነበርና ሲጠሩ ደነገጡ ። ከድንኳኑ ውጭ መደዳውን በቆሙ ጊዜ እንገታቸውን አቀርቅረው ጸሎት ጀመሩ ። ሁለት ሰዓት ተኩል ያህል በጭንቅ ቆዩ ። ይሄም ሌተና ፓርቲኒ ተጠርቶ ከራስ መኰንን ጋር ተነጋግሮ እስኪወጣ ድረስ ነበር ። ራስ መኰንንም

ሌትና ፓርቲኒን ከድንኳናቸው አስገብተው "..... መንግሥታችሁ ማጀር ሳልሳን ለመመለስ ቃል ከገባበት ጊዜ በማሳለፉ ንጉሠ ነገሥቱ በእናንተ ላይ የፈለጉትን ነገር ሁሉ ማድረግ ይችላሉ ። በመያዣነታችሁ መሠረትም መገደል አለባችሁ ። ነገር ግን የኛ ንጉሠ ነገሥት ጨዋና ደግ በመሆናቸው በሌሎች ጥፋት እነኚህን ምንም ያልበደሉትን ሰዎች ለመበቀያ አያደርጓቸውም ። ስለዚህ ነፃነታችሁን ሰጥተዋችኋል ። አሁንም ማጀር ሳልሳን እንዲልክ ለባራቲየሪ ንገረው ። እሱን ባይልክ ፊልተርን ይላክ ። ይህን ባያደርግ ግን የክርስቲያኖች ደም እንደገና መፍሰሱ ነው.....አሉት...." ይላሉ ። እነኚያ እንገደላለን ያሉት ከውጭ የቆሙት ኢጣሊያኖችም በነፃ መለቀቃቸውን ሲሰሙ ተደስተው ግራና ቀኝ ሆኖ በሚሰድባቸው ሠራዊት መሀል አቋርጠው ወጡ ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ያለበትን ክልል እስቲወጡም አራት ሰዓት ፈጀባቸው ። የኢጣሊያ ሠራዊት ካለበት አካባቢ ሲደርሱም ስለነሱ የሚያስቡት ኢጣሊያኖች ተደስተው የእቀባበል ተኩስ ተኰሱላቸው ። እነሱም ከሌላው የኢጣሊያ ወታደር ጋር ከተደባለቁ በኋላ ባንድነት ነጭ ባንዲራ ይዘው ባራቲየሪ ዘንድ ሄደው "ሳልሳ ይመለስ" እያሉ ጮሁ ።ማጀር ሳልሳም የእርቁን አሳብ ይዞ ወደ ምኒልክ ተመለሰ ።

ኢጣሊያኖች ለእርቁ ድርድር ያቀረቡትን ሐሳብ ይዞ ለመነጋገር ማጀር ሳልሳ ይኃ ላይ ከሠፈሩት ከአጤ ምኒልክ ዘንድ መጣ ። ጊዜው ስለመሸም ከበጅሮንድ ባልቻ ሠፈር አደረ ። በማግሥቱ የሳይንቱ ገዥ ራስ ቢትወደድ መንገሻ ፥ የሐረርጌው ገዥ ራስ መኰንንና ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ባንድነት ሆነው የመጣህበትን ጉዳይ ንገረን አሉት ። ማጀር ሳልሳም "....እርቁን ለመታረቅ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት ውስጥ ያሉ ሹሞች ሁሉ የኢጣሊያን የበላይነት እንዲያውቁ ያስፈልጋል ። ንጉሠ ነገሥቱና በውስጣቸው ያሉ ራሶች ሁሉ የኢጣሊያ መንግሥት ግዛት ከአሸንጌ ሐይቅ እስከ ተከዜ ወንዝ ድረስ መሆኑን እንዲያውቁ ። ጠቅላላዋ ኢትዮጵያ ደግሞ በኢጣሊያ ጥገኝነት ሥር ትሆናለች ። የኢትዮጵያ መንግሥት ወታደር ለማደርጀት ቢፈልግ ከኢጣሊያ መንግሥት ማስፈቀድ አለበት ። በኢትዮጵያ ውስጥ የኮንሲስዮን መሬት ለውጭ አገር ሰው ለመስጠት ፥ የውጭ አገር ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ እንዱስትሪ እንዲያቋቁምም ሆነ የባቡር ሐዲድ ለመዘርጋትና ይህን ለመሳሰሉት ጉዳዮች ሁሉ የኢጣሊያ መንግሥት መፍቀድ አለበት ። በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ አገር ሰዎችን ጉዳይ በዳኝነት ፍርድ የሚያይላቸው የኢጣሊያ መንግሥት ነው ። የቀረጥና የግብር ጉዳይ በኢጣሊያ ሕግና ደንብ መሠረት ይሆናል ። ኢትዮጵያ የምታሠራው ገንዘብ በኢጣሊያ እንዱስትሪ

ይሠራል ። የኢጣሊያ መንግሥት ካልፈቀደ በስተቀር የኢትዮጵያ
መንግሥት ማንኛውንም የብድር ስምምነት ከማንኛውም የውጭ መን
ግሥት ጋር አያደርግም ። የኢጣሊያ መንግሥት ፈቅዶ የኢትዮጵያ
መንግሥት ከሌላ መንግሥት ብድር ቢበደርም የኢትዮጵያ መንግ
ሥት ለሚኖርበት ዕዳ የኢጣሊያ መንግሥት ተጠያቂ አይሆንም ።
ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ውስጥ ንግድ በማስፋፋት ፣ እርሻ በማረስ ተማሪ
ቤት በመክፈትና የመሳሰሉትን ሁሉ በማድረግ ይረዳል ። ኢጣሊያኖች
በኢትዮጵያ ውስጥ መሬት ለመግዛት ኃይል አላቸው ። ንጉሡና በን
ጉሡ ሥር ያሉ ራሶች ሁሉ የኤርትራውን ገዥ ትእዛዝ ይቀበላሉ
የሚል አሳብ አቀረበ ። ይህን የእርቅ አሳብ ባጭር ባጭሩ ፍሬ ነገሩን
ወሰድኩት እንጂ በዝርዝርና በአንቀጽ ሲሄድ ሰፊ ነው ።


እዚህ ላይ ከገብረ ሥላሴ መጽሐፍ ልጥቀስ ። “. . . .ለልብ የማይ
ስማማ ፣ ለጆሮ የማይሰማ ነገር ተናገረ ። አጤ ምኒልክ ሲመልሱ
እኔ የመጣሁ የተተከለውን ባንዲራ ላስነሳ ነው እንጂ እንደዚህ
ያለውን እርቅ መቀበል አይቻለኝም ። . . . .በተረፈ ግን ግፍ የማይወ
ደውን እምላክ ጨምሬ በመጣችሁበት መንገድ እቀበላችኋለሁ ።
ባገሬ በኢትዮጵያ መንግሥት የሮማን ባንዲራ አላስተክልበትም
ብለው መለሱለት ። . . . .” ብለዋል ።

ከዚህ በኋላ በያለበት በተናጠል ቁርቋሶው ጀመረ ። ከራስ መን
ገሻ ጋር ተጣልተው ወደ ኢጣሊያ ገብተው የነበሩት ራስ ስብሐትና
ደጃዝማች ሐጐስ ተፈሪ ከጠላት ጋር ሆነን ወንድሞቻችንን እንወ
ጋም ብለው ከነመሣሪያቸውና ከነሰዋቸው ከኢጣሊያ ከድተው የካ
ቲት 4 ቀን ወደ ምኒልክ ገቡ ። ምኒልክም እነኚህን ሁለት መኳንን
ቶች በፍቅር ተቀብለው ከነሠራዊታቸው ሸልመው ስመው አገራች
ሁን ጠብቁ ብለው አርብ ዕለት አሰናበቷቸው ። ራስ ስብሐትና ደጃች
ሐጐስም ከምኒልክ ዓርብ ዕለት ተሰናብተው ሰኞና ማክሰኞ ከአዲ
ግራት ወደ እንቲጮው ከሚመጣ የኢጣሊያ ሠራዊት ጋር ጦርነት
ገጥመው 360 ኢጣሊያኖች ገድለው የምሥራች ብለው ወደ አጤ
ምኒልክ ላኩ ።

ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጐስ ተፈሪ አዲግራት ባሉ ኢጣሊያ
ኖች ላይ ከባድ ችግር አደረሱ ። የመገናኛውን ስልክ ከመበጣጠሳቸ
ውም ሌላ መንገዱን ዘግተው ለኢጣሊያኖቹ ስንቅ እንዳይደርስ
አደረጉ ። አንድ የኢጣሊያ መኰንን ለቤተሰቡ በፃፈው ደብዳቤ እንደ
ገለፀው “ . . . .ምግቡ ዱቄትና ሩዝ ብቻ ነው ። ቢኖ ፣ ቺዝ (አይብ)
ኮምጣጤ ሁሉ የለም ። የመጻፊያ ወረቀት እንኳን አጥተናል . . . .”
ብሏል ። ዶክተር እምብሮጄቲ እንደፃፈው የቴሌግራፍ ሽቦ ሲቆጥሉ



ራስ መኰንን



ራስ ስብሀት

የሔዱ ሰዎች ቆስለው እሱም ከቁስለኞቹ ጋር መመለሱንና ያቆሰለ ቻቸውንም አንዲት ሴት አድፍጣ ስትተኩስ ማየቱን ገልጿል ። አንድ ጊዜም የቴሌግራፉን ሽቦ በድንጋዮች እየቀጠቀጡ ከሚቆርጡ ሴቶች መሐል ሁለት ተይዘው መምጣታቸውንም ገልጿል ።

ዋናው ጦርነት እስቲጀመር ድረስ በተናጠል ጀብዱ ከሠሩት አንዱ ቀኛዝማች ታፈሰ ናቸው ። ወጣቱ ቀኛዝማች ታፈሰ አዲግራት የመሸገውን ኢጣሊያ፣ ከተራራ ላይ ወጥተው የኢጣሊያኖችን ሁኔታ በመነጥር ሲያዩ ኢጣሊያኖች እየተጅመለመሉ ሲመጡ አዩ ። ከዚህ በኋላ ላለው ከገብረ ሥላሴ መጽሐፍ ልጥቀስ "....እምስትና 6ሺ የሚሆኑ ኢጣሊያኖች ሰባትና 800 የሚሆኑ ባሽባዙቆች ከእርዱ ወጥተው ቀኛዝማች ታፈሰ በመነጥር ከሚያይበት ተራራ አጠገብ ከሜዳው ላይ ደረሱ ።

"ቀኛዝማች ታፈሰ አምሳ የሚሆኑ ወታደሮች ተከትለውት ነበር ። እነዚያም ሲመጡ ባየ ጊዜ ወርደን እንተኩስባቸው ብሎ ካሽ ከሮቹ ጋር ተነጋገረ ። ተነጋግረውም አልቀረ ። ሄደው ተኮሱባቸው ። ቀኛዝማች ታፈሰም ያላጌ እለት 50 የሚሆነውን የኢጣሊያ ወታደር በአንድ ጐራዴ የነዳው፣ አንድ ላይ ቆሞ የተኰሰው እይር እንደ እርባጫ ተቀልሎ የተገኘው ዕድሜውም የ25 ዓመት ጐልማሳ ነበር ። ኃይሉና ጀግንነቱ እንደነሳምሶን እንደነጌድዮን ነበርና ተኩሶ የጣለ ላቸው ጊዜ እነዚያም ሸሽተው ተመልሰው ወደ እርዳቸው ገቡ ። እሱም የሞተውን ኢጣሊያ ገፎ የቆሰለውን ባሽባዙቅ በቃሬዛ አስነ ስቶ መጥቶ ግዳይ ጣለ ።...." ብለዋል ።

## አ ድ ዋ

"....የተተከለው ድንኳን ሲታይ ከብዛቱ የተነሳ አፍሪካ ኤሮ ፓን ለመጠራረግ የተነሳች ይመስላል ። የጦርነቱ ዕለት ኢትዮጵያው ያኑ ደማቅ ቀለም ያለው ካባ ለብሰው፣ ጠመንጃና ጦር ይዘው፣ ጐራዴ ታጥቀው፣ የነብርና ያንበሳ ቆዳ ለብሰው፣ አዝማሪዎቹ እየዘፈኑ፣ ቄሶች፣ ልጆች፣ ሴቶች ሳይቀሩ ፀሐይዋ ፈንጠቅ ስትል በተራራው ላይ በታዩ ጊዜ የኢጣሊያን ጦር አሸበሩት ።...." በርክለይ

"....ውጊያው እስቲጀመር እንጠብቃለን ።....እህቴ ሆይ፣ ይህ ደብ ዳቤ ሲደርስሽ በሕይወት እንደሌለሁ ቁጠሪው ። በሕይወት የምትቀ ሪው አንቺ እህቴ ለታዘዝኩበት ሥራ በክብር መሞቴንና በክብር

መሞት ደግሞ ለሰው ልጅ አስፈላጊ መሆኑን መስክሪ ።. . . .” ካፒቴን ካኖቫቲ ለእህቱ ከፃፈው ደብዳቤ ላ. ጉየራ ኢን አፍሪካ ከሚለው መጽሐፍ ።

“. . . . በእንዲህ ዓይነቱ የጭንቅ ጊዜ ፥ መልካም ምኞቴን ልገልጽልህ እወዳለሁ ።. . . .ጥቂት ሰዓት ከሚያስኬድ ርቀት ላይ ራሶች ተሰልፈዋል ። ባንድነት ወደኛ ይጓዛሉ ። ባታሊዮናችንም እንድናፈገፍግ ብቻ ይነግረናል ። የዚህም ውጤት መጨረሻው ምን እንደሚሆን ይገባሃል ። ጦሩ እየገፋ እስቲመጣ ድረስ ብቻ እንጠባበቃለን ።. . . . ለታዘዝነው ትእዛዝ ሕይወታችንን እንሰዋለን ። የኛ ነገር ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው ። አሁን ሁሉን ነገር ትቼ የማስበው ለተከበረው ሽማግሌ አባቴና ለተከበረችው እናቴ ነው ። አንድ የምለምንህ ነገር አለኝ ። ቤተሰቦቹ ምንም ነገር ቢያገኛቸው እንድትረዳልኝ አደራ እልሃለሁ ።. . . .” መቶ አለቃ ሚሴና፥ ላ. ጉየራ. ኢን አፍሪካ ከሚባለው መጽሐፍ ።

በአገራችን የአድዋ ጦርነት ብዙ ጊዜ ተጽፏል ። አሁን ለመፃፍ የምፈልገው አንዳንድ ከዚህ በፊት በአገራችን ያልተፃፉ ነገሮችን ባጫጭር እያደረግሁ ነው ። የኢትዮጵያ ጦር ብዛትና አሰላለፍ በየ ጊዜው ተገልጿል ። የኢጣሊያ ጦር ብዛትና አሰላለፍ ግን እምብዛም አልተገለፀም ። የኢጣሊያ ጦር አሰላለፍ በዝርዝር ሲታይ እንደሚከተለው ነበር ።

በአልቤርቶኒ የሚመራው ብርጌድ ፥ በውስጡ በሜጀር ዱሪቶ የሚመራው 1ኛው ቦታሊዮን 950 ወታደሮች ፥ በሜጀር ኮሱ(COSSU) የሚመራው 6ኛው ባታሊዮን 850 ወታደሮች ፥ በሜጀር ቫሊ የሚመራው 7ኛው ባታሊዮን 950 ወታደሮች ፥ በሜጀር ጋሚራ የሚመራው 8ኛው ባታሊዮን 950 ወታደሮች ፥ ሌተና ሳፒሊ የሚመራው ባታሊዮን 376 ወታደሮች ፥ በኢንሪ የሚመራው የተራራ መድፈኛ ጦር ከ4 መድፎች ፥ ቫቢ የሚመራው ሁለተኛው መድፈኛ ክፍል ከሁለት የተራራ መድፎች ፥ ቢያንኪኒ የሚመራው 3ኛው መድፈኛ ክፍል ፥ ከአራት መድፎች ፥ ማሶየ የሚመራው 4ኛው የተራራ መድፈኛ ክፍል ከአራት መድፎች ጋር ነበሩበት ። በጠቅላላው በአልቤርቶኒ ውስጥ 4.076 ወታደሮችና 14 መድፎች ነበሩ ።

አሪሞንዴ የሚመራው ብርጌድ ደግሞ ፥ በ14ኛው ሬጂሜንት ውስጥ ዲ. እስቲቫኖ የሚመራው ባታሊዮን 423 ወታደሮች ፥ ኮምፒአና የሚመራው 350 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን ፥ ብሩስቲ በሚመራው 2ኛ ሬጂሜንት ውስጥ ቪያንቺኒ የሚመራው 450 ወታደሮች


ያሉበት ባታሊዮን ፣ ዲ. አሚቺስ የሚመራው 500 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን ፤ ባውዶይን የሚመራው 550 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን ፣ ፓቪሲ የሚመራው 220 ወታደሮች ፣ ፍራንዚኒ የሚመራው 11ኛው የተራራ መድፈኛ ክፍል ከስድስት መድፎች ጋር በጠቅላላው 2493 ወታደሮችና በየጦሩ ካሉት በጠቅላላው 12 መድፎች ነበሩት ።

ዳ. ቦርሜዳ በሚመራው ብርጌድ ውስጥ ደግሞ ፣ በራፒ 3ኛ ሬጂሜንት ውስጥ ጀርዳኖ በሚመራው 5ኛው ባታሊዮን ውስጥ 430 ወታደሮች ፣ ፕራቶ በሚመራው 6ኛ ባታሊዮን ውስጥ 430 ወታደሮች ፣ ዲ. ፎንሲካ በሚመራው 10ኛው ባታሊዮን ውስጥ 450 ወታደሮች ፣ አይራጊ በሚመራው በ6ኛው ሬጂሜንት ውስጥ ደግሞ ብራንኪ የሚመራው 430 ወታደሮች ያሉበት 3ኛው ባታሊዮን ፣ ራይኔሪ የሚመራው 450 ወታደሮች ያሉበት 13ኛው ባታሊዮን ፣ ዲ. ቪቶ የሚመራው 950 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን ፣ በወዶ ፈቃደኛነት የገቡ 210 ወታደሮች ፣ ብዞላ አመራር ሥር ማቴኖ የሚያዘው ስድስት መድፎች ያሉበት 5ኛው የተራራ መድፈኛ ክፍል ፣ ሬጋዚ የሚመራው 6 መድፎች ያሉበት 6ኛው የተራራ መድፈኛ ክፍል ጂስላ የሚመራው 6 መድፎች ያሉበት 7ኛው የተራራ መድፍ ክፍል ፣ በጠቅላላው 3.350 ወታደሮችና 18 መድፎች ነበሩበት ።

ኤልና በሚመራው ብርጌድ ውስጥ ደግሞ ፣ የ4ኛው ሬጂሜንት አዛዥ ሮሚሮ የሚያዘው ሞንቴኪ የሚመራው 7ኛው የእግረኛ ባታሊዮን ከ450 ሰዎች ጋር ፣ ቪዳንቲ የሚያዘው 450 ሰዎች ያሉበት ባታሊዮን ፣ ማንፍሬዲ የሚያዘው 480 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን፣ ናና በሚያዘው ሬጂሜንት ውስጥ ደግሞ አልፔኒ የተባለው ተራራ ወጭ ባታሊዮን ከ550 ወታደሮች ጋር ፣ ፌራሮ የሚያዘው 85ኛው ባታሊዮን ከ500 ወታደሮች ጋር ፣ ቫንዲዮል የሚያዘው 500 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን ፣ ጋሊያኖ የሚያዘው 1.150 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን ፣ ዲ. ሮሣ በሚያዘው ሬጂሜንት ውስጥ 1ኛው መድፈኛ ክፍል ከስድስት መድፎች ጋርና ከሰባ እንጂኔሮች ጋር ሆነው በጠቅላላው 4150 ወታደሮች ነበሩበት ።

በጠቅላላው ኢጣሊያ አድዋ ላይ ያሰለፈው ዘመናዊ ጦር 14.069 ነጭ ወታደርና በጠቅላላው በጦሩ 56 መድፎች ነበሩ ። ከዚህም ሌላ 1.400 የጭነት ከብት የሚነዱ ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቁ ወታደሮች እንደነበሩ አኪሌ ቢዞኒ ይገልጻል ።

የኢጣሊያ ጦር በዚህ ሁኔታ ተሰልፎ ሳለ ፣ በማጆር ሳልሳ የተላከውን የእርቅ አሳብ ምኒልክ አልቀበልም ካሉ በኋላ የኢጣሊያ ጦር



የኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያ ወደብ ላይ ከመርከብ ሲወርድ



ጄኔራል አልቤርቶኒ



ጄኔራል ባራቲየሪ

ጄኔራል ባልዲሴራ





ጄኔራል ዳቦርሚዳ



ማጆር ጋሊያኖ



ማጆር ቶዞሊ



ቲኒንቴ ማንፍሬዲኒ

በየምሽጉ ላይ የኢጣሊያን ባንዲራ ሰቀለ ። የካቲት 22_ቀን ሌቴና ጄኔራል ባራቲየሪ በቁጥር 87 የጦሩን ድልድል አወጣ ። ከድልድሉ መጨረሻም ማስጠንቀቂያ በሚል ርዕስ "....ማንኛውም የኢጣሊያ ወታደር የሚይዘው የራሱን ጥይት ፣ ለሁለት ቀን የሚበቃ ምግብ ፣ ከላይ የሚደርበው ልብስ ፣ የውሃ መያዣ ጠርሙስ ፣ አንድ ጉድጓዳ ሰሃን (ሰኬሎ) ነው ። እያንዳንዱ ወታደር በሚጓዝበት ጊዜ ተከታትሎ እንዲሄድና በየመሀሉም ሁለት የመድኃኒት ዕቃ የተጫኑ በቅሎዎች 8 ጥይት የተጫኑ በቅሎዎች እንዲገኙ ይሁን ። ሌሎቹ ዕቃ የተጫኑ 5 በቅሎዎች ላንድ ነጂ ወታደር እየተሰጠው በየባታሊዮኑ ኋላ ይከ ተሉ ። ለዛሬ እያንዳንዱ ወታደር 30 ሰላሳ ጥይት ይረከብ ። ወታደ ሮች ሁሉ ድንኳን ፣ ብርድልብስና ሌላም ጓዝ እንዳይዙ ተከልክ ሏል ።....ትእዛዝ ያፈረሰ ወይም ሰላይ መስሎ የሚጠረጠር ሁሉ እየ ተያዘ ወደ ዋናው ጦር አዛዥ እንዲላክ ።...የሚል አዋጅ አወጀ ። በጉዞው ላይ ሲጃራ ማጨስ ፣መብራት ማብራት ፣ መነጋገርም ተከለ ከለ ። ጊዜው ጨረቃ ነበርና በጨረቃዋ ጥላቸው እንዳይታይ እንዲ ጠነቀቁም ታዘዘ ።

በእኛስ በኩል ? የምኒልክ ጦር በሙሉ አድዋ አካባቢ ሠፍሩ ዋል ። ባሀታ አምኔዎስ የተባለ ኢትዮጵያዊም ከኢትዮጵያ ጦር መሀል ነው ። ባሀታ ወደ መስኮብ ተልኮ ሩሲያ ውስጥ ተምሮ የተመለሰ ወጣት ነው ። ባሀታ የአገሩ ለመወረር መታሰብ አናዶት ከምኒልክ ጋር ዘምቷል ። ጦርነቱ ሊጀመር ሶስት ቀናት ያሀል ሲቀረው የካቲት 19 ቀን 1888 ዓ.ም. ራሺያ ላሉት ለራሻውያን ጓደኞቹ አንድ ደብዳቤ ጻፈ ። ባሀታ የጻፈው ደብዳቤ ሩሲያ ውስጥ ክሮንስታት በተባለው ጋዜጣ ላይ ወጣ ። ከአድዋ ጦርነት በኋላም ኢጣሊያኖች ወደ ኢጣሊያንኛ ተርጉመው ማርዞ 16 ቀን 1896 (በኛ መጋቢት 7) ቀን በወጣው እስታምፓ በተባለው ጋዜጣ ላይ ወጣ ።

ባሀታ ፣ ሞስኮብ ላሉት ጓደኞቹ የጻፈው ለጦርነቱ ዋዜማ እሱ ባለ በት የጦር ክፍል የነበረውን ዝግጅት ነበር ። በጥቂቱ ብንወስድለት እንዲህ ይላል ። "....ምሽጋችንን እንደ ኤሮፓውያን አመሻሸግ እያ ደረግን ሌትና ቀን በመሥራት ላይ ነን ። በሺ የሚቆጠሩ ዛፎችን እን ቆርጣለን ። አንዳንዱን ለምሽጋችን እናጋድመዋለን ። አንዳንዱን ደግሞ ቁመቱን ልክ እንደ እናንተ እንደ ክሮንስታት ፎቅ ቤቶች እያደረ ግን እናቆመዋለን ።....ውፍረቱም በኔ እምነት የመድፍ ጥይት በስ ቶት የሚያልፈው አይደለም ።ሴቶችና ልጆች ደስ እያላቸው በሥራው ይረዱናል ።

"....የኛ ንጉሠ ነገሥት ብዙ ጊዜ በዚህ በኛ በኩል እያለፉ ለምን ይሄን ያህል ጥንቃቄ እንደምናደርግ ይጠይቁናል ።....በጣም

ጥሩ ቦታ ይዘናል ። ከፊት ለፊታችንም አምስት ደስ የሚሉ ኮረብታ ዎች ይታዩናል ። . . . .አራቱ በዙሪያችን ሲሆን አንዱ ግን ከኛ አቅራ ቢያ ከመሀል ነው ። ንጉሠ ነገሥታችን የሠፈሩት ከመሀከለኛው ተራራ ነው ። . . . . ከየትም ቦታ ብንሆን የንጉሠ ነገሥቱን ድንኳን እያ ለሁ ። በዚያም ያለውን የሴቶችን ዘፈንና የቄሶችን ዝማሬ እሰማለሁ ። ትናንት ንጉሠ ነገሥቴ ሠፈራችንን ለ3ኛ ጊዜ ጐበኙልን ። ራሶች በሙሉ ከእሳቸው ጋር ነበሩ ። ራስ መኰንንም መቀሌ ጦርነት ላይ የቆሰሉት አሁን ስለተሻላቸው አንድ ጊዜ እየጋለቡ በአጠገቤ ሲያ ልፉ ደፈርኩና ካባዎ ከትከሻዎ ተቀዷል ብዬ ነገርኳቸው ። ሳቁና ‘ዝም በለው ከኢጣሊያኖች አዲስና የተሻለውን ማርኬ አመጣለሁ’ ብለውኝ ቀልደውብኝ አለፉ ። . . . . እናንተ አገር እንዳየሁት የኛ አገር ወታደር መድኃኒትም ሆነ የቁስለኛ መታከሚያ ሆስፒታል የለንም ። በተለይ ባለፈው ድርጊት ተማራኪ የኢጣሊያ ቁስለኞች እየበዙብን ስለሕዱ ሰንሰለታቸውን እየፈታን እንለቃቸዋለን።. . . .” የሚል ነበር ። የአድዋ ጦርነት ሲጀምር እነባህታ የሠሩት ምሽግ ያለጥቅም ቀረ ። ጦርነቱ እንዴት ተጀመረ ? ሁለት ዓይነት ትረካ አለ ? ሁሉቱንም እንመለከታለን ።

አንዱ የፀሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ትረካ ነው ። “. . . . በዚያን ቀን የዘቡ ተራ የትግሬው ገዥ የራስ መንገሻ ነበር ። 500 ነፍጥ የሚ ሆን የያዙ የሱ ሰዎች ዘብ ሲጠብቁ በየካቲት በ23 ቀን የቅዱስ ጊዮ ርጊስ ለት ለሊቱን በ11 ሰዓት የኢጣሊያ ወታደር ተሰልፎ መጥቶ ከበሩ ላይ አደጋ ጥሎ ከዘቡኛ ጋራ ተታኰሰ ። እነዚያም ተታኩሰው ከኢጣሊያኖች 2 ባሽባዙቆችን ማረኳቸው ። ምርኮኞቹንም ቢጠይቋ ቸው እንዲህ አሉ ። የአጤ ምኒልክ ሠራዊት ቀለብ ሊያመጣ ርቆ ሄድዋል ፣ ሠፈሩ ባዶ ነው ፣ አደጋ እንጣልበት ብለው ኢጣሊያኖች 4 ጄኔራል ባባ ገሪማ በኩል ፣አንድ ጄኔራል በማርያም ሸዊቶ በኩል ተሰልፎ መጥቷል ብለው አወሩ ።

“ይህን ወሬ በሰማ ጊዜ ከዘበኞች አንዱ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሠፈር መሮጥ ጀመረ ። ቀኛዝማች ታፈሰንም ከመንገድ አገኘው ። ለሊቱም አልነጋም ፣ ገና ጨለማ ነበርና ማነህ ፣ ተባባሉ ። ይህነንም ወሬ ነገረው ። ቀኛዝማች ታፈሰም ይህነን በሰማ ጊዜ ከበቅሎ የነበ ረው በፈረስ ተዛውሮ ወደ ንጉሡ ድንኳን በፈረስ ደረሰ ። የንጉሠ ነገሥቱን የእልፍኝ ዘበኞች ተጣርቶ መምጣቱን ወደ ጃንሆይ እሰሙ ልኝ አለ ። አጤ ምኒልክም ይህንን በሰሙ ጊዜ አለጊዜው ስለምን መጣ ብለው ከእልፍኙ ድንኳን ወጥተው ጠየቁት ። እሱም ኢጣሊያ አደጋ ሊጥል ተሰልፎ ጠቅሎ መምጣቱን ተናገረ ። አጤ ምኒልክም ከሠፈሬ ድረስ መጥቶ ተኩስ ካልጀመረ እንግዲህ እኔ ተሰልፌ አል

ወጣም ይሉ ነበርና ስለዚህ እንደወትሮው ሊያስልፈን ነው እንጂ እውነት ይመጣ ይመስልሃልን ብለው መለሱለት ። እሱም ዛሬስ እር ግጥ ነው አለ ። . . . . የጦር ልብሳቸውን ለብሰው ተሰልፈው አዳራሽ ድንኳን ሄደው ተቀመጡ ። የዚህን ጊዜ ነጋ ። እንዲህም እስቲሆን ድረስ ትግሮች በ11 ሰዓት የጀመሩ ይታኮሱ ነበር ። . . . . ይላሉ ።

ሌላው ተራኪ አንቶኒ ሞክለር ነው ። "....በቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ መኳንንት ከመንጋቱ በፊት ተሰብስበው ቅዳሴ ይሰማሉ ። የቤተ ክርስቲያኑ በር ክፍት ነው ። ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ ቅዳሴውን በሚመሩበት ጊዜ ሁለት ጥይት ተተኮሰ ። ይህም ምልክት ነበረ ። በዚህ ጊዜ የሐረርጌው ራስ መኰንን የንጉሡ ታማኝ እንኆት ከቤተክርስቲያኑ ወጡ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተመልሰው ገብተው የኢጣሊያኖችን መምጣት ተናገሩ። ንጉሡም ወሬውን በፀጥታ አዳመጡ ። ከዚያም ራስ መኰንን ወደ አቡኑ ዘንድ ቀርበው በሹክሹክታ ነገሩዋቸ ውና ተመልሰው ከመቀመጫቸው ተቀመጡ ። አቡኑም መስቀላቸውን በቀኝ እጃቸው ይዘው በደከመ አነጋገር 'ልጆቼ ፣ ዛሬ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚገለጽበት ቀን ነው ። ሂዱ ። ለሃይማኖታችሁና ለንጉሣችሁ ተከላከሉ ። ሁላችሁንም ከኃጢአታችሁ እግዚአብሔር ይፍታህ' አሉ ። መኳንንቱም እየቀረበ መስቀል እየተሳለመ ወደ የሠፈሩ ሄደ። . . . ." ይላል ።

እንደ ገብረ ሥላሴ አፃፃፍ ምኒልክ ከቤተ ክርስቲያን ሳይሆን ያደሩትም ፣ ለጦርነት የተነሱትም ከሠፈራቸው ነው ። እንደ አንቶኒ አፃፃፍ ደግሞ ምኒልክ ለጦርነት የተነሱት ከቤተ ክርስቲያን ነው ። እንዲያው ሁኔታውን ለማሳወቅ እንጂ ከየትም ቢነሱ መጨረሻው ስላ ማረ ለአሚታ አያበቃም ። መጨረሻው ባያምር ኖሮ ግን " ሲፀልዩ በማደር ፈንታ ከሠፈር ድንኳን ስላደሩ" ወይም ደግሞ "ከሠፈር ሆነው ጦሩን በማደራጀት ፈንታ ለነፍሳቸው አድልተው ወይም ፈር ተው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲፀልዩ በማደራቸው" ይባል ነበር ። ለሁ ሉም ጉዳይ ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ አብረው ስለነበሩ የእሳቸ ውን መቀበሉ ይሻላል ።

የአድዋ ጦርነት እንዴት ተካሔደ እንበል ። ጠቅላይ ጦር አዛዥ ጀኔራል ባራቲየሪ ጦሩ ከማታው በ3 ሰዓት እንዲንቀሳቀስ ያዘዘው የካ ቲት 21 ቀን ነበር ። በዚህ ቀን ማለት እርብ ማታ ሊንቀሳቀስ የተዘ ጋጀው የኢጣሊያ ጦር ዝናብ በመዝነቡ ምክንያት ቀረ ። የካቲት 22 ቀን ቅዳሜ ብራ ሆኖ ስለዋለ ጦሩ ለሊቱን እንዲንቀሳቀስ አዘዘ ። በተሰጠው የስነ ሥርዓት አካሄድ መሠረት የኢጣሊያ ጦር ጉዞውን ጀመረ ። ከሌሊቱ 11 ሰዓት ተሩብ ሲሆን ጀኔራል ዳቦርሚዳ ባስተላ

ለፈው መልክት ሬቢ ተራራ ደርሻለሁ አለ ። ከሩብ ሰዓት በኋላ በ11 ሰዓት ተኩል ይሄው ጄኔራል ዳቦርሜዳ ከሬቢ ተራራ ምሥራቁን ይዣለሁ ብሎ ላከ ። ደጀን ሆኖ የተላከው ጄኔራል ኤሌና ከሌሊቱ ለ12 ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን "የታዘዝኩበትን ሥፍራዎን ይዣለሁ" ብሎ ላከ ።

በኢትዮጵያውያን በኩል የኢጣሊያ መንቀሳቀስ ወሬ እንደ ተሰማ ራስ መኰንን የሐረርጌን ጦር እየመሩ ገሰግሰው አድዋ ከተማን ያዙ ። ራስ ሚካኤል የወሎን ሠራዊት አስከትለው ሰላዶ የሚባለውን ተራራ ያዙ ። በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የሚመራው የጐጃም ጦር ፊት ለፊት ወደኢጣሊያኖች ምሽግ አመራ ። ራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ እዲ አቡን ላይ የትግራይን ሠራዊት አሰለፉ ። እጨ ምኒልክ ፣ እቴጌ ጣይቱ ፣ ራስ ወሌና ዋግሹም ጓንጉል በስተኋላ ደጀን ሆኑ ። የኦሮሞ ፈረሰኞች 13 ኪሎ ሜትር ያህል ከሚርቅ ቦታ ሁሉ ያሉትን የውሃ ምንጮች እየፈለጉ ከበው ያዙ ።

ሌሊቱን ወታደሩ እየሸለለ ፣ አዝማሪዎችም ማዝመር ጀመሩ ።

"እረ ጉዱ በዛ ፣ እረ ጉዱ በዛ ፣

በጀልባ ተሻግሮ አበሻን ሊገዛ" ይሉ ነበር ። ቄሶችና መነኮሳት መስቀል እየያዙ " . . . . ግፋ ወደፊት " ይላሉ ። ሴቶች ከባሎቻቸው ፣ ሕፃናት ካባቶቻቸው ሥር እየሆኑ ለሊቱን ሲጓዙ አደሩ ። የራስ መንገሻ ሠራዊት ለሊቱን በጄኔራል አልቤርቶኒ ከሚመራው የኢጣሊያ ጦር ጋር እንዳ ኪዳነ ምሀረት ላይ ተጋጥሞ ተኩስ ከፈተ ። ይህም ድንገተኛ ተኩስ የተከፈተበት ምክንያት የአልቤርቶኒ ቀዳሚ ጦር በኰሎኔል ቱሪቶ የሚመራው እንዳ ኪዳነ ምሀረት የሚባለውን ቦታ ሊያልፍ ሲል በመገናኘታቸው ነው ።

ከንጋቱ 12 ሰዓት ተሩብ ሲሆን አልቤርቶኒ ፣ ሌሎቹ ጄኔራሎች እንዲረዱት ጠየቀ ። ወዲያውም ጦሩ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ስለተቋረጠ መረዳዳት ያለመቻሉን ሰማ ። ለአንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን የጄኔራል ዳቦርሜዳ ብርጌድ ፣ አልበርቶኒን እንዲረዳ ታዘዘ ። ረጂው ጦር 800 ሜትር ያህል እንደተጓዘ በኢትዮጵያውያን ተያዘ ፣ በሌላ መንገድ በማርያም ሸዊቶ አልፎ ለመከላከል ጉዞ ሲጀምርም ዶራርና ናስራይ የተባሉት ተራራዎች አጥር ሆነው የዳቦርሜዳን ጦር ከለከሉት ። ሁለት ሰዓት ተሩብ ሲሆን ጄኔራል ባራቲየሪ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ጦሩን ለማበረታታት ራዮ ወደተባለው ተራራ ሄደ ። በዚያም ከእንዳ ኪዳነ ምሀረት የተመለሱ ብዙ የኢጣሊያ ቁስለኞችና የሸሹ ወታደሮች ሜዳውን ሞልተውት በማየቱ ጄኔራል ባራቲየሪ ደነገጠ ። የሸሹትንም እንደገና ወደ ጦርነቱ መለሳቸው ።

በጀኔራል አልቤርቶኒ ውስጥ ያለው 3ኛውና 4ኛው መድፈኛ ብርጌድ መድፍ ይተኩሳል ። ለእያንዳንዱ መድፍም ዘጠና 90 ጥይት ተመድቧል ። ወታደሩ በጠመንጃና በመትረየስ እየተኮሰ በተኩሱ መሬቱን አናውጧል ። ይህ ሁሉ ተኩስ እየተተኮሰ ኢትዮጵያውያኑ በዚያ ሁሉ ተኩስ መሀል ሰንጥቀው እየገቡ የኢጣሊያን ወታደር ፈጁት ። የመድፎቹ ተኩስም ከአንድ ሰዓት የበለጠ ጊዜ አልቆየም ። ኢትዮጵያውያኑ ዝም አሰኙት ። በጥቂት ጊዜ ውስጥም 81 የኢጣሊያ መኰንኖችና 48 ኢጣሊያዊ ወታደሮች ሲገደሉ የተረፈውን ወታደር ኢትዮጵያውያኖች ማረኩት ። የተማረኩት ቁስለኞች ነበሩ ። ያልቆሰሉት ግን ሸሽተው አመለጡ ።

የባታሊዮኑ ጦር መሪ የነበረው ኰሎኔል ጋሊያኖ ፊቱ ላይ ቆስሎ ተማረከ ። በምርኰ ሲሄድም ደከሞት ወደቀ ። ከዚያው ከወደቀበት እንደሆነ ግደሉኝ እንጂ ከዚህ ቦታ አልንቃንቅም በማለቱ ኢትዮጵያውያኑ ጊዜ ላለማባከን ብለው ገድለውት ሌሎቹን ምርኮኞች እየነዱ ሄዱ ።

ሮም ላለው ለኢጣሊያ የጦር ሚኒስቴር የጦርነቱ ዕለት ማለት የካቲት 23 ቀን የተላለፈ አንድ ቴሌግራም አለ ። ቴሌግራሙን ያስተላለፈው የኤርትራ ምክትል ገዥ የነበረው ላምቤርቴ ነው ። ከቴሌግራሙ ባጭሩ እንመልከት ።

"ምፅዋ መጋቢት 2.1896

"አሁን ገና ከአዲ ቀይህ አገር ገዥ አንድ ቴሌግራም ደረሰኝ ። ቴሌግራሙ የሚለው ለ29 ለሊት የሸዋን ጦር በሶስት በኩል ከቦ ለማጥቃት ስለተወሰደው እርምጃ ይገልጣል ። ዝግጅቱም በግራ አልቤርቶኒ አራት ባታሊዮን ጦርና አራት የተራራ መድፍ ይዞ ፣ በመሀል አሪሞንዲ አንደኛውን ምርጥ ብርጌድና ሁለት የተራራ መድፎች ይዞ ፣ በስተቀኝ ዳቦርሚዳ 2ኛውን ብርጌድና አራት የተራራ መድፎች ይዞ፣ ለደጀን የኤሌና ብርጌድ ከመድፎች ጋር ሆኖ ተሰልፈው ነበር ።

"ጦራችን ያለምንም ችግር አድዋ ደርሶ ነበር ። የአልቤርቶኒ ጦር አባ ገሪማ ደርሶ አድዋ ላይ የሠፈረውን ጦር ሊይዝ ነበር ። ወዲያው አበሾቹ ተኩስ ከፍተው አባረሩት ። ሠራዊቱ በሙሉ ሸሸ ። ለመሸሽና ለማምለጥ የበቁት እንኳ የመድፍ ሽፋን እየተሰጣቸው ነው ። ....መድፎቻችን በሙሉ በጠላት እጅ ገቡ ። ይህንንም የቴሌግራም ቃል ለማስተላለፍ ያበቃንና ወሬውን ያመጣልን ከጦርነቱ ቦታ በእግሩ ሸሽቶ እንዲቀይህ የገባው ቫሊንዛኖ ነው ።....ሌላ ቴሌግራም

እንደደረሰኝ ወዲያውኑ እልካለሁ ። ወታደሩ ሁሉ በየምሽቱ እንዲገባ ትእዛዝ አሳልፌአለሁ ።

ላምቤርቲ ።”

በጦርነቱ ጊዜ በኢጣሊያ አገር በሚላኖ ለሚገኙ ጋዜጦች ሁሉ ተወካይ ሆኖ የመጣው አኪሊ ቢዞኒ አገሩ ከተመለሰ በኋላ ሲ.ኤርትሪያ ኤል. ፓሳቶ.ኢ.ኤል. ፕሬዜንቴ በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሐፉ ውስጥ ሲገልጽ “ . . . .ከጧቱ 2 ሰዓት ተኩል ሲሆን ሠራዊቱ በሙሉ ቦታውን እየለቀቀ ሸሸ ። አባ ገሪማና አምባ ሹሉዳ በጠላት እጅ ወደቁ ። ጠላት በመስመር ፣ በመስመር እየሆነ ይመጣብን ጀመር ። በአካባቢው የነበሩ 14 መድፎቻችን እያጣደፉ ይተኩሱ ነበር ። . . . . ጄኔራል አልቤርቶኒ ማጥቃቱን ትቶ ወታደሩ ለራሱ እንዲከላከል ትእዛዝ ሰጠ ። የጠላት ጦር ግን የማይቻል ሆኖ መጣብን ። በግምት 15. 000 የሚሆን ሰው መጣብን ።ንጉሡም ቀይ ጃንጥላቸውን አስይዘው በወታደሩ መሀል ነበሩ ። . . . .ጠቅላላ መድፎቻችንና መትረየስ ተኳሾቻችን ባላቸው ኃይል ሁሉ በየመእዘኑ ይተኩሱ ጀመር ። . . . መድፎቻችን አቅጣጫ እየለወጡ እንዲተኩሱ ተደረገ ። . . . .6ኛውና 8ኛው ባታሊዮን ከቀኝና ከፊት ለፊት ከሚተኮሰው የጠላት ጥይት ከባድ ጉዳት ደረሰበት ።

“ . . . .የጄኔራል አልቤርቶኒ ወታደሮች በሙሉ ተያዙ ። ጠላትም ያን ቦታ አልፎ ወደፊት ገሠገሠ ። 3 ሰዓት ተኩል ሲሆን ሁሉም ተስፋ ቆረጠ ። የቀረን የምንተማመንበት አንደኛው ባታሊዮን ብቻ ነው ። እሱም በእንዳ ኪዳነ ምህረት ላይ ባደረገው ግጥሚያ ብዙ መኰንኖች አለቁበት ። ይህ አንደኛ ባታሊዮን ከሌላ ባታሊዮን በተውጣጡ ወታደሮች ተሞላ ። ወዲያውኑ የጠላት የአበሻ ወታደሮች ደርሰው ያባርሩት ጀመር ። የአሪሞንዲም ብርጌድ ብትንትኑ ወጣ ። በያለበት ሩጫና መበታተን ሆነ ።

“ . . . .ምስጋና ይግባውና 7ኛው ባታሊዮን ሶስት መድፎችን አስተርፎ ነበር ። ሕይወታችንን ለማዳን እነኚያ ሶስት መድፎች እኩል ሰዓት ያህል እንደተተኮሱ በአበሾች እጅ ወደቁ ። . . . .ለደጀን የተቀመጠው 13ኛውና 3ኛ[illegible] ብርጌድ ባንድነት ሆኖ ደረሰልን ። ደህና አድርጐ በአዲስ ጉልበ[illegible] መዋጋት ሲጀምር ልክ 4 ሰዓት ተኩል ሲሆን ከአበሾቹ ጦር የ[illegible]ረሰኛ መጣና ወረረው ።ከዚህ በኋላ የኛ ወታደሮች ፀጥ አሉ ። [illegible]ችንም ዓጥታው ነገሠ ። . . . .” በማለት በሰፊው ጽፏል ።

ረፋዱ ላይ ጄኔራል ባራቲየሪ ተማረከ ። ጄኔራል ባራቴየሪ በኋላ ጊዜ ተለቆ አገሩ ከገባ በኋላ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥቶ ነበር ።

“. . . . ጀኔራል አሪሞንዲ ጉልበቱን ተመትቶ ወደቀ ። ኢትዮጵያውያን ሊማርኩት ሲመጡ በጉራዴው እየተከላከለ አልማረክ ቢል ገደሉት። እኛ የሰለጠነው ዓለም ሥልጡን ወታደሮች ፣ ምንም እያውቁም ከሚ ባሉት ኢትዮጵያውያን የምንማረው ትምህርት አለ ። አበሾች ለባሩ ድና ለጥይት ይሳሳሉ ። የሚገድሉ ካልሆነ በስተቀር አይተኩሱም ። ለዚያውም ቢሆን አስርና 15 ያርድ ያህል ቀርበው ባንድ ጥይት ደራርበው መግደል ይፈልጋሉ ። ያለዚያ ተደበላልቀው በጉራዴ መምታት ይመርጣሉ እንጂ ጥይት ማበላሸት አይወዱም ። ይህም በማ ስጮህ ብቻ ጥይት ለሚያባክነው ለሰለጠነው አገር ወታደር ጥሩ ትምህርት ነው ። ለምሳሌ ደጀን የነበረው የመድፈኛው አዛዥ ካፒ ቴን ፍራንዚኒ መድፎቹን ይዞ ከጦር ሜዳ እንዲገባ ታዘዘ ። 30 ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዞ ከጦሩ ሜዳ ገባ ። ቦታውን አመቻችቶ አንድ የመ ድፍ ጥይት ገና እንዳስተኰሰ ተገደለ ። ይህም ሊሆን የቻለው ያቺን የመድፍ ጥይት ድምፅ የሰሙ ኢትዮጵያውያን በንዴት ተሞልተው በብዛት ሆነው ስለወረሩት ነው ። የተመካንባቸው ፣ ደጀን የነበሩት መድፎቻችንም ካንድ ጥይት ተኩስ በኋላ ተማረኩ ። . . . .” በማለት መግለጫ ሰጥቷል ።

ካፒቴን ሚናሪኒ ለአንድ ወዳጁ የፃፈው ደብዳቤ ሚላኖ ውስጥ በጋዜጣ ታትሞ ወጥቶ ነበር ። “. . . . ከቀትር በኋላው ጦርነት ተዳከ ምን ። ከጧቱ ጀምሮ መድፎቹ ይተኮሱ በነበረበት ቦታ ጀኔራላችን ብቻውን ሽቅብ ቁልቁል ይላል ። ተናዷል ፣ ተበሳጭቷል ። ‘ቀላል አይደ ለም ፣ ቀላል አይደለም’ እያለም ብቻውን ይነጋገራል ። አንዳንዴም ወደኛ ወደ መኰንኖቹና ወደ 6ኛው ሬጂሜንት አዛዥ ወደ ኰሎኔል አይራጊ ዞር እያለ ሳቅ እንደማለት ፈገግታ ያሳየናል ። ከጧት ጀምሮ ከጠቅላይ ጦር ሠፈር እንዴት መልእክት አይደርሰንም ? እነ ሱም በሕይወት ያሉ አይመስሉኝም ይለናል ። የመጨረሻችን መጀመ ሪያ መሰለን ። ውሃ ጥሙ ፣ ረሀብ አሰቃየን ። እሾክ ውስጥ ገብቶ ሰው እንዴት ይዋጋል ! ለእያንዳንዳችን ሶስትና አራት ጠላት ተሰል ፎብናል ። እንዴት ይቻላል ? . . . .” በማለት ጽፏል ።

ሉል ካፓ አድዋ በሚባለው መጽሐፍ መቶ አለቃ ሮፓ በኢጣ ሊያኖች ዘንድ እጅግ በጣም በጀግንነቱ ስለታወቀውና ስለተከበ ረው ስለ ኰሎኔል አይራጌ እሚሚት ሲገልጽ “. . . . ጦራችን እንዲ ያጠቃ ስድስት ጊዜ ጦሩን በጀግንነት ወደፊት መርቷል ። ኢትዮ ጵያውያን ግን መለሱን ። አንዳንድ ጊዜም ጦሩን የሚመራው ፈረሱ ላይ እየሆነ ነበር ። ሁለት ፈረሶችም ከጭን ሥር እየተመቱ ሞተዋል። በመጨረሻው ጊዜ በቅሎው ላይ እወጣለሁ ሲል ግራ ጐኑን ተመታ ። ጥይቷ በአካሉ ሾልካ ሄደች ። ሲወድቅ ያዩት የኢጣሊያ ወታደሮች

ሊያነሱት ተሯሩጠው ሄዱ ። እሱም እያቃሰተ እኔ ሽማግሌ ነኝና ተዉኝ ። ከዚሁ ከጠላቶቼ ፊት እሞታለሁ ። እናንተ ግን ወጣቶች ናችሁና ከዚህ መአት ራሳችሁን አድኑ ብሎ ወደፊቱ ተደፋና ሞተ ....” ሲል አትቷል ።

ካፒቴን ሞልቴዶ በፃፈው ደግሞ “. . . . ከአራተኛው ባታሊዮን አንድ የሸሸ የሱማሌ ወታደር ወደካምፓችን ሲሮጥ መጣ ። ካለሁበት በራፍ ላይ ሲደርስም ወደቀ ። የኛ ጦር ደጀን ነበር ። በአረብኛ ቋን ቋም ነገሩ ምንድነው ? ምን ሆንክ አልኩት ። አለቁ ፣ ሞቱ አለኝ ። የወ ታደሩ ጠርቡሽ (ባርኔጣው) ካጠገቡ ወድቋል ። ጠርቡሹን አቧራና ላብ በክሎታል ። ኮቱ የመድፈኞች ኮት መሆኑን ባውቅም ፣ ምልክት ያለበት የኮቱ እጅጌ ተገንጥሎ ስለሌለ ከየትኛው መድፈኛ ክፍል እንደሆነ ላውቅ አልቻልኩም ። በዚያ ክንዱ ላይም ከፉኛ ስለቆሰለ ደሙ በብዛት ይወርዳል ። ዙርያውን ከብበን በጥያቄ አጣደፍነው ። አንጌራ ፣ ማንፍሬዲኒ ፣ ቶዚሊ ፣ አስካላ እያለ ይቃዣል ።

“ምንድነው የምትለው ! አልኩት

“ሰላም መቶ አለቃ ። አበሾች ደርሰዋል ፣ እዚህ ናቸው ። የአራተ ኛው ወታደር ሁሉ አለቀ ። ሁሉም ሞቱ ። ማጆር ቶዚሊ ሞተ ። አን ጊራ ሞተ ። ማንፍሬዲኒ ሞተ ። ሁሉም ፣ ሁሉም ሞቱ አለኝ ።

“ንገረን እንዴት ሞቱ ? አልኩት ።

“ዛሬ ጧት ። አበሾቹ ብዙ ነበሩ ። ግማሹ ያህል ሞተ ። ሌሎቹ ግን መጡብን ። መድፍ ይተኮሳል ። ጥይት ይተኮሳል ። አበሾቹ ግን መጡብን ። እህ ስንትና ስንት መሰሉህ ።

“በማን ውስጥ ነበርክ ? አልኩት ።

“ማንፍሬዲኒ ውስጥ ።

“አይተሃል እሱን ?

“አዎን አይቼዋለሁ ፣ ሞቷል ።

“አስካላንስ አይተኸዋል ?

“አዎን አይቼዋለሁ ፣ ሞቷል (አስካላ ግን ቆስሎ ተማርኳል) ሁሉንም አይቻለሁ ። ሁሉም ሞተዋል ። ታመልጡ እንደሆነ እናንተም አምልጡ ። አበሾቹ ከኋላዬ ናቸው ። ጥፉ አለን የሱማሌው ወታደር ....” ሲል ጽፏል ።

ኢትዮጵያውያኖችስ የኢጣሊያን ጦር ድል ያደረጉት እንዴት ነበር ? አለቃ ተክለሥላሴ ባልታተመው መጽሐፋቸው ሲገልፁ “. . . .

ያንግዜ የኢጣሊያ ጦር ወጨፎ ሲተኩስ እረሩን በሰማይ ላይ የሚ ሄድ አንበሳ ያስመስለው ነበረ ። የሰልፉም ሥርዓት ፤ ሲራመድ አንድ ጊዜ ፤ ጥይት ሲያጐርስ አንድ ጊዜ ፤ ሲተኩስ አንድ ጊዜ ፤ ሲገል ተራውን ሰዉንም ዛፉንም ይበጣጥሰው ነበረ ። የመድፉ አረር በሰማይ ሲሄድ የተወረወረ ኮከብ ይመስል ነበረ ። ምድር ከነካ በኋላ እንደ ገና ፈንድቶ ሰው ይገል ነበረ ። የመድፉ ጥይት ዋንጫ ያህል ነበረ ። ኋላም ቀለሃውን ገረድ ለውሃ መቅጃ አደረገችው . . . . እግረኛው እሮ ጣለሁ ሲል ጫማው እየከበደው ፤ አውልቆ እንዳይሮጥ እቀበትና ቁል ቁለት ጠጠር እየወጋው ፤ የኋሊት እየተኰሰ እሮጣለሁ ሲል ከእን ዝርት የቀለለ የጁየ ፤ ከነብር የፈጠነ ቤጌምድሬ ፤ ከቋንጣ የደረቀ ትግሬ ፤ ከአሞራ የረበበ ሸዌ ፤ ከንብ የባሰ ጐጃሜ እያባረረ በየጐዳ ናው ዘለሰው ። አውሬ የነጨው ነጭ መጋዣ እየመሰለ በየዱሩ ሆዱን ገልብጦ ወደቀና የአሞራ ቀለብ ሆነ ። . . . . የመጣው መድፍ ሁሉ ከነጥይቱ ፤ ከነመንኩራኩሩ በየመንገዱ እየወደቀ ተገኘ ። ከአንድ ሥፍራ 18 መድፍ ፤ በተረፈ አምስትም ሶስትም በየመንገዱ እየወደቀ ተማረከ ። እሩቅ ድረስ የሄደው አባራሪ በነጋታው ከሠፈር ገባ ። ከቅ ርብ የተመለሰው አባራሪ ማታ በጨለማ ከሠፈር ገባ ። የማረከውም እየማረከ ፤ የገደለውም እየገደለ እየፎከረ እያቅራራ ገባ ። ያን ቀን ጦር ነቱ ብርቱ ነበረ ። በነግህ ተኩስ የተጀመረ ማታ ተለያየ ። ያን ቀን ከአማራው ከኢጣሊያውም እየቆሰለ እሚያነሳው እየታጣ ሐሩር እየያዘው በውሃ ጥም ሲጨነቅ ከየደገላው እሳት እየተነሳ አቃጥሎ ፈጀው ። ያን ጊዜ መንገዱ ባይከፋ ፤ ሠራዊቱ በረሃብ ባይጐዳ ፤ አማራ ጨክኖ ቢከተል ኖሮ ጣልያን አንድ ለዘር አይተርፍም ነበር ። እስ መራን አስለቅቆ ከጥንት ሀገሩ ይሰደው ነበረ ። ይህም ስለሆነ የኢጣ ሊያ ጦር ብርቱ ነበረ ። የብርታቱ ብርታት ቅዳሜ ለሊት በዚያ በከፋ በትግሬ መሬት በጨረቃ ፤ በጠጠር ፤ ባቀበት ፤ በቁልቁለት የጥይት ኮረጃውን ፤ የውሃ ታኒካውን ተሸክሞ እንቅልፍ አጥቶ ሲጓዝ አድሮ ሲነጋ ተኩስ ጀመረ ። ሲዋጋ ውሎ ማታ ተመልሶ ሲሄድ አድሮ አገሩ መግባቱ ያስደንቃል ። እንኳን በመከራ በደስታ ቢሆን ሁለት ለሊትና አንድ መአልት ከራብና ከጥም ጋራ አይቻልም ።. . . .” ብለዋል።

ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገብረ የሱስ ደግሞ “ዳግማዊ አጤ ምኒ ልክ” በሚባለው መጽሐፋቸው “. . . . ወታደሩ ለሊቱን ሙሉ በጀር ባው ከባድ ኮረጆውን ፤ በጫንቃው ጠበንጃውን ፤ በቀኝ ጐን የጥይት ከረጢቱን ፤ ተግራ ጐን የውሃ ታኒካውን ተሸክሞ የገረረ ከባድ ጫማ ውን እስከ ጉልበቱ አጥልቆ ድልቀፍቀፍ እያለ በዚያ ጭንጫ ፤ በዚያ ሙቀት ፤ በዚያ አቀበትና ቁልቁለት ፤ ያ ሁሉ ፈረንጅ ፤ ያ ሁሉ ጐበዝ ያ ሁሉ ወጣት ልጅ ባገሩ እንዲያ ሲያምርበት በሰው አገር ላሊበላ

ሳሚ መስሎ ኮርፈፍ ፣ ኮርፈፍ ሲል .... ሲማስን ፣ ሲደክም ፣ ሲንደ
ላቀፍ አድሮ .... ሲነጋጋ አባ ገሪማ ደረሰና መድፉን ጠመደ.... ጦርነት
ተጀመረ ። ከዚያማ ወዲአ ምን ያነጋግራል ። ኢትዮጵያዊው .... እደጋ
እንደተጣለበት ባየ ጊዜ የቻኮለ በሴጣው ፣ ያልቻኮለ በኮርቻው እየ
ተሰካ እየፈከረ ፣ እየተንደቀደቀ ገባበት ። ....የቀረው ግን ገና እንቅል
ፉን አላሳብ ተኝቶ ነበረ ። የኢጣሊአ መድፍ ነው በማለዳ የቀሰቀሰው ።
.... የሸዋ ፈረሰኛ ፣ የጐጃም እግረኛ ፣ የትግሬ ነፍጠኛ ፣ ያማራ ስል
ተኛ ከቦ ያናፋው ፣ ይቀላው ያንደገድገው ጀመረ ። ....ከእንዝርት
የቀለለ የጁዬ ፣ ተነብር የፈጠነ በጌምድሬ ፣ ተቋንጣ የደረቀ ትግሬ. ...
ፈጀው ፣ አሰጣው ፣ ዘለሰው ።.... ወደኋላ ቀርቶ የነበረው ሁሉ ነገሩን
ሳያውቅ ወደ ጦርነት ሲጓዝ ነበረ ። ነገር ግን የጀኔራል ባራቲየሪን
መሸሽና የጦሩን መፈታት ባየ ጊዜ ያ ሁሉ ወደኋላ የነበረ ኢጣሊያ
መድፈኛ መጫኛውን በጐራዴ እየቆረጠ ፣ መድፉን እየጣለ ፤ በመድፉ
ሥፍራ እሱ እየተተካ በአጋሰሱ እየጋለበ እስመራው ገባ ። ካንድ ላይ
ብቻ 18 መድፍ አንድ ጊዜ ሳይተኮስ እስከ ጥይቱ እስከ መንኮራኩሩ
ወድቆ ቀርቶ ተያዘ ።....” ብለዋል ።

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ደግሞ “....ሠራዊቱ ቀለብ ሊያ
መጣ የሄደው ፣ አክሱም ጽዮን ቤተክርስቲያን ሊስም የሄደው ....
ሁለት እጁ ነው እንጂ ፣ አንድ እጁ ለጦር አልደረሰም ። የተኩሱን
መድመቅ የሰማ ጊዜ ሠራዊቱ ተሰልፎ ተነሳ ። አጤ ምኒልክም ከበ
ቅሎ ወጥተው ወደሱ መንገድ ጀመሩ ። ሰልፉ ግን ጌታው ከሎ
ሌው ፣ ጭፍራው ከአለቃው አልተገናኘም ። በየፊቱ ክምር እንዳየ
ዝንጀሮ ወደጦሩ ፣ ወደመድፉ ይሮጥ ነበር ። ....መድፉ ይመታኛል ፣
ነፍጡም ይጥለኛል ፣ እሞታለሁ ብሎ ልቡ አልፈራበትም ። ....የቆሰለ
ውም ሰው አልጋው ይቁም እንጂ ኋላ ስትመለስ ታነሣኛለህ ፣ በመሐ
ይም ቃሌ ገዝቼሃለሁ ይለው ነበር ። እይርም ያለቀበት እንደሆነ የቆ
ሰለውን ሰው ከወገቡ ዝናሩን እየፈታ እያባረረ ወደፊት ይተኩስ
ነበር ። ሰውም ከመንገድ ርዝመት ፣ ከተኩስ ብዛት የተነሣ ደክሞት
የተቀመጠ እንደሆነ የምኒልክ ወሮታ ፣ የጮማው የጠጁ ይህ ነውን
እየተባባለ እንደገና እየተነሣ ይዋጋ ነበር ።

“ከሌሊቱ 11 ሰዓት የጀመረ እስከ 4 ሰዓት ድረስ ተኩሱ አላባ
ራም ። ድምፁም እንደ ሐምሌ ዝናም እንደማያባራው ነበረ ።....የተኩሱ
ጢስ ብዛት የሁለቱንም ወገን ለሰልፈኛው ሁሉ ከዛፍ ሥር ከጥላ
እንደተቀመጠ ሆኖለት ዋለ ። ባይናችን እንዳየነው ፣ በጆሮአችን
እንደሰማነው መፃፍ አይቻለንም ።....አጤ ምኒልክ የፊተኛውን ጦር
ድል ካደረጉ በኋላ ወደፊት ተጓዙ ። በላላውም በኩል ጦር እየጨ
መሩ ተከተሉት ። በዚህ ጊዜ 5 ሰዓት ሆኖ ነበር ።....ዘጠኝም ሰዓት

በሆነ ጊዜ ያጼ ምኒልክ ሠራዊት ቁስለኛውን የማረከውንም ኢጣሊያ እየያዘ ይመለስ ጀመረ ። አጤ ምኒልክ ግን ከጦሩ አልተመለሱም ነበር ። እቴጌም ሠራዊቱ ብዙ ብዙ እየሆነ መመለሱን ባዩ ጊዜ ንጉሥ ሳይመለሱ የት ትሄዳላችሁ ። የቆሰለውንም ሰው እኔ ካለሁበት አሳ ርፉት ፤ እናንተም ተመለሱ ብለው አስለፈፉት ።

"የእቴጌ እህት ወይዘሮ አዛለች ከሰልፉ አብራ የነበረችው ሰዉ እየማረከ እየገደለ ሲመለስ ባየችው ጊዜ . . . . አድዋ ቤት አለህን ፤ ንጉ ሥህን ፤ ጠጅህን ፤ ጮማህን ትተህ ወዴት ትመጣለህ እያለች ለፈፈ ችው ። ከዚህ በኋላ እቴጌ ምነው ጦሩ አልተፈታምን ፤ ቀኑ መሸ ብለው አንድ ጉልማሳ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ላኩ ። አጤ ምኒልክም በግራ ሲተኩስ እሰማለሁ እንጂ በዚህ ያለው አልቋል ብለው ልከው ወደ ሠፈር ምላሽ አደረጉ ። . . . . ምሽት ሆኖ ለዓይን አይታይም ነበር ። . . . ." ካሉ በኋላ በአድዋ ጦርነት የሞቱትን የጥቂት ጀግኖች ስም ይናገራሉ ።

ታሪኩን እናሳጥረውና በአድዋ ጦርነት 7560 ኢጣሊያውያንና 7100 ጥቁር ወታደሮች ሲገደሉ 954 ኢጣሊያኖች ጠፍተዋል ። 470 ኢጣሊያውያንና 958 ጥቁር ወታደሮች በጠቅላላው 1428 የጠላት ወታደሮች ቆሰሉ ። 11.000 ጠመንጃና የነበሩዋቸው 56 መድፎች በሙሉ ተማረኩ ። በኢትዮጵያውያን በኩል 7000 ሞቱ ። 10.000 ሰዎች ቆሰሉ ።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ይህን ድል ካገኙ በኋላ ለሩስያው ንጉሠ ነገሥት ዊልያም ፤ ለሮም ሊቀ ጳጳስ ሊዮን 13ኛ ፤ ለእስፓኙ ንጉሥ አልፎንሶ 13ኛ ፤ ለፓርቱጋሉ ንጉሥ ለቀዳማዊ ቁርሎስ ፤ ለስዊስ መንግሥት ሪፑብሊክ ፕሬዚዳንት ፤ ለቤልጅግ ንጉሥ ዳግማዊ ሎዎ ፖልድ ፤ ለፈረንሣይ መንግሥት ፕሬዚዳንት ለሙሴ ፌሊክስ ፎር እና ለሌሎችም መንግሥታት የሚከተለውን ደብዳቤ ፃፉ ።

" . . . . ኢትዮጵያ ነፃነትዋን ራስዋን የቻለች መንግሥት ፤ ባጠገብ ዋም ጐረቤት የሌላት መሆንዋ አስቀድሞ በኤሮፓ ነገሥታት ሁሉ የታወቀ ነው ። ከግራኝ ጀምሮ እስካሁን በአህዛብ እጅ ተከባ ዘወትር በጦርነት ድካም ነው ኑሮአችን ። ከኤሮፓ ጦር መሣሪያ አስመጥቼ ሠራዊቴን ዘወትር ከጦርነቱ ድካም አሳርፋለሁ ስል ከንጉሥ ኡምቤ ርቶ አባት ጋር የፍቅርን ነገር ጀመርኩ ። ንጉሥ ኡምቤርቶም መንግ ሥት በያዙ ጊዜ እኔም እንዳባቴ ፍቅርን እወዳለሁ ብለው ቢልኩ ብኝ እኔም እንዳባትዎ ካፈቀሩኝ እሺ ብዬ ፍቅርን ተቀበልኩ ።

"ከንት አንቶኔሊ የሚባል የኢጣሊያ ሰው በገንዘብህ ጠመንጃ ልግዛልዎ ቢለኝ ብዙ የዝሆን ጥርስና ወርቅ ሰጥቼው ይዞ ሄደ ።

ከንጉሥ ኡምቤርቶ አስፈቅዶ ገዠቀልኝ ሲያመጣ ከመንግሥት ፈቃድ ሙግገኘቱ እጅግ ደስ አለኝ ። 2ኛም ንጉሥ ኡምቤርቶ ኮንት አንቶኔሊን የመንግሥት መላክተኛ አድርገው ወደኔ ሰደዱት ። ተልኮ ያመጣውም ቃል ይህ ነው ።

"ነጋዴም እንዲነግድ ፣ የጦር መሣሪያ እንዳይከለከል ይፈቀድልዋል ። እርስዎም ባርያ እንዳይሸጥ ያስከልክሉ ፣ በሌላ መንግሥትም ያለ መሥሪያ ሁሉ ብትፈልጉ በኛ በር ይወጣላችኋል ፤ አይከለከልም ። እንደ ኤሮፓ ሥራት የተጠላው ውል ባምስት ዓመት ይለወጣል ። የተወደደው ይረጋል ። ምጥዋ ሐሩር ሆኖብናል ። ለሰዎቻችን ማሳረፊያ ጥቂት ነፋስ ያለበት ሥፍራ እንዲሰጠን የፍቅርን ውል ይህን እናድርግ ብለዋል አለኝ ። እሺ ይሁን ብዬ እኔም ለመንግሥቴና ለኔ የሚስማማና የሚጠቅም ቃል ባማርኛ በትክክል አስደርጌ አስጥፌ ብሰጠው 17ኛው ክፍል ላይ ቃሉን በኢጣሊያ ቋንቋ ለውጠው ከጥንት ጀምሮ ነፃ የነበረውን መንግሥቴን የሚያዋርድ የማይስማማኝ ቃል ቢሆንብኝ እኔ ባስጣፍኩት ባማርኛው ቃል ይርጋ ፣ የኢጣሊያው ቋንቋ ከኔ ካማርኛው ጋራ ያልተካከለ ነው ። አሁንም በትክክል እና ድርገው ብዬ ወደ ንጉሥ ኡምቤርቶ ብልክባቸው ምላሽ ሳይሰጡኝ ቀሩ ። እኔም ነገሩ ለተንኮል እንደ ሆነ አውቄ የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ አስቀድሜ ለኤሮፓ ነገሥታት ሁሉ ከንጉሥ ኡምቤርቶ በውል ነገር እንዳልተስማማን አስታወቅሁ ። የእውነት ፍርድ አገኛለሁ ስል ።

"2ኛም አምስት ዓመት ሲደርስ የጠላነው እንዲቀር ፣ የወደድነው እንዲረጋ ሰው ይላኩልኝ ብዬ ብልክ እስከ ወረቀቱም ምላሽ አስቀሩት ። ከዚህ ወዲህ ይልቅ ከፋው ነገር እየበረታ ሄደ ። አሽከሬን ደጃች መሸሻን አለ ፍርድ አሰሩት ። ልክ አስበጅቼ የሰጠኋቸውንም አገር አልፈው የሾምኩትን ሹም ራስ መንገሻን ወግተው አባረው አገሬን ትግሬን በሙሉ ያዙት ። ከዚያ አልፈው ላስታ መሬት እስከ አሸንጌ ድረስ መጡ ። ከዚህ ወዲያ አገር የሚጠብቁ መኳንንቶች ከኔ ብሰድ አላጌ ላይ በር ይዘው ቆይተው ተዋጉዋቸው ። የእግዚአብሔር ኃይል በኔ ሰዎች አድሮ ድል አደረጋቸው ። እኔም ወደዚያው ተከትዬ ብሔድ መቀሌ እርድ ገብተው አገኘሁ ። ጦርነት ከሆነ ከትልቁ ጋር እዋጋለሁ ። እናንተ ክርስቲያኖች በውሃ ጥም አትለቁ ብዬ እስከ መሣሪያቸው ክርድ አስወጥቼ ለጀኔራል ባራቲየሪ ሰደድኩለት ። እኔም ከዚያ ተጉዤ አድዋ ከተማዬ ሠፍሬ ጀኔራል ባራቲየሪ እውነት የመሰለ የእርቅ ቃል ላከብኝ ። እኔም እርቅ ከፈለጉ ብዬ ሠራዊቴን ቀለብ ሰድጂ ሳለ እንደ ኤሮፓ ነገሥታት ሥራት ሁሉ ጠብ መፈለጋቸውን ሳያስታውቁኝ እንደ ወንበዴ ሥራት ለሊት ሲገሰግስ አድሮ ሲነጋ ግንባር ካደረው ዘበኛ ጋር ጦርነት ዠመረ ።

"ጥንት ከአህዛብ ካረመኔ አገራችንን ጠብቆት የሚኖር አምላክ ከኛ ባይለይ በእግዚአብሔር ኃይል ድል አደረግኋቸው ። ከዚያ ሄጄ አስመራንም የኔን አገር ሁሉ በሙሉ አስለቅቃለሁ ብዬ ተጉዤ ሳለሁ ጀኔራል ባልዲሴራ በኢጣሊያ ሠራዊት ሁሉ ላይ ተሹሞ መጥቻለሁ ። ንጉሥ ኡምቤርቶም ሲሰዱኝ እርቅ ነውና የምፈልግ እርቅ አድርግ ብለውኛል ብሎ በማጆር ሳልሳ ወረቀት ቢልክብኝ እኔ በወደድኩት ከታረቃችሁ የሚስማማኝም ቃል ከሆነ እውነተኛ ሰው አዲስ አበባ ከተማዬ ድረስ ይምጣና ይጨርስ ብዬ እኔም ወደ ከተማዬ ተመለስሁ ።

"እስካሁን በትግሬ አለሥራት ያለቀው መኳንንትና ባላገር ለኤሮፓ ነገሥታትና መኳንንት ሁሉ የተደረገውን ግፍ አመለክታለሁ ። የኢጣሊያ ገንዘብ በላያችን ላይ የለብን ፣ ለአገራቸውም ድንበራችን የራቀ ነው ። አለም ከተፈጠረ ጀምሮ ነፃነቷን ራስዋን የቻለች መንግሥት የሆነውን በተንኰል ሊወስዱት እንዴት ይቻላቸዋል ። ይህን የግፍ ፍርድ በሙሉ ልቦናዎ በውል እንዲመለከቱት ተስፋ አለኝ ። ኢጣሊያኖች ግን ይህንን ሁሉ ግፍ ሲያደርጉብኝ እነሆ እኔ የማደርገው የነበረ እነሱን ማክበር ፣ ሲመጡ በሥራት መቀበል ፣ ሲመለሱ በሥራት ማሸኘት ፣ ደግሞ በተሰጠኝ ሥልጣን ሁሉ የባርያን ንግድ ሁሉ መከልከል ። በእኔ መንግሥት አፈንዲ መሐመድ ብ.ኛ የባርያ ንግድ አልተው ቢለኝ ስለዚህ አውሳ ጦር ሰድጄ አስ..ጋሁ ። ይህ ፈቃድ የኔ ብቻ አይደለም ። የመላ የኤሮፓ እንደሆነ አውቃለሁ ።

በመጋቢት ፳፫ ቀን በመቀሌ ..ፈር ተፃፈ በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም.

እንቲጦ ።"

የአድዋ ድል ከተገኘ በኋላ አጤ ምኒልክ ሠራዊታቸውን እየመሩ ለምን ወደ ኤርትራ ወይም ወደሐማሴን ተሻግረው ኢጣሊያን አላባረሩም ? የብዙ ሰው ጥያቄ ነው ። ምኒልክ ከአድዋ ድል በኋላ እንዲያውም ከአድዋ ጦርነት በፊት ወደ ኤርትራ ለመግባት ወስነው ነበረ ። ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ እንደፃፉት ኢጣሊያኖች ከአድዋ ጦርነት በፊት ከምሽጋቸው አልወጣ ብለው ባስቸገሩ ጊዜ ". . . . ከአድዋ ወደ አሥመራ ለመውረድ ለዚያ ሁሉ ሠራዊት የሚበቃ ቀለብ ባለመገኘቱ ተመክረና አድዋ ላይ ዝም ብለው ግፋን እስቲሄድላቸው ተቀመጡ ። . . . ." ብለዋል ። በዚሁ ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ ፀሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ሲገልጡ ". . . . ረብዕን ሐሙስን ሲመከር ከእርዱ ቢወጣልን እንዋጋለን ። ባይወጣም ወደ ሐማሴን እንግዝ ተብሎ ቁርጥ ምክር ተመከረ ። . . . ." ብለዋል ።

ከአድዋ ድል በኋላም ቢሆን ይሄው ወደ ሐማሴን ወይም ወደ ዛሬው ኤርትራ መዝመቱ ሀሳብ አልቀረም ነበር ። የቀረበት ምክንያት ግን ፕሮፌሰር አፈወርቅ እንደሚሉት “. . . . ያዲግራትን ምሽግ ሰብ ረው ቀጥለው ወደ መረብ ለመቆልቆልና አስመራ ያለውን ጦር እስከ ባህር ለማባረር አሰቡ ። ኋላ ግን ሠራዊታቸው ሁሉ ሶስት ወር ሙሉ ትግሬ ላይ በረሃብ ተጉድቶ ነበርና ከርሞ ለመመለስ ወደሸዋ ተመ ለሱ. . . . ” አለቃ ተክለ ሥላሴም ምክንያቱ ይሄው የረሃቡ ጉዳይ መሆ ኑን ሲፅፉ “. . . . ያን ጊዜ የኢጣሊያን ጦር እስከ ምፅዋ ሊያባርሩ ሞክ ረው ነበር ።ግን ሠራዊቱ ሶስት ወር በረሃብ ተጐድቶ ነበርና ተቸገሩ ። በሞተው ተክተን ፥ የከሳውን አወፍረን ከርሞ እንመለስ አሉና ተመ ለሱ . . . . ” ብለዋል ።

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ስለዚህ ጉዳይ ከአድዋ ድል በኋላ ምን እንደታሰበ ሲገልጡ “. . .እንቲጮ ሠፍረው ወደ ሐማሴን የሚ ያስኬደውን መንገድ ሲያሰልሉ መሰንበቻ ሆነ ። ከዚያም ላይ ሳልሳ የሚባል የኢጣልያ ሹም በጦርነቱ ያለቁትን ኢጣሊያኖች ልቅበር ብሎ ለማስፈቀድ መጣ ። ከመጣም በኋላ ወደ ጃንሆይ ቀርቦ የኢጣ ሊያ መንግሥት ከጃንሆይ ጋር እርቅ ወዷልና ከንጉሥ ኡምቤርቶ ዘንድ ባለማህተም ደብዳቤ እስኪመጣ ድረስ ወደ ሐማሴን አይሻ ገሩ ። ጦርዎን ያቁሙልን ብሎ ለመነ ። . . . . ” ብለዋል ።

ከጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ትረካ የተለየ ሆኖ የምናገኘው ምኒልክ ማስለላቸውንና የሳልሳን ወይም የኢጣሊያን መንግሥት ልመና ነው ። በዚያን ጊዜ አጤ ምኒልክ ጥሩ ጥሩ ሰላዮች ነበሩዋ ቸው ። ሰላዮቻቸውም አብዛኛዎቹ በኢጣሊያኖች ዘንድ ታማኝነት የነበራቸውና የኢጣሊያ ሰላይ የሆኑ ሐማሴኖች ነበሩ ። በተለይ በዚህ ጊዜ የኢጣሊያን ምስጢር ዘርዝረው ለምኒልክ የነገሩት ሐማሴኖቹ አቶ ገብረ እግዚአብሔርና ባሻ አውአሎም ናቸው ። ስለነኚህ ሁለት ሰዎች ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ባልታተመውና “ከሳባ እስከ አድዋ ጦርነት” በሚባለው መጽሐፋቸው ሲተርኩ “. . .ኢጣሊ ያኖች በእንቲጮ ሠፍረው ሳለ ገብረ እግዚአብሔርና ባሻ አውአሎም የሚባሉ ሰላዮች አበጅተው ነበርና እነዚያ ወደ አድዋ እየመጡ በአጤ ምኒልክ ሠፈር ያዩትንና የሰሙትን ሁሉ እየወሰዱ ለጀኔራል ባራቲየሪ ይነግሩ ነበር ። ቢሆንም ትውልዱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰው ሁሉ ላገሩ ነፃነትና ለንጉሡ ክብር ተቆርቋሪ ነውና ምንም ከኢጣሊ ያኖች ገንዘብ ቢቀበሉ ልባቸው እናታቸውን ኢትዮጵያን ፥ ንጉሣቸ ውን አጤ ምኒልክን አልከዳም ነበርና ከኢጣሊያኖችም ያዩትንና የሰሙትን እያመጡ በራስ አሉላ አቅራቢነት ለአጤ ምኒልክ መን ገር ጀምረው ነበር ። እነዚህ ሁለቱ ሰላዮች. . . . ጀኔራል ባልዲ ሴራ የሚ

ባል ከብዙ ሠራዊት ጋር ከኢጣሊያ አገር መጥቶ ምፅዋ ገብቷል .... እንዲጠነቀቁበት ይሁን ብለው ልከው ነበር ። ....'' በማለት ከአድዋ ጦርነት ድል በኋላ ምኒልክ ወደፊት የገፉ እንደሁ በማለት በባልዲ ሴራ የሚመራ አዲስ ጦር መምጣቱን መግለጣቸውን ጽፈዋል ።

ካቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ መጽሐፍ ደግሞ ስለዚሁ ጉዳይ ከአጤ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሚባለው ብናይ ። .... በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ይህንን ጠላታቸውን ከአስመራ አስወጥቶ ባህ ርን አሻግሮ ማባረር በአሳባቸው ውስጥ ሳይመጣባቸው አልቀረም ነበር ። ነገር ግን በቅርብ ጊዜ አቅንተው ወደ ኢትዮጵያ የጠቀለሉ ትን ጥንትም በኢትዮጵያ ንጉሥ ይገዛ የነበረው የያገሩ ነገድ ከኢት ዮጵያ አንድነት ለመለየት የአጤ ምኒልክ ከውጭ መንግሥት ጋር በጦርነት መዳከም ይረባው እንደነበር ግልጽ ነው ። ....

"የኢጣሊያ መንግሥት ምንም እንኳ አድዋ ላይ ድል ቢሆን እስከ ምጥዋ ድረስ አባረው ከአስመራ ሊያስወጡኝ የፈለጉ እንደሆነ ደግሞ አንድ ጊዜ ሳልዋጋ አስመራን አለቅም በማለት ለዚሁ በአ ድዋ ጊዜ ጠቅላይ የጦር አዛዥ ከነበረው ከጀኔራል ባራቲየሪ ይበ ልጥ ስመ ጥሩ የሆነውን ጀኔራል ቤልዲሰራን ከ15.000 የጦር ወታ ደር ጋር እንደላከው እርግጥ ነበር ። አጤ ምኒልክ ከአድዋ ጦርነት በኋላ አስመራ ውስጥ ከኢጣሊያ ከመጣው አዲስ ጦር ጋር እንደገና ቢዋጉ ድል ያደርጉ እንደነበረ አሁንስ ያንጊዜስ በርግጥ የሚያው ቀው ማን ነበር ? ....'' ብለዋል ።

የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበረው ባሮን ብላንክ እ. ኤ.አ. መጋቢት 3 ቀን 1896 ዓ.ም. (የአድዋው ጦርነት በተደረገ ማግስት ማለት ነው) ሮማ ከተማ ውስጥ ለኢጣሊያ ፓርላማ ካቀረ በው ሪፖርት ውስጥ በጥቂቱ እንጥቀስ ። ".... ወታደሮቻችን አፍ ሪካ ውስጥ መውደቃቸውን የሚገልጽ የሚያሳዝን ወሬ የያዘ ቴሌግ ራም ደርሶናል ። ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ቅኝ ግዛታችን ውስጥ ፣ የቅኝ ግዛታችንን ፀጥታ ለማስከበር በቂ ኃይል መዘጋጀቱን መግለጽ እወዳ ለሁ ። በጀኔራል ሂውሽ (HUESCH) የሚመራ ጠንካራ ኃይል ልከ ናል ። ጠቅላላው ኃይላችንም በአኩሪው ጀኔራላችን በጀኔራል ባልዲ ሴራ የሚመራ መሆኑን ለምክር ቤቱ እገልፃለሁ ።

".... ጠላት አድዋን የያዘውና የወሰደውም በእድል ነው ። እንደ ዚህ ዓይነት እድል በኤርትራ ውስጥ እንደማያጋጥም ለምክር ቤቱ ቃል እገባለሁ ። በምጥዋ ፣ በአስመራ ያሠፈርነው ጦራችንም የሚያስተ ማምንና በቂ ኃይልም ያለው ነው ። ....ቅኝ ግዛታችን ኤርትራ በሚ

ያስደንቅ ሁኔታ በሶስት መአዘን እንድትጠበቅ አድርገናል ። ይህም ምጥዋ ፣ ከረን ፣ አስመራ ላይ ያለው ኃይላችን የማይፈታ ነው ።

"....የውጫሌው ውል ከምጥዋ ባህር ገብቷል ። ....ቀደም ባለው ጊዜ የያዝነው የወሰን ጉዳይ በገዛ የጦር መሣሪያችን የነገሰው ምኒልክ በውሉ አልስማማም ብሎ የውጫሌን ውል አፍርሷል ። ....እኛ ንም ከምጥዋ ባህር ሊጨምረን ይፈልጋል ። ....ይህ ግን ፈጽሞ የማይ ሆን ነገር ነው ። .... አበሾችም ገፍተው እንደሚመጡ ቀደም ብሎ ስለታሰበበት በበርሊንና በብሩሴልስ ውል መሠረት የኤሮፓ ኃያላን መንግሥታት ቅኝ ግዛታችንን ለማስከበር ከጐናችን እንደሚሰለፉ ቃል ገብተውልናል ። ....የሩሲያ መንግሥትም ቢሆን ከሃይማኖት ጉዳይ በስተቀር በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ እንደማይገባ ነግሮናል ። መጋ ቢት 5 ቀን 1894 ዓ.ም. ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ስለሐረርጌ ጉዳይ ባወጣነው የጋራ መግለጫ ይህ ሁሉ ተካትቷል ። ከፈረንሣይም ጋር በጥሩ ግንኙነት ላይ መሆናችንን ይህ ምክር ቤት ያውቃል ።

"... የእንግሊዝ መንግሥት በዘይላ በኩልም ሆነ በሌላው ቅኝ ግዛቱ ምንም ዓይነት የጦር መሣሪያ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ እንደ ሚከለክል ቃል ገብቶልናል ። የፈረንሣይ መንግሥትም በቅኝ ግዛቱ ውስጥ የራሱ ችግር ቢኖርበትም በበርሊኑና በብሩሴልሱ ውል መሠ ረት እንደሚፈጽም ቃል ገብቶልናል ።.... ቅኝ ግዛታችን ኤርትራ እን ደማትነካ ለምክር ቤቱ ደጋግሜ ቃል እገባለሁ ። ...." ብሏል ።

ጀኔራል ባልዲሴራ ምጥዋ የገባ ዕለት በኤርትራ ያሉ የኢጣሊያ ሹማምንቶችን ሰብስቦ ስለኤርትራ ፀጥታ ጉዳይና የምኒልክ ጦር ቢገፋ ምን እርምጃ እንደሚወሰድ ተነጋገሩ ። የካቲት 23 ቀን አድዋ ላይ የኢጣሊያ ሠራዊት ድል መሆኑ እንደተሰማ ትኩስና ኃይለኛ ጦር በአሥመራና ምጥዋ ላይ በተጠንቀቅ እንዲጠብቅ መደረጉንና ወታደሩም ሞራሉ ሙሉ መሆኑን ለጀኔራል ባልዲሴራ ነገሩት ።

ኤርትራ ውስጥ በተጠንቀቅ ስለሚጠባበቀው ጦርም ገለፃ ተደ ረገለት ። ጦሩም አምስት ባታሊዮን ጦር ከማይ መሬት እስከ አዲ ቀይሀ ፣ አንድ ባታሊዮን ጦር አስመራ ላይ ፣ ሁለት ባታሊዮን ጦር አስመራና ምጥዋ መሀል ፣ አንድ ባታሊዮን ጦር ሠራኤ ላይ ፣ አንድ ባታሊዮን ጦር ከሰላ ላይ በተጠንቀቅ መሰለፉን ነገሩት ።

የኢትዮጵያ ጦር የገፋ እንደሆነ በማለት በተጠንቀቅ ኤርትራ ውስጥ የሚጠባበቀው የኢጣሊያ ጦር ምን መልክ እንደነበረው ሌ. ኤርትሪያ ኔል ፓሳቶ ኢ. ኔል ፕሬሴንቴ ከተባለው ከአኪሌ ቢዞኒ መጽሐፍ ጥቂት እንመልከት ። ጦሩ በሁለት ዲቪዥን (ክፍለጦር)

የተከፈለ ነበር ። አንደኛው ክፍለ ጦር በሌቴና ጄኔራል ዲል ማይዮ የሚመራው ሲሆን በውስጡም በሜጀር ጄኔራል ቢሲስቲ የሚታዘዝ 1ኛ ብርጌድ ፣ በሜጀር ጄኔራል ባርቤሪ የሚመራ 2ኛው ብርጌድ ነበሩ ። እነኚህን ብርጌድ የሚረዳም ሶስት የተራራ መድፎች ፣ አንድ ያገር ተወላጆች ባታሊዮን ፡ ሁለት ባለሙሉ ትጥቅ የመሐንዲስ ቡድኖች ነበሩ ። በጠቅላላው በዚህ በአንደኛው ክፍለ ጦር ውስጥ 299 መኰንኖች ፣ 8.320 ባለሌላ ማዕረጐች ፡ 1.485 የጭነት እንሰሶች ነበሩት ።

ሁለተኛው ክፍለ ጦር ደግሞ በሌተና ጄኔራል ሂውሽ የሚመራ ሲሆን በውስጡ ያሉት በሜጀር ጄኔራል ጋዙሬሊ የሚመራ 3ኛው ብርጌድ ፣ በሜጀር ጄኔራል ማዛ የሚመራው 5ኛው ብርጌድ ሲኖሩበት ሶስት የተራራ መድፎች ፣ አንድ ያገር ተወላጆች ባታሊዮን ፣ በሶስት ክፍል የተከፈሉ የመሐንዲስ ቡድኖችና ተንቃናቂ ሆስፒታል ያለው ድርጅት ነበረው ። በጠቅላላው ኤርትራ ውስጥ በተጠንቀቅ ይጠባበቅ የነበረው በኋላ ከተጨመረው ሌላ 1301 መኰንኖችና 41.545 ወታደሮች ያሉበትና 10.248 የጭነት እንስሳት ነበሩት ። የደከመው የመሀል ኢትዮጵያ ጦር ወደፊት ገፍቶ ቢሆን ኖሮ ከዚያ ከኢጣሊያ ዝግጅት ውስጥ ለወሬ ነጋሪም አይተርፍም ነበር ። በዚህ ምክንያት ነው ምኒልክ ጉዳዩን በታማኝ የሐማሴን ተወላጅ ሰላዮቻቸው አስጠንተው ወደኋላ የተመለሱት ።

ከዚህ ሌላ ደግሞ በትግራይ ፣ በጐጃምና መሀል ኢትዮጵያ የነበሩ ንጉሶችና ራሶች የምኒልክን ሥልጣን ለመንጠቅ ከምኒልክ ጋር የተዋጉና አሁንም በአድዋ ጦርነት ምኒልክ ቢደክሙ ሥልጣን ለመቀማት ያቆበቆቡ ነበሩ ።

ምኒልክ ድል አድራጊ ሠራዊታቸውን እየመሩ ግንቦት 3 ቀን 1888 ዓ.ም. አዲስ አበባ ገቡ ። በአፍሪካ የጦርነት ታሪክ ውስጥ ሁለት የተከበሩና የተደነቁ ጦርነቶች አሉ ። አንደኛው ከ2000 ዓመታት በፊት ሀኒባል ኤሮፓውያንን ድል ያደረገበት ጦርነት ሲሆን 2ኛው ደግሞ ከ2000 ዓመት በኋላ ኢትዮጵያውያን በአድዋው ጦርነት ኤሮፓውያንን ድል ያደረጉበት ጦርነት ነው ። ይህንንም ብዙ ታሪክ ፀሐፊዎች ጽፈውታል ። የአድዋው ጦርነትም የኢጣሊያን መንግሥት 200 ሚሊዮን ሊሬ ወጭ አስወጥቶታል ።

“. . . . የአድዋው ጦርነት ኢትዮጵያን በዘመናዊው የዓለም ካርታ ውስጥ ስሟን አስገባት ። . . . .” ማርጀሪ ፐርሃም

በአድዋ ድል ጊዜ በመላው ዓለም ያሉ ጋዜጦች ሁሉ በመጀመሪያ ገፃቸው የምኒልክንና የጣይቱን ፎቶግራፍ በማውጣት ወሬ

ወን ለአንባቢዎቻቸው አደረሱ ። በተለይ እ. ኤ. አ. መጋቢት 7 ቀን 1896 የወጣው ኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ፣ እ. ኤ. አ. መጋቢት 29 ቀን 1896 የወጣው ለ. ፔቲ ጄርናል የሚባለው ፈረንሳይኛ ጋዜጣ ፣ እ. አ. አ. ሚያዝያ 4 ቀን 1896 የወጣው ሐርፐርስ ዊክሊ የተባለው ጋዜጣ ፣ እነኚህ ሶስቱ የአድዋን ድል ታሪክ በሰፊው እያደረጉ ዝርዝሩን አወጡ ።

ጋዜጣዎቹ ስለጣይቱ ሲተርኩ በምሥራቅ ኢጣሊያ ንግሥት እንደነበረችው እንደ ዜኖቢያ ፣ እንደ ግብጽዋ ንግሥት እንደ ክሊዎፓትራና እንደ ታላቋ ካተሪን እያመሳሰሉ ነበር ። በሕዝቡም በኩል በፈረንሣይ ፣ በጀርመን ፣ በሩሲያና ባሜሪካ ታላላቅ ሕዝባዊ የደስታ ስብሰባዎች ተደርገዋል ። በኢጣሊያም ሁለት ዓመት ሙሉ በየቀኑ በሚወጡት ጋዜጦች ላይ ዜናው ሲወራና ስብሰባዎች ሲካሄዱ ቆዩ ። በሮም ታላላቅ መንገዶችም ሰላማዊ ሰልፍ እየበዛ ስለሄደ ዩኒቨርሲቲዎችና ቲያትር ቤቶች ሁሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንዲዘጉ ታዘዘ ።

የአድዋ ጦርነት ሽንፈት በኢጣሊያኖች ላይ እንደደረሰ የኢጣሊያ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቤት ሄዶ ድንጋይ በመወርወር ታላቅ ጉዳት አደረሰ ። ፖሊሶች በአስቸኳይ ደርሰው ጠቅላይ ሚኒስትሩን ከታላቅ አደጋ አዳኑት ። እሱም እ. ኤ. አ. ማርች 9 ቀን ስንብት ጠይቆ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ ለቀቀ ። በኔፓልም ገንፍሎ የወጣውን የሕዝብ ኃይል ፖሊሶች መከላከል ወይም ማቆም ስላልቻሉ ጦር ሠራዊት ታዞ ወጣ ። በፓቪያ ለሚቀጥለው ግጥሚያ ወደ ኤርትራ የሚመጡ ወታደሮችን የጫኑ ባቡሮች እንዳይንቀሳቀሱ ሕዝቡ ሐዲድ ላይ ድንጋይ ከምሮ ባቡሮቹን አገደ ።

በሮም ፣ በቱሪን ፣ በሚላኖና በፓቪያ ከተሞች ያሉት የሴቶች ማኅበራት "በአፍሪካ ያለው የወታደር ኃይል ይመለስ" እያሉ ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ ። የሞተውና ያልሞተው የኢጣሊያ ወታደር ቁርጡ አልታወቀ ስለነበረ በጠቅላላ የኢጣሊያ አብያተ ክርስቲያናት ለጠቅላላው ሠራዊት የሙታን ፍታት አደረጉ ። የዘማች ቤተሰቦች ዘማቾች ከአድዋ ጦርነት በፊት የፃፉላቸውን ደብዳቤ ሁሉ ለጋዜጦች ይሰጡ ጀመር ። ንጉሥ ኡምቤርቶ የልደት በዓላቸው የሚከበረው ማርች 14 ቀን ስለነበረ የልደት በዓላቸው ቀን የኀዘን ቀን ሆኖ እንዲውል አወጁ ። በሳንትስበርግ ፣ በለንደን ፣ በኒውዮርክ ፣ በቺካጐ ፣ በቦነስ አይረስና በኢየሩሳሌም ያሉ ኢጣሊያኖች ገንዘብ አዋጥተው ለሞቱት ቤተሰቦች መርጃ እንዲሆን ለኢጣሊያ ቀይ መስቀል ማኅበር ላኩ ። የንጉሥ ኡምቤርቶ ሚስት ማርጋሪታ በኢትዮጵያ ላሉት ምርኮኞች የእርዳታ መዋጮ ቢጠየቁ "አዲስ የተላከው የኢጣ

ሊያ ኃይል አበሾቹን ፈጅቶ ምርኮኞቹን ነፃ ስለሚያወጣቸው አልሰ ጥም'' ብለው እምቢ አሉ ።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ወዳጃቸውን ሞንዶን ቢዳሴን "ናና ከየ አገሩ የደረሱኝን ክምር ወረቀቶች እይ'' ብለው ከአድዋ ጦርነት በኋላ ጋበዙት ። ደብዳቤዎቹ ከዓለም ዙሪያ የተፃፉ ሲሆን "እንኳን ደስ አለዎት'' የሚሉ ነበሩ ። ሞንዶን ስለደብዳቤዎቹ ሲጽፍ "....እንዳንዶ ቹም መልስ እንዲፃፍላቸውና በፖስታ ቤት የኢትዮጵያ ቴምብር ተለጥፎ እንዲላክላቸው የሚፈልጉ ነበሩ ። ምክንያቱም ቴምብሩ ላይ የምኒልክን መልክ ለማየት እያሉ ነው ። ከአውስትራሊያና ከቬኑዜላ የተፃፉት ደግሞ የእርስዎ ወታደሮች መሆን እንፈልጋለን የሚሉ ናቸው .... ከክምሩ ደብዳቤዎች መሀል ጋዜጦችም ነበሩ ። ለፊጋሮ የምኒ ልክን ካርቶን ስዕል ያወጣበትም አብሮ ነበር ።....'' ብሏል

## የአድዋ ምርኮኞች

የምርኮኞችን ጉዳይ ስናነሳ እጅግ አድርጐ የሚያሳዝነው ከ400 በላይ የሆኑ ለኢጣሊያ ተቀጥረው የተዋጉ ሐማሴኖች እጅና እግራ ቸው መቆረጡ ነው ። ዳግማዊ አጤ ምኒልክ የኢጣሊያ ዜጐች ለሆ ኑት ምርኮኞች በቂ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው በአዋጅ ሲያዙ ፣ በሐማሴን ተወላጆች ወይም በወታደርነት መጥሪያ ባሽ ባዙቅ በሚባ ሉት ላይ ለምን ጨከኑ ? መልሱ ፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስን ለማስደሰት ሲሉ ብቻ ነው ።

"....ራስ መንገሻ.... ያን ጊዜ በጥልበቃ ጣሊያንን ሊጐዳ ደመኞችን በወርቅ እየተገዛ ሁል ጊዜ የሚወጋን ባሽ ባዙቅ ነውና ይቀጣልኝ ብሎ ጮኸ ። አጤ ምኒልክ 500 ሰው ቀኝ ቀኝ እጁን ፣ ግራ ግራ እግሩን እየቆረጠ ጣለው ። ኋላም ለኢጣሊያ ጠባቂ ሆነ ።... በማለት አለቃ ተክለ ሥላሴ ጽፈዋል ።

ፕሮፌሰር አፈወርቅ "....ዳግማዊ ምኒልክ በዚያ ደግነት ፣ በዚያ መሐሪነት ላይ የራስ መንገሻ ዮሐንስን ምክር ሰምተው ካድዋ ጦር ነት ማግስት አንድ ክፉ ሥራ ሠሩ ። ነገሩም እንዲህ ነው ።....ራስ መንገሻ በባሽባዙቅ ብርቱ ቂም ይዞ ተቀምጦ ሳለ ያዲ ጦርነት መጣና ካዲ ጦርነት ላይ ብዙ ባሽ ባዙቅ ለፈረንጆች ሎሌ ነበርና ሲዋጋ ከድሉ ላይ ተማረከ ። ራስ መንገሻ በዚያ ቂሙ የተማረከው ባሽ ባዙቅ ሁሉ እጅና እግሩን ይቆረጥልኝ ። እሱ ነው ከዋቲት ላይ የተዋጋሁ ጊዜ ለነጮች ረድቶ ድል ከመሆን ያደረሰኝ ብሎ ለጃንሆይ



Le Petit Journal

Le Petit Journal

SUPPLÉMENT ILLUSTRÉ

Huit pages : CINQ centimes

DIMANCHE 9 FÉVRIER 1896

LE PAIN COMPLET

Cover of *Le Petit Journal* of 9 February 1896, showing Crispi of Italy as a fat fool falling to the ground as Menilek stuffs a baguette of bread labeled "Makalle" in his ear



የኢጣሊያ ምርኮኞች ኢትዮጵያ ውስጥ በቆዩበት ጊዜ ።

ተናገረ ። ዳግማዊ ምኒልክ ምንም እንዲህ ያለውን ያረመኔ ቅጣትና ጭካኔ ባይወዱት የራስ መንገሻ አነጋገር ለጊዜው አስገርሟቸውና እሺ ብለው ያን የተማረከውን ሁሉ ባሽ ባዙቅ እጅ እግሩን አስቆረ ጡት ። የተቆረጠው ባሽ ባዙቅም ቁጥሩ ከ400 ይበልጥ ነበር ። . . . . እንዲህ ያለው ያረመኔ ቅጣት . . . . በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ መደረጉ ያሳዝናል ። . . . . ባሽ ባዙቅስ ላገሩ ትቶ ለባዕድ ረዳ ተብሎ በራስ መንገሻ ልሳን ተመከሰስ ፥ ተመወቀስ ፥ እጅ እግሩን ከማጣት ደረሰ ። በዚህማ ቱሆን ራስ መንገሻ ይልቅ ሳይቸግረው ያስር ነጋሪት አገር አንድነት እየገዛ ባንድ ወገን ላጤ ምኒልክ የታመነ ሎሌ መስሎ . . . . ባንድ ወገን ለእንግሊዝ መንግሥት እየላከ እባካችሁ አግዙኝ ያባቴን አልጋ ፥ ያባቴን ዘውድ የማይገባው ኃይለኛ ቀምቶኝ አይቅር ሲልና ዳግማዊ ምኒልክን ሲከስ አልነበረምን ። . . . .ያዷ ጦርነት ጊዜ ሳይቀር ባንድ ወገን ላጤ ምኒልክ የረዳ መስሎ ከኢጣሊያኖች ጋር እየተ ዋጋ ፥ ባንድ ወገን ውስጥ ለውስጥ ለእንግሊዞች እባካችሁ ኃይለኛ ያባቴን መንግሥት እንደቀማኝ አይቅር ። አባቴን በቴዎድሮስ ጊዜ እንዳገዛችሁ እኔንም አግዙኝ ብሎ ላከ . . . . እንግዲህ ባሽ ባዙቅ አይ ቀጡ ቅጣት ከተቀጣ ይሄን ሁሉ ላደረገው ለራስ መንገሻ እንዴት ያለ ቅጣት በተገባ ነበር ። . . . .” ብለዋል ። ይህን በዚሁ እናቁመው ።

ጄኔራል ባልዲሰራ እንደታዘዘው ከኢጣሊያ አዲስ በመጣው ጦር ኢትዮጵያን እንደ ገና ሊወጋ አስቦ ውጊያ ቢጀምር ግን የተማ ረኩት ኢጣሊያኖች እንደሚያልቁ ስለገባው እስረኞች ኢጣሊያኖችን በቅድሚያ ለማስለቀቅ እንታረቅና ምርኮኞቹ ይለቀቁ ብሎ ወደ ምኒ ልክ ላከ ። አጤ ምኒልክም የመጣው አዲስ ጦር ከፍተኛ ኃይል ያለው መሆኑን አውቀው ስለነበር ኃይላቸውን ገምተው አዲስ ውል ተዋው ለን የውጫሌ ውል መፍረሱን ለዓለም ነገሥታት ሁሉ ካላሳወቃ ችሁ ምርኮኞቹን አለቅም ብለው ሸዋ ገቡ ።

ምርኮው እንዴት ነበር ? ኒኮላስ ሊዎንቲቭ እንደፃፈው “. . . ንጉሡ ድል ማድረጋቸውን እንዳወቁ ፥ እጅ የሚሰጡትን ኢጣሊያኖች ፥ ሠራ ዊታቸው እንዳይገድል በአዋጅ አስጠነቀቁ ። እንስራ ተሸክመው ለሠ ራዊቱ ውሃ ያቀብሉ የነበሩ የኢትዮጵያ ሴቶች ሁሉ ሸክማቸውን እያስቀመጡ ምርኮኞቹን እስረኞች በማጋዝ ይረዱ ጀመር ። ሬሣዎች በብዛት ተከምረዋል ። . . . በሜዳው ላይ በትንሹ ይወርድ የነበረው ደም ወደ ወንዝነት ተለውጧል ። . . . .የቆሰለውም ሆነ ያልቆሰለው ኢጣ ሊያዊ ላለመማረክ ሬሣ እየመሰለ ከሬሣዎች ጋር ይተኛ ጀመር ። ኢትዮ ጵያውያኖቹም በሕይወት ያለውን ሰው ከሬሣዎች መሀል እየመረጡ ማውጣቱ ከብዛቱ የተነሣ ጊዜ ስለ ወሰደባቸው፣ አድካሚም ሥራ ስለሆነባቸው የመሬቱን ሣር እሳት ለቀቁበትና ከፍተኛ ጭስ አስነሱ።

በየሬሳው መሐል የተኙት በሕይወት ያሉት ኢጣሊያኖች ጭሱ ስላ ፈናቸው ጭሱን ከለላ እያደረጉ ለማምለጥ እየሮጡ ይሸሹ ጀመር ። ኢትዮጵያውያኖችም በዚህ ዘዴ ተጠቅመው ኢጣሊያኖችን እየለ ቀሙ ይይዙ ጀመር ። ምርኮኛውንም እየያዙ ወደ ንጉሱ ሲሄዱ እልል በል አሞራ እልል በል ጥቁሩ ፣

ያው የሰው ሥጋ ውረድ ወደ ምድሩ "እያሉ ይዘፍኑ ነበር. . . ." ብኋል ። እንዲገጥም ያደረግሁት እኔ ነኝ ።

ግሊከን ደግሞ ". . . .በጦርነቱ ተካፋይ የነበሩት አቡነ ማቴዎስ እንዳጫወቱኝ. . . . በዚያ ጊዜ ምኒልክ አንድ መጠለያ አቋቁመው ስለ ነበር ልብስ ፣ ምግብና ውሃ ይሰጣል ። ለቁስለኞችም የሕክምና እር ዳታ ይደረግ ነበር ። የተማረኩትም ኢጣሊያኖች በምኒልክ ድንኳን ሥር የተደለደሉት በመንገዳቸው ላይ ሕይወታቸውን የሚያቆዩበት ምግብ ይሰጣቸው ነበር ። . . . . ይህም በገባው ረሃብ ምክንያት የሚጓ ዙበት መንገድ ወታደሩን የሚቀልብ ምግብ አልነበረውምና ነው ። የቆሰሉት ኢጣሊያኖ ች የሚጓዙበት በቅሎ ተሰጥቷቸዋል ። ያልቆሰሉት ግን በእግራቸው ነበር የሚጓዙት ። አዲስ አበባ እንደደ ረሱ በተቻለ መጠን በጥሩ ኑሮ እንዲኖሩ ተደረገ ። . . . . ንጉሡም በተ ቻለና ባላቸው መጠን እስረኞቹን በማስደሰት የኢትዮጵያ መንግስት የሰለጠነ መንግሥት መሆኑን ለማሳወቅ ተመኝተዋል ። ይህም ተሳክ ቶላቸዋል ። አልፈው ተርፈው ገንዘብ እንኳ ይሰጡዋቸው ነበር ። በነፍስ ወከፍም ለእያንዳንዱ 3 ሶስት ብር ሰጥተዋል ። የጦር እንግ ዶች መሆናቸውንም አሳውቀው መጠለያ ቤት ሁሉ ሰጥተዋቸዋል ።

". . . . እስረኞቹን ሕዝቡ አሊ እያለ ነው የሚጠራቸው ። በዚያው ሳቢያ በመንገድ ላይ የሚታይ ነጭ ሁሉ አሊ ነው የሚባለው ። ምኒ ልክም ይህን አዲስ አጠራር ለማስተው ቢሞክሩም አሁን ለግዜው አልቻሉም ።

"የተማረኩትን ኢጣሊያኖች ኢትዮጵያኖቹ ተከፋፈሉዋቸው ። ለምኒልክ የደረሱዋቸው ምርኮኛ ኢጣሊያኖች በምግብም ሆነ በሌላ አልተቸገሩም ። ለሌሎቹ መኳንንት የደረሱት ኢጣሊያኖች ግን የም ግብ ችግር ነበረባቸው ። . . . . በሰው ቤትም በምሪት ተሰጡ ። ምኒልክ እነኚህን የጦር እንግዶች የተረከበ ሁሉ የማዳንና የመንከባከብ ግዴታ አለበት ብለው አዋጅ አስነገሩ ።

". . . . አንድ ቀን አንድ ምሪት የተሰጠው የኢትዮጵያ ወታደር በፈረስ ሆኖ የተሰጠውን ምርኮኛ ኢጣሊያዊ ጧት ለሽንቱ ብሎ ወደ ዱር ሄዱ ። ኢጣሊያኑም የኢትዮጵያውያኑን ወታደር ፈረስ ማድነቅ ጀመረ ። ኢጣሊያኑ በሚያውቃት ትንሽ አማርኛ የወታደሩን ፈረስ

እያሞጋገሰ በኮርቻው ላይ ተቀምጦ ፈረሱን ቢያየው ደስ እንደሚ ለው ለወታደሩ ነገረው ። ወታደሩም ፈረሱን ለኢጣሊያኑ ሰጠው ። ኢጣሊያኑም ከፈረሱ ላይ ወጣ ። ኢጣሊያኑ ወዲያውኑ ፈረሱን ኮር ኩሮ በመጋለብ ከወታደሩ ዓይን ተሰወረ ። ወታደሩም አንድ ሁለት ጥይት ተኮሰ ። አላገኘውም ። አንድ ቀን የሚስተር ኢልግ አሽከር ያ ወታደር ጠመንጃውን ይዞ ጫካ ውስጥ ሲንጐራደድ አገኘውና ምን ታደርጋለህ ? ቢለው እየህ ፣ ጣሊያኑ ጠፋብኝ ። መልካም መስሎ የሰይጣን ሥራ ሠራ ። እዚህ እየመጣሁ የምጠብቀውም እሱን ወይም ሌላ የምይዘው ጣሊያን ባገኝ ብዬ ነው አለው . . . .'' ብሏል ።

ለ. ቴምፕስ በተባለው ጋዜጣ ሞንዶን ቪዳሌ እ. ኤ. አ. ሐምሌ 14 ቀን 1896 በወጣው ላይ እንደፃፈው ''. . . . ጣይቱ በግቢያቸው ውስጥ ባለው ሜዳ ላይ ምርኮኞችን ይጋብዙ ነበር ። ከጄኔራል አል ቤርቶኒ ጀምሮ ሁሉም ባንድነት በኤሮፓውያን ደንብ ይጋበዛሉ ። በሚመገቡበት ጠረጴዛም ላይ ሰሃን ፣ ሹካ ፣ ማንኪያ ፣ የአፍ መጥረ ጊያ ፎጣ ፣ የተለያዩ ቢኖዎችና አበባ እንኳ ሳይቀር እየተደረገ ነበር . . . .'' ብሏል ። የምርኮኞቹ የሥራ ችሎታ እየተጠየቀም ሰዓት ሰሪ ዎች ፣ አትክልተኞች ፣ አናጢዎች ፣ መካኒኮች ፣ ሰዓሊዎችና ጥቂት ሐኪሞች በአዲስ አበባ ውስጥ ሥራ እየተሰጣቸው ያዙ ። የተለየ የሥራ ችሎታ የሌላቸውም መንገድ እንዲሠሩ ተደረገ ። ዋናው እስረኛ ጄኔራል አልቤርቶኒ በአዛዥ ዛማኔል ጥበቃ ሥር ሆኖ ለግሉ ድንኳን ፣ ፈረስና አሽከሮችም ተሰጥተውታል ።

ሌተና ኔኮሊቲ አልቲማሪ በመጽሐፉ ራሱ ስለደረሰበት ሁኔታ ጽፏል ። ኔኮሊቲ በአድዋ ጦርነት ላይ ተመቶ ቆስሎ ነበር ። የተመታው በጥይት ሲሆን ጥይቲቱ ደረቱን ቀዳ አልፋለች ። ኔኮሊቲ ሕይወቱን ስቶ ወድቋል ። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የኢትዮጵያ ሴቶች ፣ ምርኮ ኞች በሚሰበሰቡበት ጊዜ ቁስለኛውን ኔኮሊቲን አግኝተው ወደ ቤታቸው አስገብተውታል ። ኔኮሊቲ በኤርትራ አምስት ዓመት የቆየ በመሆኑ ትግርኛ ቋንቋ መስማትም ሆነ መናገር ይችላል ። ከዚህ በኋላ ያለውን ጉዳይ ሲተነትን እንዲህ ይላል ። ''. . . .ስነቃ ራሴን አንድ ጐጆ ውስጥ አገኘሁት ። በጦርነቱ ማግስት መሆኑ ነው ።የተመታሁባት ጥይት ደረቴን ቀዳ በማለፍዋ ትንሽም ስንቀሳቀስ ያመኛል ። . . . . አንዲት አሮጊት ሴት በደም የተነከረ ጃኬቴን ፈታች ። ልብሴንም ግራና ቀኝ አስለቅቃ የቁስሉን ቀዳዳ ትመረምር ጀመር ። . . . .እሷ ይህን ስታደርግ ሌሎች ሴቶች ተሰብስበው ያዝኑልኝና ይጨነቁ ነበር ። . . . .አሮጊቷ ሴት ቁስሉ አደገኛ አይደለም ስትል ሰማኋት ። ወዲያውም መድኃኒት አደረገችልኝ . . . .ቁስሉም በጥቂት ቀን ውስጥ ዳነ ። . . . .ምርኮኛ ሆኜ ተቀመጥሁ ። . . . .''

እናቴ ወይዘሮ ትበልጫለሽ እንዳርጌ ስለኢጣሊያኖቹ ምርኮኞች የምግብ ጉዳይ ያጫውቱኝ የነበረው ትዝ ይለኛል ። “. . . .በምግብ ችግር ነበረባቸው ። የበርበሬ ወጥ ተሰጥቷቸው ሲበሉ ፊታቸው ጁህ መስሎ ይቀላል ። እምባቸው ሁሉ ዱብ ዱብ ይላል ። የተሻለ ምግብ የሆነላቸው ገንፎ ነበር ። ገንፎ እየተሰጣቸው ሲበሉም እየሰለቻቸው በየግድግዳው ላይ የተለጠፈ የፈረንጅ ፎቶግራፍ ሲያዩ ገንፎውን በፎቶግራፉ ፊት ላይ እየላከኩ እኔ የምበላውን ብላ ፣ ቅመሰው . . . .ይሉ ነበር ። . . . .” በማለት አጫውተውኛል ።

አውጉስቶስ ቢ ዊልዲ ደግሞ “. . . .በአዲስ አበባ ውስጥ ብዙውን ጊዜዬን ያሳለፍኩት እድዋ ላይ ከተማረኩት ኢጣሊያ እስረኞች ጋር ነው ። ጀኔራል አልቤርቶኒ እየደጋገመ የሚያወራው የአድዋን ጦርነት ጉዳይ ነው ። እኔም የአድዋውን ጦር ሜዳ ተመልክቼ ነገሩንም በደንብ አውቃለሁ ። ከሱ የተሻለም እኔ ደህና አድርጌ እስረዳለሁ ። . . . . ሽምፐር በጦርነቱ ጊዜ ከጀኔራል ባራቲየሪ ጋር ይዋጋ ነበር ። እንሱም ቢሆኑ በጦርነቱ ሜዳ የሆነውን የዳቦርሜዳን ወይም የጀኔራል አልቤርቶኒን ሁኔታ አያውቁም ነበር ። . . . .ጀኔራል ባራቲየሪም በጥላናቸው መሠረት እንዳይዋጋ ተቋርጦ መቅረቱን አያውቁም ። . . . .ጀኔራል አልቤርቶኒ እየደጋገመ የሚጠይቀኝ ቦታዬን ለቅቄ በተባረርኩ ጊዜ በምን ምክንያት እርዳታ አልደረሰልኝም ? የመሀሉ ጦርስ ለምን ወደፊት አልገፋም ? ለምልከው መልክትስ ለምን መልስ አልተሰጠኝም ?እያለ ነበር. . . በኢጣሊያ መኰንኖች ምንም ዓይነት ተቃውሞ የለም ።አብዛኛዎቹ በጀግንነት ሠርተዋል ። እስኪሞቱ ወይም እስኪቆስሉ ተዋግተዋል ። ጥይት አለቀ ። ከዚህ የበለጠ ምን ያድርጉ ? እገራቸውስ ከዚህ ሌላ ምን ትጠብቅባቸዋለች ? . . . .” እያለ ጽፏል ።

ከጦርነቱ ጥቂት ቀናት በኋላ ስለምርኮኞች ጉዳይ ለመነጋገር ከጀኔራል ባልዲሴራ በተላከው በማጆሬ ሳልሳ በሚመራው ቡድን ውስጥ ሌተና ሮቪርሲ በመንገድ ስላየውና ስለሁኔታው የገለጠው በላቫሪባር መጽሐፍ ተገልጿል ። “. . . .የየሃን አካባቢ ስናልፍ በዚያ ቦታ አንዲት ትንሽ ወንዝ አገኘን ። በወንዙዋም ዙሪያ በሙሉ የኛ ወታደሮች ሬሣ በማንባሩ እየተደፋ ተኝቷል ። . . . .ጦርነቱ ከተካሄደ 8 ቀን ሆኖታል ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ጅብ እንኳ አልነካቸውም “ዓይን ማየት እስከሚችልበት ድረስ ሬሣዎች እየተደራረቡ ወድቀዋል ። . . . . . . . .” ይልና አዲስ አበባ ከገባ በኋላ ደግሞ “. . . .በዚያም በከረምንበት ጊዜ የኛዎቹ ወታደሮች ተራቁተዋል ፣ ደክመዋል ። በረሃብ ተሰቃይተዋል . . . .” ብሏል ።

ምርኮኞቹ ብዛታቸው ስንት ነበረ ? የምርኮኞቹን ጉዳይ ለመነጋገር ወደ ኢትዮጵያ ተልከው ከመጡት መሀል ቁስ ዎርዚዊዝ እንደ

ፃፉት በሸዋ ውስጥ 2864 የኢጣሊያ ምርኮኞች ነበሩ ብለዋል ።
ከጦርነቱ ጥቂት ወሮች ቆይቶ አዲስ አበባ የገባው ዌልዲ ደግሞ
"....ኢጣሊያኖቹ ምርኮኞች 4000 ያህል ይሆናሉ ። ኢጣሊያ ከቅኝ
ግዛቶቿ ካሰለፈቻቸው ወታደሮችም የተማረኩት ያንኑ ያህል ይሆ
ናሉ ። ...." ብሏል ።

መላ ኤሮፓ ከአድዋ ድል በኋላ በምኒልክ ላይ አድሟል ። ትላ
ልቅ የጦር መሣሪያ ቀርቶ እንዲት ጥይት እንኳን ወደ ኢትዮጵያ
እንዳይገባ እንግሊዝና ፈረንሳይ በየቅኝ ግዛቶቻቸው በኩል ጥብቅ
ቁጥጥር እንዲያደርጉ ተስማምተዋል ። በአፍሪካ ቅኝ ግዛት የነበሯ
ቸው የኤሮፓ መንግሥታት በሙሉ በአንድ ኃይል ተሰባስበው የም
ኒልክን መንግሥት ለማጥፋት ፕላን አውጥተዋል ። ሊያስተባብሯ
ቸው የቻለውም በቅኝ ግዛት አገሮች ሁሉ የምኒልክ ኃይል የኤሮ
ፓን ኃያል መንግሥት ድል ማድረግ ከተሰማ፣ ቅኝ ተገዢዎች ይነ
ሡብናል በሚል ሰበብ ነበር ። ነገሩ እውነት ነበር ። በአሜሪካ ያሉ
ጥቁር አሜሪካውያን አፍሪካ ኤሮፓን ድል አደረገ እያሉ የደስታ ሰላ
ማዊ ሰልፍ በማድረግ ከባድ ብጥብጥ አንስተው ነበር ። ይህን በመሳ
ሰለው የጥቁሮች መደሰት ምክንያት ኤሮፓውያን ተባብረው የአድዋ
ድል በአፍሪካም ሆነ በኤስያ እንዳይወራ አስከለከሉ ።

በዚያን ጊዜ የዛሬዋ ጂቡቲ አቦክ ትባል ነበር ። የአቦኩ ፈረን
ሣዊው ቶኝ ገዥ ሙሴ ላጋርድ የምኒልክ ወዳጅ ነበር ። ምኒልክ ለዚያ
ወዳጃቸው መጋቢት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. በፃፉለት ደብዳቤ "....
መሣሪያ ወደ አበሻ አይምጣብን ብሎ የፈረንሣይ መንግሥት ለጊ
ዜው እሺ ማለቱ በኤሮፓ ሥራት ቢያዝ ነው ። ....ዳሩ ግን እንደ
እውነት ፍርድ ቢሆን ኢጣሊያኖች ከጦርነት ቢሉ ውጊያ አልፈለግ
ኋቸውም ። ከአገሬም የመጡብኝ እነሱ ፣ የወጉኝም እነሱ ሆነው
በዚሁ ላይ መሣሪያ ሊያስከለክሉኝ ፍርድ ይሰጣቸዋል ብዬ ተስፋ
አልነበረኝም ። እኔ ብሆን ከነፃነቴና ከወዳጅነቴ በቀር የፈለግኋቸው
ነገር አልነበረኝም ። እነሱ ግን ቢሆኑ የቀድሞው ይቅርና ከዛሬ
ዓመት ወዲህ ያደረጉኝን ከኔ ይበልጥ አንተ ታውቃለህ....በግፍ የመጡ
ሰዎች ናቸውና በጦርም በድንጋይም ቢሆን እግዚአብሔር ሳይረዳን
አይቀርም ።....እኔ የክርስቲያን ደምና ገንዘብ ፈላጊ አይደለሁም ። የም
ፈልገው የአገሬን ነፃነት ብቻ ነው ። ..." ብለዋል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖቱን እንደሚወድ ያወቁት ኢጣሊያ
ኖች፣ የሮማው ሊቀ ጳጳሳት ሊዎን 13ኛ ምኒልክ ምርኮኞቹን እንዲ
ለቁ የልመና ደብዳቤ እንዲጽፉላቸው አደረጉ ። የሮማው ሊቀ ጳጳሳት
ሊዮን 13ኛም የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉላቸው ።

ለኃይሉ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት
ለዳግማዊ ምኒልክ

ሰላም ለርስዎ ይሁን ።

ክርስቲያናዊ በሆነው ልብዎ የምመክርዎትን አመዛዝነው የል ግሥና ሥራ እንዲያደርጉ እለምንዎታለሁ ።

የዚህ የዘመቻ ድል በእጅዎ ብዙ የኢጣሊያ ምርኮኞች አሳልፎ ሰጥቶዎታል ። የእነዚህም የኢጣሊያኖች መማረክ በዚህ አገር ያሉ ትን በሺ የሚቆጠሩትን የእናቶቻቸውንና የሚስቶቻቸውን የልብ ኀዘንና ጭንቀት ከማበርከት በቀር ምንም ያህል የግርማዊነትዎን ኃይልና ዝና ሊያስፋፉ አይችልም ። እኛም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስ ቶስ በተቀበልነው አደራ እንደ ልጆቻችን ያህል እንወዳቸዋለንና እነዚህን ምርኮኞች በቶሎ በነፃ እንዲለቋቸው በቅድስት ሥላሴና በድንግል ማርያም ወይም በዓለም ካለው በሚወዱት ስም እለምንዎ ታለሁ ።

ኃያሉ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ፤

ይህንን የምለምንዎትን እንደ ክፉ ሰው እምቢ ማለትዎ በመን ግሥታት ፊት የተገለጸ አይሁን ። ይህቺንም የተከበረች ደብዳቤዬን ለምስክር እታሪክዎ መዝገብ ያግቧት ።

በዚህም በሚያደርጉት የቸርነት ሥራ ርሁሩህና የሁሉ አባት የሆነው እግዚአብሔር ይክስዎታል ። ከዚህም በቀር በብዙ የሚቆጠሩ ሰዎች ሊያመሰግንዎ ድምፃቸውን ያነሳሉ ። ከነዚሁም የመጀመሪ ያዎቹ እኛ ነን ።

ይህ የልመና ቃል እንዲፈፀም በተስፋ ከመጠባበቅ ጋር ልዑል እግዚአብሔርን በንጉሠ ነገሥቱና በቤተ ሰቦቹ ላይ በረከቱን እንዲ ያወርድ እንጸልያለን ።

ሮማ እቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያ አጠገብ ግንቦት 11 ቀን 1896

የሊቀ ጳጳሱ ውትወታ እውነት ለምርኮኞች ኢጣሊያኖች አስ በው ሳይሆን ምርኮኞቹ ተለቀው ጀኔራል ባልዲሴራ በታዘዘውና ባመጣው ትኩስ ጦር የደከመውን የኢትዮጵያን ሠራዊት ሳያገግም ለመምታት እንዲችል ነበር ። እንዲህ ዓይነቱ ጥንስስ መጠንሰሱን አጤ ምኒልክ ያውቃሉ ። ለእግዚአብሔር እድሬአለሁ ያሉት መነኩሴ ለሰው ኃይልና ለምድር ጥቅም በመንበርከካቸው ፤ ዜጋቸው የሆ ነው ታላቁ የኢጣሊያ መንግሥት በትንሽቱ ኢትዮጵያ ላይ ጦርነት

ሲያንሳ ያላወገዙት፣ ባሁኑ ጊዜ አማላጅነት በመግባታቸው ምኒልክ እዝነውና ታዝበው የሚከተለውን ደብዳቤ በአቡነ መቃሪዎስ እጅ ላኩ።

ይድረስ ወደ ክበሩ ወደ ተቀደሱ የሮማ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ሊዎን ፲፫ኛ። የከበረው የአባትነት ደብዳቤዎ በአቡነ መቃሪዎስ እጅ ደረሰልኝ። በዚህም ደብዳቤዎ የቀድሞው መላላካችንን አሳምሮ የሚያስታውስ፣ እግዚአብሔር ከእኔ እጅ የጣላቸውን ስለኢጣሊያ ምርኮኞች የቸርነት ሥራ እንድሰራ የሚያመለክት መሆኑን በጣም አየሁ። ደግሞም የከበረ ቅድስናዎ ከአቡነ መቃሪዎስ የበለጠ መልክተኛ ነገሩን በጣም አስረድቶ፣ አጣፍጦ ሀሳቡን የሚናገር መላክ እንዳይቻልዎ አውቃችን። የክርስቲያን ሁሉ አባት የላከው እጅግ የሚያስደንቅ ደብዳቤዎን ሳነበብሁ ጊዜ ልቤን መታው። ዳግመኛም የከበረውን የመላክተኛዎን የቃል ንግግር በሰማሁ ጊዜ ልቤ ቅድስናዎን በማክበር፣ ለለመኑኝ ጉዳይ ለመፈፀም ጨክኖ ነበር። እኔ ሳልፈልገው ከዚህ በፊት ጦር ደማቸው ለፈሰሰ፣ በከንቱ ላለቁት ወታደሮች እጅግ አለቀስሁ። ነገር ግን ቅድስናዎ የተመኙትን ለመፈፀም የኢጣሊያ መንግሥት ያልታሰበው የዛሬ ሥራቸው የማያስፈጽመኝ ሆነ። ይህንንም ማለት የእርቅ ፈቃድና በደህና ለመላላክ መመኘታቸውን ካሳዩኝ በኋላ ሥራቸው በጦርነት እንዳለን አድርገው ይሄዱ ጀመር። አሁንም የሚገባኝን ንጉሥነቴንና የሕዝብ አባትነቴን ይህን አውቄ በጄ ያለውን የእርቅ መያዣ መልቀቅ የማይቻለኝ ሆነ። ቅድስናዎ ያሰበውን ደስ ለማሰኘት የኔንም መልካሙን ሀሳብ ለመፈፀም ከለከለኝ። በክርስቲያንነቴና በንጉሥነቴ አውጥቼ አውርጄ ሳበቃ የፍቅሬን ምልክትና ብዙ ማክበሬን በሌላ ቀን አደርገዋለሁ ማለት ስለሆነብኝ ዛሬ ሳይሆንልኝ በመቅረቱ እጅግ ያሳዝነኛል። እግዚአብሔር አደራ የሰጠኝን መንግሥቴን፣ የሕዝቤን ነፃነት የምፈልግ ስለሆንሁ በክርስቲያኖች ሁሉ በማክበር የሚሰማውን የቅድስናዎን ድምፅ ፋኛ ብሰው እንዲያሰሙልን ተስፋ አለን። ይህ የሆነ እንደሆነ ከዘመዶቻቸው ለተለዩ በቅርቡ ለመመለስ እንዲመቸን ማድረግዎ ነው። ነገር ግን ይህ ነገር እስኪጨረስ ድረስ ከኔ ዘንድ ያሉት ምርኮኞች እንደ ክርስቲያን ሥራ ከዚህ ቀደም ጠብቄ በመልካም አድርጌ እንዳኖርኋቸው ደልቶንም ከእንግዲህ ወዲያ ስለርስዎ ፍቅር በጣሙን [illegible] በያቲና ኦሮምሬ እንዳኖሬቻቸው በዚህ አይጠርጥሩኝ።

በመስከረም በ፳፪ ቀን ተፃፈ በአዲስ አበባ በ፲፰፻፹፱ ዓ.ም.

ምኒልክ በምርኮኞቹ መልቀቅ ጨከኑ። ከጠቅላላዎቹ የኢጣሊያ ምርኮኞች ያለ አማላጅና ያለ ምንም ልመና ነፃ የተለቀቀ አንድ ኢጣሊያዊ ተራ ወታደር ብቻ ነው። የዚያ ኢጣሊያ ተራ ወታደር እናት

አዲስ አበባ ላለው ተማራኪ ልጅዋ ደብዳቤ ፃፈችለት ። በደብዳቤ ዋም “ .... ልጄ ሞተሃል ብለውኝ ተስፋ ብቆርጥ እንደ ሌሎች እናቶች ሁሉ አልቅሼ ይወጣልኝ ነበር ። አሁን ግን ቀንም ለሊትም ላንተ ለልጄ እንዳለቀስሁ ነኝ ። ምን ቦታ ወድቀህ እንደሆን አላይህም ። ከአፌ እየነጠልኩ ያለችኝን ደህና ምግብ እያበላሁ ያሳደግሁህ ልጄ ዛሬ የምትበላውን አላውቅም .... ልጄ ፣ እንደምወድህ ታውቃለህ ። .... የማምነው አምላክ በሰላም ያገናኘናል ብዩ ተስፋ አደርጋለሁ ። .... ልጄ ፣ በሕይወት መጥተህልኝ ዓይንህን እስካይ ድረስም ውሎዬ ከቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ነው ። .... ለቤተ ክርስቲያኗም በየቀኑ አንዳንድ ሻማ ስለት ተስዬ በየቀኑ እያበራሁ ላንተ ለልጄ እየተንበረከክሁ እፀልያለሁ ። .... በፀሎቴ ብርታት ተለቀህ እንደም ትመጣ ተስፋ አለኝና አንተም ባለህበት ጸልይ ። .... የምወድህ ልጄ ። አይዞህ ፣ በርትተህ ኑር ..... አንተም እንደምትናፍቀኝ አውቃለሁ ። ለቅሶዬ ባክኖ አይቀርምና እንገናኛለን ። .... ” የሚል ቃል ነበረበት ።

ይህ ደብዳቤ የደረሰው ምርኮኛ ደብዳቤውን አንብቦ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ ። ወሬው ከምኒልክ ዘንድ ደረሰ ። አጤ ምኒልክ ምርኮኛ ውን አስጠርተው ደብዳቤው እየተነበበ ተተረጐመላቸው ። ደብዳቤው ካለቀ በኋላ ምኒልክ በነገሩ አዝነውና አልቅሰው “ሂድ በነፃ አሰናብቸ ሃለሁ ። የእናትህ እምባ አማለደህ” ብለው በበቅሎ አድርገው አሥ መራ ድረስ አሸኝተው ሰደዱት ።

በሊቀ ጳጳሱ መልክተኛ በሞንሲኞር ማካሪዮ የሚመራው ቡድን አዲስ አበባ እንደገባና የሊቀ ጳጳሱን ደብዳቤ ካቀረበ በኋላ ለምርኮ ኞቹ ከየዘመዶቻቸው የተላከውን ስጦታ ለመስጠት እንዲፈቀድለት ጠየቀ ።

ምኒልክም ሁለት ምርኮኞች ለማካሪዮ አቅርበው የተላከውን ስጦታ እንዲቀበሉ አደረጉ ። የኢጣሊያ ሕዝብ 1,752,181 ሊሬ አዋጥቶ ዕቃ ገዝቶ ለምርኮኞቹ ልኮ ነበር ። የተላከውም ዕቃ ቦት ጫማ ፣ ጨርቃጨርቅ ፣ እስፖንጅ ፣ ብሩሽ ፣ ፒፖ ፣ ሰዓት ፣ ሳሙናና የመሳሰሉ ነበር ።

ኢጣሊያኖች ምርኮኞቹን አስፈትተው እንደገና ድጋሚ መልስ ለመውጋት ያሰቡት አሳብ አልሆንላቸው አለ ። ከዚህ በኋላ የተጠናከረ ጦራቸው ኤርትራን እንዲጠብቅ ሆኖ ጥቅምት 17 ቀን 1889 ዓ.ም. የእርቅ ውል ከምኒልክ ጋር ለፀኛ ጊዜ ተዋዋሉ ። ውሉም የሚከተለው ነበር ።

በኢትዮጵያ መንግሥትና በኢጣሊያ መንግሥት መሀል የተደረገ የእርቅ ውል ይህ ነው ። በቅድስት ሥላሴ ስም እንጀምራለን ።

ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክና በስም መጀመሪያ ኡምቤርቶ የኢጣሊያ ንጉሥ ጦርነት ለማስቀረት ዱሮ የነበረውን ፍቅራቸውን መልሰው ለማደስ ስለወደዱ ከዚህ ቀጥሎ የሚጣፈውን ውል ተዋዋልን ።

ይህንንም ውል ለመዋዋል ከኢጣሊያ መንግሥት ሙሉ ሥል ጣን የተቀበለ በሳንሞሪስና በሳንላዛር በኢጣሊያ ዘውድ ሊሻን የተሸ ለመ ፥ ማጆር ዶክተር ሲዛር ኔራሲኒን መርጠው ላኩ ። የማጆር ኔራ ሲኒ ስልጣን የተካከለ መልካም መሆኑ ስለታየኝ ፥ የክቡረ ማጆር ኔራ ሲኒ በኢጣሊያ ንጉሥ ስምና በጃንሆይ በዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የጋላም አገር ሁሉ ንጉሠ ነገሥት እርስዎ ተቀም ጠው ቀጥሎ የሚፃፈውን ክፍል ሁሉ ተስማምተው ተዋዋሉ ።

## መጀመሪያ ክፍል ።

በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መሐል የተደረገው ጦርነት ጭራሽ ቀር ቷል ። እንዲህ ስለሆነ በኢጣሊያ ንጉሥና በጃንሆይ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በወራሾቻቸውም በዜጐቻቸውም ፤ ለዘላለም እርቅና ፍቅር ይኖራል ።

## ሁለተኛ ክፍል

በ25 ሚያዝያ 1881 በውጫሌ ሠፈር የተደረገው ውልና በኋላ ታርሞ የተጨመረው ውል ሁሉ ጨርሶ ተፍቋል ። እንደተፋቀም ጭራሽ ይቀራል ።

## ሶስተኛ ክፍል

የኢጣሊያ መንግሥት የኢትዮጵያን ነፃነት እራሱን የቻለ ባለ ነፃ መንግሥት መሆኑን ጨርሶ ተቀብሏል ።

## አራተኛ ክፍል

እነዚህ ሁለቱ በዚህ ውል የሚዋዋሉ ነገሥታት በአገሩ ድምበር ነገር ሳይስማሙ ቢቀሩ በእርቁ ቶሎ ለመዋዋልና ለሁለቱም አገር የረፍት መልካም ፍቅር ለማድረግ ስለወደዱ እስከ ዓመት ድረስ ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና የኢጣሊያ ንጉሥ የመረጧቸው ሽማግሌዎች በፍቅር ተስማምተው የወሰኑን ነገር እንዲጨርሱ ተዋ ውለናል ። ወሰኑ እስኪወሰን ድረስ ግን ሁለቱ ተዋደው ዛሬ ባሉበት በመቆያው ወሰን በመረብና በበለሳ በሙና ወንዞች ላይ ሳይተላለፉ እረግተው ይቆያሉ ።

## አምስተኛ ክፍል

የኢትዮጵያና የኢጣሊያ መንግሥት ተስማምተው ይህን ወሰን እስኪጨርሱ ድረስ የኢጣሊያ መንግሥት ከዚህ አገር ለማንም ማን መንግሥት መስጠትና መልቀቅ አይቻለውም ። ዛሬም የኢጣሊያ መንግሥት በእጁ ከያዘው አገር መልቀቅ ያማረው እንደሆን ለኢትዮጵያ መንግሥት ይመልሳል ።

## ስድስተኛ ክፍል

የኢትዮጵያ መንግሥትና የኢጣሊያ መንግሥት የጥበብና የንግድ ሥራ ለመርዳት ቢፈልጉ ሁለቱ መንግሥታት ተስማምተው ውሉን ኋላ ማድረግ ይመቻቸዋል ።

## ሰባተኛ ክፍል

ይህ አሁን የተደረገው ውል እነዚህ ሁለቱ የተዋዋሉ ነገሥታት በጥንቃቄ ለሌሎች ነገሥታት ያስታውቃሉ ።

## ስምንተኛ ክፍል

ይህም አሁን ያደረግነው ውል ከዛሬ አንስቶ ሶስት ወር ድረስ በኢጣሊያ መንግሥት ፈጽሞ ይታተማል ።

## ዘጠነኛ ክፍል

ይህ ዛሬ የተደረገው የእርቅ ውል ተካክሎ ባማርኛና በፈረንሣይ ቋንቋ በሁለት ላይ ይጻፋል ። ታትሞም ሲያበቃ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና በኢጣሊያ ቤተ መንግሥት ይቀመጣል ።

በዚህ ተስማምተው ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እርስዎ እራስዎና የከበረ ማገርር ኔራሲኒ በኢጣሊያ ንጉሥ ስም ተቀባብለው በየማኅተማቸው ይህን ውል አተሙ ።

በጥቅምት በ፲፭ ቀን ተፃፈ አዲስ አበባ ከተማ ፲፰፻፹፱ ዓ. ም.

እዚህ ውል ላይ እስከ ዛሬ ድረስ ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልተገለጠ አንድ ታሪካዊ የሆነ አንቀፅ አለ ። እሱም 5ኛው አንቀፅ ነው ። አንቀፁ ውስጥ በግልጥ እንደሚታየው የኢጣሊያ መንግሥት ከያዘው የኤርትራ ይዞታው ለሌላ የውጭ መንግሥት መስጠት እንደማይችልና መልቀቅም የፈለገ እንደሆነ ኤርትራን ማስረከብ ያለበት ለኢትዮጵያ መንግሥት መሆኑን ይወስናል ።

ይህ አዋዋል 1ኛ ፣ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል መሆንዋን ፣ 2ኛ ምኒልክ ለጊዜው በጦር ኃይል ማስለቀቅ ባይችሉም የኢጣሊያ መን ግሥት አገሪቱን በሰላም መንገድ እንዲመልስላቸው መዋዋላቸውን ፣ 3ኛ ፣ የኤርትራ ጉዳይ በምኒልክ ዘመን ፍጻሜ ባያገኝ እንኳ በልጅ ልጅ ዘመንም ቢሆን ኤርትራ ለኢትዮጵያ እንድትመለስ የሚያነጋግ ነው ።

ምንም እንኳን ይህን የውጫሌን ውል የሚያስቀረውንና ጠንቶ የሚኖር የወዳጅነት ውል ቢዋዋሉም ምኒልክ ምርኮኞቹን ለመልቀቅ አልፈለጉም ። ያልፈለጉበትም ምክንያት አንደኛ ውሉ ተጽፎ በምኒልክ በኩል ተፈርሞ ማኅተም ሲታተምበተ በኢጣሊያኖች በኩል ግን ፊርማ ብቻ ተፈርሞበት ኢጣሊያ አገር ሔዶ ማህተም ይደረግበታል ስለተ ባለ ማህተም የተደረገበት የእርቁ ደብዳቤ እስቲደርሳቸው ድረስ ነው ። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ውሉ የኢጣሊያ መንግሥት ማህተም ተደርጎበት ቢመጣም እንኳ የእንግሊዝና የፈረንሳይ መንግሥታት በዚህ የእርቅ ውል ላይ ያላቸውን አስተያየት ለመጠበቅ ነበር ።

የኢጣሊያ ሕዝብ ስለምርኮኞቹ መለቀቅ መንግሥቱን ወጥሮ ይዞ ስለነበር የኢጣሊያ መንግሥት ስለምርኮኞቹ በአስቸኳይ መለቀቅ እና ካሣ ጉዳይ ደግሞ ከምኒልክ ጋር የሚከተለውን ውል ተዋዋለ ።

ስለኢጣሊያ ወታደሮች ምርኮኞች

የሚደረገው ውል ይህ ነው ።

ይህን ውል በቅድስት ሥላሴ ስም እንጀምራለን ።

በጃንሆይ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ፣ በጋላም አገር ሁሉ ንጉሠ ነገሥትና በከበረ ማጆር ኔራሲኒ ከንጉሥ ኡምቤርቶ ሙሉ ሥልጣን ተቀብሎ የተላከ ። ቀጥሎ የተጻፈውን ውል ተስማምተው ተዋዋሉ ።

## መዠመሪያ ክፍል

በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መንግሥት መሀከል ዛሬ ስለተደረገው የእርቅ ውል በኢትዮጵያ መንግሥት ያሉ የኢጣሊያ ወታደሮች ምር ኮኞች ተለቀዋል ። ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እነኚህን ምርኮ ኞች በማፍጠን ሰብስበው ይህ የእርቅ ውል ተጠንቅቆ ታትሞ ሲመ ጣላቸው ሐረርጌ ላይ ከኢጣሊያ መንግሥት ሙሉ ሥልጣን ተቀብሎ ለመጣ ሰው ያስረክባሉ ።

## ሁለተኛ ክፍል

እነኚህ የጦር ምርኮኞች ወደ አገራቸው ሲመለሱ እንዳይችገሩ ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የኢጣሊያ የቀይ መስቀል ማህበሮች ጀልዴሳ ድረስ መጥተው እንዲቀበሉዋቸው ይፈቅዱላቸዋል ፡፡

## ሶስተኛ ክፍል

የኢጣሊያ ንጉሥ መልክተኞች እነኚህን ምርኮኞች ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በብርቱ አቀማጥለው ማስቀመጣቸውን እሱ ራሱ ስላየ ፣ እንዲህም አድርጎ አቀማመጥ ለማስቀመጥ ብዙ ገንዘብ እንደፈጀ ፣ ለእነኚህ ያወጡትን ገንዘብ የኢጣሊያ መንግሥት እንዲከፍል ባለዕዳ መሆኑን ተቀብሏል ፡፡

ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግን የዚህን የገንዘቡን ኪሣራ ነገር የኢጣሊያ መንግሥት እንዳወቀ ፈርዶ ሊሰጣቸው ፍርዱን በኢጣሊያ መንግሥት ላይ ጥለውታል ፡፡ በዚህም ውል ተስማምተው ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እርሳቸው ራሳቸውና የከበሩ ማጆር ኔራሲኒ በኢጣሊያ ንጉሥ ስም ተቀባብለው በየማህተማቸው ይህን ውል አተሙ ፡፡

በጥቅምት በ፲፯ ቀን በአዲስ አበባ ከተማ በ፲፰፻፹፱ ዓ.ም. ተጻፈ ፡፡

ምኒልክ የምርኮኞቹን ማስለቀቂያ ውል ቢዋዋሉም ምርኮኞቹን ወዲያውኑ አለቀቁም ፡፡ የሌሎቹን መንግሥታት አስተያየት ሲጠብቁ ቆይተው ምንም ተቃውሞ ባለማሰማታቸው አምስት ወር ከአስር ቀን ቆይተው ኔራሲኒ ከኢትዮጵያ ግዛት ከወጣ በኋላ የምርኮኞቹን መለቀቅ ምኒልክ በይፋ አሳወቁ ፡፡ ይህንንም የእስረኞቹን መለቀቅ ጂቡቲ ሆኖ ለሚጠባበቀው ለማጆር ኔራሲኒ በደብዳቤ አሳወቁት ፡፡

ይድረስ ከማጆር ኔራሲኒ
የኢጣሊያ ንጉስ ባለሙሉ ሥልጣን መልክተኛ ፡፡

ጂቡቲ በ፲፪ የካቲት በ፲፰፻፺፯ በሙሴ ሞንዶን እጅ የላከው የስልክ ቃል ደረሰልኝ ፡፡ በኢትዮጵያ መንግሥት ውስጥ ተማርከው የነበሩትን የኢጣሊያ ምርኮኞች ሁሉ በአዋጅ አሰብስቤ ልቅም አድርጌ ወዳገራቸው ሰድጃቸዋለሁ ፡፡

በመጋቢት በ፲፯ ቀን በአዲስ አበባ በ፲፰፻፹፱ ዓ ም ተጻፈ ፡፡

ኢጣሊያ በ፫ኛው የምርኮኞች የውል ክፍል ቃል በገባችው መሠረትና የጦር ካሣ ጭምር አስር ሚሊዮን ሊሬ ለኢትዮጵያ መንግሥት ከፈለች ፡፡

ይህም ገንዘብ የኢትዮጵያ መንግሥት ለአድዋ ጦርነት ያወጣውን
ወጪ በእጥፍ የሚተካ ነው ይባላል ።

ምርኮኞቹ ተለቀው ከኢትዮጵያ ሲወጡ እንዴት እንደነበር ትረካ
የምናገኘው ከግሊከን መጽሐፍ ነው ። የኢጣሊያ ምርኮኞች በተለቀ
ቁበት ሰሞን የእንግሊዝ መልክተኛ በመሆን በሐረርጌ በኩል ወደ አዲስ
አበባ የገባው ግሊከን በመጽሐፉ ውስጥ አልፎ አልፎ የምርኮኞቹን
ሁኔታ ይገልፃል ። ባንድ ላይ ሳቀናጀው እንደሚከተለው ይላል ።
"....ከዳደብ እንደተነሳን ሁለት የኢጣሊያ መኰንኖችና 196 ተራ
ወታደሮች አበሻ ውስጥ ታስረው የነበሩ ወደ ጠረፍ ሲሄዱ አገኘና
ቸው ። ሁለም የሚሄዱት በእግራቸው ሲሆን አንድ ሁለት ያህል ቁስ
ለኞችና ሕሞምተኞች ብቻ በቅሎ ላይ ተቀምጠው ይሄዳሉ ።....
ጠቋቁረዋል እንጂ ጤነኞችና በሚገባ የተያዙ ናቸው ። ከመኰንኖቹ
ጋር ጥቂት ተነጋገርን ።....እዚች ቦታ እስኪደርሱም 38 ቀናት ሆኖ
አቸዋል ። በመጀመሪያዎቹ አንድና ሁለት ሳምንታት በመንገዳቸው
ላይ የሚበሉት ምግብ ለማግኘት ከባድ ችግር ደርሶባቸው ነበር ።
የአገሬው ሕዝብ ምንም ነገር አልሸጥላቸው ብሎ እምቢ ብሎ ነበር ።
ሐረር ሲደርሱ ግን ከአገራቸው የመጣውን የኢጣሊያን የቀይ መስቀል
ማኅበር ስላገኙ ልብሳቸውን አልብሶ ለቀሪው ጉዞአቸው ስንቅ የሚ
ሆን ምግብ አስይዟቸዋል ።

"....ቢያ ቀቦባ ስንደርስ....የኢጣሊያ ቀይ መስቀል ማኅበር
በካፒቴን ብራኮ የሚመራው ቡድን ብዙ ድንኳኖች አስተክሎ ቢኖ ፣
ቢራ ፣ የተጣራ ውሃና ሁሉን ነገር አከማችቷል ። ይህ ሁሉ ለኢጣሊ
ያኖች እስረኞች ነው ። እስረኞቹም መቶም ከዚያም በላይ እየሆኑ በየ
ጊዜው ይደርሳሉ ። ካፒቴን ብራኮ ከኛ ጋራ ምግብ በላ ። በደግነቱም
ጥቂት ሣጥን ቢራና ኪአንቲ ሰጠን ። ይህም ዘይላ ለሚደርሱ እስረ
ኞች ሐሪንግተን ስለሚያደርግላቸው ደግነት ብድር ነው አለን ። በማ
ግስተም ሰባት የኢጣሊያ መኰንኖች ያሉበት 200 ወታደሮች መጡ ።
እኛም ግመሎቻችንን ለማሳረፍ ፣ ሸሚዞቻችንን ለማጠብና በጠቅላ
ላው ጓዙ በሙሉ እንዲያርፍ አንድ ቀን ውሎ አድርገን ነበርና ማታ
ጥቂቶቻችን ፣ እስረኞች ከነበሩት ጋር ለመጫወት ወደ ሠፈራቸው
ሄድን ። በሐሩሩ ምክንያት ጠቋቁረዋል ፣ ደክመዋል ። ጤናቸው ግን
ጥሩ ነው ። በጉዞአቸው ም ችግር አላጋጠማቸውም ። ከብዙ ጊዜ እስረ
ኛነት በኋላ ከኤሮፓውያን ጋር በመገናኘታቸው በጣም ደስ ብሏቸ
ዋል ። ከአድዋ እስከ አዲስ አበባ እስኪጓዙ ድረስ በመንገድ ላይ ስላ
ጋጠማቸው ብዙ አጫወቱን ። ማራኪዎቻቸው በደንብ እንዳልያዙዋ
ቸው ፣ የምግብ ችግር እንደነበረባቸውና አበሾችም ቢሆኑ ለራሳቸውም
የሚበሉት እንዳልነበራቸው አጫወቱን ። አዲስ አበባ እንደደረሱ ግን

ምኒልክ በሚገባ እንደያዙዋቸውና አንድ ኢጣሊያዊና አንድ አበሻ ቢጣሉም ነገሩን አጣርተው አበሻውን እንዴት እንደቀጡት ፣ በዚህም ምክንያት ማራኪዎቻቸው ወይም አስተናጋጆቻቸው በሚገባ እንደያዙዋቸው. . . . አጫውቱን. . . .

"ወደ ቀርሳ ስንጓዝ ከእሥር የተፈቱ 13 ኢጣሊያኖችን አገኘን ። አብዛኛዎቹ የታመሙ ወይም የቆሰሉ ናቸው ። አልፈውን ሄዱ ።. . . . ያልገለጽኩት ነገር ከሐረር ስንነሳ ጀኔራል አልቤርቶኒ ከ200 እስረኞች ጋር ሐረር ገብቶ ነበር ። እኛም አልተገናኘናቸውም ። . . . . ሾላ ልንደርስ ስንል በመንገድ ላይ አንድ የኢጣሊያ ጦር መድፈኛ የነበረ መቶ አለቃ ኢጣሊያዊ አገኘን ። እሱም እንደነገረን ከአገሪቱ ለመውጣት የመጨረሻው ኢጣሊያዊ መሆኑን አጫወተን. . . .ግን ያሉበት ያልታወቁ ኢጣሊያኖች ቀርተዋል ። በአሁኑ ጊዜም ሊገኙ እንዳልቻሉ ነገረን ።. . . .ባልጪ እንደደረስን ሰፊ በሆነ ጥርጊያ መንገድ ተጓዝን ። መንገዱንም የሠሩት የኢጣሊያ ምርኮኞች ናቸው ።. . . ." በማለት ጽፈዋል ።

# የኢትዮጵያ ዕድገት

"....ምኒልክ ዘመናዊ ኢትዮጵያን የፈጠረ ሰው ነው...."

ኢንስክሎፒዲያ ብሪታኒካ

አጤ ምኒልክ ከነገሡ በኋላ እስካሁን እንዳነበብነው መሣፍን ቱንም ሆነ ባላባቱን በወዳጅነትና በፍቅር ስለተቃረቡት አብዛኛው ያለምንም ደም መፋሰስ ሲገብርላቸው እምቢ ያለውንም በጦር ኃይል እያስገበሩ ፣ የወጋቸውን መልሰው ስለሚሾሙ ፍቅር በዝቶ ከተቢታተ ነችው ኢትዮጵያ ዛሬ ያለንባትን ኢትዮጵያን መሠረቱ ።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ እጅግ በጣም ሥራ ወዳድ ሰው ነበሩ ። ሥራ ወዳድ በመሆናቸው ብዙው የሥልጣኔ ሥራ ወደ አገራችን የገባው በምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው ። አጤ ምኒልክ በዘመናቸው በኤሮፓ የነበረ የሥልጣኔ ሥራ ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ አድር ገዋል ። ማስገባት ብቻ ሳይሆንም ሌሎችን ለማበረታታት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚገባውን አዲስ ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሠሩት ወይም የሚጠቀሙበት ምኒልክ ራሳቸው ነበሩ ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጀመሪያዋን አውቶሞ ቢል የነዱ ምኒልክ ናቸው ። በኢትዮጵያ ሾፌሮች ታሪክ ውስጥ ፔርፌ ክት ድራይቨር የሚለውን የመጀመሪያውን የመንጃ ፈቃድ የተቀበሉ ምኒልክ ናቸው ። በመኪና የሚፈጨውን እህል የሚፈጨው ጋኔን ነው ተብሎ ይታመን በነበረበት ጊዜ ጋኔን ያለመሆኑን ለማሳወቅ የመ ጀመሪያውና የመጨረሻውም ኢትዮጵያዊ ዱቄት አስፈጭ ንጉሥ ምኒልክ ናቸው ። የመጀመሪያውን ስልክ አስገብተው ጋኔን ከዘፋት አጠገብ ይውጣ ብለው የዘመኑ ጳጳስ ጭምር ከባድ ተቃውሞ ቢያነሱባ ቸው ታግለው ስልክን የመሠረቱ ምኒልክ ናቸው ። የመጀመሪያዋን ብስክሌት መንዳት ተምረው የነዱ ምኒልክ ናቸው ። ጣይቱን ብስክ ሌት መንዳት አስተምረው ሴቶች ከመሸፋፈንና ከማፈር እንዲወጡ የታገሉ ምኒልክ ናቸው ። ሆቴል መብላት ነውር ያለመሆኑን ለማስተ ማር በአዲስ አበባ የመጀመሪያውን ሆቴል ከፍተው ሚስታቸውን ጣይ ቱን ወጥቤት አድርገው በገንዘባቸው መኳንንት እየጋበዙ ሆቴል መብ ላትን ያስተማሩ ምኒልክ ናቸው ። የዛሬውን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ

በ1881 ዓ.ም. በአዋጅ አረንጓዴ ፡ ቢጫ ፡ ቀይ ፡ እንዲሆን ያደረጉ ምኒልክ ናቸው ።

የተለያዩ አበቦችንና ጽጌረዳዎችን ከኤሮፓ እያስመጡ እስካሁን የምንጠቀምባቸውን ልዩ አበቦች ያራቡ ምኒልክ ናቸው ። የኩክ ፡ የእንጆሪ ፡ የወይን እና የመሳሰሉትን የአትክልት ልዩ ዘሮች እያስመጡ ያራቡ ምኒልክ ናቸው ። እስከዛሬ ለኢትዮጵያ ትልቅ ጥቅም የሚሰጠውን ባህር ዛፍን አስመጥተው የተከሉና ያባዙ ምኒልክ ናቸው ።

በአዲስ አበባ የመጀመሪያውን የውጭ አገር ትምህርት ቤት የከፈቱ ፡ የመጀመሪያውን የሙዚቃ ትምህርት ቤት ያቋቋሙ ምኒልክ ናቸው ። ኤሌክትሪክና ባቡር ያስገቡ ፡ ዘመናዊ የመንገድ ሥራ ያስጀመሩ ፡ ፖስታ ድርጅትን ያቋቋሙ ምኒልክ ናቸው ። ሰው ሲባል እኩል ነውና ማንም ሰው ፡ ሰውን ባርያ እንዳይል ብለው የባርያን ነፃነት ያወጁና ሰው እንደከብት እንዳይሸጥ የታገሉ ምኒልክ ናቸው ። ሴት ልጅ በወላጆችዋ ምርጫ ሳይሆን በፈቃድዋ የመረጠችውን ባል እንድታገባ ያወጁና ለሴት ልጆች ነፃነት የታገሉ ምኒልክ ናቸው ። ሠራተኛ በሥራው እንዳይበደል አዋጅ ያስነገሩ ፡ ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ አስገዳጅ ሕግ ያወጡ ምኒልክ ናቸው ። የተሠራ ጨርቅ ከማስመጣት ይልቅ ድር እያስመጡ ማሠራት እንደሚረክስ አውቀው ድር ማስመጣትን የጀመሩ ምኒልክ ናቸው ። ጥይት ፋብሪካን ሲያቋቁሙ ‘‘አፍሪካውያን ነፃ መውጣት አለባቸው ፡ ኢትዮጵያም የጥንት ክብርዋን ፡ ወሰንዋን በሙሉ ለማስከበር ትነሳለች’’ ብለው ለኤሮፓውያን ደብዳቤ የፃፉ ምኒልክ ናቸው ።

በ1874 ዓ.ም. ከተማቸውን እንጦጦ ካደረጉ በኋላ በአምስተኛው ዓመት ቁልቁለቱን ወርደው ዋና ከተማቸው አዲስ አበባ እንዲሆን የወሰኑ ምኒልክ ናቸው ። ስለምኒልክ እጅግ በጣም ብዙ ታሪክ አለ ።

በመላው ዓለም ዝናቸው የታወቀው ታላቁ ምኒልክ ዝናቸውን ያገኑት በሥራቸው እንጂ በዘራቸው አልነበረም ። ሹመት በዘር እንጂ በሥራ ባልነበረበት ዘመን የተገኙት ምኒልክ የሚሾሙት የተገላቢጦሽ ነበር ። ሹመት በሥራ ብለው ያወጁም ምኒልክ ናቸው ።

ለዚህ ጉዳይ የሚሆን አንድ ምሳሌ ላምጣ ። የንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ እናት ወይዘሮ አያህሉሽ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ ናቸው ። በዚህ ምክንያት ምኒልክና ወልደ ጊዮርጊስ የታናሽና የታላቅ ልጆች ናቸው ። ምኒልክ ፡ ንጉሠ ሸዋ ሲባሉ ወልደ ጊዮርጊስ የደጃች ጉበና አሽከር ነበሩ ። ምኒልክ ጉበናን ጠርተው ‘‘ወልደ ጊዮርጊስን ሥራና

ውጊያ እንድታስተምረው አሽከር አድርጌ ሰጥቼሃለሁ” አሏቸው ። አቶ ወልደ ጊዮርጊስም በጐበና ቤት እያገለገሉ ብዙ የጀግንነት ሥራ ከሠሩ በኋላ ፊታውራሪ ተባሉ ። አገር በማቅናት ተግባር የጐበና ተካፋይ ሆነው በመገኘታቸው ደጃዝማች ተባሉ ። በኋላም ራስ ተባሉ ። እንዲህ እያሉ በሥራቸው አደጉ እንጂ ምኒልክ ወንድሜ ነው ብለው እንዲያው በዋልፈሰስ አልሾሟቸውም ። ወንድማቸው ወልደ ጊዮርጊስ የሰው ቤት አሽከር በነበሩበት ጊዜ ፥ በጦርነት ተማርከው ቤተ መንግሥት የሰለጠኑት የተለያዩ ብሔረሰብ የሆኑት ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ፥ ደጃዝማች ባልቻ ፥ ወህኒ አዛዥ ወልደጻዲቅና ሌሎችም ፥ የቤተመንግሥት ታላላቅ መኳንንትና አድራጊ ፈጣሪ ነበሩ ። ምኒልክ ሰውን በሥራ እንጂ በዘርና በጐሣው የማይሾሙ ነበሩ ።

ማንኛውም መኳንንት በየአገሩ ላይ ከሚያገኛቸው የእጅ ሥራ አዋቂዎች መሀል የምኒልክን ድርሻ ወደ አዲስ አበባ እንዲልክ አዘዋል ። ምኒልክም ለእነኚህ ከየአገሩ ለሚመጡላቸው የጅ ሥራ አዋቂዎች ከቤተ መንግሥቱ ፊት ለፊት ያለውን ቦታ ለማረፊያ ሰጥተዋቸዋል ። ሠፈሩም ሠራተኛ ሠፈር ይባል ነበር ። እስከዛሬም በዚያው ስሙ ይጠራል ።

ምኒልክ እነኚህን ሠራተኞች ከሰበሰቡ በኋላ የጅ ሥራ አዋቂዎቹ በሕብረተሰቡ ጥላቻ ከኅብረተሰቡ የተገለሉ ሆኑ ። በዚህ የሚናደዱት ምኒልክም አስደንጋጭ የሆነ ብርቱ አዋጅ አወጁ ።

ሠራተኛን በሥራው የምትሰድብ ተወኝ ።

ከዚህ ቀደም ብረት ቢሠራ ጠይብ ፥ ሸማ ቢሠራ ሸማኔ ፥ ቢጽፍ ጠንቋይ ፥ ቤተክርስቲያን ቢያገለግል ደብተራ እያላችሁ ፥ አርሶ ነጪን ከጥቁር አምርቶ የሚያገባውን አራሽ ከዘውድ ይበልጣል የሚባለውን ገበሬ እያላችሁ ፥ ነጋዴን ነግዶ ወርቁን ግምጃውን ይዞ ቢገባ አንተ ነጋዴ ገጣባ አጣቢ እያላችሁ ፥ በየሥራው ሁሉ ትሰድባላችሁ ልጁ ምናምን ሥራ የማያውቀው ሰነፉ ፥ ብልሁን እየተሳደበ አስቸገረ። ቀድሞም ይህ ሁሉ ፍጥረት የተገኘው ከአዳምና ከሄዋን ነው እንጂ ሌላ ሁለተኛ ፍጥረት የለም ።

ይህ ሁሉ ካለመማር የተነሣ ነው ። አዳምንም ብላ በአፈ ገጽከ ብሎታል ። ይህ ከቀረ ሁሉ ቦዘንተኛ ከሆነ መንግሥት የለ ፥ አገር የለ ። በወዲያ አገር ግን በኤሮፓ ሁሉ አዲስ ሥራ አውጥቶ መድፍ ፥ ነፍጥ ባቡር ቢሠራ ሌላውንም እግዚአብሔር የገለጠለትን ሥራ ሁሉ ቢሠራ መሐንዲስ እየተባለ እየተመሰገነ ሠራተኛውም ብዙ ይጨምር

ለታል እንጂ በሥራው አይሰደብበትም ። እናንተ ግን እንዲህ እየተሳ ደባችሁ አገሬን ባዶ ልታደርጉትና ልታጠፉት ነው ።

እንግዲህ ግን እንዲህ ብሎ የተሳደበ እኔን የሰደበ ነው እንጂ ሌላውን መስደብ አይደለም ። ዳግመኛ ግን ሲሳደብ የተገኘ ሰው መቀ ጫውን አንዳንድ ዓመት ይታሠራል ። ሹማምንትም አስረህ ዓመት ለማስቀመጥ የሚቸግርህ የሆነ እንደሆነ አስረህ ወዲህ ስደድልኝ ።

ጥር ፲፯ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም. ።

ከዚህ አዋጅ እንደምንረዳው የምኒልክ ሠራተኛ መውደድ ከማ ንኛውም ንጉሥ የበለጠ ነው ። ማንኛውም ንጉሥ ከማንም በላይ ዘውድ ነው ሲል ምኒልክ ግን ከዘውዱ በላይ ገበሬ ነው ማለታቸው የተለየ ያደርጋቸዋል ። ሠራተኛን የሰደበ እኔን ሰደበ ማለታቸውም ምኒልክ ምን ያህል ሠራተኛ ወዳድና ሠራተኛ እንደነበሩ ይገልፃል ።

ምኒልክ ሠራተኛን የሚወዱት አዋጅ በማወጅና በሥራው ብቻ አልነበረም ። ከእሳቸው በፊት ያልነበረ ለሠራተኛ ደሞዝ መክፈል የጀመሩ ምኒልክ ናቸው ። የእንጀራ ቤት ሠራተኞች ማለት እንጀራ ጋጋሪዎች ፡ ሥራ ቤቶች ፡ አቡኪዎችና ይህን የመሳሰለ ሥራ የሚሠሩ ባመት ፲፯ ጥሬ ብርና ሶስት ሜትር አቡጀዲ ብትን ጨርቅ ለእያንዳ ንዳቸው ሲሰጥ በየወሩም ስድስት ቁና እህል ይሰጣቸዋል ። በየቀኑም ጠቅላላው የቤተ መንግሥቱ ተራ ሠራተኛ አንድ ጋሬና አንድ ማኛ እንጀራ ፡ አንድ ትልቅ ጭልፋ የሥጋ ወጥ (ጦም ከሆነ የክክ ወጥ) ለቁርስ ሲሰጥ ፡ ለምሳ ድርጎው ያው ሆኖ አንድ ኩባያ ጠላ ይጨመ ራል ። ራትም እንደዚሁ ነው ። ሠራተኛው ምግቡን የሚበላበት ትልቅ አዳራሽ አለው ። በአዳራሹም ውስጥ ረጅም ጠረጴዛ ተዘርግቶ እያንዳ ንዱ ሠራተኛ የሚጠቀምበትም የራሱ ቦታ አለው ።

ብረት ቀጥቃጮች በየወሩ አንዳንድ ብር ደሞዝ ሲኖራቸው ፣ በያመቱ ከ25 እስከ 33 ብር ድረስ በጉርሻ መልክ ይሰጣል ። የወር ቀለብ እህልና የዓመት ልብሳቸው ከደሞዛቸው ሌላ ይሰጣል ። ድንጋይ ጠራቢዎች በየወሩ አንዳንድ ጥሬ ብር ደሞዝና እህል ሲሰጣቸው በያመቱ ሶስት ሜትር አቡጀዲ ይታደላቸዋል ።

ለድንጋይ ቀጥቃጭ ወይም ፈላጭ አለቆች በየወሩ ሶስት ብር ተኩል ሲከፈል ፣ ድንጋይ አጠራረቡን ለሚያስተምሩ ለሁለት አረቦች ላንደኛው ዘጠና ብር ለሁለተኛው መቶ ብር ይከፈል ነበር ።

በሥጋጃ ሥራ ለተሰማሩ ሴት ሠራተኞች የወር ደሞዛቸው ሁለት ብርና አንድ አሞሌ ጨው ሲሆን ፡ ባመት ሁለት ጊዜ ልብስ ይሰጣቸ

ዋል ። የየቀኑ ምግባቸው ከቤተ መንግሥቱ ነው ። አንድ መቶ ፈትል ፈታይ ሴቶች በቤተመንግሥቱ ነበሩ ። እነዚህም ሴቶች የምኒልክንና ለሽልማት የሚሰጥ ልብስ ፡ ቀጭን ፈታይ ስለነበሩ ደሞዛቸው ከሌሎቹ ሴቶች አጠፌታ ነበር ። ከመንዝ የመጡ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ባና ሠሪዎች ነበሩ ። ባና በዚያ ዘመን ብዙ ጥቅም ነበረው ። ከልብስነት እስከ ድንኳንነት ያገለግል ስለነበር የባና ሠራተኛ ደሞዝ ከብረት ሰሪዎች ደሞዝ ጋር ተመሳሳይ ነበር ።

በቤተ መንግሥቱ አርባ ያህል ወጥ ሰሪዎች ሲኖሩ የእነሱም ደሞዝ በየወሩ እስከ ሶስት ብር እንደየማዕረጋቸው የሚከፈላቸው ነበሩ ። ድርጎአቸው ግን እንደሌላዎቹ ተመሳሳይ ነው ። ከወጥ ቤት ሠራተኞች የደሞዝ ብልጫ ያላቸው አምስት ሴቶች ነበሩ ። እነኚህም ሴቶች የምኒልክንና የመኳንንቱን የቅምሻ ወጥ የሚሠሩ ናቸው ።

ምኒልክ ብዙ ጊዜ በሠራተኞች መሀል እየተገኙ አርአያ በመሆን ያበረታቱ ነበርና ወደሠራተኞቹ ዘንድ በሄዱ ቁጥር ሠራተኛው ቆሽሾ ያዩታል ። ለምን እንደማይታጠቡ ሲጠይቋቸው የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ እንዶዱን ስለጨረሰውና ያለውም እንዶድ በግል ሰዎች ስለ ተያዘ በእንዶድ ማጣት ምክንያት መሆኑን ነገሩዋቸው ። ምኒልክም "ከሰው አትጣሉ ፡ እግዚአብሔር ያበቀለውን እንዶድ ለእናንተ አልሰጥ ካሉ ለእናንተ ደግሞ እኔ አለሁላችሁ" ብለው እያንዳንዱ ሠራተኛ በየአሥራ አምስት ቀኑ አንዳንድ ኪሎ ግራም ሣሙና እንዲሰጣቸው አዘዙላቸው ።


ምኒልክ በሥራው ሁሉ ከሠራተኞቻቸው የማይለዩ ሰው ነበሩ ። ምኒልክ ለሥራና ለሠራተኛ ያላቸው ክብር የተለየ ነበር ። ለዚህም ማስረጃ የሚሆን ለሞንድ በተባለው የፈረንሳይ ጋዜጣ ላይ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የነበረው ክሉቢ ስኪ የጻፈውን እንመልከት ።

"....ስለሚዘረጋው የባቡር መስመር ጉዳይ ከፈረንሳይ ሚኒስትር ጋር ጉባኤ አድርገው ሲነጋገሩ አንድ አሽከር ገባና በጆሮአቸው አንድ ነገር ነገራቸው ። እንደመሰለኝ 'ጌቶች ። ቁልፍ ሠሪው ለቁልፉ መግጠሚያ ሚስማር ይፈልጋል' ያላቸው መሰለኝ ። ምኒልክም የግምጃ ቤቱን ቁልፍ አውጥተው ሰጡትና 'አምስት ሚስማር አውጣና ውሰድለት ። አይበቃም ያለህ እንደሆን ተመልሰህ ናና ንገረኝ' አሉት ። ከዚህ በኋላ የተቋረጠው ንግግራችን ቀጠለ....ጥቂት ቆይቶ ደግሞ ሁለት የፈረስ ዘበኞች ገቡና 'ጌቶች ። በቅሎዎቹ ወጥተው ሔዱ ።....ፈለጋቸውም አልገኝ አለ' አሉዋቸው ። ምኒልክም ከዙፋናቸው ፈጥነው ወርደው ከፎቁ ባንደኛው ክፍል ገቡና በሩቅ ማያ መነጥራቸው የአካባቢውን

መንገድና ኮረብታ ሁሉ እያዩ ይፈልጉ ጀመር ። ጥቂት ሚስማር ወይም የሁለት እህዮች ጉዳይ የታላቁን ዋናውን ከተማ ከዓለም ጋር የሚያገናኘውን የባቡር ሐዲዱን ሥራ ንግግር አቋረጠ ።. . . .'' ብሏል ። ይህን ስናይ ምኒልክ ስነ ሥርዓትን ያልጠበቁ ቢያስመስላቸውም ዋናው ነገር የምኒልክ በር ለማንኛውም ሠራተኛ በማንኛውም ጊዜ ክፍት መሆኑን ያሳያል ።

ምኒልክ በየቀኑ ከተሲያት በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እየተዟዟሩ ሕዝቡ የሠራውን ሥራ ይጐበኛሉ ። ጥሩ ሥራ ሲያዩ ሰሪውን አስጠርተው አመስግነው የገንዘብ ጉርሻ ሰጥተው "ለከርሞ ደግሞ ሌላ ሠርተህ እንድታሳየኝ'' ብለው ያልፋሉ ። እንዲህ አይነቱንም የሥራ ጉብኝት በማድረግ እስከ 11 እና 12 ሰዓት ድረስ ይቆያሉ ። ከዚያ ተመልሰው በቤተ መንግሥቱ ግቢ በብስክሌት ይንሸራሸራሉ ። ". . . .ስለምኒልክ ብዙ ነገር ሰምቻለሁ ። የሚገርመው ነገር ምኒልክ በቤተመንግሥቱ ግቢ ውስጥ በብስክሌት ይንሸራሸራሉ ። እቴጌይቱ ያን ሁሉ ውፍረት ይዘው ብስክሌት ይነዳሉ ።....'' ሲል ቪቫን ጽፏል ።

ምኒልክ ታላቅ የሥራ ሰውና ሥራ ወዳድ መሆናቸውን ምን ምን ነገሮችን እንደሠሩና እንዳሠሩ ከታላላቅ ሥራዎቻቸው ጥቂቶቹን ቀጥሎ በመጠነኛ ዝርዝር እንመለከታለን ።



የመጀመሪያዋ ትምህርት ቤት

# ትምህርት

"....ምኒልክ ዘመናዊ ትምህርት ቤትን በመክፈት በኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናዊ የትምህርት ዘር የዘሩ ናቸው ።....ትምህርት ቤቱም የተሠራው ንጉሠ ነገሥቱ በሰጡት የግል ገንዘብ ነው ።...."

ጆን ማርካኪስ ።

ምኒልክ ዘመናዊ ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ለመክፈት ሲያስቡ ተቃውሞ ተነስቶባቸው ነበር ። ተቃውሞውም የውጭ ሰው የሚያስተምረው የውጭ ትምህርት በአገራችን ከገባ ሃይማኖታችን ይጠፋል በማለት ነበር ። ምኒልክ ግን ይህን እምነትና ጥርጣሬ ከሕዝቡ አእምሮ ለማጥፋት በሃይማኖት ከሚመሳሰሉዋቸው ከግብፅ መምህራን ለማስመጣት አስበው ለእስክንድርያው የኦርቶዶክስ ፓትርያርክ ደብዳቤ ፃፉ ።

ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ይድረስ ከአቡነ ቄርሎስ

በአዲስ አበባ ከተማችን ትልቅ የተማሪ ቤት ለማድረግ አስበ ናል ። ይህንንም አሳባችንን አባታችን አቡነ ማቴዎስ ሰምተው በሀገ ራችን በግብፅ ብዙ የተማሩ ፣ ለማስተማርም የበቁ ሰዎች አሉ ቢሉን ወደ እርስዎ ወደ አቡነ ቄርሎስ ልከው እንዲሰዱልን ያድርጉ ብለን ነግረናቸው ይሄው ጽፈውሎታልና ያቡነ ማቴዎስን ማህተም አይተው የሚገኝልዎ የሆነ እንደሆነ ያለ ትግስት በስልክ በቶሎ ቢያስታውቁን እንወዳለን ። ወደርስዎ መላካችን ከሌላ አገር ከማስመጣት ለትምህርት፣ ለሁሉም ነገር የሃይማኖት ወንድሞቻችን ቢመጡ ይሻላል ብለን ነው ።

ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም. አዲስ አበባ ተጻፈ

ይህን የምኒልክን ደብዳቤ በመደገፍ በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ሃይ ማኖት ሊቀ ጳጳስ የሆኑት አቡነ ማቴዎስ ደግሞ ወደ አቡነ ቄርሎስ ደብዳቤ ላኩ ። ለአቡነ ቄርሎስ የተላከውን በአረብኛ የተፃፈውን የአቡነ ማቴዎስን ደብዳቤ ብላታ ጳውሎስ ከአረብኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ የተረጐሙት እንዲህ ይላል ።

"ጃንሆይ ፣ በአዲስ አበባ ከተማዎ ታላቅ የተማሪ ቤት ለማድረግ ማሰባቸውን ብሰማ ካገራችን ከግብፅ ብዙ የተማሩ ለማስተማር የበቁ መምህራኖች አሉ ብዩ ባመለከታቸው ፣ እሺ ምን ከፋ ፣ ይህ እንደዚህ ያለው ነገር ፈቃዴ ነው ብለውኛልና አሁንም እርስዎ ካስተማሩዋቸው ከልጆችዎ ለመምህርነት የበቁ ፣ እንግሊዝና ፈረንሣዊ ፣ ደግሞ ሌላም ብልሐት ፣ ሂሳብም የሚያስተምሩ የቀናች ኦርቶዶክሣዊትን ሃይማኖት ተምረው የሚያስተምሩ መርጠው ይላኩልን ። የሚመጡትም የመም ህራን ቁጥር ፯ ወይም ፰ ይሁን ። የወር ደመወዛቸው ሺ—ሺ ብር ነው። ምናልባት ባዲስ አበባ ከተማ ብዙ ፈረንጆች አሉ ። አንዳቸው አንድ የተማሪ ቤት ለማቆም ይቻላቸዋልና የሚልኩልን መምህራኖች አጥብ ቀው የተማሩ ይሆኑ ።

"ይህንን ማለታችን ምናልባት በቋንቋ የሚፈታተን የተነሳ እንደሆን ሁላችን እንዳናፍር ብለን ነው ። ደግሞ ከትምህርት ጋራ ትሩ ፋት የመላባቸው ይሁኑ ። ለሰው እብነት የሚሆኑ ናቸውና ። ሥራቸው ያማረ እንደሆነ ክብሩ የርስዎ ነው ።

ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ ።

በዚህም ጥያቄ መሠረት ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ያላቸው 15 ግብፃውያን በ1898 ዓ.ም. በሃና ሳሌብ መሪነት አዲስ አበባ ገቡ ። ሐና ሳሊብም ትምህርት ቤቱ በ1900 ዓ.ም. በጥቅምት ወር በንጉሠ ነገሥቱ ተመርቆ ሲከፈት የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ሆነው ተሾሙ ። ትምህርት ቤቱም ለሴትና ለወንድ መማሪያ መሆኑ ታወጀ ።

አጤ ምኒልክ ከውጭ ይልቅ በውስጥ ያለው ክርክር ያስቸግራቸው ስለነበር ያን ሁሉ አሸንፈው ዛሬ በስማቸው የሚጠራውን ትምህርት ቤት ፣ የሙሴ ኤልግ መኖሪያ ቤት በነበረችው ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተዋት ማስተማር እንደተጀመረ ምኒልክ በ1898 ዓ.ም. የሚከተለውን አዋጅ አወጁ ።

አዋጅ ።

ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ።

ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

እስካሁን ማንም የጅ ሥራ አዋቂ የነበረ ሰው በውርደት ስም ይጠራ ነበር ። ስለዚህም ማንም ሰው ለመማርና ለመሰልጠን የሚደክም አልነበረም ። በዚህ ጉጂ በሆነ ሁኔታ ብንኖር ቤተ ክርስቲያኖች ይዘጋሉ ። ይልቁንም ክርስቲያን አይገኝም ።

በሌሎች አገሮች እያንዳንዱን ነገር ብቻ መማር ሳይሆን ፣ አዲስ ነገሮችም ይሠራሉ ። ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ ለወደፊት ወንድ ልጅችና ሴት ልጆች ሁሉ ከስድስት ዓመታቸው በኋላ ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይሁን ።

ልጆቻቸውን ለማስተማር ለማይተጉ ቤተሰቦች ፣ ወላጆቻቸው ሲሞቱ ፣ ንብረታቸው ለልጆቻቸው መሆኑ ቀርቶ ለመንግሥት ይተላለፋል ። ተማሪ ቤቶችንና አስተማሪዎችን የሚያዘጋጀው መንግሥቱ ነው ።''

ልጁን የማያስተምር ወላጅ ሀብቱ እንደሚወረስ ማወጅ ፣ እንኳን በዚያ ጨለማ ዘመን በሰለጠነውም ቦታ አስደንጋጭና ኃይለኛ አዋጅ ነው ።

ምኒልክ ሁሉንም እንደሞያው ያከብሩ ነበርና ነሐሴ 27 ቀን 1899 ለሐና ሳሊብ ለትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር የፃፉት ደብዳቤ እንዲህ ይላል ። ''ይድረስ ከሐና ። የትምህርት ቤት አለቃ ። አዲስ አበባ

ሰላም ላንተ ይሁን ።

ብሩ አንዳንድ ቀን እያረፈደ መምጣቱ እኔ ሥራ እያስያዝኩት

ነው እንጂ ለትምህርት ወስልቶ አይደለም ። ይህን ታውቅ ብዬ ነው።”

መጀመሪያ ነገር አስተማሪውም ቢሆን ምንም ነገር ሊያደርግ አይችልም ። እንኳን ከቤተ መንግስት የሚመጣው ልጅና የየመኳንንቱ ልጅ ሁሉ የፈለገ ቀን እየተማረ ፡ ሳይፈልግ እየቀረ ነበር ። ምኒልክ ግን የትምህርት ቤቱን ሥርዓት በማክበር ፡ የመምህሩንም ሞራል ለመጠበቅ ቢባል እንኳ ፡ በመልክተኛ ሊሆን የሚችለውን ነገር ራሳ ቸው ደብዳቤ ጽፈው ማህተማቸውን አትመው ጉዳዩን አሳወቁ ። ይህም ድርጊት የአስተዳደር ችሎታቸውን ከማስረዳቱም በላይ “ማን አለብኝነት” የማያጠቃቸው ንጉሥ እንደነበሩ ያሳውቃል ።

ምኒልክ ለትምህርት ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ ቢሆንም በዘመኑ የነበረው አስተሳሰብ ግን መማር ሃይማኖት ያስለውጣል ፡ የተማረ ሰው ፈሪ ይሆናል የሚል አስተሳሰብ ስለነበር ሕዝቡ ልጆቹን አላስተም ር አለ ። ቀደም ብሎ በተነበበው አዋጅ መሠረት ፈርቶ ልጆቹን ተማሪ ቤት ያስገባው ሁሉ እንደገና ልጆቹን ከተማሪ ቤት ያስቀር ጀመር ። በዚህ የተናደዱት ምኒልክ እንደገና በ1900 ዓ ም መስከረም 21 ቀን የሚከ ተለውን አዋጅ አወጁ ።

“በሀገራችን ትምህርትም ጥበብም ቢማር መስደቢያ ሆነ ። ስለዚህ የትምህርት ነገር ቀረ ። ትምህርት ሲቀር ቤተ ክርስቲያን ይዘጋል ። ቤተ ክርስቲያን ከሌለ ክርስትያንነት አይገኝም ። ሌላው አገር ፡ እንኳን ጥንት የነበረውን ትምህርት ሌላ አዲስ ጥበብ እያወጣ ይማራል ። አሁንም ልጅህን ወንዱንም ሴቱንም ከሰባት ዓመት በላይ ያለውን ከተማሪ ቤት እያስገባህ አስተምር ። የላስተማርህ ሰው እንደ መካን ሰው ርስትህን ሹም ይወርስሃል እንጂ ያልተማረ ልጅህ አይወርስ ህም ። ላስተማሪውም ቀለብና ደሞዝ እኔ እችላለሁ ።”

ምኒልክ አንዳንዶቹን ከትምህርት ቤት የቀሩትን ልጆችና ወላጆ ችንም ጭምር ልጆች ለምን ከተማሪ ቤት እንደሚቀሩ እየጠየቁ አጣሩ ። የሚቀሩብትም ዋናው ምክንያት አስተማሪዎቹ በመማታታቸ ውና በመሳደባቸው መሆኑ ታወቀ ። ይህን የተማሪዎቹን ሰበብ የሰ ሙት ምኒልክ የተማሪዎቹንም መብት ለማስጠበቅ ግብፃውያን አስ ተማሪዎቹን እንዲመክሩላቸው በኢትዮጵያ ተቀማጭ ለሆኑት ግብጻዊ ጳጳስ ደብዳቤ ጻፉላቸው ።

ይድረስ ከአቡነ ማቴዎስ

እነዚህ አስተማሪዎች የሚማሩትን ልጆች ሁሉ እየተማቱ ትም ህርትም አልገባቸው አለ ። ወጊዱ እያሉ አያሌ ልጆች ከትምህርት

ወጡ አሉ ። ማስተማር ድንጋይ እንደመውቀር ያህል ነው ። ዓመት ሳያዩዋቸው ወጊዱ ብሎ መስደድ መቼ መልካም ነው ። ደግሞስ የት ምህርት ነገር ባገራቸው የምንሰማው ፭ ዓመት ፮ ዓመት ድረስ ነው አሉ ። ይሂማ ቋንቋው ላገራችን ሰው እንግዳ ነው ። እነሱስ የሰው ባህርይ እየቻሉ ማስተማር ነው እንጂ በትንሹ ነገር ሁሉ ለምን ይበሳጫሉ ። ይህማ ሲሆን ጊዜ ምን የሚማር ሰው ይገኛል ። እኛስ ብዙ ደሞዝ መስጠታችን ባገራችን ትምህርት እንዲገባ ብለን አይደለምን። ደግሞ እነዚህን ለትምህርት የገቡ ልጆች ሁሉ አስተማሪዎቹ አያውቋቸውም ። ልጅ ዘውዴ ልጆቹንም ፣ አባታቸውንም ያውቃልና እሱ ባልደረባ ሆኖ የእገሌ ልጅ ወሳለተ ፣ የእገሌ ልጅ እንዲህ ሆነ እያለ ለእናንተም ለእኛም እያስታወቀን የወሳለተው ይቀጣል ብንል ባንድ ቦታ ሁለት ሹም አይሆንም ብለው ከለከሉ አሉ ። አሁንም ይኸው ለማስተርጐም ብዬ አቶ ገብሬን አድርጌአለሁና ደግሞ ከሱ ጋር ጠብ እንዳያደርጉ ይምከሩዋቸው ። ይህንን ወረቀት ግን ወደ እርስዎ መጻፌ እኔ ብነግራቸው ይደነግጣሉ ብዬ ነው ። የኔን መስማት ሳያስታውቁ በፈሊጥ አድርገው እንዲነግሩዋቸው ይሁን ።

ታህሳስ ፫ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ምኒልክ አዋጁን አውጀው ፣ ለጳጳሱም ደብዳቤ ጽፈው የተማሪዎቹን መመለስ ቢጠብቁም ልጆቹ ከትምህርት ቤቱ አልተመለሱም ። ልጆቻቸውንና አሽከሮቻቸውን ተማሪ ቤት አስገብተው መልሰው ላስወጧቸው መኳንንቶች ሁሉ ደብዳቤ እየጻፉ ተማሪ ቤት አስገብተዋቸው የነበሩትን ልጆች ሁሉ ወደ ተማሪ ቤት እንዲመልሷቸው አዘዙ ። የምኒልክ የትዕዛዝ ደብዳቤ የደረሳቸው መኳንንቶችም ለትእዛዝ ያህል ብቻ አንድና ሁለት የተጠሉ አሽከሮችን ወደ ተማሪ ቤት እየላኩ ሌሎቹን አስቀሩ ። ይህን የተረዱት ምኒልክ የትምህርት ቤቱን መዝገብና የስም መጥሪያ ደብተር አስቀርበው አንድ ሰው ስንት ልጆች ተማሪ ቤት አስገብቶ እንደነበረና ምን ያህሎቹ እንደቀሩ ካጣሩ በኋላ እያንዳንዱ መኳንንት ያስቀራቸውን ልጆች ሁሉ እንዲልክ የስም ዝርዝራቸውን ጭምር እየጻፉ ላኩ ። ምኒልክ እነዚህን ደብዳቤዎች ያጻፉዋቸው ታመው ደብረሊባኖስ ጠበል ሊነከሩ ሔደው በነበረ ጊዜ ነው ። ከእነዚያም ደብዳቤዎች ጥቂቶቹን እናንብብ ።

ይድረስ ከደጃዝማች ተፈሪ

አዲስ አበባ ፈረንጅ አስተማሪዎች ዘንድ ሲማሩ የነበሩት ያንተ አሽከሮች ለትምህርታቸው በመስከረም ተመልሰው አዲስ አበባ ይምጡ ብለን ነበር ። አስተማሪዎቹ መጥተው እነሱ እስታሁን ሳይመጡ

ቀሩ ። አሁንም በለጠ ገብረጻዲቅ ፣ ገብረየስ ፣ በሻህ ፣ ገብረ ሥላሴ ፣ ኃይሌ ፣ ደግሞ ኃይሌ ቆለጭ ፣ ላቀው ወልደየስ ፣ ተፈሪ በለው ፣ ጥበበ እሸቴና ፣ ዘውዴ ዳማ ፣ ዘገየ ቆለጭ ፣ ገብረኪዳን ነጋሽ ። እነዚህ ቶሎ አዲስ አበባ መጥተው ትምህርታቸውን እንዲማሩ ይሁን ። እንግዲህ ግን እነዚህ ልጆች እተማሪ ቤት ሳይመጡ የቀሩ እንደሆነ የአስተማ ሪዎቹን ደሞዝ እናንተ ትከፍላላችሁ ።

ታህሳስ ፴ ቀን ፲፱፻፩ ዓ.ም. ደብረ ሊባኖስ ተጻፈ ።

ይድረስ ከነጋድራስ ኃይለጊዮርጊስ

አዲስ አበባ ከፈረንጆች አስተማሪዎች ዘንድ ባንተ ስም የገቡት ተማሪዎች አበበ ወልደ ሚካኤል ፣ አበበ ይርጉ ፣ አባተ አይተንፍሱ ፣ በቀለ ዘገየ ፣ በሻህ ተክለሃይማኖት ፣ ገብረየስ ጋረድ ፣ ዘውዴ ዘመድ አገኘሁ ፣ ክፍሌ ወልደ ሕፃን ፣ ዘውዴ ግዛው ፣ ቅጣው ዘለለው ፣ ወርቄ አስጨናቂ ፣ ሸዋይርጋ ወልደሕፃን ፣ ስምረቱ ወልደሚካኤል እነዚህ እየወሰለቱ ትምህርቱን ትተዋል ብለውኛልና እነዚህን የተቆጠሩ ልጆች በቶሎ እተማሪ ቤት ገብተው እንዲማሩ ይሁን ። እንግዲህ ግን እነዚህ ልጆች ትምህርታቸውን ሳይማሩ የቀሩ እንደሆነ ግን ያስተማሪ ዎቹን ደሞዝ እናንተ ትከፍላላችሁ ።

ታኅሣሥ ፴ ቀን ፲፱፻፩ ዓ ም ደብረ ሊባኖስ ተጻፈ

ይድረስ ከራስ ወልደ ጊዮርጊስ

አዲስ አበባ ከፈረንጆች አስተማሪዎች ዘንድ ይማሩ የነበሩት የእርስዎ አሽከሮች አለነ አበሻ ፣ ጕበና አባመርጋ ፣ መሸሻ ወልደ ጻዲቅ እነዚህ እየወሰለቱ ትምህርት ትተዋል ብለው አስተማሪዎቹ ወደጃን ሆይ ቢልኩ እነዚህ የተቆጠሩት ልጆች በቶሎ ተማሪ ቤቱ ገብተው እንዲማሩ ይሁን ። እንግዲህ ግን እነዚህ ልጆች ትምህርታቸውን ሳይ ማሩ የቀሩ እንደሆነ ያስተማሪዎቹን ደሞዝ እናንተ ትከፍላላችሁ ብለ ዋል ። በጃንሆይ ማህተም አለመጻፌ የማህተሙ ሣጥን እሠፈር ቆይ ቶብኝ ነው ።

ታህሳስ ፴ ቀን ፲፱፻፩ ዓ.ም. ደብረ ሊባኖስ ተጻፈ ።

ምኒልክ ኢትዮጵያውያኖችን ለማስተማር ያላቸው ፍላጎት ከፍ ተኛ በመሆኑ ለመጨረሻ ጊዜ ለግድያ የተነሳባቸውን ሕመም ታመው ለጠበል ደብረ ሊባኖስ ሔደው እንኳን የተማሪዎቹን ጉዳይ አልረ ሱም ነበር ። በመጨረሻው ደብዳቤ ላይ ጻሕፈው “. . . . .የማህተሙ

ሣጥን እሠፈር ቆይቶብኝ ነው ” ያለበት ምክንያት በዚያች ሰዓት ምኒልክ ከሠፈራቸው ወጥተው ተራራው ሥር ጠበል በመነከር ላይ ነበሩ ። ጉዳዩ አስቸኳይ በመሆኑ ጸሐፊው ከጠበሉ ቦታ ደብዳቤውን ጽፎ የላከው በመሆኑ ነው ።

## ባቡር

አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ ያሰሩዋቸውን ኤሮፓውያን እስረ ኞችን ለማስለቀቅ የእንግሊዝ ጦር በመጣበት ጊዜ ጦሩ ከወደቦቻችን ወርዶ በኢትዮጵያ መሬት ሐዲድ ዘርግቶ መድፍና ከባድ ዕቃ በመን ኮራኩር በቀላሉ ያመላልስ እንደነበረ አጤ ምኒልክ ሰምተዋል ። መቅ ደላ ተቀምጠውም በነበረበት ጊዜ በዚያ ከነበሩ የውጭ አገር ሰዎች ጋር በመጫወት ብዙ ተምረዋል ። በተለይ የእስረኛው የዎልድሜየር ተማሪ ስለነበሩ ስለሐዲድ ባቡር በዝርዝር ነግሮአቸዋል ። ምኒልክ በሸዋ ንጉሥ ከሆኑ በኋላ ያን ሐዲድ አዘርግተው ባቡር ለማስገባት አሰቡ ። ይህም ሀሳባቸው እንዲፈቀድላቸው የበላያቸውን ንጉሠ ነገሥ ቱን አጤ ዮሐንስን ፈቃድ ጠየቁ ። በአጤ ዮሐንስ አካባቢ የነበሩ መኳንንቶች መክረው ምኒልክ ከግዛታቸው ከሸዋ ውጭ ሐዲድ ለመ ዘርጋት እንደማይችሉ ተነገራቸው ።

የአልፍሬድ ኢልግን ታሪክ የፃፈው ኬለር በመጽሐፉ ሲያትት “. . . .የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ለባቡር ሐዲድ ሥራ ብዙ ጓጉተው ነበር ። በእሳቸው መቸኮልና መጓጓት ምክንያት አልፍሬድ ኢልግ በሥራና በአሳብ ተጠምዶ ነበር ። የባቡሩ ሥራ እንዴት እንደሚካሄድ ለማሳየት አንድ ሞዴል ሰራ ። ሞዴሉ ጐታች ጋሪዎችን እየጐተተ በሐዲድ ላይ ሲሄድ የሚያሳይ ነበር ። ምኒልክም ሞዴሉን አይተው ተደሰቱ ። ኢልግ ሠራተኛ እንዲፈልግም ሙሉ ሥልጣን ሰጡት ። ኢል ግም ሙሉ ፈቃድ ካገኘ በኋላ የባቡሩ ሐዲድ ከወሰን ጀምሮ እንጦጦ ድረስ እንዳይሠራ አጤ ዮሐንስ ፈቃድ ስለከለከሉዋቸው ነገሩ ቀረ....” ይላል ።

አጤ ምኒልክ የሀዲዱን መስመር በሸዋ ውስጥ ብቻ መዘርጋቱ ምንም ጥቅም እንደማይሰጥ ተገንዝበው ፣ ጊዜ እስቲያገኙ አሳባቸውን አዘገዩት ። በኢትዮጵያ ላይ ሙሉ ሥልጣን አግኝተው ንጉሠ ነገሥት ከተባሉ በኋላ የሐዲዱ መዘርጋቱን አሳብ አንቀሳቀሱት ።

ፈረንሣዊው ሙሴ ፖውል ሶሌሌ በባቡሩ ሐዲድ መዘርጋት አሳብ ላይ ስሜት አደረበት ። ከአቦክ (ጂቡቲ ውስጥ) ተነስቶ አንኮ

በር ቢያርስ የሚያዋጣ መሆኑን አሰበ ። የምኒልክ የቅርብ ወዳጅና ነጋዴ የነበረው ፈረንሣዊው ሙሴ ሳቡሬ ለወዳጆቹ ለፈረንሣዮች ሲመክር ለመሥራት ቢፈልጉ ምኒልክ ሙሉ ሥልጣን እንደሚሰጧቸው ቃል ገባ ።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በ1882 ዓ ም በጥቅምት ወር ንጉሠ ነገሥት ሲሆኑ በኅዳር ወር ስለባቡሩ ጉዳይ እንዲነጋገርላቸው ሙሴ ሳቡሬን ወደ ፈረንሣይ ፕሬዚዳንት ወደ ሙሴ ካርኖ ዘንድ ላኩት ። ኤሮፓውያን ኢትዮጵያን ለመከፋፈል የሚያስቡበት ዘመን ስለነበረ የምኒልክ ጥያቄ አጥጋቢ መልስ አላገኘም ።

በአጥኒዎች በኩል በተደረገው ጥናት ሀዲዱ ያኔ ዱር ከነበረችው ከጂቡቲ እንጂ ፡ ከተማ ከነበረው ከአቦክ ቢነሳ ሥራው አስቸጋሪ እንደሚሆን ታወቀ ። አቦክ በዚያን ጊዜ የፈረንሣይ ቅኝ ግዛት የነበረችው የጂቡቲ ዋና ከተማ ይሁን እንጂ ወደብነቱ የማይወደድ ነበር ። ከዚህም ሌላ ሐዲዱን ከአቦክ ለመጀመር መንገዱ መልካም ባለመሆኑ ከጂቡቲ እንዲጀመር የመሐንዲሶቹ ጥናት ወሰነ ።

ምኒልክ ከፈረንሣይ መንግሥት የሚጠብቁት መልስ እየዘገየ በመሄዱ የቴክኒክ አማካሪያቸው የነበረው ሙሴ አልፍሬድ ኢልግ ከማንኛውም ኩባንያ ጋር ተዋውሎ ሀዲዱን ለማሠራት የሚችልበትን ፈቃድና የሚዋዋልበትን የውል ዓይነት መጋቢት 1 ቀን 1886 ዓ ም የተፃፈውን በማኅተማቸው አትመው ሰጡት ።

ይህን ፈቃድና የሚዋዋልበትን የመንደርደሪያ አሳብ ሙሴ ኢልግ ካገኘ በኋላ ከሽፍኔ ጋር በመሆን ፓሪስ ከተማ ውስጥ ቢሮ ከፈቱ ። ከዚያም ከፈረንሣይ መንግሥትና ከሀብታሞች ጋር ንግግር ጀመሩ ። ብዙ ሰዎች እንደሚሉት የባቡሩን ሐዲድ ሥራ በውል የተቀበለ ኢልግ ነው ይላሉ ። ኢልግ ከሌሎች ኩባንያዎች ጋር የሚዋዋልበትን የውል ዓይነት ተቀብሎ የምኒልክ ወኪል የሆነ ሰው እንጂ ራሱ እሠራለሁ ብሎ በሥራ ተቋራጭነት ከምኒልክ ጋር አልተዋዋለም ።

ስለ ሀዲድ መዘርጋት ጉዳይ የሚያነጋግሩዋቸው ሀብታሞች ሁሉ ''የባቡሩ መስመር ቢዘረጋ ምን ጥቅም ይገኝበታል?'' የሚል ጥያቄ ስላቀረቡ ጥናቱ ተፈጽሞ ውጤቱ ቀረበ ። ስለዚሁ ጥናት ጉዳይ ኬለር እንደፃፈው በ50,000 ግመሎች የሚጫን 12,000 ቶን ጭነት በያመቱ ከሸዋ ብቻ እንደሚወጣ ተረጋገጠ ። ይህም ጭነት ሲተነተን 33,000 የግመል ጭነት ቡና ፡ 1200 የግመል ጭነት ቆዳ ፡ 500 የግመል ጭነት የዝሆን ጥርስና ሌላም ዕቃዎች ናቸው ። ገቢው ዕቃስ? ተባለ ።

ወደ አገር ውስጥ በሚገባው በኩል 6,800 የግመል ጭነት ከጥጥ የተሠሩ ልብሶች ፡ 7500 የግመል ጭነት ጨው ፡ አንድ ሺ የግመል ጭነት የተለያዩ ዕቃዎች መሆናቸውን አጥኚው ኮሚቴ አረጋገጠ ። ይህም ገቢ ዕቃ ከጠረፍ አዲስ አበባ ድረስ 25 ቀን ጉዞ እንደሚፈጅበትና ላንድ ቶን ክብደትም ከ73 እስከ 77 ብር መከፈሉን አጠና ። ኬለር በመጽሐፉ እንደሚተነትነው በዚች ሀብቷ ባልተነካበት ድንግል መሬት ገብቶ ሥራ መጀመሩ ለኤሮፓ ብዙ ጥሬ ዕቃ ማቅረብ እንደ ሚቻል ተረጋግጦ ሀብታሞች ተደሰቱ ። የመዘርጊያውስ ዋጋ? ተባለ ።

በዚች ባልታወቀች አገር ውስጥ የሀዲዱ መዘርጊያ ዋጋ ይሄን ያህል ይሆናል ተብሎ ለመወሰን አስቸገረ ። እንዲያው በደፈናው እንደ አፍሪካ አገሮች ግምት ተባለና ለአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት አንድ መቶ ሺ ፍራንክ እንደሚያስፈልግ ተገመተ ። ጠቅላላ ማሠሪያውም 33 ሚሊዮን 500,000 ፍራንክ ይሆናል ተባለ ።

የጥናቱ ጉዳይ በዚህ አበቃና ኩባንያዎቹ ከፈረንሣይ ቅኝ ግዛት ከጅቡቲ ተነስቶ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን ድረስ 90 ኪሎሜትር መንገድ ለመሥራት እንዲፈቀድላቸው የፈረንሣይን መንግሥት ጠየቁ ። የፈረንሣይ መንግሥትም ሐዲዱን ከባህር ጠረፍ አምስት ኪሎ ሜትር ገባ ብሎ እንዲሠራና በባቡሩም ምንም ዓይነት የጦር መሣሪያ እንዳይጫን ውል ይደረግ እያለ ሲያንገራግር የአድዋው ጦርነት ተነሳና ጉዳዩ ተቋረጠ ።

የአድዋ ጦርነት ከመነሳቱ በፊት የኢጣሊያ መንግሥት የውጫሌን ውል ምክንያት በማድረግ በማያገባው ገብቶ የፈረንሣይ መንግሥት ለባቡሩ መንገድ መዘርጋት ፈቃድ እንዳይሰጥ አስጠንቅቆ ነበር ። ምኒልክም ደጋግመው የፈረንሣይን መንግሥት ቢጠይቁ ፡ ፈረንሣይና ኢጣሊያ የምኒልክን ጥያቄ ንቀው እርስ በርሳቸው ስለሚያዋጣቸው ጥቅም ብቻ እንግሊዝን ጨምረው ኢትዮጵያን ተከፋፍለው ለመያዝ በኢትዮጵያ ላይ ይዶልቱ ጀመር ። ይህ ነገር ተደጋግሞ ከምኒልክ ዘንድ ስለ ደረሰ ጦር አውጀው የኢጣሊያን ድንፋታ አድዋ ላይ አበረዱለት ። በአድዋው ድል እንግሊዝና ፈረንሣይም ተደናገጡ ።

ከአድዋው ድል በኋላ ምኒልክ ለፈረንሣይ መንግሥት "....ታዲያስ? የባቡሩ መስመር ሥራ ጉዳይ እንዴት ነው?" የሚል ጥያቄ እንደገና አቀረቡ ። የኢጣሊያ ውርደት ትምህርት የሆነው የፈረንሣይ መንግሥት ለኩባንያው ፈቃድ ለመስጠት መዘጋጀቱን ገለጠ ። ወዲያውም እ ኤ አ ሚያዝያ 27 ቀን በተፃፈ ደብዳቤ የፈረንሣይ የቅኝ አገሮች ሚኒስትር ለአቦኩ አገረ ገዥ ለባቡሩ መንገድ ሥራ ከጂቡቲ ኢትዮጵያ ድረስ ቢዘረጋ የሚስማማ መሆኑን ገለጡለት ።

ሌላ ችግር ተፈጠረ ። "....የባቡሩ መንገድ ሥራ ከጅቡቲ የሚነሳ ከሆነ የእንግሊዝን ጥቅም የሚነካ በመሆኑ እንቃወማለን ።...." ሲል የእንግሊዝ መንግሥት የበፊቱን መግለጫውን ደገመው ። በኤደን የነበረው የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት አስተዳዳሪም ኮሎኔል ፈርስ እ አ አ "በ1፰96 ዓ.ም. ኅዳር 13 ቀን ያወጣነውን መግለጫ እናስታውሳለን" ካሉ በኋላ "....ከጂቡቲ የሚነሳው የባቡር መስመር ሥራው ሲያልቅ የዘይላ በር ንግድ ፈጽሞ ይሞታልና የእንግሊዝ መንግሥት በጥብቅ ሊያስብበት ይገባል...." አለ ። አከታትሎም የእንግሊዝ ሚሊተሪ ኢንተሉጀንስ ሰርቪስ ዋና ዲሬክተር የነበረው ሜጀር ጄኔራል አርዶፍ "....የመስመሩ ሥራ ከጂቡቲ ይልቅ ከዘይላ ቢነሳ እንስማማለን ። ከጂቡቲ የሚነሳ ከሆነ ግን በእንግሊዝ ሶማሌ በዘይላ በኩል ወደ ኢትዮጵያ የሚገባውም ሆነ ከኢትዮጵያ የሚወጣው ሸቀጥ የዘይላን በር ጥቅም ስለሚያስቀር የጂቡቲን ሥራ ፈጽሙን አንስማማም ።...." ሲል የእንግሊዝን ቁርጥ አሳብ አበሰረ ።

ጥንቱንም በተደረገው ጥናት ዘይላ ተጠንቶ በርቀትና በበረሃው ብዛት ፤ በወደቡም አለመመቸት የዘይላው ጥናት ወድቋል ። ምኒልክ ይህን ችግር ሲሰሙ የሚቀርቧቸውን ፈረንጆች ሰብስበው "....ድሮም ኢጣሊያኖች አውከውኝ ያው እንደሰማችሁት አድዋ ላይ ተገላገልን ። አሁን ደግሞ እንግሊዞች አገሬ እንዳትሰለጥን የሚያደናቅፉኝ ከሆነ፣ ሌላ የማደርገው ስለሌለኝ እንደ አድዋው ነው ማድረግ ያለብኝ ። ፈረንሣዮችም ዘመዶቻቸውን እየደገፉ እኔን ባዕድ አድርገው ከጠሉኝ ላገሬ ስል ከነሱም ጋር እገጥማለሁ ። ይህን ነገር እንዲያስቡበት እንደሚሆን አድርጉ ።.....ለየሰዎቻችሁም ንገሩ ..." አሉ ።

ይህ የምኒልክ ንግግር በኤሮፓ ጋዜጦች ላይ ወጣ ። በኢጣሊያ ላይ የደረሰው የአድዋ ውርደት ኤሮፓን አስፈርቶ ነበርና የፈረንሣይ መንግሥት ከኢትዮጵያ በኩል የሚጠየቀውን ሁሉ በወዳጅነት ለመፈፀም እንደሚችል መግለጫ አወጣ ። የእንግሊዝ መንግሥትም.... እንደሚሆነው ይሁን...በሚል አሳብ ጭጭ አለ ።

በአገር ውስጥ ደግሞ የባቡር መስመር እንዳይዘረጋ ከፍተኛ ተቃውሞ ከነበራቸው መሀል እቴጌ ጣይቱና ራስ መኰንን ነበሩበት ። ሌሎቹንም መኳንንቶች ጨምሮ የእቴጌ ጣይቱና የራስ መኰንን ተቃውሞ በአገሪቱ መሻሻል ጉዳይ ሳይሆን ፡ የባቡሩ መስመር ከተዘረጋ ፈረንጆች ወደ ኢትዮጵያ በመግባት አገራችንን ይወስዱታል በማለት ነው ። በኢትዮጵያ ውስጥ በዚያ ዘመን የእንግሊዝ መንግሥት ሹም የነበረው ሀሪንግተን ስለዚሁ ጉዳይ ከፃፈው ብንጠቅስ "....ከራስ መኰንን ጋር ስንጨዋወት የባቡሩ መስመር ጉዳይ ተነሳ ።አሳቸውም

ስለዚሁ ጉዳይ ሲያጫውቱኝ ይሄን የባቡር መንገድ ሥራ አልወደድኩ ትም ።. . . .በምንም ነገር ከሐረር እንዳደርስም አልፈቅድም ።....አጤ ምኒልክ ግን ለዚህ ሥራ የግምጃ ቤታቸውን ቁልፍ ሰጥተዋል ። እኔ ግን በነገሩ ኀዘን ይሰማኛል ። ለምን ብትለኝ የባቡሩ መንገድ ከተሠራ ሐረ ርም ሐረር አልሆነችም ፡ ሸዋም ሸዋ አልሆን አሉኝ ። ይህንንም የባ ቡር መንገድ ሥራ ራስ መኰንን ብቻ ሳይሆኑ ሌሎቹም ራሶች ይቃ ወሙታል ።....'' ሲል ጽፏል ።

በኢትዮጵያ የእንግሊዝ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የነበረው ሬኔል ሮድ እንደፃፈው ደግሞ "....ካንድ ኢትዮጵያዊ ሹም ጋር ስንጫወት አዲስ ሊሠራ ስለታቀደው የባቡር መስመር ሥራ እነሳና ይሄን የባቡር መንገድ አልወደድነውም ። የጠላነው ከባህር ጋር በመገ ናኘቱ ነው ። እኛ አገር ውስጥ ብቻ ቢሆን ኖሮ ምንም አልነበረም ። ይሄ የባህሩ በር ነገር ጥሩ አይደለም ። ብንቃወምም አሻፈረኝ ስላሉን ዝም በላቸው ሠርተው ሲጨርሱ ፡ ሥራውንም ባህሩንም አብረን እና ጠፋዋለን....አሉኝ....'' ሲል ጽፏል ።

ሮድ ስለዚሁ ተቃውሞ ጉዳይ ሲገልጥ " ....የሥራው ተቃዋሚ ዎች ሹማምንቶቹ ብቻ አይደሉም ። ከጠረፍ ጀምሮ ያለው ሕዝብ በሙሉ የባቡሩን መስመር መዘርጋት ይቃወማል ። ከተቃዋሚው ሕዝብ መሀል አብዛኛዎቹ ባለ ግመሎች ናቸው ። ሐዲዱ ከተዘረጋ የግመል ማከራየት ሥራቸው ስለሚቀር ሌላውን ሕዝብ በመስበክ ሥራውን በኃይል ይቃወማሉ....'' ብሏል ። እነዚህ በጠረፍና በቆላው አካባቢ የነበሩ ግመል አከራዮች በቃል የነበራቸውን ተቃውሞ በተግ ባር ላይ አውለውታል ።

ሳድለር ስለዚሁ ጉዳይ ሲጥፍ "....ራስ መኰንን የአካባቢውን ባላባቶችና ሽማግሌዎች ሰብስበው ስለባቡሩ መስመር ሥራ አነጋገሩዋ ቸው ። ባላባቶቹም ከልጅነታችን ጀምሮ የምንነግደው በግመል ፡ የም ንጓዘው በእግር ነው ። ይሄ የባቡር ነገር ያጠፋናል ። ስለዚህ እኛም ሲጀመር እናጠፋዋለን አሉዋቸው ። ራስ መኰንንም 'እኔ በግድ ውደዱት አልላችሁም ፡ የምታስቡትንም ተዉ ብዬ አላዝም ። የማት ፈልጉትንም ነገር በግድ ይሁን አልልም ። ይህን ነገር ኢሳዎችም ፡ ጋሎችም ፡ አማሮችም እኩል ስለምታስቡት እንደፈለጋችሁ' አሏቸው ። . . . .'' ሲል ጽፏል ። ራስ መኰንን ጠጋኝ መስለው በሥራው ላይ እንቅፋት እንዲፈጠር መቀስቀሳቸውን ከሳድለር ጽሑፍ እንረዳለን ።

ኩባንያው ከፈረንሣይ መንግሥት ፈቃዱን ካገኘ በኋላ የመሥ ሪያ ገንዘብ ለመሰብሰብ ሼር አዘጋጀ ። እያንዳንዱ ዕጣ 500 ፍራንክ የሆነ 28 000 ዕጣ አዘጋጀ ። በዚህም ዕጣ 14 ሚሊዮን ፍራንክ ለማግ

ኘት ነበር ። በውጭም ሆነ በውስጥ ባለው ተቃውሞ ምክንያት በዕጣ ሽያጭ 8 738 000 ፍራንክ ብቻ ተገኘ ። እንደገና በሌላ ዘዴ ሌላ ሙከራ ተደረገ ። ይህም ቦንድ በመሸጥ ነበር ። አሁንም እያንዳንዱ 500 ፍራንክ የሆነ 56 000 ቦንድ አዘጋጀ ። በዚህም የቦንድ ሽያጭ ቢያንስ 25 ሚሊዮን ፍራንክ ለማግኘት ታስቦ ነበር ። አሁንም በውስጥም ሆነ በውጭ ባለው ተፅእኖ ምክንያት ከቦንድ ሽያጭ 51ሺ ፍራንክ ብቻ ተገኘ ።

ሁሉም ሆነና የባቡር ሐዲድ መዘርጋቱ ሥራ በ1890 ሕዳር 22 ቀን ጂቡቲ ላይ ተጀመረ ። የፈረንሣይ መንግሥትም ከተማውን ከእቦክ አንስቶ የሐዲዱ ሥራ ወደ ተጀመረበት ወደ ጅቡቲ ማዛወሩን ቀጠለ ። የባቡሩ መስመር ሥራም እየተፋጠነ ሄዶ የመጀመሪያው ባቡር ከጂ ቡቲ ተነስቶ በ1893 ዓ ም ሐምሌ 15 ቀን ከኢትዮጵያ ግዛት ደወሌ ደረሰ ። ይህ የመጀመሪያው ባቡር ከጂቡቲ ተነስቶ ከወሰን የመጀመሪ ያው ጣቢያ ደወሌ ለመድረስ አምስት ሰዓት ተኩል ፈጀበት ።

የሐዲዱ መዘርጋት ሥራ ይካሄድ ጀመር ። ለሥራው እንቅፋት ከሆኑት የሰው ልጆች በቀር ምስጦች ሌላ ተቀዋሚዎች ሆነው ተገኙ። በብዙ የኤሮፓና የእስያ አገሮች እንደሚደረገው ለሐዲዱ መዘርጊያ አግድሞሽ እንጨት እለፍ እለፍ እየተደረገ ተጣለ ። በላዩም ላይ ሐዲዱ በብሎን እየታሠረ ሥራው ፎቀቅ አለ ። በጥቂት ቀናት ውስጥ ምስ ጦች አግድሞሹን እንጨት በልተውት ባዶ ብሎንና ሐዲዱን ለኩባን ያው ተዉለት ። የስልክ መስመሩም ሥራ ከሐዲዱ ሥራ ጋር እብሮ ይጓዝ ስለነበር ለስልኩ ሽቦ መዘርጊያ የተተከሉት እንጨቶችም በም ስጥ ተበሉ ።

ሚስታቸውን እቴጌ ጣይቱን ፣ ወዳጆቻቸውንና ወንድማቸውን ራስ መኰንንን ፣ ዋና ጠላቶቻቸውን ኢጣሊያን ፣ እንግሊዝንና ፈረንሳይን በጦርነትም ፣ በፖለቲካም ፣ በልመናም ፣ በግዴታም ድል ያደረጉት ምኒ ልክ በምስጥ መሸነፋቸውን አሜን ብለው ተቀበሉ ።

"እንዲያው ምስጥ በሌለበት ደጋ ደጋውን እያደረጋችሁ ብታመጡ ትስ" አሉ ምኒልክ ። ዋና የቴክኒክ አማካሪያቸው ኢልግም "ጃንሆይ ፣ አዳል መሬት ውስጥ ምን ደጋ አለ? " ቢላቸው "ስማኝ" አሉ ምኒ ልክ "ስማኝ ኢልግ ፣ ሌላውን በጦርም ፣ በጉልበትም ፣ በማስፈራራትም አሸነፍኩ ። ከውጭውም ፣ ከአገሬውም ሰው ተጣላሁ ። ጂማ ፣ ከፋ ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ያለው ሕዝብ በጭለማ መቅረቱ ነው ። በውሉ ነጭ አባይ ድረስ ማለቴም የከፋውም ንግድ እንዲሄድለት ብዬ እንጂ እኔማ የሸዋው ነጋዴ የሚሰጠኝን መብላት ይበቃኝ የለምን ። ሰው በኩል ያለውን እኔ ጨርሻለሁ ። ከምስጥ ጋር ያለውን ግን እናንተ

ጨርሱ እንጂ የባቡሩ ሥራ እንዳይቋረጥ ነግሬሃለሁ ። . . . .”
ብለው ያን ጫማ መስፋት አቅቶት በምኒልክ ፊትና የወደቀውንና ዋና የቴክኒክ አማካሪያቸው ያደረጉትን እንጂኔር ኢልግን አስጠነቀቁት ። ለስልኩ ሽቦ መስቀያም እንጨት መሆኑ ቀርቶ ብረት እንዲሆንና ለሐዲዱ መዘርጊያ አግዳሚም የሚጋደመው ደግሞ በእንጨቱ ፈንታ ብረት እንዲሆን ተወሰነ ። በዚህ የአሠራር ዘዴ ሥራው እንደገና ተጀመረ ። ለእያንዳንዱ ሀዲድ 13 አግድሞሽ ብረት እየተደረገ ለአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት በመሀከለኛ ግምት 13,333 አግዳሚ ብረቶች ተጋደሙ ። ለስልኩ መዘርጊያ የሚሆኑት ብረቶችም በ70 ሜትር ርቀት ተተከሉ ። በላያቸው ላይም አራት ሽቦ ተዘረጋ ።

ለአንድ ኪሎ ሜትር ርዝመት ሥራ የሚያስፈልገው ሐዲድና የስልኩ ብረት 70.000 ኪሎ ግራም ክብደት ያለው ነው ። ይህ ሁሉ የሚጓጓዘው በግመል እየተጫነ ነው ። በዚህ ዓይነት አሠራር ሰው ብቻ ሳይሆን ከሰው የበለጠ ያስቸገሩት ምስጦችም ድል ሆኑ ። ከዚያ በኋላ ደግሞ ሌላ ችግር ተፈጠረ ።

በእቴጌ ጣይቱ ፣ በራስ መኰንንና በሌሎችም መኳንንቶች የተጠነ ሰሰው የባቡሩ መስመር መዘርጋት ሥራ ተቃውሞ በተግባር ይገለጽ ጀመር ። ወረበሎች በሐዲዱ መስመር ሥራ አካባቢ እያደፈጡ ሠራተ ኛውን ሕዝብ በተኩስ ብዛት ያሸብሩት ጀመር ። 30 ሠራተኞችም ተገደሉ ። ወረበሎቹ ፣ ፈረንጆችንም ጭምር ያባርሩ ጀመር ። ሠራተኞቹ ፈረንጆችም እንደ አረብ እየጠመጠሙና እያገለደሙ በየአረቡ ቤት ይደበቁ ጀመር ። በኤደን ያለው የፈረንሳይ መንግሥት ወኪል በጂቡቲ ያሉትን ዜጐቹን ለማስጠበቅ በጦር መርከብ የተጫኑ ተጨማሪ ወታ ደሮችን ወደ ጂቡቲ ላከ ።

በአፋር በረሃ ውስጥ ሁማ በተባለ ቦታ ሽፍቶች ከባድ ግጭት አድርሰው ከሠራተኛው መሀል ከነደሉ በኋላ የሐዲዱን መስመር የሚ ሠሩት ሠራተኞች ተበታተኑ ። አዲስ እየተቀጠረ የሚመጣውም ሠራ ተኛ ባንዲት ጥይት ጩኸት እየተደናበረ ድራሽ አምላኩ ይጠፋ ጀመር።

ጉዳዩ ለምኒልክ ቀረበ ። ምኒልክም “በሉዋ ምክሩበት” አሉ ።

የሥራው ተቃዋሚዎች ሽብር ለማስነሳት አስበው “አገሩ በጦር ይመታ” አሉዋቸው ። ምኒልክ ግን “ወንበዴው ያለው እንጉያዬ ፣ በጦር ይመታ የምትሉት ምንም ያላደረገውን ገሩን ሕዝብ ነው ። እኔ አውቅበታለሁ” ብለው ስብሰባውን በተኑ ። ከነጮቹ ጋር ተማከ ረው በፈረንጅ ሹም የሚታዘዙ ኢትዮጵያውያን ወታደሮችን ለጥበቃ አሰማሩ ። ለስድስት ለሰባት ሠራተኛ አንድ ጠመንጃ የያዘ ጠባቂ

ተደረገ ። እየሰረገ የሚመጣውንም ሽፍታ እያስያዙ በየጉሣው መሀል እንዲሰቀልና መቀጣጫ እንዲሆን በገመድ እየተንጠለጠለ ስምንት ቀን ያህል እንዲቆይ አደረጉ ። ረብሻው ጋብ አለ ።

ባላባቶቹ ሥራውን እንዲቃወሙ ከኢትዮጵያ መኳንንት ተነግሮ አቸው ስለነበር ምኒልክ ደግሞ በበኩላቸው ባላባቶቹን እየጠሩ ካባ በመሸለም ፣ ባላምባራስና ቀኛዝማች ድረስ የማዕረግ ስም በመስ ጠት ፣ ልጆቻቸውን ክርስትናና በማንሳትና በቤተ መንግሥት ለማሳደግ እየተረከቡ ፣ ገንዘብ እየሰጡ የተቃዋሚዎቻቸውን አድማ በዘዴ አከሸ ፉት ። ኩባንያውም በመጋቢት ወር 1890 ዓ.ም. ለኢሳ ባላባቶች 2000 ሩፒ ሰጥቶ ፤ ሥራው ከነሱ ክልል በሰላም ሲወጣ ደግሞ 5000 ሩፒ የሚጨምርላቸው መሆኑን ነግሮ ተቃዋሚዎች በገንዘብ ሰንሰለት ታሠሩ ።

የግሪኩ ኮንትራክተር ሙሴ ማርቆስ ለሀሬንግተን አጫውቶት ሀሬንግተን እንደ ፃፈው ላንድ ኪሎ ሜትር ርቀት ሥራ ከ30 000 እስከ 40 000 ፍራንክ ድረስ ኩባንያው ያወጣ ጀመር ። ገንዘቡንም ከፍ ያደረገው ለጉቦ የሚወጣው ነው ። ሙሴ ማርቆስ ሲናገር "....ጣቢ ያዎችን በየቅርቡ ያደረግነው ለምን መሰለህ? በየጣቢያዎቹ ጦር እየሰፈረ ወስላቶችን ለመጠበቅ እንዲያመች ነው ። ትልቁ ችግራችን ደግሞ ለስልክ የምንዘረጋውን የመዳብ ሽቦ እየቆራረጡ ሴቶቹ አም ባር ያደርጉታል. . . .ምኒልክ የመዳብ አምባር በእጅዋ ላይ የተገኘባት ሴት እጅዋ ይቆረጣል ብለው ባያውጁ ኖሮ ሥራው ሊንቀሳቀስ አይ ችልም ነበር. . . ." ብሏል ።


በዚህ ሁኔታ ብዙ ችግሮችን በማለፍ ሥራው ተካሂዶ የመጀመ ሪያው ባቡር ታህሣሥ 14 ቀን 1895 ዓ.ም. ፤ በጥር ማለቂያ በ1890 ከተመሠረተችው ድሬዳዋ ገባ ። ከጂቡቲ ከንጋቱ በ12 ሰዓት የተነ ሣው ባቡር ድሬዳዋ የገባው ከምሽቱ 2 ሰዓት ሲሆን ነው ። ከጂቡቲ ድሬዳዋ ለመድረስ 14 ሰዐት ፈጅቶበታል ።


ከድሬዳዋ አዲስ አበባ ድረስ ለሚዘረጋው የባቡር መንገድ ደግሞ እንደገና ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ሌላ ውል አዘጋጅተው በዚያ መሠረት እንዲሠራ ጥር 21 ቀን 1900 ዓ.ም. ከዶክተር ቢታሊያን ጋር ተፈራ ረሙ ። በዚህ ዘመን ምኒልክ ጤና አልነበሩምና ምናልባት ቢሞቱ ሥራው እንዳይቋረጥ በማለት ለወራሽንት ያጩዋቸው ልጅ ኢያሱ ውሉን በማህተማቸው እንዲያፀድቁ አደረጉ ።

በዚሁ ውል መሠረት የመስመሩ ሥራ አዋሽ ከደረሰ በኋላ ደግሞ ቆመ ። ከዚህ በኋላ ምኒልክ በጠና ታመው ነበርና መዋዋል



የድሬዳዋ የመጀመሪያው ባቡር ጣቢያ ።





የድሮው አዳማ የዛሬው ናዝሬት ባቡር ጣቢያ

ስለማይችሉ ቆመ ። ሚያዝያ 25 ቀን 1905 ዓ. ም. በኢትዮጵያ ስም ቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስ ፣ በምድር ባቡር ኩባንያ ስም ጄኔራል ፋሚን ሆነው ከአዋሽ እስከ አዲስ አበባ ስለሚሠራው መንገድ ውል ከተፈረመ በኋላ በ1907 ዓ. ም. ሐዲዱ አቃቂ ከተማ ደረሰ ። በዚህ ዘመን ምኒልክ ከሞቱ ዓመት ሆኗቸው ነበር ። ከዚያም ሁለት ዓመት ቆይቶ በ1909 ዓ. ም. የመጀመሪያው ባቡር አዲስ አበባ ገባ ።

የባቡሩም ጉዞ በበጋው ወራት በየሳምንቱ እሁድና ረቡዕ ከአዲስ አበባ ወደ ጂቡቲ ጉዞ ይጀምራል ። በክረምት ወራት ግን ፕሮግራሙን ለውጦ እንዳመቸው ይጓዛል ። ስለዚያ ዘመኑ የባቡር ሁኔታ ዜርቮስ እንደፃፈው 54 ጉታች ፣ 36 ማለፊያ የመንገደኛ ጋሪ ፣ 10 ባለ1ኛና 2ኛ ማዕረግ ያላቸው ጋሪዎች ፣ 26 የ3ኛ ማዕረግ ጋሪዎች ፣ 445 የዕቃ ጋሪዎች ነበሩት ።

ምኒልክም የደከሙበትን የባቡር ውጤት አቃቂ እንኳን መድረሱን ሳያዩ ቀሩ ።

## ስልክ

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በኢትዮጵያ ውስጥ በስልክ መነጋገር የተጀመረው በ1892 ዓ. ም. ነው ይላሉ ። ይህ የመጀመሪያው የክፍለ ሀገር ስልክ ከአዲስ አበባ ሐረር ድረስ የተዘረጋበት ዘመን እንጂ ከዚያ በፊት በአዲስ አበባ ስልክ ገብቶ ነበር ።

ራስ መኰንን የኢጣሊያን አገር ጉብኝተው በ1882 ዓ ም. ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ የስልክ መነጋገሪያ መሣሪያ ይዘው መጥተው ነበር ። ራስ መኰንን ያመጡትን የስልክ መነጋገሪያ መሣሪያ ለአጤ ምኒልክ ሰጡአቸው ። አጤ ምኒልክም ለማንኛውም የቴክኒክ ሥራ አዋቂ ያደረጉትን ፈረንሳዊውን እስቴቬኒን ወደ ቤተ መንግሥት አስጠርተው ስልኩን እንዲሠሩው አዘዙት ።

እስቴቬኒን በዚያው በ1882 ዓ. ም. ስልኩን ከምኒልክ እዳራሽ እስከ ግምጃ ቤታቸው ድረስ ዘረጋው ። ሥራው ተሠርቶ እንዳለቀም ምኒልክ እንዲነጋገሩበት ተደረገ ። ምኒልክም ጥቂት ተነጋግረው “. . . . ፈጥነው ከተቀመጡበት ተነሱ” ይላል እስቴቬኒን “መነጋገሪያውንም ከጠረጴዛው ላይ አስቀምጠው ያነጋገራቸው የግምጃ ቤቱ ሹም በቅርብ እንዳለ ብለው በመስኮት በኩል ተመለከቱ ። . . . .”

ፓርሴል ደግሞ አልቴምፖ ዲ ሚኒልክ በሚባለው መጽሐፉ የኢትዮጵያን የስልክ ታሪክ ይተርካል ። “. . . . ስልክ እንደገባ ለመ ጀመሪያ ጊዜ ከአጤ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ገብቶ ነበርና በስልኩ መግባት ተነስቶ የነበረው ተቃውሞ በይፋ ወጥቶ ከአጤ ምኒልክ ዘንድ ደረሰ ።

“ከቀሳውስት የተውጣጡ ስምንት ተወካዮች ከአጤ ምኒልክ ዘንድ ቀርበው ይህ ስልክ የጋኔን ሥራ ስለሆነ ከቤተ መንግሥቱ እንዲ ወጣ ፤ ከአገሪቱም ጨርሶ እንዲጠፋ ብለው አመለከቱ ። ምኒልክም አሳባችሁ ደህና ነው ። መልሱን ግን ነገ እነግራችኋለሁ ብለው ካሰና በቷቸው በኋላ በማግሥቱ መኳንንቱን ሰብስበው ፤ ጳጳሱ ባሉበት ፤ ‘እነዚህ ቄሶች በማይሆነው ሁሉ እየተቃወሙ አስቸግረውኛል ። አሁን ደግሞ ስልክ ባገሬ ባስገባ የሰይጣን ሥራ ነው እያሉ ለሕዝብ መስበ ካቸውን ሰምታችኋል ። እኔም የሰይጣን ሥራ ላለመሆኑ ለማሳመን ባስብም ከኔም ዘንድ መጥተው የሰይጣን ሥራ ስለሆነ አስወጣ አሉኝ ። የሰይጣን ሥራ ያለመሆኑንም ነገርኳቸው ። እነሱ ግን በቁጣቸው ይቃ ዣሉ ። ሥራዬንም የሚያደናቅፉኝ ይሆናሉና ከእንግዲህ ወዲያ የኦር ቶዶክስ ሃይማኖቱን ትቼ ከነሱ ለመለየት ስል ሃይማኖቴን መለወጤ ነው’ አሉ ። መኳንንቱና ጳጳሱም ተነስተው ‘ጃንሆይ ፤ ሃይማኖትዎን አይለውጡብን ፤ ያም ነገር እዚያው እንዳለ ይቀመጥ ። ዳግመኛም እነዚህ ሰዎች እንዳያሰናክሉዎ እኛ ቃል እንገባለን’ ብለው ለመኑዋ ቸው።....” ሲል ጽፏል ።

እስቴቬኒን ስለቄሶቹ ሲናገር “. . . .እንዲነጋገር ያደረግሁት እኔ በመሆኔ በሃይማኖት ነገር መግባቴን እንዳቆም ወዳጆቼ የሆኑ አንዳንድ ቄሶች መከሩኝ . . . .” ይላል ። ምኒልክ ዘንድ ከገባ ከሁለት ዓመት ኋላ ከፍርድ ሚኒስትሩ ከአፈንጉሥ ነሲቡ ቤት ገባ ። አፈንጉሥ አንድ ቀን የስልኩን ሽቦ ሲነኩ የኤሌትሪክ ንዝረት ተሰማቸውና ደነገጡ ። በዚያ የነበሩት የንስሐ አባታቸው ቄስ ፤ ስልኩን ቀስ ብለው ወደ ውጭ አወጡና በእሳት አቃጠሉት ። ቤቱንም በሙሉ ጠበል ረጩት ።

አብዛኛው መኳንንት ስልክ ሰይጣን ነው እያለ ባይነጋገርበትም በምኒልክና በጥቂት መኳንንቶቻቸው መሀል በስልክ መነጋገርና ጉዳይን መፈፀም እየተወደደ ሄደ ። በስልክ መነጋገሩ እየተለመደ ቢሄድም ተነጋጋሪዎቹ የሚገናኙት በስልከኞች አማካይነት ስለነበረ ብዙውን ጊዜ ስልከኞች ከስልኩ ቤት እየጠፉ ችግር ፈጠሩ ። በዚህ የተናደዱት ምኒልክም ለመጀመሪያ ጊዜ የመጀመሪያውን የስልከኞችን የተራና የሥራ ደንብ አወጡ ። ደንቡም ቀጥሎ ያለው ነው ።

ለቴሌግራም ፀሐፊዎችና ለስልክ ቀጣዮች ፥

ለባላገሮችና ለጭቃ ሹሞች ፥

ለአበጋዞችም የተሰጠው ትእዛዝ ይህ ነው ።

*መጀመሪያ*

ቴሌግራም ፀሐፊዎች ጧት በ12 ሰዓት ወደ ስልክ ቤት ገብተው እስከ 6 ሰዓት ይቀመጣሉ ። ከ6 ሰዓት በኋላ ግን በተፈለጉ በ5 ደቂቃ እንዲገኙ ሆነው ተጠባባቂዎቻቸውን እየተዉ ይሄዳሉ ። በተፈለጉ በ5 ደቂቃ ያልተገኙ እንደሆነ በወር ቀለባቸው ይቀጣሉ ። 15 ደቂቃ የጠፉ እንደሆነ አንድ ወር ይታሠራሉ ። 20 ደቂቃ የጠፉ እንደሆነ 4 ወር ይታሠራሉ ። ሌሎችም የሚፈለጉበት ጉዳይ የተገኘ እንደሆነ ከስልክ ቤት አይለዩም ። በተራ ይጠባበቃሉ ።

የስልክ ሥራ ከሆነ ቴሌግራም ፀሐፊዎች የስልክ ቀጣዮችን ያዟቸዋል ። ስልክ ቀጣዮችም ጧት በአንድ ሰዓት እስልክ ቤት ይገባሉ ። ማታ በ2 ሰዓት ይወጣሉ ። ሌሊትም በተራ ይጠብቃሉ ። ተረኛውም ፥ ለሊት ቢሆን ፥ ቀንም ቢሆን ከስልክ ቤት አይወጣም ። ነገር ግን የሌሊትና የቀን ተረኛ ለብቻው ነው ። ቀን የጠበቀው ለሊት ፥ ለሊት የጠበቀው ቀን አይጠብቅም ። ስልክ በተደወለ በ4 ደቂቃ ተረኛው ከዚያ መኖሩን ያላሳወቀ እንደሆነ በወር ቀለቡ ይቀጣል ። 15 ደቂቃ የጠፋ እንደሆነ አንድ ወር ይታሠራል ። ከዚያ ወዲያ ያለው ቅጣት ብርቱ ነው ።

ስልክ ቀጣዮች የመንግሥት ቃል ከተፈፀመ በኋላ በዋጋ የሚነጋገረውን ሰው እየጠሩ በጭቃ ሹምና በቴሌግራም ፀሐፊው ፊት ያነጋግራሉ ። ዋጋውንም እየተቀበሉ በቴሌግራም ፀሐፊዎች መዝገብ እየተፃፈ በጭቃ ሹም እጅ ይቀመጣል ። ያለ ዋጋ ያነጋገረ ፥ ከዋጋ ከፍሎ ያስቀረ ሰው ዋጋውን ከፍሎ ፥ ያስቀረው ገንዘብ ተሰልቶ ፥ በአንድ 4 ይከፍላል ። ደግሞ ጭቃ ሹምና ቴሌግራም ፀሐፊው ሳያዩ ስልክ ቀጣዮች ዋጋ የተቀበሉ እንደሆነ በአንድ 4 ይከፍላሉ ።

ከቴሌግራም ፀሐፊዎች ወይም ከስልክ ቀጣዮች ፥ ከነሱም ተጠባባቂዎች ቢሆን የመንግስት ሚስጢር አውጥቶ የተገኘ ሰው ቅጣቱ ካገር የተለየ አዲስ ቅጣት ነው ። የሌላውም ሰው ጉዳይ ቢሆን መንግስት የሚያነሳ ነገር የሆነ እንደሆነ ለስልኩ ሹም ፈጥኖ ያስታውቃል ። ከስልኩ ሹም በቀረ ለሌላ ሰው የነገረ እንደሆነ ብርቱ ቅጣት ይቀጣል።

የቴሌግራም ዋጋ በ20 ቃል አንድ ብር ፥ በአስር ቃል አላድ ፥ በአምስት ቃል ሩብ ነው ። ደግሞ በቴሌፎን የሚነጋገር ሰው ዋጋ በአስር ደቂቃ አንድ ብር ፥ በአምስት ደቂቃ አላድ ፥ በሁለት ደቂቃ ሩብ ነው ።

ከስልክ ቀጣዮችና ከቴሌግራም ፀሐፊዎች ጋር ከስልክ ቤት እየ ዋለ ፡ የስልክን ዋጋ እየተቀበለ የሚያስቀምጥ ጭቃ ሹም የሻለቆች ይሰጣሉ ። ጭቃ ሹሙም ጧት በ12 ሰዓት እስልክ ቤት ይገባል ። ማታ በ12 ሰዓት ከስልክ ቤት ይወጣል ። ስልክ የተቆረጠ እንደሆነ ስልክ ቀጣዮች ሳያስቀጥሉ አይውሉም ። የስፍራው ርቀት የታወቀ ሩቅ ካልሆነ በቀር በመሬታቸውም ስልክ የተተከለባቸው ባላገሮች ስልኩን በሥርዓት ይጠብቃሉ ። እሳት እንዳይበላውና ከብት እንዳይጥለው ስልኩ የተቆረጠ ፡ እንጨት የወደቀ እንደሆነ ፡ ያን ጊዜውን ለጭቃ ሹሙ ያስታውቃሉ ። ያላስታወቁ የሆነ እንደሆነ ግን በቀን ልክ አስር አስር ብር መቀጫ ይሰጣሉ ። እስከ ሁለት ጊዜ ። በሶስተኛው ርስታቸውን ይነቀላሉ ። የዚህም የመቀጫ ብር በቴሌግራም ፀሐፊ መዝገብ እየተ ፃፈ በጭቃ ሹሙ እጅ ይቀመጣል ።

ጭቃ ሹሞች ፡ ባላገሮች ስልክ ተቆርጧል ወይም እንጨቱን ወድቋል ብለው ሲነግሯቸው ሥፍራው ቅርብ እንደሆነ እስከ አንድ ሰዓት ለስልክ ቀጣዮች ያስታውቃሉ ። የራቀ እንደሆነ እስከ 12 ሰዓት ያስታውቃሉ ። ያላስታወቁ እንደሆነ ግን እንደ ሥፍራው ርቀት በቀኑ ቁጥር 20 ብር መቀጫ ይሰጣሉ ። በሁለተኛው ንብረታቸውን ይወረ ሳሉ ።

ሰው በተንኮል ስልክ የቆረጠ እንደሆነ ፡ ይህን ሰው ባላገሩ ባፍር ሳታ አውጥቶ ለጭቃ ሹሞች ይስጥ ። ጭቃ ሹሞቹም ለሻለቆች ይሰ ጧቸዋል ። በመንግስት ፈቃድ ይሰቀላል ። የሻለቆችና ጭቃሹሞች ፡ ባላ ገሮች ለስልክ የቸገረውን ነገር ስልከኞቹ ሲነግሩዋቸው ፈጥነው የሚ መቸውን ነገር ያደርጋሉ ። ለማድረግ የማይመቻቸውን ፈጥነው ለመን ግሥት ሹም ያስታውቃሉ ። ይህን ሰምተው ዝም ብለው የመንግስት ሥራ የቀረ እንደሆነ በመጀመሪያ 500 ብር ። በሁለተኛው ሺ ብር መቀጫ ይሰጣሉ ። በሶስተኛው ሹማምንቶቹ ሹመታቸውን ይሻራሉ ። ባላገሮቹም ንብረታቸውን ያጣሉ ።

ስልክ ቀጣዮች ስልክ በሚቀጥሉበት አገር የስልክ እንጨትና መሰላል ባላገሮች ያቀርቡላቸዋል ። ቀጥለውም እስቲሄዱ ራትና ምሳ ጭቃ ሹሞች ይሰጣሉ ። ስልክ ቀጣዮች ውሃ የሞላባቸው እንደሆነ ፡ ከብትም ከመንገድ የጠፋባቸው እንደሆነ ወይም የሞተባቸው እንደሆነ ጭቃ ሹሞች ከብት ያውሷቸዋል ። በዋናም ያሻግሩዋቸዋል ።

ስልክ ቀጣዮችና ቴሌግራም ጸሐፊዎች በተራቸው ቀን አይከሰ ሱም ። ቅጣትም የተገኘባቸው እንደሆነ የስልክ አለቃው ሰምቶ ይቀ ጣሉ ። ቀለባቸውንም ቴሌፎን ከተተከለበት ሥፍራ ይቀበላሉ ። ጌታ ከሌለውና ጠባቂ ከሌለው መሬት የተተከለውን ስልክ የሚጠብቁ

ጭቃ ሹሞች ናቸው ። ውድማ የሆነ እንደሆነ ግን የሻለቃው ያስጠ ብቃል ።

ለስልክ መቀጠያ አራት በቅሎ ከነመጫሪያው የሻለቃ ይሰጣል ። ቴሌፎን ከተተከለበት እጠገብ እንዳይከሱ እያበላ ያስቀምጣሉ ። እነዚ ህንም በቅሎዎች እንዳይከሱባቸው ተጠንቅቀው ያበላሉ ። በቅሎዎቹ የከሱባቸው እንደሆነ ባንድ በቅሎ ፪ በቅሎ ይከፈላል ። በእነዚህ በቅሎዎች የመንግስት ትዕዛዝ የሚፈጽሙ ስልክ ቀጣዮች ትእዛዛቸ ውን አድርሰው ሲመለሱ በቅሎዎቹን እዚያው ከሚበሉበት ቦታ እየ መለሱ ያስረክባሉ ። ከቤታቸውም አያውሉም ። አያሳድሩም ። ከመን ግስት ትእዛዝ በቀር ። እነዚህ በቅሎች ስልክ ቀጣዮች ለጉዳያቸው የተ መላለሱባቸው እንደሆነ ፣ በመጀመሪያ እሥር ፲ ብር ፣ በሁለተኛው ሃያ ፳ ብር ይከፍላሉ ። በሶስተኛው ብርቱ ቅጣት ይቀጣሉ ። በቅጣት የሚሰበሰበው ገንዘብ ብርም ቢሆን ፣ በቅሎም ቢሆን ፣ በቴሌግራም ፀሐፊዎች መዝገብ እየተፃፈ በጭቃ ሹሙ እጅ ይቀመጣል ።

ግንቦት ፲፫ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ ም አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ ።

ምኒልክ ይህን ደንብ ካወጡ በኋላ በ፲፰፻፺፱ ዓ.ም. በጥቅምት ወር ማዕከላዊ የቴሌፎንና ቴሌግራፍ መሥሪያ ቤት ተቋቋመ ።

በአገሪቱ ውስጥ በነበረው የእንጨት ችግር ምክንያት የስልክ ሽቦው የሚዘረጋው በየወርካው ዛፍ ላይ ሁሉ በማሰር ነበር ። ባንዳንድ ቦታም የተተከለው የስልክ እንጨት ጠንካራ ባለመሆኑ የስልኩ ሽቦ ከነእንጨቱ እየወደቀ ከባድ ችግር ፈጠረ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ከአዲስ አበባ ሐረር ድረስ የተዘረጋው የስልክ መስመር ገና ወረቱ ሳያልቅለት ሽቦው መሬት ተኛ ። በዚህ ምክንያት የስልኩ መገናኛ ስለተቋረጠ አጤ ምኒልክ ለፊታውራሪ ባንቴ አንድ ደብዳቤ ጽፈው ለስልኩ ሽቦ ጥበቃ እንዲደረግ አዋጅ እንዲነገር አዘዙ ። ደብዳቤውና የአዋጁ ቃል የሚከተሉት ናቸው ።

ይድረስ ከፊታውራሪ በንቴ ፦

ካዋሽ እንስቶ ሐረርጌ ድረስ ያለው የስልክ እንጨት እየተሠበረ ሺቦው መሬት እየወደቀ ። ደግሞ ከዛፍ ላይ የተበጀው እንደገና ዛፉ እየለመለመ ነፋስ ሲመታው ሽቦውን እያወዛወዘው እማያነጋግር ቢሆን ፣ ይሄው ሠራተኞች ሰድጃለሁና በተሰበረውም ፣ በመጥፎውም እንጨት ፈንታ ወፍራም እንጨት እየተተከለ ቶሎ ቶሎ እንዲበጅ አድርግ ። ተሠርቶ እስኪያልቅ ድረስ የሻለቃ ፣ የሻለቃው በያገር በያገሩ አብሮ ቶሎ ቶሎ ያስተክል ። በዚህ ነገር በጣም በርታ ፣ አደ

ራህን ። ደግሞ የስልኩ ነገር ይኸው ያዋጅ ቃል ሰድጄልሃለሁና ስልኩ በየተተከለበት አገር ሁሉ በየሻለቃው እንድታስነግር ይሁን ።

የካቲት ፲፩ ቀን ፲፱፻ ዓመተ ምህረት አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ ።

ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ስማ

በሐረርጌ አውራጃ ስልክ በየተተከለበት አገር ያለህ ሰው ስልክ በተበጠሰ ጊዜ ለባለምድሩ ለመልከኛው ወይም ለጭቃ ሹሙ አስታ ውቀህ እለቱን ለስልከኞች ንገር ። ቦታው እርቆ ዕለቱን ለስልከኞች ለመንገር ጊዜ የመሸብህ እንደሆነ በማግሥቱ ንገር ። ምድሩ ግን ጠፍ የሆነ እንደሆነ መልከኛና የሻለቃ አስጠብቅ ። ደግሞ እንጨቱን መብ ረቅ በመታው ጊዜ የመንግሥት ሥራ እንዳይፈታ ትርፍ ትርፍ የስልክ እንጨት ለመለወጫ አስቀምጥ ።

መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻ ዓመተ ምሕረት ተፃፈ ።

ስልክ ገና ከመግባቱ ስልክ የሚያስፈልገው ለአስቸኳይ ጉዳይ ብቻ መሆኑን ምኒልክ ለየመኳንንቶቻቸው ያስተምሩ ነበር ።

ይድረስ ከራስ ተሰማ

. . . . የስልኩ ነገር ባይሆንልኝ ነው ብለህ ላከብኝ ። ስልኩስ ቢሆን የሚያስቸኩል ብርቱ ጉዳይ ሲገኝ ለመነጋገር ነው ። ሌላውን ጉዳይ እንደዚሁ መላላክ ነው እንጂ ስንቱ ነገር በስልክ ያልቃል ።. . . .

ጥቅምት ፳፮ ቀን ፲፱፻ ዓ ም

ይድረስ ለዋግ ሹም ጓንጉል

የስልከኞቹን ነገር የላኩት ቃል ሁሉ ምላሽ አልመጣልኝም ብለህ ላክብኝ ። የሚያስቸኩል ብርቱ ጉዳይ ሲሆን በስልክ መነጋገር ነው ። አለዚያማ ሌላ ሌላውን ጉዳይ ሁሉ እንደዚሁ በደብዳቤ መላክ ነው እንጂ ስንቱ ነገር በስልክ ያልቃል ።. . . .

ጥቅምት ፳፯ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.



“የአዲስ አበባ ቴሌፎን ሠራተኛ ነው ፤ ጥቂት ደንበኞች አሉዋቸው ። እነኚህም ደንበኞችን ለማገናኘት ከሰላሳ ደቂቃ እስከ ሁለት ሰዓት ጊዜ ይወስዳል ።”




ምኒልክ ፖስታና ስልክ ቤትን መርቀው ከፈቱ ።

## ፖስታ

ኢትዮጵያ የዓለም ፖስታ ድርጅት አባል የሆነችው 1900 ዓ.ም. ሲሆን ሥራው የተጀመረው ግን በ1886 ዓ.ም. ግድም ነው። ኢትዮጵያ ከዓለም የፖስታ ድርጅት እስክትገባ ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ሚኒስቴሩ አልተቋቋመም ነበር። ዳግማዊ አጤ ምኒልክ የኢትዮጵያ የፖስታ ሥራ በዓለም ታውቆ ተቀባይ እንዲኖረው ለማድረግ ጥረዋል። በአገሪቱ ላይ የነበረው ችግር ኢትዮጵያን ከዓለም ፖስታ ማኅበር ማስገባት ብቻ ሳይሆን በሞያው የሰለጠነ ሰው ማግኘቱም ነበር።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በ1885 ዓ ም የካቲት 10 ቀን ከፖስታ ማኅበር ለመግባት ደብዳቤ ቢጽፉ "መጀመሪያ የፖስታ ሥራ ማካሄዱን ይጀምሩ" የሚል መልስ አገኙ። ምኒልክም በፈረንሣይ አገር ፓሪስ ከተማ ውስጥ በመልካቸው የተቀረፀ ቴምብር በ1886 ዓ.ም. በጥቅምት ወር አሳትመው ገበያ ላይ በማዋል ሥራውን ጀመሩ። በተቻለ መጠን ሥራውን ካቋቋሙና ካስጀመሩ በኋላ በተግባሩ ለሚረዳቸው ለስዊስ መንግሥት ፕሬዚዳንት የሚከተለውን ደብዳቤ ፃፉ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ።
ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ይድረስ ከስዊስ መንግሥት ሪፑብሊክ ፕሬዚዳንት

ሰላም ለርስዎ ይሁን።

በ፲፰፻፹፭ በየካቲት ፲ ቀን የኢትዮጵያ መንግሥት ቀድሞ ከነበሩት የክርስቲያን ነገሥታት አንድ ተብሎ የሚጠራ ስለሆነ ያገሬም ሕዝብ ከሮፓ ጋራ እያደረ እየተቃረበ እንዲሄድ ብዬ ለእናንተ መንግሥት ከፖስታ ማኅበር ልግባ ብዬ ላክሁ። እርስዎም ከዚህ ማኅበር ልግባካሉ እንደ ፖስታ ሥርዓት የፖስታውን መንገድ በሚገባ ቀኑ ሳይተላለፍ ማድረግ ይገባዎታል ብለው ላኩብኝ። አሁንም እኔ ከትልቁ ከተማዬ ከእንጦጦ አንኮበር፣ ከእንጦጦ ሐረር፣ ከሐረር ጂቡቲ በሥራት እንዲመላለስ አደረግሁ። ይህም መመላለስ በ፰ በ፰ ቀን ሳይጐድል ይመላለሳል። ከጂቡቲም ፖስታ ጋራ ከፍራንሲስ መንግሥት ጋራ በጣም ስለረዱኝ ፖስታችን ተጋጥሚልና እነዚያንም ማመስገን ይገባኛል። እናንተም በወገናችሁ ከኔ መንግሥት አንስቶ ከሮፓ ሕዝብ ጋራ የሚያጋጥመውን ለፖስታ የሚያስፈልገውን የኔን መንግሥት ፖስታ የሚያጋጥመውን ነገር ሁሉ እንድታቀኑልኝ ተስፋ አለኝ። እኔም በመንግሥቱ ሥራት እንዲገባ፣ ደግሞም አገሬ ከሮፓ ክርስቲያን ሕዝብ

ሁሉ ጋራ በጣም እንዲለማመድ ብዬ ለዚህ ለፖስታ የሚገባ ነገር ሁሉ ጠንክሬአለሁ ። በዚሁ በፖስታ ነገር በመዠመሪያ ስለላኩሁልዎ ደብዳቤ የኢጣሊያን መንግሥት አንዳንድ ምክንያት አንስቶ ነበር ብለው ላኩብኝ ። ከዚህ መንግሥት ጋራ ተዋውዬ የነበረው ውል ሳን ስማማ ብንቀር በሚገባ ሆኖ ፈረሰ ። የተጨረሰውም በየካቲት በ፳ ቀን በ ፲፰፻፹፭* መጨረሻ ሆነ ።

እንዲህ ከሆነ ዛሬ የኢጣሊያ መንግሥት ለዚህ ነገር የሚፈልገው ምክንያት ሁሉ አለ ብልሃት ነው ። ሙሴ ኢልግን እጅግ ያገለገለኝ የኔ መሐንዲስ ለዚህ ለፖስታ ማኅበር ለመግባት የሚያስፈልገውን ጉዳይ ሁሉ ለመፈፀም ሙሉ ሥልጣን ሰጥቼዋለሁ ።

በመጋቢት ፲ ቀን በ፲፰፻፹፯ ዓመተ ምሕረት ተፃፈ ።

በዘመኑ የፖስታ ማኅበር ዋና መሥሪያ ቤት በስዊስ ውስጥ በበርኔ ከተማ ነበር ። ዳግማዊ ምኒልክ ለስዊሱ ፕሬዚዳንት ደብዳቤ የፃፉበትም አንዱ ምክንያት ይኼ ነበር ። ኢትዮጵያ በፖስታ ሥራ እንቅ ስቃሴዋን ከጀመረች በኋላ በቀጥታ ከማኅበሩ እንድትገባ ምኒልክ የሚ ከተለውን ደብዳቤ በኢትዮጵያ የፈረንሣይ ሚኒስትር ለነበሩት ፃፉ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ይድረስ ከሚኒስትር ክሎቢኮብስኪ

ሰላም ላንተ ይሁን ።

የኢትዮጵያ ቴሌግራፍና ፖስታ እንደ ሮፓ መንግሥት ደንብ ከኡኒዮን ፖስታ እንዲገባ አስታውቅሃለሁ ። ሌሎቹ መንግሥቶች እንደሚከፍሉት ገንዘብ እኛም ባመት ባመት እንደደንቡ ለኡኒዮን ፖስታል እንሰጣለን ። የፖስታና የቴሌግራፍ ሠራተኞች ከዚህ ቀደም ስድስት ሰዎች እንድታስመጣልን ጠይቀን ነበር ። አሁንም በቶሎ እንድታስመጣልን ይሁን ። ደመወዛቸውንም እንደ ሥራቸው መጠን ከመቶ አንስቶ እስከ መቶ አምሳ ድረስ በተዋረድ እንሰጣለን ። ደግሞ ስለ መንግሥታችን ጥቅም ቴሌግራፋችን በሥራት በትክክል እንዲሄድ የምድር ባቡር ኩምፓንዮች ባቆሙት የስልክ ብረት ላይ እስከ ወሰና ችን ድረስ የስልክ ሽቦ እንዲዘረጋበት የፈረንሳይ መንግሥት እስከ

* የውጫሌን ውል አፍርሻለሁ ብለው ለኤሮፓ መንግሥታት ያሳወቁበት ዘመን ነው ።

ወሰኑ ድረስ ሸቦ ዘርግቶ ከኢትዮጵያ ወሰን የስልክ ሸቦ ጋራ እንዲ ጋጠም ለመላላክ እንዲመችን ብታደርግልን ደስ ይለኛል ።

ጥር ፳፪ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ኢትዮጵያ ከዓለም የፖስታ ድርጅት ከገባች በኋላ የፖስታው ሥራ በሚገባ ይካሄድ ጀመር ። በዘመኑ አዲስ አበባ መጥቶ የነበረው ግሊከን “. . . .የፖስታ አገልግሎት ተቋቁሟል ። በየሳምንቱ አንድ ጊዜ ከአዲስ አበባ ወደ ሐረር የሚሔድ የምኒልክ መልክተኛ አለ ። . . . .” ሲል ጽፏል ።

ምኒልክ የፖስታ ድርጅትን ካቋቋሙ በኋላ ሥራው የተጀመረው ወዲያውኑ ነው ። ሙሴ ኢልግ ወደ አገሩ ዙሪክ ሔዶ በነበረበት ጊዜ ምኒልክ በጻፉለት ደብዳቤ “. . . .ፖስታ ማበጀታችን እንኳን ያንተ የወዳጆችን ደብዳቤና የማንም ነጋዴ ደብዳቤ ሁሉ እንዲመላለስበት ነበር ። ያንተ ደብዳቤ መጥፋቱ ፖስታ ለምን ተደላደለ ብለህ አኩር ፈህ ይሆን ወይስ የምድር ባቡር እስከ አዲስ አበባ ድረስ እስቲበጅ መጠበቅህ ይሆን ። ያለዚያ ያንተን ደብዳቤ የሚውጥ አውሬ ከመንገድ ላይ እንዳለ ቁርጡን አስታውቀኝ ።. . . .” ብለዋል ። ይህን ደብዳቤ የጻፉት ሐምሌ 13 ቀን 1887 ዓ.ም. ነው ። በዚያ ዘመንም ማለት ኢትዮጵያ ፖስታ ማህበር ከመግባትዋ 13 ዓመት በፊትም የፖስታው ሥራ ይካሄድ እንደነበረ ይገመታል ።

ኢትዮጵያ ከዓለም የፖስታ ማህበር ከገባች በኋላ በማመላለሱ ተግባር በኩል ከፍተኛ ችግር ደርሶ ነበር ። ይህንንም ችግር ምኒልክ በእንዴት ያለ ዘዴ እንደተወጡት ለሐረርጌው ገዥ ለደጃዝማች ባል ቻና የአፋር ገዥ ለነበሩት ለአዛዥ ወልደጣዲቅ የጻፉዋቸውን ሁለት ደብዳቤዎች እንመልከት ።

ይድረስ ከደጃዝማች ባልቻ

የዚህ የፖስታ አመጣጥና አካሄድ እጅግ የሚያስቸግር ሆነ ። ባለ ትዳርና ባለርስት የሆነ ዋና ዋና ሰው ካላመላለሰው ባለደሞዝ ወታደር አመላልሶት ፖስታው ቢጠፋና ከጊዜው ቢተላለፍ እሱን ቀጥተን የም ንጠቀምበት ነገር የለም ። አሁንም ከአዋሽ ወዲህ ቴሌፎን በተተከለ በት ቦታ ሁሉ ዋና ዋናውን ገባር ፣ እርስትና ትዳር ያለውን እየመረጥን በቅሎውም ሰውም እንዳይጐዳ በየተራ እንዲያመላልስ ሃያ ፳ ሰውና ፲ አስር በቅሎ አድርገናል ። ስለዚህ ላንተም ይሄው የደንቡን ወረ ቀት ልኬልሃለሁ ። ይህንንም የደንቡን ወረቀት አይተህ ከአማራው

ባለቀላድ ባለትዳር ባለትዳሩን መርጠህ በግዛትህ ቴሌፎን በተተከለ በት ቦታ እንደዚሁ እንደደንቡ ሃያ ፳ ሰው፣ሃያ ፳ በቅሎ አድርግ ። የሰዎቹን ቁጥር ስም ስማቸውን በየቦታው የምታደርጋቸውን ለይተህ አስታውቀኝ ።

መስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፩ ዓ.ም.

ይድረስ ከወህኒ አዛዥ ወልደጻዲቅ

ከይሮፓ ነገሥታት ደብዳቤ ከሚመላለስበት ከስዊስ መንግሥት ከፍቅር ማኅበራቸው ገባን ። ደስ አለኝ ። ነገር ግን እማህበር ስለገባንና ደስ ስላለኝ ፖስታው ሲመላለስ የሚገባበት ጊዜ፣ እንኳን ቀኑ ይተላለፍና ከሰዓትም ከደቂቃም ቢሆን የተላለፈ እንደሆነ በስዊስ ማህበር ዳኛ ተከሰን ካሣ ጨምረን የጠፋውን ገንዘብ እንከፍላለን ። አለጥፋት ፖስታ በደህና የተመላለሰ እንደሆነ ለመንግሥታችን እጅግ ክብር እጅግ ጥቅም ነው ። በዚህም በፖስታው የሚመላለስ ወረቀት ብቻ አይደለም ። ወርቅ፣ አልማዝ፣ የገንዘብ ማድረጊያ የኃዋላ ወረቀት ይመላለስበታል ። በዚህም ፖስታችንን የሚያመላልሱ መንግሥታት የእንግሊዝ፣ የጀርመን፣ የፈረንሳይ፣ የሞስኮብ፣ የኢጣሊያ፣ የነምሳ፣ የእስፓኝና የቤልጅግ፣ የስዊስ፣ የፖርቱጋል፣ የቱርክ፣ የሞንትኔግሮ፣ የሆላንድ፣ የኖርቤጅ፣ የቡልጋሪያ፣ የአሜሪካ፣ የዣፓን፣ የቤን፣ የሌሎችም የዓለም ሁሉ መንግሥታት ነው ።

የሚመላለሰው ዕቃ በኛ በኩል ነው ። ስለዚህ ሁሉ ነገር በየሥፍራው ለጠያር ግመል ማብሊያ ከድሬዳዋ እስከ ጭባ ድረስ፣ አንድ ደብዳቤ፣ አንድ ዕቃ ቢጠፋ ጥፋቱም ምስጋናውም ባንተ ላይ ነውና እንዳፈጥን በጠያር እንዲመላለስልኝ አድርግ ።

ለጠያርም ግመል ማረፊያ ቦታ የረር ላይ አንዱን ጐሣ፣ ዳራኤላ ላይ አንዱን ጐሣ፣ ቢለን ላይ አንዱን ጐሣ፣ አዋራ መልካ ላይ አንዱን ጐሣ፣ መርጠህ አንስተህ እንዳንዱ ቦታ ላይ የአዳልና የኢሳ የአማርኛ አፍ ያወቁ፣ በረሃውን የለመዱ፣ ንብረት ያላቸው አስር ፲ ዋና ዋና ሰውና ሃያ ፳ ጠያር ግመል ማስቀመጥ ነው ። ቢላል ላይ ግን ውሃውና ቦታው ለግመል የተመቸ ነው ብለውኛልና ሲሆን ፩፻ አለዚያ ስልሳና ሰባ ግመል እያስገራህ ለማስተጓጓዣ እንዲሆን በብዙ አድርግ ። ከድሬዳዋ እስከ አጨባ ሲሔድም ሲመጣም፣ ሲሆን አለዚያ በአራት ቀን ከዚያም እንዳይተላለፍ ይሁን ። ይህን ሁሉ ትእዛዝ የሚሰሙትን በየቦታው ዋና ዋና ሁነው የሚቀመጡትን ሹሞችህን ከበየነ ድረስ ሰደሃቸው ከበየነ የደንቡን ወረቀት ተቀብለው በዚህ በፖስታው ነገር

የሱን ትእዛዝ እንዲሰሙ አድርግ ። ለሰዎቹም ጠመንጃና ጥይት አስ ቀድመን እንሰጣቸዋለን ። ደሞዛቸውንም በወር በወር ይቀበላሉ ። ስለ ዚህ ቁጥራቸውንና ስማቸውን እስተሚቀመጡበት ቦታ ለይተህ በደብ ዳቤ እንድታስታውቀኝ ይሁን

ሕዳር ፳፯ ቀን ፲፱፻፩ ዓ. ም.

በኢትዮጵያ የፖስታ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የውጭ አገር ሰዎችን አስለቅቀው በሥራው ላይ የተሾሙት ኢትዮጵያውያን አቶ በለጠ የሐረር የፖስታና የስልክ ቤት ሹም ፤ አቶ ድንቁ የድሬዳዋ ፖስታ ቤት ሹም ፤ አቶ በየነ መርሻ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ወሰን ላይ የደወሌ ፖስታ ቤት ሹም ናቸው ። እነዚህም ሰዎች በዳግማዊ አጤ ምኒልክ የተሾሙት ጥቅምት 19 ቀን 1901 ዓ. ም. ነው ።

## ኤሌትሪክ

አንድ ቀን ምኒልክ ከውጭ አገር ከመጡ ፈረንጆች ጋር እየተ ዘዋወሩ አዲስ አበባ ከተማን ሲጐበኙ ወንጀለኞች ከተሰቀሉበት ቦታ ደረሱ ። እነኚያን የተሰቀሉትን ሰዎች ፤ ፈረንጆች እንዳያዩ ምኒልክ ወደሌላ አቅጣጫ እየጠቆሙ ወሬ ያወሩላቸው ጀመር ። ፈረንጆቹ ግን የተሰቀሉትን ሰዎች ስላዩ ምኒልክን ፤ "ጃንሆይ ። ለምን በእንዲህ አይነት አገዳደል ሰውን ይቀጣሉ?" ብለው ጠየቁዋቸው ።

ምኒልክም "እነኚህ ሰው የገደሉ ሽፍቶችና ሌቦች ናቸው ። በእናንተ አገር ሰው የገደለ ሰው በሕግ አይገደልምን?" አሏቸው ።

ፈረንጆቹም "መገደል ይገደላል ። የሚገደለው ግን እንደዚህ በአደባባይ ሳይሆን በቤት ውስጥ በኤሌትሪክ ወንበር ነው" አሏቸው።

"ወንበሩ እንዴት ይገድላል?" አሉ ምኒልክ ።

"እንዲሞት የተፈረደበት ወንጀለኛ ከወንበሩ ላይ ቁጭ ሲል ቁልፉ ይከፈታል ። ቁልፉ ሲከፈትም ወዲያው ይሞታል " ብለው አስረዱዋቸው ። ምኒልክ በዚህ በአዲሱ የወንጀለኞች የመግደያ ዘዴ ተደስተው በአስቸኳይ ሶስት ወንበሮች እንዲመጡላቸው አዘዙ ።

ሶስቱ ወንበሮች ከአሜሪካ ተገዝተው አዲስ አበባ ገቡ ። ምኒል ክም በወንበሮቹ መምጣት ተደስተው ሞት የተፈረደባቸውን ወንጀ ለኞች አስቀርበው በነዚያ ወንበሮች እንዲገደሉ አዘዙና አገዳደሉን ለመመልከት ከወንበሮቹ ዙሪያ ቆሙ ።

መሐንዲስ አማካሪዎቻቸውም "ጃንሆይ ። ወንበሩ እኮ እንዲሁ አይገድልም" አሏቸው ።

"ኋላስ?" አሉ ምኒልክ ።

"ኤሌትሪክ ከሌለ አይገድልም" አሏቸው ።

"ምንድነው ኤሌትሪክ?" አሉ ምኒልክ ።

"ኤሌትሪክ ለመብራትም ፣ ለኃይልም የሚሆን ነገር ነው" ብለው ስለኤሌትሪክ ጥቅም በሰፊው አስረዱዋቸው ።

"እሱን ነገር ደግሞ ቶሎ ብላችሁ አስመጡልኝ ። ከነዚህ ወንበ ሮችም አንዱን ለኔ መቀመጫ ከዙፋን ቤት አድርጉልኝ ። አንዱን ደግሞ ለአባተ ስጡት" ብለው አዘዙ ። ከዚህ በኋላም ኤሌትሪክ በኢትዮጵያ ገባ ። ለመጀመሪያ ጊዜም በ1889 ዓ.ም. በቤተ መንግሥት ውስጥ በራ ።

## አውቶሞቢል

በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ የሆነችው የመጀመሪያዋ አውቶ ሞቢል አዲስ አበባ የገባችው በ1900 ዓ ም ነው ። ያቺ የመጀመሪ ያይቱ አውቶሞቢል የመጣችው ከእንግሊዝ አገር ነው ።

መኪናይቱን ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት ያሰበው ቤንትሌይ የተ ባለ ሰው ነው ። ቤንትሌይ ስለምኒልክ እየጠየቀ ብዙ ወሬ ሰም ቷል ። ከሰማውም ዜና ምኒልክ የመኪናን ታሪክና ሥራ እየሰሙ መኪና ለማየት ይጓጓሉ ሲሉ ሰምቷል ። ቤንትሌይ መኪና ይዞ አዲስ አበባ ለመግባትና ለምኒልክ ለማሳየት ወሰነ ። ለእንዲህ ዓይነቱ ረጅምና መንገድ ለሌለበት ጉዞ ጠንካራ አውቶሞቢል እንደሚያስፈልግ አሰበ። ይህንንም አሳቡን ዌልሲሌይ ቱል ኤንድ ሞተር ማኒፋክቸሪንግ ኩም ፓኒ ሥራ አስኪያጅ ለሆነው ለሚስተር ሲድሌይ አጫወተው ። ሚስተር ሴድሌይም ይህን አሳብ ደግፎ መኪና መረጣ ጀመሩ ።

የአውቶሞቢል ጉዳይ በኩባንያው በኩል የሚፈጸም ሆነ ። ለቤን ትሌይ ሌላ ችግር የሆነበት ጓደኛ ወይም ሹፌር የማግኘቱ ነገር ነበር ። የሚፈልገው ሰው ፣ የሚደሰት ፣ የማይደከመው ፣ የማይመረር ፣ የማይበሳጭ ፣ የራሱን መኪና ብዙ ጊዜ የነዳና ጥሩ የሾፌርነት ልምድ ያለው ሰው ነበር ። የአሳቡ ጠንሳሽ ቤንትሌይ እንዲህ ዓይነቱን ሰው ለማግኘት ለንደን ከተማ ውስጥ ሲፈልግና ሲያስፈልግ ቆየ ። አንድ

ቀን ቤንትሌይ ፣ በሚስተር ዌልስ መኪና አብረው ሲሔዱ የዌልስን የመኪና አነዳድ አይቶ ደስ አለው ። ወዲያውኑ "ስማ ዌልስ ፣ በሚመ ጣው ሣምንት ከኔ ጋር ወደ አቢሲኒያ ትሄዳለህ?" አለው ። ዌልስም "በደስታ ጌታው ፣ ግን አቢሲኒያ የት ነች?" ሲል ጠየቀ ።

የእንግሊዝ ጋዜጠኞች ይህን ጉዳይ ይከታተሉ ስለነበር እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 18 ቀን 1907 ዓ.ም. የእንግሊዝ ጋዜጠኞች ማኅበር አባላት ትሮካዴሮ በተባለ ሆቴል ቅዳሜ ማታ የመሰነባበቻ ግብዣ አደረጉላ ቸው ።

እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 19 ቀን እሁድ ወደ ፎልክስተን ጉዞአቸውን ጀመሩ ። ዌልስ እየነዳ ከጐኑ ቤንትሌይ ተቀምጧል ። ከኋላው መቀመጫ 'እደረሳችሁበት እደርሳለሁ" ያለ አንድ ቡሊ የሚሉት ወጣት ተቀ ምጧል ። ቤንትሌይ የዙሉ ቋንቋ በሚገባ የሚችል ሲሆን አማርኛም አጥንቶ በመጠኑ ይናገራል ።

ከፈረንሣይ ዋና ከተማ ፓሪስ ሲደርሱ ጋዜጠኞች ቃለ መጠይቅ አደረጉላቸው ። ከሶስት ቀናት በኋላ ወደ ማርሴል ተጓዙ ። ቤንዚን የቻላቸው ላካምፓኝ ጀኔራል ዱፔትሮሊዮም የተባለ ኩባንያ ነው ። 750 ጋሎን ቤንዚን ሰጥቷቸዋል ። በምግብ በኩል እያንዳንዱ ሳጥን 144 ጠርሙስ የያዘ ስድስት ሳጥን አክሶ (OXO)
100 ጣሣ ሥጋ
25 ኪሎ ግራም የሻይ ቅጠል
72 ጣሳ ብስኩት
50 ከረጢት ፍራፍሬ
40 ጣሳ ደረቅ ብስኩት
20 ኪሎ ግራም ፩ መአዘን ስኳር
4 ትልልቅ ሳጥን የፍሬ ጭማቂ
288 ጣሳ የቆርቆሮ ወተት
288 ጣሳ ሰርዲን
40 ጠርሙስ የቡና ዱቄት
100 ጣሳ ለሾርባ የሚሆን ምግብ
10 ከረጢት ዱቄት ፣ ጥቂት ጠርሙሶች ውስኪ ፣ የመንገድና የከ ተማ ልብስ ፣ መድኃኒት ፣ አራት ጠመንጃና ሶስት ሽጉጥ ፣ የሁለት ጊዜ ቅያሬ ጐማና የመንገድ መለያ ካርታ ፣ ታርጋ ቁጥርዋ ዲ 3130 የሆ ነችውን መኪና ይዘው መርከብ ላይ ተሳፈሩ ።

ሃያ ሰባት ቀን ሙሉ በባህር ላይ ሲጓዙ ከርመው ጂቡቲ ደረሱ ። ጂቡቲ ሲደርሱ ከአገራቸው ከእንግሊዝ ከወጡ ሁለት ወር ሆኗቸ

ቀን ቤንትሌይ ፣ በሚስተር ዌልስ መኪና አብረው ሲሔዱ የዌልስን የመኪና አነዳድ አይቶ ደስ አለው ። ወዲያውኑ “ስማ ዌልስ ፣ በሚመ ጣው ሣምንት ከኔ ጋር ወደ አቢሲኒያ ትሄዳለህ?” አለው ። ዌልስም “በደስታ ጌታው ፣ ግን አቢሲኒያ የት ነች?” ሲል ጠየቀ ።

የእንግሊዝ ጋዜጠኞች ይህን ጉዳይ ይከታተሉ ስለነበር እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 18 ቀን 1907 ዓ.ም. የእንግሊዝ ጋዜጠኞች ማኅበር አባላት ትሮካዲሮ በተባለ ሆቴል ቅዳሜ ማታ የመሰነባበቻ ግብዣ አደረጉላ ቸው ።

እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 19 ቀን እሁድ ወደ ፎልክስተን ጉዞአቸውን ጀመሩ ። ዌልስ እየነዳ ከጐኑ ቤንትሌይ ተቀምጧል ። ከኋላው መቀመጫ ‘እደረሳችሁበት እደርሳለሁ” ያለ አንድ ቡሊ የሚሉት ወጣት ተቀ ምጧል ። ቤንትሌይ የዞሉ ቋንቋ በሚገባ የሚችል ሲሆን አማርኛም አጥንቶ በመጠኑ ይናገራል ።

ከፈረንሣይ ዋና ከተማ ፓሪስ ሲደርሱ ጋዜጠኞች ቃለ መጠይቅ አደረጉላቸው ። ከሶስት ቀናት በኋላ ወደ ማርሴል ተጓዙ ። ቤንዚን የቻላቸው ላካምፓኝ ጀኔራል ዱፔትሮሊዮም የተባለ ኩባንያ ነው ። 750 ጋሎን ቤንዚን ሰጥቷቸዋል ። በምግብ በኩል እያንዳንዱ ሳጥን
144 ጠርሙስ የያዘ ስድስት ሳጥን አክሶ (OXO)
100 ጣሣ ሥጋ
25 ኪሎ ግራም የሻይ ቅጠል
72 ጣሳ ብስኩት
50 ከረጢት ፍራፍሬ
40 ጣሳ ደረቅ ብስኩት
20 ኪሎ ግራም ፩ መአዘን ስኳር
4 ትልልቅ ሳጥን የፍሬ ጭማቂ
288 ጣሳ የቆርቆሮ ወተት
288 ጣሳ ሰርዲን
40 ጠርሙስ የቡና ዱቄት
100 ጣሳ ለሾርባ የሚሆን ምግብ
10 ከረጢት ዱቄት ፣ ጥቂት ጠርሙሶች ውስኪ ፣ የመንገድና የከ ተማ ልብስ ፣ መድኃኒት ፣ አራት ጠመንጃና ሶስት ሽጉጥ ፣ የሁለት ጊዜ ቅያሬ ጐማና የመንገድ መለያ ካርታ ፣ ታርጋ ቁጥርዋ ዲ 3130 የሆ ነችውን መኪና ይዘው መርከብ ላይ ተሳፈሩ ።

ሃያ ሰባት ቀን ሙሉ በባህር ላይ ሲጓዙ ከርመው ጂቡቲ ደረሱ ። ጂቡቲ ሲደርሱ ከአገራቸው ከእንግሊዝ ከወጡ ሁለት ወር ሆኗቸ

ዋል ። ጂቡቲ እንደደረሱም ለጂቡቲም የመጀመሪያ መኪና ስለነበረች ታሪክ ሰሪዎች ተብለው የጂቡቲው አገረ ገዥ ሙሴ ፓስካል የራት ግብዣ አደረጉላቸው ። በዚያ የራት ግብዣ ላይም ሌሎች ሁለት አውቶሞቢሎች ከፈረንሣይ አገር ሊመጡ መነሳታቸውን ቤትንቴሌይ ሰማ ። በዚህ ምክንያት እንዳይቀደም ብሎ ቤንትሌይ ጂቡቲ ሊቆይ አልፈለገም ።

በጅቡቲ ሕዝቡ እየተደነቀና እየከበበ መኪናዋን እያየ 10 ቀን ቆዩ ። አሥር ቀን የቆዩበት ምክንያት ስለመንገዳቸው ጥናት ሲያደርጉ ነበር ። ጂቡቲ ያሉት ፈረንሣዮች መኪናይቱ ወደ ኢትዮጵያ እንዳት ገባ በይፋ ባይናገሩም በተግባር ይገልጹ ነበርና በመንገድ ላይ ታርደው እንደሚቀሩ እየነገሩዋቸው ቆዩ ። በመጨረሻው የጂቡቲ ባለሥልጣኖች ከጂቡቲ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ፈቃድ እንደማይሰጣቸው አስረድተው ወደ እንግሊዝ ሶማሌ ቢሔዱ ግን እንደማይከለክሏቸው ነገሩዋቸው ።


እነ ቤንትሌይ ከጂቡቲ ወደ እንግሊዝ ሶማሌ ዕቃቸውን በኪራይ ግመል አስጭነው በመኪናቸው ጉዞ ጀመሩ ። ከጂቡቲ በተነሱ በአራተኛው ቀን ዘይላ ደረሱ ። ዘይላ እንደደረሱም የዘይላው አገረ ገዥ "ወደ ጂቡቲ ተመልሳችሁ መኪናዋን በባቡር ድሬዳዋ ድረስ ላኩ እንጂ ከዚህ ከዘይላ በመኪናዋ እንድትሄዱ አልፈቅድም ። ከድሬዳዋ በኋላ ግን የራሳችሁ ጉዳይ ነው" አላቸው ። እነቤንትሌይ የፈለገው ይሁን ብለው ዕቃዎቻቸውን በግመል ጭነው አስቀደሙና በመኪናቸው ጉዞአቸውን ወደ ኢትዮጵያ ጀመሩ ።

". . . . ከኢትዮጵያ ግዛት ዱአሌ ላይ ስንደርስ በየቤቱ በራፍ የኢትዮጵያ ባንዲራ ተሰቅሎ አየን ። በኛም መኪና ላይ የእንግሊዝና የኢትዮጵያ ባንዲራ ግራና ቀኝ ተሰቅሏል ። ከመንደርዋ ስንገባ ብዙ ተኩስ ተሰማ ። ተኩስም የተተኮሰው ለክብራችን መሆኑ ተነገረን ። ወደ መሀል ስንገባ በሰልፍ የቆሙ የኢትዮጵያ ወታደሮች አጋጠሙን ። ቤንትሌይ ከመኪናዋ ላይ ወርዶ ሰላምታ ሰጠ ። ከሰልፉ አዛዥ ጋርም ተጨባበጡ ። ግሪካዊው ነጋዴ ጆርጂም ከዚያው ነበረ ። ጆርጂ ኢትዮጵያ ከገባ ከአሥር እስከ 15 ዓመታት ስለሚሆነው የመኪና ነገር ለጆርጂም አዲሱና ብርቁ ነበር ። ከዚያም ግብዣ ተደረገልንና ጠጅ ሁሉ ጠጣን ። መኰንኑም በጉዞአችን ሁሉ ምንም ችግር እንዳይገጥመንና የሚቸግረንን ሁሉ እንዲረዳን ከምኒልክ መታዘዙን ነገረን ። . . . . ይላል ሐሲ ።

ድሬዳዋ ሲደርሱ ታላቅ አቀባበል ተደረገ ። ሕዝቡ የኢትዮጵያንና የእንግሊዝን ባንዲራ እየያዘ በሰልፍ ተቀበላቸው ። ስለክብራቸውም




የመጀመሪያዋ አውቶሞቢል ዱአሌ ስትደርስ የተደረገ አቀባበል ።



ድሬዳዋ ገቡ ።




የድሬዳዋ ሙቀትና የአውቶሞቢልዋ የኋላ አካል ።



ስንቅና ዕቃቸው የሚጓዘው በእንስሳት እየተጫነ ነበር።




የአዲስ አበባው ጉዞ



ወደ አዲስ አበባ ተቃረቡ ።



አዲስ አበባ ከተማ ከመግባታቸው በፊት ታላቅ አቀባበል ተደረገላቸው ።



አውቶሞቢልዋ እቴጌ ሆቴል ደርሳ ቆመች ።

ብዙ ጥይት ተተኰሰ ። ቤንትሌይ ሲናገር “. . . . በድሬዳዋ ከመኳንንቱ ጋር ስጨባበጥ የመጨባበጡ ሥርዓት ብቻ እኩል ሰዓት ፈጀብኝ . . . .” ብሏል ። በድሬዳዋ ታላቅ ግብር ተደረገ ። ግብዣውንም አዘጋጅተው ግብር ያገቡት የድሬዳዋው ጉምሩክ ኃላፊ አቶ ንጋቱ ናቸው ።

ሐረር ያሉ መኳንንት መኪናዋን ማየት ስለፈለጉ መኪናዋን ይዘው ሐረር ሄዱ ። ከሐረሩና ከድሬዳዋው ጉብኝት በኋላ በአሰቦት በኩል መንገዳቸውን ወደ አዲስ አበባ አመሩ ።

በብረሃው ውስጥ መጀመሪያ የኢሳው ፡ ቀጥሎ የአፋሩ ሕዝብ ከባድ ችግር ፈጠረባቸው ። ከዕቃ አጓጓዦቻቸውም መሀል ተገደሉባ ቸው ። በዚያ ላይ የመንገዱ ሥራ ከባድ ድካም ነበረበት ። አዋሽን ተሻግረው ሸዋ ግዛት ከገቡ በኋላ ግን በየደረሱበት መጥን እየታዘዘ ጠጁ ፡ ሥጋው ፡ ወተቱ ፡ እንቁላሉ ሁሉ ይቀርብላቸው ነበር ።

የመኪናዋ የተፈጥሮ የመጨረሻ ታላቅ ፍጥነት በሰዓት 65 ኪሎ ሜትር ነው ። የአምስት ሰዎች መቀመጫ ፡ 18 የፈረስ ጉልበትና አራት ሲሊንደር ነበራት ። በበረሃ በሚጓዙበት ጊዜ ፍጥነታቸው በሰዓት አንድ ኪሎ ሜትር ነበር ። ምክንያቱም አሸዋው መኪናዋን አላስኬድ እያለ በማስቸገሩ ሱማሌዎችን እየቀጠሩ ድንጋይ በማስነጠፍ ይጓዙ ስለነበር ነው ። አንዳንዴም በበቅሎ እየተጐተተች ፡ ድንጋያማ ወንዝ ሲያጋጥምም በሰው ሸክም እየተሻገረች ፡ ተራራ ሲሆን እየተገፋች ነበር ጉዞዋ ።

ከአገራቸው በተነሱ በሰባተኛው ወር በ1900 ዓ.ም. ታህሳስ 20 ቀን አዲስ አበባ አካባቢ ደረሱ ። እንዳትረሱት የሚያስፈልገው ነገር መኪናይቱ ሰዎቹን ይዛ ትጓዝ እንጂ ማንኛውም ዕቃቸውና ስንቃቸው የሚጓዘው በግመል ተጭኖ ነው ። ከጓዛቸውም ጋር የሚገ ናኙት ማታ ሠፈር ላይ ነው ። ቤንዚንም የሚሞላውና ዘይትም የሚ ጨመረው ያኔ ነው ።

አዲስ አበባ ለመግባት ጥቂት ሲቀራቸው እጅግ ብዙ ሕዝብ ተሰልፎ ጠበቃቸው ። ከፍተኛ አቀባበልም ተደረገላቸው ። ከዚያም ትልቅ ድንኳን ተተክሎ ስለነበር ረፍት አድርገው ሲጋበዙ ውለው ድንኳኑ ውስጥ አደሩ ። በማግሥቱም ወደ አዲስ አበባ ከተማ ጉዞአ ቸውን ጀመሩ ።

አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሲደርሱ ሁለት ሺህ ያህል ፈረሰኛ ሊቀበላቸው መጣ ። በዚህ ሕዝብ መሀከልም የአዲስ አበባ ከንቲባ አብረው ነበሩ ። ሕዝቡ ሆ እያለ አቀባበል ሲያደርግ ባለመኪነኞቹም የመኪናይቱን ጥሩንባ እየነፉ አዳመቁት ። ፈረሶች ግን እየደነበሩ አስ

ችገሩ ። መላመድ አይቀርምና ፈረሶች መኪናዋን ሲላመዱዋት በፈረሰ ኞች ታጅባና ተከባ ጉዞው ወደ አዲስ አበባ ተጀመረ ።

አዲስ አበባ ከተማ ዳርቻ ሲደርሱ ለአቀባበላቸው ቁጥሩ ያልታ ወቀ መድፍ ተተኰሰ ። በዚያም መኪናይቱ ቆማ ለሁለተኛ ጊዜ ለተደ ረገው አቀባበል ሥነሥርዓት ተጀመረ ። በኢትዮጵያ የእንግሊዝ መን ግሥት ተወካይ የነበሩት ሚስተር ሆለር መኪናይቱን ከእንግሊዝ አገር ጀምሮ ይዟት ለመጣው ለቤንትሌይ ሰላምታ ሰጥተው ተቀበሉት ። ወዲያውኑም ባጠገባቸው ከነበሩት ከራስ ወልደ ጊዮርጊስ ጋር አስተ ዋወቁት ። ስለዚያች ቦታ እውቂያ ሐሴ ሲገልጽ "....ስማቸውን አሁን ከረሳናቸው ታላላቅ ሰዎች ጋር ተዋወቅን ...." ብሏል ። ከዚህ የአቀ ባበል ሥነ ሥርዓት በኋላ በፈረሰኞች ታጅበው ወደ መሀል ከተማ ጉዞው ተጀመረ ። የሚጓዙበት መንገድ ግራ ቀኙ በሕዝብ የተሞላ ነበር ።

መኪናይቱን የሚነዳው ዌልስ እየተጀነነ ጉዞው ቀጠለ ። ዳግማዊ ምኒልክ "ካዲሱ ሆቴል ይረፉ" ብለው ስለነበር ታህሣሥ 21 ቀን 1900 ዓ ም በጊዜው እቴጌ ሆቴል ይባል ከነበረው ከእቴጌ ጣይቱ የግል ሆቴል ገቡ ። መንገደኞቹ ተጣጥበው ሲጨርሱ ታላቅ ግብር ቀረበ ። ግብሩ እንዳለቀ የዳግማዊ አጤ ምኒልክ መልክተኛ መጣና "መኪናዋን አምጡና ቶሎ ልያት ብለዋል" አላቸው ። ቤንትሌይም "መኪናዋ ስለቆሸሸች እስክናጥባት ድረስ ጊዜ ይሰጠን" ብሎ ለእንግሊዙ ጉዳይ ፈጻሚ ለሆለር ነገረ ። ሆለርም ይህን መልክት ይዞ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ዘንድ ሄደና በጉዳዩ ተነጋግሮ ለጧት አምስት ሰዓት ቀጠሮ ተቀብሎ ተመለሰ ።

በቀጠሮው መሠረት በማግስቱ መኪናዋን ይዘው ወደ ግቢ ሔዱ ። መኪናዋንም ከሕዝቡ መሀል ከግቢ አቁመው እጅ ለመንሣትና ከምኒልክ ጋር ለመተዋወቅ ወደ አዳራሹ ገቡ ። ከምኒልክ ጋር በአዳ ራሹ ውስጥ ከተዋወቁ በኋላ ምኒልክ መኪናዋን ለማየት ወጡ ። መኪናዋ አጠገብ ሆነው በቤንትሌይ አስረጅነት ስለ መኪናዋ ጉዳይ አንድ ባንድ ተረዱ ። በዚህ ጊዜ አብዛኛው መኳንንትና ሕዝብ መኪ ናዋን መጠጋት ፈርቶ ነበር ። ምኒልክም መኪናዋን እንዳይጠጉ ብዙ ዎቹ ብዙ መከረዋቸው ነበር ። ምኒልክ ግን የሁሉንም የማስፈራሪያ ምክር አልሰማ ብለው መኪናዋን ተጠግተው አዩ ።

ምኒልክ መኪናዋ አጠገብ ቆመው ለእንግሊዝ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ለሆለር ያጫውቱት ጀመር ። "....እየህ ፣ ያ ሁሉ ማስፈራርቾ የለም ። እኔን አንድ ሰው ለመግደል ብሎም ይሄን ሁሉ መንገድ አቋርጦ የሚመጣ ወንበዴ አይደለም ። መሣሪያውም ቢሆን ቀድሞ

እንደተነገረኝ ሆኖ አላገኘሁትም ።....'' አሉት ። ቤንትሌይም መኪናው ምንም አደጋ እንደማያደርስና እሱም ቢሆን እጁም እግሩም ደህና መሆኑን አካሉን እያሳየ ነገራቸው ። ምኒልክም ለቤንትሌይ ሲመልሱ ''.... ገብቶኛል ፤ እያየሁህ ምን ትነግረኛለህ ። ባለፉት ወራት በየቀኑ ስለመኪናዋ ይነገረኝ የነበረው መኪናዋ ላይ የተቀመጥኩ እንደሆነ እንደምታፈናጥረኝ አድርገው ነበር ። እኔም እባካችሁ ይሄ ሞኝነት ነው። እኔን ለማፈናጠር እኮ መኪናዋም አብራኝ መፈናጠር አለባት እላ ቸው ነበር ። ደግሞም እየተፈናጠረች ታስቸግራለች ካላችሁ እስኪ ያጁዋን ሁሉ ታፈናጥራለች ማለት ነው ። ታፈናጠረችው ታዲያ እንዴት ያስኬዳታል ? ተላምዷት ነው ካላችሁም እኔም እላመዳታለሁ እላቸው ነበር ።....'' አሉና የቤንትሌይን ትከሻ ተደገፉት ። ጥቂት ቆይተው የቤንትሌይን ትከሻ ለቀቁና ምኒልክ አጐንብሰው ውስጡን ማየት ጀመሩ ።

ምኒልክ አጐንብሰው የመኪናዋን ጉያ ሲመለከቱ ሆለር ወደ ቤንትሌይ ጠጋ አለና በጆሮው ''በአምስት ፓውንድ እወራረድሃለሁ ፤ ሽማግሌውን መኪናዋ ላይ አስቀምጠህ መንዳት አትችልም'' አለው ። ቤንትሌይም ''በሚገባ እወራረዳለሁ'' አለና ወደ ምኒልክ ጠጋ ብሎ ''ጃንሆይ ፡ መኪናዋን በተግባር ላይ ሆና ሊያዩዋት አይፈልጉም?'' አላቸው ። ''እሱማ በደስታ ነው እንጂ ። ብቻ ግን በበቅሎና በእሷ መሀል ያለው ፍጥነት ምን ያህል ነው?'' አሉት ።

ቤንትሌይም ''ብዙ ልዩነት አለ ጃንሆይ'' አላቸው ።

ምኒልክም ''ደግ ነው ። ለመሆኑ ገበያ ደርሳ ለመመለስ ምን ያህል ጊዜ ይፈጅባታል? እየህ ፡ እኛ በበቅሎ ከዚህ ገበያ ደርሶ ለመመ ለስ ግማሽ ሰዓት ይበቃናል ። የዚህንም ነገር ለማወቅ እንዲረዳኝ በል አንተም ከገበያው ዳርቻ የሚሸጥ አትክልት አለና ለመድረስህ ምልክት እንዲሆነኝ በመኪናህ ሂደህ እሱን ይዘህልኝ ና'' አሉት ።

ዌልስ ሊነዳ ከመኪናዋ ላይ ተቀመጠ ። ቤንትሌይም ከዌልስ ጐን ተቀመጠና ''በተቻለ መጠን ከምንጊዜውም በበለጠ ፍጠንልኝ'' አለው ። የምኒልክ ፈተና ስላስጨነቃቸው መንገዱ ጥሩ ቢሆንም ድን ገት መኪናዋ ብትበላሽስ እያሉ በማሰብ ሳይነጋገሩ ጉዞ ጀመሩ ። በሰዓት 50 ኪሎ ሜትር ፍጥነት ተጓዙ ። ገበያ ደርሰው ምኒልክ የጠየቁዋ ቸውን አትክልት በቅርጫት ይዘው ተመለሱ ። ግቢ ደርሰው አትክ ልቱን ለምኒልክ ሲያሳዩ ምኒልክ ሰዓታቸውን አይተው ''ጥሩ ነው ። ስድስት ደቂቃ ሆነባችሁ'' አሉት ።

ምኒልክም ይህን ፈተና ለቤንትሌይ ሲሰጡ ፈረንጅ ብልጥ ስለ ሆነ ያሞኘኛል ብለው ለምስክርነት ሁለት መኳንንቶች ከመኪናዋ

ኋላ ተቀምጠው አብረው እንዲሄዱ አድርገው ነበር ። መኪናዋ ገቢያ ደርሳ እንደተመለሰች ምኒልክ የመኳንንቶቻቸውን ሁኔታ አዩና ወደ ቤንትሌይ ዞር ብለው "ሁለቱን ሚኒስትሮቼን በማስደንገጣችሁ ብቻ አዝኛለሁ እንጂ በተረፈ መኪናዋ ደህና ነች" አሉ ። እነኚያም ሁለት ሚኒስትሮች ከመኪናዋ ላይ ተደግፈው ሲወርዱ ምኒልክ አዩና "ምን አስፈራችሁ? እኔ አሁን እያስኬድኳት ላሳያችሁ ነው" አሏቸው ። ቤንትሌይም ድምጡን ከፍ አድርጎ ለእንግሊዙ ጉዳይ ፈጻሚ ለሆለር "ንገርልኝ ፣ ሚኒስትሮችዎ እንዴት እንደፈሩ አይተዋል ። እርስዎ ግን እንደማይፈሩ ለምን አያሳዩዋቸውም? በልልኝ" አለው ።

ሆለር ተርጉሞ ሳይጨርስ ምኒልክ ተደስተው ራቅ ብላ ከቆመችው መኪና ላይ ሊወጡ ተንዞ ። ሚኒስትሮቹና መኳንንቱ ምኒልክን እየተጠጉ እንዳይወጡ አሉዋቸው ። ምኒልክም ሰዎቹ በከለከሉዋቸው ቁጥር በኃይል እየሳቁ ታህሳስ 22 ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ መኪናዋ ላይ ወጥተው ከነጂው ከዌልስ ጐን ተቀመጡ ። ሆለር እና ቤንትሌይ ከኋላ ተቀመጡ ። ምኒልክም ዌልስን "ቀስ ብለህ ጀምር" አሉት ። ይህ ሁሉ ሲሆን እቴጌ ጣይቱ ይህን ተአምር ነገር በመስኮት ይመለከቱ ነበር ። ምኒልክ መኪናዋ ላይ ለመቀመጥ በወሰኑ ጊዜ አብረው ለመሔድ ጣይቱን ጥሩ ቢሉ ጣይቱ ፈርተው እምቢ አሉ ።

አውቶሞቢሏ ጉዞዋን ጀመረች ። እግረኛውም ፣ ፈረሰኛውም ማጀብ ስለነበረበት ዙርያውን ከበበ ። መኪናዋ ፍጥነት ስትጨምር አጃቢው እየቀረ ሄደ ። ምኒልክም የአጀቡን መቅረት እንዳዩ ወደ ሆለር ዞር ብለው "የበለጠ ፈጠን እንዲያደርጋት ንገረው" አሉት ። መኪናዋ ፈጠነች ። ምኒልክም ደስ ብሏቸው ይስቁ ጀመር ። "አፍጥን በለው ፣ በጣም ፣ በጣም አፍጥናት በለው" ይሉ ጀመር ። መጨረሻዋ ፍጥነት ድረስ ተነዳች ። ሾፌሩ ዌልስ ዞር እያለ የምኒልክን ሁኔታ ሲያይ በደስታ ብዛት ትንፋሻቸው ቁርጥ እስቲል ይስቃሉ ። ". . . . በጣም የሚያስቃቸውም ያ ሁሉ አጀብ አድማሱ እጠገብ (እጅግ በጣም ርቆ) መቅረቱን እያዩ ነው . . . ." ብሏል ሄል ።

አሥር ማይል ያህል በአዲስ ዓለም መንገድ እንደሄዱ ምኒልክ የዌልስን ክንድ ያዝ አደረጉና "በል በቃህ ። መልሳትና እንመለስ" አሉት ። አንዳንድ የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊዎች ስለመጀመሪያይቱ መኪና ሲጽፉ ምኒልክን በጊዜው መኪና ላይ ማስቀመጡ ነውር እየመሰላቸው "ካንድ ጊዜ በስተቀር አልተቀመጡባትም" እያሉ ጽፈዋል ። ምኒልክ ግን ከመኪናዋ ጋር የተያያዘ ብዙ ታሪክ ያላቸው ሰው ናቸው ።

ምኒልክ የመጀመሪያ ጊዜ የመኪና ላይ ግልቢያቸውን ጨርሰው ሲመለሱ በየመንገዱ ላይ ተበታትኖ የቀረው አጃቢ ሁሉ ወደ መኪ

ናዋ እየተጠጋ የምኒልክን በሕይወት መኖር ፈዞ ያያል ። ምኒልክም ፈገግታ እያሳዩ ያልፉ ጀመር ። ምኒልክ ከሠራዊቱ መሐል ሲደባለቁ መኳንንቱ ሁሉ ፈዝዞ ነበር ። ምኒልክም አይናቸውና ፊታቸው ላይ ያለውን አቧራ እየጠራረጉና እየሳቁ "ካፒቴን ፣ ካፒቴን ፣ ደግሞ መቼ ነው የምንሄደው? ነገ በስንት ሰዓት እንሂድ?" ብለው ሆለርን ጠየቁት ። ሆለርም "እርስዎን በሚያስደስትዎ ሰዓት መሄድ እንችላለን" አላቸው ። ምኒልክም "ጥሩ ነው ፤ እንግዲያው ነገ በአራት ሰዓት ይሁን" አሉት ። ቤንትሌይ ፈቃደኛነቱን ለመግለጽ እጅ ሲነሳ ሆለር ጠጋ አለውና "አራት ሰዓት ማለት ጧት አስር ሰዓት ነው እንጂ እንደኛ አራት ሰዓት አይምሰልህ" አለው ። ይህ ሰዓት የተመረጠበትም ዋናው ምክንያት ሁልጊዜ ጧት አራት ሰዓት የምኒልክ የእረፍት ሰዓት ስለሆነ ነው ።

ከሰዓት በኋላ ምኒልክ እንግዶቹ ካረፉበት ሆቴል ቤት ሄዱ ። ከዚያም ከሆቴል ቤቱ ለእንግዶቹ ሙሉ ግብዣ ጋበዟቸው ። ሄል እንደፃፈው ". . . . ምኒልክ እግራቸው ሥር የተኛውን የውሻቸውን ጆሮ እያሻሹ ብዙ ተጫወቱ . . . ." ይላል ። እንግሊዞቹም ልዩ ልዩ በቴክኒክ የሚፈፀም አስማት ሲያሳዩዋቸው ቆዩ ። ምኒልክም በጥበቡ ሲደነቁና ሲስቁ ከቆዩ በኋላ "ይሄን ጥበብ ለኔ ሳታስተምሩኝ አገራ ችሁ ይዛችሁት አትገቡም" አሏቸው ። እያንዳንዱ የቴክኒክ አስማት በሚታይበትም ጊዜ ምኒልክ እንባቸው እስቲወርድ ድረስ እየሳቁ "እስቲ ድገመውና አሳየኝ" ይሉ ነበር ። ከሆቴል ቤቱ ከሁለት ሰዓት በላይ ከእንግሊዞቹ ጋር ሲጫወቱ ቆይተው ለመሄድ ሲነሱ ፣ ለእንግ ዶቹ ለማዳ አንበሶች ሸለሙዋቸው ። ከዚያም የእንግዶቹን እጅ ጨብ ጠው በቅሏቸው ላይ ተቀምጠው ሊሄዱ ሲሉ "ጣይቱ ለማየት ጓጉ ታለችና ጧት እንዳትቀሩ" ብለው ሄዱ ።

በማግሥቱ በቀጠሮው ሰዓት ዌልስ አማርኛ ስለማያውቅ የሾፌ ርነቱን ቦታ ቤንትሌይ ያዘ ። ቤንትሌይ ከጐኑ ምኒልክን አስቀምጦ ሲንሸራሸሩ ቆይተው ተመለሱ ። በመልሱ ጉዞአቸው ላይ ምኒልክ "ትናንትም ዌልስ ሲያስኬዳት ዛሬም አንተ ስታስኬዳት እንዳየሁት ሥራው ጉልበት የማይጠይቅ ቀላል ሥራ ነውና እንድታስተምረኝ ። ሥራዋ እንዲያውም ለሽማግሌ የሚሆን ነው . . . ." አሉት ። ከቤተ መንግሥቱ ግቢ ሲገቡም የመኪናዋን መሪ ብቻ ይዘው ገቡ ። መሪዋን ይዘው መኪናዋ በመሄድዋም ምኒልክ በጣም ደስ አላቸው ።

ምኒልክ በጠየቁት መሠረት የመኪናዋን አነዳድ መማር ጀመሩ ። ቁልፍ መክፈት ፣ ሞተር ማስነሳት ፣ ፍሬን መያዝ ፣ ማርሽ መለወጥና የመሳሰሉትን ተራ በተራ ተማሩዋቸው ። ዘይት መለወጡንም አሳዩ

ዋቸው ። ይህ ሁሉ ሲሆን ከኢትዮጵያውያን መሀል ተጠግቶ ከምኒልክ ጋር የሚያጠና ሰው አልነበረም ። አንድ ቀን ምኒልክ እንግዶቹን ከአዳራሽ ጋብዘዋቸው ምግብ በልተው ከጨረሱ በኋላ ሲያወሩ "ሁሉን ነገር የኔ አገር ሰው ቢያውቅልኝ ደስ ይለኝ ነበር ። ግን አይ ሆንላቸውም ። በጅም አይሉም ። እንዲህ እንዲህ ያለ ነገር መሥራት የሚወድ አንድ ኤዳልጂ የሚባል ሕንድ አለ ። እሱ እንዲህ ያለ ነገር ስለሚወድ እኔንና እሱን በደንብ አድርጋችሁ አስተምሩን" አሉ ። ሁለቱም በደንብ ተማሩ ።

ምኒልክ የመንጃ ፈቃድ ሊቀበል የመጀመሪያውን ፈተና ሊፈ ተኑ ተዘጋጁ ። አጃቢ የሆነውን ፈረሰኛውንና ምስክሩን ሁሉ ወደፊት ቅደሙ ብለው አዘዙ ። ፈረሰኛው ሁሉ ጋልቦ ሲሔድላቸው ምኒልክ መንዳት ጀመሩ ። ለፈተናው ጊዜም ሁለት ሰዓት ሙሉ ነድተው ችሎ ታቸውን አሳዩ ። ግሩም የሆነ ሾፌር ወጣቸው ። ሄል በመጽሐፉ ፔርፈክት ድራይቨር ይላቸዋል ።

ሕንዳዊው ኤደልጂ የመጀመሪያዋን አውቶሞቢል መንዳት ተምሮ የምኒልክ ሾፌር ከሆነ በኋላ ፣ ለመኪናዋ ቴክኒካዊ ሥራና ለሾፌርነትም ጭምር ደግሞ ኢጣሊያዊው ሲኞር አልዋቲ ተመረጡ ። አልዋቲ ለመ ኪናዋ ሥራ ብቻ ሳይሆን በቤተ መንግሥቱ ግቢ አካባቢ ላለው ወፍ ጮና ለሌላውም የቤተ መንግሥቱ ቴክኒካዊ ሥራ ኃላፊ ነበሩ ። መኪ ናዋን ይዘው የመጡት ሰዎች መኪናዋን ይዘው ለመመለስ የፈለጉት በካርቱም በኩል ነበር ። ምኒልክ ግን ያመጧትን ሰዎች ሸልመው የመኪናዋን ዋጋ ከፍለው መኪናዋን አስቀርተው ሰዎቹን አሰናበቱ ።


ከመጀመሪያዋ መኪናም ተከታትሎ ጥር 15 ቀን ጀርመናዊው አርኖልድ ሆልዝ ሌላ ናኪ የተባለች መኪና ይዞ አዲስ አበባ ገባ ።



ምኒልክ ከእልፍኝ ወጥተው እውቶሞቢልዋን ተመለከቱ ።



አውቶሞቢላቸው ላይ ፤ ከዌልስ ጐን ተቀመጡ ።




ሞተሩ ተነስቶ ቤንዚን መስጫው ሲነካ መኪናዋ በመጮህዋ ሳቁ ። ከኋላ የተ
ቀመጡት በኢትዮጵያ የእንግሊዝና የመስኮብ ሚኒስትሮች ናቸው ።



የመጀመሪያ የአውቶሞቢል ጉዞአቸውን ጀመሩ።



ከውሻቸው ጋር ።



ከመጀመሪያዎቹ ባህር ዛፎች ።

## ባህር ዛፍ

አንዳንድ ሰዎች ሲያወሩ አዲስ አበባ ላይ በደረሰው የእንጨት ችግር ምክንያት የባህር ዛፍ ወደ ኢትዮጵያ ገባ ይላሉ ። በዘመኑ የደ ረሰው የእንጨት ችግር አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በመላው ኢት ዮጵያ ነበር ።

ባህር ዛፍ ወደ ኢትዮጵያ ሊገባ የቻለው አዲስ አበባ ላይ በደ ረሰው የእንጨት ማለቅ ምክንያት መሆኑም እውነት ነው ። በኢትዮ ጵያ ለእንጨት ማለቅ ምክንያት ከሆኑት አንዳንዶቹን ከታሪክ ፀሐ ፊዎች ብንጠቅስ ሀሪስ እንደፃፈው የቤት መዝጊያ በመጋዝ የሚሰነጠቅ

ስላልሆነ ካንድ ግንድ የሚፈለፈል በመሆኑና ቤቶች ሁሉ በምሰሶ የሚቆሙ በመሆናቸው ነው ይላል ።

ሉዊስ ላንዲ እ ኤ አ በ1870 ሪፖርት ላይ "....በሸዋ የነበረው ታላላቁ የወይራ ዛፍ ሁሉ አለቀ ። 10 ኪሎ ግራም ከሰል ለማክሰል 1000 ኪሎ ግራም እንጨት ይነዳል...." ብሏል ። ሮቢን እንደጻፈው ደግሞ "....በሐረር ዙሪያ ያሉ ሰዎች በዛፍ ሥር እሳት የማንደድ ባህል አላቸው ። ዛፉ እስቲወድቅ ድረስ በመደጋገም እሳት ያነዱበታል። በዚህ ዓይነት በእሳት ቃጠሎ የሚወድቀው ዛፍ ጉቶው ሁሉ ስለሚቃጠል እንደገና ሊያቆጠቁጥ እንኳ አይችልም ...." ብሏል ።

አማኑኤል ሬይ "....ዛፉን የጨረሰው መሬቱን ሁሉ ለኩብት ግጦሽ የማዋል ልምድ ስላላቸው መሬቱ ሳር እንዲያበቅል እያሉ ያቃጥሉታል ። በመሬቱ ላይ ቁጥቋጦ ብትኖርም አብራ ትቃጠላለች ። ባለፈው ጊዜ በቁሉቢ ያየሁት ደን አሁን ባዶ ሆንዋል...." ይላል ። ማሳይ እንደገፉት ለዛፍ ማለቅ ሌላው ምክንያት አውሬ ለማጥፋት እያሉ ደኑን ስለሚያቃጥሉት ነው ብለዋል ። እነዚህን በመሳሰሉ የተለያዩ ምክንያቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ዛፍ አለቀ ።

በዛፍ ማለቅ ምክንያት ምን ያህል ችግር ደርሶ እንደነበር ዲ አባዲ ሲጽፍ ፡ ".... በአምመራ አካባቢ ያለው ደን ጠፍቶ ቦታው ባንዳንድ ቁጥቋጦዎች ተሸፍኗል.... " ሲል ሌዥን ደግሞ ".... በአድዋ ሕዝቡ በግንድ እጦት ከባድ ችግር ደርሶበታል ...." ብሏል ።

ቴዎድሮስን ለመውጋት ከመጡት እንግሊዞች ጋር አብሮ የመጣው ማይደን "....አገሪቱ ዛፍ የለባትም ። በትግሬ ውስጥ ለቴሌግራፍ ሽቦ መዘርጊያ የሚሆን አንድ ግንድ አጥተን ከባድ ችግር ደረሰብን ። ኢንጂኔሮቻችንም የሚሠሩበት አጥተው ተቸግረው ነበር ። አዲግራት ስንደርስ የጦር መሪው ሰር ሮበርት ናፒር ስድስት ግንድ ላመጣ ሰው አንድ ጥሬ ብር እሰጣለሁ ብሎ ስላወጀ ፡ ሕዝቡ የሚያመጣው ግንድ ቢያጣ ቤቱን የሠራበትን ግንድ እየነቀለ አመጣ...." ሲል ጽፍዋል ።

ዌልዲ "....በሰሜን ሸዋ እንጨት የሚባል ነገር ስላልነበረ ምግባችንን የምናበስለው በኩበት ነበር...." ብሏል ። እንግዲህ ባጭሩ የጠቃቀስናቸው ታሪኮች በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ ደኑ እንዴት እንዳለቀና ምን ያህል ችግር ደርሶ እንደነበር ያስረዳሉ ።

ባህር ዛፍ እንዴት መጣ? አጤ ምኒልክ አማካሪያቸው የነበረውን ፈረንሣዊውን ሞንዶን ቪዳሌን ጠርተው "ዛፉ አለቀ ። እንኳን ለቤት መሥሪያ ለማገዶም የሚሆን ጠፋ ፡ ምን ይሻላል?" አሉት ። "አውስ

ትራሊያ ውስጥ ” አላቸው ሞንደን “እውስትራሊያ ውስጥ ኢካሊፕ ቶስ የሚባል አንድ የዛፍ ዘር አለ ። ያ ዛፍ ቶሎ የሚደርስ ነው ። ያዛፍ መጥቶ ቢተከል በአስር ዓመት ውስጥ አገሪቱ ጫካ ትሆናለች” አላ ቸው ። ምኒልክ በነገሩ ደስ አላቸው ። በዛፉ ታሪክ ቢደሰቱም ባንድ ሰው አሳብ ርምጃ አይወስዱም ነበርና ቸናስኪን አስጠርተው የዛፉ ነገር እንዴት ይሁን? አሉትና ሞንዶን ስለነገራቸው ዛፍ ታሪክ አጫ ወቱት ። ቸናስኪም በእርግጥ ጥሩ የዛፍ ዘር መሆኑን ነገራቸው ። “ይሁን እንዳላችሁት ይሆናል” ብለው ከሸኙት በኋላ ለባቡር ሀዲድ መንገድ ሥራ የመጣውን እንግሊዛዊውን ካፒቴን አብሬን አስጠሩትና እንደገና ስለ ዛፉ ጉዳይ ጠየቁት ። አብሬም ጥሩ ዛፍ መሆኑን አረጋገ ጠላቸው ። ከዚህ በኋላ ምኒልክ ሶስት የተለያዩ የውጭ አገር ሰዎች የመሰከሩለትን የዛፍ ዘር በ1886 ዓ ም እንዲመጣ አዘዙ ።

ችግኙ ተፈልቶ እንደደረሰ ስሙ የባህር ዛፍ ተባለ ። ከባህር ማዶ አገር የመጣ ለማለት ነው ። ምኒልክ ባህር ዛፍ የሚለውን ስም ከሰየሙ በኋላ “የባህር ዛፍ የተተከለበትን መሬት ግብሩን ምሬአለሁ” ብለው አወጁ ። ሕዝቡ በሽሚያ ይተክል ጀመር ። እንዲያውም ችግኙ ተወዶ 40 ችግኝ ባንድ ጥሬ ብር መሸጥ ጀመረ ። አተካከሉም በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በመላው ኢትዮጵያ ተስፋፋ ።

በአዲስ አበባ ከተማ የተተከሉት ዛፎች ደን ሲሆኑ ውሃ እየደረቀ ሄደ ። ጉድጓዶችም ፣ ምንጮችም ደረቁ ። ከራስ ሙኰንን ቤት ቢታች ያለችው ራስ መኰንን ምንጭ የምትባለዋ ብቻ ቀረች ። በአዲስ አበባ ላይ ከባድ የውሃ ችግር ደረሰ ። ይህን ችግር ያመጣው ባህር ዛፍ መሆኑ ስለታወቀ ባህር ዛፎች እንዲነቀሉ ታዘዘ ። ማንም ሰው ካለው ባህር ዛፍ ሩቡን እያስቀረ ሌላውን እንዲነቅል ተባለ ፣ ተነቀለ ።

ምኒልክም “ትከል ብለነው ተከለ ። አሁን ደግሞ ንቀል አል ነው ። ዛፍ ቀርቶ ልምጭ ከሚቸግርበት ሁኔታ ልንደርስ ነውና ምከ ሩበት” አሉ ። በምክሩ መሠረት ሌሎች የዛፍ ዘሮች ከውጭ እየመጡ ተተከሉ ። የባህር ዛፉም ጥናት አብሮ ቀጥሎ ነበርና ቶማስ ሆለር 1898 ዓ.ም. በፃፈው ሪፖርት “. . . .ከሕንድ ፣ ከሲይሎን ፣ ከእንግሊዝ አገርና ከሌሎችም አገሮች ኢካልፕቱስ (ባህር ዛፍ) እየመጣ እንደገና በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተተከሉ ። . . . . ጥሩው ዓይነት ተጠንቶም በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠር ተተከለ ። . . . .” ብኋል ። የመጀመሪያው ባሕር ዛፍ ውሃዎችን ካደረቀ በኋላ እንዲጠፉ ሲደረግ ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ከመጣው ዘጠኝ ዓይነት የባሕር ዛፍ ዘር ውስጥ ተመርጦ የተሻለው እንዲራባ ተደረገ ። ከዚህ በኋላም የባሕር ዛፍ ተክል ተስፋፋ ።

ባህር ዛፍ አዲስ አበባ መቼ ገብቶ መተከል እንደ ተጀመረ ዘመኑ በትክክል አይታወቅም ። እጤ ምኒልክ ዛፉ እንዲመጣላቸው ያዘዙት

በ1886 ዓ.ም. ነው ። በዚህ ዘመን ካዘዙ ፡ መቼ አዲስ አበባ ደርሶ በየ ትኛው ዘመን እንደተተከለ የሚያስረዳ አላገኘሁም ። ኬለር እንደ ፃፈው በ1891 ዓ.ም. ኢ.ልግ ብዙ ባህር ዛፎች ችግኞች መትከሉን ይገልፃል ። አቅራቢያ ግምት ለመስጠት ኢ.ልግ የምኒልክ ረዳት ስለ ነበረ ችግኙ እንደደረሰ እንደተከለው ስለሚታመን አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባህር ዛፍ መተከል የተጀመረው በ1891 ዓ.ም. በየካቲት ወር ነው ቢባል መልካም ሊሆን ይችል ይመስለኛል ።

ባህር ዛፍ ለምቶ ጥቂት እንደቆየ አንድ መቶ አጠና የሚሸጠው በአንድ ማርትሬዚያ ብር ነበር ። በምኒልክ የመጨረሻ ዘመን ገደማ እንደገና የባህር ዛፍ ተክል እንዲቀነስ የሚል አዋጅ በእርሻ ሚኒስቴር ወጣ ። አዋጁም የሚከተለው ነው ።

የኢትዮጵያ መንግሥት
የርሻና የመሥሪያ ሚኒስቴር

ማስታወቂያ

በመጀመሪያ ጃንሆይ ይህንን ያዲስ አበባን ከተማ ለመሥራት የቆረቆሩ ጊዜ መሬቱ ባዶ ምናምን ዛፍ የሌለበት ነበር ። ነገር ግን ለጊዜው እንዲያደምቅና እንዲያምር ፡ ላይን ማረፊያ እንዲሆን ተብሎ በቶሎ እሚያድግ ይህንን አካላብቶስ አስመጡ እንጂ ።

የጃንሆይ አሣብ ግን ለአገራችን ለሕዝቡ የሚጠቅም ፡ ፍሬው የሚበላ ፡ እንጨቱም ሥራ የሚይዝ ጥቅም ያለውን ሁሉ እያስመጡ ለማስተከል ነበረ ። ይህም ይታወቅ ዘንድ በያይነቱ አስመጥተው መፈተናቸው አልቀረም ። ከተፈተነውም ሁሉ አንድ ዓይነት አልጠ ፋም ። ሁሉም ጥንት ከተገኘበት ከሀገሩ የበለጠ እየሆነ በቀላል ለም ቷል እንጂ ።

ይህንንም በትልቁ ዓይነት ኮክ ። በቱት በሐሩ ዛፍ ። በጽጌረዳ ። በስፕሬ ተረዱት ። እነዚህን የመሰሉ ብዙ ዛፎችና ተክሎች አሉ ። እኛም ይህን ዓይነቱን ነው ጥቅም የሌለውን ዛፍ አሳንሰን ጥቅም ያለባቸውን እናብዛ ማለታችን ።

ቱትም የሚባለው የሐር ዛፍ ፍሬው ይበላል ። ቅጠሉም የሐር ትል ማርባት ለወደደ ሰው ዋና ነገር ነው ። ይህም ባይሆን ደግሞ ፡ ቅጠሉን ለላምና ለበሬ ፡ ለበግና ለፍየል ቢያበሉት እጅግ ያወፍራል ። ግንዱም በያመቱ ሲቆረጥ ለሥራ ይሆናል ። ብዙ ገንዘብ ያወጣል ። ቁመቱም በልክ ነው ።

እንደዚህ ያለውን ጥቅም ያለበትን ዛፍ ለማልማት ነው ልዑል አልጋ ወራሽም[1] ያሰቡት ። ይህ አካላብቶስ ግን የሚባለው አትክልትና መሬት ከማጥፋት በቀር ምንም ምን ጥቅም የለውም ። ባጠገቡ ምንጭ ያለ እንደሆነ ያደርቀዋል ። የጉድጓዱንም ውሃ ሁሉ ሥሩ እየሳበ እየጠጣ አደረቀው ። እንጨቱም ሥራ አይይዝ ፣ ፍሬውም አይበላ ። አሁንም በየቦታው አካላብቶስ ያለው ሁለት እጁን ይንቀል ። አንዱ እጅ ይቆይ ። በተነቀለው ፈንታ ጥቅም የሚገኝበትን የዛፍ ግልገል እንሰጣለን ።

መጋቢት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳ ዓመተ ምህረት አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ ።

በመንግሥት በኩል ይጥፋ ቢባልም በብዙ የሕዝብ ትግል ባህር ዛፍ እየለማ ሄደ ። ሕዝቡ ባህር ዛፍን የወደደበት ምክንያት ባለበት ከባድ የእንጨት ችግርና ቶሎ ደራሽ በመሆኑ ጭምር ነበር ። በተለይም ደግሞ ከተቆረጠ በኋላ እንደገና በማቆጥቆጡ ተወዳጅ ሆነ ።

## ቧንቧ ውሃ

አዲስ አበባ ከተማ ከተመሠረተችና የነዋሪዋ ብዛት እየጨመረ ከሄደ በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የውሃ እጥረት እያስቸገረ ሄደ ። ገንቦውን እየተሸከመ በየወንዙና በየምንጩ የሚንከራተተው በዛ ። በተለይ በሣምንት ሶስት ጊዜ ግብር የሚያበላው ቤተ መንግሥት ለጠላና ጠጅ መጥመቂያ ቀርቶ ለቡሆ ማቡኪያ በመቸገሩ ምንጮች እየተከለሉ ለቤተ መንግሥት ብቻ እንዲውሉ ተደረገ ። ይህም ቢሆን የምንጮቹም ሁኔታ እያደር እያነሰ በመሄዱ ለችግሩ ማቃለያ የሚሆን ዘዴ አልተገኘም ።

አጤ ምኒልክ የውጭ አገር አማካሪዎቻቸውን ሰብስበው "በእናንተ አገር የውሃ ነገር እንዴት ይሆናል?" አሏቸው ። በፈረንጅ አገር ውሃ እንዳይባክን ምንጮች እየተከለሉ ውሃው በቧንቧ እየተጠለፈ እንዴት አድርጎ ከቤት ድረስ እንደሚመጣ አስረዱዋቸው ። ያ ቧንቧ የተባለው ሥራ እንዲሠራ ዋና አማካሪያቸውንና መሐንዲሳቸውን ሙሴ ኢልግን አዘዙት ።

ኢልግ ፕላኑን አወጣ ። አሠራሩንም ለአጤ ምኒልክ አሳየ ። እዚህ ላይ ኬለር እንዲህ ይላል " . . . .ኢልግም በአካባቢው ካለ ተራራ ሥር

1 ልዑል አልጋ ወራሽ የሚለው ኢያሱን ነው ።

ከሚመነጨው ምንጭ ፡ ውሃ በቧንቧ ለማምጣት አሳብ አቀረበ ። በም ኒልክ ችሎት ያሉ ሰዎች አሳቡን ተቃወሙ ። የተቃወሙትም ውሃን ከተራራ ወደታች ማምጣት ይቻላል እንጂ ከታች ወደ ተራራ ማው ጣት አይቻልም ብለው ነው ። ምኒልክ ግን በኢልግ አሳብ ተስማም ተው እንደ ኢልግ አስተሳሰብና ፕላን ቧንቧዎች ተዘረጉ. . . .”

ምኒልክ ለቧንቧው መግዣ ሰባት ሺ ማርትሬዚያ ብር ሰጥተዋል። ይህ ሰባት ሺ ብር የጨረሰው ቧንቧ ፡ የመዘርጋት ሥራ በ1886 ዓ.ም. በጥር ወር አለቀ ። ከላይ ከኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ካለ ምንጭ የተጠለፈው ውሃ ከቤተ መንግሥቱ ካለው የመጨረሻ ቧንቧ አልደርስ አለ ። ቧንቧው ሲከፈትም ጠብ የምትል ውሃ ታጣች ። ውሃው የቀረበት ምክንያት ይፈለግ ጀመር ። ወደ ኬለር መጽሐፍ ብንመለስ “ . . . . ኢልግ እንደገና ሥራውን ይፈትሽ ጀመር ። በፍተሻ እንደተገ ኘው ውሃው ሊመጣ ያልቻለው ቧንቧው በጥቅ ፍሬ በመደፈኑ ሆኖ ተገኘ ። ጥቅ ፍሬው ተጠርጐ ከወጣ በኋላ ውሃው ከቤተ መንግሥቱ ደረሰ ። ሥራውም ተደነቀ . . . .” ይላል ።

ያ የቧንቧ ውሃ በ1886 ዓ.ም. ማለት አዲስ አበባ ከተማ በተመ ሠረተች በሰባተኛ ዓመት ከቤተ መንግሥቱ ደረሰ ። በዘመኑ የነበሩት ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ስለ ቧንቧው ሲገልጡ “ . . . .አደባባዩ ላይ ውሃ በመዘውር ገብቶ ይፈስ ነበር ። የውሃውም አመጣጥ እንዲህ ነው ። አጤ ምኒልክ መሐንዲሱን አዝዘው ከእንጦጦ ደጋ መሐንዲሱ በኖራ እያስገነባ ውሃውን በቦይ አመጣው ። አዲስ አበባም ከሚጻው ላይ በደረሰ ጊዜ ጉድጓድ በሰፊው ተቆፍሮ ውስጡ በኖራ ፡ ባሸዋ ፡ በከሰል እንዳይደፈርስ ሆኖ አምሮ ተበጀ ። ከዚያ ላይ ከፈረንጅ አገር በሰባት ሺ ብር ተገዝቶ የመጣ የውሃ መዘውር ተተከለበት ። መሐን ዲሱ መሬቱን በትክክሉ እያስቆፈረ ፡ ኖራውን እያስነጠፈ ፡ መዘውሩን እያቀጣጠለ ከቅጥሩ ውስጥ አደረሰው ። ከቅጥሩም በደረሰ ጊዜ በማለ ፊያ ወጥቤት መካከል እየፈሰሰ መጣ ። ደግሞ አዳራሹን ወደ ግራ እያ ደረገ አደባባዩ ገባ ።

“አደባባዩም በደረሰ ጊዜ እንደዚሁ ተቆፍሮ በኖራ ፡ በስሚንቶ ተበጅቶ ሥራውም እንደ ሳህን እንደመሶብ ወርቅ ያለ ነው ። በአራቱ መአዘን እንደ ምንጭ ይፈሳል ። ከታች የባህር መቋሚያ አለው ። ይኸ ውም ውሃ በእልፍኙ ደጃፍ ይፈሳል ። አትክልቱንም ያጠጣል ። ከእል ፍኙም ደጃፍ ላይ በኖራ ፡ በሲሚንቶ ተሠርቷል ። መቅጃው ፡ የሸማ ማጠቢያው ለየብቻ ነው ። ያጼ ምኒልክ ፡ የእቴጌ ጣይቱም ድርቦች፡ የባለሟሎቹም የልፍኝ አሽከሮችም ልብስ ማጠቢያ በልዩ ልዩ ተሠ ርቷል ። ይኸ ውሃ ከገባ ሸማ ለማጠብ ወደ ቀንዝ የወረደ ሰው የለም ።



የጂንጂ መቅበሪያውን ቦይ ምኒልክ ሲያስቆፍሩ ።

በልፍኙ ፡ በሰገነቱም ማህል ለማህል ይፈሳል ። በግብርም ጊዜ በአደ ባባዩ ይፈሳል ።

"ይህንኑም ውሃ ሁለቱ ይጠጡታል ። የሚጠጡትም እነዚህ ናቸው ። ካዳራሹ ሳይገባ ቀርቶ ፀሐይ የመታው ፡ እንድም አዳራሽ ገብቶ ጠጅና አረቂ የተኮሰው ከዚያ ወንዝ ሁሉም ይጠጣሉ ። ያንነም ውሃ የሚያየው ሰው ሁሉ ከሥጋው ከጠጁ ይልቅ ውሃውን ያደንቃሉ ። ከደረቅ መሬት ላይ ስለመገኘቱ ። ንጉሥ ንጉሥቱም ካዳራሽ ወደ እል ፍኝም ሲመለሱ ውሃውም በመዘውር ተመልሶ ወደ ታዘዘበት ይፈ ሳል . . . ." ሲሉ ጽፈዋል ።

በዘመኑም "እንዲህ ያለ ንጉሥ የንጉሥ ቂናጣ
ውሃ በመዘውር ሰገነት አወጣ
አሁን ከዚህ ወዲያ ምን ጥበብ ሊመጣ ።" ተብሎ ተገጠመ።

በቤተ መንግሥቱ የገባው የቧንቧ ውሃ ሁሉን አስደስቶ ዘዴው ከታወቀና ከተጠና በኋላ ፡ ይህ የቧንቧ ውሃ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እንዲዳረስ ምኒልክ የውሃ ቧንቧ አስገዙ ። የተገዛውም የውሃ ቧንቧ ከጂቡቲ ፡ ድሬዳዋ ድረስ በባቡር ከመጣ በኋላ በዘመኑ የባቡሩ መስመር አዲስ አበባ ስላልደረሰ ከድሬዳዋ አዲስ አበባ ድረስ በሰው ሸክም እንዲመጣ ምኒልክ አዘዙ ። ምኒልክ ትእዛዝ ከሰጡባቸው ከብ ዙዎቹ ደብዳቤዎች መሀል አራቱን ደብዳቤዎች ከዚህ ቀጥዬ አስገ ብቻቸዋለሁ ።

ይድረስ ከልጅ ግዛው

ከድሬዳዋ በልፍ የተነሣ የውሃ ቦምባ ብረት መጥቷል ። እታህ ሳስ አቦ ድረስ አንተ ከተማ አጠገብ እመንገድ ዳር ጠቅሎ ይሰብሰብ ብያለሁ ። ከወዲህም ይህንኑ የቦምባ ብረት ለማንሳት ደጃች ውቤንም ፡ ሌላም ሰው አዝዣለሁ ። ለታህሳስ ሚካኤል አንተ ዘንድ ይገባል ። እስከዚያ ድረስ የቦምባው ብረት ከታች እንደመጣልህ እየተቀበልክ ከመንገድ ዳር ከደህና ሥፍራ አቆይተህ የሚያነሳው ሰው ለታህሳስ ሚካኤል አንተ ዘንድ ሲገባ ፡ በየሹሙ በየሹሙ እገሌ ይህን ያህል ፡ እገሌ ይህን ያህል ያንሳ እያልክ በደብዳቤ እያደረግህ እንድትሰጥ ይሁን ። አንተም ያገርህን ሰው ወታደርም ቢሆን አንድ ሳይቀር በጢስ አዘህ የቻልከውን ያህል በብዙ አስነስተህ አንተው ራስህ እሲይዘህ መጥተህ ሎሜ ውስጥ ጠዬ ማርያም ድረስ እንድታመጣ ይሁን ። ከዚያ ወዲህ እኔ ሄጄ አስመጣለሁ ።

ኅዳር ፲፩ ቀን ፲፱፻ ዓመተ ምህረት አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ ።

ይድረስ ከፊታውራሪ አብተማርያም

ከታች ከድሬዳዋ የተነሣ የውሃ ማውጫ ቦምባ ብረት ባሩሲ በኩል ይምጣ ብያለሁና ይህንን ለማንሳት እነደጃች ውቤን ካዋሽ ማዶ ያለውን አገር ሁሉ አዝዣለሁና ምናልባት ከዚህ ቀደም የተበጀው መንገድ የተበላሸ እንዳለ ካዋሽ ጀምሮ ሎሚ ፣ ጠዴ ማርያም ድረስ ያለውን ያንተን ግዛት መንገድ የተበላሸ የተበላሸውን እንድታበጅ ይሁን ።

ሕዳር ፳ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ

ይድረስ ከደጃዝማች ውቤ

የውሃ ቦምባ ብረት ከድሬዳዋ ተነስቶ በጨርጨር በኩል መጥቷል ። ይህንኑ ብረት እግዛው ወልደ ገብርኤል አገር ተሰብስቦ ቆይቶ ካዋሽ ማዶ ያለው አገር ሁሉ አንስቶ ሎሚ ፣ ጠዴ ማርያም ድረስ ያምጣ ብዬ አዝዣለሁና አንተም ያገርህን ሰው በጢስ አዘህ እግዛው ወልደ ገብርኤል አገር ድረስ ለታህሣሥ ማርያም አንተው ራስህ ሰውህን ይዘህ ሄደህ የቦምባውን ብረት አስነስተህ ሎሚ ፣ ጠዴ ማርያም ድረስ እንዲመጣልኝ ይሁን ። ነገር ግን ብረቱ ብዙ ነው ። በመጀመሪያ ጨርሳችሁ ሳታነሱ የተረፋችሁ እንደሆነ ሁለተኛ ተመልሳችሁ የምታነሱ እናንተው ናችሁና ጠንክራችሁ አንድ ጊዜ እንዲነሳ ማድረግ ነው ። መንገዱም ከዚህ ቀደም የተበጀው ተበላሽቶ እንደሆነ ብረቱን ለሚሸከመው ሰው እንዳያስቸግር የተበላሸውን መንገድ ማስበጃጀት ነው ።

ኅዳር ፳፫ ቀን ፲፱፻ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

ይድረስ ለፊታውራሪ ሀብተማርያም

ከሐረርጌ የመጣ የውሃ ማውጫ ቦምባ ብረት ፣ ጉት እግዛው ወልደ ገብርኤል አገር ገብቷል ። ይህንኑ ለማንሳት ካዋሽ ማዶ ያለውን ሰው ሁሉ አዝዣለሁና አንተም ካዋሽ ወዲያ ማዶ ያለውን አገርህን ፣ ካዋሽ ወዲህ ማዶ ያለውንም አገርህን አንድ ሳይቀር በጢስ አዘህ በቅሎ ፣ ጌኛም ፣ አህያም ያለው ከብቱን እየያዘ አንተ ዘንድ ጠንካራ ሹም ጨምረህ ሰውን ጠቅሎ ይዞ ሄዶ ለታህሳስ ማርያም ፣ ጉት እግዛው ወልደ ገብርኤል አገር ገብቶ በከብትም ፣ በሰውም ሸክም አስነስቶ ሎሚ ፣ ጠዴ ማርያም ድረስ እንዲያመጣልኝ ይሁን ። ያንተ ሰው የሚያነሳውም የቦምባ ብረት ቁጥሩ ከወፍራሙ ዓይነት ሺ ብረት ።

ከቀጭኑ ዓይነት ሺ ብረት ነውና ይኸንን አንድ ጊዜ ጨርሶ እንዲ ያመጣ አድርግልኝ ። የዚህ የቦምባ ብረት ነገር የምቸኩልበት ብርቱ ጉዳይ ነውና ይኸንን ያዘዝሁህን ሁለቱን ሺ ብረት ቶሎ ሳታነሳ ቀር ተህ ወደ ኋላ የቀረብኝ እንደ ሆነ አይሆንም ።

ታህሣሥ ፮ ቀን ፲፱፻ ዓመተ ምህረት አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

ምኒልክ ያሠሩት የቧንቧ ውሃ እምብዛም ሳይስፋፋ የኢጣሊያ ፋሽስት ኢትዮጵያን እስኪያዘበት ዘመን ድረስ ቆየ ። በዚያን ዘመን የነበረው የቧንቧ ውሃ ላንዳንድ ምርጥ መኳንንቶች ቤቶች የገባ እንጂ አብዛኛው የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ ውሃ የሚቀዳው ከወንዝ ፣ ከም ንጭና ከጉድጓድ ነበር ።

## ሕክምና

ከአጤ ምኒልክ በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ የሕክምና ተግባር ተስፋፍቶ ነበር ባይባልም ተጀምሮ ነበር ። ዳግማዊ ምኒልክ በ1872 ዓ.ም. ከኢጣሊያ ያስመጧቸው ዶክተር ራጋዛ ፣ ዶክተር ትራቢርሲ ፣ ዶክተር ኒራዚኒ ፣ እና ዶክተር አልፊዮ ለሐረርጌና ለሸዋ ተደልድለ ዋል ። የሸዋዎቹም ሐኪሞች ልጥ ማረፊያ ከሚባለው አገር ላይ ነበሩ ።

በ1889 ዓ.ም. ዳግማዊ ምኒልክ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ አንድ ፋርማሲና ክሊኒክ አቋቁመው ነበር ። በአድዋው ጦርነት ምክንያት ከሩሲያ የቀይ መስቀል ማኅበር የተላኩት ሐኪሞች በጀኔራል ሻቪዶቭ መሪነት በሐምሌ ወር 1888 ዓ.ም. አዲስ አበባ ገቡ ። በዚህም የቀይ መስቀል ቡድን ውስጥ ሰባት ሐኪሞች ፣ 12 ነርሶችና አንድ ፋርማ ሲስት ነበሩበት ። እነዚህ የቀይ መስቀል ማኅበር የሕክምና ቡድኖች አዲስ አበባ ውስጥ ሥራቸውን የጀመሩት ካገራቸው ይዘው በመጡት ድንኳን ውስጥ ነበር ። ሐኪሞቹ ሥራ የጀመሩት ሐምሌ 19 ቀን ነው ።

ይህ የሩሲያ ቀይ መስቀል ማኅበር ሕክምና በሚሠራበት ጊዜ ምኒልክ በሥፍራው በመገኘት ያበረታቱ ነበር ። እሸቸሴፍ እንደጻፈው “. . . . ኦፕራሲዮን በምናደርግበት ጊዜ ምኒልክ በኦፕራሲዮን ክፍል መገኘት ይወዳሉ ። . . . .በዚያም ቆመው የኦፕራሲዮኑን ሥራ በሚመ ለከቱበት ጊዜ የበሽተኛውን እጅ ይይዛሉ ። በኋላም ኦፕራሲዮኑ አልቆ በሽተኛው እስቲነቃ ጠብቀው ሲነቃ እግዚአብሔር ይርዳህ ፣ እሱ ያድንህ ብለውት ይሄዳሉ ። . . . .” ብሏል ።

ምኒልክ እነኚህን ሐኪሞች አስጠርተው ለሕዝብ በሚሰጡትም ሆነ በሚሸጡት መድኃኒት ሁሉ ላይ መድኃኒቱ ለምን በሽታ እንደ ሚጠቅም በአማርኛ እየፃፉ በሚሸጥበት በየብልቃጡ እንዲለጥፉ አዘዟቸው ። የሚለጠፈውም የመድኃኒቱ ስም ብቻ ሳይሆን የመድኃኒቱ አጠቃቀም ወይም አደራረግ ጭምር ነበር ። አብዛኛዎቹም መግለጫ የተለጠፉባቸው መድኃኒቶች የጉንፋን ፣ የኮሶ ፣ የተቅማጥ ፣ የቂጢኝ ፣ መድኃኒቶች ብልቃጥ ላይ እንደነበሩ ደ ካስትሮ ገልጾታል ።

ከዚህም ሌላ ዳግማዊ ምኒልክ እነዚሁኑ የሩሲያ ቀይ መስቀል አባላትን አስጠርተው "…. በፈረንጅ አገር አለ እንደምትሉት ያለ ለአገሬ ሕዝብ ማስተማሪያ የሚሆን በስዕል እየሳላችሁ በአማርኛ እየፃፋችሁ አድርጉልኝ ….” አሏቸው ። በዚሁ ትእዛዝ መሠረት ከቀይ መስቀሉ ጋር ተጨማሪ ሆኖ የመጣው ፔትሮሹሴቭ የጤና ጥበቃ ማስተማሪያውን ድርሰት ጽፎ ከጨረሰ በኋላ ኢትዮጵያዊው አቶ በዛብህ ኤልያስ ተርጉመውት አንድ የሕክምና መጽሔት ወጣ ።

ይህ መጽሔት 22 ገጽ ያለው ሆኖ በአሥር ክፍሎች ተከፍሎ ስዕሎች ያሉበት ነበር ። በመጽሔቱ ውስጥ ካሉት ስዕሎች መሀል አንዱ የሰው አፅም ሲሆን ሌላዎቹ ግን ስለቁስል አስተሳሰርና ስለ ቁስለኛ አነሳስ ጉዳይ የሚያሳይ ወይም የሚያስተምሩ ነበሩ ። ስለጤና ጉዳይ የሚናገረው አንደኛው ክፍል ሞያሌን ማውጣትና ከወጣች በኋላ በእሳት ማቃጠል ፣ ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜም አካልን በሳሙናና በሙቅ ውሃ መታጠብ ፣ ሳሙና ባይኖር ልብስን በእንዶድ ማጠብ ፣ የተኙበትን አልጋ ማጽዳት ፣ አንድ ቁስል ቆስሎ መድኃ ኒት ሲደረግ ፣ ቁስሉ ባንድ ጊዜ ካልዳነ እየደጋገሙ እስቲድን ድረስ መድኃኒቱን ማድረግ እንደሚገባ ይመክራል ።

በሁለተኛው ክፍል የተፃፈው ስለ ዓይን ሕመም ነው ። ለዓይን ሕመም መምጫ ዋናው ነገር በአደፈ እጅ አይንን መንካት ስለሆነ በተለይ ጨብጥ የያዘው ሰው በሽታውን ነክቶ ፣ ዓይኑን ቢነካ ዓይን ስለሚመርዝ እንዲህ ዓይነቱ ነገር ሲያጋጥም በንጹህ መሀረብ ወይም እርጥብ ውሃ በነካው ንጹህ ጨርቅ ለአስራ አምስት ቀናት ያህል አይ ንን መጥረግ ነው ይላል ።

ሶስተኛው ክፍል ስለቅማልና መዥገ ይናገራል ። ቅማል የሚመ ጣው ጠጉርንና ልብስን ባለማጠብ ስለሆነ በየቀኑ መታጠብና በርኬ የተባለውን መድኃኒት መቀባት ጥሩ መሆኑን ይገልፃል ።

አራተኛው ክፍል ስለቁስል ይናገራል ። ቁስልን በንጹህ መያዝና ሁልጊዜ በንጹህ ውሃ እያጠቡ በንጹህ ጨርቅ ማሠርና ምንም ነገር

እንዳይነካው መጠባበቅ ፥ ዶፊር ጥሩ መድኃኒት ስለሆነ ቁስሉን እያጠዱ ዶፊር መነስነስ እንደሚገባ ይነግራል ። በተለይ ቁስሉ የሚደማ ከሆነ በወስሌ ሐር ወይም በነጭ ጠንካራ ክር መስፋት ይገባል ። ቁስሉ ከመሰፋቱ በፊት ግን የመስፊያው መርፌና ክር መቀቀል እንዳለበት ይመክራል ።

አምስተኛው ክፍል ስለ ኮሶ ጉዳይ ይናገራል ። ኮሶ የሚታየው ጥሬ ሥጋ በመብላት ፥ ቆሻሻ ውሃ በመጠጣት ነው ። ኮሶ መጠጣት ደግሞ መጥፎ ነገር ስለሆነ የተቀቀለ ሥጋ መብላትና የተፈላ ውሃ መጠጣት ጥሩ መሆኑን ይመክራል ።


ስድስተኛው ክፍል ስለሆድ ሕመም ይገልጣል ። ሆድ ሕመምን የሚያመጣው በርበሬ ስለሆነ አንድ ሰው የሆድ ሕመም ካለበት በርበሬ ቀንሶ ይብላ ። የፈላ ወተት ይጠጣ ። መሬት ከመተኛት ይልቅ አልጋ ላይ መተኛቱ ጥሩ መሆኑን ይናገራል ። አልጋ የማይገኝ ከሆነ ሆዱን ያመመው ሰው የተደለደለ ምንጣፍ አንጥፎ ቢተኛ ይበጃል ይላል ።

ሰባተኛው ክፍል ስለወባ ያስተምራል ። ወባ የያዘው ሰው የወባ መድኃኒት ኪኒን ስላለ ኪኒን እንዲውጥ ይመክራል ። አዋዋጡንም ሲያስረዳ ጧት ግማሽ ግራም ፥ ማታ ደግሞ ግማሽ ግራም ሆኖ ከምግብ በኋላ በውሃ መዋጥ እንደሚያስፈልግ ይመክራል ።




ስምንተኛው ክፍል ስለቂጥኝና ስለቂጥኝ ጠባይ የሚገልጽ ነው ። የቂጥኝን ጠባይ ይገልጽና አንድ ገላው የተሰነጠቀ ሰው ቂጥኝ ከያዘው ጋር ግንኙነት ቢያደርግ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ብቻ ሣይሆን ፥ በዚህም እንደሚጋባ ይገልጻል ። የቂጥኝ መድኃኒትም እን ጓኩም ገድራር ሪጂሪያ ኳሴኔሪ ነው ይላል ። ይህም በዘመኑ የነበረ መድሐኒት ነው ።

ስለመድኃኒቱ አጠቃቀም ሲያስረዳ ፥ ይህን መድኃኒት ከእግር ጀምሮ መቀባት ነው ፥ ይልና ወር ሙሉ እየደጋገሙ መቀባት እንደሚ ያስፈልግ ይገልጣል ። መድኃኒቱን ከተቀቡ በኋላ በየአምስት ቀን በሙቅ ውሃና በሳሙና ገላን መታጠብ ነው ይልና ለቁርጥማት ሕመሙ ደግሞ እንዲሆን ከመድኃኒቱ አንዳንድ ጉንጭ ጧት ማታ መጠጣት ነው ይላል ። ከዚህ ሌላ ሐኪም ቅባት ፥ ኪኒን ፥ ሌላም መድኃኒት ሊያዝ እንደሚችል ይናገራል ።

ዘጠነኛው ክፍል ስለስብራትና ውልቃት የሚናገር ነው ። "የት ከሻ ውልቃት ሲያጋጥም እጁን ወደላይ አድርገህ ትከሻውን ቁልቁል ግፋና ከደረቱ ጋር አጣብቀህ በጨርቅ ጥብቅ አድርገህ እሰረው ። ይህም እስራት ሶስት ወይም አራት ቀናት ይቆይ" ይላል ። ለጣት ውልቃትና ለስብራትም እንደዚሁ ይመክራል ።

፮፡  6. ፯፡  7.


ለዚህ፡ እጣት፡ ለጅ፡ ቍስሮ ሰላ፡ የጣት፡
እየተሳሰ ር፡ ማሳየት፡ ነው።

 8. ፡ ፰፡  9. ፲  10.

ለዚህ፡ ክንድና፡ እግሩ፡ ሲታሰ ር፡ ማሳየ
ት፡ ነው።

፲፩፡  11 ፲፪፡  . 12.

እራስና፡ ላይ፡ በቍስ፡ ለሚደረግ ተሰራ፡ ማሳያ፡
ነው፡

፲፫፡  13. ፲፬፡  14.

ይህ፡ የዥ፡ እስተዛሰ ር፡ በቍስለኛ፡ ነው።

ከመጽሐፉ እንደኛው ገፅ

አሥረኛው ክፍል ስለዉብጥ የሚናገር ክፍል ነው ። ዉብጥ የያዘው ብልት አሥራ አምስት ቀን ሙሉ ቢልዛሙም ኩፓኤፍ የተ ባለውን መድኃኒት ስድስት ጠብታ እያደረጉ ማጠብ ፣ ከዚህ በኋላ በመጨረሻ ካሉ ጂየርማን ጋኒሉም የተባለውን መድኃኒት መቀባት ነው ይልና የመጽሄቱ ሐተታ ያልቃል ። ይህ መጽሐት ዛሬ በሶቭየት ሕብረት ሌኒንግራድ ባለው ሳይንስ ሙዚየም ውስጥ ዘሩ ተቀምጧል ።

አዲስ አበባ የገባው የቀይ መስቀል ማኅበር የሕክምና ቡድን አሥር ኢትዮጵያውያኖችን ስለሕክምና ያስተምር ነበር ። ከነዚህም ከአሥሩ አምስቱ ወደ ሩስያ ሄደው እንዲማሩ ተደርጓል ። ወደ ሩሲያ ለሕክምና ትምህርት የሄዱትም ዳኜ ቸርነት ፣ ግዛው ጋሻው ፣ ወልደ መስቀልና ስሙ ወልደመስቀል የሚባሉት ናቸው ። የአንዱ ስም ግን ለጊዜው አልታወቀም ። እነኚህም ሰዎች ወደሩሲያ ሄደው በሳን ፒትስ በርግ ሚሊተሪ አካዳሚ ውስጥ ተምረው በ1893 ዓ ም ወደ ኢትዮ ጵያ ተመልሰዋል ።

ይህ የሕክምና ቡድን ዓመት ያህል ከሠራ በኋላ ወደ አገሩ እንዲመለስ ሲደረግ በምትካቸው ሶስት ዶክተሮች ፣ ሁለት የሐኪም ረዳቶችና አንድ ፋርማሲስት መጥተዋል ።

የሩሲያውያኖች በኢትዮጵያ መግባትና መንሰራፋት ያሳሰበው የፈረንሣይ መንግሥት በ1889 ዓ ም ዶክተር ሩሳው ፈረንሣዮችን እንዲያክሙ በሚል ሰበብ ወደ ኢትዮጵያ ላካቸው ። በቀጠለው ዓመት በዶክተር ውርዝ የሚመሩ ከፓሪስ የሕክምና ፋክልቲ የተውጣጡ ቡድኖች ፈንጣጣን ለመከተብ በሚል ሰበብ አዲስ አበባ ገቡ ። ስለ ፈንጣጣ አደገኛነትና ዓይን ማጥፋትም እያስተማሩ ሕዝቡ እንዲከተብ ይናገሩ ጀመር ።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክም የፈንጣጣውን ክትባት በፈረንሣዮቹ እጅ ከተከተቡ በኋላ አርባ መኳንንትም ተከተቡ ። ፈረንሣዮቹ በዳግ ማዊ አጤ ምኒልክ ዘንድ ታማኝ ሆነው ለመገኘትና ወዳጅነትን ለመ ፍጠር ብለው ፈንጣጣ ዳግመኛ በምትይዝበት ጊዜ ዓይን ታጠፋለች በማለት ምኒልክን ሰብከው ከተቡዋቸው ። ይህ አጭበርባሪ ውርዝ የተ ባለው ፈረንሳዊ ሐኪም ስለዚያን ጊዜው ሁኔታ ሲገልጽ “ . . . .በአም ስተኛው ቀን ወሬ ጠየቅሁ ። ምንም እንደሌለ ሰማሁ ። ምልክት ያሳያል ያልኩትም እንደሌለ ተነገረኝ ። በዚህ አነጋገር እኔን ደስ ይበለኝ እንጂ ሥራው ሁሉ ሀሰት ነበር ። . . . . እውነቱን ለመናገር ስለአቀማ መሙም ሆነ ስለአደራረጉ ምንም አልተማርኩም ። ግን በመላ ምት የተሠራው ሥራ ውጤቱ ጥሩ ሆነልኝ ። በምኒልክም አይን ተወደድሁ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የክትባቱን ሥራ እንድገፋበት ታዘዝኩ . . . .”

ብኋል ። ውርዝ የሚያውቀው የኩብት ሐኪምነት የደስታ ወይም የሹኬ በሽታ ክትባትን ነው ። ታላላቅ መንግሥታት በሚያደርጉት የፖለቲካ ሽሚያ ፣ በታናናሽ አገሮች ላይ ምን ያህል በደል እንደሚፈጽሙ ይህ አንዱ ማስረጃ ነው ።

ይኸው የፈንጣጣ በሽታ ጉዳይ ምኒልክን ስላሳሰባቸው ሚያዝያ 24 ቀን 1890 ዓ.ም. አዋጅ አናገሩ ። አዋጁም "....በዚህ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የፈንጣጣን በሽታ የሚያጠፋ ስለተገኘ ፣ ማንኛ ውም ሰው ለጊዮርጊስ ዋዜማ ዕለት ዶክተር ውርዝ ቤት እየሄደ እንዲታከም ። ፈንጣጣው ይዟችሁ ከሆነ ግን አትሂዱ" የሚል ነበር ። ስለዚህ ጉዳይ ውርዝ እንደጻፈው "....ይህ አዋጅ በገበያ ቦታ ተነበበ ። አዋጁ በተነበበ ማግሥትም መቶ የሚሆኑ ወንዶች ፣ ሴቶች ፣ ልጆች ሁሉ ሊከተቡ ወጡ ።.... ሰውም ስለበዛ በራፌ ላይ ዘብ አቆምሁ ። .... የሶስት ፣ የአራት ፣ የአምስትና የስድስት ቀናት ጉዞ እየተጓዙ ከሠፈራቸው አዲስ አበባ ድረስ ይመጡ ጀመር ። ተራ ደርሷቸው እስኪከተቡም በቤቴ አካባቢ ሠፈር አርገው ይከርማሉ ።.... ከየካቲት ወር እስከ ነሐሴ ድረስም 20,700 ሰዎች አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከተብን ። ከዚህ በኋላ በዝናቡ ምክንያት ክትባቱን አቆምን ።...." ብኋል ።

በ1893 ዓ.ም. ኢጣሊያኖች አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባለው ሌጋሲዮናቸው አንድ ክሊኒክ ከፈቱ ። የክሊኒኩም ኃላፊ ዶክተር በሪ የሌ ይባል ነበር ። ከመስከረም ወር 1894 ዓ ም. ጀምሮ እስከ ሚያዝያ ወር 1903 ዓ.ም. ድረስ 59,695 ሰዎች አክመው 6000 ሰዎችን የፈን ጣጣ ክትባት ከተቡ ። ይኸ የክትባት ነገር እያሳሰበ ስለሄደና ውጤ ቱም መልካም ስለሆነ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ እንኮበር የነበረውን የልጅ ልጃቸውን ኢያሱን ዶክተር ደ ካስትሮ በ1893 ዓ.ም. እንዲከ ትበው አደረጉ ።

ሶስት መንግሥታት ማለት ሩሲያ ፣ ፈረንሣይና ኢጣሊያ በሕክ ምና ሰበብ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሕዝቡና ከንጉሡ ወዳጅነት ሲፈጥሩ ትመለከት የነበረችው እንግሊዝ ፣ ሌሎች እንዳደረጉት ሁሉ ዶክተር ዊክማን የሚባሉትን ሰው በሌጋሲዮንዋ ውስጥ የሕክምና ኃላፊ አድርጋ ሾመች ። እንግሊዞች እንደሌሎቹ መንግሥታት ሐኪሞች በፈንጣጣ በሽታ ክትባት ሠረታ አልገቡም ። የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚ ያጠቃውን ሌላ በሽታ ፈልገው ኮሶ መሆኑን ሲያውቁ በዚያ ገቡ ። ዊክማን እንደገለፀው ባመት ለአምስት ሺ ሰዎች የኮሶ መድኃኒት ይሰጡ ነበር ። የሁሉም ሕክምና የፖለቲካ ሰበብ ስለነበረው መድኃ ኒት የሚሰጠው በነፃ ነበር ።

ደቻሰን ፈረን የተባለ የሕክምና ቡድን ገባ ። ይህም ቡድን ከ1893 ዓ.ም. እስከ 1895 ዓ.ም. ድረስ በዶክተር ጉፈን እየተመራ ብዙ ሰዎችን አከመ ። ከእነኚህም ከታከሙት ሰዎች መሀል አንዷ ኛይቱ የእቴጌ ጣይቱ እናት ወይዘሮ የውብዳር ናቸው ።

እንዲህ የመሳሰለው ጉዳይ ከተካሄደ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች ሁሉ ሐኪሞች ነን ይሉ ጀመር ። ከእነ ኚህም አንዱ ባላምባራስ ጊዮርጊስ ናቸው ። ባላምባራስ ጊዮርጊስ አዲስ አበባ የኖሩ ግሪካዊ ሲሆኑ ሐኪምነትንም ፣ ፋርማሲስትነትንም ደርበው ያዙ ። በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሱቅ ያላቸው ፈረንጣዮችና ሕንዶች ሁሉ ሱቃቸውን የተለያዩ መድኃኒቶች መሸጫ ቤት አደረ ጉት ። በብዛት በአረቦች ሱቅ የሚገኘው ደግሞ ግሪ ሜርኩሪ ሶልፌት የሚባለው መድኃኒት ነበር ። ይህም ለቂጥኝ በሽታ ፍቱን መድኃኒት ስለነበረ ነው ።

ይህን በመሳሰለው ብጥብጥ መሀል የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሀኪም ፣ ዶክተር ወርቅነህ ሥራ ጀመሩ ። ዶክተር ወርቅነህ የእንግ ሊዝ ጦር መቅደላ ላይ ቴዎድሮስን አሸንፎ አንዳንድ ኢትዮጵያውያንን ወዳገሩ ሲወስድ የተወሰዱ ሰው ናቸው ። ከመቅደላ ሲወሰዱ ቸው የሶስት ዓመት ልጅ ነበሩ ። ከዚያም ወደ ሕንድ ተወስደው ቻርልስ ቻምበሊ ንና ኮሎኔል ማርቲን እየረዱ አስተማሩዋቸው ። ስማቸውም በመጀመሪያ ወሳጆቻቸው አንዳንድ ስም ቻርልስ ማርቲን ተብለው ነበር ። ዶክተር ወርቅነህ ላሆር ሜዳካል ኮሌጅ ገብተው ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በ1874 ዓ.ም. ተመረቁ ። ከዚያም ሕንድ አገር ላለው የእንግሊዝ የሕክምና ሥራ ረዳት ቀዳጅ ተብለው ተሾሙ ። ትምህርታቸውን ለመ ቀጠል ወደ እስኮትላንድ ሄደው በ1882 ዓ. ም. ተመርቀው ወጡ ።

ወርቅነህ ትምህርታቸውን ከፈፀሙ በኋላ ወደ በርማ ሄዱ ። እዚያም ዲስትሪክት ሜዲካል ኦፊሰር ኤንድ ሲቪል ሰርጀን ተብለው ተሾሙ ። ወርቅነህ ምንም ይሁን ምን ትውልድ አገራቸውን ኢትዮጵ ያን አልረሱም ። በ1888 ዓ. ም. ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር መነሳቷን ሰሙ ። ወዲያውኑ ተነስተው ጉዞአቸውን ወደ አዲስ አበባ ጀመሩ ። አዲስ አበባም እንደደረሱ ከምኒልክ ዘንድ ቀርበው አማርኛ አያውቁም ነበርና በአስተርጓሚ ተነጋገሩ ። ሐኪም ወርቅነህ አዲስ አበባ ውስጥ ከመሀል ከተማ ድንኳናቸውን ተክለው ሕዝቡን በነፃ ያክሙ ጀመር ። ወርቅነህ ይሰቃዩ ጀመር ። ፈረንጣዮችና ሩሲያኖች ከባድ ተቃውሞ አነሱባቸው ። የእንግሊዝ ሰላይ ነው እያሉም ያስወ ሩባቸው ጀመር ።

## ሆስፒታል

የሆስፒታል ሥራ የተጀመረው መጋቢት 7 ቀን 1890 ዓ. ም. ነው ። በመጀመሪያው ዓመትም ዛሬ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ከሚ ባለው ውስጥ 8,378 ሕመምተኞች ታክመዋል ። ከነዚህ ውስጥ 153 ሰዎች ኦፕራሲዮን ተደርገዋል ። 3,602 ሰዎች ከሆስፒታሉ መድኃኒት ተቀብለዋል ። በ1891 ዓ. ም. ደግሞ 12,009 ሰዎች ታክመዋል ። ይህም የወታደሮችን ሕክምና ሳይጨምር ነው ። ከዶክተሮቹ አንዱ ዶክተር ብሮብጺን ለወታደር ሕክምና ተደልድለው ስለነበር ከጥቅምት ወር 1891 ዓ. ም. ጀምረው እስከ መጋቢት ወር ድረስ 11,653 ወታደ ሮችን አክመዋል ። ከዚህ ውስጥም 45 ከፍተኛና 134 አነስተኛ ኦፕራ ሲዮኖች አድርገዋል ።

በ1890 ዓ. ም. የተጀመረው የሆስፒታሉ ሥራ በ1891 ዓ. ም. በሐምሌ ወር የውጭ በሽተኞች መቀበያ ክሊኒክና የኦፕራሲዮን ክፍሉ ሥራ ተጠናቀቀ ። በ1896 ዓ. ም. የፋርማሲውና የመጋዘኑ ሥራ አለቀ ።

በሩሲያውያን ቀይ መስቀል ማኅበር ተቋቁሞ ሥራ የጀመረው ሐኪም ቤት ለአሥር ዓመታት ያህል ካገለገለ በኋላ በ1898 ዓ. ም. ተዘጋ ። የተዘጋበትም ምክንያት ሐኪም ቤቱ ገንዘብ እያስከፈለ ያክም ስለነበረ ካገኘው ገቢ ቀረጥ እንዲከፍል ስለተጠየቀ ነው ። ማዳም ዳበርት እንደፃፉት “ . . . . በአዲስ አበባ ከተማ ያለው የሩሲያ አምባ ሳደር ጀኔራል ሊሽን ወደ መንግሥቱ ከተማ ወደ ሳን ፔተርስበርግ ስድስት ሺ ሩብል ቀረጥ እንዲከፍል መጠየቁን በቴሌግራም አስታወቀ ። ካገሩ መንግሥትም ሆስፒታሉን ዝጋ እንጂ እንዳትከፍል የሚል መልስ ስለደረሰው ሆስፒታሉ ተዘጋ . . . . ” ብለዋል ።

ምንም እንኳን በሐረር አንድ መጠነኛ ሆስፒታል ቢኖርም አዲስ አበባ ግን የቀበናው ሆስፒታል ከተዘጋ በኋላ ያለ ሆስፒታል ቀረች ። ይህን ሁኔታ የተመለከቱት ዳግማዊ አጤ ምኒልክም ሆስፒታል ለማ ቋቋም የሚያስችላቸውን እርዳታ ጠየቁ ።

ይድረስ ከክቡሩ ታላቁ ወዳጃችን ዳግማዊ ኒኮላዎስ ቄሣር ።
የመስኮብ ንጉሠ ነገሥት

ሰላም ለእርስዎ ይሁን ። ክቡር ወዳጃችን ሆይ ።

. . . .በኀዘናችሁና በርህራሄያችሁ ብዛት ስለኛ ስለወዳጆቻችሁ ርዳታ መድኃኒቱን ጭምር ያመጡልን ሐኪሞች ሐሳብዎን አይተው መልካም አድርገው ረድተውን ነበረ ። ነገር ግን ጊዜያቸውን አድር

ሰው ወደ አገራቸው ተመልሰው ከሔዱ በኋላ ሰዎችን መድሐኒቱን ለምዶ ሕመምተኛው ሲበዛ ሐኪም የሚያንስን ቢሆን ወደእርስዎ ለማ ስታወቅ የጻፍንሎትን ወረቀት ማቆየታችን ከዚያም ነገሩ እስቲረጋጋ ለመንግሥትዎም ሰላምና ጤና እረፍት እንዲሰጥልን ብለን እግዚአብ ሔርን ስንለምን ቆየን ።

ደግሞም እስካሁን አንዱ ሐኪም ሲረዳን ቆየ ። አሁን ደግሞ ያለው አንዱ ሐኪም ወደ አገሩ ተመልሶ ሔደ ። እንኳን ይህ ታላቁ ጉዳይ ትንሹም ጉዳይ ቢሆን የተለመደ ሲቀር እጅግ አድርጐ ያሳዝ ናል ። እኛም እርስዎን በመታመናችን እርዳታዎና ምክር አይቀርብ ንም ስንል ተስፋ አለን ። አሁንም ምክርዎንና ገንዘብዎን ሳይነፍጉን ከተጀመረ እስካሁን ድረስ በእርስዎ እርዳታ ብዙ ሰው ተፈወሰልን ። የሩሲያም መንግሥት እስካሁን ለኛ ብሎ ብዙ መድከሙን አውቀን በልባችን አልተውነውም ።

ደግሞም ሐኪሞች ወደዚህ ሊመጡልን የማይመች የሆን እንደ ሆን ሁልጊዜ እርስዎን ከማሳሰብ የመንግሥት የመድኃኒት ቤት ጐስቢ ታል ለማበጀት የመድኃኒቱንም መሣሪያና የጐስቢታሉን አደራረግ ምክሩን አይነፍጉንም ስንል ተስፋ አለን ። አሁንም ቢሆን ከእርስዎ እንዳይቀርብን እናውቃለን ። ነገር ግን በሐኪሞቹ መቅረት ለኛ ረዳት ብለው የላኩልንን መድኃኒት እዚህ ያሉት መልክተኞችዎ ወደ ሥፍ ራቸው ቢወስዱት በእውነት ሰዎችም በነገሩ አዘኑበት ። እኛም ለእርስዎ በውነት በንጹህ ልብ ወዳጃችን ለሆኑ ይህን ሁሉ ለማስታወስ ጻፍን ልዎ ። ቢመችዎ እንደቀድሞ ቸርነትዎ ይፈፅሙልኛል ።

ደግሞም በአገራችን ብዙ ሐኪም እያለ በከተማችሁ ከትልቁ እስከ ትንሹ አንዳንድ የመንግሥት ጐስቢታል ይቆማል ሲባል እን ሰማለን ። እኛም የምናፈቅረውና የምናምነው የእናንተን ረዳትነት ነውና ይህንን የጻፍንሎን ቃል እንዲቀበሉን ተስፋ አለን ። ደግሞም ከሁሉም ነገር እምነት ይበልጣል ። ለኛም ለኢትዮጵያ ወገናችን ያለሩ ሲያ መንግሥት ይህን ያህል ውለታ ርዳታና ቸርነት የዋለልን የለም። ከተጀመረ እስካሁን ያደረጉልን ሁሉ ለእርስዎ ትንሽ ቢሆን ለኛ እስከ ልጅ ልጅ የሚያልፍ ምሥጋናና ውለታችን ነው ። ይሄውም ወደ ፊት እንዲሆንልን ብለን የምናስታውቅዎ ጉዳያችን እንደዚሁ እስከ ልጅ ልጃችን ለብዙ ጊዜ መታሰቢያ የሚሆን ነው ። አሁንም ቢሆን ለኢትዮጵያ መንግሥት ያለ እናንተ ሌላ ረዳት የለንም ብለን ለዚህ ለጐስቢታል እርዳታ የሚያስፈልገንን ማስታወቃችን ነው ። ይህንንም ጐስቢታል ለማቆም በኛ አገር የሚገኘውን ብረት እንጨት ፡ ድንጋይም የሰውም ጉልበት ቢሆን አይቸግረንም ። የሚቸግረን ግን የጐስቢታሉ

ቤት ራሱን እስኪችል ጐስቢታል የሚያስፈልገውን መሣሪያና መድ ኃኒት ነው ። ደግሞ ፈቃድዎ ቢሆን ቀድሞ መጥተው ከተመለሱት ሐኪሞች ጋራ መድኃኒት ሊቀምም መጥቶ የነበረው ፈርምቢፍት ሊኪያኖፍ የሚባል ሁለት ረዳቶች ጨምሮ ቢመጣልን እንወዳለን ።

ይህንንም ማለታችን እዚህ መጥቶ ሳለ ቋንቋችንን ጥቂት ለምዶ ባህሪውም ከሰዎች ተስማምቶልን በመልካም ረድቶን ነበርና ስለዚህ ነው ። ይልቁንም እሱ ይምጣልን ማለታችን በእናንተ በወዳጆቻችን እርዳታ ለመሥራት ባሰብነው ጐስቢታል የሚያስፈልገውን መሣሪያና መድኃኒት የእርስዎ ፈቃድዎ ሆኖ ከተጠየቀ ፤ ባየበት ሁሉ እሱ ያመለ ክታል ብለን ነው ። እሱም የጐስቢታሉን መሥሪያና የመድኃኒቱን አደራረግ ለኛ ሰዎች ካስለመደልን በኋላ ተመልሶ ይሄዳል ። . . . .

የካቲት ፳፱ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም. አዲስ አበባ

ምኒልክ ይህን የእርዳታ ጥያቄ ካቀረቡ በኋላ እርዳታ ማግኘት ያለማግኘታቸውን አላወቅሁም ። ስለሆስፒታሉ መከፈት ዶክተር መረብ እንደጻፈው “ . . . .ሩሲያውያኖቹ ዘግተውት የሔዱት ሆስፒ ታል እንደገና በመንግሥት ወጪ በሚገባ ተሠርቶ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ተባለ ። . . . . ” በማለት ሆስፒታሉ በ፲፱፻፩ ዓ/ም መከፈ ቱን ይገልጻል ። የዚህ ሆስፒታል የመጀመሪያው ሐኪምም ዶክተር ቪታሊን ነበሩ ። እንደ መረብ አጻጻፍ “....ሆስፒታሉ ዘመናዊ የሆኑ ነርሶች ያሉበት ነበር ። በየቀኑም እስከ አስር በሽተኞች ድረስ ያክ ማል ። መድኃኒትም የሚሰጠው በነፃ ነበር ።....”

## የመድኃኒት መሸጫ ሱቆች (ፋርማሲ)

በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያው የመድኃኒት መሸጫ ሱቅ (ፋርማሲ) ሕዳር 22 ቀን 1904 ዓ.ም. ተከፈተ ። ስሙም ፋርማሲያ ላ ጆርጂያ ነበር ። ይህን ፋርማሲ የከፈተው ዶክተር መረብ ነው ። ስሙ ንም የሰየመው በእናት አገሩ በሶቭየት በጆርጂያ ስም ነበር ። ፋርማ ሲው የተከፈተው ራስ መኰንን ጉዳና ላይ ሲሆን ቤቱ ያለበትን መሬት የተከራየው ገራሲሞስ ከሚባል ግሪካዊ ነበር ።

በዳግማዊ አጤ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የተለየ ጤና ጥበቃ ሚኒስ ቴር ባይኖርም ሚኒስቴሮችን ለማቋቋም በወጣው የአገር አገዛዝ ሚኒ ስቴር ደንብ ውስጥ በ፮ኛው አንቀጽ “. . . .ከጤና ሚኒስቴር ጋር ተስማምተው የሰው ጤና ይጠብቃሉ” ይላል ። በዘየ ዘመን የጤና

ሚኒስቴር ደንቡ ይውጣለት እንጂ የተለየ ሚኒስትር አልተሾመለትም ነበር ። ቦታውን ግን ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ በተደራቢነት ይዘው ይመሩት ነበር ። ለማስረጃ ያህልም በ1904 ዓ.ም. የወጣው የፈንጣጣ ክትባት አዋጅ እንዲህ ይላል ።

ምክር

አሁን በከተማው ፈንጣጣ ገብታ ሰውን ሁሉ እንደምትፈጅ ታያ ላችሁ ። ይኸችንም ክፉ በሽታ ካገር ለማጥፋት በከተማ ያለው ሰው አዋቂውም ልጁም ከከብት ሐኪም ዘንድ ወይም ከሆስፒታል እየሄደ ይከተብ ።

ለመከተቡም ዋጋ አያስፈልግም ። ጊዜም አያስፈታ ። ካምስት ደቂቃም ይበልጥ አያቆይ ። አሁንም ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ የምታ ስቡ ሰዎች ሁሉ ። ሳታስከትቡ ቀርታችሁ ሰው ቢሞትባችሁ በስንፍ ናችሁ መሆኑን እወቁት ።

መጋቢት ፱ ቀን ፲፱፻፬ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ።

ነጋድራስና ኃይለ ጊዮርጊስ

የንግድን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ።

በ1905 ዓ.ም. ደግሞ የዚህ የጤና ሚኒስቴር ሥራ ለርሻና መሥ ሪያ ሚኒስቴር የተሰጠ ይመስላል ። በዘመኑ የርሻና የመሥሪያ ሚኒስ ትር የነበሩት ስለፈንጣጣ ቀጥሎ ያለውን አውጀዋል ።

የኢትዮጵያ መንግሥት
የርሻና የመሥሪያ ሚኒስቴር

ስለፈንጣጣ ምክር ።

ፈንጣጣ ለሚከተብ ሰው ሁሉ ጉለሌ በከብት ሐኪሞች ዘንድ አዲስ መድኃኒት አለ ብለን ከዚህ ቀደም አስታውቀን ነበረ ። ነገር ግን ሰው ሁሉ ማስከተቡን እየተወ ዛሬ በየስፍራው ፈንጣጣ ገብቶ ብዙ ሰዎች ሞቱ ።

አሁንም ፈንጣጣ ያልወጣለት ሰው ሁሉ ወደ ከብት ሐኪሞች እየሄደ ይከተብ ። አስቀድሞ በወረራ ካልያዘው ይከላከልለታል ። በወረራ ከያዘው በኋላ ግን ቢከተብም አይከላከልለትም ። ስለዚህ በጕረቤትና በቤቱ ሳይገባ በቶሎ መከተብ ነው ። ደግሞ በድንገት በጕረቤትና

በቤት ገብቶ አንድ ሰው ቢታመም የቀሩትን ሰዎች ሳይወራቸው በቶሎ እየወሰዱ ማስከተብ ነው ።

ተከትቦም ፈንጣጣው በወጣ ጊዜ እንደ ሀገራችን ፈንጣጣ አካል ያጐድላል ። መልክ ያበላሻል ተብሎ አይጠረጠርም ። ጥላም የለውም። ይህን ብሉ ይህን አትብሉ አይባልም ። ስራም አያስፈታ ።

ሕፃናት በተወለዱ በሁለት ወር ሊከተቡ ይችላሉ ። ይህም እስከ አሥራ አምስት ዓመት ይጠብቃቸዋል ። ደግሞ ባሥራ አምስት ዓመ ታቸው ሁለተኛ ተከትበው እስከ እድሜ ልካቸው ይበቃቸዋል ።

አገራቸው ሩቅ የሆነ ሰዎች እየመጡ መድኃኒቱን እየገዙ ይው ሰዱ ። አከታተቡንም ሐኪሞቹ ያሳያሉ ። የመድኃኒቱ ዋጋ ላንድ ሰው ሁለት ተሙን ነው ። የሚከትቡትም ከእሁድ በቀር ዘወትር ከጧት እስከ አምስት ሰዓት ነው ።

ይህን ምክር ካስታወቅናችሁ በኋላ ሳታስከትቡ ብትቀሩ ፈንጣ ጣ መጥቶ ልጆቻችሁን በገደለባችሁ ጊዜ ትልቅ ጠጠት ይሆንባችኋል ።

፲፱፻፰ ፡ ታህሳስ ፫ አዲስ አበባ ።

ፈንጣጣ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው ከኢትዮጵያ መሆኑን ያውቃሉ?

ምኒልክ ስለ ሕክምናና ጤና ጥበቃ የተሻለ አስተያየት ነበራ ቸው ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉድጓድ ቆፍሮ ሽንት ቤት ማዘጋጀት ባለ መደበት ዘመን ምኒልክ ማንኛውም ሰው የሽንት ቤት ጉድጓድ እየ ቆፈረ እንዲፀዳዳ በ1898 ዓ ም ጥቅምት 25 ቀን በአዋጅ አስጠንቅ ቀዋል ። የአዋጁም መጨረሻ አረፍተ ነገር "....ሳትቆፍር እዳሪ ተቀምጠህ ክፉ በሽታ የተገኘብህ መቀጫህን ለደሞዝተኛ አደርገዋ ለሁ" የሚል ነበር ። ለደሞዘተኛ የሚለው ቃል በዘመኑ የተቋቋሙ ጤና ተቆጣጣሪ ዘበኞች ስለነበሩ መቀጫው ለነሱ ደሞዝ ይሆናል ማለታቸው ነው ።

ምኒልክ ስለሕክምና ምንም በማያውቁ መኳንንቶቻቸው ዘንድ እሳቸው እንደ አዋቂ ሐኪም ሆነው ይታሰቡ ነበር ። ራሳቸውም ቢሆኑ በሐኪሞች ላይ ታላቅ እምነትና አድናቆት የነበራቸው ሰው ነበሩ ። ለማንኛውም ሕመም ሆነ አደጋ "ሐኪም ጥሩ" የሚሉ ነበሩ ። ጥቂት ደብዳቤዎቻቸውን እንመልከት ።

ይድረስ ከቢትወደድ ኢልግ

የራስ ሚካኤል አሽከር በቀደም ከደጋ ማንድ ስናነሳ ሳንቃ ከሆዱ ላይ ወድቆበት በብርቱ ታሞ ሊሞት ነው ። አሁንም የኢጣሊያ ሐኪም

መጥቶ ሁለት ሶስት ቀን አይቶት ቢመለስ እወዳለሁና ነገ ነግረኸው መጥቶ እንዲያየው ይሁን ።

ሚያዝያ ፪ ቀን አዲስ ዓለም ከተማ ተጻፈ በ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ይድረስ ከማጀር ቺኮዲኮላ

ዘለቀን ወደ አዲስ ዓለም ልኬው ሲሔድ ከከብት ወድቆ ታሟል ። ወዳንተ እንዳይመጣ የማይችል ሆን አሉ ። የተኛበትም አዲስ ዓለም ከኔ ቤት ጓዳ ነው ። አሁንም ሐኪሙ እየሔደ እንዲያየው ይሁን ።

ጥቅምት ፱ ቀን ገነት ከተማ ተጻፈ በ፲፰፻፺፰ ዓ.ም.

ይድረስ ከደጃዝማች ሉልሰገድ

የበሽታህን ነገር በጉ ነኝ ብለህ ብትልክብኝ ደስ አለኝ ።. . . . ንዳድ ለታመመ ሰው ከሆዱ የማስወጣበት መድኃኒት ያልከውን ለዚ ህማ መድኃኒቱ ኪኒን ነው ። ዛሬ እኛ ዘንድ ኪኒን አይገኝልህም ። የሚገኝ ወደ ሐረርጌ ነውና እዚያ ልከህ አስጠይቀህ የሚገዛ ኪኒን የተገኘ እንደሆነ እንድታስታውቀኝ ይሁን ።

ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም. አዲስ አበባ ተጻፈ ።

ይድረስ ከራስ ሚካኤል

የወይዘሮ ተዋበችን ሕመም ነገር ለገብረ ሕይወት የላከውን ደብ ዳቤ አየሁት ። እሱም በቃል ነገረኝ ። አሁንም ሕመምዋ ሩህ እንደሆነ መድኃኒት አደራረጉን ለገብረ ሕይወት አሳይቼ ሰድጀዋለሁ ። ደግሞም ከሁሉ ይልቅ ሐኪሞች ቢያዩዋት ይሻላል ። ኢያሱ እንኳ ያንጊዜ ታሞ ሳለ አይናገር እህል ውሃ አይቀምስ የነበረ ተስፋ እስክ ንቆርጥ ድረስ ከሞት የደረሰ ምንም ፈቃዱ የእግዚአብሔር ቢሆን በሐኪሙ ምክንያት ዳነ ።

ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም. አዲስ አበባ ተጻፈ ።

ይድረስ ከራስ ወልዴ

የሕመምህን ነገር የላከውን ወረቀት አየሁት ። ነገር ግን መድኃ ኒት የሚያውቅ ወጌሻ አግኝቼ መድሐኒት ጀምሬአለሁና ከሐኪም መጥቼ በሰንጢ አልተለተልም ብለህ የላክብኝ ፣ እንደዚህ ያለ ቃል መላክህ ይሄ ሞያ ሆኖ ነውን ። እኔስ ለዘለዓለም በሽተኛ ሆነህ ከመ

ቅረት ምንም ቢሆን ሳላስቀድድህ አልቀርም ፡፡ እለዚያ ስለት ከፈራህ ደብረ ሊባኖስ ሔደህ መቀመጥ ነው ፡፡

ጥር ፳፯ ቀን አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ በ፲፰፻፺፱ ዓ.ም. ፡፡

ይድረስ ከደጃዝማች አባተ

የእህል ወጥ እንዳትበላ ከዚህ ቀደም ሐኪሞች ከልክለውሃል ፡፡ አሁንም የእህል ወጥ መብላትህ ቀርቶ አሳ እንድትበላ ይሁን ፡፡

መጋቢት ፰ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ ም አዲስ አበባ ተጻፈ ፡፡

ይድረስ ከራስ ወልዴ

የሕመምክን ነገር በጐ ነኝ ብለህ ብትልክብኝ ደስ አለኝ ፡፡ ነገር ግን ሐኪሞች ይዩህ ብልህ ይሄ ነገር የማይሆን ሆነ ፡፡ ደግሞስ የሞቱት ሰዎች ሁሉ እየተረሱ ቀርተው የለምን ፡፡ አንተስ በገዛ እጅህ ልሙት ካልክ ምን ይደረጋል ፡፡ የእርያ ሽንት መድኃኒት ነው ብለውኛል ይገኝ እንደሆነ ብለህ ላክብኝ ፡፡ ይልቅ በዚያው በአንተ በኩል ከቆላው አገር መፈለግ ነው እንጂ ወደዚህማ የት ይገኛል ፡፡

ሰኔ ፳፯ ቀን በአዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ በ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ይድረስ ከወይዘሮ አስለፈች

ለደጃች ይልማ የሳል መድኃኒት ብለሽ የላክሺብኝን ይሄው ሰድጃለሁ ፡፡ ከዚህ መድኃኒት በጥርኝ ለክቶ በጥሩ ውሃ ከሱካር ጋራ አፍልቶ በሻሽ አጣርቶ በጣም ሳይበርድ ጧትም ቀን ፣ ማታም ቢሆን በትንሽ ኩባያ ወይም በቻይ ፍንጃል መጠጣት ነው ፡፡

ደግሞ አንዱ ዓይነት አደራረግ እንዲህ ነው ፡፡ በላስታ ቅቤ ከዚህ ከመድኃኒቱ አንድ ጭብጥ ጨምሮ ውሃ ሳይገባበት በቅቤ ብቻ አንጨቅጭቆ አሳድሮ ማለዳ አቅልጦ በመጭመቂያ ጨምቆ ቅቤ እንደሚጠጣ ሁሉ ጧት ጧት በትንሽ ኩባያ ወይም በትልቅ በቻይ ፍንጃል መጠጣት ነው ፡፡ ሳሉ እስቲለቅ ድረስ ፡፡ ደግሞም ቅቤው እንዳይሰለች አንድ ቀን በውሃና በሱኳር የተፈላውን ፣ ደግሞ አንድ ቀን በቅቤው ብቻ የተጨቀጨቀውን መጠጣት ነው ፡፡ ሕመሙስ መደበቁ ለምንድነው ፡፡ አስቀድሞ ለኛ ማስታወቅ ነበር እንጂ ፡፡ አሁንም እግዚአብሔር በቀላሉ ያድርግለት ፡፡

መስከረም ፱ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ከራስ ወልዴ

ደብዳቤህም ደረሰልኝ ። መድኃኒት ይምጣልኝ ያልከውን ይሄው ሰድጄልሃለሁ ። አደራረጉንም ለዳኜ ጽፌንለታል ። እሱ ያውቀዋል ። ደግሞ እግዚአብሔር በቀላሉ ያድርግልህ ።

መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም. ተጻፈ ።

ይድረስ ከዋግሹም ከበደ

. . . . የኮሶ መድኃኒት ግን እኛ ዘንድ ያለው አልቋል ። ከፈረንጅ አገር እንዲመጣ ልኬአለሁ ። በመጣልኝ ጊዜ ይሆናል ። . . . .

ጥቅምት ፯ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ከራስ ወሌ

ደብዳቤህ ደረሰልኝ ። በጉንትህን ብትልክብኝ እጅግ ደስ አለኝ ። ደግሞ እግዚአብሔር ጭራሹን ያሳምረው ። ነገር ግን የዚህን የመጠጥ ነገር ብትተወው መልካም ነው ። ሌላ በሽታ የለብህም ። ይህን መጠጥ ከተውህ ሕመምከን ጭራሽ እንድትድን የታወቀ ነው ። . . . .

ህዳር ፯ ቀን ፲፱፻ ዓ ም

## ባንክ

ለመጀመሪያ ጊዜ ባንክ የተቋቋመው በዳግማዊ አጤ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በ1898 ዓ.ም. ነው ።

በፈረንጅ አገር ስላለው የገንዘብ መበደሪያ ቤት ጉዳይ አማካሪ ዎቻቸው ምኒልክን አማከሩዋቸው ። የውጭውንም ሆነ የአገር ውስ ጡን ንግድ ለማስፋፋት ባንክ ጠቃሚ መሆኑንና በተለይም የውጭው ንግድ ያለ ባንክ ሊካሄድ ያለመቻሉን ነገሩዋቸው ። ምኒልክ በአሳቡ ከተስማሙ በኋላ ባንኩን ለማቋቋም ኃላፊነቱ ለማን እንደሚሰጥ ጠየቁ ። ፈረንሳዊው ሙሴ ደልሐርቤ ይህን ነገር ለማቋቋም ይችላልና ለእሱ ይሰጠው ተባለ ። ምኒልክም “. . . .የፈረንሳዮችን ነገር ተዉኝ ። የባቡር ሐዲድ ከጂቡቲ እስከ እንጦጦ ፣ ከዚያም እስከ ከፋና ነጭ አባይ ድረስ እንዘረጋለን ብለው ውሉታን ከተዋዋልን በኋላ እንኳን ነጭ አባይ ፥አዲስ አበባም ለማድረስ አቅቷቸዋልና እንደገና ደግሞ

በዚህ ጉዳይ ከእነሱ ጋር አልዋዋልም ። የሚሆን ከሆነ የሚሆን ሰው ፈልጉ. . . .” አሉ ።

“እንግሊዞችስ?” ተባለ ።

“እንሞክራቸዋ ።” አሉ ምኒልክ “እንግሊዞች የሆዳቸውን በሆዳቸው እየያዙ ተንኰል የሚወዱ ቢሆኑም አገር የማያስገፉ ውል ተደርጐ ይሰጣቸው . . . .” አሉ ። ይህን ሐተታ ሐሪንግተን ፣ ክሮመር ፣ ቻልመር እና ጉይዶርፕ በሰፊው ጽፈውታል ።

አጤ ምኒልክ በሁሉም ላይ ጥርጣሬ ስለነበራቸው እንደምድር ባቡር ዓይነት የባንኩንም ሥራ ውክልናውን ለኢልግና ለሽፍኔ ሰጡ። ውክልና የሰጡበትም ደብዳቤ ይህ ነው ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ይድረስ ከቢትወደድ ኢልግ ፣ ከሙሴ ሽፍኔ

ያገራችንን ንግድ ለማበረታታትና ከሌላ መንግሥት ጋር ያለውን የንግድ መላላክ ለማቅናት አንድ ባንክ በመንግሥታችን ስም ለማቆም ፈቃዴ ስለሆነ ይህነን ፈቃዴን ለመፈፀም ብርቱ ጥሩ የባንክ ማኅበር እንድትስማሙልኝ አዝዣችኋለሁ ። ይህ የመንግሥቴ ባንክ እንደሌላ የመንግሥት ባንክ ለማቆም ፈቃዴ ነውና ለኔ የሚገባኝን ፣ ለነዚህ የሚገባቸውን የምታደርጉትን ውል በብርቱ እንድትጠብቁ ይሁን ። ይህ ባንክ ቶሎ እንዲቆምልን ስለወደድሁ ከባንክ ማኅበሮች ጋር የተስማማችሁትን ውል ወደኔ ለማስወደድ በቶሎ እንድትልኩልኝ ይሁን ።

በሐምሌ በ፬ ቀን ፲፰፻፺፯ ዓመተ ምህረት አዲስ አበባ ።

ሚያዝያ 27 ቀን 1895 ዓ.ም. ሐሪንግተን ለእንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቴሌግራም አስተላለፈ ። በመልክቱም “ንጉሠ ነገሥቱ በአበሻ አገር ላይ ባንክ ለማቋቋም ያስባሉ ። ይህንንም የንጉሠ ነገሥቱን አሳብ ለማስፈጸም እንዲቻል ሰር ካሴል ወይም ሌላ የታወቀ ሰው መጥቶ ይነጋገር” አለ ። ይህ መልክት ያለ ምንም መልስ አንድ ዓመት ከመንፈቅ ከቆየ በኋላ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሎርድ ክሮመር እንደ ኤሮፓ አቆጣጠር ታህሳስ 24 ቀን 1904 ዓ.ም. (በኛ 1897) ለግብፁ ብሔራዊ ባንክ አዛዥ ለሰር ኤልዊን ፓልመር ደብዳቤ ፃፉ ። በተፃፈው ደብዳቤ ላይ “. . . .ምኒልክ የአምሳ ዓመት

ውል ይሰጡናል ። በውሉ መሠረት 1. ባንክ እናቋቁማለን ፡ 2. የብረትና የወረቀት ገንዘቦች ይሠራሉ. . . .” የሚልና ይህን የመሳሰሉ ገለፃዎች ያለበት ደብዳቤ ተላከ ። የግብፁ ባንክ ብሔራዊ አዛዥ ሰር ኤልዊንም ታህሣሥ 27 ቀን (እ.ኤ.አ.) በዚያው ዘመን በተፃፈ ደብዳቤ አንድ አጥኚ ቡድን ወደ አዲስ አበባ እንደሚላክ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴራቸው አሳወቁ ።

ከግብፅ ብሔራዊ ባንክ ወደ አዲስ አበባ የተላከው ቡድን መጋቢት 1 ቀን 1897 ዓ.ም. ባንኩን ለማቋቋም የሚቻልበትን ውል ተዋዋሉ ። በውሉ አንቀጽ 1. የግብፅ ብሔራዊ ባንክ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚያቋቁመው ባንክ አፍ አቢሲኒያ ለሚባለው የአምሳ ዓመት የባለቤትነት ውል ሲሰጥ ኩባንያው ቢያንስ የአምስት መቶ ሺ ፓውንድ ካፒታል እንዲኖረው ፡ ይልና ባንኩን ለማቋቋም መዋጮ ለመሰብሰብ በመንግሥት ፈቃድ በለንደን ፡ በፓሪስ ፡ በኒውዮርክ ፡ በበርሊን ፡ በሮም ፡ በቪየና ፡ በካይሮና በአዲስ አበባ ለሚኖሩ ሕዝቦች ዕጣ እንደሚሸጥ ፡ የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ከተማ ይሆንና ቅርንጫፍ ለማቋቋም ግን ምክር እየተደረገ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ለማስፋፋት እንደሚቻል ይገልጻል ።

በአንቀጽ ፪ በዚህ በተሰጠው አምሳ ዓመት ጊዜ ውስጥ ፩. ንጉሠ ነገሥቱ በግዛታቸው ሌላ ባንክ እንዳይቋቋም መስማማታቸውን ፡ ፪ በወርቅም ሆነ በብር ነፃ ልውውጥ እንዲኖር ፡ ፫. ከባንኩ ውጭ ፡ መንግሥት ምንም ዓይነት ገንዘብ እንዳያሠራ ፡ ፬. የመንግሥት የሆነ የሕዝብ ሀብት በባንኩ እንዲቀመጥና በቼክ እንዲታዘዝ ፡ ፭. የመበደሪያውን ሕግ ባንኩ እንዲያወጣ ። ፮. ባንኩ አስፈላጊ በመሰለውና ገበያ ባለበት ቦታ መጋዘን እንዲሠራ ፡ ፯. የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ፡ ቅርንጫፎችና መጋዘን የሚሠራበትን ቦታ መንግሥት መሬቱን በነፃ እንዲሰጥ ፡ ፰. ባንኩ የሚያስመጣውን ዕቃ በባቡር እያስጫነ ያለቀረጥ ማግባት እንደሚቻል ተደነገገ ። እንዲህ እንዲህ እያለ ይሄድና በ፲፩ኛው አንቀጽ ላይ “ባንኩ እስከ ሐምሌ 24 ቀን 1898 ዓ.ም. ድረስ ሥራ ባይጀምር ይህ ውል ይሠረዛል” ይላል ።

ባንኩ ሥራውን ሊጀምር ሲል የቦርድ አባሎች እንዲመረጡ ተደረገ ። አጤ ምኒልክ ለባንኩ ቦርድ አባልነት ራስ ተሰማንና ራስ ወልደ ጊዮርጊስን መረጡ ። የሚሸጠው ዕጣ ብዛት አንድ መቶ ሺ እንዲሆን ተወሰነና ለእንግሊዙ ኢጂፕቲያን 25,000፡ ለፈረንሣይ 12,500፡ ለኢጣልያ 12,500 ተደለደለና አምስት ሺ ዕጣ ለቦርድ ዲሬክተር አባሎች ተያዘ ። ከቀረው 45,000 ውስጥ 7500 ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች ፡ 6625 ዕጣ በካይሮ በአሌክሳንድሪያ ለሚኖሩ ፡ ሌላው በለንደን ፡


ባንኩ ሥራውን በይፋ የጀመረበት ቤት



የድሮው ገንዘብ የአሞሌ ጨው ክምር

በፓሪስ ፣ በሮም ፣ በበርሊን በቪየናና በኒውዮርክ ለሚኖሩ ሰዎች ተደልድሎ መሸጥ ተጀመረ ።

ባንኩ ዛሬ ዩኒቨርስቲ ከሆነው ራስ መኰንን ቤት ውስጥ ተቋቋመ። የካቲት 8 ቀን 1898 ዓ.ም. በዛሬው ጠቅላይ ግምጃ ቤት በንጉሠ ነገሥቱ በዳግማዊ አጤ ምኒልክ ተመርቆ ሥራውን በይፋ ጀመረ ።

## ገንዘብ

ዳግማዊ ምኒልክ በ1895 ዓ.ም. በሰኔ ወር ያስመጡት የብር መሥሪያ መኪና አዲስ አበባ ገብቶ ነበርና ባንክ እንደተቋቋመ የብር መኪናውም ሥራውን ጀመረ ። የብር መሥሪያ መኪና በኋላ ጊዜ ሥራውን ቢጀምርም ለመጀመሪያ ጊዜ ግን በሊኦን ሽፍኒ አማካሪነት የብሩ ሥራ ፓሪስ ላለ የገንዘብ መሥሪያ ፋብሪካ ኮንትራቱ ተሰጠ ። የብሩን አወራረር ቅርጽ ዲዛይን ያወጣው ላ ግራኝ የተባለ ሰው ነው ። ራስ መኰንን የኢጣሊያን አገር በጐበኙበት ጊዜ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከክሪስፒ ጋር ባደረጉት ውል መሠረት ከብር በታች ያሉት ቅንስናሽ ገንዘቦች ሮም ላለ ብር ሰሪ ተሰጠ ። የእነኚህን ቅንስናሽ ገንዘቦችን ቅርፅ ያወጣው ደግሞ ፈረንሣዊው ቻፕሊን ነው ።

ለመጀመሪያ ጊዜ በምኒልክ መልክ ታትመው የወጡት ገንዘቦች ሥራ ላይ የዋሉት ባንክ ከመቋቋሙ በፊት በ1886 ዓ ም ላይ ነበር ። እነኚህም በዚያን ጊዜ የታተሙት ገንዘቦች ፣ ባለ አንድ ብር 20,200

| | | |
|---|---|---|
| አላድ(ግማሽ) | 10,200 | |
| ሩብ | 15,200 | |
| ተሙን | 25,200 | |
| መሐለቅ | 200 | |
| ቤሳ | 200 | እና በአንድ |

ብር 64 የሚመነዘሩ ክፍልፋይ ሳንቲሞች 200 ብዛት ያላቸው ነበሩ ። ከነዚህ ገንዘቦች በኋላ በውጫሌ ውል ምክንያት በምኒልክ ላይ ያለውጫና በአድዋ ጦርነት እስኪወገድ ድረስ ምኒልክ ከውጭ አገሮች ጋር የነበራቸው ግንኙነት ተቋርጦ ስለነበር የገንዘቡ መሠራትም አብሮ ተቋረጠ ።

የገንዘብ ማሳተሙ ተግባር መቋረጡ ብቻ ሳይሆን አዲሱ የምኒልክ ገንዘብ በአገር ውስጥም ቢሆን ተቀባይ አጥቶ ነበር ። በነባሩ ብር

ላይ ያለው የማርትሬዚያ መልክ ተለውጦ የምኒልክ መልክ በመተካቱም ሕዝቡ ሌላ ገንዘብ እየመሰለው አልገበያይ አለ ። በምኒልክ መልክ የታተመው አዲሱ ገንዘብ ተቀባይ በማጣቱ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በ1900 ዓ/ም ነሐሴ ፪ ቀን አንድ አዋጅ አወጁ ።

"ለገበያ መገበያየት እንዲመች ብዬ በኔ መልክና በኔ ስም ያሳተምኩትን ብርና ሩብ የሌላ መንግሥት ነው ፣ በዚህ አልገበያይም እያልክ እርስ በርስህ ትጣላበታለህ አሉ ። አልቀበልም ማለትህ ከቀድሞው ብርና ሩብ ምን የጐደለ ነገር አለና ነው ። አሁንም የፊተኛውም ያሁኑም ብርና ሩብ ትክክል ነውና በዚያው በቀድሞው ልክ መገበያየት ነው ። እንግዲህ በዚህ በአዲሱ ብርና ሩብ ነገር የተጣላ ሰው መቀጫህን ባንድ ብር ፲ ብር ፣ ባንድ ሩብ ፭ ብር ትከፍላለህ ። ከዚህ ወዲህ ይህንን የኋለኛውን ብርና ሩብ አልቀበልም የሚለውን ሰው እጁን ይዘህ አምጣልኝ ። ገንዘቡን እመርቅልሃለሁ ።"

ምኒልክ ይህን አዋጅ ቢያውጁም አሁንም ቢሆን ተቀባይ አጣ ። እንዲያውም ሁሉንም ትቶ እንደ ጥንቱ በጥይት ይገበያይ ጀመር ። ይህንንም የሰሙት ምኒልክ እንደገና ሌላ አዋጅ አወጁ ።

"ከዚህ ቀደም ነጋዴም ፣ ወታደርም ፣ ባላገርም የሆንክ ሰው ሁሉ በየገበያውና በየመንገዱ በየሥፍራው ሁሉ በጥይት ስትገበያይ ትኖር ነበር ። አሁን ግን በኔ መልክና ስም የተሠራ ብር ፣ አላድ ፣ ሩብ ፣ ተሙን፣ መሀለቅ አድርጌአለሁና በዚህ ተገበያይ እንጂ እንግዲህ በጥይት መገበያየት ይቅር ብያለሁ ። የሚሸጥም ጥይት ከቤቱ ያለው ሰው ሁሉ እጅምሩክ እየወሰደ ለጅምሩክ ሹም ይስጥ ። ጥይትም ለመግዛት የፈለገ ሰው እጅምሩኩ እየሄደ ይግዛው ። ይህንንም አዋጅ አፍርሶ ጥይት ርስ በራሱ ሲሻሻጥና ሲገዛዛ የተገኘ ሰው ገዢውም ሻጭውም ስለቅጣታቸው ባንድ ጥይት አንዳንድ ብር ይከፈሉ ። ይህንንም አዋጅ አፍርሶ በጥይት ሲሻሻጥ አግኝቶ ወደ ዳኛ ያመጣ ሰው በቅጣት ከሚከፍሉት ገንዘብ እኩሌታውን ለያገኘው መርቄለታለሁ ።

ህዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፩ ዓ ም እንጦጦ ከተማ ተፃፈ ።

አጤ ምኒልክ ቅንስናሽ ገንዘቦችና ሙሉ ብር በመልካቸው ቢያስቀርፁም ሕዝቡ በማርትሬዚያ ብር ምትክ በደስታ አልተቀበለውም ። ቅድም እንደተባለው ብሩ የታተመው ፈረንሣይ አገር ስለነበር ሕዝቡ 'የፈረንሣይ ብር' ወይም "የመንግሥት ብር" ወይም የጃንሆይ ብር እያለ የተለያየ መጠሪያ አወጣለት ። ገዢና ሻጭም ሲገናኙ "በጃንሆይ ብር ነው ? ወይስ በሴት ብር ? እያሉ ይለዩ ጀመር ። የሴት ብር የሚባለው በብሩ ላይ የንግሥት ማርትሬዛ መልክ ስላለበት ነበር ።



የምኒልክ ብር የፊትና የኋላ መልኩ ።




ማርትሬዚያ ብር የፊትና የኋላ መልኩ



አንድ፡ብር፡
(፲፰፻፹፱)፡





የብር፡ አላድ፡
(፲፰፻፺፭)፡





የብር፡ሩብ፡
(፲፰፻፺፭)፡





አንድ፡ግርሽ፡(መሐለቅ)፡
(፲፰፻፺፭)፡



በምኒልክ፤ ዘመን የታተሙ ገንዘቦች ።

በሕዝቡ እምነት መሠረት በሁለቱ ብር ላይ ትንሽ ልዩነት አለ ። ሁለቱን ብር ለያይተው በሚዛን ላይ ሲያስቀምጡት የማርት ሬዚያ ብር ትንሽ ደፋ ያደርጋል ። ከምኒልክ ብር የማርትሬዚያ ብር ከበድ ይላል ማለት ነው ። ሁለቱን ብሮች ተራ በተራ ድንጋይ ላይ ሲጥሏቸው የማርትሬዚያው ብር ክልል ያለ ድምፅ ሲያሰማ የምኒልክ ብር ግን ዶፍ የሚል ድምፅ ስለሚያሰማ ሕዝቡ ንፁህ ብር አይደለም በማለት በውዴታ ቀርቶ በግዴታም አልቀበለው አለ ።

በምኒልክ ጊዜ የተሠራው አላድ ወይም ግማሹ ብር ከንፁህ ብር የተሠራ ነበር ። የምኒልክ መልክ ስላለበት ብቻ ከተለመደው ብር የተለየ ነው በማለት ሕዝቡ አልወደደውም ።

ሩብ የተባለው በአንድ ብር አራት የሚመነዘረው ገንዘብም ከንፁህ ብር የተሠራ ነበር ። የእሱም ዕድል እንደ አላዱ ሆነ ።

ተሙን በብር ስምንት ትመነዘራለች ። የተሠራችውም እንደ ዚሁ ከንፁህ ብር ነበር ። እነ ዜርቮስ እንደሚሉት ቃሉ ከኢጣሊያኖች የተወሰደ ነው ሲሉ ሞንታዶን ደግሞ በኢትዮጵያ የምትጠራበት ስም ባአላ ነው ይላል ። ተሙን በ1889 ዓ. ም. የታተመች ስትሆን ብዛት አልነበራትምና በሕዝቡ እጅ ተበትና አለቀች ።

ከተሙን ቀጥሎ ዝቅተኛ ዋጋ ያለው ግርሽ ነበር ። ዛሬ አንዳንድ ሰዎች ቀርሺ ከሚለው የኦሮምኛ ቃል ጋር በማመሳሰል ግርሽ አንድ ብር እንደነበር ይናገራሉ ። አይደለም ። ግርሽ በአንድ ብር 16 የሚመነዘር ነበር ። ግርሽ የታተመው ከብር ሳይሆን ከመዳብ ነበር ። እንደ ዶክተር ዜርቦስ አገላለጽ ግርሽ ማለት በአረብኛ ቋንቋ ትንሽ ገንዘብ ማለት ስለሆነ ስሙ በዚያ ሳቢያ የወጣ ነው ። የመጀመሪያው በ1886 ዓ. ም. የታተመው የአጤ ምኒልክ መልክ ያለበት የፖስታ ቴምብርም ዋጋ አንድ ግርሽ ነበር ። የግርሽ አላድ ፣ የግርሽ ሩብ ዋጋ ያላቸው ቴምብሮች ታትመው ነበር ።

ግርሽ የተለያዩ ስሞች ነበሩት ። ከአረብ በተወሰደው ቃል ሐረርጌዎች መሐልቅ ሲሉ ኤሮፓውያን ደግሞ ፒያስተር ይሉታል ። ኦሮሞች ከአረብኛ ሳግ የሚለውን ቃል ወስደው ስቃ ይሉት ነበር ። ኩናማዎች ደግሞ ግሪስያ ይሉታል ።

በ1888 ዓ. ም. ደግሞ የግርሽ አላድ (ግማሽ) የምትባል ታተመች ። ይህቺም በአንድ ብር 32 ትመነዘር ነበር ። ፀሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴና ዶክተር ዜርቦስ በመጽሐፎቻቸው እንደሚገልፁት በዚያው ዘመን ማለት በ1888 ዓ. ም. የግርሽ ሩብ የምትባል ገንዘብ ታትማ ነበር ። ይህቺ የግርሽ ሩብ በአንድ ብር 64 ትመነዘር ነበር ። ከዚች ከግርሽ

ሩብ ያነሰች ሴንቴሜ የሚሏት ቅንስናሽ ገንዘብ ታትማ ነበር ። ይህች
ሴንቴሜ የተባለች ገንዘብ በአንድ ብር አንድ መቶ ትመነዘር ነበር ።

የግርሽ ሩብ የሚባለው ስም በመንግሥት ይሰጣት እንጂ አብዛ
ኛው ሕዝብ የለመዳትና የምትታወቀው ቤሣ እየተባለች ነው ። ቤሣ
የሚለው ቃል የተወሰደው ከሄንዱስታን ነው ።

## ማተሚያ

በ1889 ዓ. ም. አንድ ፈረንሣዊ ነጋዴ የመጽሐፍት ማተሚያ
መኪና አምጥቶ ነበር ። ይህም በአንዳንድ ተቃውሞ ምክንያት ከሥራ
ላይ ሊውል አልቻለም ። በዚያ ዘመን አብዛኛው የኢትዮጵያ መኳን
ንትና ቀሳውስት ዘመናዊው ጥበብ ሁሉ የሰይጣን ሥራ እየመሰላቸው
ይቃወሙ ስለነበር ፈረንሣዊው ያመጣው የማተሚያ መኪናም ሥራ ላይ
ሳይውል ቀረ ።

ይህን የተገነዘቡት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ቀስ በቀስ የዘመናዊ
ጥበብ ተቃዋሚዎችን በምክርም በጨዋታም ካሰለጠኑ በኋላ የሲሪ
ያው ነጋዴ ኤዶልቢ የማተሚያ መኪና እንዲያስመጣላቸው አዘዙት ።
ኤድልቢም በታዘዘው መሠረት የማተሚያው መኪና በ1898 ዓ. ም.
መጥቶ ሥራውን ጀመረ ።

## ጋዜጣ

“. . . . ምኒልክ በሰላም ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አባል ፣ በጦር ጊዜ
ደግሞ ፣ . . . . ተዋጊ ንጉሥ ነው ። ስለዘመናዊው አለም ዜናም አእም
ሮው ክፍት ነው ። . . . .” ማርገሪ ፐርሐም ።

ምኒልክ የጋዜጣን ታሪክ ቢያውቁም ለጋዜጣ ሠራተኛነት ሰው
በማጣት ቆዩ ። አቶ ገብረ እግዚአብሔር የተባሉ የሐማሴን ተወላጅ
በ1888 ዓ.ም. በሰኔ ወር ከኢጣሊያኖች ከድተው ሐረር ልዑል ራ
መኰንን ዘንድ ገቡ ። ስለ ኢትዮጵያ ባላቸው ፍቅር ምክንያት ብዘ
የሥልጣኔ ነገሮችን እንደሚናገሩ ምኒልክ ሰሙ ። ምኒልክ በአቶ ገብረ
እግዚአብሔር ንግግር እየተደሰቱ “መኰንን ባይቀየመኝ ይኸን ሰው
ለኔ አደርገው ነበር” እያሉ ለየመኳንንቱ ይነገራሉ ። በዚህ መሐ
ልዑል ራስ መኰንን ሞቱ ። የአቶ ገብረ እግዚአብሔር ደጋፊ ራ
መኰንን ሲሞቱ የሐረርጌ መኳንንት አቶ ገብረ እግዚአብሔር

ከሰሰ ። የከሰሱዋቸውም ይሰድቧቸው በነበረው ስድብ ሳይሆን "መሬት ትዞራለች እንጂ ፀሐይ አትዞርም ብለህ ተናግረሃል"ብለው ነው ።

አጤ ምኒልክ ይህን እንደሰሙ የሐረርጌ ግዛት ለተሰጣቸው ለራስ መኰንን ልጅ ለደጃች ይልማ ደብዳቤ ጽፈው ገብረ እግዚአብ ሔርን ወደ አዲስ አበባ አስመጧቸው ። ከዚህ በኋላ ሐረር ሆነው ይናገሩት የነበረውን ሁሉ በወረቀት እየፃፉ ለየመኳንንቱ እንዲያድሉ አዘዟቸው ። ይህም ልክ እንደጋዜጣ በእጅ እየተፃፈ በየሣምንቱ በም ኒልክ ግብር ላይ ይታደል ጀመር ። በሥራው የተደሰቱት ምኒልክ በብ ዛቱ ማነስ ይበሳጩ ጀመር ።

ግሪካዊው ካባዲአስ ደግሞ ለምኒልክ ባቀረቡት ምክር የጋዜጣ መልክ ያለው በእጅ እየተፃፈ በየሣምንቱ 24 ግልባጭ እየወጣ ለመ ኳንንቱ ይታደል ጀመር ። የዚህንም ስም ምኒልክ ራሳቸው "አእምሮ" ብለው ሰየሙት ። ኮፒ ማድረጊያ መሣሪያ በመገኘቱም በየሣምንቱ የአእምሮ ብዛት 200 ኮፒ ሆነ ። ይህን የተመለከቱት አጤ ምኒልክ በካባዲአስ ሥራ ተደስተው አዘጋጁ በሥራው እንዲገፉበትና የማተ ሚያ መኪናም እንደሚያስመጡላቸው ተስፋ ሰጡአቸው ። የእጅ ጽሁ ፉን የማባዛቱ ሥራ ግን በ1895 ዓ.ም. ቆመ ። የማተሚያው መኪና እስከ 1898 ዓ.ም. ድረስ አልመጣም ነበር ።

ማተሚያው መኪና በኢድልቢ አስመጭነት ከመጣ በኋላ ለመ ጀመሪያ ጊዜ በሕትመት ጐህ የተባለ ጋዜጣ ወጣ ። ይህ ጐህ ተብሎ የተሰየመው ጋዜጣ በ1900 ዓ.ም. ሐምሌ 17 ቀን ታትሞ ሲወጣ የያዘው ጽሑፍ የሚከተለው ነበር ።

እጅግ የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን ሆይ

ሰሚ ጆሮ ፥ ልባዊ አእምሮ ይስጣችሁ ብዬ ሰላምታ አቀርባለሁ ። ከብዙ ዓመት ከብዙም ዘመን በኋላ እኔ የኢትዮጵያ ጎህ የምሆነው ዜናዊ ጋዜጣ በግርማዊ ገናና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ትእዛዝ ፥ ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ ከኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ምንስትርነት የተሾመ ። በሙሴ ኤድልቢ እጅ ከኤሮጳ ወደ አዲስ አበባ አስመጡኝ ።

የኢትዮጵያ ሕዝብም የሰው ልብ ቶሎ የሚከፍት ፥ ከስንፍናም የምታነቃ ብርሃን መጣህልን ብለው ትንሹ ትልቁ በክብር ተቀበ ሉኝ ። ለእግዚአብሔር ፥ ለመንግሥት የሚጠቅም ሥራም ላትምላችሁ ተሰናዳሁ ። ስለዚህ ይህን ሥራ አይቶ ፥ ቃሌንም ሰምቶ ፥የማይነቃ ሰው የኤሊን ስንፍናዋን ፥ የጉጉት በቀን አለማየትዋን ይመስላል ።

ነገር ግን የነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ የውጭ ምንስትር ፡ ጃንሆይና ንግሥታችን ፤ መንግሥታችንም ወደውሃል ፡ ሁሉም ይስሙሃል ፡ስምህ ንም ጉህ ብለው ሰይመውልሃልና ደስ ይበልህ ስላሉኝ ፡ በዚህ ቀንም ሰው ሁሉ ሕያው ሁን ጉህ አጋዣችን ሆይ ብለው መረቁኝ ። በታላቅ ደስታ በክብርም ዋልኩ ። የክርስትና አባቶቼም ራሶች ፡ ሊቃውንቶች ፤ ምንስተሮችና ደጅ አዝማች ፡ ወምበሮች ፡ ፀሐፎች ፡ መኳንንቶች ሁሉ ናቸው ። አምላክ ኢትዮጵያ ይክበር ይመስገን በአይሮጳ ፡ በእስያ ፤ በአሜሪካ ፤ በአፍሪቂያ ፡ በአውስትራሊያም ከእንቅልፋቸው አንቅቼ በእውቀት እስከ አየር እንዳደረስኳቸው ዛሬም ወደ ኢትዮጵያ እጆች ዋን ወደ እግዚአብሔር ከምትዘረጋ አገር ያመጣኸኝ ።

እድሜ ለምኒልክ ከነሠራዊቱ ብዬ እጸልያለሁ ።

የኢትዮጵያ እውነተኛ አገልጋይ ። ጉህ

ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻ ዓመተ ምህረት አዲስ አበባ

እግቢ ታተመ

በዚህ ድርሰት "እግቢ ታተመ" ሲል በአጤ ምኒልክ ቤተ መን ግሥት ውስጥ ማተሚያ ቤቱ መቋቋሙን ያስረዳል ። ሌላው ነገር ደግሞ በ1900 ዓ.ም. ሐምሌ 17 ቀን የዋለው አርብ ዕለት ነው ። ጋዜጣው ሐምሌ 17 ቀን በማለቱ ይታተም የነበረው አርብ ቀን ነበር ማለት ነው ። ወይም ደግሞ ድርሰቱ አርብ ቀን ተጽፎ ጋዜጣው ቅዳሜ ቀን ታትሞ ወጣ ማለትም ይቻላል ።

አእምሮ ጋዜጣ በ1905 እንደገና በማተሚያ ቤት እየታተመ ሥራ ውን በጀመረበት ዘመን በየሣምንቱ በፈረንሣዊኛ ቋንቋ የሚታተም ለኩርየር—ዱ.ኢትየፒ የሚባል ጋዜጣ በ1905 ዓ.ም. ደስቫጅስ በተ ባሉ ፈረንሳዊ አዘጋጅነት መታተም ጀመረ ።

## ሆ ቴ ል

በአዲስ አበባ የእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተሠርታ በም ትመረቅበት ጊዜ በመላ ኢትዮጵያ ያሉ መኳንንት ለምረቃው ተጠ ርተው ነበር ። ለተጠራው እንግዳ ማሳረፊያ እንጦጦ አይበቃ ስለነበር እቴጌ ጣይቱ ከእንጦጦ ተራራ ሥር ያለው ሕዝብ ሁሉ ለሚጠራው እንግዳ መጠለያ ቤት እንዲሰጥ ሕዝቡን ለመኑ ። እንግዳ የሚያሳድር

ውሎ ሽሮ ፡ በርበሬና ቅቤ ፡ ዱቄትና ሥጋ ከቤተ መንግሥቱ እየወሰደ እንግዶቹን እንዲያስተናግድ አዘዙ ። በዚህ ዓይነት የእንጦጦ ቤተ ክርስቲያን ምረቃ ተፈፀመ ። ከዚህም በኋላ ለሚመጣው እንግዳ ማረፊያና መመገቢያ ችግር እየሆነ መጣ ።

ምኒልክ "እህእ" እያሉ ወሬ ያጠያይቁ ጀመር ። "በፈረንጅ አገር ሆቴል የሚባል ቤት ስላለ ማንኛውም እንግዳ ገንዘቡን እየከፈለ ያርፍበታል ፡ ምግቡንም ይበላበታል" አሏቸው ። በዚህ መሠረት ሥራው እንዲጀመር አዘው ሕንፃው ተሠርቶ ሆቴል ቤቱ በ1898 ዓ.ም. በነሐሴ ወር ሥራውን ጀመረ ። ፀሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ስለሆቴል ቤቱ ሲያብራሩ "ስሙም ሆቴል ተባለ" ይላሉ ። ኃላፊነቱንም ፡ ሥራውንም እቴጌ ጣይቱ ተረክበው ይመሩና ያስተዳድሩ ጀመር ። በ1900 ዓ.ም. ጥቅምት 25 ቀን ምኒልክ በአዲስ አበባ ያሉ ዲፕሎማቶችንና የውጭ አገር ሰዎችን ጋብዘው ሆቴሉን አስመረቁ ። የመጀመሪያው ሥራ አስኪያጅም ሙሴ ፍሬደሪክ ሐል ነበረ ። በኋላ ግን አቶ ዘለቃ አጋርደው ተሾሙ ።

እንደ አገር አባባል ጣይቱ እጅ የሚያስቆረጥም ወጥ እያሠሩ ገበያ ቢጠብቁ ጠፋ ። እንኳን ምግብ መብላት ፡ ከግሪኮች ሻይ ቤት ገብቶ ሻይ መጠጣት ነውር ነበርና ጣይቱ ጢት የሚያሠሩት ወጥ ለሠራተኞቹ የማታ ራት ይሆን ጀመር ። የሚስታቸው ገበያ ማጣት ያሳሰባቸው አጤ ምኒልክ አንድ ቀን ከችሎት ሊነሱ ሲሉ በአካባቢያቸው ላሉ መኳንንቶች "ጣይቱ ምግብ የሚሸጥበት ቤት ከፍታለችና ኑ እንሂድና ልጋብዛችሁ" ብለው ወሰዱዋቸው ። መኳንንት በላ ፡ ጠጣና ምኒልክ 30 ብር ከፈሉ ።

በማግሥቱ እንደተለመደው ገበያ ቢጠበቅ ጠፋ ። ቀጥሎም ጠፋ ፡ ቀጥሎም ጠፋ ። እንደገና ምኒልክ ሆቴል ገብቶ መብላት ነውር ያለመሆኑን ለመኳንንቱ ገልፀው እንደገና ምሳ ጋበዙ ። በሌላው ቀን አሁንም ገበያ አልተገኘም ። ቢጠበቅ ፡ ቢጠበቅ ድርሽ የሚል ሰው ጠፋ ። በሌላ ቀን ደግሞ አጤ ምኒልክ ከችሎት ሊነሱ ሲሉ በዙሪያቸው ላሉ መኳንንት ፡ "ሰማችሁ ወዳጆቼ" አሉ ። "በፈረንጅ አገር አንድ ቀን አንድ ሰው የጋበዘ እንደሆነ ያ የተጋበዘ ሰው በሌላ ቀን ደግሞ ብድሩን ይከፍላል ። ብድሩን ካልከፈለ ግን እንደ ነውር ይቆጠርበታል ። " ብለው ንግግራቸውን ሳይጨርሱ መኳንንቱ "እርስዎን ፈርተንና አፍረን ነው እንጂ የሚሆንልን ከሆነ የምኒልክን ብድር ለመመለስ እኔ አለሁ" እያለ ተራ በተራ ከሆቴል ቤት ምኒልክንና ጣይቱን ይጋብዝ ጀመረ ። ገበያ እየደራ ሄደ ። ምሳችንን እቴጌ ሆቴል ሄደን እንብላ የሚለው ስለበዛም ስሙ እቴጌ ሆቴል ተባለ ።

ዛሬ በታላላቅና በሌሎችም ሆቴል ቤቶች ጋሻና ጦር እየተሰቀለ እናያለን ። እንዲህ አይነቱ አደራረግ የተጀመረው በምኒልክ ነው ።

ይድረስ ከደጃዝማች ሥዩም ።

. . . .የላክኸው የዝሆን ጥርስ አልጋና ተምቤን የተሠራ ጋሻ ደረሰልኝ ። ጋሻው ግን ለግራኝ ተብሎ ተሠርቶ እንደሆነ ነው እንጂ ሌላ ሰው ይይዘዋል ተብሎ አልተሠራም ። ነገር ግን ለሆቴል ቤት ለላንቲካ እንዲሆን አደረግሁት . . . .”

መጋቢት ፫ ቀን ፲፱፻ ዓ/ም

## ሰንደቅ ዓላማ

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የመለያ ሰንደቅ ዓላማ ቢኖራትም እንዲህ እንዳሁኑ ቋሚ የሆነ አንድ ባንዲራ አልነበራትም ። እያንዳንዱ ንጉሥ በነገሠ ጊዜ የራሱ መለያ የሆነ ዓላማ ያወጣ ነበር ። ከዳግማዊ አጤ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በፊትም ቀይ፥ ቢጫ፥ አረንጓዴ የሆነ ዓላማ ነበረ ። ይህም ዓላማ ወይም ባንዲራ በሕዝቡ ዘንድ ተስፋፍቶ ባይታወቅም በሚያውቁትም መሣፍንት ዘንድ ቢሆን አሰቃቀሉ የቀለሙን አቀማመጥ በተለያየ መንገድ እያደረገ ነበር ።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ እንደነገሡ የኢትዮጵያ ዓላማ አረንጓዴ፥ ቢጫና ቀይ እንዲሆን በአዋጅ አሳውጀው በበዓል ቀንም ማንኛውም ሰው በቤቱ ወይም በግቢው እንዲሰቅል ስላወጁ አረንጓዴ፥ ቢጫና ቀይ የሆነው የኢትዮጵያ ባንዲራ በሕዝብ ዘንድ ስለተለመደ ቋሚ ሆኖ ቀረ ።

ባንዲራ የሚለውን ስም ከ1928 ዓ/ም ወዲህ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከወረረ በኋላ ከኢጣሊያንኛ የተወሰደ ስም ነው የሚሉ አሉ ። ባንዲራ የሚለውን ስም የወሰድነው ግን በግራኝ አህመድ ወረራ ጊዜ ፖርቱጋሎች ኢትዮጵያ ውስጥ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ነው ። ፖርቱጋሎች ዘመቻ በሚወጡበት ጊዜ ሁሉ ባንዲራችንን እናስቀድም ይሉ ስለነበረ ተከታዩ የኢትዮጵያ ሕዝብም የባንዲራን ስም ከዚያ ያዘ።

## ፖሊስ (ዘበኛ)

መለያ ልብስ ያለው ዘበኛ ወይም ፖሊስ የተቋቋመው በ1901 ዓ ም በግንቦት ወር ነው ። በአገራችን ሥርዓት መሠረት ማንኛውም የመኳንንት አሽከር እንደ ፖሊስ እየሆነ ይሠራ ስለነበር ምንም



በዘመናዊ መለዮ የተቋቋመው የአራዳ ዘበኛ (ፖሊስ)

በማያውቀው ባላገር ዘንድ ለሌባና ለቀማኛ አመችቶ ነበር ። ይህን ለቅሚያ አመቺ የሆነ ዘዴ ለማስጣል ዳግማዊ ምኒልክ በ1901 ዓ ም መለያ ልብስ ያለው ዘመናዊ የፖሊስ ድርጅትን በአዋጅ አቋቋሙ ። አዋጁም እንዲህ ይላል ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

አዋጅ ።

ለሊት ሌባ እንዳይበዛ ፣ ቀን አነባብሮ እንዳያነሳ ፣ በተረፈ ክፉን ነገር ሁሉ የሚጠብቅ ዘበኛ ብናቆም ሁሉም ዘበኛ ነኝ እያለ እንዳይዝ ቁጥርና ባንዲራ ያለበት በራስ ላይ የሚደረግ ምልክት አበጅቻለሁ ። ያነን ምልክት ያደረገ ዘበኛ ቢይዝህ መያዝ ነው እንጂ ይህን ጥሰህ የተጣላህ ሰው ትቀጣለህ ።

ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ

የምስጢር የስለላ ዘበኛም አቋቁመው ሕዝቡ እንዲጠነቀቅ በማ ለት በባርኔጣው ላይ "የምስጢር ዘበኛ" የሚል ጽሑፍ ተደርጐለት ነበር ።

## ሰዓት እላፊ

አዲስ አበባ ከተቆረቆረች በኋላ መጠጥ ቤቶች እየበረከቱ በመ ሄዳቸው ለሊቱን በሙሉ ተኩስ ሳያባራ ያድር ጀመር ። ይህን የፀጥታ መበላሸት ያወቁት ዳግማዊ ምኒልክ በኢትዮጵያ ውስጥ የማይታወቅ የሰዓት እላፊን አዋጅ አወጁ ። አዋጁ የሚሠራው በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ሳይሆን በመላ ኢትዮጵያም እንዲሠራበት ተደርጐ የተደነገገ ነበር ። እጤ ምኒልክ የአዋጁን ቃል በግል ደብዳቤያቸው መሸኛ እያደረጉ ለየመኳንንቱ ሁሉ በያገሩ ላኩለት ። በደብዳቤያቸውም"…. ለሊት ለሊት ተኩስ የማይተኮስበት ከተማ ከሆነ ሕዝቡ ሰላማዊ ነውና እላፊ አታድርግበት ። ተኩስ እየተተኮሰ ፀጥታውን የሚነሳ ከሆነ ግን እላፊውን ትከልበት…." እያሉ ላኩ ።

ብላታ መርስኤ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ በልጅነታቸው ማለት በ1896 ዓ ም በአዲስ አበባ ከተማ ስላዩት ሁኔታ በመጽሐፋቸው ሲገልፁ የሰዓት እላፊንም ነገር ገልጠዋል ። እንዲህ ይላሉ ። "….ሌሊት

ከተማዋን የሚጠብቁት ዘበኞች ከሐረርጌ የመጡ ሲሆኑ ሱማሌዎች ነበሩ ። ሕዝቡ ደወርያ ይላቸዋል ። ማታ ሶስት ሰዓት ሲሆን ለሕዝቡ የሚያሰሙት አንድ የጩኸት ድምፅ አላቸው ። ሕዝቡም ያን ድምፅ ሲሰማ በቤቱና በግቢው መከተት አለበት ። ሱማሌ ከጮኸ በኋላ ከአጥሩ ውጭ በመንገዱም ሆነ በሜዳ ላይ የተገኘውን ሰው እየያዙ ይወስዱና አስረው ያሳድሩታል ። በማግሥቱም መቀጫ አስከፍለው ይለቁታል ። መቀጫውም አንድ ሩብ እንደነበር አስታውሳለሁ ። በዚያ ጊዜ የነዚህ ዘበኞች ሥልጣን የቱን ያህል እንደሚፈራና እንደሚከበር በጣም ትዝ ይለኛል ። ....'' ብለዋል ።

የሰዓት እላፊ ደንብ ምኒልክ ማውጣታቸውን ኮሄን ፣ አብኩነር ፣ ሮሲን፣ ሞታንዶን እና መረብ እነኚህ ሁሉ በየመጽሐፋቸው ጽፈውታል። እነዚህ ታሪክ ፀሐፊዎች እንደ ፃፉት ከመሸ በኋላ መዘዋወር ቀርቶ ቤቱን ከፍቶ በበራፉ ላይ ቆሞ የተገኘ ሁሉ ታስሮ አድሮ በማግሥቱ መቀጫውን ይከፍል ነበር ። የምኒልክ አዋጅና የማስገንዘቢያ ደብዳቤ ከደረሳቸው መኳንንት መሀል በቅድሚያ የሰዓት እላፊን በተግባር ያዋሉት የጐጃሙ ራስ ኃይሉ ናቸው ።

የጐጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ሞተው ልጃቸው ደጃዝማች ኃይሉ በዳግማዊ ምኒልክ ራስ ተብለው በጐጃም ላይ ተሾሙ ። ራስ ኃይሉ የአባታቸውን ግዛት ጐጃምን ከያዙ በኋላ የታወጀውን የሰዓት እላፊ በተጠናከረ ሁኔታ በሥራ ላይ አዋሉት ።

አለቃ ተክለ ሥላሴ ስለዚሁ የሰዓት እላፊ የጐጃምን ሁኔታ ሲገልጡ ''. . . . ራስ ኃይሉ . . . . ቀድሞ ያልነበረ ነገር ለስሙ ማከፊያ ፣ ለድሃ ማሳዘኛ አዲስ ግብር በጐጃም ተከለ ። . . . . በከተማው ውስጥ ሱማሌና የእንጨት ቀረጥ ተከለ ። የሱማሌው አለቃ ፈይሳ የሚባል ባሪያ ነበር ። ገና በሁለት ሰዓት ከግብር ውሃ ላይ እየያዘ የመኳንንቱንም ፣ የወታደሩንም ፣ የነጋዴውንም ምሽት ፣ ከብት ጠፍቶት የሚፈልገውን ሁሉ ሰው አንዳንድ ብር ይከፈለው ነበረ ። ደግሞ ሴት ቤቱን ሲይዝ የወንድ ምሽት ናት ብሎ አይተውም ነበረ ። ከቤቱ ወስዶ ሲጫወትባት ያድር ነበር ። አንድ ወይዘሮ ከወይዘሮ አሰለፈች እልፍኝ አምሽታ ሶስት ገረዶች ፣ ሁለት አሽከሮች አስከትላ በበቅሎዋ ስትሔድ ፈይሳ እመቤቲቱን ፣ ጭፍሮቹ ሎሌ ገረድዋን እየነዱ ወሰዱ ። ፈይሳ እንተኛ ቢላት ከባሪያ ጋራ ተኝቼም አላውቅ ። እንዳንተ ያለሰው ቋሚዬ ፣ ለጓሚዬ ነበረ ። የራስ ኃይሉን ነፍስ አይማር ፣ ለሴቶች ልጆ ቻቸውም ብድሩ ይቆይ ብላ ተራገመች ። ፈይሳም የግድ ጥሎ አደረ ጋት ። ፈይሳ ነክቶኝ ነበረ ብሎ ለባልሽ አይነግርም ። ምልክትና ማህ ተምም የለው ብሎ አላገጠባት ። በነጋው በደንቡ ዋስ ጠርታ ከነ



ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት

አሽከሮቿ ብር ከፈለች ። ይህንንም ነገር ባልዋ በሰማ ጊዜ ፈይሳን ሊገድል አሰበ ። ሚስቱን ከተማ የሚያኖር ሰው ርጉም ይሁን አለ ። ያን ጊዜ ራስ ኃይሉ በጃንሆይ ደንብ ብሎ ሱማሌ ያበጀ በጃንሆይ ደንብ በአራት ሰዓት የጠፋ ከብትና የከዳ ሎሌ ሊያስጠብቅ ሆኖ አይደለም ። በምክንያቱ የድሃ ብር ቶሎ ቶሎ ለመሰብሰብ ነው ። ያን ጊዜ በፈይሳ ውስጥ የነበረው ባርያውም ፣ ወላሞውም ፣ አረመኔ ጭፍራ ብዙ ነበር ። ያን ጊዜ ፈይሳ ከጥሩንባው አስቀድሞ ጭፍራውን ሰዶ በየጓሮው አትክልት ደብቆ ሲነፋ ከግብር ውሃ ላይ ድንገት እንደነብር ያንቀው ነበረ ። ጥንቱን ጥሩንባ በጃንሆይ ደንብ መነፋቱ ተሰብሰብ ብሎ ለማስጠንቀቅ ነበረ ። ራስ ኃይሉ ግን የጃንሆይን ደንብ ምክንያት አድርጎ የድሃውን ገንዘብ ሰበሰበ ። ፈይሳም እጅግ ከብሮ ነበረ ። ራስ ኃይሉም ጥንቱን የፈለገው ገንዘብ ነውና ፈይሳ ብዙ ገንዘብ ከሰበሰበ በኋላ በወር በወር አስር አስር ብር የሚከፍለው አንሶት ምክንያት ፈልጐ ወረሰው ። ፈይሳም በድሃ ገንዘብ ሥጋና ጠጅ አረቂ ለምዶ የባሪያ ኩሩ የነበረው ፣ ሲቸር ብስጭትና ችጋር ገደለው. . . .'' ብለዋል ።

## ፎቶግራፍ

ምኒልክ የውጭ አማካሪያቸውን ጠሩትና እየሳቁ ''አንድ ነገር ሰማሁ ። ይሄም የሰማሁት ነገር ፍፁም ውሸት መሆኑን አውቄአለሁ ። ይሄ የሰማሁት ነገር እኔን ትንሽ ያደርግና ከነቤተ መንግሥቴ ፣ ሌላው ቤት ሁሉ ፣ ሕዝቡ ፣ በቅሎና ፈረሱ ሁሉ ሳይቀር እትንሽ ጥቁር ሣጥን ውስጥ ይጨምረናል አሉ ። ይሄ ነገር ፈጽሞ የማይቻል ነገር ነው ። እውነት ነው ካልክ እንዴት ሊሆን ይችላል?'' አሉት ። አማካሪውም እውነት መሆኑን ቢነግራቸው ''እንዴት ሊሆን ይችላል ። ደግሞ እኮ እዚያች ትንሽ ሣጥን ውስጥ የሚጨምረን እየዘቀዘቀን ነው አሉ ። አሁን እኔን ከዚህ አንስቶ ራሴን ቁልቁል ፣ እግሬን ሽቅብ የሚያደርገኝ ነገር እንዴት ይኖራል? ያውም ሰው ሳያግዘው ነው አሉ'' አሉት ። ከዚህ በኋላ ካሜራ እንዲመጣ ታዞ ካሜራው ከነፎቶግ ራፍ አንሺው በ1875 ዓ.ም. መጣ ።

ካሜራው ከመጣ በኋላ ደግሞ ሐንስ እንደፃፈው ምኒልክ አዲስ በመጣው ካሜራ ፎቶግራፍ እንዳይነሱ ቀሳውስት ከለከሉዋቸው ። ርኩስ ነገር በመሆኑም እንዲጠፋ ብለው ነገሩዋቸው ። ''ምኒልክም'' ይላል ሐንስ ''ምኒልክም እግዚአብሔር የፈጠረውን ነገር ሁሉ አት ንኩ ፣ አታድርጉ ፣ እርኩስ ነው ማለት ፈጣሪን እግዚአብሔርን መቃ ወም ነው ። ምክንያቱም ሁሉን ነገር የሚፈጥር እግዚአብሔር ነውና

.... እንዲህ ያለ ደንቆሮ አሳብ አታስቡ ። .... ይሄ ነገር ከዚህ ካለ ሁበት እንስቶ ሲዘቀዝቀኝ እየዋለሁና ዞር በሉ ከፊቴ .... ብለው አባረሩዋቸው ። ከዚያም በኋላ ፎቶግራፉን ተነሱና መልካቸውን በማ የታቸው ወደዱት ። .... ” ይላል ። ምኒልክ መጀመሪያ ፎቶግራፍ የተ ነሱት ግንቦት 13 ቀን 1875 ዓ.ም. ነው ።

ምኒልክ አዲስ የመጣውን ነገር ሁሉ መማር ይወዱ ነበርና ፎቶግራፍ ማንሳት ብቻ ሳይሆን ፊልም አጥቦ ማተሙንም ጭምር ተማሩ ። ቪክቶር ጉድሮፕ እንደፃፈላቸው አጤ ምኒልክ ፎቶግራፍ ማንሳት ይወዳሉ እንጂ ማጠቡን አይወዱም ነበር ።

ከዚህ በኋላ የቤተ መንግሥት ፎቶግራፉ አንሺ ሆኖ የገባው ቦያጂያን በ1897 ዓ.ም. የሕዝብ ፍቶግራፍ ማንሳት ሱቁን ከፈተ ።

## የጽሕፈት መኪና

በ1887 ዓ.ም. አዲስ አበባ መጥቶ የነበረው አሚሪካዊው መልእ ክተኛ እስኪነር ለዳግማዊ አጤ ምኒልክ የጽሕፈት መኪና (ታይፕ ራይተር) ሰጥቷቸው ነበር ። እስኪነር እና ኸርዝብሩክ እንደፃፉት “ንጉሡ የጽሕፈት መኪናውን ሁኔታ ከተመለከቱ በኋላ ደስ የሚል ጥሩ ነገር ነው ። ለምን በአማርኛ የሚጽፍ የለም? አሁንም በአማርኛ የሚጽፍ ይሠራልኝ ብለው አዘዙ ። .... ” ይላሉ ።

የጽሕፈት መኪናው ሥራ በምኒልክ ዘመን ባይደርስም ምኒልክ ከሞቱ ከአሥር ዓመት በኋላ በ1916 ዓ.ም. አቶ አለሙ ሀብተሚካኤል የተባሉ ሰው የአማርኛ ታይፕራይተር አወጡ ። ከአቶ ዓለሙ ሀብተ ሚካኤል በኋላ ማለት በ1923 ዓ.ም. አቶ አያና ብሩ አወጡ ። አቶ አያና ብሩ ባወጡበት ዘመን ዶክተር አለመወርቅ ለብቻቸው ሌላ አውጥተው ነበር ።

## ሲኒማ

ቻርልስ ሚኬል እንደጻፈው ምኒልክ ከእስቴቬኒን ጋር ሲጫወቱ እስቲቬኒን የሲኒማን መኖር አጫወታቸው ። “ሲኒማ ምንድነው እሱ?” ብለው ጠየቁ ። እስቲቬኒንም የሲኒማን ታሪክ ዘርዝሮ ካስረዳ በኋላ ለማስመጣት ፈልጎ ቁሶችን ፈርቶ መተዉን ነገራቸው ። ምኒ ልክም “ቄስ ይኑር አይኑር እሱን ተወውና ይሄን ነገር ለማየት ስለም

ፈልግ ቶሎ ብለህ አስመጣ'' ብለው አዘዙት ። በ1889 ዓ.ም. ፕሮጀ ክተሩ ከነ ፊልሙ መጣ ። ምኒልክም መኳንንቶቻቸውን ይዘው ሚያ ዝያ 1 ቀን ፊልሙን ለመመልከት ከእልፍኝ ተገኙ ።

ፊልሙ ሃይማኖት ነክ ሆኖ የሚያሳየው የክርስቶስን ታሪክ ነበር ። ክርስቶስ በባህር ላይ እየተራመደ በእግሩ ሲሄድ በታየበት ጊዜ መኳንንቱም ፣ ሁሉም ተንስተው እጅ ነሱ ። ፊልሙ አልቆ ከራስ መኰንን ጋር በሚጨዋወቱበት ጊዜ ምኒልክ " .... እነኚህ ፈረንጆች እኮ የማይሠሩት ነገር የለም ። ሁሉንም ነገር ሲሰሩ የሰው ነፍስ ብቻ መሥራት አልቻሉም'' ብለው ተናገሩ ።

የመጀመሪያው የሕዝብ ሲኒማ ቤት በ1890 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ተከፈተ ። ሲኒማ ቤቱን የከፈተው አንድ ከአልጀሪያ የመጣ ፈረንሣዊ ነው ። ይህን በዘመኑ የማይታመን ምትሀት መሰል ነገር የሚያየው ሕዝብ የሲኒማ ቤቱን ሰይጣን ቤት ብሎ ሰየመው ። በተለይ ቀሳው ስት ሕዝቡ ከሰይጣን ቤት እየሄደ ሰይጣን እንዳያይ እያሉ ስላወገዙ ሲኒማ ቤቱ ከሰረ ። ባለቤቱም የሲኒማ ማሳያውን ዕቃ አዲስ አበባ ለነበረው የኢጣሊያ ሚኒስትር ለቺኮዲኮላ ሸጦ አገር ጥሎ ወጣ ።

የኢጣሊያኑ ሚኒስትር ያን ፕሮጀክት ለእጤ ምኒልክ በስጦታ ሰጠ ። ምኒልክም በቤተ መንግሥታቸው አዳራሽ ከመኳንንቱና ከቀሳው ስቱ ጋር መንፈሳዊ ፊልሞችን በማየት እንዲለመድ ካደረጉ በኋላ ገቢያ እንደሚገኝ እምነት ተጥሎ በ1901 ዓ. ም. ወንድማማቾቹ እነ ቦይኮቢች ለሕዝብ የሚሆን ሌላ ሲኒማ ቤት በምኒልክ አበረታችነት ከፍተው ነበር ። ይህም ሲኒማ ቤት አንድ አመት ያህል ከሠራ በኋላ በፕሮጀክተሩ መበላሸት ምክንያት ተዘጋ ። ከዚህ በኋላ የተሳካ ሥራ የተጀመረው ድሬዳዋ ውስጥ ነው ።

### ወፍጮ

የወፍጮ መኪና በኢትዮጵያ ውስጥ ለማቋቋም ከባድ ችግር ነበር ። የሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በ1835 ዓ. ም. ገዳማ አንድ በውሃ የሚ ፈጭ አስመጥተው ቢያስተክሉ ቀሳውስት የሰይጣን ሥራ ነውና በወፍጮው የተፈጨውን እህል የበላ የሰይጣን አገልጋይ በመሆኑ አውግዘናል ስላሉ ወፍጮው ፈራርሶ ወደቀ ። ከዚያም ዘመን ቀደም ብንል አቡነ ሰላማ ወፍጮ እንዲገባ ብለው ለእጤ ቴዎድሮስ ቢያ ማከሯቸው ". . . .የሴቶቻችንን ክንድ ምን ልናደርግበት ነው ?'' ብለው ወፍጮውን ከለከሉ ። እጤ ዮሐንስ ". . . .በጉዞ ላይ እህል የሚፈጩ ሴቶችን ከማጓዝ የሚገላግለን ነው. . . .'' ብለው ወፍጮ

ቢያስተክሉ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ እንደደረሰው ሁሉ በእሳቸውም ላይ የሰይጣን ፈጪ ነው ተብሎ ስለተወገዘ ቀረ ። ይህን የወፍጮ ታሪክ ሐሪስም ሊዝንም ጽፈውታል ።

በኋለኛው ጊዜ የማንኛውንም ውግዘትም ሆነ ተቃውሞ አሸን ፈው ወፍጮን ያቋቋሙ ምኒልክ ናቸው ። በአድዋ ዘመቻ ጊዜ ጓዙን ያበዛው የፈጪና የወፍጮ ጭንቀት መሆኑን ያወቁት ምኒልክ ለግላ ቸው ብዙ እህል የሚፈጭ ወፍጮ እንዲያስመጣላቸው እስቲቬኒን አዘዙት ። ወፍጮውም መጥቶ በ1893 ዓ. ም. ተተከለ ። ወፍጮው የሚፈጨው በሰይጣን ሳይሆን በሰው መሆኑን ለማሳየት ምኒልክ ከወፍጮው ቤት እየሄዱ በአስፈጪነት ተግባር ተካፋይ ሆኑ ። በግብር ጊዜም መኳንንቱና ቀሳውስቱ ሰይጣን በፈጨው ዱቄት የተሠራውን እንጀራ አንበላም ሲሉ ምኒልክ ደግሞ በእጅ በተፈጨ ዱቄት የተጋገረ እንጀራ አልበላም ይሉ ጀመር ። ለየመኳንንቱ ሲያስረዱም “ . . . . ፈጫ ይቱ በምትፈጭበት ጊዜ ንፍጧ ሲመጣ ተናፍጣ ወዲያው ትፈጫለች ። ኩሷን ጠርጋ ወዲያው ትፈጫለች ። . . . . ለዚህ ነው በንፁህ ድንጋይ የተፈጨውን የመኪናውን ዱቄት የምወደው . . . . ” ይሉ ጀመር ።

በዚህ ወፍጮ ቤት ከተፈጨው ዱቄት የእስቲቬኒን ሚስት ዳቦ ጋግራ ለምኒልክ ሰጠች ። ምኒልክም ቀምሰው ስለጣፈጣቸው ይሄን የዳቦ መጋገር ሥራ እንድትበረታበት ስለነገሩዋት ከፈረንሣይ አገር ዳቦ(ፉርኖ) ጋጋሪ አስመጥታ የሚሸጥበት ሱቅ ከፈተች ። ሱቁን ምኒልክ እንዲመርቁ ተጠይቀው ስለነበር ለምረቃው ከሱቅ ሲገቡ ትኩስ ዳቦ ቀረበላቸው ። ምኒልክ ሲበሉ ያዩ መኳንንት ትንሽ ትንሽ ቀመሱ ። በዚህም ምኒልክ ተደስተው ለጤና የሚበጅ መሆኑን ነግረው ወዲያ ውኑ በየቀኑ የሃያ ብር ዳቦ ከቤተ መንግሥት እንዲመጣላቸው የዳቦ ኮንትራት ሲይዙ በመኪና ወፍጮ የተፈጨ ዱቄት የዳቦ ገበያ ደራ ። እስቲቬኒን ስለዚህ ጉዳይ አል ቴምፖ ዲ ሚኒልክ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ሲገልፅ “ . . . . ምኒልክ የሃያ ብር ዳቦ ኮንትራት እንደያዙ ጣይ ቱም እንደዚሁ የሃያ ብር ዳቦ በየቀኑ እንዲላክ ኮንትራት ስለያዙ በቀን የተረጋገጠ አርባ ብር የዳቦ ሽያጭ ገቢ ነበረኝ . . . . ” ይላል ። የዳቦ ገበያ በመድራቱና ዳቦው በየመኳንንቱ ዘንድ በመወደዱ የመኪና ወፍጮ ዱቄትም ለመበላት እየተለመደ ሔደ ።

## ጫማ

ሰንደል ጫማ እንጂ ሽፍን ጫማ ማድረግ በአገራችን አልተለመ ደም ነበር ። ሽፍን ጫማ የሚጠላበትም ምክንያት ያገራችን የበቅሎም ሆነ የፈረስ እርካብ ጫማውን የማያስገባ ጠባብ ስለነበረ ነው ።

አንዳንድ መኳንንት በእግር በሚሄዱበት ጊዜ ነጠላ ጫማ አድርገው ይጓዙና በቅሎ ወይም ፈረስ በሚቀመጡበት ጊዜ ጫማው ወልቆ አሽከር ይይዝና በባዶ እግራቸው ከበቅሎ ይወጡ ነበር ። ይህም ሁኔታ እስከ ኋለኛው ዘመን ድረስ ነበር ። እኔም ደርሼበታለሁ ።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ የሸፍን ጫማን ጠቃሚነት ከፈረንጆች ከተረዱ በኋላ ሰፊ እርካብ አሠርተው ሽፍን ጫማ ማድረግ ጀመሩ ። መረብ ፡ ዊልዴ ፡ እና ሮሰን እንደፃፉት ምኒልክ መኳንንቱ ሁሉ ሽፍን ጫማ እንዲያደርግ ቢመክሩም ሰሚ አጡ ። ሽፍን ጫማ የሚያደርግም እንደቆማጣ ተቆጠረ ። ምኒልክም ቆማጣ ያለመሆናቸውን በአደባባይ ባዶ እግራቸውን እያሳዩ ሽፍን ጫማ ቢያደርጉም ተከታይ ጠፋ ። ምኒልክ በውዴታ እንጂ በግዴታ የማያምኑ ሰው ስለነበሩ የልጅ ልጃቸውን ኢያሱን እንኳን ሽፍን ጫማ ማስደረግ አቃታቸው ።

ምኒልክ ከአማካሪዎቻቸው ፈረንጆች ጋር ከተማከሩ በኋላ በ1902 ዓ.ም. ከፊት ጣትን ፣ ከኋላ ተረከዝን የሚሸፍን ግማሽ ሽፍን ጫማ አሠርተው "ቆማጣ ላለመሆንህ ግማሽ እግርህ ይታያልና እኔን የወደድህ እኔን ምሰል ። ሽፍን መጫሚያ ከእሾህ ፣ ከብርድና ከእንቅፋት ከሌላም ነገር ይከላከልልሃል ብዬ ነውና ለጤናህ ስትል አድርግ" ብለው ችሎት ላይ ከተናገሩ በኋላ ጥቂት ሠራዊት እየቀፈፈው ያን ጫማ ማድረግ ጀመረ ።

## ድር

ለኢትዮጵያውያን ልብስ የሚሆን ድርም ሆነ ማግ በኢትዮጵያውያን ሴቶች ብቻ ተፈትሎ የሚገኝ ነበር ። የሚሸጥ ጨርቅ የሚገኘው ከኤሮፓ ወይም ከእስያ ተሠርቶ የሚመጣው ብቻ ነው ። ይህም ከውጭ የሚመጣው ጨርቅ ዋጋው ውድ በመሆኑ ከጥቂት ሀብታሞች በስተቀር የሚገዛና የሚለብሰው አልነበረም ።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ የሸማኔዎችን አሠራር ለማሻሻል በተነሱበት ጊዜ ሸማኔዎች ጉድጓድ ቆፍረው መሥራታቸው የሚቀርበት ዘዴ እንዲፈለግ ሲመክሩ በውጭ አገር ድር ወይም ማግ በመኪና ተፈትሎ በብዛት እንደሚሸጥ ሰሙ ። ከዚህ በኋላ አስመጡልኝ ብለው በ1897 ዓ.ም. ድር መጣ ። ስለዚያን ጊዜው ድር አመጣጥ ጉዳይ ዲፕሎማቲክ ኤንድ ኮንስለር ሪፖርት ፎር 1905—6 ኦን ትሬድ ኦፍ አቢሲኒያ በሚባለው በዘመኑ ሪፖርት ላይ "....ምኒልክ ጨርቁን ከማስመጣት ይልቅ ክሩ እንዲመጣ በማድረጋቸውና ልብሱ አገር ውስጥ በመሠ

ራቱ የልብስ ዋጋ ረከሰ ። ከሩም ለአበሾች መን የተስማማ ነው ። ይህ በመሆኑ በውጭ አገር የተሠራ ጨርቅ ዋጋው እየቀነሰ ሄደ ።. . . .” ይላል ።

## የሙዚቃ ትምህርት ቤት

የሙዚቃ ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ የተከፈተው በ1887 ዓ.ም. ነው ። ምኒልክ ከሩሲያ የሙዚቃ አስተማሪ አስመጥተው ትምህርት ቤቱን በከፈቱበት ጊዜ ከመምህሩ ጋር 40 የተለያየ ዓይነት የሙዚቃ መሣሪያ መጥቶ ነበር ። ሞንዶን ቪዳሌ “. . . . .አማራዎች እንማርም ስላሉ ለመምህሩ ለሚሌውስኪ የወላይታና የሻንቅላ ሰዎች ተሰጥተ ውት ሆርኒት እና ሳክስሆርን ማስተማር ጀመረ ።. . . .በአራተኛው ወር ማርስሊስ የተባለውን ዜማ መጫወት ቻሉ ። መምህሩ ሚሌውስኪ የደረሰውን የኢትዮጵያ መዝሙርም ይጫወቱት ነበር ።. . . .” በማለት እ.አ.አ. ጥቅምት 25 ቀን 1897 በወጣው ለ ቴፕስ ጋዜጣ ላይ ጽፏል ።

ሙዚቃ አስተማሪዎቹ የሥራ ጊዜያቸውን ጨርሰው ሲመለሱም ምኒልክ ሁለት ኢትዮጵያውያን ወደ ሩሲያ ሄደው እንዲማሩ አድር ገዋል ። እነዚህም ሁለት ኢትዮጵያውያን ወደሩሲያ እንዲሄዱ አዲስ አበባ ለነበረው ለመስኮብ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን መልክተኛ ለጄኔራል ብላሶፍ አጤ ምኒልክ የሚከተለውን ደብዳቤ ፃፉ ።

ይድረስ ከጄኔራል ብላሶፍ

ከመስኮብ አገር የመጡት ሁለት ሙዚቃ ነፊዎች ወደ አገራቸው መመለሳቸው ቢሆን የመስኮብ መንግሥት ሙዚቃ ወድቆ እንዳይቀር፣ ከኔ ሁለት አሽከሮች ከነዚያ ጋር ወደ መስኮብ አገር መስደዴ ነው ። የሙዚቃ ሥራ እንዲማሩልኝ ፣ ከትምህርት ቤት እንዲገቡ ፣ አንተ ለመስኮብ መንግሥት እንድታስታውቅልኝ እለምንሃለሁ ። ሙዚቃውም የመስኮብ መንግሥት መታሰቢያ ።

ነሐሴ ፮ ቀን ፲፰፻፺ ዓ ም አዲስ አበባ ።

## የሙዚቃ ሸክላ

በሸክላ (ዲስክ) እየተቀረፀ የሚጫወተው መሣሪያ (ግራማፎን) ወደ ኢትዮጵያ የገባው በምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው ። የመጀመሪያውን ግራማፎን በ1889 ዓ.ም. ሄንሪ ዶ ኦርሊንስ እና ኒኮላስ ሊዎንቲቭ ለምኒልክ አመጡላቸው ። ይህም እነ ሊዎንቲቭ ያመጡት ግራማፎን

መጫወት ብቻ እንጂ ድምፅ የማይቀዳ ነበረ ። በኋላ ግን ባመቱ ማለት በ1890 ዓ ም ከንግሥት ቪክቶሪያ የተላኩ የእንግሊዝ መል ክተኞች በመጡ ጊዜ ግራማፎኑንና ድምፅ መቅጃውን ይዘውላቸው መጡ ። እነኚህ መልእክተኞች የእንግሊዝን ንግሥት የንግሥት ቪክቶ ሪያን ሰላምታ በዲስክ ቀርፀው አምጥተው ስለነበረ ምኒልክና ጣይቱ ባሉበት መልክተኞቹ ዲስኩን አሰሙ ። ጣይቱም ስማቸውን ዲስኩ ውስጥ ሲሰሙ "እረ የኔንም ስም ትናገራለች" አሉ ። በኋላም የምኒ ልክና የጣይቱ ድምፃቸው(ሰላምታቸው) ተቀድቶ ለንግሥት ቪክቶሪያ ተላከ ። እንግዲህ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፃቸው በዲስክ የተቀረፀው የምኒልክና የጣይቱ ነው ።

ዛሬ በእንግሊዝ አገር በለንደን ከተማ ብሪቲሽ ኢንስቲቲውት ኦፍ ሪከርድ ሳውንድ በተባለው ሙዚየም ውስጥ የሚገኘው የጣይቱን ድምፅ የያዘው ሬኮርድ ከሞላ ጐደል እንዲህ የሚል የጣይቱ ንግግር አለበት ። "እኔ እቴጌ ጣይቱ ፡ የኢትዮጵያ ብርሃን ። ለታላቋ ንግሥት ቢክቶሪያ ፡ ለታላቋ የእንግሊዝ ንግሥት የምለው እግዚአብሔር ጤንነ ቱን ይስጥዎት ። ያስተላለፉልኝ መልክት ደረሰልኝ ። አሁንም የእግ ዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ የኔ ድምፅ ወደተከበረው የንግሥት ጆሮ ደረሰ። እግዚአብሔር ጤናና ረጅም ዕድሜ ይስጥዎ ።"

## ፍልውሃ

የመጀመሪያውን የፍልውሃ መታጠቢያ ቤት በ1897 ዓ.ም. ግድም በዳግማዊ ምኒልክ ትእዛዝ የሠራው ሰርኪስ ቴርዚያን ነው ። ሰርኪስ የፍልውሃውን ቤት ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ ምኒልክ ሥራ አስኪያጅ እንዲሆን ሾመውት በእሱ ሥራ አስኪያጅነት ይመራ ጀመር ። በኋላ ግን በ1900 ዓ.ም. አዲስ አበባ ለገባው ለአብርሃም ከኡርሃዚን የሥራው ኃላፊነት ተሰጠው ። በዚህ ጊዜም ማለት ጥር 25 ቀን 1900 ዓ.ም. የሚከተለው የፍልውሃ ደንብ ወጣ ።

"መኳንንት ከሚገቡበት ሽራ ላይኛው ቤት የሚገባ ሰው አንድ ብር ሰጥቶ ፯ ቀን ተጠምቆ ይወጣ ። ከዝቅተኛው ቤት የሚገባ ሰው ፩. ሩብ ሰጥቶ ፯ ቀን ተጠምቆ ይውጣ"

የሁሉም የፍልውሃ መታጠቢያ ቤት አስተዳዳሪነት አልስማማ ያላቸው ምኒልክ ሥራውን ተረክበው ራሳቸው ይመሩ ጀመር ። ዛህን ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ "....መታጠቢያ የሚሆኑ ገንዳ ሁሉ አሰበጁ ። በፊት ዋናው ኃላፊ አንድ አርመን ነበረ ። በኋላ ግን ነጋድራስ ተሰማ



በፍልውሃው ላይ ቤት ከመሠራቱ በፊት ።



የመጀመሪያዎቹ ሙዚቃ ተማሪዎች

እሸቴ ተሾሙ ። ገቢውም በዓመት ከ500 ወደ ሁለት ሺ ብር ከፍ አለ ። የመግቢያው ዋጋ ለአንደኛ ማዕረግ ላንድ ማምንት አንድ ብር ፥ ለሁለተኛ ማዕረግ አላድ ሲሆን ፫ኛው ማዕረግ በነፃ ነበር ። .... በውሃው ጤና ሰጭነት ምክንያት ኤሮፓውያን ከውሃው እያስቀዱ ወደቤታቸው ያስገዛሉ ። አራት ጉራጌዎችን አራት ታኒካ ያሲዙና ጉራጌዎቹ በዚያ ሞልተው ያመጡላቸዋል ። እቤት እስቲደርስም ውሃው አይቀዘቅዝም" ብሏል ። በምኒልክ ጊዜ ፍልውሃውን የጐበኘው ኸርዝብሩክ"..... ዋናው ተወዳጅነቱ ቁምጥናና ቂጢኝ ያድናል መባሉ ነው ። የሚገርመው ደግሞ እውነትም ያድናል ....." ሲል ጽፏል ።

## ላ ስ ቲ ክ

በዳግማዊ አጤ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ኢትዮጵያ ከነበራት የውጭ ገቢያ አንዱ ላስቲክ ወይም ጐማ ነበረ ። ምኒልክ ቀደም ብለው ስለ ላስቲክ ፍለጋ ከብዙ የውጭ አገር ኩባንያዎች ጋር ደብዳቤ ቢፃፃፉም ከኩባንያዎቹ ሁሉ ጥሩ ውጤት ያስገኘው አንድ የእንግሊዝ ኩባንያ ነበር ። ኩባንያው በ1898 ዓ ም በኢትዮጵያ ውስጥ ሲቋቋም መጠሪያው ኢትዮጵያን ሬይን ፑሩፍ መኖፖሊ ይባል ነበር ። ይህ ኩባንያ እንደስሙ ሁሉ የላስቲክ የዝናብ ልብስ በኢትዮጵያ እየሠራ ለውጭ ለመሸጥ ታላቅ ውጥን ነበረው ። ግን በጐማው ወይም በላስቲኩ ሽያጭ ጥቂት ዘመን እንደሠራ ምኒልክ ሲሞቱ ኩባንያውም ሞተ ።

የላስቲክ ሥራ እንደተጀመረ የላስቲክ ዛፍ በየአገሩ በብዛት እን ዲተከል ምኒልክ ከኩባንያው ጋር ተዋውለው ስለነበር የዛፍ ተከላው ሥራ በሰፊው ይካሄድ ጀመር ። ምኒልክም ለዛፍ ተከላው ሥራ መኳ ንንቶቻቸውን ካዘዙበት ደብዳቤ ለዓይነት ያህል አንዱ የሚከተለው ነው ።

ይድረስ ከራስ ተሰማ

ከደጃዝማች ጀቴ

ይህን ደብዳቤ የያዘ ሙሴ ብራይስ የሚባል የላስቲክ ኩባንያ ሰው ባንተ አገር ውስጥ የላስቲክ ዛፍ ለመትከል ወደ አንተ መጥቷ ልና ከበረሃው ላይ ደህና መሬት እየፈለገ ይትከል ። አይከልክል ። በተረፈ በሥራው ሁሉ እንድትረዳው ይሁን ።

ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይህ የላስቲክ ኩባንያ መሥራት እንደጀመረ ማንኛውም ሰው የላስቲኩን ጥሬ ዕቃ ከኢትዮጵያ እያወጣ ውጭ አገር ይሸጥ ጀመር ። በዚህም የሽሚያ ገበያ የላስቲክ ዛፎች ውሃ ወይም ወተት በገፍ እየወጣ በመፍሰስ ይበላሽ ጀመር ። በዚህ ምክንያት ምኒልክ ለየመኳንንቱ ሚያዝያ 13 ቀን 1900 ዓ.ም. በጻፉት ደብዳቤ "ባንተ አገር ውስጥ ላስቲክ የሚያወጡ ሰዎች የላስቲኩን ቀረጥና ግብር አዲስ አበባ ላይ መክፈላቸውን የሚመሰክር ወረቀት ካላሳዩ በቀር እንግዲህ ወዲህ ምንም ላስቲክ ካገርህ እንዳይወጣ ጠንክረህ እንድትጠብቅ ይሁን" እያሉ አስታወቁ ።

የላስቲኩ ኩባንያ ሰዎችና ተባባሪዎቻቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚሠራው ላስቲክ በቅኝ ግዛታቸው በኩል እየተቀበሉ የላስቲኩን ጥሬ ዕቃ ከኢትዮጵያ ውጭ በማስወጣታቸው በኢትዮጵያ የተቋቋመው ኩባንያ በጥሬ ዕቃ እጦት ምክንያት ወደ ኪሣራ አዘነበለ ። ይህንንም ጉዳይ የምኒልክ ተወካይ የሆነው የሶሪያው ሰው ኢዶልቢ ለምኒልክ አመለከተ ። ምኒልክም ላስቲኩ ከኢትዮጵያ በሚወጣበት በኩል ገዢ ለሆኑት ለራስ ወልደ ጊዮርጊስ ጥር 5 ቀን 1902 ዓ.ም. በጻፉላቸው ደብዳቤ "ላስቲክ የሚገዙ የሙሴ ኢዶልቢ ሰዎች ላስቲኩን እዚሁ አዲስ አበባ እያመጡ እጅምሩክ እየተመዘነ ይውሰዱ እንጂ በዚያ በኩል ወደ ሌላ አገር እንዳይወስዱ በውል እንድታስጠብቅ ይሁን" በማለት አስጠነቀቁዋቸው ።

በዚህ ትግል ላይ እንደተሆነ የምኒልክም ሕመም እየጠና በሙሴዱ የላስቲኩ ሥራ ተቆጣጣሪና ደጋፊ በማጣቱ ሁሉም ባክኖ ኩባንያውም ተዘጋ ።

## ትምባሆ

የትምባሆ ሥራ በኢትዮጵያ ሞኖፖል ሆኖ በመንግሥት እጅ የሆነው በ1900 ዓ.ም. በምኒልክ ዘመን ነው ። የትምባሆ ሞኖፖሉ ሥራ ሐረር ውስጥ በሙሴ ሐናፌ ኃላፊነት የሚመራ ነበር ። ሐናፌ ሥራውን በሚገባ ባለማካሄዱ በ1901 ዓ.ም. በሐናፌ ቦታ ሙሴ ቤር ባኮፍ ተተካ ።

ይህ የሹም ሽር በተደረገበት ጊዜ ምኒልክ ለሐረርጌው ገዥ ለደጃዝማች ባልቻ የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉላቸው ።

ይድረስ ከደጃዝማች ባልቻ ።

ባገራችን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ያለውን የትምባሆ ሥራ የመንግሥታችን ሞኖፖል አድርገን ቀድሞ ሥራውን ሁሉ ጠብቆ የሚሠራ ሐናፊን አድርገን ነበር ። አሁን ግን የዚህን የትምባሆ ሥራ ሁሉ በመንግሥታችን ስም የሚሠራና የሚጠብቅ ቤርባኮፍን አድርገናልና ሐናፊ ሥራውን ከለቀቀበት ቀን ጀምሮ እስካሁን ድረስ የተሸጠውን ትምባሆና ያልተሸጠውን ፡ አሁን ያለውንም ትንባሆ ሁሉ ከነሒሳቡ እንዲረከብና ሥራውንም ቀድሞ በሐናፊ ጊዜ እንደነበረው በሥራት በአገርህ ውስጥ ከቤርባኮፍ በቀር ሌላ ሰው ትምባሆ እንዳይሠራ ፥ ከውጭ አገር አምጥቶ እንዳይሸጥ አዋጅ አድርገህ በውል ማስጠበቅ ነው ። ደግሞ ሥራውም የኛ የመንግሥታችን ነውና በሁሉም ነገር እንድትረዳው ይሁን ።

ሐምሌ ፲ ቀን ፲፱፻፩ ዓ. ም.


## መንገድ

የተቻለውን ያህል ኢትዮጵያን በመንገድ ለማገናኘት ምኒልክ ታላቅ ውጥን ነበራቸው ። በ1896 ዓ.ም. የመንገድ መዳመጫ ሩሎ እና ሰረገላ ካስመጡ በኋላ ሠረገላው የሚሔድበት መንገድ በሩሎው እየተዳመጠ ይሠራ ጀመር ። ይህ የመንገድ ሥራ ከአዲስ አበባ እስከ አዲስ ዓለም ድረስ የተሠራው መልካም ሲሆን ሌላውን አገር ለማዳረስ ግን የገንዘብ ችግር አጋጠመ ። ሕዝቡ በየጊዜው ለመንገድ ሥራ እየታዘዘ በመውጣቱ የራሱ የግብርና ሥራ ታወከ ። ይህን የተገነዘቡት ምኒልክ ሕዝቡ በጉልበቱ ፈንታ ብር እንዲያወጣና የመንገድ ሥራ በተቀጣሪዎች እንዲሠራ ወሰኑ ።

ሕዝቡ ገንዘብ እንዲያወጣም አዋጅ ታወጀ ። አዋጁም በአንድ ከብት አንድ ብር እንዲያወጣ ነበር ። ገንዘብ ማዋጣት እንደተጀመረም በመዋጮው አዋጅ ሕዝቡ መማረር ጀመረ ። ይህንንም የሕዝቡን ማማረር የወሎው መምህር አካለ ወልድ ለምኒልክ ገልፀው ጻፉላቸው። ምኒልክም የሚከተለውን መለሱላቸው ።

ይድረስ ከመምህር አካለ ወልድ

ስለምድር ባቡር ሥራ ገንዘብ አውጡ ባልነው ሰው አለቀስ ብለው የላኩብኝ ደብዳቤ ደረሰልኝ ። ያገራችንማ ሰው ምን እውቀት አለው ። ደርቡሽ ቢመጣ ከደርቡሽ ጋራ ሆኖ ይዋጋናል ። ፈረንጅም ቢመጣ ከፈረንጅ ጋራ ሆኖ ይዋጋናል ። እኔ ግን ይሄንን የምድር ባቡር መንገድ ይበጅ ማለቴ ለአገራችን መጠበቂያ ብዬ ነው እንጂ



ምኒልክ ቋጥኞችን በድማሚት እያስፈረሱ መንገድ ሲያሠሩ ።



ምኒልክ ግንጥላ ተይዞላቸው የአዲስ አበባ ከተማን መንገድ ሲያሠሩ ።



የመጀመሪያው ዳምጠው (ሩሎ) የአዲስ አበባን መንገድ ሲሠራ ።



ድልድይ የሌለበት መንገድ (አዋሽ)



ግቤ ወንዝ ላይ የተሠራው የግቤ የመጀመሪያው ድልድይ ።



**11459** Nel 1902 Menelik II, l'imperatore d'Abissinia, esaminò personalmente due progetti per la costruzione di un ponte e i relativi modellini. Poichè gli era stato assicurato che questi ultimi avevano le identiche caratteristiche di quelli reali, li provò con un pugno: uno andò in pezzi, mentre l'altro resistette, e venne prescelto.

እ.ኤ.አ.በ1974 (በኛ 1966) ዓ.ም. የወጣው ላቤቱማና ኢንግሚስቲካ የተባለው የኢጣሊያ መጽሔት 44ኛ ዓመት ቁጥር 2258 ላይ "የማይታመኑ እውነቶች" በሚል ርእስ ስር የምኒልክን ስዕል አውጥቷል ። ጽሑፉ የሚለው በ1902 (በኛ 1894) ዓ.ም. ምኒልክ ድልድይ ለማሠራት አስበው የሚሠራው ድልድይ ሁለት ሞዴሎች ቀረቡላቸው ። ምኒልክም የሚሠራውን ድልድይ ጥንካሬ ለማወቅ ሁለቱን የድልድይ ሞዴሎች በየተራ በጡጫ መቱዋቸው ። አንደኛው ሲሰበር ሁለተኛው አልተሰበረም ። ከዚህ ሙከራ በኋላ ያልተሰበረው ዓይነት እንዲሠራ አዘዙ ።

እኔ ልሔድበት ፡ ሰው ላመላልስበት አይደለም ። ደግሞም የወሎን ፡ የበጌምድርን ሰው እዬ ዮሐንስ እንኳን ከብቱን ፡ የበኸር ልጁ ሳይቀር እየተሻለጉ ሲያስጨንቁት እኔም ስመላለስ ያን ያህል እየተዘረፈ ይኖር አልነበረምን ። ዛሬ ያንን ሁሉ መከራውን ረሳውና ላገራችን ጥቅም ይሆናል ብለን በጭራ አንድ ብር አውጣ ብንለው በዚህ መመረሩ እጅግ የሚገርም ነው ። እንኳን በአስር በአሥራ አምስት ዓመት እንዲያውስ ባመት ባመቱ ለንጉሡ ግብር አይገባውምን ። ይህስ ከእንቅልፌ ለምን ቀሰቀሳችሁኝ እንደማለት ያለ ነው እንጂ በጭራ አንዳንድ ብር አውጡ ቢባል የሚጎዳ ሆኖ አይደለም ። በተረፈ ሌላውን ነገር ሁሉ ከእቴጌ ደብዳቤ ያገኙታል ።

ታህሳስ ፳፱ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ምኒልክ ከመምህር አካለ ወልድ የሚያበሳጭ ደብዳቤ ቢደርሳቸውም የትግራዩ ገዥ ደጃዝማች አብርሃ ደግሞ በመንገድ ሥራው መዋጮ የሚያበረታታ ደብዳቤ ይጽፉላቸው ነበር ። ደጃች አብርሃ ለምኒልክ እንዴት ያለ ደብዳቤ ጽፈውላቸው እንደነበረ ምኒልክ ከጻፉላቸው መልስ ውስጥ መረዳት እንችላለን ።

ይድረስ ከደጃዝማች አብርሃ ።

ለተሰማ የላክልኝን ደብዳቤ አየሁት ። እሱም በቃል የላከውን ሁሉንም ነገረኝ ። ስለ ምድር ባቡሩ ሥራ በጭራ ይውጣ ያልነው ብር ነገር ፡ ይሄ ነገር በኛ ብቻ አይደለም ። በፈረንጆችም አገር ነውና በዚህ ነገር አይዘኑ ብለህ የላክብኝን አየሁት ። እውነትህን ነው ። የዚህ ነገር የሚገርም ነው ። እኔም ይህ የምድር ባቡር የገባ እንደሆነ ለአገራችን ጥቅም ነውና በጭራ ይውጣ ማለቴ ድሃውም ባለጠጋውም እንዳቅም እንዳቅሙ እንዲያወጣ ብዬ ነው እንጂ በአገር በአገሩ ፈሰስ ጥዬ ማስወጣቱን አላጣሁትም ነበር ። ቀድሞስ በየዓመት በየዓመቱ ፈሰስ እየጣሉ ይቀበሉት የነበረውን ገንዘብ ድፍን ትግሬ ያውቀው የለምን ። አለዚያ አይሆንም ካለ እጥፍ እያደረግን እንቀበለዋለን ።

ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ምንም እንኳን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ባለው የከብት ብዛት ልክ ገንዘብ እንዲያዋጣ ቢታዘዝም ሕዝቡ በሜና ሳይያዝ ቀስ በቀስ እንዲከፍል ተደርጎለት ነበር ። ይህንንም ለመረዳት ቀጥሎ ያሉትን ደብዳቤዎች እንመልከት ።

ይድረስ ከራስ ሚካኤል ።

በጭራ አዋጡ ብለን ያዘዝነውን ብር ቶሎ ቶሎ አውጡ እያልክ አስቸኩለኸዋል አሉ ። ድሃው እንዳይጨነቅ በወዝ በወዝ እያደረግህ

ማስወጣት ነው እንጂ አንድ ጊዜ ጨርሰህ አውጣ ያልነውማ እንዳሆን ድሃው ከብቱ ይረከስበትና አይሸጥለትም ። አሁንም ድሃው ጨርሶ ለመስጠት ገንዘብ ይቸግረዋልና የተቸገረ የተቸገረው ሰው እኩሌታውን ዘንድሮ እየሰጠ ደግሞ እኩሌታውን ከብቱን እየሸጠ በጥቢ እንዲሰጥ ይሁን ። ነገር ግን ጨርሶ መስጠቱ የማይቀር ነውና ገንዘብ አለኝ ዘንድሮ ጨርሼ እሰጣለሁ ያለ እንደሆነ መቀበል ነው ።. . . .

ጥር ፲፭ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ከፊታውራሪ በንቲ ።

ስለባቡሩ መንገድ ሥራ በጭራ ያውጣ ያልነው ብር አገሩ ተጐድቷልና ቢቀይ ይሻላል ያልከውን መልካም አደረግህ ። አሁንም ማውጣቱ ይቆይና አንተው እንዳልከው በሌላ ጊዜ እኛ አውጣ ስንለው ያውጣ ።

መጋቢት ፳፬ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ለደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ።

ለባቡሩ ሥራ ይውጣ ያልነውን ብር ዛሬ ጨርሶ ለመስጠት ገንዘብ የሚቸግረውን ሰው አንድ ጊዜ ጨርሰህ ካላወጣህ እያላችሁ አታጣድፉት ። እንደተገኘ እንደተገኘለት እያሰናዳ እንዲሰጥ ይሁን ።

ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ዛሬ የመኪና መንገድ ይባል እንጂ በኔ ዕድሜ እንኳ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የባቡር መንገድ ነበር የሚባለው ። ከነዘፈኑም "የባቡሩ መንገድ ሰፊው ካለልሽ

ምነው በጠባቡ በልቤ መጣሽ" ይባል ነበር ።

ይህ የባቡር መንገድ መዋጮ የታዘዘበትም ዋናው ምክንያት ሕዝቡ መንገዱን በጉልበቱ እንዲሠራ ታስቦ ነበረ ። ይህ የሆነ እንደሆነ መንገዱን እንዲሠራ የሚታዘዘው ድሃው ነው ። ሀብታሙ ግን እንዳችም የሥራ መዋጮ እንደማያደርግ ስለታወቀ ብር በማዋጣቱ እንዲሠራ ተደረገ ። ሀብታሞችም ብር ማውጣቱ ቀርቶ በጉልበት እንዲሠራ የሚል አሳብ አቅርበው ነበር ። ምኒልክ ግን አይሆንም አሉ ። ይህንንም አሳብ ጥሩ አድርጎ የሚያብራራልን ምኒልክ ለአባ ኃይሉ የጻፉት ደብዳቤ ነው ።

በጭራ ይውጣ ያልነውን የፈሰሱን ብር ነገር የላኩትን ደብዳቤ አየሁት ። ነገር ግን ለኢትዮጵያ ጥቅም የሚሆን ባገራችን ባቡር ለማግባት የባቡሩን መንገድ ሥራ ጀምረናል ። ለዚሁም በየአገሩ ያለውን ሰው ሁሉ ሥራ እንዳንለው የሱ የራሱ ሥራ ይቀራል ብለን በኪራይ የሚሠራበትን ገንዘብ ያውጣ ማለታችን ስለዚህ ነው ። አሁንም ይህ ደንብ በእናንተ ብቻ አይደለም ። ባገር ሁሉ የሆነ ነውና ማውጣቱ የማይቀር ነው ።

ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻ ዓ. ም.

ይህን የመዋጮ ብር ማንም ሰው ለራሱ ጥቅም እንዳይነካው አስገዘቱ ። ምኒልክ ራሳቸውም ከገንዘቡ ምንም ላይነኩ ማሉ ። አንድ ጊዜ ራስ ወሌ ገንዘብ ችግራቸውና ከዚህ ለመንገድ ሥራ ከተዋጣው ገንዘብ ለመበደር ምኒልክን ጠየቁ ። ምኒልክም ህዳር 8 ቀን 1902 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ሲመልሱላቸው “. . . .ወሌ ሙት. . . .ይህ የጭራ ብር እንዳይነካ ግዝት ነው ። እኔም መሀላ አለብኝ ። ከሱ ላይ አንድም ብር ለሌላ ጉዳይ አይግባ . . . .ያንኑ የጭራውን ብር ሁሉ ልቅም አድርገህ እንጦጢያ ድረስ ሰደህ ለወሀኒ አዛዥ ቸርነት አስረክብልኝ ። እሱ ወደዚህ ያመጣልኛል ።. . . .’’ ብለዋቸዋል ።

በዚህም ከሕዝብ በተዋጣው ገንዘብ በአባይና ባንዳንድ ታላላቅ ወንዞች ላይ ድልድዮች ተሠሩ ። ሌላውም ሥራ በመቀጠል ላይ እንዳለ የምኒልክ ሕመም እየጠና በመሔዱና በመሞታቸው ሥራው ሁሉ ተቋረጠ ።

## አራዊት ጥበቃ

በእንግሊዝ አገር የአራዊት ፡ የአእዋፍና የአሣ መጠበቂያ ማኅበር ግንቦት 12 ቀን 1893 ዓ. ም. መቋቋሙንና ኢትዮጵያም በዚህ ማኅበር እንድትገባ በማለት ሙሴ ቤርድ ለምኒልክ አሜወታቸው ። የደንቡንም ግልባጭ አነበበላቸው ። ምኒልክ በሰሙት በአራዊት ጥበቃው ደንብ ተደሰቱ ። ይህንንም ሁኔታ በኢትዮጵያ የእንግሊዝ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የሆነው ሚስተር ሀሪንግተን የአገሩን መንግሥት ጠይቆ የተብራራ መልስና ሙሉውንም የማኅበሩን ደንብ እንዲያስመጣላቸው ጠየቁት ። ሚስተር ሀሪንግተንም ሁሉን አሟልቶ ካስመጣላቸውና ካስረዳቸው በኋላ ምኒልክ የማኅበሩ ሊቀመንበር ለነበሩት ለእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደብዳቤ ጻፉ ።

ይድረስ ከክቡር ሎርድ ላንድስድወን ።

የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

በሎንደን ከተማ በግንቦት በ፲፪ ቀን ፲፰፻፺፫ ዓ. ም. የኤሮፓ ነገሥታቶች የተዋዋሉትን የአውሬና የአእዋፍ ፡ የአሣ መጠበቂያ ውል በኮሎኔል ሀሪንግቶን እጅ ተቀብዬ አየሁት ። መረመርሁት ። በዚህ ውል ያገኘሁትን ሐሳብና የነገሥታቶችን መልካም ፈቃድ እጅግ ወድጃለሁ ። ይህንንም ያሰቡትን የአውሬና የወፍ ፡ የአሣ መጠበቂያ በመንግሥቴ ውስጥ ለመፈፀም እኔ የሚቻለኝንና የሚመቸኝን ሁሉ ለማድረግ ፈቃዴ መሆኑን አመለክታለሁ ።

ህዳር ፳፰ ቀን ፲፰፻፺፬ ዓ. ም. አዲስ ዓለም ከተማ

ኢትዮጵያ ከአራዊት ጥበቃ ማኅበር ከገባች በኋላ ምኒልክ አውሬ እያደኑ የሚኖሩትም ሰዎች ቢሆኑ ባንድነት ባንድ ቦታ ሠፍረው ሊያድኑ የሚችሉት አውሬም ተለይቶ ተነገራቸው ። ከዚህ በተረፈ ግን ማንም ሰው ያለ መንግሥት እንዲያውም ያለ ምኒልክ ፈቃድ ታላላቅ አውሬ እንዳያድን በጥብቅ ተከለከለ ።

ይህንንም ክልከላ ምኒልክ ለየመኳንንቱ ነሐሴ 11 ቀን 1900 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ አሳወቁ ። ያም ደብዳቤ እንዲህ የሚል ነበር ። ‘‘. . . . በየበረሃው ተበታትነው አውሬ እያደኑ የሚኖሩ ሰዎች እዚህ መጥተው ነበር ። እነዚህም ሰዎች አዳኝ ሁሉ ሰባስበው ከደጃዝማች ተፈሪ ግዛት ውስጥ ቦኮ ከተማ አድርገው የምስክር ወረቀት ይዘው እያደኑ እንዲቀመጡ ፈቅጄላቸዋለሁ ። ደግሞ ከዚህ ቀደም ሳይቀበልና የምስክር ወረቀት ሳይዝ ዝሆን ሲያድን ያገኙትን ሰው ሁሉ እንዲይዙ እነሱን አዝዤአቸዋለሁ ። ያለፈቃድና ያለ ምስክር ወረቀት ሲያድን አግኝተው የሚይዙትን ሰው እየተቀበልክ ወደዚህ እንድትሰድልኝ ይሁን ። የምስክሩንም ወረቀት እንድታየው ይሄው ዓይነቱን ሰድጃልሃለሁ ።’’

ምኒልክ ለዝሆን ገዳዮች ይሰጡዋቸው ከነበሩት ከብዙዎቹ የፈቃድ ወረቀቶች መሀል ሁለቱን እንመልከት ።

ይድረስ ከራስ ወልደጊዮርጊስ ።

አሽከርህ ኃይለ ኢየሱስ ዝሆን እንድገድል ይፈቀድልኝ ብሎ ቢያስቸግረኝ አንድ ዝሆን እንዲገድል ፈቅጄለታለሁና ትልቅ ጥርስ ያለው አንድ ዝሆን እንዲገድል ይሁን ። እሱ የገደለውንም የዝሆን

ጥርስ ለብቻው ለይተህ ታሳየኛለህ ። ነገር ግን ካንድ ዝሆን በቀር ሌላ እንኳን ሊገድል አቁስሎም ቢገኝ እጁን ይዘህ ስደድልኝ ።

ጥር ፪ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ይድረስ ከራስ ተሰማ ።

አሽከርህ በየነ ዝሆን እንድገድል ይፈቀድልኝ ቢለኝ ፈቅጄለታለሁና ትልቅ ጥርስ ያለው አንድ ዝሆን እንዲገድል ይሁን ። ጥርሱንም እኔ እገዛዋለሁ ። ነገር ግን ጥርስ የሌለው ወይም ጥርሱ ትንንሽ የሆነ ዝሆን የገደለ እንደሆነ እጁን ይዘህ አስረህ ስደድልኝ ።

ጥር ፬ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ጥርሱ ትልልቅ የሆነ ዝሆን ማለት ዝሆኑ እድገቱን ያበቃና ያረጀ ማለት ነው ።

## ጥይት

ቅኝ ገዢዎች ኢትዮጵያን የመያዝ አሳባቸው አልተኛ ስለነበረ በየሰበብ አስባቡ እያደረጉ የጦር መሣሪያ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ይከለክሉ ጀመር ። ምኒልክም እንዲህ ዓይነቱ ሙግትና ልመና ስለሰለቻቸው ለየጠመንጃዎቹ የሚሆኑ ጥይቶች የሚሠሩበትን የጥይት ፋብሪካ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በ1899 ዓ. ም. አቋቋሙ ። የፋብሪካው መሣሪያ የተገዛው ከእንግሊዝ አገር ግሪንውድ ከተባለ ኩባንያ ነበር ።

## ብስክሌት

ብስክሌት አዲስ አበባ ከተማ የገባው በ1893 ዓ.ም. ነው ። የመጀመሪያዋ ብስክሌት አዲስ አበባ እንደገባች ምኒልክ ዘንድ ቀረበች ። ዳግማዊ አጤ ምኒልክም ብስክሌቷን ተመልክተው “ . . . .ከአሻንጉሊት ትንሽ ሻል ትላለች ።. . . .” ማለታቸውንና ነድተው እንዲያሳዩዋቸውም መጠየቃቸውን ጉአዶሮፕ ጽፏል ። ምኒልክ የብስክሌቷን አነዳድ ከተመለከቱ በኋላ ተደንቀው “ያልገባኝ ነገር እግር ከመወዛወዝ ካላረፈ ድካሙ ምን ቀረለት” አሉ ። የዕለቱ ዕለትም አነዳድዋን አስተምሩኝ ብለው ካባቸውን ጥለው ልምምድ መጀመራቸውን ቪክቶር ጉአዶሮፕ ጽፎላቸዋል ።

# ቀይ መስቀል

እቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ

ይህንን ደብዳቤ ለሚያይ ሕዝብ ሁሉ ሰላምታቹን እሰጣለሁ ። ለክርስቲያን ፣ ለተጐዱም ሕዝብ ለነዳያን ፣ ለቆሰሉም ብርቱ ሕመም ለታመሙም ሕዝብና ሠራዊት የፍቅር መልካም ሥርዓትና የርኅራኄ ርዳታ ለማሳየት ስላሰብን ይህንንም የርኅራኄ መልካም ምግባር ለመፈጸም በመንግሥታችን በኢትዮጵያ የቀይ መስቀል ማኅበር ለመትከል ወደድን ። በእውነተኛ ልብ የተከልነው የቀይ መስቀል ማኅበር እግዚአብሔር ለመጠበቅ ስላበቃን ማኅበራችንን ለረዳ ለዶክተር ኩርት ሂርትስቡርህ በክበረው ቀይ መስቀል ንሻኖችን አክብረን ሸልመነዋል ። ይህንንም ንሻን በደረቱ እንዲይዘው ፈቅደንለታል ።

ሰኔ 9 ቀን 1899 ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

በደብዳቤው ላይ እንዳነበብነው እቴጌ ጣይቱ የማኅበሩ የበነይ ጠባቂ ለመሆን መፍቀዳቸውን ገልጸዋል ። በዘመኑም የቀይ መስቀል ኒሻን አሠርተው እንደነበረም ደብዳቤው ይገልጸዋል ። ማኅበሩ በእርግጥ የተቋቋመው በ1899 ዓ ም ነው ባንልም ከአስር ዓመታት በፊት ደግሞ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በ1889 ዓ.ም. ጥቅምት 12 ቀን ፣ ጥቅምት 27 ቀንና ኅዳር 18 ቀን ሶስት ደብዳቤዎችን በማከታተል ለሩሲያው ንጉሥ ባለቤት ለንግሥት ማርያም የቀይ መስቀልን መመሥረታቸውን ጽፈው ነበር ። ለማስረጃ ያህል ጥቅምት 12 ቀን የጻፉትን ደብዳቤ እንመልከት ።

ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ይድረስ ከመስኰብ ነገሥታት እቴጌ ማርያም ፌኦዶሮፍና ፤ በከበሩት በተመሰገኑት እጅግ በሚያፀዕቱት ባልዎ ንጉሠ ነገሥት እስከ ንድር ልብ የነበረውን የኛን ፍቅር አሳብ አለመርሳትዎ ዛሬ እኛን ባስቸገረ ጊዜ ለመርዳት የቀይ መስቀል ማኅበር ሐኪሞች በመላክዎ ገለጡት ። ይኸንንም የእውነተኛ የክርስቲያን ፍቅር ሥራ ከሁለት ሺ ዘመን ጀምሮ በአሕዛብ መሐል ለምንኖረው ከጥሩ ልቦና አስበው ለኛ ስለላኩልን እግዚአብሔር ያመስግንልን ።

ደግሞ ያሰቡት ፡ የክርስቲያን ፍቅር ፍፁም እንዲሆን አስበው ሥራውና ቃሉ የተካከለ ጀኔራል ሽዊደፍን በውነት ለተላኩበት የክርስቲያን የቸርነት ሥራ ለማሳየት ሌትና ቀን ለሚተጉ ከመዠመሪያው እስከ ኋለኛው ያሉ ሐኪሞች ለሙሉ ኢትዮጵያ አብነት የሆኑ ስለላኩልን እጅግ እናመሰግናለን ።

እኛም ፤ ሕዝባችንም የርስዎን አብነት አይተን ምንም እስከ ዛሬ ድረስ ባገራችን በወንጌል የተጻፈው ሥራ ስላልጠፋ አደራረጉ ቢጣፍጠን የቀይ መስቀል ማኅበር በርስዎ አብነት ፤ በኢትዮጵያ በእቴጌ ጣይቱ ጥግንት ተክልነው ። መሠረቱ እርስዎ ስለሆኑ ከእግዚአብሔር ረዳትነት ጋር ለዘላለም እንዲፀና ተስፋ አለን ። ይህንንም የሰሩልን ፡ ያመለከቱን መልካም ሥራ በኛና በሕዝባችን ልብ ታትሞ ይኖራል ። ይህ አሁን ያሳዩን የክርስቲያን ፍቅርና ሥራ የቸርነት ብቻ እንዳልሆን አየነው ። ትልቁ የመስኰብ መንግሥት እግዚአብሔር መንግሥታችሁን እንዲያከብር ከረዳችሁ ነፃነታችሁ ለዘላለም በጣም ይታወቅ ብሎ ይህን የቀይ መስቀል ማኅበሮች በመላኩ ተረዳነው ። ይህንንም የረቀቀ ነገር አስበው ስለላኩልን እድሜዎን እንዲያረዝምልን ፡ ሕዝብዎንም እንዲጠብቅልን ፡ የተመሰገኑት የልጅዎንም መንግሥት እንዲያሰነብትልን እግዚአብሔርን እንለምናለን ።

ጥቅምት ፲፪ ቀን ፲፰፻፹፱ ዓ.ም. አዲስ አበባ ተፃፈ ።

የቀይ መስቀል ማኅበር አባላት ኢትዮጵያ ውስጥ የገቡት ከአድዋ ድል በኋላ መንፈቅ ያህል ቆይተው ስለሆን ስለቀይ መስቀል ማኅበር አላማና ተግባር ዳግማዊ አጤ ምኒልክም ሆኑ እቴጌ ጣይቱ በሚገባ ያውቃሉ ። ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ወዲህ ማለት ቢያንስ ከ1889 ዓ.ም. ጀምሮ የቀይ መስቀል ማኅበር ስም በአዲስ አበባ ከተማ የታወቀ ነበር ። የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ከዓለም ቀይ መስቀል ማኅበር በሩሲያዊዋ ንግሥት አማካይነት ተመዝግቦ አባል ሆኖ ይሆን ?

## አረቄ

የኤሮፓን መጠጥ ሱቅ በመክፈት በኢትዮጵያ ያስለመዱ አርመኖች ናቸው ። አብዛኛው መጠጥ በኤሮፓውያን ይዞታ የሚቀመም ነጭ አረቄ ወይም አኒቼ ነበር ። ይህ የአኒቼ ፋብሪካ በ1890 ዓ.ም. ገደማ ተባዛ ። ማርዲሮስ አዝናቦሪያን አረቄ ማውጣት እንደጀመሩ በአረቄው ተወዳጅነት የተነሳ ማርዲሮስ አረቄ ጠጭው በዛ ። የማርዲሮስ አረቄን ለመወዳደር እየተባለ ሌላው ሁሉ አልኮሉን እያበዛ ያወጣ ጀመር ። በዚህም ምክንያት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሰካራምና በሽተኛው እየበዛ ስለሄደ አጤ ምኒልክ የሚከተለውን አዋጅ አወጁ ።

ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

አዋጅ

ቀድሞ ጠጅና አረቄ የሚሸጥና የሚገዛ ሰው በልክ ነበር ። አሁን ግን ሰው ሁሉ ሌላ ሥራውን እየተወ ሁሉም መሸተኛ ሆነ ። የሚገዛም ሰው አልፎ ሂያጅ መንገደኛና ነጋዴ ፤ ከወታደርም ደጅ ጠኚ የሆነ ሰው ነበር ። አሁን ግን የከተማው ሰው ሁሉ መሸተኛ ሆነና የሌባና የቀጣፊ መቃጠሪያ ሆነ ። አረቄም የሚሸጠው ሰው ሁሉ ፤ ሲቢርቶውን እየበጠበጠ ፤ ሌላም መድኃኒት እየጨመረ እየሸጠ ፤ እየገዛ የሚጠጣው ሁሉ ሕመምተኛ የሚሆን ቢሆን ስለዚህ ለጠጅና ለአረቄው መሸጫ ለብቻው ሥፍራ ለይተናልና አረቄም ፤ ጠጅም የምትገዛ ሰው ከዚያ እየሄድህ ግዛ እንጂ ከሌላ ዘንድ አትግዛ ። ሻጭም፤ ገዢም ከዚህ ከተፈቀደው ቦታ በቀር ከሌላ ዘንድ ስትገዛ የተገኘህ ሰው በከብትህ ትቀጣለህ ።

ጳጉሜ ፱ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓመተ ምሕረት

## ሥራ ማቆም

ሥራ የማቆም አድማ የተጀመረውም በምኒልክ ዘመን ነው ። የእንጦጦ ማርያም ቤት ክርስቲያን እንደገና ታድሳ በምትሠራበት በ1898 ዓ.ም. በታህሣሥ ወር ሳይታሰብ የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ቆመ ። ሥራው በምን ምክንያት እንደቆመ ቢጠየቅ ሠራተኞቹ ግሪኮች ደሞዛቸው ስላልተከፈላቸው ሥራ ማቆማቸውን ምኒልክ ሰሙ ። ወዲያውኑም ሥራ ያቆሙትን ግሪኮች አስጠርተው አባብለውና ደሞዛቸውን

ክፍለው ሥራው እንዲጀመር አደረጉ ። ሥራው ሳይቆም ደሞዛቸው እንዲከፈላቸው ለምን እንዳልጠየቁ ምኒልክ ግራ ገብቷቸው ሳለ በአጠገባቸው ያሉ የውጭ አገር ሰዎች "በፈረንጅ አገር ደንቡ ሥራ ማቆም ነው" አሉዋቸው ። ምኒልክም "የፈረንጅ ፈሊጡ ሁሉ ድንቅ ነው ። የጉልበቱን ዋጋ በጉልበቱ ለማግኘት ማሰቡ ነው ።" ብለው መለሱ ።

ይህ የምኒልክ መልስ አሰጣጥ እንደ አዋጅ ሆኖ ስለተቆጠረ በአዲስ አበባ ያሉ ግንብ ገንቢ ፈረንጆች በሙሉ በ1899 ዓ.ም.በግን ቦት ወር የመገንባት ሥራቸውን ከዳር እስከ ዳር አቆሙ ። ቢጠየቁም "የምንገነባበት ዋጋ ስላነሰን ነው" አሉ ። ይህን የሰሙት ምኒልክም "እነሰን ካሉ ይበቃናል የሚሉትን እየሰጣችሁ አሠሩዋቸው" ብለው ስላዘዙ የገንቢዎች የመገንቢያ ዋጋ ከፍ አለ ።

## የሚኒስትሮች መሾም

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ሚኒስትሮች የተሾሙት ጥቅምት 14 ቀን 1900 ዓ.ም. ነው ። በዚያን ጊዜም በዳግማዊ አጤ ምኒልክ የተሾሙት የመጀመሪያዎቹ ሰባት ሚኒስትሮች የሚከተሉት ናቸው ።

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ/ | አፈንጉሥ ነሲቡ መስቀሉ | የዳኝነት ሚኒስትር |
| 2ኛ/ | ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ | የጦር ሚኒስትር |
| 3ኛ/ | ፀሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ | የጽሕፈት ሚኒስትር |
| 4ኛ/ | በጅሮንድ ሙሉጌታ | የገንዘብና የጓዳ ሚኒስትር |
| 5ኛ/ | ሊቀ መኳስ ከተማ | ያገር ግዛት ሚኒስትር |
| 6ኛ/ | ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ | የንግድና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር |
| 7ኛ/ | ከንቲባ ወልደ ጻዲቅ ጉሹ | የርሻና የመሥሪያ ሚኒስትር |

ምኒልክ እነኚህን ሚኒስትሮች እንደሾሙ በአዲስ አበባ ያሉ የውጭ አገር መንግሥታት ተወካዮች ሹመቱን እንዲያውቁት የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉ ።

"... የዩሮፓን ሥርዓት በአገራችን በኢትዮጵያ ካሰብን ብዙ ጊዜ ነው ። እናንተም የሮፓ ሥርዓት በኢትዮጵያ ቢለመድ መልካም

ነው እያላችሁ ስታመለክቱኝ ነበር ። አሁንም የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ለመፈፀም ቢያበቃኝ ምኒስትሮች ለመሾም ዠምሬ ። አፈንጉሥ ነሲቡን ። ፊታውራሪ አብተ ጊዮርጊስን ። ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴን ። በጅሮንድ ሙሉጌታን ። ሊቀመኳስ ከተማን ። ነጋድራስ ኃይለጊዮርጊ ስን ። ከንቲባ ወልደጻዲቅን አድርጌአለሁና ይህንን እንድታውቁት ብዬ ነው ።

ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻ ዓመተ ምህረት አዲስ አበባ ተጻፈ ።

ሚኒስትሮቹ ከተሾሙ ከ15 ቀናት በኋላ ደግሞ ለሚኒስትሮቹ መመሪያ የሚሆን ደንብ አወጡ ። የወጣውንም ደንብ በሚቀጥለው ደብዳቤ ሸኚነት ለእያንዳንዱ ሚኒስትር ላኩላቸው ።

የመንግሥት ሥርዓት

"ባገራችን በኢትዮጵያ የሮጳ ሰው ነገሥታቱም ቆንሲል ሁሉ ገቡ ። እነዚህም በኢትዮጵያ መንግሥት ሥራት ያልተለመደ ነው ፤ ሥራት የሌለው አገር ምን መንግሥት ይባላል እያሉ አገራችን መወረፉን ታውቃላችሁ ። ለመውሰድም በኛ ላይ እንደተነሱም ታውቃላችሁ ። አሁንም ምንም የቀድሞው የኢትዮጵያ ሥራት ቢኖር ከጥቂት ቀን በኋላ ቀርቷልና አገራችንን እንደ አሮጳ ሥራት ለማድረግ አስቤ ይሄንን ባንደኛ ወረቀት የተፃፈውን ደንብ ጽፌላችኋለሁና በዚሁ ባስያዝኳችሁ ሥራ ሳትጣሉ ፣ ሳትመቀኛኙ በእውነት እርስ በርሳችሁ ተስማምታችሁ ጠንክራችሁ መንግሥታችንን መርዳት ነው ።

እንዲህ ሁነን በሚገባ ሥራት ሕዝባችንን ጠብቀን ከያዝነው ለመንግሥታችንና ለሀገራችን ጥቅም ይሆናል ። አገራችንን ሌላ አይ መኘውም ። እኔም እስካሁን ብደክም ብደክም ሚኒስቴር ፣ መማክርት ፣ ቆንሲል የለበት ፣ ባንድ ሰው አሳብ ብቻ እያሉ አሙን እንጂ አላመሰ ገኑንም ።

አሁንም እንቅልፍ ሳትወዱ ፣ መጠጥ ሳታበዙ ፣ ገንዘብን ጠልታ ችሁ ፣ ሰውን ወዳችሁ ፣ ተግታችሁ ይሄንን ሥራ እንድትፈፅሙልኝ ተስፋ አለኝ ። ለዚህ ሥራ እኔ እናንተን አምኜ ስላደረግሁ እናንተም የምታምኑትን ፣ ገንዘብ የማይወደውን ፣ ድሃ የማይበድለውን ፣ እናንቀን የሚረዳችሁን ሰው እየፈለጋችሁ እያመለከታችሁኝ ከሥራው ማግባት ያስፈልጋችኋል ።

ገንዘብም ቢሆን እኔ ደሞዝ እሰጣለሁ እንጂ ከድሃ ፣ እንኳን ትልቅ ገንዘብ አንድ መሀለቅም እንኳ ቢሆን ከዚያው ከተወሰነለት ከግብሩ

በቀር ሌላ እንዳይነካ ማድረግ ነው ። ከዚህ ከተጻፈው ደንብ አልፋ ችሁ ድሃ አላግባብ የተበደለ እንደሆነ እኔም እጠላችኋለሁ ። እናንተም ትዋረዳላችሁ ። በነፍሳችሁም በወንጌል ፣ በመስቀል አምላችኋለሁ ፤ አስገዝታችኋለሁ ።"

የመጀመሪያዎቹ ሰባት ሚኒስትሮች ተሹመው ሥራ ከጀመሩ በኋላ ሥራ የሚበዛበትና አስፈላጊ የሆኑ ሚኒስቴሮች እየተከፈቱ በተጨማሪ አዛዥ መታፈሪያ የግቢ ሚኒስትር ፣ ቀኛዝማች መኰንን ተወንድ በላይ የሥራ ሚኒስትር ተብለው ተሾሙ ። የፖስታና የቴሌ ፎን ሥራ በዚያን ጊዜ እጅግም ያልተስፋፋ ስለነበረ በግቢ ሚኒስቴር ሥር ሆኖ የበላይ አለቃ ልጅ በየነ ይመር የፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌ ፎን ሹም ተብለው ተሾሙ ።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ የመጀመሪያዎቹን ሚኒስትሮች ከሾሙ ከአምስት ወር በኋላ ደግሞ ለጠቅላላ ተሿሚዎቹ የሚከተለውን ደብ ዳቤ ፃፉላቸው ።

"እኔ እናንተን ምንስቴርም ፣ ወንበርም መሾሜ ለመንግሥታችንና ለሕዝባችን ጥቅም እንዲሆን ነው ።

"አሁንም በዚህ ባስያዝኳችሁ ሥራ ሳትጣሉ ፣ ሳትመቀኛኙ ፣ እንቅልፍ ሳትወዱ ፣ መጠጥ ሳታበዙ ፣ ገንዘብ ጠልታችሁ ፣ ሰውን ወዳ ችሁ እርስ በርሳችሁ ተስማምታችሁ ፣ ጠንክራችሁ ፣ በውነት መንግሥ ታችንን እንድትረዱ ይሁን። በዚህም በያዛችሁት ሥራ ከእውነተኛው ነገር በቀር እገሌን እንወደውም ፣ በዚህ ነገር እንጉዳው እንዳትሉ ። ገንዘብም መተያያ ብትቀበሉ ፣ ገንዘብ ስጥቶናል ብላችሁ ሳታደሉ ፣ በእውነት ሕዝባችንን ልትጠብቁ አምኛችኋለሁና እናንተም በዚሁ ቃል ታመኑልኝ ።

ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻ ዓመተ ምህረት አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ ።

እነዚህ ሚኒስትሮች ከ1900 ዓ. ም. ጀምሮ ሲሠሩ ከቆዩ በኋላ፣ ተቃዋሚ እየተነሳ ሄደ ። በተለይ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ታመው ኢያሱ ሥልጣን ሲይዙ ሕዝቡ በሚኒስትሮች ላይ ያለውን ተቃውሞ አባባሰ ። ሚኒስትሮችም የሕዝቡን ተቃውሞ ለማብረድ የስብከት ወረ ቀት መበተንና በጋዜጣም ማውጣት ጀመሩ ። ከስብከት ጽሑፎቻቸው አንዱ ከዚህ የሚከተለው ነው ። ጽሑፉ አንዳንዴ 3ኛን ሰው እንደ ሁለተኛ ሰው እያደረገ ይጠራል ። ለምሳሌ እሳቸው ለማለት እርስዎ ይላል ።



አፈንጉሥ ነሲቡ ።



ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ



ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ



በጅሮንድ ሙሉጌታ (በኋላ ራስ)



ሊቀ መኳስ ከተማ ።



ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ



ከንቲባ ወልደጻድቅ



እዛዥ መታፈሪያ



ቀኛዝማች መኰንን ተወንድ በላይ ።

## የምኒስትሮች የምክር ቃል ።

የሀገራችን የኢትዮጵያ ሰዎች መኳንንቱም ሠራዊቱም ከዚህ ቀጥሎ የተፃፈውን ቃል እናስታውቃችኋለን ። ቃሉንም በውል መር ምሩት ። ነገርም የሚታወቅ በመመርመር ነው እንጂ በመስማት ብቻ አይደለም ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም ከጥንት ጀምሮ እራሱን የቻለ ቢሆን ጭራሽ በዓለም ሁሉ የታወቀው ባጤ ምኒልክ ነው ። አጤ ምኒልክ ሀገርዎን አደላድለው ብዙ ዘመን ከገዙ በኋላ ድንገት ሕመም ቢያድርብዎ ጳጳሱን ከነካህናቱ ፡ መኳንንቱን ከነሠራዊቱ ሰብስበው ያልጋ ወራሽ ልጃቸውን አስታወቁን ። እርስ በርሳችንም እንዳንጣላ እውነተኛ ታላቅ ምክራቸውን መከሩን ። ጌታችን አጤ ምኒልክ ሕመ ማቸው በርትቶ እቤት በመዋላቸው አዝነን ሳለን እረኛ እንደሌላቸው በጎች እንዳንበተን ያልጋ ወራሽ ልጃቸውን ልጅ ኢያሱን በመስጠታ ቸው እጅግ ደስ አለን ። ጌታችንም አጤ ምኒልክ አስበው እንደሰጡን ያልጋ ወራሻቸውን ልዑል ልጅ ኢያሱን እግዚአብሔር አጠንክሮ ይኸው እስካሁን በፀጥታ ኖርን ። ቀድሞ ስንኳ በየበረሃው አንዳንድ ሽፍታ አይጠፋም ነበር ። ዛሬ ግን ውቃቢያቸው በርትቶ በዚህ አገር እንደዚህ ያለ ሽፍታ አለ ተብሎ አይሰማም ። እኛ ግን እግዚአብሔር እንደዚህ ያለ መልካም ሥራ ቢሠራልን እየተስማማን መንግሥታች ንን እየጠበቅን በፍቅር መኖራችንን ትተን እርስ በርሳችን እየተጣላን ለባእድ መሳለቂያ እንዳንሆን ጃንሆይ የመከሩንን ምክር ጠንክረን ማጽናት ይገባናል ። የሕዝቡን አንድነት ፡ ያገራችንን ፀጥታ የማይወዱ ምቀኞች በየጊዜው እየተነሱ ሀሰቱን እውነት እያስመሰሉ ለመኳንንቱና ለሠራዊቱ እያወሩ የሕዝቡን ልብ ለመከፋፈል ይፈልጋሉ ። አሁን እንኳ በ፲፱፻፭ ዓመተ ምሕረት በዚህ ባለፈው ወር በጥቅምት ጃንሆይ ይና ፈሱ በማለት ምክንያት ከልፍኝ እስከ ገብርኤል መንገድ መደልደ ሉን ብንሰማ አዝነን ፡ እንኳንስ የብዙ ቀን ሕመምተኛና የወር በሽ ተኛ እንኳ እንዳያገረሽበት ተብሎ ፈጥኖ ከደጅ አይውጣ ይባላል ። ስለዚህ ቢቸግረን መኳንንቱንም ሠራዊቱንም ሰብስበን ብንማከር እንዳንድ ልብ መካሪ እንዳንድ ቃል ተናጋሪ ሆኖ ከዚህ ቀደም ጌታ ችን ሕመም የጸናባቸው በዚሁ ወርኃት በጥቅምት ነበር ። ዛሬም የነ ፋስ ኃይል የሚበረታበት ጊዜ ነው ። የዳኑ መስሎን ሐኪም ሳያያቸው ልጅ ኢያሱም ከሌሉበት ይውጡ ብለን ጃንሆይ እንዳች ቢሆኑብን ጉዳትና ጭንቀቱ የኛው አይደለምን? እዚያው እንዳሉ እንደ ጥንቱ ይሰንብቱልን ብለን በፍቅር የመከርነውን ቃል አፍርሰው ጃንሆይ ልውጣ ቢሉ አናስወጣም ብለው ከለከሉ የሚባል የሐሰት ወሬ

ተወራ ። ላጤ ምኒልክ ደህንነት ስንኳ የኢትዮጵያ ሕዝብና ሌላ ባእድ ቢሆን ደስ የማይለው ሆኖ ነውን? ይኸንንም ሐሰት ያወራ የጃንሆይን ጤና የሚጠላና የኢትዮጵያን ጥፋት የሚወድ ነው ።

ደግሞ ከዚህ በኋላ ይህ ሐሰት ወሬ ቢገለጥበት መንግሥቱን ወዶ አንድነት ተስማምቶ የሚኖረውን ሕዝቡን አለያይቶ ለማፋጀትና ደም ለማፍሰስ ጃንሆይን እንኮበር ሊያወርዱአቸው ነው የሚል የበለጠ ሐሰት በአለሙ ሁሉ ተወራ ። ጠላት አጥፍተው ከትንሽ እስከ ትልቁ ሁሉንም በየማእረጉ ሹመው ሸልመው ኢትዮጵያን አልምተው ያቆዩንን አባታችንን ፡ ጌታችንን ፡ ጃንሆይን በዚህ በነፋስ አይውጡብን ብለን ስንጨነቅ እንዴት ያለ ክርስቲያን እንኮበር ይውረዱ ብሎ ይመክራል? ወይስ እንዴት ያለ ልጅ አባቱን አስወጥቶ እኔ ልግባ ይላል? ደግሞስ እንደዚህ ያለ ሀሳብ ካለ ሠራዊቱ በቤት ሥራ ለምን ይደክማል? ይህን ሥራ እንኳንስ ክርስቲያን አህዛብም አያደርገው ። ደሞ እኛ ቀድሞም ምለናል ፡ ተገዝተናል ፡ አሁንም ይህ ሁሉ ክፉ ሀሳብ በልጅ ኢያሱም በኛም ልብ እንዳልታሰበ ያው መሀላና ግዝት ዛሬ ይድረስብን ። ይህም የሐሰት ወሬ መንግሥቱንና ሀገሩን ከሚወድ ሰው እንዳልወጣ የታወቀ ነው ። ሀገሩንና መንግሥቱን የሚወድ ሰው ግን፣ እንኳን ያልሆነውንና የሆነ ነውር እንኳን ቢያገኝ ለመንግሥቱና ለሀገሩ ሲል መልካም ምክር ይመክራል ። አሁንም ይህ ክፉ ወሬ ከምቀኛ የመጣ ነውና ይህን ያወራ ቢገኝ የመንግሥት በደለኛ መሆኑ ይታወቅ ነበረ ። እሱ ግን ተሰውሮ ይህን እንክርዳድ ዘሩን እየዘራ ስንዴ ልባችንን አረም ሊያስበላው ያሰበ ነው ።

ክቡራን ወንድሞቻችን ሆይ ፡ የጌታውን ልጅና አልጋ የሚጠብቅ ላደራ የበቃ ሰው እንደዚህ ያለውን ሐሰት ወሬ ሲሰማ እውነት ነው ለማለት አይገባውም ። ይህ ወሬ የነፋስ ያህል ነው ። እንግዲህ ያጤ ምኒልክ ፍቅር በወሬ ሊካድ መንግሥታቸውስ በወሬ ሊፈታ ነውን? ደግሞስ ይህንን ያወራ ምቀኛ ከመካከላችን ነው ። በመሐላና በግዝት አውጥተን እንለየው ። ምን እስኪያደርግ ነው የምንጠብቀው ። አሁንም በየስፍራችን እንፈልግ ፡ እንመርምር ፡ ወደፊትም ጃንሆይ እንደመከሩን ነፋስ እንዳይገባብን አንድ ልብ ሁነን በፍቅር መንግሥታችንን ብን ጠብቅ መልካም ነው ።

ታኅሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፰ ዓመተ ምሕረት አዲስ በአበባ ተፃፈ ።

(የጥያቄ ምልክት የጨመርኩ እኔ ነኝ)

ይህን በመሳሰለው ስብከት የሚኒስትሮቹ የሥልጣን ዕድሜ ቢራዘምም በ1910 ዓ. ም. የሕዝቡ አድማ ገነፈለ ፡ የመጀመሪያዎቹ ሚኒስትሮችም ተሻሩ ።

## የውጭ አገር ሰዎች

“ . . . . ሚስተር ጆን ሜየር ሸዋ ካለው የቅዱስ ክሪስኮና ሚሲዮን ለመደባለቅ ወደ ሸዋ ሔደ ። መሔዱን አጤ ዮሐንስ እንደሰሙ በሸዋ ያሉትን ኤሮጳውያን በሙሉ እንዲያስወጡ ምኒልክን ጠየቋቸው ። ምኒልክም ‘አገሬን ከኤሮጳውያኖች ለይቼ ልዘጋት አልፈልግም ። ምክንያቱም እወዳቸዋለሁ’ ብለው መለሱላቸው. . . .” ዎልድሜየር ።

የውጭ አገር ሰዎች በርከት በማለታቸውና ኢትዮጵያ ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር የምታደርገው ግንኙነት ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ በመሄዱ ዳግማዊ ምኒልክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን አቋ ቋሙ ። ለመጀመሪያ ጊዜም ከተሾሙት ሚኒስትሮች መሐል ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ የንግድ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው ተሹመዋል ።

አዲሱን የውጭ አገር ሚኒስቴር ካቋቋሙም በኋላ ደንብ አወጡ ። ደንቡ በታወጀበት ጊዜ በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ የውጭ አገር ሰዎች ብዛት እንደ ዶክተር መረብ አጻጻፍ 1,095 ሰዎች ነበሩ ። እነ ኚህም የውጭ አገር ሰዎች 334 ግሪኮች ፥ 227 አረቦች ፥ 149 ሕንዶች ፥ 146 አርመኖች ፥ 63 ፈረንሣዮች ፥ 42 ኢጣሊያኖች ፥ 20 ጀርመኖች ፥ 13 ሁንጋሪያኖች ፥ 15 ቱርኮች ፥ 13 ስዊሶች ፥ 14 እንግሊዞች ፥ 11 ግብ ጾች ፥ 10 ሶሪያውያንና ሊባኖሳውያን ፥ 8 አፍጋኒስቶች ፥ 7 ፖርቱጋሎች፥ 6 ሩሲያኖችና ቡልጋሪያኖች ፥ 6 ካውካሶች ፥ 5 አሜሪካኖች ፥ 3 አው ስትሪያኖች ፥ 2 ቤልጅጎችና 1 የዛሬው የሶቭየት ጆርጂያዊ ነበሩ ።

በአዲስ አበባ ከተማ የቤት ሥራ እየበዛ ሲሄድም ሕንዶችና አረ ቦች መግባት ጀመሩ ። ታላቁ ቤተ መንግሥት በሚሠራበት ጊዜ ቄልዲ እንዳያቸው “. . . . እነዚህ ሰዎች በሙሉ ከኤደን የመጡ ናቸው ። የሚከፈላቸውም ጥሩ ደሞዝ ነው ። ምግባቸውንም ከንጉሡ ስለሚያገኙ ደሞዛቸውን በሙሉ ተቀማጭ ያደርጉታል. . . .” ብሏል ። አርመኖች እየበዙ በሄዱ ጊዜ የኦቶማን ሡልጣን አብዱል ሐሚድ ዳግማዊ ምኒልክ አርመኖችን ከኢትዮጵያ እንዲያስወጡ ጠይቋቸው ነበር ። ምኒልክም “የማትፈልጋቸው አርመኖች ካሉህ ሁሉንም ላክ ልኝ” ብለው መለሱለት ይባላል ። ግሪኮችም በቤት ሥራ ፥ አረቄ በማውጣት ፥ የእህል ወፍጮ በማቋቋም ፥ ዘይት በመጭመቅና በዳቦ መጋገር ሥራ ተሰማሩ ።

ቦየስ የተባለ ታሪክ ፀሐፊ እንደገለፀው “. . . .በምሥራቅ አፍ ሪካ ባሉ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች ተዘዋውሬ አዲስ አበባ ስመጣ አዲስ የሆነ ነገር አጋጠመኝ ። ይህም አንድ አፍሪካዊ ፤ ነጮችን እያዘዘ ቤት ሲያሰራ ማየቱ ነው. . . .” ብሏል ። ቦየስ እንዳለው ኢትዮጵያውያኖች ፈረንጆችን የሚጠሩዋቸው “ባርያዎች” እያሉ ነበር ።

እውቅ ነጋዴ የነበረው ከአርመኖች ዲክራን አቢያን ነው ። ዲክ ራን የመጣው ከካይሮ ነው ። ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ የነበረ አንድ ምዕመን ካይሮ ሲደርስ አርመኖች ኮሙኒቲ ዘንድ ሄዶ ምኒልክ ጥበብ የሚያውቅ የውጭ አገር ሰው እንደሚፈልጉ ከነገረ በኋላ በወርቅና በአልማዝ ሥራው የታወቀው ዲክራን ወደ ኢትዮጵያ መጣ ። ምኒልክና ጣይቱ የነገሡበትንም ዘውድ የሠራው እሱ ነው።

በ1889 ዓ.ም. በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መሐል የወዳጅነት ውል ከተፈረመ በኋላ የሕንድ ነጋዴዎች አዲስ አበባን ሞሏት ። የመጀመሪያዎቹም የሕንድ ነጋዴዎች በታኅሳስ ወር 1891 ዓ.ም. በብዛት ሆነው ገቡ ። የእነኚህም ሕንዳውያን ዋና ንግድ ጨርቃ ጨርቅ፣ ሽቶና ቅመማ ቅመም የመሳሰሉ ነበሩ ።

ከግሪኮች የታወቁትና የቆዩት ነጋዴ ጊዮርጊስ ናቸው ። ሽማግ ሌው ሙሴ ጊዮርጊስ በአገሪቱ ውስጥ በመቆየታቸው ባላምባራስ ተብለው ተሹመዋል ። ባላምባራስ ጊዮርጊስ በካይሮ ሙዚቃ አስተማሪ ነበሩ ። በ1875 ዓ.ም. ገደማም የአጤ ምኒልክ ልብስ ሰፊ ሆነው ነበር ። በአዲስ አበባ ከተማ ካሉት ሱቆች ሁሉ የባላምባራስ ጊዮርጊስ ሱቅ ጥበባዊ ዕቃዎች የሚሸጡበት ሱቅ ነበር ። ግሪኮችና ኢጣሊያኖችም በቤት ሥራው ተግባር ላይ ተሠማርተው ነበር ። ዜርቮስ እንደሚገል ፀው በቤተ ክርስቲያንና በድልድይ ሥራ የተሠማሩ ግሪኮች ፡ ሕንዶ ችና ኢጣሊያኖች ነበሩ ። ግሪኮችና ኢጣሊያኖች በርካሽ ዋጋ ይሠሩ እንደነበረም መረብ ይገልጣል ።

የውጭ አገር ሰዎች እየበዙ መሄድ ምኒልክን ያሳስብ ጀመር ። ኤርትራን ፡ አሰብንና ጂቡቲን ነጮች ማረፊያ መሬት እንገዛለን እያሉ እንደወሰዱ ምኒልክ ያውቁ ነበርና ማንኛውም መሬት ያለእሳቸው ፈቃድና ትዕዛዝ የውጭ አገር ሰው እንዳይገዛ ለሚኒስትሮች ትዕዛዝ አሳለፉ ። በትዕዛዙ መሠረትም ሳይፈጸም በመቅረቱ አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ ሆነ ። በዚህም ምክንያት የማያጣላና የማያቀያይም የውጭ አገር ሰዎች ንጉሡ ብቻ ሲፈቅዱ መግዛት እንዲችሉ የሚል አዋጅ ጥቅምት 20 ቀን 1900 ዓ.ም. አወጁ ።

ምኒልክ በእሳቸው ፈቃድ ብቻ የውጭ አገር ሰዎች መሬት መግ ዛት መቻላቸውን ካወጁ በኋላ ፡ ብዙ የውጭ አገር ሰዎች አጉረመረሙ ።

የጥቅማቸውን መነካት እንደመብት መነካት አድርገውም ያስወሩ ጀመር ፡፡ ምኒልክ ግን ለማንኛውም ሐሜታ ፍንክች አላሉም ፡፡ ፈረንሣዊው ሚሼል እንደጻፈው "....መሬት በሙሉ የንጉሠ ነገሥቱ ነው ፡፡ የሚሸጡም ፥ የሚሰጡም ንጉሡ ናቸው ፡፡ ይህም ቢሆን ፥ ማለት የሰጡትንም ሆነ እንዲሸጥ የፈቀዱትን መሬት ባስፈለገ ጊዜ መውሰድ ወይም መከልከል የሚችሉበት ሥልጣን አላቸው....ያለ ንጉሡ ፈቃድ መሬት መግዛት አይቻልም ፡፡ ቢገዛም ደግሞ ንጉሡ መልሰው መውሰድ ይችላሉ...." ብሏል ፡፡

ብዙ የጦር መሣሪያ ወደ ሸዋ በማስገባቱ ከምኒልክ ወዳጅ የሆነው ፈረንሣዊው ነጋዴ ቦሌሊ እንደገለጸው "....ንጉሡ አቃቂ ወንዝ አጠገብ መሬት ሰጥተውኛል ፡፡ መሬት ለመስጠትም ሥልጣን ያላቸው ንጉሡ ብቻ ናቸው ፡፡ ንጉሡ በሰጡኝ መሬት ላይ የፈለገኝን ለመሥራት ሙሉ ነፃነት አለኝ ፡፡....ጧት ለአንድ ወይም ለሁለት ሰዓት ያህል በመሬቴ ላይ ፈረሶቼን ሳለማምድ እቆያለሁ ፡፡ አደን አድናለሁ፥ አሳ አጠምዳለሁ ፡፡....ግን በተሰጠኝ መሬት እንድገብርበት ስላልተፈቀደልኝ መሬቱ የኔ ለመሆኑ ምንም ዋስትና የለኝም...." ብሏል ፡፡

እ.ኤ.አ. በ1901 ዓ.ም. ገብቶ እስከ 1903 ዓ.ም. ድረስ በአዲስ አበባ የቆየው ደችሰን ፋርኔት የተባለ ሚሽን እንደጻፈው "...እንዳጠናነው በአቢሲኒያ ውስጥ ኤሮጳውያኖች መሬት እንዲገዙ አይፈቀድም ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ቤት የተሠራበትም ሆነ ያልተሠራበት ቦታ ያላቸው ኤሮጳውያን አሉ ፡፡ እነኚህ ኤሮጳውያኖች መሬቱን ያገኙት ከንጉሡ በስጦታ ነው ፡፡....ንጉሡ መሬት የመስጠትና መልሶ የመውሰድ ሥልጣን ቢኖራቸውም መሬቱን መልሰው የሚወስዱት ያ ኤሮጳዊ ወንጀል ሲገኝበት ነው እንጂ ጨዋ ከሆነ አይነኩበትም ፡፡ መሬቱን ቢወስዱም በላዩ ላይ ለተሠራው ሥራ ካሣ ይከፍላሉ ፡፡...." ብሏል ፡፡

ፈረንሣዊው ሁጅ ለሩ በመጽሐፉ ንጉሡ መሬት በነፃ እንደ ሰጡትና እሱም መሬቱን በገንዘቤ እንድገዛ ይፍቀዱልኝ ቢላቸው "በነፃ ብሰጥህ ለምን በገንዘቤ ልግዛ ትላለህ አሉኝ ፡፡ እኔም 'በገንዘብህ የገዛኸው ስላልሆነ ልትሸጠውም ሆነ ለሌላ ልታውለው አትችልም' የሚሉኝን ሰዎች አፍ ለማዘጋት ብዬ ነው አልኳቸው ፡፡ ምኒልክም 'በአገርህ ልዑል መሆንህን አውቃለሁ ፡፡ የኛ አገር ፍትሐ ነገሥት ልዑሎች መሬት ይሸጡ አይልም ፡፡ ደግሞ ያገሬ መሬት ባለቤቱ ሌላ ነው ፡፡ ጋሎች ፥ አማሮችም ካባቶቻቸው እየተቀበሉ ያቆዩት መሬት ነው ፡፡...ስለዚህ መሬቱ የሁሉም ስለሆነ አይሸጥም ፡፡ ማንም ሰው መሬቱን ሊሸጥ አይችልም ፡፡ መሬትን መሸጥም ፥ መስጠትም

የሚችለው የመሬቱ ጌታ ነው ። እስቲ ልጠይቅህ ፣ አንድ የእንግሊዝ ሰው ፈረንሣይ አገር መሬት ልግዛ ብሎ የሚጠይቀው በእንግሊዝ ሕግ መሠረት ነው ወይስ በፈረንሣይ ሕግ መሠረት?' አሉኝ ። እኔም በፈረንሣይ ሕግ መሠረት ነው አልኳቸው ። ምኒልክም ይሄ ከሆነ በአገርህ አንድ የውጭ አገር ሰው አንዷት የመሬት ቁራጭ በገንዘቡ እንዲገዛ ብለው ንጉሣችሁ ይፈቅዱለታል?' አሉኝ ። እኔም የለም አንድ ሰው ባለው መሬት ግብር ይከፍላል እንጂ በኤሮጳ አንዱ ባንዱ አገር መሬት የለውም አልኳቸው ። ምኒልክም 'እዚህም እኛ ጋ ልክ እንደ ኤሮጳ ነው ። አንድ የውጭ ሰው አበሻ ውስጥ መሬት ማግኘት የሚች ለው በአበሻ ሕግ መሠረት ነው ።. . . .የውጭ አገር ሰዎችንም መሬት እንድትገዙ ከፈቀድኩና ባለመሬት ከሆናችሁማ ለኔ ምን ቀርቶኝ እገዛለሁ አሉኝ. . . .'' ይላል ።

ሬይ የተባለው ታሪክ ፀሐፊ ደግሞ ". . . .ማንም ኤሮጳዊ በአበሻ ውስጥ መሬት እንዲገዛ አይፈቀድለትም ። በኪራይ ግን 30 ዓመት ድረስ መያዝ ይችላል ። በልጅ ኢያሱ ዘመን አንዳንድ የውጭ አገር ሰዎች መሬት መግዛት ጀምረዋል ። በ1908 ዓ. ም. (እ. ኤ. አ.) ምኒልክ ሽባ (ፓራላይዝ) ከመሆናቸው በፊት ግን ፣ እንኳን የውጭ አገር ሰዎች፣ አበሾችም ቢሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የግል የሆነ መሬት አልነበራቸውም ። ጠቅላላ ከተማው በንጉሡ ሥልጣን ሥር ነበር ።

"ምኒልክ ለአንዳንድ አበሾች በከተማው ውስጥ መሬት ሰጥተ ዋል ። የሰጡትም እንዲያለሙትና እንዲሠፍሩበት እንጂ የግላቸው እን ዲሆን አይደለም ። ንጉሡ እንደታመሙ መኳንንቱ ሁሉ የመሬት ሽሚያ ጀመረ ። በይዞታችን መሠረት እንገብር እያሉም የኢያሱን ሞግ ዚት ራስ ተሰማን ማስፈቀድ ጀመሩ ። አቡኑም ከመኳንንቱ ጋር እየ ተሻሙ የቤተ ክርስቲያን ቦታ እያሉ ይይዙ ጀመር ። ራስ ተሰማም በልጅ ኢያሱ የተሾሙበትን ቢትወደድ በሚለው ማዕረጋቸው እያ ተሙ መሬቱን ይሰጡ ጀመር ። በዚህ ሽሚያ መሐል የውጭ አገር ሰዎችም ገብተው መሬት ማግኘት ጀመሩ ። አሁን ደግሞ ነገሩን ወደ ነበረበት ለመመለስ "አበሻ ያበሾች ነች'' የሚል ፍልስፍና ተጀምሮ አል ።. . . .'' ብሏል ።

የውጭ አገር ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥ እየበዙ የሄዱበት ዋናው ምክንያት ለመግባትም ሆነ ለመውጣት ቁጥጥር ስላልነበረ ነው ። የውጭ አገር ሰዎችን እንደፈለጉ መግባትና መውጣት ለማስቀረትና አገሪቱ በሥነ ሥርዓት እንድትመራ የሚከተለው አዋጅ ታወጀ ።

## አዋጅ

እስከዛሬ ድረስ ቆንስሉ ሳይታወቅ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር
ብዙ ዓይነት የውጭ አገር ሰው አለ ። ስለዚህ ካሁን ቀደም በሌጋሲ
ዮን መዝገብ ያልተጣፈ የውጭ አገር ሰው ሁሉ ቆንስሉን አስታውቆ
በሌጋሲዮኑ መዝገብ ይጣፍ ።

ቆንስል የሌለው ግን እንደዚህ ቀደሙ ያለ ቆንስል አዲስ አበባ
መኖር አይችልምና ስለዚህ የሚያድርበትን ቆንስል ለይቶ ያስታውቅ።

ደግሞ ቆንስል ሳይኖረው ቀርቶ ዜግነቱን ወደ ኢትዮጵያ መን
ግሥት ማድረግ የሚፈልግ ሰው ግን ይኸንኑ ዜግነቱን ወደ ኢትዮ
ጵያ መንግሥት ማድረጉን የሚፈቅድለትን ወረቀት ከመንግሥቱ
ተቀብሎ ካመጣ በኋላ ፣ እንደ ደንቡ ከኢትዮጵያ መንግሥት መዝገብ
ይጣፋል ። እንደዚሁም ቆንሲሉን አስታውቆ በሌጋሲዮኑ ወይም በኢ
ትዮጵያ መንግሥት መዝገብ ለመጣፍ ከዛሬ ጀምሮ እሶስት ወር
ድረስ ቀን ሰጥተናል ። ከዛሬ ጀምሮ እሶስት ወር ድረስ እንደ ደንቡ
ከመዝገብ ሳይጣፍ የቀረ ሰው ግን የኢትዮጵያን መንግሥት ለቆ
መውጣቱ የታወቀ ይሁን ።

ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም አዲስ አበባ ተፃፈ ።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ለውጭ አገር ሰዎች የነበራቸው አስተያ
የት ከፍ ያለ ነበር ። ያደንቋቸዋል ፣ ያከብሩዋቸዋል ። አንድ ሰው ወስ
ለት ካለ ግን የተከበረውን ያህል ይዋረዳል ። ብዙዎቹ የውጭ አገር
ሰዎች ይህን የምኒልክን ጠባይ እያብራሩ ገልጸውታል ። በአዲስ አበባ
ከተማ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የነበረው የውጭ አገር ሰዎች አቀ
ባበል እንዴት እንደነበር ከኸርበርት ቪቫን መጽሐፍ በጥቂቱ እንመ
ልከት ።

“. . . . ሰኞ ከሰዓት በኋላ በአሥር ሰዓት ተኩል ከንጉሡ ጋር
እንደምገናኝ ተነገረኝ ። ምኒልክ ከጧት 11 ወይም 12 ሰዓት ሥራ ይጀ
ምራሉ ። በጥቂት ሰዓታት ውስጥም ሥራቸውን ይጨርሳሉ ። በእንግ
ሊዝ ለጋሲዮን ውስጥ አንድ ቤይሩት የተማረ አበሻ ስላለ እሱን ለአ
ስተርጓሚነት ይገኔ ተጓዝን ። አበሻው አስተርጓሚ ረጅም ጭራ ባለው
ነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ፣ ቢጫ ቦት ጫማ አድርጎ ፣ ሰማያዊ ኮትና
ሐር ሸሚዝ ለብሷል ። እኔም በደካማዋ አሳዛኝ በቅሎዬ ተቀምጬ ፣
ያለኝን ልብስ ለባብሼ ፣ ካኪ ባርኔጣዬን አድርጌአለሁ ። ሁኔታዬም
እኔኑ ራሴን ያስቀኝ ነበር ።

‘‘. . . .ግቢው በረጃጅም እንጨት ታጥሯል ። አምስት ወይም ስድ ስት ርምጃ ስፋት ባለው በር ሥር አለፍን ። ከዚያ ውጭ በቅሎና ፈረስ የሚጠብቁ ብዙ ጭፍራዎች አሉ ።. . . .ሌላውን አጥር አልፈን ስንገባ ከበቅሎ እንድንወርድ ጠየቁን ። በእግራችን ወደሚቀጥለው ግቢ ወደሚያስገባው በር ሄድን ። ይህ በር ካለፍናቸው በሮች ሁሉ ረጅምና ሰፊ ነው ። በስተግራችን መቅደስ የመሰለ ከእንጨት የተሠራ ሕንፃ አለ ። የምኒልክ አዳራሽ ነው ። በበረንዳው ላይ የተለያዩ ሥዕ ሎች አሉ ። ግቢውን በሚያሳይበት አቅጣጫ በኩል ጥቋቁር አበሾች ቆመዋል ። ከነሱም አጠገብ የንጉሡ ወንበር አለ ። በእንግሊዝ ሊጋሲ ዮን አግኝቼው የነበረ አጋፋሪ ደረጃውን እየሮጠ ወርዶ መጣና እጄን ጨበጠኝ ። ከዚያም መምጣታችንን ለንጉሡ ለመንገር ተመልሶ ሄደ ።

‘‘ከካፒቴን ሀሪንግተንና ከኔ የመጣውን ስጦታ በሳጥን ከያዘው ሰውዬ ጋር ጥጋት ይዘን ቆምን ። ከኋላችን ያለው የፍርድ አዳራሽ ነው ። ከብ ሕንፃ ነው ። ንጉሡ ከበረንዳው ላይ ይሆኑና የቀረበላቸውን የፍርድ ጉዳይ ሁሉ የሚፈጽሙት ከዚያ ነው ።

‘‘ከቆምንበት በስተቀኛችን ያለው የግብር አዳራሽ ነው ። ረጅም ነው ። በታላላቅ የግብር ጊዜ እስከ 10,000 ሰዎች ገብተው ጥሬ ሥጋ ይበሉበታል ። ካለንበት ቦታ 20 ደቂቃ ያህል ቆየን ። ስንጠራ ትልቁን የሕዝብ አዳራሽ አልፈን ሄድን ። ሐር የለበሱ መከዳዎችን አየሁ ። ይህም ንጉሡ ነገሥቱ የውጭ አገር ሰዎችን የሚገናኙበት ቦታ ነው ። አለፍ ብሎ ያላለቀ ደረጃ አለ ። ደረጃውም ወደ ምኒልክ ልዩ በረንዳ የሚወስድ ነው . . . .ንጉሡ በእንጨት ወንበር ላይ እግራቸውን አጣ ምረው ተቀምጠው አየሁ ። በአልባሌ ሁኔታ የሚታዩ አበሾች አሉ ። . . . .የልጅ ልጃቸው ጥሩ ልብስ ለባብሶ ባዶ እግሩን ከንጉሡ ወንበር ኋላ ቆሟል ። ከኋላቸው ስዕሎች አሉ ። ከነኛ የተለያዩ ስዕሎች ውስ ጥም ደስ የሚል የፒኮክ ወፍ ስዕል አይቻለሁ ። በስዕሉ ነጫጭ ፈረ ሶች ፡ አበባዎች ፡ ዝሆኖች ሁሉ አሉ ።

‘‘. . . .የማስተዋወቅ ስርዓት አልተካሄደም ። እንደገባሁ ምኒልክ እጃቸውን ዘረጉልኝ ። እጅ መሳም እንደሚገባ ነግረውኝ ነበርና እጅ ንስቼ ያን የተከበረ እጅ በክንፈሬ ነካሁት ። ንጉሡም ደስ አላቸውና ‘‘እሺ’’ ሲሉ ሰማኋቸው ። መች መጣህ? ሲሉ ጠየቁኝ ። እኔም ሳልቆይ መልሱን ነገርኩ ። እንዲያው ወሬ ለመጀመር ነው እንጂ የጠየቁት መቼ እንደመጣሁ ያውቃሉ ። እንኳን በአዲስ አበባ በጠቅላላው በአገ ራቱ ውስጥ ያለው የአውሮፓውያን እንቅስቃሴ ዕለት በዕለት ሁኔታው ይነገራቸዋል ። አስተርጓሚውንም ስለኔ የተለያየ ጥያቄ ጠየቁት ። ለኔ እንዲያስተረጉምልኝም ጊዜ ይሰጡታል ። ከዚያ በኋላ አጠገባቸው

ወዳለ ወንበር ጠቆሙኝና እንድቀመጥ አዘዙኝ ። . . . .ስጦታ የተያዘ በት ሳጥን ቀረበ ። ከበፊቱ ለንጉሡ ምን ስጦታ እንደምሰጥ ከባድ አሳብ ይዞኝ ነበር ። ስጦታ ማምጣት ደግሞ ሥርዓት ነበር ። ኢትዮጵያውያ ንም ከብዙ ሺ ዓመታት ጀምረው እንደ ልምድ የያዙት ነው ። ስጦ ታው እንደግብር ይቆጠራል ። ኢትዮጵያውያን እንደ ግብር ቢቆጥሩ ትም የተሰጣቸውን ይቀበላሉ እንጂ አያስገድዱም ። እንደ ፈረንሣዩ አገር ጐብኚ አሻንጉሊት ሰጥቼ ንጉሡን እንዳላስቆጣ ተነግሮኛል ። ልጅ መሰልኩህ ወይስ የማላውቅ መሰልኩህ? ብለውታል አሉ ። ደስ ያለኝ ነገር እኔ ያመጣሁላቸው መውዜር ሽጉጥ ነው ። ይሄንንም ያመ ጣሁት ንጉሡ ጠመንጃና የቴክኒክ ዕቃ እንደሚወዱ ስላጠናሁ ነው ። የመውዜር ሽጉጥ ከተፈለሰፈበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ሰዎች ለምኒልክ እንዳመጡላቸው ሰምቻለሁ ። የእንግሊዙ ሚኒስትር የላኩት የተለየ ሽጉጥ ግን ምኒልክን በጣም አስደስታቸው ። ያላዩት ነበር ። ሽጉጡን ይዘው ለብዙ ደቂቃዎች ወደ በረንዳው እያነጣጠሩ ኢላማ መግባቱን ሲያዩበት ቆዩ ።

“. . . .ቀጥሎ የኔ ስጦታ የሆነውን መውዜር ሽጉጥ ሰጠኋቸው ። ምኒልክ ብዙ መውዜር ሽጉጥ ቢኖራቸውም እኔን ለማስደሰት ብለው በፈገግታ ተቀበሉኝና ደስ ብሏቸው ወደጐናቸው አሳልፈው ሰጡ ። ከዚያ በኋላ ስለሥራዬ ምን ያህል ጊዜ እንደምቆይ ፣ ስለዕድሜዬና ይህን ስለመሳሰሉ ጠንካራ ስላልሆኑ ጉዳዮች ሲጠይቁኝ ቆዩ ። የእሳቸው ሲያበቃ በተራዬ ደግሞ እኔ እንድጠይቃቸው ለአስተርጓሚዬ ነገ ሩት ። ታላላቅ ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን ለመጐብኘት እንድ ችል ፈቃድ ጠየኳቸው ። ምኒልክም ሁሉም ነገር ይቻላል ። አንተ ጨዋ ከሆንክ እፈለግህበት ቦታ ሁሉ ማንም ሳያቆምህ እየተዘዋወ ርክ እንድትጐበኝ ፈቃድ ይሰጥሃል አሉኝ ። ለእንግሊዝ ሕዝብ በኔ በኩል የሚልኩት መልዕክት አለን? አልኳቸው ። ንጉሡ ነገሥቱም ‘ንገራቸው ፡ ወዳጅነታቸውንና ድጋፋቸውን እፈልጋለሁ ። ይሄንንም እንደሚያደርጉ አምናለሁ ። አንዳንድ ሰዎችም ስለ እናንተ የሚነግሩኝ እውነት ሆኖ አላገኘሁትም ። እንግሊዞች ተስፋ ይሰጣሉ እንጂ በቃላ ቸው አይረጉም ይሉኝ ነበር ። ግን እራሴ እንዳገኘሁት የእንግሊዝ ሰው በቃሉ የሚረጋ ነው ። ለሰዎችህ ንገራቸው ፣ እነሱን ለማየት ደስ ይለኛል ። ግን ዋና ከተማዬ ድረስ ለመምጣት መንገዱ ሩቅ ነው” አሉ ። እኔም የእንግሊዝ ሕዝብ በጣም ደስ የሚለው እርስዎ በመሐሉ ቢገኙለት ነበር አልኳቸው ። ሳቁ ፣ ዓይናቸውንም ለጥቂት ጊዜ ጨፍ ነው ቆዩና ‘አገራችሁን ለማየት ብዙ ጊዜ አሳብ ነበረኝ ። ስለ መርከ ቦቻችሁ ፣ ስለ ፋብሪካዎቻችሁ ፣ ስለ ፍልሥፍናችሁ ሁሉ ሰምቻለሁ ። ጥሩ ጥሩ ፈረሶችና ውሻዎችም አሏችሁ ። . . . . ወደ እንግሊዝ አገር

ብሄድ ብዙ ጠቃሚ ነገሮችን እንደማገኝ አውቃለሁ ። ለአገሬም ብዙ የሚጠቅሙ ነገሮችን አመጣ ነበር ። አየህ ፤ አሁን ከሐረር ጋር የምንገናኝበት ስልክ አሠርቻለሁ ። አንድ ቀን ደግሞ የባቡር ሐዲድ ይኖረናል ። ግን እንዴ ጉዞ ብጀምር ብዙ የምጐበኛቸው ቦታዎች አሉኝ ። ለምሳሌ ሕንድ አለ ። በዚያም ያለው ዝሆን ለማዳ ሆኖ እንደ አህያና እንደ በቅሎ እንደሚሠራ ነግረውኛል ። እኛ አሁን ብዙ ዝሆኖች አሉን ። ግን ማንም ለማዳ አላደረጋቸውም ። ለማዳ ለማድረግም ዘዴውን ማወቅ እፈልጋለሁ' አሉኝ ።

"....አርባ ደቂቃ ያህል ከምኒልክ ጋር ከተጫዋወትን በኋላ ለተደረገልኝ ከፍተኛ ርዳታ በአስተርጓሚው አማካይነት አመሰገንሁ ። ምኒልክም እኔን በማየታቸው መደሰታቸውንና የሚያስፈልገኝ ነገር ቢኖር ለእሳቸው እንድነግራቸው ነግረውኝ እጅ ነስቼ ወጣሁ ። ...."

ከእንግሊዝ መንግሥት የተላከው እንግሊዛዊው ከንት ግሊከን ደግሞ ስለምኒልክ እንግዳ አቀባበል የሚከተለውን ጽፏል ። "....በማግሥቱ ዘጠኝ (በኛ አቆጣጠር ከጧቱ ፫) ሰዓት ከምኒልክ ጋር የምንገናኝበት ጊዜ ስለነበር ሚስተር ኢልግ እና ግራዝማች ዮሴፍ አብረው መጡ ። ሁለቱም ሙሉ የማዕረግ ልብስ ለብሰዋል ። የኢትዮጵያ ኮከብ የሚባለውንም ኒሻን አድርገዋል ። ኮከቡ ከወርቅ የተሠራ ነው ። ያንገት ማጥለቂያው ማተቡ ባገሬቱ ሰንደቅ ዓላማ በሆነው ቀይ ፣ ቢጫ ፣ አረንጓዴ ጨርቅ ተከቧል ።....ከእነሱ ጋር የመጣውም ሠራዊት በሺ የሚቆጠር ነው ። የሕዝቡ አለባበስ ቀይ ጥለት ያለው ነጭ ሸማ ነው ። በጦርነት ተካፋይ የነበሩት ሰዎች ነጭ ሐር ሸሚዝ ለብሰዋል ። በየቦታውም የኢትዮጵያ ዓላማ የሆነው አረንጓዴ ፣ ቢጫ ፣ ቀይ ባንዲራ ይውለበለባል ። አጀቡ ለሁለት ተከፍሏል ። በእያንዳንዱም ክፍል ከሶስት እስከ 4,000 ሰዎች አሉበት ።....አፈንጉሡ ወይም የፍርድ ሹሙ ጨዋ ሽማግሌ ሰው ናቸው ። ሰፊ ጥቁር ባርኔጣ አድርገዋል ። ከባርኔጣው ሥር አረንጓዴ ሐር ጨርቅ አስረዋል ። ዙሪያውን በወርቅ ክር የተዘመዘመ ጥቁር ሐር ካባ ለብሰዋል ። ከውስጥ ውብ የሆነ ወይን ጠጅ መልክ ያለው ሸሚዝ ለብሰዋል ። ቀይ የሐር ሰገባ ያለው ረጅም ጐራዴ ታጥቀዋል ። ተከታያቸው ጠመንጃቸውን እንግቦ በወርቅ ያጌጠ ጋሻቸውን ይዟል ። በጠቅላላው ውብ ናቸው ።

"ግሩም የሆነች በቅሎ ዙሪያውን በወርቅ ክር የተዘመዘመ ሐር ላብስ ለብሳ ከምኒልክ ዘንድ በተላከችው በቅሎ ሚስተር ሮድ ተቀምጦ በብዙ አጀብ ታጅበን ወደ ቤተ መንግሥት ሄድን ።....ድምፁ የቀረበን ሄደ ። በመጨረሻም አየናቸው ። የንጉሡ ነጋሪት መቺዎች ናቸው ። ነጋሪት መቺዎቹ 15 ወይም 20 ይሆናሉ ። እነኚህ ሻንቅሎች

ነጋሪት መቺዎች መሬት ላይ መደዳውን ተቀምጠዋል ። ረጃጅም ቀይ ሽንትር ያለበት ሸሚዝ ለብሰዋል ። እያንዳንዱ ሁለት የከረቦ መምቻ ዱላ ይዟል ። ከፊታቸውም መጠነኛ የሆኑ ከረቦዎች ከመሬት ላይ ተቀ ምጠዋል ። የያዙዋቸው የከረቦ መምቻ ዱላዎች አንደኛው ወፍራም ሲሆን ፡ እንደኛው ቀጭን ነው ። የዱላዎቹ መቅጠንና መወፈር ከረቦው በሚመታበት ጊዜ ሁለት የተለያዩ ድምፆችን ያወጣሉ ።

“. . . .የመጀመሪያውን በር ስንገባ ጦር የያዙ ብዙ ወታደሮች ሁለተኛው በር ድረስ ቆመዋል ። ሁለተኛውን በር እንዳለፍን 70 የሚሆኑ መድፎች ግቢው ውስጥ ተጠምደዋል ። መድፎቹ ያሉት ከትልቁ አዳራሽ አጠገብ ነው ። ከመድፎቹ ውስጥ አርባ ዘጠኙ ከአ ድዋው ጦርነት የተማረኩ ናቸው ። በእያንዳንዱ መድፍ አጠገብ መድፍ ተኳሾች ቆመዋል ። መድፍ ተኳሾቹ መደቡ አረንጓዴ ሆኖ በሐር የተጠለፈ ልብስ ለብሰዋል ። መልዕክተኞቹ በሙሉ በቂ ብርሃን ከሌለበት አዳራሽ ውስጥ ገባን ።

“. . . .ንጉሠ ነገሥቱ ከአዳራሹ መጨረሻ ካለው ዙፋናቸው ላይ ተቀምጠዋል ። ዙፋኑ በሐር የተሸፈነና በጥሩ ምንጣፎች ያጌጠ ነው ። ንጉሡ ግንባራቸው ላይ የተለመደውን ነጭ ሻሽ አስረዋል ። ሻሹ ከኋላቸው በኩል ክፍት ሰማያዊ በሆነ ማበጃ ታብቶ ማበቻው ጨርቅ ከጀርባቸው ላይ ወርዷል ። .... ማንጠልጠያው ባንገታቸው ዙሪያ ዞሮ ደረታቸው ላይ የሚታየው ከሩሲያ ካተሪይን የተሸለሙት ታላቅ የክ ብር ኒሻን ነው ።

“ንጉሡ በሚያስገርም ሁኔታ በጥልፍ ባጌጠ መከዳ ላይ ተቀም ጠዋል ። ጠንካራ በሆነ እጃቸው ከሚስተር ሮድ ጋር ተጨባበጡ ። ጠቆር ብሎ ፈንጣጣ በጠቀጠቀው ፊታቸውም ፈገግታ አሳዩ ። ከንግሥት ለተላከነው ልዩ መልዕክተኞችም ካንገታቸው ቀልበስ ብለው እጅ ነሱንና እንድንቀመጥ አዘዙን ።

“በስተቀኛቸው አዲስ አበባ ውስጥ የሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች ቆመዋል ። ከእነሱም ውስጥ የኦርሊንስ ልዑል ሄንሪ ፡ ለቪኮንት ዶ ፖንኬንስ ፡ ሙሴ ሙሪኮን ፡ የፖስታ ቤት ዲሬክተሩ ሙሴ ሞንዶን ፡ ሙሴ ቦንቫሎ ፡ ኰሎኔል ሊዎንቴቭ እና ሁለት የሩሲያ መኰንኖች የኮሳክ ልብስ ለብሰው ቆመዋል ። ሙሴ ሳቡሬ እና ብዙ ሌሎች ኤሮ ጳውያንም ቆመዋል ። በጠቅላላው 15 ያህል ይሆናሉ ። አብዛኛዎቹ የቆሙት ኤሮጳውያን አጊጠውና መዳሊያዎቻቸውን አድርገው ነው ።

“ሙሴ ኢልግ አማካሪ እንደመሆኑ ከምኒልክ ቀኝ ጐን ቆምዋል ። በስተግራቸው በኩል ልዑላን ፡ የየአውራጃ ገገር የሆኑት ራሶች ፡ ደጃዝ

ማቾች ፡ ቀኛዝማቾች ፡ ግራዝማቾች ቆመዋል ። ንጉሡ ዘንድ ጢጋ ብለው መሬት ላይ የተቀመጡት የሚቴ የቴዎድሮስ ልጅ ራስ መሸሻና ከጥቂት ዓመታት በፊት የምኒልክን መንግሥት ለመገልበጥ ተነስተው ያል ተሳካላቸው ራስ ሥላሴ ነበሩ ። በአዳራሹ ዙሪያ ክብ ፡ የጋላ ባህል ልብስ የለበሱ ብዙ ሰዎች ቆመዋል ።

"እንደልማዳቸው ከንጉሡ በስተኋላ በወርቅ ክር የተጠለፈ ቀይ ዣንጥላ ተይዟል ። የንግሥት ጣይቱ የወንድም ልጅ ደጃች ጉግሣ ትልቅ ጭራ ይዘው ከንጉሡ በስተግራ ቆመዋል ። ንጉሡ አስተርጓሚያቸውን የሲናን ጠርተው ከፊት ለፊታቸው ለተቀመጥነው መልዕክተኞች እንኳን ደህና መጣችሁ የሚል ቃል ተናገሩ ።

"ንጉሡ ይህን ቃል ሲናገሩ ከመልዕክተኞቹ ኋላ የቆሙት የሕንድ ወታደሮች በተጠንቀቅ ሲቆሙ ከውጭ መድፍ ይተኮስ ጀመር ። በዚህ ጊዜ ሁላችንም ተነስተን ቆምን ። ወዲያውኑ ንጉሡ ነገሥቱ እንድንቀመጥ ጠየቁን ። ከዚህ በኋላ ሚስተር ሮድ በእንግሊዝኛ ንግግር ማድረግ ሲጀምር አስተርጓሚያችን ወልደ ሃይማኖት ቃል በቃል ይተረጉም ጀመር ።

"ሚስተር ሮድ ያደረገው ንግግር እንደሚከተለው ነበር ። ለግርማዊነትዎ የተላከውን ደብዳቤ ከታላቋ የእንግሊዝ ፡ የአይርላንድና የሕንድ ንግሥት ከሆኑት ከገርዩ ያመጣሁትን ደብዳቤ አቀርባለሁ ። ንግሥታችን 60 የደስታ ዘመን አሳልፈዋል ። ከማንኛውም ዜጋና ሕዝብ ጋር በሰላምና በወዳጅነት ቆይተዋል ። ለዚሁ ለታላቅ ወዳጅነትና በሰላም አብሮ ለመኖር የሚያስችለውን ከንግሥታችን የተላከውን ልዩ መልዕክት ለግርማዊነትዎ ሳቀርብ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል ። በሁለቱ አገሮቻችን መሐል ፀንቶ የቆየው ወዳጅነት ለወደፊቱም እንዲቀጥል የንግሥታችን ምኞት ነው ብሎ ተናገረ ።

"ንግግሩ ካለቀ በኋላ እያንዳንዳችንን ከንጉሡ ጋር ሚስተር ሮድ አስተዋወቀን ። ከዚህ በኋላ ልንሄድ ተነሳን ። ከመሄዳችን በፊት ንጉሡ ነገሥቱ አዲስ በተሠራውና ነገ በሚከበረው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በዓል ላይ እንድንገኝ ጋበዙን ። ከሚስተር ሮድ ጋርም በቀጠሮ ለብቻ እንደሚነጋገሩ ነገሩት ። ከዚህ በኋላ እጅ እየነሳን ወጣን ።

". . . .አንድ ቀን ግንቦት 6 ቀን ጧት ከንጉሡ ጋር ምሳ እንድንበላ ግብዣ መጠራታችንን የሚነግር መልዕክተኛ መጥቶ ነገረን ። በየሳምንቱ ሐሙስ የውጭ ሰዎችና መኳንንቶች ከንጉሡ ጋር ምሳ የሚበሉበት ቀን ነው ። ከቀኑ 11 ሰዓት (በኛ 5) ሲሆን ወደ ቤተ

መንግሥት የሚወስደን ብዙ አጀብ መጣ ። ከቤተ መንግሥት ስንደ ርስ ንጉሡ በዙፋናቸው ተቀምጠዋል ። በስተቀኛቸው ለስምንት ሰዎች የሚበቃ በኤሮጳውያን ይዞታ የተዘጋጀ አንድ ጠረጴዛ አለ ።. . . .በጠረ ጴዛው አጠገብ እንድንቀመጥ ተነገረን ።. . . .ግሩም የሆነ ምግብም ቀረበልን ። ኃይለኛ ጠጅና አረቄም ታደለ ። ምኒልክ በሀገር ትራስ በተመላው ዙፋናቸው ተቀምጠው የአበሾችን ምግብ ይበላሉ ። መጀ መሪያ በሀር ጨርቅ የተሸፈነ ትልቅ መሶብ መጣና ከፊታቸው ካለው ጠረጴዛ ላይ ተደረገ ። ከመሶቡ አጠገብ በአበባ ማስቀመጫ ብዙ አበባዎች ተደርገው ተቀምጠዋል ። መመገብ እንደጀመሩ መሳፍንቱ ፣ ሚኒስትሮች ፣ ቀሳውስት ፣ የጦር አዛዦች እየገቡ መሬት ላይ ተቀመጡ። ለንጉሡ የቅርብ የሆኑና የቅርብ ረዳቶቻቸው ከንጉሡ አጠገብ ተቀም ጠው በመሶብ ፣ በሰሃን ከንጉሡ ምግብ እየወጣላቸው ይበላሉ ። ለእያ ንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ጠጅ በሐር ጨርቅ እየተሸፈነ ነው ። . . . .ንጉሡ ምግባቸውን በልተው ካበቁ በኋላ ሲጃራ እንድናጨስ ፈቀዱልን ። በንጉሥ ዮሐንስ ጊዜ ትንባሆ የሚያጨስ ሰው ከንፈሩ ይቆረጥ የሚል አዋጅ ስለነበር ፣ አሁን ያ ቀርቶ ንጉሡ ምኒልክ እንድ ና ጨስ በመፍቀዳቸው አገሪቱ ወደ ዘመናዊ አስተዳደር ማምራትዋን አወቅን ።. . . .ምኒልክ እያጨሱም ። እጫሽ እንዲበዛም እያበረታቱም። ግን የኤሮጳን እንግዶች በሚቀበሉበት ጊዜ ወይም ሲጋብዙ ፣ አብል ተው አጠጥተው እንዲያጨሱ ይፈቅዳሉ ። ሲናገሩም በልተው ፣ ጠጥተው ማጨስ ስለሚፈልጉ እንደ አገራቸው ልማድ ይሁን ይላሉ ።

"....ከዚህ በኋላ ከፊታችን ያለው መጋረጃ ተገለጠ ። ወዲያውኑ አዛዦቹ በትልቁ አዳራሽ ረጃጅም የመመገቢያ ሳጠራ ይዘረጉ ጀመር ። በእያንዳንዱ መመገቢያ መሐልም 6 ጫማ ስፋት ያለው ባዶ ቦታ አለ ። ዝግጅቱ ሲያልቅ በሩ ተከፈተ ። ከዚያም በሹሙ አማካይነት ሰው ይገባ ጀመር ።. . . .በእያንዳንዱ መመገቢያም አሥር አሥር ሰዎች ይቀመጡ ጀመር ። የበሰለ ሥጋ ታደለ ። በትልልቅ ብርሌም ጠጅ ተሰጠ ። በሩብ ሰዓት ውስጥም ግብሩ አለቀ ። ባዶ የሆኑት ብርሌዎች እንደገና ይሞሉ ጀመር ። ሹሙ ሲያዝ የበሉት ባንድ በር ሲወጡ ፣ ያልበሉት በሌላ በር ገቡ ። አዳራሹ ሲሞላ በሩ ተዘጋ ። እንደ መጀመሪያው ሁሉ አሁንም የገባው 500 ሰው ይሆናል ።. . . .እንዲህ እያለ አራት ጊዜ ግብሩ ተደጋገመ ። ግብሩንም የተጋበዘው 2000 ሰው መሆኑ ነው ።

". . . . ግብሩ አልቆ ከመውጣታችን በፊት ምኒልክ ከሚስተር ሮድ እና ከጊንቺንግ ጋር ጭውውት ጀመሩ ። ጭውውቱም በኢትዮጵያ የእባብ መርዝ መድኃኒት ስለሌለ ፣ የእባብ መድኃኒት እንዲያስመጡላ ቸው ነበር ። በቤተ መንግሥቱ የእባብ መድኃኒት ስላለ ፣ ሕዝቡ በተነ ከሰ ጊዜ ወደ ቤተ መንግሥት ይመጣል ። ብዙው ግን መምጣት ስለ



በምኒልክ ግብር ላይ ለውጭ አገር ሰዎች ምግብ በጠረጴዛ ይዘጋጅላቸው ነበር ። (በአገር ሰዓሊ የተሳለ)

ማይችል ፤ በየቦታው የእባብ መድኃኒት ለሕዝቡ እንዲደረግለት መፈ ለጋቸውን ምኒልክ ጠየቁ ። እነ ፔንቺንግ ስለ ጀርሞች ነገሩዋቸው ። ንጉሠ ነገሥቱ ለሳይንስ ከፍተኛ ስሜት ስላላቸው ፤ በማግሥቱ ሚስተር ሮድ ማይክሮስኮፕ ሰጣቸው ። ንጉሡም በዚያ ለመጀመሪያ ጊዜ ጀርም አይተው በጣም ተደሰቱ ። ሌሎች ፍልሥፍናዎችንም ለማየት እንደ ሚመኙ ነገሩት ። ሮድ ፤ ማይክሮስኮፑን ከመስጠቱ በፊት ይህን ነገር ካመጣሁት ቆይቼ ነበር ፤ ግን የጥንቆላ ነገር ነው ስላሉኝ ፈርቼ አቆ የሁት ቢላቸው ፤ ምኒልክ በጣም ስቀው እውነትህን ነው ፤ በአጤ ዮሐ ንስ ጊዜ ቄሶች ሁሉን ነገር አይቀበሉ ስለነበር ከባድ ችግር ነበር ። አሁን ግን ሁሉም ነፃ ሆኖ በነፃ እንዲገባ ደንብ ወጥቷል አሉት ።. . . . ሲል ጽፏል ።

በካርቱም ባንክ ለችግር ጊዜ ብለው ያስቀመጡት ቡልዮን የወ ርቅ ወይም የብር ሀብት ነበረ ። ስለዚሁ ጉዳይ ማርገሪ ሲጽፉ “. . . .በኔም ጊዜ ሆነ ከኔ በኋላ በኢትዮጵያ ጠላት ቢገባ ፤ ረሃብ ቢነሳ ለኢትዮጵያ የሚሰጥ ነው ።. . . .ብለው ነው ያስቀመጡት ።. . . .” ይላሉ ። ይህ ልኩን ያላወቅሁት ሀብት በ1928 የኢጣሊያ ጦርነት ጊዜ ለኢት ዮጵያ መንግሥት ተሰጥቷል ።

አጤ ምኒልክ በጥቁር አሜሪካውያን ዘንድ የተለየ መወደድና አክብሮት ነበራቸው ። ጥቁር አሜሪካኖች ምኒልክን የሚወዱበት ምክ ንያት ፤ በዘመኑ በጥቁር ዓለም የተገኙ ፤ በዓለም ዝናቸው የገነነ አኩሪ መሆናቸውን ስለሚሰሙና ስለሚያውቁም ነው ። በዚህ ብቻ ሳይሆን ፤ በአፍሪካ ውስጥ በነፃነቷ የምትኖር አገር ኢትዮጵያ ብቻ በመሆንዋ “አኩሪዋ ጥቁር ኮከብ” የሚል ስያሜም ሰጥተዋት ነበር ።

ዊልያም ኤች ኤሊስ የተባለ ሀብታም ጥቁር አሜሪካዊ ስለ ኢት ዮጵያ የተጻፉ መጻሕፍትን ከመላው ኤርጳ እየገዛ ስለ ኢትዮጵያ ያጠና ጀመር ። ኤሊስ ስለ ኢትዮጵያ ካጠና በኋላ ፤ ከምኒልክ ለመገናኘት ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ ጉዞውን ጀመረ ።

ኤሊስ ጉዞውን ከመጀመሩ በፊት ስለ ኤሊስ ብዙ የአሜሪካ ጋዜጦች ጽፈውለታል ። እ.ኤ.አ. በ1903 ዓ.ም. የታተመው ዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ “. . . .የኤሊስ የአበሻ ጉዞ ብዙ ገንዘብ ያስወጣው እንጂ ዝነኛ ያደርገዋል ። ስለዚያ አገር ሲያጠናም ዓመታት አልፎታል ። . . . .በእስፔይን ፤ በጀርመን ፤ በእንግሊዝና በሌሎችም ቋንቋዎች ስለ አቢሲኒያ የተጻፉ መጻሕፍት እየገዛ ሲያጠና ከርሟል ።. . . .” በማለት ሰፊ ሐተታ ጽፎለታል ።

ክሊቭሊንድ ፕሬስ የተባለው ጋዜጣ እ.ኤ.አ. መስከረም 23 ቀን 1903 ዓ.ም. በወጣው እትሙ “. . . .ባልና ሚስቱ ኤሊስና ወይዘሮ

ኤሊስ የአበሻው ንጉሥ የምኒልክ እንግዳ ሊሆን ነው ። ኤሊስ ለዝና ብሎ የሚያወጣው ወጭ በሚሊዮን የሚቆጠር ነው ።. . . .ለምኒልክ የሚወስዱትን ስጦታ ሲመርጡ ብዙ ጊዜያት አሳልፈዋል ። ኤሊስ ለምኒልክ ለመስጠት የሚፈልገው ተራ ስጦታ አይደለም ። ኤሊስ በዓለም ላይ ምኒልክን የሚወዳደር ሰው የለም ብሎ ስለሚያምን ፡ የተለየ ስጦታ ለመውሰድ ይፈልጋል ። ምኒልክ የጦር መሣሪያ እንደሚወዱ ስላጠና ፡ ከሚወስድላቸው ስጦታዎች መሐል አንዱ ሽጉጥ ነው ። ሽጉጡ በልዩ ትዕዛዝ የተሠራ ሲሆን ፡ ሙሉ በሙሉ በንፁህ ወርቅ ብቻ የተሠራ ነው ። ሽጉጡ በወርቅ ብቻ መሠራቱ ሳይሆን ፡ እጀታውና አንዳንድ ክፍሉ በአልማዝ ፈርጥ ያጌጠ ነው ።. . . .ጥቁሩ ኤሊስ ለጥቁሩ ንጉሥ ከፍተኛ አክብሮት አለው ። ከቤቱ ለሚሄዱ ወዳጆቹ ሁሉ ለምኒልክ የሚወስደውን ሽጉጥ እያሳየ 'እናንተ ነጭ አሜሪካኖች ትንቁናላችሁ እንጂ እኛ ጥቁሮች ትልቅ ሕዝቦች ነን ። ለአሁኑ የጥቁር ትውልድ ማስረጃ የሚሆኑም ፡ ምናልባት ሳይንቁት የሚቀበሉኝ ቢሆን ይሄን ከወርቅና ከአልማዝ ያሠራሁትን ሽጉጥ እንዳቅሜ የማበረክትላቸው ታላቁ ንጉሥ ምኒልክ ናቸው ።. . . .ይላል ። አበሻ አገር ለመድረስ ግን ጉዞው ከባድና አስቸጋሪ ነው ።. . . .'' በማለት በሰፊው ጽፎአል ።

ኒውዮርክ ዎርልድ የሚባለው ጋዜጣ እ.ኤ.አ. ሰኔ 27 ቀን በወጣው እትሙ ''የቱክሳሱ ጥቁር ጉዞውን ጀመረ'' በሚል ርዕስ ይነሳና ''. . . .ወደ አፍሪካ በሚያደርገው ጉዞ ለንጉሥ ምኒልክ የሚሰጠው ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች ብቻ በአምስት ታላላቅ ሣጥኖች ውስጥ ይዟል ።. . . .'' በማለት ሰፊ ሐተታ ጽፎአል ።

ኤሊስ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ወደ አገሩ ተመለሰ ። እ.ኤ.አ. ጥር 1 ቀን 1904 ዓ.ም. የወጣው ኒውዮርክ ታይምስ ስለ ኤሊስ ጉዞና መመለስ ሰፊ ሐተታ ጽፎ ነበር ። በሐተታው ውስጥ ኤሊስን አነጋግሮ የሰጠውን መልስ ሁሉ አስፍሮለታል ። ኤሊስ ለጋዜጣው በሰጠው መልስ በምኒልክ ዘንድ ስላጋጠመው ደስታ ፡ በቤተ መንግሥቱ ስለ ሚበላው ግብር ከገለጸ በኋላ ፡ ''. . . .በአዳራሹ ውስጥ ካሉት መኳንንቶች ጋር ምኒልክ ካስተዋወቁኝ በኋላ ፡ ንግግር እንዳደርግ ተጠየቅሁ ። ኔም ቆሜ ስናገር 'በሞንሮኤ ፍልስፍና መሠረት አሜሪካ ለአሜ ካውያን ነች ፡ በምኒልክ ፍልስፍና መሠረት ደግሞ አፍሪካ ለአፍ ካውያን ፡ ኤሮጳም የኤሮጳውያን የሚሆኑበት ጊዜ ቅርብ ነው እንዳ ኩ ፡ ምኒልክ እጄን ጨብጠው ያዙና እንባ ባቀረረው ዓይናቸው እያ ኝ 'ይሄን ያሁኑን ንግግርህን ድገመው' ብለውኝ ደገምኩ ። ከግብሩ ኋላ ከምኒልክ ጋር ወደ እልፍኝ አዳራሻቸው ሄደን ። እዚያም ስለ ሜሪካ ታላላቅ ሰዎችና ለአሜሪካ ምን እንደሠሩ እንዳሜውቁቸው በየቁኝ ። እኔም ዋሽንግተን ፡ እንዴት አሜሪካን ከእንግሊዝ ነፃ አወጣ ።

ሊንከን ጥቁሮችን ነፃ ከማውጣቱም በላይ ፣ የአገሪቱን አንድነት አስ ከበረ ። ሩዝቤልት ደግሞ አንድነታችን እንዲጠነክር አደረገ ብዬ እንደ ተናገርኩ 'ጐበዞች ናቸው' አሉኝ ምኒልክ ። 'ጐበዝ ሰው እወዳለሁ ። ንጉሶች ሁሉ እንደ እናንተ ሩዝቤልት ጐበዝ ቢሆኑ እንዴት ጥሩ በሆነ ነበር ። ሁልጊዜ ጦርነት የሚፈልግ ንጉሥ ሰይጣን ይጠጋውና በጐቹን ሰይጣን ይሰርቅበታል' አሉኝ ። የሩዝቤልትን ፎቶግራፍ ሰጠ ኋቸውና ካዩ በኋላ ፡ 'አንተ ያልነገርከኝ አንድ ጥቁር ሰውዬ በእናንተ አገር አለ ። አንድሪው ካርኒጌ የሚባለውን ጥቁር አሜሪካዊ አታውቀ ውም ? እኔ ስለሱ ብዙ ሰምቻለሁ ። እግዚአብሔር በረከቱን ያሳድርበ ትና እንደሱ ያለ ጐበዝ ሰው እወዳለሁና ፎቶግራፉ እንዳለህ አሳየኝ' አሉኝ ። እኔም ፎቶግራፉን ያለመያዜንና አገሬ ስመለስ እንደምልክላ ቸው ቃል ገባሁ ።

". . . . ንጉሡ ምኒልክ ስለ አበሻ ነፃነት ምን ያህል እንደ ደከሙ ካጫወቱኝ በኋላ ፣ 'አበሻ ምን ጊዜም ነፃ አገር ሆና የምትኖር ናት ። በክርስቲያን ደንብ አገራችን እንድትለማ የሚቀርቡንን ሁሉ በታላቅ ደስታ ፣ በአክብሮት እንቀበላቸዋለን ። በሌላ ለሚመጡብን ግን ሁላችንም እናልቃለን እንጂ ሳናልቅ አገራችንን ለሌላ አንሰጥም' አሉኝ የዚያች በተፈጥሮ የበለፀገች አገር ንጉሥ ። . . . " በማለት የተናገረውን ጋዜጣው በሰፊው አውጥቶታል ።

በዚያው ዕለት ማለት እ.ኤ.አ. ጥር 1 ቀን 1904 ዓ. ም. የወጣው ኒውዮርክ ዴይሊ ኒውስ ጋዜጣ ደግሞ የኤሊስን ኢንተርቪው ሲያወጣ ". . . .ምኒልክ አሜሪካኖች ወደ አገራቸው እንዲመጡላቸው ይፈል ጋሉ ። ሲያጫውቱኝም 'እስካሁን እናንተ አሜሪካኖች ከወሰናችሁ አልፋችሁ የሌላ ወሰን መድፈራችሁን አልሰማሁም ። ሌሎቹ ግን እንደ እናንተ አርፈው ከአገራቸው የሚቀመጡ አይደሉም' ብለውኛል ። በሌላ ጊዜ ሲያጫውቱኝም 'አየህ ፡ እነኚህ ፈረንጆች ሳልነካቸው ይነ ኩኝና ንጉሥ ምኒልክ መጥፎ ሰው ነው ይሉኛል ፤ እኔ ግን ለወዳጆቼ መጥፎ አይደለሁም ። እኛ አበሾች አንድ ጠባይ አለን ። ለምናምናቸው ወዳጆቻችን ሰላማዊና እንኳን ደህና መጣችሁ የምንል ነን ። ጠላት ከሆኑብን ግን እንደ ዱር ክፉ አውሬ ማንንም ሳንፈራ ጠላቶቻችንን ማጥፋት እንወዳለን ። ይሄ ነው ጠባያችን' አሉኝ. . . ." በማለት ኤሊስ የተናገራቸውን ጋዜጣው ሰፋ ካለ ዜና ጋር አውጥቶታል ።

እ.ኤ.አ. ታኅሣሥ 17 ቀን 1904 ዓ. ም. የወጣው ፒትስበርግ ፖስት የተባለው ጋዜጣ "ምኒልክ የአብርሃም ሊንከንን ታሪክ ሲሰሙ አለቀሱ" በሚል ርዕስ ተነስቶ ኤሊስ የነገረውን ታሪክ ሲጽፍ ". . . .ፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን ባሪያዎችን ነፃ ያወጣበትን ታሪክ


ሲሰሙ ምኒልክ አለቀሱ ። ይህንንም የአብርሃም ሊንከንን ታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ መስማታቸውን ነገሩኝ ። ምኒልክ እንባቸውን እየጠረጉ ምን ዓይነት ትልቅ ሰው ኖርዋል ! አሉ ። ወዲያውም አየህ ፤ እንደ አብርሃም ሊንከን ማድረግ አልችልም ። እሱ ብዙ ሥራ የሠራ ነው ። እኔ ያደረግሁት ነገር እስከዛሬ በባርነት የነበሩ ሰዎች እንደዚያው እንዲቆዩ ሆነው ፤ ከእንግዲህ ወዲያ እነኚያ ባርያዎች የሚወልዷቸው ልጆች ግን ነፃ እንዲወጡ አውጇለሁ ። ከዚህ ሌላ ምን ላድርግ ? ቀስ በቀስ ሁሉንም ነፃ አወጣለሁ ።. . . .አሉኝ. . . .'' በማለት ኤሊስ የነገረውን በስፊው አውጥቷል ።

ኤሊስ በኢትዮጵያ ውስጥ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሊያቋቁም ከምኒልክ ጋር ተዋውሎ የጥጥ መትከያ መሬት ሁሉ ተቀብሎ ነበር ። ጉዳዩ ፍጻሜ ሳያገኝ ምኒልክ በመሞታቸው የፋብሪካውም ጉዳይ አብሮ ሞተ ።



SA MAJESTÉ MÉNÉLIK II

ROI DES ROIS D'ÉTHIOPIE



የምኒልክ የጅ ጽሑፍና ፊርማ ። በዚያ ዘመን ምኒልክ በፎቶግራፋቸው ግርጌ እየ ጻፉና እየፈረሙ ለውጭ አገር ሰዎች መታሰቢያ ይሰጡ ነበር ።



ምኒልክ በአዲስ አበባ ያለውን
የኢጣሊያ ኤምባሲ ሲጎበኙ ።

# አስተዳደር

“. . . . ምኒልክ በጥበብ ሕዝቡን ሲያስተዳድር ፡ ሕዝቡ በፍቅር እንዲከተለው እንጂ በፍርሐት እንዲገዛለት አይፈልግም. . . .በዚህም ምክንያት በማስተዳደሩ በኩል የወጣለት ጥሩ መሪ ነው ።....” ግሊክን።

“. . . . በምኒልክ ዘመን የአገሪቱ ክብር አደገ ። የዘመናዊ አስተዳደር መሠረትም ተጣለ ። ንጉሡም በዘመናዊና በዘዴ አስተዳደር ይመራሉ . . . .” ኢላንዶርፍ ።

“. . . . በምኒልክና በሕዝቡ መሀል ርቀት የለም ። ....” ሮድ ።

ምኒልክ በአስተዳደር በኩል ዘዴኛ ነበሩ ። ምን ጊዜም ቢሆን ጠላቶቻቸውን በፍቅር ለመሳብና የፍቅር እሥረኛ ለማድረግ የሚጥሩ ነበሩ ። “የሚጠሉህን ሰዎች ከማጥፋት ፡ የሚጠሉብህን ነገር አጥፋ” በሚለው ምሳሌ የሚመሩ ይመስላሉ ። ለምሳሌ ከአጤ ዮሐንስ ጋር ተባብረው እየወጉና እየሸፈቱ ያስቸግሩዋቸው የነበሩትን ራስ ሚካ ኤልን የፍቅር ወዳጅ አድርገው ልጃቸውን ዳሩላቸው ። ልጃቸውን የዳሩላቸው ለመያዣ ብለው በሩቁ ሳይሆን የምኒልክ ቤት ለሚካኤል ፡ የሚካኤል ቤት ለምኒልክ ልዩነት የሌለበት ሁለቱም እንደቤታቸው የሚያዙበት ነበር ።

ከጐጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር እምባቦ ላይ ተዋግተው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ድል ሆኑ ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በብዙ ጥይቶች ቆስለው ስለነበር ምኒልክ ምርኮኛውንና ቁስለኛውን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን በሕዝብ ፊት ታቅፈው ፡ ስመው ፡ ደማቸውን በለ በሱት ጋቢ ጠራርገው ፡ ራሳቸው ከወጊኞች ጋር ሆነው ማከማቸው ሳይነዳቸውና በሆዳቸው ቂም ሳይዙ ቀርተው አይደለም ። እንጦጦ ላይ ራስ ደረሶ “ብናሸንፍ ኖሮ ቆራርጠን እንጥሎት ነበር” እንዳሏቸው ሁሉ ምኒልክ መቆራረጡ አላቃታቸውም ። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት ለቴዎድሮስም ስላልበጀ ጠላት ማብዛት መሆኑን አውቀው ከፉ ጠላ ታቸውን በመልካም ፍቅር አሠሩዋቸው ። ይህን ያየ ጐጃሜም ለጥ ሰጥ ብሎ ተገዛላቸው ። በንጉሥ ተክለሃይማኖትና በምኒልክ መሀልም እንዴት ያለ ፍቅር እንደነበር የሚከተለው የንጉሥ ተክለሃይማኖት ደብዳቤ ያስረዳል ።

ይድረስ ኀበ ሥዩመ እግዚአብሔር ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ጃንሆዬ ይሄ ፈረንጅ ከትግሬ ራስ መኰንን በልፍ ሰደደኝ ብሎ ጉድሩ ሳለሁ በልፍ መጣ ። በዚህ ልሰድድህ ብለው በቅሎዬ ሞቶብኝ በእግሬ ተጉዤ ደክሞኛል ። አርፌ በዚያ በኩል በጃርሶ ተሻግሬ እሔዳለሁ ብሎ ቆየ ። አሁንም ሰድጄዋለሁ ። ጃንሆዬ ደግሞ የወዲያ አገር የኢየሩሳሌም ተክል ከዚህ የማለማው ደጅ እጠናለሁ ። ይህንንም ስላልሁ እኔም የሀገሬን ተክል ጐመን ዘርን ያህል ነገር ለጃንሆዬ አበድሬአለሁ ። ብድሬን ከነአራጣው ይክፈሉኝ።ለጌታ የነገሩት በሰኔ የተከሉት አይጠፋምና ሰኔ ሳያልቅ እንድተክለው ብዬ አመለክታለሁ ። ደግሞ ጃንሆዬ ለከንፈሬ መድኀኒት ለጥርሴ መለቃለቂያ የሰጡኝ አለቀብኝና ላስታውስዎ ብዬ ነው ። የተላከ ከንጉሥ ተክለሃይማኖት ርቱዕ ሃይማኖት ወልዱ ለቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ሕያው አበ ነጋሢ። መድኃኒዓለም ጤና ይስልኝ ብዬ አሥር ፤ አሥር ጊዜ እጅ እነሳለሁ ። በሰኔ በ ፳ ቀን በ፲፰፻፺፪ ዓመት ምሕረት በደብረ ማርቆስ ከተማ ተጻፈ ።

ማህተም

በዚህ ደብዳቤ ላይ እንዳየነው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አጤ ምኒልክን ጃንሆይ እያሉ ሳይሆን በማቆላመጥ ጃንሆዬ እያሉ ነው የጻፉላቸው ። ይህም ምን ያህል ፍቅርና ወዳጅነት በመሀላቸው እንደ ነበረ ያሳያል ።

ወላይታን ለማስገበር የዘመቱ ጊዜ ፡ ሶስት ወር ያቆያቸውና በደ ፈጣም ውጊያ ብዙ ሰው የፈጁባቸው የወላይታው ባላባት ጦና ነበሩ ። በኋላ ድል ሆነው ሲሸሹ ምኒልክ "እያምልጥህ አባረህ ያዝልኝ" ብለው ጦና ብዙ ቦታ በጦር ተወግተው በማይረባ ቃሬዛ ሆነው ከም ኒልክ ፊት ቀረቡ ። ምኒልክም በሕዝብ ፊት ከዙፋናቸው ወርደው በጋቢያቸው የጦናን ደም ጠርገው ፡ በማይረባ ቃሬዛ ያመጧቸውን ወታ ደሮች ተቆጥተው "ወንድሜን እንዲህ አደረጋችሁት?" ብለው አስታ መው አዳኑዋቸው ። የወላይታንም መኳንንት ሰብስበው ከመከሩ በኋላ "ልጄን ፡ ወዳጄን ፡ ጦናን ሾሜልሃለሁና ግብርህን እንድታገባ" ብለው አዋጅ አስነገሩ ። ያን ጊዜ ሸሽቶና ከድቶ ወደ ኬንያ የገባው ሠራዊት ሁሉ "....እንደ ቴዎድሮስ የሚቆራርጡ መስለውን ነው እንጂ...." እያለ ሁሉም ተመልሶ አገሩ ገባ ። ጦናም ፍፁም ታማኝ ሆነው ሲያገ ለግሉ ኖሩ ። ይህም ጠላትን በጦር ብቻ ሳይሆን በዘዴ የመወዳጀት ችሎታ እንደነበራቸው ያሳያል ። አስተዳደር ማለትም ሁሉን መቻልን የሚጠይቅ ነው ።

በኋለኛው ዘመን ከመሐል አገር ወደዳር አገር የተሾመው ሁሉ ድሃውን እየነጠቀ ፡ ርስት እያበጀ ተደላድሎ ይቀመጥ እንጂ በምኒልክ ዘመን ድልድሉ ወይም ሹመቱ እንደዚያ አልነበረም ። ከመሐል አገር የሚሾመው ሰው ሠራዊቱን ወይም ወታደሮቹን ይዞ ያን አገር ሌላ ጠላት በጦር እንዳይደፍረው ይጠብቃል እንጂ በአስተዳደር ሥራ አይገ ባም ነበር ። አስተዳደሩ ግብሩን ለመሀከለኛው መንግሥት ሲገብር ፡ ያ ወታደሮቹን ይዞ የተቀመጠው ተሿሚ ደሞዙን ከነሠራዊቱ እንዲ ገበር ከተወሰነው ገንዘብ ላይ ገባሪው ቀንሶ ለጦሩ ደሞዝ ሰጥቶ ቀሪ ውን ለመንግሥት ግምጃ ቤት ያስገባ ነበር ።

ለምሳሌ በወለጋው ገዥ በደጃዝማች ጆቴ ላይ ሐምሌ 14 ቀን 1900 ዓ ም አዲስ አበባ የታወጀውን አዋጅ እንመልከት ። "አዋጅ" ካለ በኋላ "ከዚህ ቀደም ደጃች ጆቴ የመንግሥት ገንዘብ እያጠፋ በወንጀል ቢረታ ፡ ሌላም ብዙ ኃጢአት ቢገኝበት ፡ ሁሉንም እየተውሀ

አሳልፈው ነበር ። አሁን ግን ድሃዬን አላግባብ እየዘረፈና ያልሆነ ቅጣት እየቀጣ፣ በዚሁ እየተረታ የድሃው ግፍ ቢበዛ እሱን እዚህ አቆይቼ በአገሩ ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስን ምስለኔ ሾሜአለሁና የጥንት ግብራችሁን በሱ እጅ እያወጣችሁ አገራችሁን አልሙ ። ወዲያ ወዲህ የተበተነውም ድሃ በየሥፍራው ተመልሶ ይግባ''

አዋጁ ውስጥ ሶስት ነገሮች እናገኛለን ። 1ኛ እኔን በድሎኝ ሳይሉ ድሃዬን በድሎ ማለታቸው ከሁሉ በላይ ድሃውን እንደሚያከብሩ ያሳያል ። ፪ኛው ምስለኔ ሾሜአለሁ ኦሉ እንጂ ገዢ ሾሜልሃለሁ አላሉም ። ምስለኔ ማለት እንደኔ መሳይ፣ እኔን መስሎ የሚሠራ ስጥቼ ሃለሁ ማለታቸው ነው ። ፫ኛው የመንግሥት ገንዘብ እያጠፉ ሲሉ እንዳለፉት ነገሥታት ያገራቱ ገቢ ሁሉ ወደሳቸው የሚገባ ሳይሆን የመንግሥት በመንግሥት ግምጃ ቤት ይገባ እንደነበር ያሳያል ።

የድሃ ነገር ከተነሳ ምኒልክ ለድሆች በጣም የሚቆረቆሩ ሰው ነበሩ ። ለድሆችም ጠበቃና ዳኛ ነበሩ ። ይህንንም ከብዙዎቹ ደብዳቤዎቻቸውና አዋጆቻቸው እንረዳለን ። ለምሳሌ ስለ ወላይታ ሕዝብ እንመልከት ።

ሸሽቶ ከኢትዮጵያ ወጥቶ ወደ ጎረቤት አገር ተሰዶ የነበረው የወላይታ ሕዝብ ተመልሶ ወደ አገሩ በመግባቱ ምኒልክ ተደስተው የወላይታ ሕዝብ እንዳይበደል በግል ቁጥጥራቸው ሥር አድርገውት ነበር ። ግዛቱንም በግል እንደራሴአቸው በአዛዥ ባደግ ሥር አደረጉት ። አዛዥ ባደግ ግን ሕዝቡን እየበደሉ አስቸገሩ ።

ይህን የሰሙት ዳግማዊ ምኒልክም ነሐሴ 29 ቀን 1899 ዓ.ም. ለአዛዥ ባደግ የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉላቸው ። ''....የወላሞ ባላገሮች ችግራችንን ለማመልከት ወደዚህ እንዳንመጣ በየኬላው በር አስጠብቆ አስከለከለን ። እኛም ይህን ፈርተን በአሩሲ ዞረን መጣን ። ሌሎቹ ግን በመንገድ ሲመጡ ተይዘው ታስረዋል ብለው ጮሁልኝ ።

''ጪሂ ወደዚህ ሲመጣ ለምን ይከለከላል ። አሁንም ለጩኸት ወደዚህ የሚመጣ ሰው አይከልከል ። ከዚህ ቀደም ወደዚህ ሲመጡ የታሰሩትም ሰዎች ይፈቱ ። ነገሩንም በመጣህ ጊዜ ትነጋገራለህ ። ግብርም ተጨመረብን ብለዋልና ከዚያው እኛ ከሠራንላቸው ከዓመቱ ግብራቸው በቀር ሌላ ትርፍ ግብር አይነካ ። ነገር ግን ለጩኸት መጥተን ወደዚያ መመለሱን ፈራን ቢሉ ይሄው ከልክሌን ዳኛ ሰጥቼ ሰድጂአቸዋለሁ ።''

ይህን ደብዳቤ ለአዛዥ ባደግ ቢልኩላቸውም አዛዥ ባደግ በስውር የወላሞን ሕዝብ መበደላቸውን ቀጠሉ ። ይህንኑ የወላሞን

ሕዝብ መበያል ምኒልክ እንደሰሙ እንደገና ከሁለት ወር በኋላ የሚ ከተለውን ደብዳቤ ጻፉ ።

ይድረስ ከአዛዥ ባደግ ።

ወላሞን ለኔ ጉልት አድርጌ አንተን መሾሜ ድሃ እንዳይበደል ፣ ከነፍስ ገዳይ በቀር እንዳይታሰር ፡ እንዳይወረስ ፡ አገሩን ደህና አድር ገህ እንድትጠብቅልኝ ነበረ ። አሁን ግን ደሃው ተበደልን እያለ ዕለት ዕለት ለጩኸት ይመጣል ። ደግሞም ሳይበደል ይህን ያህል ሰው ይመጣል ተብሎ አይጠረጠርም ። አንተስ ይህን ያህል ሰው እየተሰበ ሰበ ሲመጣ ሳትሰማ ቀርተህ ነውን ። ወይስ እኔን አይሰማም ብለህ ነው ። አሁንም የታሰረው ሁሉ ከነፍስ ገዳይ በቀር በዋስ ይፈታ ። የተወረሰ ገንዘቡም አንድ ሳይቀር በዋስ ይመለስ ። አለዚያ የማይሆን ከሆነ አገሩ ብዙ ወታደር ይይዝልኛል ። አከፋፍዬ እሰጠዋለሁ ።

ጥቅምት ፯ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም. አዲስ አበባ ተጻፈ ።

ምኒልክ ቀልድ የማያበዙና ተጨዋች ስለነበሩ ሁሉም እንደአባት እንጂ እንደ ገዢ አያያቸውም ነበርና በወላይታ ያሉ ሹማምንቶች ድሃ መበደላቸውን ቀጠሉ ። በዚህ የተናደዱት ምኒልክ የወላይታ ሹማምንቶች በኮሚቴ እንዲመሩ ነሐሴ 2 ቀን 1900 ዓ.ም. የሚከተለ ውን ደብዳቤ ላኩላቸው ።

‘‘....ከዚህ ቀደም ወላሞ የተሾሙ ሹማምንቶች ሁሉ አላግባብ እየበደሉ ብዙ ገንዘብ እንደጠፉ የሰማችሁት ነው ። አሁንም እናንተን መርጬ ወላሞ መሾሜ ድሃዬን እንድትጠብቁልኝ ነውና እዚያው ደንብ ካደረግነው ከዓመት ግብሩና እኔ ከማዘው ትእዛዝ በቀር ሌላ በምንም በምንም ድሃው እንዳይነካ ይሁን ። እንግዲህ ግን ከዚህ ቀደም ተሾመው እንደነበሩት ሰዎች አላግባብ አድርጋችሁ ይህን ተበደልን ፡ ይህን ተበላን ፡ ብሎ የጮኸልኝ እንደሆን በገንዘባችሁ ብቻ አይደለም ፡ ርርቱ ቅጣት ትቀጣላችሁ ። ደግሞ ከእናንተው ሹማምን ቶቹ ውስጥ አንዱ አላግባብ ድሃ በደለ ፡ ገንዘብ በላ ማለት የሰማችሁ እንደሆነ እናንተ ተሰብስባችሁ ፡ እሱን አስጠርታችሁ ፡ ነገሩን አይታ ችሁ ጨርሱ ። እናንተ ለመጨረስ የማይመቻችሁ የሆነ እንደሆነ ግን ወደኔ ላኩልኝ.... ለራሳችሁ የምትበሉት ዳኝነት እሱ በፈቃዱ እየ ወደደ የሚሰጣችሁን መተያያ ነው ። በተረፈ ከባላገሩ በምንም በምንም አመካኝታችሁ የምትነኩት ገንዘብ የለም ።....’’

ዳግማዊ ምኒልክ ይህን ደብዳቤ ለሹማምንቱ ከላኩ በኋላ ሕዝቡ ደግሞ ነገሩን እንዲያውቀው የሚከተለውን አዋጅ አወጁለት ።

"ከዚህ ቀደም ወላጆ የተሾሙት ሹማምንቶች ሁሉ እናንተን እየበደሉ ገንዘባችሁን አላግባብ እየወሰዱ አገር ቢያበላሹ ይሄው ደግሞ ሌሎች ሰዎች መርጬ ሾሜላችኋለሁና በኔ ትእዛዝ ያለውን ግብር እየሰጣችሁ ተስማምታችሁ ተቀመጡ ። ነገር ግን በውስጣችሁ የተሾሙትንንሹ ሹማምንት አላግባብ ገንዘብ አምጡ ያላችሁ እንደሆነ ገንዘቡን ሳትሰጡ ለእውነተኛው ሹማችሁ ንገሩ ። እሱም ያላግባብ ያደረጋችሁ እንደሆነ እንደዚህ ያለውን ነገር ሁሉ በወላጆ ተሹመው የሔዱት ሹማምንቶቻችሁ አንድ ላይ ሆነው የተበደለውን ይዩ ብያለሁና ለእነሱ አመልክቱ ። ከእነዚያም ያልሆነላችሁ የሆነ እንደሆነ ግን ያው የተበደለው ሰው በባልደረባው እየመጣ ያመልክት እንጂ ብዙ ሰው ባድማ እየተሰበሰበ መሬሁ መልካም አይደለም ። ይህን መንገደኛውን ሁሉ የሚያበድብ ፡ ቤት የሚያቃጥል ፡ ሰው የሚሸጥ ፈንጋይና ወንበዴ በያገራችሁ መርምራችሁ አውጥታችሁ ወደኔ ስደዱልኝ ። በደሉንም እያየሁ በዚህ ሥራ አስይዘዋለሁ ። ከዚያ ወዲያ ፈንጋይ ወንበዴ ሳታወጡ ቀርታችሁ የተገኘባችሁ እንደሆነ የተገኘበት አገር ሺህ ብር ይከፍላል ።

ነሐሴ ፪ ቀን ፲፱፻ ዓ. ም

ወደ ጐጃም ድህኅ ደግሞ እንመለስና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከሞቱ በኋላ በጐጃም ራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲከም ተሾመው ነበር። መንገሻ ድሃውን እየበደሉ ስላስቸገሩ ድሃው አዲስ አበባ ድረስ መጥቶ ለምኒልክ ጮኸ ። ምኒልክም ድሃው የጮኸበት ጉዳይ እንዲፈፀምለትና በደል እንዳይደርስበት ደብዳቤ ጽፈው በጫሂው ሕዝብ እጅ ለራስ ቢትወደድ መንገሻ ላኩ ። በምስጢር ግን ሌላ የግል ደብዳቤ በሌላ ሰው እጅ ላኩላቸው ። በግል የተፃፈላቸውን ደብዳቤ እናንብብ ።

ይድረስ ከራስ ቢትወደድ መንገሻ ።

የሚሔዱና የዲንሳ ፡ የይልማና ሰዎች ተሰብስበው መጥተው ጮሁልኝ ። የጮሁበትንም ነገር ቃሉን እንድታየው ብዬ የሰጡኝን ደብዳቤ ይሄው ሰድጄልሃለሁ ። ነገር ግን ይፍሬታና ግድም እንደጮኸ እንደለፈለፈ ተለያየ ። ቢጌምድርም እንደጮኸ እንደለፈለፈ ተለያየ ። ሳይንትም እንደዚሁ ተፈታ ። ደግሞ አሁን ሚሔዱን ይልማናን እንዲህ አድርገህ ታስጨንቀዋለህን ። እኔስ ጋሻ ስደድልኝ ማለቴ እዚያ አገር ጋሻ ሰንጅ ብዙ ነውና በጥቂት ዋጋ ይገኛል ብዬ ገዝተህ እንድትሰድልኝ ነው እንጂ ከመኳንንቱ ከባላገሩ የጋሻ ፈሰስ ጥለህ መቼ አስወጣልኝ አልኩህ ። ነጭ ማርም ስደድልኝ ማለቴ የዚያ አገር ማር ሁሉ

መልካም ነውና ላንተ ከሚገባልህ መርጠህ ላክልኝ አልኩህ እንጂ ነጭ ማር ካላመጣችሁ እያልክ ደሃውን የምታስጨንቀው በምን ነገር ነው ። የዛሬ ድሃ ላም የለው ፡ በሬ የለው ፡ ምን ጉን አለው ብለህ ነው። ደግሞስ አንተ የምታቀቸው እኔ የሾምኳቸው ፡ ያሳደኳቸው ፡ የፊተኞቹም ያባቴ ሽማግሌዎች ሁሉ አለቁ ። ያለኸው አንድ አንተ ነህ ። እንግዲህማ ለኔ አድሜ ማዘን ፡ ለመንግሥቱም ማዘን ነበር እንጂ እንዲህ አድርገህ ደሃውን ብታስጨንቀው ምን ትጠቀማለህ ። ይህ ሁሉ የጨዋ ልጅ ሽማግሌ እንግዲህ ተመልሰን አገራችን እንገባም ፡ የራስ መንገሻን ፊት አናይም ፡ እንደወጣን እንቀራለን ብሎ እዚህ መጥቶ ያለቅሳል ። ይኸንን እግዚአብሔር ይወደዋልን ። የመረረው ድሃ ይገባል ከውሃ የሚሉ ተረት ባንተ ደረሰ ። አገዛዝ እንደኔራሱ ሚካኤል ፡ እንደኔራስ ወሌ ነው እንጂ እንዲህ አስጨንቆ መልካም ነውን ። አሁንም ከዚህ ቀደም እንደነበሩ እንደጥንታቸው ይኑሩ እንጂ ቀድሞ ያልነበረ ነገር አትንካ ። ነገር ግን ደብዳቤም ብልክብህ ፡ ብመክርህም አትሰማኝ ። ተመክረህም አትድን ። እንግዲህስ ሁለተኛ እንዲህ ያለ ነገር የሰማሁ እንደሆን መንገሻ ሙት ፡ ማርያምን ፡ ድሃው ከወደደበት እንዲኖር አዋጅ እነግርለታለሁ ። ይህንንም ደብዳቤ በነሱ እጅ ከመስደድ ብዬ በቃቤቱ በቢያድግልኝ እጅ ነው የሰደድኩልህ ።

ኅዳር ፰ ቀን ፲፰፻፺፫ ዓመተ ምሕረት እንጦጦ ተጻፈ ።

የራስ ቢትወደድ መንገሻ ነገር ከተነግ የሚያርፉ ሰው አልነበሩም ። ባነበብነው ደብዳቤ መሠረት ምኒልክን በመፍራት ሊጮህና ሊያሳጣ የሚችለውን የቅርብ ደሃ መበደላቸውን ቢያቆሙም ፡ ራቅ የለውንና በዚያን ጊዜ በየዋህነት ይገዛ የነበረውን ሻንቅላ የሚባለውን ሕብረተሰብ ባርያ እያደረጉ ማጉላላት ጀመሩ ። ምኒልክም ይህን ነገር ከሰላዮቻቸው እንደሰሙ ተናደው እንደገና የንዴት ደብዳቤ ፃፉላቸው ። የካቲት 7 ቀን 1899 ዓ.ም. ለራስ ቢትወደድ መንገሻ የተፃፈው ደብዳቤ እንዲህ ይላል ።

"..... ሻንቅላ ወርቅ እየገበረ ፡ ግብሩ ሳይጉድል ፡ እዚያው አገሩ ነዶ አርሶ ፡ ቆፍሮ የሚያገለግለውን እንደ ከብት ሁሉ ባመት ባመቱ የመለመልክ ታስወጣለህ አሉ ። እኛ ከየት አገር እየመለመልን ስና ሀጣ አይተህ ነው እንዲህ ማድረግህ ። ልጅህን ስትድር የሰጠኸውን ሻንቅላ ሰምተናል ። እንግዲህ ግን አንድ ሻንቅላ ተመልምሎ ታገሩ ሀጣ ያሉኝ እንደሆነ ሁለተኛ እኔና አንተ መገናኛ የለንም ።"

ምኒልክ የኢትዮጵያን ዘመናዊ አስተዳደር የመሠረቱ ታላቅ ሰው በሩ ። በድሮው ጊዜ ወታደር የተባለ ሁሉ የገንዘብ ደሞዝም ሆነ

የእህል ቀለብ ስለማይሰጠው በየባላገሩ ቤት በምሪት እየተሰጠ የሚያ በላውም ፣ የሚያሳድረውም ባላገር ነበር ። ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ስለዚህ ጉዳይ ሲያትቱ “. . . .እስከ ትላንት ድረስ . . . .የኢት ዮጵያ ድሃ ለወታደር መጫወቻ ባርያ ነበረ ። ባርያ በገዛ እራሱ ማዘዝ እንደማይሆንለት ፣ የኢትዮጵያ ድሃም በገዛ ቤቱ ማዘዝ አይሆንለትም ነበር ። የሚያዝበት ፣ ቀርፋፋ ጋሻ ያነገበና አንድ ባለጌ ጦር የያዘ ፣ . . . . ወታደር . . . . እንኳንስ ተሠሪነት ገብቶ ፣ ሄዶም ባደረበት አገር ሳይቀር ደሃውን የፊጥኝ አስሮ ነጭ ኑግ ፣ ጥቁር ወተት ውለድ ሲልና ባለቤቶቹ ምሽቲቱ እንድገረድ ፣ ባልየው እንደሎሌ ፣ እግር አጥበው ፣ አልጋ አንጥፈው ፣ ትራፊውን በልተው ፣ እነሱ ከምድር ፣ እሱ ካልጋ ተኝተው ያድሩ ነበር ። አንዳንድ ጊዜ መልከ መልካም ምሽት የነበረ ችው ባላገር. . . . በግፍ ላይ ግፍ በውርደት ላይ ውርደት ታክሎበት ያድር ነበር ።. . . . አንድ ቀን በቴዎድሮስ ጊዜ. . . . ነፍጠኛ ተቤቱ ተመርቶ ገባና ባለቤቲቱ መልከ ቅን ሁና ባያት ጊዜ ነፍጡን ከጉል በቱ ላይ አድርጎ ፣ አንተ ይህቺ እህትህ ስንት ዓመቷ ነው ፣ ቁርጥ አንተን ትመስላለች አለው ። ያ ባላገር ግን ምሽቴ ናት ማለቱን ፈራ ። ያም እርጉም ነፍጠኛ በጥፊ እያጣፈረ ያቺን ምሽቱን ይዞበት አደረ ። ከዚህ በኋላ ያ መከረኛ ድሃ አዘንና ንዴት ያዘውና “ካገር እኖር ብዬ ፣ ከብት እነዳ ብዬ ፣ ልጅ አሳድግ ብዬ ፣

“ለባሻ ዳርኩለት ሚስቴን እቴ ብዬ” ብሎ አንጐራጐረ. . . . .አሁን በደጉ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ግን ያ ሁሉ መከራ ፣ ያ ሁሉ ግፍ ቀረ. . . .” ብለዋል ።

ይህን አሠራርና የባላገሩን መበደል ያውቁ የነበሩት ምኒልክ ለወታደር በሙሉ አበል ቆርጠው ፣ ባላገሩ ከሚገብረው ግብር በስተ ቀር እንዳይነካ ብለው አወጁ ። ከባላገር ቤት እየገባ በነፃ በሚበ ላው ወታደርም ከነአለቃው ጭምር ከፍተኛ ቅጣት በመቅጣታቸው ባላገር ተንፈስ አለ ። በወታደርም ስም ጠመንጃ ወይም ጦር የያዘ ነጋዴ ሁሉ ወታደር ነኝ እያለ ለንግድ በሚነዝበት መንገድ ባላገሩን ያስቸግር ስለነበረ ማንም ሰው በገንዘቡ ገዝቶ እንጂ ከባላገር በነፃ ምንም ነገር እንዳይነካ አወጁ ።

ለምሳሌ ለዚህ ጉዳይ ካወጁዋቸው ብዙ አዋጆች መሀል መጋቢት 14 ቀን 1900 ዓ.ም. ያወጁትን ብንመለከት “. . . .የተሰበረውን የአ ባይን ድልድይ አሠርቻለሁና በዚያ የምትመላለስ ሰው ሁሉ ስንቅ ህን እየበላህ ሂድ እንጂ እኔ ካዘዝኩለት ሰው በቀር ከባላገር ደጅ አት ድረስ ። እንኳን ሌላ ነገር ገለባና ድርቆሽም ቢሆን በገንዘብህ ግዛ እንጂ የባላገር ገንዘብ አለዋጋ አትንካ ። በድልድዩም ዳር ያለህ ባላገር

በዚያ የሚመላለስ ሰው ገንዘብህን እንዳይነካብህ አዋጅ አድርጌል ሃለሁ'' ይላል ።

ምኒልክ ድሃን ስለሚወዱ ድሃው የድሃ አባት ይላቸው ነበረ ። በግብር ጊዜ እንኳ እንዳለፉት ነገሥታትና መኳንንት የግብሩ ቅድሚያ ለመኳንንት ሳይሆን መጀመሪያ የሚጀመረው በድሃው ነበር ። በግብሩ በየቀኑ ከእሁድ በስተቀር እስከ ሶስት ሺህ ሰው ይበላል ። እሁድ ግን አንድ ሺ ሰው ተጨማሪ ይሆንና ግብር በደው አራት ሺ ሰው ይደርሳል ። በዚህ የሰው መብዛት ምክንያት የምኒልክ ግብር የሚጀመረው ከጧቱ በ3 ሰዓት ነው ። መጀመሪያ ግብር የሚበሉት ዘበኞች ናቸው ። ዘበኞች በልተው ለጥበቃ ሲወጡ ቄሶች ይቀጥላሉ ። ከዚያ በኋላ መኖሪያቸው አዲስ አበባ ከተማ ያልሆነ መንገደኞች ፣ ወታደሮች ፣ ነጋዴዎች ከበሉ በኋላ ነዋሪው ሕዝብ ይገባል ። ግብሩም እንደ ጥንቱ ፣ ገብቶ መሻማት ሳይሆን ለአንድ ሰው አንድ ጋሬና (መናኛ) አንድ ጤፍ እንጀራ ፣ አንድ ትልቅ ጭልፋ ቀይወጥ ፣ ሙዳ ሥጋ ፣ አንድ ኩባያ ጠጅ ይሰጠዋል ። ለዚህ ነው "ቀድሞም ጠቢብ ነበር ሰለሞን አባቱ ፣ ምኒልክ ይበልጣል ሰው ይዞ መብላቱ'' ተብሎ የተገጠመላቸው ።

ምኒልክ ለድሆች ምን ያህል ተቆርቋሪ እንደነበሩ ብዙ ማስረጃዎች አሉ ። ካነበብኳቸው በብዙ ሺህ ከሚቆጠሩ የምኒልክ ደብዳቤዎች ውስጥ ስለድሆች ከሚናገሩት ጥቂቶቹን ለማስረጃ እንመልከታቸው ። ምኒልክ አንድ ድሃ ሰው ሲበድል ለምን ይበደላል የሚሉ ሰው እንደ ነበሩም ደብዳቤዎቹ ያስረዳሉ ።

የጐጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ሞተው ልጆቻቸው እርስ በራሳቸው እየተጣሉ ጐጃምን በጥብጠውት ነበር ። ይህ የንጉሥ ተክለሃይማኖት ልጆች መጣላት የሰለቻቸው ምኒልክ ፊታውራሪ ተሰማንና ግራዝማች ወልደዮሐንስን በጐጃም እንደራሴአቸው አድርገው ልከዋቸው ነበር ።


ይድረስ ከግራዝማች ወልደ ዮሐንስ ።

. . . . መርሻ ኑርልኝ የሚባል ሰው በውርርድና በዳኝነት 68 ብር ተበላሁ አለ ። አንድ ድሃ እንዴት 68 ብር ይበላል ። ለሱም ዳኝነት እንድታይለት ይሁን ።


ትሳስ ፳፬ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ. ም. ተጻፈ

ይድረስ ከደጃዝማች ገሠሠ ።

ይሄ አበጋዝ ኃይሉ የሚባል ሰው ቀድሞ ጭቃ ሆኜ ባላገር ባዝ ደበደበኝ ። በዳኛ ተከስሼ ካሣውንም በላ ። ከሌላ ሰው ብጣላ ቂም



የግብር ማብሊያው አዳራሽ ሲሠራ



እዳራሹ ተሠርቶ ካለቀ በኋላ የማብረ በላው ተራ እጠባበቅ ።



ግብር ሲበላ ።

አድርገው ውርርድና ዳኝነት አንድ መቶ ብር ፣ ሁለት የቀንድ ከብት ፣ ሁለት አህያ በሉኝ ብሎ ጮኸልኝ ። ካንድ ድሃ በዳኝነት ይህን ያህል እንዴት ይበላል ። አሁንም ይሄ የተበላው ገንዘብ ይመለስና በጥቢ አንተ ስትመጣ ነገሩ ይታይለታል ።

ሰኔ ፲፫ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ ም. አ.አ. ከተማ ተጻፈ

ይድረስ ከደጃዝማች ባልቻ ።

ይሄ ያርቢ ኮሎ የሚባል ሰው አባቴ ተጢሬ ነው ። እኔም ለብቻ ሆኜ ጉጆ ሳልይዝ በአባትህም በአንተም ገብር አሉኝ ብሎ ጮኸልኝ። እዚያው አባቱ ቤት ሆኖ በጦረ በሁለት ፊት ለምን ይገብራል ። ሌላ ነገር አለበት የምትል እንደሆነ ነገሩን ከሚያውቅ ሰው ጋራ እያይዘህ እንድትሰደው ይሁን ።

መጋቢት ፴ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም. አ.አ. ከተማ ተጻፈ ።

ይድረስ ከደጃዝማች ጆቴ ።

. . . . ካንተ አገር ውስጥ የተበደለ ድሃ ቢኖር ከኔ እየመጣ ይጮህ ። ነገር ግን አለአግባብ በእንደዚህ ያለ ነገር ተበደልኩ ብሎ አንድ ድሃ ለጩኸት የመጣ እንደሆነ ጭራሽ አገርህን ሽሬ ለሌላ እሰጣለሁ ።

ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ. ም. አ.አ. ከተማ ተጻፈ ።

ይድረስ ከደጃዝማች ጉግሳ ።

. . . . ወታደሩ በየባላገሩ ቤት ምሪት የገባ እንደሆነ ድሃው ይበተናል ። አገሩም ይጠፋልና ከእሽከርና ከገረድ በቀር ሁለት መቶ ሰው ይዘህ ለዚሁም እንጨትና ውሃ ካለበት ከደህና ሥፍራ ከተማ አሠርተህ እዚያ ቢቀመጥ መልካም ነው ። ደሃውን ደህና አድርጎ ጠብቆ ከያዙት ትርፉ ብዙ ነው ። . . . .

፲፰፻፺፱ ዓ. .ም አዲስ አበባ ተጻፈ ።

ራስ መኰንን ከሞቱ በኋላ ፊታውራሪ ባንቴ ለሐረርጌ እንደ ጥብቅ ገዥ ሆነው ተሹመው ነበር ። በፊታውራሪ ባንቴ ጊዜም ሕዝቡ ተበደልኩ ብሎ ለምኒልክ አመለከተ ። ምኒልክም ለፊታውራሪ ባንቴ ደብዳቤ ጻፉ ።

ይድረስ ከፊታውራሪ ባንቴ ።

የሐረርጌ ሰዎች . . . . ወታደሩ በቤታችን እየተቀመጠ እስከዛሬ ድረስ ቤታችንን አለቀቀልንም ። ከዚህ ቀደም ራስ መኰንን ካንድም

ሁለት ጊዜ አዋጅ ነግረውልን ነበረ አሉ ። የሚገብሩበትን ቤታቸውን ይዞ መቀመጡስ ስለምንድነው ። አሁንም ቤታቸውን እነሱ ይዘው የወደደ ሰው ኪራይ እየከፈለ ይቀመጥ ። በተረፈ ለወታደሩ ቦታ ከው ጭም ቢሆን ሰጥታችሁ እየሠራ ይቀመጥ ። አለባለቤቱ ፈቃድ ወታደሩ እንዳይቀመጥበት ይሁን ።

ደግሞ የአስራቱን እህል ሲያገቡ ከአውድማ በተሰፈረው ልክ ሰፍረው አይቀበሉንም ። እዚያው እንደጓዱ አፍ እንዳለወገን እየተ ሰፈረ እጥፍ ሁለት እጅ ያስጨምሩናል ብለዋልና እንዳለወገን የድሃው ገንዘብ ለምን ያልፋል ። ይህንንም በተቀበሉት ልክ ተሰፍሮ እንዲገባ ይሁን ።

ደግሞ ሠራተኛው ሳይሰማራ በሩ በሌሊት እየተከፈተ ለአትክ ልታችን አሊጋ ቆጥ ያበጀነውን እንጨት ማንም እያነሳ ከብትም እየ ገባበት አትክልቱ እየተረጋገጠ ተበላሸብን ብለዋልና ሰውም ከብትም እንዳይደርስ ይህንንም እንድታደርግላቸው ይሁን ።

ደግሞ አህያችን እየተነጠቀ አለኪራይ ማንም ይጭንበታል አሉ ። የድሃ ገንዘብ አለሥርዓት መነጠቁ ስለምንድነው ። አሁንም ሁለተኛ እንዳይነጠቅባቸው አድርግ ።

ትሳስ ፳፩ ቀን ፲፱፻ ዓ. ም. አ. አ. ከተማ ተጻፈ ።

ይድረስ ከደጃዝማች ጆቴ ።

ባንተ ጩኸት የመጣውን ባላገር ነገሩን እንድናይለት አንተ ቶሎ ሳትመጣ ቀረህ ። ደሃው ግን እጅግ ተበድለናል ብሎ ይጮሃል ። እኔም እዚህ ያለውን ውሰድና አስታርቅ ። እዚያም ያለውን አስታርቅና አስ ፈታ ብዬ ፊታውራሪ ወልደ ማርያምን ሰድጄዋለሁና እሱ የነገረህን ሁሉ እንድትሰማ ይሁን ። ሌላ ዳኛ እንዳልሰድ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የላካቸው ዳኞች አንተ ያልካቸውን መስማት እንጂ ለድ ሃው ምንም ያደረጉለት ነገር የለም ብለው ቢነግሩኝ ነው ። የእንፊሌ ዎችን ግን አንተው መጥተህ እንድትጨርስ ይሁን ።

ትሳስ ፴ ቀን ፲፱፻ ዓ. ም. አ. አ. ከተማ ተጻፈ ።

ይድረስ ከራስ ተሰማ ።

ደብዳቤህም ደረሰልኝ ። ሻንቅላውን አልገብርም ያለ እንደሆነ አጥፋት ብዬ ሰው ስደድሁ ያልከውን ቀስ እያሉ እያባበሉ ማድረግ

ነው እንጂ በጦርነትማ ከሔዱበት ፡ ጭራሽ ይጠፋ የለምን ። አሁንም የሚመችህ የሆነ እንደሆነ ብልሃት እያደረግህ እንዲገባ ብታደርግ መልካም ነው ።

በጥር ፬ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም. አ. አ. ከተማ ተጻፈ ።

ይድረስ ከራስ ወልደ ጊዮርጊስ ።

በአገር ድሃ እንዳይበደል ይመልከቱ ብለን አንተ አገር የመጡት ሰዎች እስካሁን እያዩ የጻፉትን ወረቀት ይዘው በቶሎ እንዲመጡ ይሁን ።

በጥር በ፳፱ ቀን ፲፱፻፪ ዓ.ም. አ.አ. ከተማ ተጻፈ ።

የምኒልክን ደብዳቤዎች ስንመለከት ምኒልክ ምን ዓይነት ሰው እንደነበሩ ከደብዳቤዎቻቸው እንረዳለን ። ፍርድ በትክክል የሚፈርዱ ሰው እንደነበሩም ብዙ ታሪክ ፀሐፊዎች ጽፈዋል ። በኋላ ንግሥት የሆኑት ልጃቸው ወይዘሮ ዘውዲቱ ፡ መምሬ ገብረዮሐንስ የሚባለውን ሰው ርስቱን ወስደው ከመሪጌትነቱም ነቀሉት ። ቄሱ መጥቶ ለምኒልክ ጮኸ ። ምኒልክም ልጄ ደስ ካላት ትውሰደው ፡ ላንተ ምትኩን እሰ ጥሃለሁ ሳይሉ ሰኔ 20 ቀን 1899 ዓ.ም. ለልጃቸው ለወይዘሮ ዘውዲቱ ደብዳቤ ሲጽፉ “. . . . ፴፰ ዓመት ሙሉ የያዝኩትን መሪጌትነቴን ነቀለችኝ አለ ። ፴፰ ዓመት የያዘውን ለምን ይነቀላል ። አሁንም አይነ ካበት ። ሌላ ነገር አለኝ ያልሽ እንደሆነ በመስከረም እኔ አይላችኋ ለሁ” አሉዋቸው ።

በአስተዳደር ዘመናቸው ሁሉ የሰውን ልጅ መብት የሚጠብቁ እንጂ ለራሳቸው ምቾት ሲሉ የሌላውን መብት የሚገፉ አልነበሩም ። እንደ ዘመኑ ሥርዓት የነበሩዋቸውን ባሪያዎች ሁሉ በባርነት ሳይሆን በደሞዝ ማስተዳደር ጀምረው አርአያ ለመሆን የሞከሩ ፡ ሴት ልጅ በእናት አባቷ ትእዛዝ ብቻ ባል ማግባትዋ ቀርቶ ፡ በራስዋ ምርጫ የወደደችውን እንድታገባ ትእዛዝ ያወጡ ሰው ነበሩ ።

የወይዘሮ ንግሥት ተክለ ሃይማኖትን ጉዳይ ለማንሳት ፈለግሁ ። ወይዘሮ ንግሥት የጐጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ልጅ ናቸው ። አባታቸው ከሞቱ በኋላ ሁለት ባሎች መጡላቸው ። 1ኛው የራስ ቢትወደድ መንገሻ ልጅ ደጃች መርድ ሲሆን ፤ ፪ኛው ደግሞ ደጃች ገሠሠ ናቸው ። ሁለቱም ባሎች ለሴቲቱ እንዳባት ሆነው እንዲድሩላ ቸው ምኒልክን ጠየቁ ። ዳግማዊ ምኒልክ ከእሳቸው በፊት እንደሚደ ረገው ሥርዓት ሁሉ አጋር ለሚሆናቸው ፡ ወይም ለሚወዱት መዳር

ይኖሩ ነበር ። እንኳን ባልም ሚስትም የሌላቸው ወንድና ሴት ተገኝተ ውና ያላቸውንም እያፋቱ እንደ እቴጌ ጣይቱ አደራረግ ጥግ ወይም አጋር ፍለጋ መዳር ወይም በጋብቻ መተሳሰር ልማድ በነበረበት ዘመን ፣ ምኒልክ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ለመፈፀም አሻፈረኝ አሉ ።

ባጭሩ ለማውራት መጀመሪያ የወይዘሮ ንግሥትን ፈቃድ ለማ ወቅ ጥቅምት 8 ቀን 1899 ዓ ም ከአዲስ አበባ ወደ ጐጃም በፃፉት ደብዳቤ "ያንቺን ነገር ራስ ቢትወደድ መንገሻም ፣ ደጃች ገሠሠም እሺ ብላናለች እያሉ ላኩብኝ ። እኔ ግን እንደፈቀደች ብዬ ልኬአለሁ ። አሁንም የዚህን ነገር አንቺ የምትፈቅጂውን እማገባው እከሌን ነው ብለሽ ቁርጥ ቃል ቶሎ ላኪብኝ" ብለው ላኩባቸው ። ነገሩ እየከረረ መኳንንቶቹ እንዳይጣሉም በመሀል ዳኛ እንዲሆኑ ግራዝማች ወልደ ዮሐንስን ሾሙ ። ግራዝማች ግን እንደ ዘመኑ ባህል በራሳቸው ሥል ጣን ላንደኛው ለመዳር ግፊትና ጫና ጀመሩ ። ይህን የሰሙት ምኒል ክም ". . . . . አንተ አባት ሆነህ ቀጥረህ ስጥ ብየህ ነበር ። አሁን ግን እሷ ሳትፈቅድ የንስሐ አባትዋን አስረህ ፣ እሷንም ከጃንሆይ አጣላሻ ለሁ ብለህ አለፈቃድዋ ልትሰጣት ነው አሉ ። እሷ የፈቀዳትን ታገባለች እንጂ አንተ ይህን ሁሉ ማድረግህ ማን አዘዘህና ነው ። ....አሁንም ፊት እንደላኩብህ እሷ የወደደችውን ታግባ" ብለው ጥቅምት 14 ቀን ደብዳቤ ፃፉላቸው ። ከ15 ቀናት በኋላ ለወይዘሮ ንግሥት በጻፉላቸ ውም ደብዳቤ ". . . . አንቺ የፈቀድሽውን እገሌን አገባለሁ ብለሽ ንገ ሪና እሱ አባት ሆኖ ይስጥሽ ። ጭራሽም አላገባም ብትይም እንደወ ደድሽ" ብለው ላኩባቸው ። ለዚህም መልስ ወይዘሮ ንግሥት ደጃች ገሠሠን አገባለሁ ብለው ስለላኩ ለደጃች ገሠሠ ተዳሩ ።

ልጅ መርድ ሳያገባት ቀረ ብለው የተናደዱት ራስ ቢትወደድ መንገሻ ለአጤ ምኒልክ ይህንኑ የሚገልፅ ደብዳቤ ፃፉላቸው ። አጤ ምኒልክም ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለራስ ቢትወደድ መንገሻ ፃፉ ።

". . . . . መርድ ሊያገባት የነበረችውን ደጃች ገሠሠ ሊወስዳት ነው ብለህ ላክብኝ ። ቀድሞስ አንተ ወይዘሮ ላቀች* እሺ ብላለች ። ነገር ግን አለጃንሆይ ፈቃድ አይሆንም አለች ብለህ ብትነግረኝ ፣ እኔም እሺ ምን ከፋኝ ታግባ ብዬ ላክሁ ። እስዋ እንደወደደች ነው እንጂ ፣ እገሌን ታግባ ፣ እገሌን አታግባ የምለው እኔ ምን አግብቶኝ ነው ። አንተስ ቀድሞውን የሷን ልብ ሳትይዝ ፣ እሷን ሳትለማመጥ ወደኔ ምን ያስለምን ነበር ። አሁንስ ደግሞ ከጀመርከውስ ወዲያ የሷን ዝምድና ከፈለግኸው አባቷ የሞተባት ችግረኛ ነበረች ፣ ይህን ገንዘብ

---

* የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሚስት የወይዘሮ ንግሥት እናት ናቸው ።

ለችግርሽ ጉዳይ አድርጊ ፡ ይህች በቅሎ ላንቺ ትሁን ፡ ይሄነን ጉልት ሰጥቼሻለሁ ብለህ እዚያው አባቷ አገር ፡ ሲሆን ሁለት ጉልት ፡ ሳይሆን አንድ ጉልት ሰጥተህ ፡ እቆላምጠህ ባታለልካት ነበር እንጂ ፡ አሁን እሷ አይሆንልኝም ፡ የወደድሁትን አገባለሁ ስትል ጊዜ የንጉሥ ተክለሃይ ማኖትን ልጅ ገረድ ይመስል በግድ አንቁ ልሰጣት ነውን ፡ ምን ይሁን ማለትህ ነው ።

እንዲያውስ ቀርቦ ያንሳኝ ያለች ጊዜ ፈቃድዋ አለመሆኑን በዚህ አታውቅምን ። ነገር ግን ፡ እኔ ያገባኝ የነበረ ፡ እሷ ከቀድሞ ፡ ንጉሥ ላሉት ይስጡኝ ብላኝ ፈቃድ ሰጥታኝ በሆን ፡ እንግዲያውስ የለመነኝ መርድ ነው ብዬ እበይን ነበር ። እሷ ሳትፈቅድ ማን በግድ ይላል ። አንተ ግን ሁልጊዜ የጌትነት ሥራ እኔ ያልሁት ለምን ይቀራል ብለህ ነው እንጂ ይህስ ነገር የሚያስልክ ሆኖ አይደለም ። እንኳን ይህቺ ፡ የወለድካት እንኳ ልጅህ ላቀች አልታዘዝ ብላ አሸንፋ ቀረች ። ደግ ሞም የዚህ ነገር በደብዳቤ አያልቅም ። በተገናኘን ጊዜ እንነጋገራለን ።

ኅዳር ፰ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓመተ ምህረት አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ ።

በጋብቻው በኩልም ይህ ብቻ አይደለም ። እስላምና ክርስቲያን እንዲጋባ የሚያደርጉ ታላቅ ንጉሥ ነበሩ ። ሁለቱንም ቢሆን ከመጋ ባት የሚከለክል የሃይማኖት ደንብ ያለመኖሩን አይተው ልጃቸውን ወይዘሮ ሸዋረጋን ለወሎው ኢማም መሐመድ አሊ ድረዋል ። ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንደሚገልጡት "....ያልተጠመቀ እስላም የተጠመቀች ይቱን ክርስቲያን ማግባት ያልተለመደ ነበርና ለጊዜው ሕዝቡ ሁሉ በጣም ገረመው...." ብለዋል ። እንዲህ ዓይነቱን ስንመለከት ምኒ ልክ በአበተዳደር ዘመናቸው ለሰው ልጅ መብት ምን ያህል ያስቡ እንደነበረ እንረዳለን ።

ምኒልክ ያወጡትን ደንብ ሲያፈርሱ ፡ ወይም ሲሳሳቱም ቢሆን ሹማምንቶቻቸውን ይቅርታ የሚጠይቁ ሰው ነበሩ ። ሹሞቻቸውም በግልጽ ደንብ ሽረዋል ፡ አላግባብ ሠርተዋል እያሉ ይከራከሩዋቸው ነበር ። ምኒልክም ተከራክረው ከተሸነፉ "አጥፍቻለሁ ቅጡኝ" የሚሉ እንጂ "ተደፈርኩ" የሚሉ አልነበሩም ። አንድ ጊዜ አንዲት ሴት የም ኒልክን የአትክልት ቦታ በርስትነት እንዲሰጣቸው ለመኑ ። ምኒልክም ሰጥቼሻለሁ አሏቸው ። ሹማምንቶቻቸው ቀርበው "ጃንሆይ ፡ ይህ ቦታ ለቤተ መንግሥቱ አትክልት ማቅረቢያ ብለን ያለማነው ነው ። ለቤተ መንግሥቱ ሸንኮራም ሆነ ሙዝ ፡ ትርንጎም ሆነ ሎሚ የሚመጣው ከዚህ ቦታ ስለሆነ ለሴቲቱ ሌላ ይሰጥና ታልማ እንጂ ይሄን መስጠት አይሆንም" አሏቸው ። ምኒልክም "እሷም እኮ የለመነችኝ ትርንጎና

ሎሚ በማየቷ ነው ። ሌላ ደረቅማ መች ትለምን ነበር ። የለመንችው ገብቼ ልብላ ብላ ነው እንጂ ሥርቼ ላልማ ብላ አይደለም ። ሴት ናት ። አቅም የላትምና ስጧት'' አሉ ። በዚህ በምኒልክ ትእዛዝ የተናደዱት አዛዦች ፡ "ጃንሆይ ፡ ለእርስዎስ ፍሬው ከየት ይመጣል ?'' ቢሏቸው "ኢትዮጵያ በሙሉ የኔ ሆና ለትንሽ ፍሬና መሬት ብዬ እንዴት ይህቺን የጓጓች ሴት እከለክላታለሁ ። ይሄ የለማው ለሷ ይሰጥና ለራሴ ፍሬ ካማረኝ እኔ አለማለሁ'' ብለው አሰጧት ። ሴትዮዋም መሬት ስማ "ጃንሆይ ፡ ከፍሬው ግብር አውጥቼ ድርሻዎን የየለት ምግቦን ፍሬ እልክሎታለሁና ሌላ መሬት ለፍሬ ብለው አያልሙ'' ብትላቸው "ይሄማ ገላገልሽኝ ። ሌላ ሥራ ከመፍታትም አዳንሽኝ ።ግን ሹሞቼ ይሄን ነገር ሰምተዋልና ፍሬው ቢደርቅ ከየት ታመጫለሽ ። ያስሩሻል'' አሉ ፡ ያቺም ተራ ሴት ጠንካራ ኖራ "ባሌ ወታደር ነው ። እንዳይዘርፍም እንዳይቀማም እርስዎ ባዋጅ ከልክለዋል ። ለእርስዎ ብዬም ከሰው አትክልት ገብቼ አልሰርቅም ። የሰጡኝ መሬት ፍሬ ሲኖረው ብዙውን እኔ ፡ ከባሌና ከልጆቼ ጋር እንበላለን ። ድርሻዎንም እንልካለን ። ካላፈራ ግን የምሰጥዎት የለኝም ። ሁሌ ፍሬ እንዲያፈራም መርቀው ይስጡኝ'' አለቻቸውና መርቀው ሰጧት ። ይህን ታሪክ ያጫወቱኝ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ናቸው ። ግሪንፊልድም ". . . .ምኒልክ ምንምርስት አልነበራቸውም ። ምናልባትም ኢትዮጵያ በሙሉ የኔ ነች በሚሉት ምክንያት ይሆናል. . . .'' ሲል ጽፎላቸዋል ።

ንጉሶቹ ቀርተው መኳንንቱ እንኳ ብዙ ሀብትና ገንዘብ በያዙበት ጊዜ ምኒልክ የገንዘብ ችግር እየደረሰባቸው ከየነጋዴው እየተበደሩ የሚኖሩ ነበሩ ። ይህን ለማወቅ ኅዳር 14 ቀን 1900 ዓ. ም. ለደጃች ገሠሠ በፃፉት ደብዳቤ ". . . . ብር ለመውሰድ የሰደድሃቸውን ሰዎች ያከረምናቸው ብር ባይመጣልኝ ነው ። እስካሁን እንኳ ሳይመጣልኝ ቀርቶ ደመወዘተኛውም አልተቀበለም ። አሁንም ሰዎችህ ይህን ሲጠብቁ ብዙ ቀን እንዳይቆዩ ብዬ ከነጋዴ ተበድሬ 5000 ብር ሰድጄልሃለሁ. . . .'' በማለት ጽፈውላቸዋል ።

እንደ አገራችን ባህልና ልማድ ፡ እንኳን መኳንንቱ ድሃውም ቢሆን ጠንቋይ ይወድ ነበር ። መኳንንቶችም ፡ የታወቁ ጠንቋዮች ወይም ቃልቾች ሲገኙ የግል እያደረጉ ያስቀምጧቸው ነበር ። ምኒልክ ግን የተገላቢጦሽ ነበሩ ። ሐምሌ 11 ቀን 1900 ዓ. ም. ያወጁት አዋጅ ጠንቋይ እንደማይወዱ ይነግራል ። አዋጁም እንዲህ ይላል ". . . .ከጠንቋይና ከባለዛር ዘንድ የሚያስጠነቁል ሰው ጠንቋይም አስጠንቋይም ይቀጣል ብዬ ከዚህ ቀደም አዋጅ ነግሬ ነበር ። አሁን ግን እዚሁ እከተማችን ተገኘ ። አሁንም እከተማ በየሠፈርህ ያለውን ጠንቋይና ባለዛር የምታውቀውንም ፡ ልብህ የሚጠረጥረውንም እጁን ይዘህ

አምጣልኝ ። ይህንንም ያደረገ መንግሥቴን መውደዱ በዚህ ይታወቃል ። እንግዲህ ግን ደብቆ የተገኘ እኔንም መንግሥቴንም ባይወድ ነውና ጠንቋይና ባለዛር የተገኘበት ሰው እሱንም ፡ ጠንቋዩንም ጠላቱ በመስከረበት እቀጣዋለሁ ። እርስቱንና ገንዘቡንም ለከሳሽ መርቄለታለሁ'' ይላል ። ከባድ አዋጅ ነው ። በተለይ "ጠላቱ በመስከረበት'' የሚለው ቃል አደገኛና መድረሻ የሚያሳጣ ነው ።

ምኒልክ ለድሃ ሕዝባቸው ተቆርቋሪ በመሆናቸው በክረምት ፍርድ ቤቶች ሁሉ እንዲዘጉ በአዋጅ የደነገጉ ሰው ናቸው ። ሐምሌ 13 ቀን 1900 ዓ. ም. ከታወጀው አዋጅ ብጠቅስ " . . . .ለነገር የመጣህ ሰው ሁሉ በየአገርህ ገብተህ እርሻህን እረስ ። ነገርህን በመስከረም እየመጣህ ጨርስ ። በመሬትም የተጣላ ሰው እስካሁን በእጁ የነበረውን እንዳለ በእጁ ይዞ ክርሞ በመስከረም ይታይለታል ።ሹማምንትም እስከ መስቀል ድረስ በዳኝነትና በውርርድ አታግት. . . .''ይላል።

ምኒልክ እርቆ አሳቢ መልካም አስተዳዳሪ መሆናቸውን የምንረዳበት ብዙ ምክንያቶች አሉ ። እስካሁን ያነበብናቸው ትረካዎች ጥሩ ምስክሮች ቢሆኑም ሌላ ሌላም ጥቃቅን የሚመስሉ ነገሮች አሉ ። ለምሳሌ በድሮው ጊዜ አንድ ሰው ትንፋሹ ከተቋረጠ ሞተ ተብሎ ወዲያውኑ ይቀበር ነበር ። ምኒልክ ግን ሐምሌ 13 ቀን 1900 ዓ.ም. ባወጡት አዋጅ ቶሎ መቅበርን ከለከሉ ። አዋጁም " . . . .የታመመ ሰው ብዙ ቀን ታሞ ቢሞት ፡ ድንገትም ቢሞት ፡ 12 ሰዓት ሳትጠብቅ አትቅበር ። ለቅሶም 12 ሰዓት ሳይሆን ጭራሽ መሞቱ ሳይታወቅ አታልቅስ ። 12 ሰዓት ሳይሆን ያለቀሰ ሰው ፡ 12 ሰዓት ሳይሆን የቀበረ የነፍስ ገዳይ ያህል ነውና ይቀጣል'' ይላል ።

የኀዘን ለቅሶንም ቢሆን ሥርዓት ያሲያዙ ምኒልክ ናቸው ። በድሮው ጊዜ አንድ ኀዘንተኛ ቢያንስ ለአርባ ቀናት ያህል ከቤት ውስጥ በኀዘን በመቀመጥ ከመጣው ጋር ሁሉ እየተላቀሰ ይከርም ነበር ። ይህ እንዳይሆን አንድ ኀዘንተኛ ለኀዘን ከቤቱ የሚቀመጥበት ጊዜ ለሶስት ቀናት ብቻ እንዲሆን አወጁ ። በዚህ ሶስት ቀናት እንዲሆን በተባለው አዋጅ ሕዝቡ ከፍቶት ሲያጉረመርም ምኒልክ የልጅ ልጃቸው ከወይዘሮ ሸዋረጋና ከወዳጆ ጉበና በ1877 ዓ.ም. የተወለደው ደጃች ወሰን ሰገድ ገና በወጣትነት ጊዜው ሞተ ። ለቀብር የተሰበሰበው የአዲስ አበባ ሕዝብም "በራሳቸው መጣ ። እስቲ የእዝኑን ቀን ብዛት እናያለን'' እያለ እያማ ጠበቀ ። ምኒልክ ግን ልጃቸውን ቀብረው ፡ ከቀብር መልስ ከችሎት ተቀምጠው ሥራ ጀመሩ ።

በማግስቱም በያገሩ ላሉት መኳንንት ሁሉ ለእያንዳንዳቸው በየስማቸው ቃሉ አንድ ዓይነት የሆነውን ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጻፉ



ደጃዝማች ወሰን ሰገድ

ላቸው ። "ምንም ብናለቅስ ፣ ብናዝን ፣ ማቅም ቢለበስ እግዚአብሔር ፊቱን አልመለሰልንም ። አሁን ደግሞ ይሄው ልጁ ደጃዝማች ወሰን ሰገድ ታሞ ነበር ። በመጋቢት ፳ ቀን አረፈ ። እኔም የእግዚአብሔርን አመጣጥ ስለፈራሁ መድፍ ሳላስተኩስ እምቢልታም መለከትም ሳላስ ነፋ ተቀበረ ። እናንተም እንዲሁ ዝም ብላችሁ በልባችሁ በየቤታችሁ እዘኑ እንጂ የወትሮውን የለቅሶና የኀዘን ሥርዓት መተው ነው ። አን ተም እዚያው ሆነህ ኀዘንህ ነውና እዚያው ሥራህን ያዝ እንጂ ለልቅሶ ብለህ ሥራህን ትተህ ወደዚህ አትምጣ ። እግዚአብሔር በሕ ይወት ለመገናኘት ያብቃን ።

መጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ምኒልክ ኀዘን የደረሰበትንም ሰው ሲያፅናኑ ኀዘኑን እንዲተዉ ይመክራሉ እንጂ በኀዘኑ እንዲገፉበት አያደርጉም ነበር ። ይህን ከመ ሳሰሉት ደብዳቤዎቻቸው አንዱን እንመልከት ።

ይድረስ ከእሜቴ እሴተማርያም ።

የልጅሽን መሞት ሰማሁ ። እንዴት ያለ ያልታሰበ አደጋ አገኘሽ። እግዚአብሔር ያጥናሽ ። ምንጊዜም ሰው ተፈጥሮ መሞት ልማድ ነው ። ነገር ግን አንቺ ኀዘን እያበዛሽ ኀዘን ተለይቶሽ አያውቅም ። ከእግዚ አብሔር ጋራ መተላለክ መቼ መልካም ነው ። በኀዘንም ሰው ከተመ ለሰ የሞቱት ሁሉ ይመለሱ አልነበረምን ። አሁንም እንግዲህ ወዲህ ኀዘን የሆነ ነገር የሰማሁብሽ እንደሆነ ሁሉንም የምትፈጂያቸው አንቺ ነሽ እንጂ እግዚአብሔር አይደለም ። ይህንንም ማለቴ ለሚሞቱት ሰዎች አዝኜ ነው እንጂ ላንቺ ብዬ አይደለም ።

መጋቢት ፳፫ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ሰው ሲሞት አቀባበሩ ድሃ ከሆነ እንዲያው ጉድጓድ ቢጤ ተምሶ ሳይርቅ ይቀበር ነበር ። ይህም ጅቦች ሬሣውን እያወጡ መብ ላት በመላ ኢትዮጵያ የተለመደ ነበር ። ምኒልክ ግን ሰኔ 16 ቀን 1900 ዓ.ም. የሚከተለውን አዋጅ አወጁ ። "ሰው ሲሞት መቅበር ከጥንት የመጣ ልማድና ትእዛዝ ነበር ። አሁን ግን በየገዳሙ ዋሻና በየአድባራቱ አፀድ ውስጥ ሁሉ የሚታየው የሰው አጽም ብቻ ሆነ ። የጥንት ልማድና ሥርዓት መቅረቱስ ለምንድነው፧ አሁንም በየገዳ ሙና በየአድባራቱ በሌላውም ሥፍራ ሁሉ ሳይቀበር የተገኘውን የሰው አጽም የክርስቲያን ፣ የእረመኔም ቢሆን በየግዛትህ ፣ በየአጥቢያህ እያስፈለግህ ቅበር ። አዲስም ጉድጓድ ሲቆፈር የተገኘውን አጽም

ወደ ውጭ እንዳይቀር መልሰህ ቅበር ። እንግዲህ ወዲህ ግን በየግዛቱና በየኢትዮጲያው የሰው አጽም ሳይቀብር የተገኘ ሰው ብርቱ ቅጣት ይቀጣል ። መሬትህንም ትነቀላለህ ።'' ይህ የምኒልክ አዋጅ እስከዛሬ ድረስ በመፈፀም ላይ ነው ። መቃብር ሲቆፈር የሚገኝ አጥንት አሁንም ከዚያው ተመልሶ ይቀበራል ።

ምኒልክ መቅበርን በአዋጅ የተናገሩት ለሰው ብቻ ሳይሆን ለከብቱም ጭምር ነው ። የከብት ማከሚያ መድኃኒት ካስመጡ በኋላ ስለክትባቱና ስለሚሞተውም ከብት የሚከተለውን አወጁ ። ''በአገራችን የከብት በሽታ መድኃኒት በመታጣቱ ከብት ሁሉ ሲያልቅ ኖረ ። ዛሬ ግን ለቀንድ ከብትም ፡ ለጋማ ከብትም ፡ ለእንስሳት ሁሉ መድኃኒት የሚያደርግ ሐኪም አስመጥቻለሁና ከብት የታመመብህ ሰው ለሹምህ እየነገርክ ለከብቱ መድኃኒት ይደረግለታል ። ከብቱም በታመመ ጊዜ የታመመውን ከብት ከደህናው ከብት እየለየህ ለብቻው አጥር እያሳጠርህ አስታም ። ቢሞትብህም ለሹምህ እየነገርክ ትልቅ ጉድጓድ እየቆፈርክ ከነቆዳው ሲሞት የወደቀበትንም መሬት እየቆፈርክ አፈሩንም አብረህ ቅበር ። ነገር ግን የሞተውን ከብት ብቻውን ለመቅበር ያልቻለ ሰው በየወረዳው ያለው ሰው በሹም እየታዘዘ አብሮ ይቅበር ። እንዲህ ሆኖ በጥንቃቄ እየተጠበቀ የተቀበረ እንደሆነ በሽታው ይጠፋል ። ከብቱም እንደቀድሞው ይበዛል ። ሥጋውን እበላለሁ ፡ ቆዳውን እሸጣለሁ ብሎ ያልቀበረ ሰው ፡ በሽተኛውን ከብት ከደህናው ከብት የቀላቀለ ሰው ይወረሳል ።

መጋቢት ፲፱ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም. አዲስ አበባ ።

እንግሊዛዊው ዲፕሎማት ግሊከን በመጽሐፉ የፃፈውን ልጥቀስ ። '' .... የወደፊቷ አበሻ ምኒልክ በሁፋናቸው እስካሉ ድረስ ባለብሩህ ተስፋ ነች ። ንጉሡ የሥራ ጊዜያቸውን ሁሉ የሚያሳልፉት ለአገሪቱና ለሕዝቡ አንድነት በመሥራት ነው ። ሕዝቡ ግን ወደፊት ተራማጅ ባለመሆኑ ጊዜ ይወስዳል ። . . . . '' ብሏል ።

ምኒልክ ደግና አስተዋይ አስተዳዳሪ ነበሩ ። የሐረርጌ ጦርነት ሰሞን አዲስ አበባ የቀሩት ራስ ጐበና መንግሥት ሊገለብጡ ነበር ተብለው ተከሰሱ ። ምኒልክ ችሎት ላይ ቀርበው መኳንንቱ ሲፈርድ ይሙት ቢቃ ሲል ግማሹ ደግሞ ይታሠራል እንጂ ጐበናን ያህል ሰው አይገደልም እየለ ፈረደ ። ፍርዱን የሚያፀኑት ምኒልክ ስለሆኑ ከሁለት አንዱን ያፀናሉ ተብለው ሲጠብቁ '' . . . . ጐበናን እዚህ ለማድረስ ሰላሳ ዓመት ፈጅቶብኛል ። ላንድ ቀን ጥፋቱ ብዬ የሰላሳ ዓመት ድካሜን አላበላሽምና ምሬዋለሁ ፡ እንደጥንቱ ይኑር'' ብለው ፈረዱ ።

ጐበናን የመሰለ ታላቅ ጀግና ሰው መግደሉ ባያቅትም ፡ ጐበናን የመሰለ ታላቅ ጀግና ማፍራቱ ግን ብዙ ዓመት ይጨርሳል ።

የምኒልክ የችሎት ጊዜ ከጧቱ ፩ ሰዓት በኋላ ነው ። ረቡዕ የፍትሐ ብሔር ክርክር ፡ አርብ የወንጀል ጉዳይ ይዳኛሉ ። ከቅዳሜና ከእሁድ በስተቀር በሌላው ቀን ችሎት አለ ። ምኒልክ ቀጠሮ ያለው ነገረተኛ ባይኖርም ችሎት ይቀመጣሉ ። በችሎት ሲቀመጡ ማንኛውም ባለ ጉዳይ "አቤት" ይላል ። ይህም አቤት ባይ በእልፍኝ አስከልካዩ አማካይነት እየቀረበ ጉዳዩን ያመለክታል ። ጉዳዩ ቀላል ከሆነ ወዲያው ይፈፀምለታል ። ጉዳዩ ከባድ ወይም ማጣራት የሚያስፈልገው ከሆነ "እከሌና እከሌ ያጣሩልህ" ተብሎ ወዲያው ባልደረባ ይቀበላል ። እነኚያም ባልደረባ የሆኑት ሰዎች ዕለቱን አጣርተው ያቀርባሉ ። ችግር ቢያጋጥምም ችግሩን ለምኒልክ ነግረው ቀን ያስቀጥላሉ እንጂ በፈቃዳቸው ማሳደር አይችሉም ። ያሳደሩ ዳግመኛ በዚያ ችሎት ቦታ አይገኙም ። ምኒልክ ችሎት በሚቀመጡበት ጊዜ ከኋላቸው ጠመንጃና ጋሻ የያዙ 30 ሰዎች ይቆማሉ ።

የምኒልክን የአስተዳደር ሁኔታ ስንመለከት የፌዴሬሽን አቋምነት የነበረው ነው ። ደጋግሜ እንዳልኩት በየትኛውም አገር ለአስተዳደር የሚሾመው የአገሩ ተወላጅ ሲሆን ጦሩን የሚያዘውና አገሩን የሚጠብቀው ግን ከማዕከላዊ መንግሥት የሚሾመው ሰው ነው ። በየአገሩ ያሉት አስተዳዳሪዎችም የተወሰነባቸውን ግብር ለማዕከላዊው መንግሥት ከመገበር በስተቀር ሌላ የሚጠየቁት አልነበረም ። ዳኝነትና ፍርድም ሰው ከገደለ ሰው በስተቀር የየአስተዳዳሪዎቹ ነበር ።

እርግጥ እንዲህ ዓይነቱ አስተዳደር በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ በእኩልነት ደረጃ አልነበረም ። አንዳንዱ አገር ከጥንት የንጉሥ ግዛት የነበረው የንጉሱ ልጅ ወይም ዝርያ ለአስተዳዳሪነት ሲሾም በበላዩም ሌላ የወታደር አስተዳዳሪ አይደረግበትም ። ያም ቢሆን አስተዳዳሪው የአገራቱን ግብር ሰብስቦ ለራሱ ወይም ለግዛቱ ልማት ካዋለ በኋላ ለማዕከላዊው መንግሥት የተወሰነበትን ግብር ይከፍላል ። በዘመኑ የነበሩት የዝርያ አስተዳዳሪዎች ግን የሕዝቡን ግብር ለአገራቱ ልማት በማዋል ፈንታ ለራሳቸው ጥቅም ያውሉት ነበር ። ጠቀም ያለ ልማት ሠሩ የሚባሉት አገረ ገዢዎችም በወንዝ ላይ ድልድይ ማሠራት ነበር ። የጂማው አባ ጅፋር ግን ለግዛታቸው ከሁሉ ተለይተው ጠቀም ያለ ተግባር የፈፀሙ ናቸው ።

የአገር አስተዳደር ጉዳይ ከተነሳ ግዛቶች በአማካሪዎች ሥልጣን ሥር እንዲተዳደሩም ጀምረው ነበር ። እርግጥ በሁሉም ዘንድ ተጀምሮ

ነበር ባይባልም ያንጊዜ ከሌሎቹ ግዛቶች ሁሉጠን ብላ ትታይ በነበረችው በድሬዳዋ ከተማ ተጀምሮ ነበር ። ለድሬዳዋ ከተማ በሰኔ 27 ቀን 1898 ዓ. ም. የተሰጠው በመማክርት የመተዳደሪያ ደንብ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

እኔ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ፤

ይህንን ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ፈቃድ ሰጥቻለሁ ።

## መጀመሪያ ክፍል

ለድሬዳዋ ከተማ ጥቅም ሁሉ እየመረመሩ የሚሠሩ አማካሪዎች ይመረጣሉ ። ለዚህም ምክር የሚመረጡ እነዚህ ናቸው ።

መጀመሪያ ፤ የሐረር ገዥ ደጃዝማች ይልማ ።

ሁለተኛ ፤ ነጋድራስ ይገዙ ።

ሶስተኛ ፤ የጅምሩክ ሹም አቶ ንጋቱ ።

አራተኛ ፤ የምድር ባቡሩ የሥራ አለቃ ሙሴ ቢ ።

አምስተኛ ፤ ድሬዳዋ የሚቀመጠው የኩባንያዎች ወኪል ሙሴ ካሬት ።

ስድስተኛ ፤ የድሬዳዋ ሐኪም ዶክተር አንቷን — እነዚህ ናቸው ።

## ሁለተኛ ክፍል

የእነዚህም አማካሪዎች አለቃቸው የደጃዝማች ይልማ እንደራሴ ነው ። ይህም አለቃ ጉዳይ በታሰበ ጊዜ ለምክር ይሰበስባቸዋል ። ጉዳይም ባይኖር በወር በወሩ መሰብሰባቸው አይቀርም ።

## ሶስተኛ ክፍል

እንደዚህም ተሰብስበው ለከተማው ፀጥታ የሚመችውን ነገር ሁሉ ይመክራሉ ። በከተማውም ለሚታሰበው ጉዳይ ፤ ለሚያስፈልገውም ገንዘብ ይህ ይበቃል ብለው ይቆርጣሉ ። ይህም ገንዘብ የሚወጣው በከተማው ውስጥ ከሚኖሩ ሰዎች ነው ።

## አራተኛ ክፍል

እነዚህም የከተማ አማካሪዎች የመከሩት ቃል ሲተካከል ከሁለት ላይ ተጽፎ አንዱ ወደ ጃንሆይ ፤ አንዱ ለሐረር ገዥ ለደጃዝማች ይልማ ይላካል ።

## አምስተኛ ክፍል

ድሬዳዋ ያለውም የደጃዝማች ይልማ እንደራሴ እነዚህ የመከፋ ትን ቃል ሁሉ ለማስተረፍ ፈቃድ አለው ።

ሰኔ ፳፮ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ. ም.

ምኒልክ የነበራቸውን የአስተዳደር ጥበብ በመጠኑ ገልጫለሁ ። በምኒልክ የአስተዳደር ታሪክ ውስጥ እኔን የሚገርመኝ አለ ። በውስጥም ሆነ በውጭ ታላላቅ የሆኑ አገሪቱን የመምራትና መንግሥቱን የማስተዳደር ሥራ እያለባቸው ለተራ ነገሮች ሁሉ ከየመኳንንቱ ጋር ደብዳቤ መጻጻፋቸው ነው ።

ከምኒልክ ደብዳቤዎች አምስት ሺህ ያህሎቹን አንብቤአለሁ ። በነዚህ ባነበብኳቸው ደብዳቤዎች ብዙ ቁም ነገር ያለባቸው አሉ ። አንዳንዶቹ ደግሞ እንኳን ባንድ ንጉሠ ነገሥት ደረጃ በተራ መኳን ንትም ደረጃ ቢሆን ደብዳቤ ሊጻፍባቸው የማይገቡ ናቸው ።

ደብዳቤዎቻቸውን ስናነብ ምኒልክ ሥልጣን ወዳድና የሁሉንም ሥልጣን ጠቅለው የያዙ ሊያስመስላቸውም ይችላል ። ግን በዚህ ዓይ ነቱ አፈራረድ ምንም እንኳን ሥልጣን ይወዳሉ ብንልም የታሠሩ ኩበት ለቃሚዎችን ለማስፈታት ፣ ኖራ ለማስነጠርና ጠርቡ እንዳይወ ላገድ በደንብ አስቀምጡት የሚል ደብዳቤ የመጻፍ ሥልጣን አይሻ ሙም ። ሁኔታው ባጭሩ ግን በለሞንድ ጋዜጣ ላይ በኢትዮጵያ የፈ ረንሣይ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የነበረው ክሎብስኪ እንደጻፈው ከሁሉ ጋር መሥራት ስለሚወዱና ሥራ ወዳድ በመሆና ቸው ነው ። የቀልድ አጻጻፋቸውም ቢሆን ምን ያህል ተወዳጅነት እንደሚያተርፍላቸው መገመት ይቻላል ።

ደብዳቤዎቻቸውን ስናይ ምኒልክ ሥራ የሚጀምሩት ከለሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ነው የተባለውን እውነት ሆኖ እናገኘዋለን ። ጥቃቅን ነገር ሁሉ ምን ያህል ሥራ ያበዛባቸው እንደነበርም እንረዳለን ። ለዓይነት ያህልም ሥራ አስፈች ደብዳቤዎቻቸውን ከዚህ ቀጥዬ ሳስ ገባ እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎችም መኖራቸውን ለመግለጽ እወዳለሁ ። ደብዳቤዎቹ የተቀመጡት በተፃፉበት ቀን ተራ መሠረት ነው ። ደብዳ

ቤዎቹ አንዳንዶ ለአንባቢ ግራ የሚያጋቡ የመሰሉኝን ከየደብዳቤዎቹ ግርጌ በቅንፍ መጠነኛ መግለጫ ሰጥቻለሁ ።

ይድረስ ከሙሴ ኢልግ

ለአትክልት ውሃ ማጠጫ ሰው በእጁ እየያዘ ወዲያም ወዲህ እየወሰደ የሚያጠጣበትን እፈልጋለሁና 200 ሜትር የሚሆን ፈልገህ ቶሎ እንዲመጣልኝ ይሁን ። ያውም የላስቲክ የሆነ እንደሆነ መንገዱ ቆላ ነውና ሲመጣ እንዳይበላሽ የላስቲክ መሆኑ ቀርቶ የሸማ እንዲ ሆንልኝ ይሁን ።

ጥቅምት ፳፯ ቀን ፲፰፻፹፯ ዓ. ም. አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

(ኢልግ በዚህ ጊዜ ዙሪክ ነበር)

ይድረስ ከክቡሩ የመስኮብ መንግሥት ትልቁ ዱክ ኒኮላዎስ ።

በኮንት ሊዎንቲዬቭ እጅ የላኩልኝ ውሾች ከኔ ዘንድ ሳይደርሱ በመንገድ ሞቱ ብሎ ቢነግረኝ እጅግ አሳዘነኝ ። እርስዎ ግን ስለመል ካሙ አሳብዎ እግዚአብሔር ያመስግንዎ ።

በሰኔ ፫ ቀን በአ. አ. ከተማ ተጻፈ በ፲፰፻፹፱ ዓ. ም.

ይድረስ ከሙሴ ለበርቱዋ

የላክልኝ የሸቱ ሳሙና ደረሰልኝ ። ሽታውም እጅግ ማለፊያ ነው ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ።

በጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፰፻፺፪ ዓ. ም. አ. አ. ተጻፈ ።

ይድረስ ከሙሴ ሞኬ ።

በሙሴ ጋቲከር እጅ የላክልኝ ዶሮዎች በመንገድ ከሞቱት በተ ቀር ደረሱልኝ ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ። እነዚህንም ዶሮዎች ሐረ ርጌ ላይ ማስቀመጤ አገሩን ጥቂት እስቲለምዱት ብዬ ነው እንጂ የከፋት ነገር የለም ።

በጥቅምት ፳፭ ቀን ፲፰፻፺፪ ዓ.ም. አ.አ. ተጻፈ ።

ይድረስ ኀበ ክብርት ወልዕልት ንግሥት ቪክቶሪያ ።

የእንግሊዝ ንግስት ፤ የሕንድ ነገሥታት ንግሥት ፤ የሃይማኖት ጠባቂ፤ የክርስቲያን ረዳት ።

ሰላም ለርስዎ ይሁን ። የሰደዱልኝ ሁለት ፈረሶችና ውሾች ደረሱልኝ ። ፈረሶቹም እጅግ ያማሩ ማለፊያ ናቸው ። ውሾቹም ሩጫቸው ትንግርት ነው ። በአገራችን እንደዚህ ሩጦ ጥንቸል የሚይዝ ውሻ ከዚህ በፊት አላየንም ። ይህንን ሁሉ አስበው ስለሰደዱልኝ እጅግ አመሰግንዎታለሁ ።

በሰኔ በ፭ ቀን ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. አ.አ. ከተማ ተጻፈ ።

ይድረስ ከደጃዝማች ሊ.ምንቴ፣ ።

ከዚህ ቀደም ያመጣህልኝ ባለወርቅ ባርኔጣ አንድ ብቻ ሆኖና አሮጌ ሆነብኝ ። አሁንም እንደዚያው ያለ ማለፊያ ባርኔጣ እንድታመጣልኝ ይሁን ። ሁሉንም ነገር አንተ ታውቀዋለህ ።

ጥቅምት ፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. አ. አ. ከተማ ተጻፈ ።

(ሊ.ምንቴ፣ በኢትዮጵያ የመስኮብ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ነበር ። ይህ ደብዳቤ በተጻፈለት ጊዜ ለሥራ ጉዳይ ወደ ሞስኮ ሔዶ ነበር ።)

ይድረስ ከቢትወደድ ኢልግ ።

. . . ለጫማ የሚሆን የብረት ቅርጫር ከዚህ እኔ ዘንድ ታጣ ። ምናልባት አንተ ዘንድ ይገኝ እንደሆነ እንድትሰድልኝ ይሁን ።

ሐምሌ ፱ ቀን አዲስ ዓለም ከተማ ተጻፈ. ፲፱፻፶፫ ዓ.ም.

(ድሮ የጫማ ቆዳ ፡ ሶሉ እንዳያልቅ ፡ በሶሉ.ታም ላይ እንዳያዳልጥ ከጫማው ሥር ብረት ወይም ኩርንችት ሚስማር ይመታበት ነበር ። በዚህ ጊዜ ኢልግ አዲስ አበባ ነበር ። ላከ ወይስ ቀረ?)

ይድረስ ከቢትወደድ ኢልግ ።

የሰደድክልኝ የጫማ ቅርጫር ደረሰልኝ ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ። ማነሱ ነው እንጂ ቅርጫሩ እጅግ ማለፊያ ነው ። ለሁለት ጫማ እንኳ ሳይበቃ ቀረ ። አሁንም የዚህን ዓይነት ቅርጫር ልከህ እንድታስ

መጣልኝ ይሁን ። .... ሚስትህስ ለጤናዋ እንዴት ናት ። ለሷም ሰላምታ እንድታደርስልኝ ይሁን ።

ሐምሌ ፲፫ ቀን አዲስ ዓለም ከተማ ተጻፈ በ፲፰፻፺፫ ዓ.ም.

ይድረስ ከቢትወደድ ኢልግ ።

. . . .የጫማውም ቅርቃር ደረሰልኝ ። እኔስ አነሰ ብዬ መላኬ ለኋላው እንድታስመጣልኝ ነው እንጂ ለአሁኑስ አያስቸኩልም ነበር ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ።

ሐምሌ ፳፰ ቀን አዲስ ዓለም ከተማ ተጻፈ በ፲፰፻፺፫ ዓ.ም.

ይድረስ ከቢትወደድ ኢልግ ።

የነገርከኝ የቁንጫ መድኃኒት በስሃን አድርገን ብንሞክረው የሚያልቀው ቁንጫ እጅግ በጣም ጉድ ነው ። አንተው እንዳልከው እውነተኛ መድኃኒት ሆነ ።

መስከረም ፺ ቀን አዲስ ዓለም ከተማ ተጻፈ በ፲፰፻፺፬ ዓ.ም.

ይድረስ ሚላንስ ከተማ ካሉ የሚላንስ ማህበር አለቆች ።
. . . .ከእናንተ ላይ ብር ለመዳረግ እንዲመቸኝ ሁለት ሽህ የሚባል መጽሐፍ ላኩልኝ ።

ታህሣሥ ፲፰ ቀን ፲፰፻፺፬ ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

(ከውጭ አገር ዕቃ ለማስመጫ ሚላን ከተማ ባንክ ገንዘብ አስቀምጠው ነበር ። ሽህ ያሉትም ቼክ ማለታቸው ነው ። ይህም ቼክ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ መግባቱ ነው ።)

ይድረስ ከአባ እንድርያስ ።

እጅግ የሚጣፍጥ እራንጅ በዘውግ እጅ የላኩልኝ ሁለት አገልግል ደረሰልኝ ። ለእርብና ለሮብ በቃኝ እግዚአብሔር ይስጥልኝ ።

መስከረም ፺ ቀን አዲስ ዓለም ከተማ ተጻፈ በ፲፰፻፺፭ ዓ.ም.
(ሁለት አገልግል የተባለው ሁለት ካርቶን ነው ። ልጅ ዘውገም በጅቡቲ የምኒልክ ጉዳይ ፈጻሚ ነበሩ)

ይድረስ ከሙሴ ቤርድ ።

የባቡሩን መንገድ የምንለካበት የውሃ ልክ እዚህ እኛ ዘንድ

የማይገኝ ሆነ ። እናንተ ዘንድ የመንገድ መለኪያ የውሃ ልክ አለ ማለት ሰምቻለሁና እንዲመጣልኝ ይሁን ።

መስከረም ፳፯ ቀን አዲስ ዓለም ከተማ ተጻፈ በ፲፱፻፳፭ ዓ.ም.

(ከአዲስ አበባ እስከ አዲስ ዓለም ድረስ የመኪና መንገድ በሚ ያሠሩበት ጊዜ ነው)

ይድረስ ከማጆር ቺኮዲኮላ ።

ከሴላ የተወለዱ ውሾች ብዙ ነበሩ ። የቀሩት አልቀው ሁለቱ ቢቀሩ እነዚህ እንኳ ቢተርፉ ብዬ ወዳንተ ልኬአቸዋለሁ ። አንተ ዘንድ እንዲቆዩልኝ ይሁን ።

ጥቅምት ፩ ቀን ገነት ከተማ ተጻፈ ፲፱፻፳፱ ዓ.ም.

(ቺኮዲኮላ በኢትዮጵያ የኢጣሊያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ነበር)

ይድረስ ከአለቃ ወልዴ ያሬድ ።

ያንተ ነገር ሾሜ ሸልሜ አክብሬ ሳኖርህ በየሰዉ ቤት እየሔድህ እየሰከርክ ሰው መስደብ ማዋረድ ሆነ ። እንዳንተ ያለ ሽማግሌ ሌላ ሰው ይመክር ነበረ እንጂ ይሄ ያንተ ሥራ አልነበረም ። እኔ በዚህ እየሰከርህ ክፉ ነገር በመናገርህ ነው እንጂ ሌላ ነገር አግኝቼብህ አይደለም ። አሁንም እንደልብህ መናገርህን ፣ ስካርህን እተዋለሁ ያልክ እንደሆነ እንድትመጣ ይሁን ። ይህን አልተውም ያልክ እንደ ሆነ ግን እዚያው እንዳወቅህ ሁን ።

ጥቅምት ? ገነት ከተማ ተጻፈ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም.

ይድረስ ከራስ ወልዴ ።

ከግሼ ላንተ ለራስህ የሚገባውን የዝተት ግብር ዋጋውን ሸማም ብትል ፣ ብርም ብትል እኔ እሰጥሃለሁና ዝተቱን እዚያው አንተ እንዳይ በላሽ አሳምረህ አስረግጠህ እዚህ አዲስ አበባ ድረስ እንዲመጣልኝ ይሁን ። የተሸካሚውንም ፣ ዝተቱን የረገጠበትንም ኪራይ እኔ እዚሁ እሰጣለሁ ።

ጥቅምት ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. አ.አ. ከተማ ተጻፈ ።

ይድረስ ከአዛዥ ወልደጻዲቅ ።

ወዶ ገበያ በነበሩት በፊታውራሪ አባየሪ ከብቶች ልውጫ የሰደድ ክልኝ ፴፮ ሰንጋ ደረሰልኝ ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ። ነገር ግን ለባለጌ የተለወጠ ይመስል ምነው ከቁጥሩ አትርፈህ ሳትሰድልኝ ቀረህ ። የአዳል ገዢ ሆነህ ምንያለህ ስስታም ነህ ።

ጥቅምት ፴ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም.

ይድረስ ከደጃዝማች መሸሻ

. . . . ባርኔጣና መጋረጃ ሰድጃለሁ ያልከውን ባርኔጣው ደረሰልኝ ። ነገር ግን ጠበበና ለኔ የማይሆነኝ ሆነ እንጂ ሥራው እጅግ ማለፊያ ነበር ። መጋረጃው ግን እስካሁን አልደረሰኝም ።

በሕዳር በ፳ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም. እንጦጦ ተጻፈ ።

ይድረስ ከራስ ሚካኤል ።

አምና የሰጠኸኝ ቦራ ፈረስ ለኔ ይሆናል ብዬ ነበር ። እንኳን ለኔ ለማንም ሰው የማይሆን ነው ። አሁንም እንዲያው ከመቅረት ለባለ ቤቱ እንኳ ትመልስለት እንደሁ ብዬ ይሄው ሰድጄልሃለሁ ።

ታህሣሥ ፳፮ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም.

ይድረስ ከደጃዝማች በሻህ ።

ከዚህ ቀደም የሰጠኸኝ ዳማ ፈረስ ሽንቱን እየከለከለው ቢበላም የማይወፍር ሆነ ። አሁንም በኔ እንዳይቆጠርብኝ ብዬ ይሄው ሰድጄልሃ ለሁ ።

ታህሳስ ፳፮ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም.

ይድረስ ከራስ ወልዴ

ደብዳቤህም ደረሰልኝ ። ራስ ሚካኤል ጌሾ ቸግሮኛልና ስደድልኝ ብሎ ላከብኝ ያልከውን ምን ከፋኝ ፣ እንድትሰድለት ይሁን ።

ታሳስ ፳፮ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም. አ.አ.ከተማ ተጻፈ ።

ይድረስ ከፊታውራሪ ተሰማ ።

መምህር ዜና የደብረ ዘይትን ቤተ ክርስቲያን የሚሠሩልኝ አንድ

ጭቃ ሠሪና አንድ አናጢ ከለከሉኝ ብሏልና ሁለቱንም ሠራተኞች አትንኩ ። ቤተ ክርስቲያኑን ይሠሩላቸው ።

ታህሣሥ ፴ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም.

ይድረስ ከወይዘሮ ዘውዲቱ ደስታ ።

በቅሎ ተቃጠለብሽ ማለት ሰማሁ ። አንቺ ግን ሙቼም አትወጂኝ። በቅሎዬ ተቃጠለብኝ ብለሽ ሳትልኪብኝ ቀረሽ ። የአፈንጉስ ነሲቡ በቅሎዎች ሁሉ ተቃጥለው ፤ ከኔ ነገር ሠርቶ የወሰደው ግራጫ በቅሎም ተቃጥሎ ፤ የሚሔድበት በቅሎ አጥቶ እየታዘለ ቢመጣልኝ እወድ ነበረ ። አሁንም እርጥባን ማለፊያ በቅሎ ሰድጄልሻለሁ ። ለአፈንጉስ ነሲቡ ያዋስሽ እንደሆን እንኳን በቅሎዋን አገርሽንም እነቅልሻለሁ ። ኮርቻ ግን አለመጨመሬ ኮርቻ አልተቃጠለብሽም ብዬ ነው ።

ጥር ፪ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም.

(ወይዘሮ ዘውዲቱ ደስታ የአፈ ንጉስ ነሲቡ ሚስት ነበሩ ።)

ይድረስ ከፊታውራሪ ሀብተ ማርያም ።

ሀብተማርያም የሚባለውን ሹምከን አስረህ የላክልኝ ደረሰልኝ። ነገር ግን እሱ ከፈረንጆች የማይስማማ ነውና እሱን ወደ ሌላ ሥፍራ አድርገህ ሌላ ሰው አድርግ ። እሱስ እንኳን ከፈረንጆች ከኔም የማይስማማ ነው ። . . . .

የካቲት ፮ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም.

ይድረስ ከግራዝማች ድልነሳሁ ።

ለመንገዳችን መስተንግዶ የሚሆን ደነባ የሚደገስ አምስት ዳውላ ጌሾ ለአሳላፊ መሸሻ ይሰጠው ። ከአሥራቱ ጌሾ ።

የካቲት ፳ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም.

ይድረስ ከራስ ወልዴ

ደሴ ጌሾ ይግባ ብዬ ነበረ ። እስካሁን አልገባም አሉ ። አሁንም ፫፻ ዳውላ ጌሾ ይህ ደብዳቤ እንደደረሰህ አስነስተህ ደሴ እንድታስገባ ይሁን ። የጌሾ ነገር ቸግሯልና እንዳይውል እንዳያድር ቶሎ ስደድ ።

የካቲት ፳፰ ቀን አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ በ፲፰፻፺፰ ዓ.ም.

ይድረስ ከፊታውራሪ ይፍሩ ።

ደሴ ጌሾ ይግባ ብዬ ነበረ ። አሁን ግን አልገባም ብለውኛልና የቀወትን ገባር እዘህ ከኛ ጌሾ መቶ ዳውላ ጌሾ አስጭነህ ደሴ ድረስ ቶሎ አስገባ ። የኛም ጌሾ ባይኖር ከባላገሩ አስመጥተህ ለባላገሩ ዋጋ ውን እንሰጣለን ። ጌሾውን በዚህ ቀን ደሴ ገባልን ብላችሁ በስልክ አስ ታውቁኝ ብያለሁና ቶሎ ሳትሰድ የቀረህ እንደሆን አይሆንም ።

የካቲት ፳፰ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም.

(ምኒልክ ወደ ደሴ ለመሔድ አስበው ስለነበረ እዚያ ለሚደረ ገው ድግስ ጌሾ ማስላካቸው ነው)

ይድረስ ከራስ ሚካኤል ።

ባመት ባመቱ ነጭ ማር ትሰድልኝ ነበረ ። ዘንድሮ ግን እኛ ወደ ዚያ እንመጣለን ብለን ነበርና በዚህ ምክንያት ሳይመጣልኝ ቀረ ። አሁንም ለኔ የሚሆን ነጭ ማር በቤቱ ታጥቷልና ብዙ እንኳን አል ልም የተገኘልህን ያህል ነጭ ማር እንድትሰድልኝ ይሁን ። ደግሞም ከየጁም ከሌላም ዘንድ የምክትል የሚሆን ማር ደሴ ለኛ መቀበያ የገባ እንዳለ ያንንም አብረህ አስጭነህ ስደድልኝ ።

ግንቦት ፲፭ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም.አ.አ.ተጻፈ ።

(የነጭ ማር ብርዝ ይወዱ ነበር)

ይ ድረስ ከማውላ ።

ገነት መውረድዎን ሳላውቅ የሥራውን ነገር ሳልመካከር ሔዱ ብኝ ብለህ ላክብኝ ። አንተ ምንጊዜም ጌትነት በዝቶብሃልና ተጋድመህ ትውላለህ ። በየት ታገኘኝ ። እኔማ የዚሁት የሥራውን ነገር እንነግርሃ ለሁ ብዬ ብዙ ቆይቼ ከረፋዱ ነው የመጣሁት ። አሁንም በጧት በጧት እየገባህ ሥራውን ቶሎ ቶሎ አሠራ ። እንጨት ሠራተኛ ያልከውንም ሱልጣን ሌላ ሥራ ይዟል ፣ መሀመድና ኡመር ይሥሩልህ ።

ግንቦት ፳፩ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም. ገነት ከተማ ተጻፈ ።

(ማውላ ተራ አናጢ ነበር)

ይድረስ ከራስ ቢትወደድ መንገሻ ።

አምሳ ጉንዶ ማር ደረሰልኝ ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ። ነገር ግን ይህን ሁሉ ማር መላክህ ምን ሥፍራ ሊበቃው ነው ። ቤትስ ፣ ጋንስ ማስቀመጫ የት ይገኛል ።

ሰኔ ፳፰ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም.

(ሲያሾፉ የጻፉት ነው)

ይድረስ እጅግ ከከበሩ ማክስ ኢጉን

የፍረስትንበርግ መስፍን ፣ የጀርመን ንጉሠ ነገሥት የመጀመሪያ ባለማዕረግ ።

በደየው ኤሽን ግንብ

ሰላም ለርስዎ ይሁን ። ስለፍቅር ብለው በሙሴ ሆልስ እጅ ከፋብሪካዎ የላኩልኝ ቢራ ደረሰልኝ ። ቢራውም እጅግ ያማረና የጣፈጠ ሆኖ አገኘሁት ። እኔ ግን በዚህ የወዳጅነት ሐሳብዎ ብዙ ደስ አለኝ ። ይህችም የቢራ ፋብሪካዎ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቤተ መንግሥት እቅራቢ እንድትባል ፈቅጃለሁ ። . . . .

ሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም. አ.አ.ከተማ ተጻፈ ።

(ፋብሪካዎቻቸውን "በስምዎ አቅራቢ ብለን እንድንሰይም ይፈቀድልን" እያሉ ብዙ ኤሮፓውያኖች ይጠይቁዋቸው ስለነበረ ይህም የቢራ ፋብሪካ በምኒልክ ስም አቅራቢ እንዲባል መፍቀዳቸው ነው ።)

ይድረስ ከራስ ተሰማ ።

ውሻውም በደህና ደረሰልኝ ። እኔስ ትንሽ መስሎኝ ለእነዚህ ውሾች ልክ ይሆናል ብዬ ነበረ ።

ነሐሴ ፲፫ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም.

ይድረስ ከደጃዝማች ሀብተ ማርያም

የሰደድካቸውን ፈረሶች አየኋቸው ። መጋላውን ፈረስ ወስጃለሁ ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ። አንተስ የቤተ ክርስቲያኑን ሥራ ትተህ ፈረስ የምትጋልብ ነህን ። ደግሞስ መጋለቡን የት ታውቅበታለህ ።

ህዳር ፱ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም. ተፃፈ

ይድረስ ከደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ።

የፊታውራሪ ሥዩም ባርያዎች ከሡፌር ኩብት ሊለቅሙ ቢወጡ ተያዙ ያልከውን ልቀቁ ብያለሁ ።

ህዳር ፴ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ይድረስ ከራስ ወልደጊዮርጊስ ።

ጅሩ የደጃች ተድላ ልጆች ይዘውት የነበረውን መሬትና ሰላሌ ደጃች ተሰማ ለጠበል መጠጫ የሰጡኝ መሬት ተያዘብን ብለው ሰዎቹ ላኩብኝ ያልከውን መንኩሰህ ደብረ ሊባኖስ ስትቀመጥ ያን ጊዜ ይሆናል ።

ጥር ፪ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ይድረስ ከደጃዝማች ውቤ ።

. . ድጅኖና ድማሚት ይምጣልኝ ያልከውን አራት ድማሚት ፣ የድማሚት መሰርሰሪያውንም ሰድጄልሃለሁ ፣ ነገር ግን ዲጂኖው ዋጋ ያልወጣለት ነውና እንዳይበላሽ ደህና አድርገህ መያዝ ነው ። የተበ ላሸ እንደሆነ ትከፍላለህ ።

ሚያዝያ ፪ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ይድረስ ከደጃዝማች በሻህ ።

ለግንቦት ሚካኤል አባታችንን እጅ ለመንሳት የቤተ ክርስቲያኑንም ሥራ ለማየት ግንቦት ፩ ቀን ወይም በ፯ ቀን ከአዲስ አበባ ተነስቼ ወደ ደብረ ሊባኖስ የምመጣ ነኝና የባላገሩንም መጥን አዘህ ሁሉንም ነገር ተሰናድተህ እንድትቆይ ይሁን ። ደግሞ ደብረ ሊባኖስ ከቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ የኔ ድንኳን የሚተከልበትን ሥፍራ ጉድፉንም ሁሉንም ነገር አሁኑኑ አስቀድመህ አሳምረህ አስጠርገህ እንድትቆይ ይሁን ። ድንኳን የሚተከልበትንም ሥፍራ የደጃች አባተ ሰው ያሳይሃል ።

ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ይድረስ ከእጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ ።

ለግንቦት ሚካኤል አባታችንን እጅ ለመንሳት ፣ የቤተ ክርስቲያኑንም ሥራ ለማየት በግንቦት በ፭ ወይም በ፯ ከአዲስ አበባ ተነስቼ

ደብረ ሊባኖስ የምመጣ ነኝና ነገሩን እንዲያውቁት ይሁን ። አሁኑኑ አስቀድሜ መላኬ ድግሱን እንዳይጨርሱት ብዬ ነው ።

ሚያዝያ ፳፮ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ይድረስ ከፊታውራሪ ተሰማ ።

ፊታውራሪ መኰንን የደጃች ወዳጇን ፈረሱን መልሰው ኮርቻውን በለውጥ የተቀመጠ ነው ብለው ከለከሉኝ ብሎ ላከብኝ ። ከፈረሱ ጋር እዚያው ከተገኘ ለሱ መስጠት ነው እንጂ ለምን ይከለከላል ።

ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ይድረስ ከእጨጌ ወልደጊዮርጊስ

....የላኩትን ደብዳቤ አየሁት ። ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያኑ ሥራ እንጨት ቸግሮናልና እንጨት ይዘውልን የመጡ እንደሆነ አበላለሁ ያሉትን የቤተ ክርስቲያኑን የጣራ እንጨት እዚሁ እንዲሠራ አዝዣለሁ ።ተሠርቶ ይመጣል ።

ግንቦት ፪ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ይድረስ ከመጋቢ ወልደ ሥላሴ ።

ፍሬ ሰንበት የሚባል አሽከር ትምህርት ለመማር አባ ወልደ አምላክ ዘንድ ቀርቷልና ተምሮ እስኪመጣ ድረስ እንደልብ ድርጎውን እንዲሰጡት ይሁን ።

ግንቦት ፲፯ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ይድረስ ከዘመድ አገኘሁ ።

ለደብረ ሊባኖስ ቤተ ክርስቲያን አቶ ብስራቴን በኪራይ የሚሠሩትን አናጢዎች አሠራ ብዬ አዝዤው ነበረ ። አንተ ግን ዛፉን አላስ ቆርጥም ብለህ ከልክለህ እስካሁን አልተሠራም አሉ ። አንት ወደል፣ እኔ ያዘዝኩትን መከልከልህ ምን አገባህና ነው ። ዳግመኛ እፊቴ አት ደርስ እንደሆነ ነው እንጂ በደህናህ እንዲህ አትጫወትብኝም ። አና ጢዎቹም ወዳንተ እየሔዱ ይሠራሉ ብለውኛልና በኪራይ የሚሠራው አናጢ ሁሉ አቶ ብስራቴ ዘንድ ይሥራ ። የታሠሩትም አናጢዎች በዋስ ይፈቱ ።

ግንቦት ፲፯ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ይድረስ ከራስ ወልዴ ።

የሰደድህልኝ በቅሎ ደረሰችልኝ ። በቅሎዋ ስለመንገዱ ካከማ በውል አላየኋትም እንጂ ማለፊያ ነች ። ነገር ግን ደግሞ ከዚች የሚ በልጥ ሌላ ማለፊያ በቅሎ ያገኘህ እንደሆነ ማለፊያ በቅሎ ሰጥቻለሁ ብለህ ያንን የምታስተው አይደለችም ።

ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ. ም .

ይድረስ ከደጃዝማች አብርሃ ።

ደጃች ተድላ መቀሌ ካለው ቤቱ ከቤት ጠባቂዬ አንድ በሬ ፣ አትክልት የሚመላለስበት አንድ አህያ ፤ እነዚህን ደጃች አብርሃ ወሰደ ብኝ ብሏልና እውነት ሔዶበት እንደሆነ የቤት ጠባቂውንም ጥንድ በሬ ፣ አህያውም እንዲመለስለት ይሁን ። ለእንግዲሁም ቤቱ አይነካ በት ።

ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ. ም.

ይድረስ ከደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ።

ዳኖ እህቱን ለነገሬ ድሮለት ወዲያው ከወንድ ይገኘሻለሁ ባለ በት ነገር አፈንጉሥ ነሲቡ ከዚህ ቀደም እኔ ፊት ተጋጥሞ ዳኖ ረቷል ብሎ ቢነግረኝ ከብቱን መክፈሉ ይቆይና ተያይዘው ይምጡ ። ዋስ አስጠርተህ ለመስከረም አቦ አያይዘህ አፈጣጥመህ ወደኔ ስደድልኝ ።

ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ. ም.

ይድረስ ከደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ።

ተድላ ሕዳሩ የሚባል ሰው የቀረብኩባትን ሚስቴን ፍታ ብለው ያዙኝ ። ከአቡን ዘንድ ደብዳቤ ብወስድ ሳይሆንልኝ ቀረ ብሎ ጮኸ ልኝ ። የቀረበባትን ሚስቱን ስለምን ተፋቱ ትሉታላችሁ ። አሁንም በዚህ የተነሳ ንብቴም ተይዞብኛል ፣ ዋሴም ታግቶብኛል ብሏልና የተያዘ በትም ከብት በዋስ ይመለስለትና ከባላጋራው ጋር በጥቢ አያይዘህ ወደኔ ስደድልኝ ።

ሰኔ ፴ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ .ም.

ይድረስ ከራስ ሚካኤል ።

ወደ ትልቅ መንግሥት የተላከ ሰው እውቀትን የሚያሰንፍ መጠጥ መጠጣት አይገባውምና ስለዚህ አንተም ከቢሺ ውሃና ከሱካር

ውሃ ፣ ከሶዳ ውሃ ፣ ከሎሚናት ፣ ከእነዚህ ከአራቱ በቀር ሌላ መጠጥ አትቅመስ ። አደራህን ።

ሐምሌ ፲ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ. ም.

ይድረስ ከአቶ አብርሃ ።

የመጋዝ መስንጠቂያውን ሥራ ነገር በዕለት በዕለት የሠራኸውን በስልክ እንድታስታውቀኝ ብለንህ ነበር ። እስካሁን በስልክ ብንፈልግህም አጣንህ ። አሁንም ሁሉንም ነገር ይህን ወረቀት ይዞ ለመጣ ሰው ላክብን ። ለእንግዲህም ዕለት ዕለት የሠራሃቸውን ቶሎ ቶሎ በስልክ እንድታስታውቀን ይሁን ።

ነሐሴ ፱ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ. ም.

ይድረስ ከእጨጌ ወልደጊዮርጊስ ።

ደብዳቤዎ ደረሰልኝ ። . . . ይሄው አንድ ማለፊያ ከብ መሳል ሰድጃለሁ ። በቀደምም አንድ ለኮቴ ሰድጃለሁ ። ሌላውን ልዝብ መሳል ግን እኛም የምናስመጣው ከዚያው ከዜጋመል ነውና እርስዎም ከዚያው ከዜጋመል ከየባላገሩም ቤት ቢሆን ማስፈለግ ነው ። የኔ ድግን መጋዝ እጨርቆስ ዘንድ አለና ይምጣልኝ ያለውን ጨርቆስን ብንጠይቀው የሰጠኝ ሁለት ከብ መጋዝ ነው እንጂ ድግን መጋዝ አልሰጠኝም አለ ። አሁንም ድግኑ መጋዝ ያለበትን እዚህ ሥፍራ ነው ካሉ ያስታውቁን ። ጠመንጃ መፍቻውንና ማሸጊያውን ግን ይሄው ሰዶናል ።

ነሐሴ ፲ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ. ም.

(መሳል ፣ ለኮቴ ፣ ሁለቱም ፣ የቢለዋ መሳያ ድንጋዮች ናቸው ።)

ይድረስ ከአባ ጅፋር ።

የእንጀራውን ሳጥን ዓይነት የሰደድክልኝን አየሁት ። ይህ ከብ ሆነና እንጀራ ለማስቀመጥ አይመችም ። አሁንም አራት መዓዘን አድርጐ ለመሥራት ያመች እንደሆነ አራት መዓዘን ሆኖ ቢሠራ መልካም ነበረ ። አራት መዓዘን አድርጐ ለመሥራት የማያመች የሆነ እንደሆነ ግን እንደዚሁ እንደሰደድክልኝ ዓይነት ሆኖ ቁመቱ ከፍ እንዲል ሶስት ዙር ይጨመርበት ። በተረፈ ለአሽከርህም በቃል ነግሬዋለሁ ።

ነሐሴ ፳፯ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ. ም.

ይድረስ ከራስ ወልዴ ።

የምልክ አምባን አቦ ቤተ ክርስቲያን የሰማይ ቁጣ አቃጠለብኝ ብለህ የላክብኝን ደብዳቤ አየሁት ። አንተ የሠራኸው ቤተ ክርስቲያን ጐጆ ተቃጠለብኝ ማለትህ እንደሆነ ነው እንጂ አንተ የሠራኸው ምን ቤተ ክርስቲያን ይባላል ።

መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻ ዓ. ም.

ይድረስ ከደጃች ይልማ ።

ይሄ አለምነህ ዜና የሚባል ሰው ራስ መኰንን የሰጡኝን በቅሎ ብታመም ሸጨ ብበላው አሁን ክፈል ብለው ተያዝዬ ታሰረብኝ ብሏልና ተያዦን ፍታለትና እኔ እከፍላለሁ ።

መስከረም ፲ ቀን ፲፱፻ ዓ. ም.

ይድረስ ከመምህር ክፍሌ ።

ይህ በቀለ የሚባል አሽከር ሌባ እየሆነ ቢያስቸግረን አሰርነው ። ቢታሰርም ሌብነቱን የማይተው ሆነ ። አሸነፈን ። እንደጋኔንም አለበት ። በእግር ብረት አጠንክረው አስረው ጠበል እያጠመቁ ሲድን እዚያው ለገዳሙ አገልጋይ ይሁን ።

መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻ ዓ. ም.

ይድረስ ከወህኒ አዛዥ ወልደ ጻዲቅ ።

ደብዳቤህም ደረሰልኝ ። ለኖራው ማንጠር ወይዘሮ ሰማዕቷ አገር ኖራ ማንጠር የሚያውቁ ሁለት ገባሮች አሉ ያልከውን ምን ከፋ ወዳንተ ሔደው ያንጥሩ ። ለወይዘሮ ሰማዕቷም ነግረናታል ።

ጥቅምት ፬ ቀን ፲፱፻ ዓ. ም.

ይድረስ ከፊታውራሪ ማዘንጊያ ።

ፊታውራሪነት ተሾምኩ ብለህ የላክኸውን አየሁት ። እንኳን ደስ አለህ ። እግዚአብሔር እንኳን ከዘመን ዘመን አብሮ አሸጋገረን ። ደግሞ እንደዚሁ ዘመነ ማቴዎስ አብሮ በደህና ለመድረስ ያብቃን። የጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ነገር ክረምት ሆኖ ብዙ አልተሠራም ። አንተ ግን እዚህ በመሆኔ ነው እንጂ ያንድ ባቡር ያህል እሸከም

ነበር ብለህ ላክህብኝ ። አንተማ ከድተኸኝ ሄደህ ምን ባለሟል ነህና እንዲህ ብለህ ትልክብኛለህ ። ወይም ደጃች ሥዩም ልኩህ ት መጣና አስሬ ድንጋይ አስፈልጥሃለሁ ።

ጥቅምት ፲፱ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም. አ.አ. ከተማ ተጻፈ

ይድረስ ከወይዘሮ ሰማዕቷ ።

እንቺ ውስጥ ኖራ ማንጠር የሚያውቁ ሁለት ገባሮች አሉ ብለ ውኛልና ወህኒ አዛዥ ወልደጻዲቅ ዘንድ ቶሎ ሔደው ኖራ እንዲያ ነጥሩ ይሁን ።

ጥቅምት ፮ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ከደጃዝማች ውቤ ።

ደብዳቤህም ደረሰልኝ ።.... እህልና በርበሬ ይዳርጉኝ ብለህ ላክ ብኝ ። አንተ እዚህ ሥፍራ አለ ብለህ ብታስታውቀኝ ነበር እንጂ እኔ እህልና በርበሬ ያለበትን በምን አውቀዋለሁ ። አሁንም እዚህ ሥፍራ አለ ብለህ እንድትልክብኝ ይሁን ።

ኅዳር ፮ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ከአቶ ሁሴን ።

የሰደድከውንም ደብዳቤ አየሁት ። እዱር የሚሠራውን እንጨት ጨርሼ ደብረሊባኖስ መላግ ጀምሬአለሁና መላጊያ ይምጣልኝ ብለህ የላክብኝን ዘንድሮ አካርሚኝ ውቅር ነው እንጂ ዓይነተኛው ውቅር ቀርቷልና አንተም የመላጊያውን ሥራ ትተህ እንጨቱ እንዳይዘባባ ከደህና ሥፍራ አስቀልለህ ቶሎ መምጣት ነው ። ይህን ቃል በቀደምም ልኬብሃለሁ ። ባይደርስህ ነው እንጂ ። ነገር ግን የሳንቃ ነገር ችግርአ ልና አንተ እስክትመጣ ድረስ ሁነኛ ሹሞችህን ጨረቻ ድረስ ሰደህ ሳንቃ በብዙ እንድታሰነጥቅ ይሁን ።

———ቀን የሌለው ።

ይድረስ ከደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ።

የሆጂሌ አምስቱ ሚስቶች ካንተ ዘንድ ናቸው ብሎኛልና እንድ ትሰጠው ይሁን ።

ታህሣሥ ፳፩ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ከደጃዝማች አብርሃ ።

ይሄው አንድ ፈረስ ከነመጫሪያው ፣ ልብስም ላንተ ሙሉ ልብስ ፣ የላስቲክ ጫማም ሰድጄልሃለሁ ።

ታህሣሥ ፳፱ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ለወህኒ አዛዥ ወልደ ጻዲቅ

የዋግሹምን ልጅ ገሠሠን ይሄው ከቢትወደድ አጥናፌ ጋር ወዳንተ ሰድጄዋለሁ ። ነገር ግን ሥርዓት ሳይማር አድጐ ባለጌ ሆንዋልና አንተ እየተቆጣጠርህም እየመከርህም ቢሆን እንድታሰለጥነው ይሁን። ወዳንተ መስደዴ ሥርዓት እንዲማር ነው እንጂ መታሰር የለበትም። ቀለቡንም በወር በወሩ ሁለት ሁለት ዳውላ እህል ፣ ሁለት ሁለት ጉንዶ ማር ፣ ለወር ጨው ሁለት ሁለት ብር እንዲቀበል ይሁን ። በተረፈ ለእርድ የሚሆነውን በግ ፣ ሌላ ሌላውንም ነገር አንተ እንደ እውቀትህ መስጠት ነው ።

ጥር ፬ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ከራስ ተሰማ ።

.... የላክልኝ የብረት ሜትር ደረሰልኝ ። እጅግ ማለፊያ ነው ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ።

ጥር ፱ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ከደጃዝማች አባተ ።

ፊታውራሪ ጉርፉ መሬቴንም ገንዘቤንም ተወረስሁ ብሎ ጮኸልኝ ። እኔ እሱን አስሬ ቀጣሁ እንጂ ይወረስ አላልሁ ። ለምን ይያዝበታል ። አሁንም መሬቱ እንዲለቀቅለት ። ገንዘቡም ፣ ከብቱም እንዲመለስለት ይሁን ።

ጥር ፲፭ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ከራስ ቢትወደድ መንገሻ ።

ፊታውራሪ አበጀ ሚስቴን እኔ ሳልፈታት ደጃች ኪዳነ ማርያም ወስዶ ለሌላ ዳረብኝ ብሎ ጮሆልኛልና አያይዘህ ስደድልኝ ።

ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ከደጃዝማች አባተ ።

ፊታውራሪ ጉርፉ መሬቴንም ገንዘቤንም ተወረበሁ ብሎ ጮኸ ልኝ ። እኔ እሱን እስሬ ቀጣሁ እንጂ ይወረስ አላልሁ ። ለምን ይያዝ በታል ። አሁንም መሬቱ እንዲለቀቅለት ። ገንዘቡም ፣ ከብቱም እንዲ መለስለት ይሁን ።

ጥር ፲፭ ቀን ፲፱፻ ዓ. ም.

ይድረስ ከራስ ቢትወደድ መንገሻ ።

ፊታውራሪ አበጀ ሚስቴን እኔ ሳልፈታት ደጃች ኪዳነ ማርያም ወስዶ ለሌላ ዳረብኝ ብሎ ጮሆልኛልና አያይዘህ ስደድልኝ ።

ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻ ዓ. ም.

ይድረስ ከራስ ወሌ ።

ሰላሳ ጉንዶ ብለህ የላክልኝ ነጭ ማር እዚህ እኛ ዘንድ ቢሰፈር ዘጠና ጉንዶ ሆነ ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ። ድርብና ኩታ ብለህ የላክ ብኸኝን ዛሬ ማለፊያው ድርብ ሁሉ አልቆ ላንተ የሚሆን ማለፊያ ድርብ አይገኝም ። ደግምስ አንተ መልበስ የምትወደው ጃኖ ነው ።

ጥር ፳፬ ቀን ፲፱፻ ዓ. ም.

ይድረስ ለልጄ ለወይዘሮ ዘውዲቱ ።

. . . . ሳንቃ የሚገጥም እናጢ ያልሺውን ፈረንጅም ቢሆን ፣ አረብም ቢሆን ምንጊዜም በዋጋ ነው የሚሠሩ ። አሁንም ዋጋ ሰጥቼ ይሠራልኝ ያልሽ እንደሆነ ላኪብኝ ።ዋጋውን ተነጋግረን እንሰደዋለን ።

ጥር ፳፭ ቀን ፲፱፻ ዓ. ም.

ይድረስ ለእጨጌ ወልደጊዮርጊስ ።

ደብዳቤዎ ደረሰልኝ ። የቤተ ክርስቲያኑን ነገር በቁርበት እንማግር አሉ ያሉትን በገመድ ብቻ የሆነ እንደሆነ ማገሩ ይላላል ። አልፎ አልፎ ጠፍር እየገባ ብዙውን በቀላድ መማገር ይሻላል ብዬ ከዚህ ጥቂት ቆዳ ሰድጃለሁና እንደዚሁ እያደረጋችሁ እንዲማገር ይሁን ።

ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻ ዓ. ም.

ይድረስ ከእጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ ።

የቤተ ክርስቲያኑ ድልድል በምሥራቅ በኩል ነቃብን ፡ ለዚህ ሥራ ሰው ይታዘዝልን ያሉትን ሰዉ በዚሁ በቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ሲለፋ ባጀ ። ደግሞ አሁን አዝመራውን ትቶ ሥራ ስናዘው ጊዜ ደሃው ያዝንብናል ። ይልቅ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዕለት ለጠበል ደብረ ሊባ ኖስ የተሰበሰበውን ሰው ስለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ብላችሁ ለምና ችሁ ድንጋዩን ቢጥልላችሁ ይሻላል ።

ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ከአለቃ እስጢፋኖስ ።

ላሊበላ እንዳይራብህ እስከልክል ብዬ ነግሬህ ነበረ ። አሁን የላሊበ ላው ጨኸት አገር ሊፈታ ሆነ ።አሁንም አንተ ሥራ ይበዛብሃልና የላሊበላውን ሹመት ለጌታሁን ሰጥቼዋለሁ ። ልቀቅለት ። ደግሞ እሱ ያስጮኽ እንደሆነ እንደዚሁ ይሻራል ።

ግንቦት ፳፬ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ለቀኛዝማች ይብሳ ።

መኳንንቶች እልፍኝ አምሽተው ሲሔዱ የሚበራ አስር ፋና በገመዳ እጅ ስጥ ።

ሰኔ ፲፬ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

ይድረስ ከደጃች ሙሉጌታ ።

አለቃ ሲፈታ ለሚጽፈው ዳዊት 18 ብራና ስጥ ።

ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፩

## አማላጅነት

ምኒልክ ለማንኛውም መኳንንት ሆነ ለመኳንንት አሽከር አማ ላጅ ነበሩ ። ከጌታው የተጣላ አሽከር ከጌታው ለመታረቅ ሲፈልግ ከምኒልክ ዘንድ መጥቶ እንዲያማልዱት ይነግራል ። ምኒልክም የቀረ በውን በቃል ፡የራቀውን ደብዳቤ በመጻፍ ያስታርቁ ነበር ። ለማስረጃ ያህል ከብዙዎቹ የአማላጅነት ደብዳቤዎቻቸው ጥቂቱን እንመልከት ። ደብዳቤዎቹ የተቀመጡት በቀኑ ቅደም ተከተል ነው ።

ይድረስ ከአባ ጅፋር ።

የዘንጀሮ ባላባት ገብረ መድህን ወደኔ መምጣቱ ክርስትና ለመነሳት ነው እንጂ ለሌላ ነገር አይደለም ። አሁን ግን ያለፈቃዳቸው ሳል ሰናበት ወደዚህ በመምጣቴ ይቀየሙኛል ያስታርቁኝ ቢለኝ ይሄው ሰድጃለሁና አንተም ከልብ ምረኸው እንደ ቀድሞአችሁ በፍቅር ተስማምታችሁ መቀመጥ ነው ።

ሰኔ ፴ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

ይድረስ ከአለቃ እስጢፋኖስ ።

ወልደ ሥላሴ የሚባል የኡራኤል ደብተራ በሰው ነገር ተቀይሞብኛልና ያስምሩኝ ብሎ ደብዳቤ ላከብኝ ። አንተን ግን በደለኝም አላለም ። አሁንም የበደለህ ነገር እንዳለ ትተህ ከልብ ማርልኝ ። ከካህናቶቹም ጠብ እንዳለው አንተ ከአንገዦት እንድታስታርቅልኝ ይሁን ።

ኅዳር ፯ ቀን ፲፱፻፪ ዓ.ም.

ይድረስ ከራስ ኃይሉ ።

ፊታውራሪ ተሰማ ፡ ተሰማ ጐሹ ራስ ኃይሉ ተጣልተውኛል አስምሩኝ ብሎ ደብዳቤ ላከብኝ ። አንተን ግን ያለ ጥፋት ትበድለዋለህ ብዬ አልጠረጥርህም ። ነገር ግን ጥፋተኛን ቢምሩት እግዚአብሔርም ይወደዋልና አንተም ስለኔ ብለህ ከልብህ እንድትምረው ይሁን ።

ትሳስ ፳፫ ቀን ፲፱፻፫

(ባይታረቁ ምን ያደርጋሉ ?)

ይድረስ ከራስ ኃይሉ ።

ፊታውራሪ ተሰማ ራስ ኃይሉ ተጣልተውኛል ብሎ ከዚህ ቀደም ቢልክብኝ ታርቀኸው እንደ ጥንታችሁ በፍቅር ተስማምታችሁ ተቀመጡ ብዬ ልኬብህ ነበር ። አሁን ግን እርቁም አልሰላልኝም ፡ ወደዚህም ለደጅ ጥናት እንዳልመጣ ተከለከልኩ ብሎ ላከብኝ ። አሁንም ሲሆን ፊት እንደላኩብህ ከልብ ምረኸው እንደቀድሞአችሁ በፍቅር ተስማምታችሁ መቀመጥ ነው ። እርቁ የማይሰላ እንደሆነ ግን ወደዚህ ቢመጣ እንዳይከለከል ። ቤቱም ገንዘቡም እንዳይነካ ።

ሚያዝያ ፯ ቀን ፲፱፻፫ ዓ.ም.

(ምኒልክ ለሁሉም ነገር አስታራቂ ወይም አማላጅ አልነበሩም ። ቀጥሎ ያለውን እናብብ)

ይድረስ ከደጃዝማች ብርዬ ።

ደብዳቤህም ደረሰልኝ ። ጐፋ ከደጃዝማች ለማ አገር የተጋደሉትን ሰዎች ነገር የላክብኝን አየሁት ። የነፍስ ገዳይ ነገር ያንኑ ባለደሙን ማማለድ ነው እንጂ እኔማ ማማለድ መቼ ይገባኛል ።ባለደሙ እታረቃለሁ ያለ እንደሆነ ግን ደስ ይለኛል እንጂ ምን ከፋ ።

ህዳር ፳፪ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም.

(ራሳቸውስ አማላጅ ይቀበላሉ ወይ ? ይቀበላሉ ። ይታረቃሉ ። በማይሆን ነገር ግን አይሆንም ይሉ ነበር )

ይድረስ ከሙሴ አርሎፍ

አንድ ሴት አማላጅ ልካኛለች ያልከውን በአገራችን ገባርም ግንደበልም ቢሆን ይገብራል እንጂ እንደዚህ ያለ ልምድ የለም ። የሷን የገባር መሬት የፈታይ ያደረግንላት እንደሆነ ደግሞ ሌላው ሁሉ ይለምድብኛልና ይሄ አይመችም ።

ጥቅምት ፭ ቀን ገነት ከተማ ተጻፈ በ፲፰፻፺፭ ዓ.ም.



ምኒልክ በጉን በኩል ሲታዩ

# ጠባይና ሰውነት

"....ምኒልክ የኃይለኛነት ጠባይ አላቸው ። አሳባቸውም በመልካም ሁኔታ እያስተዳደሩ የአገራቸውን ዕድገት ለማፋጠን ነው ። ... ምኒልክ የተከበሩ በጣም ትልቅ ሰው ናቸው ።...."

ግሊከን

"....የማያውቁትን ነገር ሁሉ ማየት ፤ ማጥናትና መሥራት ይወዳሉ ።...."

ሮድ

"....አንድ ቀን በኢትዮጵያ ውስጥ ስላሉት ኤሮፓውያን ጉዳይ አንስተን ከእቴጌ ጣይቱ ጋር ስንጫወት ንጉሱ ገር ሰው በመሆናቸው ሰው የሚላቸውን ሁሉ ያምናሉ ብለው አጫወቱኝ ።..."

ክሉቢኮብስኪ

"... ታዋቂነታቸው በፖለቲካ ብቻ አይደለም ። የሳይንስ ውጤት በሆኑ ጥበባዊ ሥራዎችም እውቅ ናቸው ።...."

ግሊከን

"....ኢትዮጵያውያንና እኔ እድገትና መሻሻል እንፈልጋለን ። እቴጌይቱ ፣ መኳንንቱና ቀሳውስቱ ግን እኛን ይቃወሙናል ። እኔና የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እናሸንፋቸዋለን በማለት ምኒልክ አጫወቱኝ ።...."

ሊ. ሩ

"....እቴጌ ጣይቱ የውጭ አገር ሰዎችን ስለማያምኑ የንጉሡን እርምጃ ይቃወማሉ ።...."

ሊሸን

"....ምኒልክ ሲያጫውቱኝ.... 'ወጣቶቻችን መማር ይኖርባቸዋል ። ገና ብዙ የሚሠራ ሥራ አለን ። በጣም ወደኋላ የቀረን ሕዝቦች ነን'....አሉኝ ።...."

እስኪነር

"....ምኒልክ ለሐኪሞቻቸው አስቸጋሪ በሽተኛ ናቸው ። ሲያማ ቸው ሐኪሞቹን ይፈልጋሉ ። ሥራ እንዳይሠሩና እንዲያርፉ ሲነግሩ ዋቸው እሺ ይላሉ ። ሲሻላቸው የሐኪሞቹን ምክር ትተው ከባድ ሥራ ስለሚሠሩ ሕመሙ ይነሳባቸዋል ።...."

ብሪስ

ግሊከን እንዳለው ምኒልክ የኃይለኛነት ጠባይ አለባቸው ። ኃይለኛነታቸውም የተለየ ጠባይ ነበረው ። አንድ ሰው አንድ ጥፋት ባጠፋ ጊዜ ምኒልክ ይናደዳሉ ። እንደተናደዱም ወዲያውኑ እርምጃ አይወስዱም ። ጥቂት ቆየት ብለው ካንድ ክፍል ውስጥ ይገቡና ያን ሰውየ ያስጠራሉ ። ሰውዬው ተጠርቶ እስኪመጣ ምኒልክ ደህና ቆመጥ ዱላቸውን ይዘው ይጠብቃሉ ።ጥፋተኛው ወይም ያናደዳቸው ሰው ካሉበት ክፍል ሲገባ በያዙት ዱላ ደህና አድርገው ደብድበው ይለ ቁታል ። ምኒልክ ሰውየውን በሚመቱበት ጊዜ የሚመቱት አስጐንብ ሰው ጀርባውን ነው ። ይህም ከአጉል ቦታ ተመትቶ እንዳይደማ ወይም እንዳይበላሽ ነው ። ደብድበው ሲበቃቸው ሁለቱም ከነበሩ በት ቦታ ያለ ቂም ወዳጅ መስለው ይመለሳሉ ። ተደብዳቢው ያልተነካ መስሎ በፈገግታ ቢመለስም ሁሉም የቀመሰውና የሚቀምሰውም ስለሆነ ጉዳዩን ያውቀዋል ። ደጃች ከበደ ተሰማ እንዳጫወቱኝ ተደብዳ ቢውን ጓደኞቹ ስንት ፍትፍት ጕረስክ ወይም ስንት ብርሌ ጠጅ ጠጣህ እያሉ ይቀልዱበታል ። ይህም ድብደባ ለተራ ሰዎች ብቻ ሳይ ሆን እስከ ራስ ማዕረግ ድረስ ያሉት ሁሉ የቀመሱት ነው ። በዚህ ነው ሕዝቡ አባታችን ይላቸው የነበረው ። ለዚህ ነው ከዳር እስከዳር ለጥ ሰጥ ብሎ የተገዛላቸው ።


ምኒልክ ሩህሩህ ነበሩ ። የእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተሠ ርቶ ሊያልቅ ጥቂት ሲቀረው ምኒልክ ችሎት ላይ ተቀምጠው ሰው የገደለ ሰው ቀርቦ የሞት ፍርድ ተፈረደበት ። የሟቹ ወገኖች ስለዘ መዳቸው ደም ገንዘብ (ወጆ) ይቀበሉ እንደሆነ ቢጠየቁ "የወንድማ ችን ገዳይ ይገደልልን እንጂ ወጆ አንቀበልም" አሉ ። ያ ሰው የገደለ ወንጀለኛ እንዲገደል ለሟቹ ወገኖች ሲሰጥ ድምጡን ከፍ አድርጐ "ጃንሆይ ፣ በሥራዬ ነውና መገደሉንስ ልገደል ። ግን የዚችን ቤተ ክርስቲያን መጨረሻ እስካይ ዕድሜ ይሰጠኝና ልገደል" ብሎ ለመነ ። ይህን የሰሙት ምኒልክ ከመቀመጫቸው ተነስተው ተፋራጆች ከሚ ቆሙበት ቦታ ቆመው ከፊት ለፊታቸው ላሉት መኳንንቶች "ከሟች ወገኖች አማልዱኝ ። ወጆውን እኔ ራሴ ከግምጃ ቤቴ እከፍላለሁና ይሄን ሰው እንድታስምሩልኝ ተማጥኛችኋለሁ" ብለው አጐነበሱ ። በዚህ ጊዜ ወንጀለኛውን ለመግደል የተረከቡት የሟች ወገኖች በም

ኒልክ እግር ላይ ተደፍተው እየተላቀሱ "ምረናል፣ ምረናል፣ ወጀ ውንም አንቀበልምና ለእርሶ ስንል ምረናል" አሉዋቸው ። ከዚህ በኋላ ምኒልክ "ነፍሱን ማሩልኝ አልኩ እንጂ ወጀውንማ መማር ፍርድ ማጓደል ነው" ብለው ገንዘቡን ከፈሉ ።


ከሌሊቱ 11 ሰዓት ሲሆን ግቢ አካባቢ ካሉት ከሶስቱ ቤተ ክርስ ቲያናት ወዳንዱ ሄደው እስከ ጧቱ አንድ ሰዓት ድረስ በፀሎት ይቆ ያሉ ። ከቤተክርስቲያን መልስ ከእቴጌይቱና ካንዳንድ መኳንንት ጋር ቁርስ ይበላሉ ። ከ3 እስከ 4 ሰዓት ባለው ጊዜ አዳራሽ ተገኝተው ዲፕሎማቶችንና አገር ገዥዎችን ያነጋግራሉ ።

በችሎት ጊዜ አሳላፊና ወታደር፣ በቅሎ ያገርና አሽከር ግብር ይበላሉ ። የእኝኛ ግብር እንዳለቀ ምኒልክ ከችሎት ይነሳሉ ። መኳንን ቱንም ይዘው ወደ ግብር አዳራሽ ይገባሉ ። ምሳ ይበላሉ ። ምኒልክ ምንጊዜም የማይረሱት አመላቸው፤ አጃቢ ሠራዊት ሳይበላ እሳቸው አይበሉም ነበር ። አንድ ጊዜ ከደጃች ውቤ ቤት ተጋብዘው ሄዱ ። ደጃች ውቤም አማታቸውን ምኒልክን እጅ ነስተው ከተቀበሉ በኋላ ወደ ቤት እንዲገቡ ቢጠይቋቸው "በፊት አሽከሮቼን አስገባና አብላልኝ" ብለው እምቢ አሉ ። አጃቢ አሽከሮች ለግብር ሲገቡ የምኒልክና የየመኳ ኳንንቱን በቅሎዎች የያዙ አሽከሮች ቀሩ ። ይህን ያዩት ምኒልክ በቅ ሎአቸውን "መደቡትን ወዲህ አምጣት" ሲሉ አሽከሮች እየሮጡ በቅሎአቸውን አቀረቡላቸው ። አብረዋቸው ያሉት መኳንንቶችም ወዴት ሊሄዱ ነው እያሉ ሲጠብቁ ምኒልክ የበቅሎዋን መሳቢያ ለኮ ከአሽከሮቻቸው ተቀብለው "ሂድ ግባና ምሳህን ብላ" አሉት ። ሁሉም ደነገጡ ። ምኒልክም አሽከሮቻቸውን ተቆጥተው ወደ ግብር እንዲ ገቡ ሲያደርጉ እጎናቸው የነበሩት ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ከም ኒልክ እጅ በቅሎዋን ለመቀበል "ይስጡኝ እኔ ልያዛት" አሏቸው ። ምኒልክም "የኔን ተውልኝና ያንተን ካንተ አሽከር ተቀበል" አሏ ቸው ። ከዚህ በኋላ መኳንንቱ ሁሉ ከአሽከሩ በቅሎውን እየተቀበለ ሲይዝ አሽከር ምሳውን ሊበላ ወደ ግብር ገባ ። ምኒልክ ካንዲት የኮክ ዛፍ ሥር በቅሎአቸውን ይዘው ቆመው አሽከሮቻቸው በልተው እስቲወጡ ድረስ ጠጅ እየተጠጣ ይጠብቁ ጀመር ።


አንዳንድ ታሪክ ፀሐፊዎች ምኒልክን መጠጥ ይወዱ እንደነበር ሲጽፉ ብዙ ጸሐፊዎችና ያገራችን ሰዎችም ምኒልክ መጠጥ እንደማ ይወዱ ይናገራሉ ። እርግጥ በቤተ መንግሥቱ በተለይ ለውጭ አገር ሰዎች የተለዩ የመጠጥ ዓይነቶች ይቀርባሉ ። ከዚያ በፊት በኢትዮጵያው ያን ተሰምቶ የማይታወቀው ውስኪ በበረዶ የሚቀርበው በምኒልክ ቤተ መንግሥት ነበር ። ብዙ ታሪካቸውን የጻፉ ሰዎች እንደጻፉት ምኒልክ ከመጠጥ የሚወዱት ብርዝና ወተት ነበር ።



ምኒልክ ፡ ጣይቱና መኳንንት በመጠጥ ግብዣ ላይ



የምኒልክ በቅሎ



የምኒልክ ፈረስ

ሁልጊዜ ከምሳ በኋላ ሥራ ካለ እልፍኝ ይገኛሉ ። ሥራ ሲጨርሱም በቤተ መንግሥቱ ግቢ ውስጥ መንሸራሸርና በየሠራተኛው ዘንድ እየተገኙ ሥራውን ማየት ይወዳሉ ። ከዚህ ሌላ በበቅሎ ሆነው በከተማው ውስጥ ይዞራሉ ። በከተማ ውስጥ በሚዞሩበት ጊዜ ማንኛውም ሰው ሥራውን ያሳያል ። የተሸለመለመ አንኮላ ወይም ቅል ፣ የመጥረቢያ መያዣ ዛቢያ ፣ ከበግ ጠጉር የሚሠራ ባና ወይም ቆብ ፣ ከሰሌን የሚሠራ ባርኔጣና ይህንን የመሳሰሉትን ነገሮች ሁሉ ሕዝቡ ለምኒልክ ለማሳየት ይዞ ይቀርባል ። ምኒልክ በበቅሎ ሆነው ሲጓዙ ያ አንድ ነገር ለማሳየት የፈለገ ሰው ከእጁ ውጭ ሆኖ ያን የሚያሳየውን ነገር በረጅም እንጨት ከፍ አድርጐ ይዞ ይቆማል ፣ ወይም ከእጀቡ ጋር ይጓዛል ። ይህን ሲያደርግ ወዲያው ይጠራና ከምኒልክ ዘንድ ይቀርባል ። ምኒልክም ሥራውን አይተው ፣ የሚሻሻል ካለም መክረው ፣ ከሌለም አመስግነው ለወደፊቱ የበለጠ እንዲሠራ ነግረው ገንዘብ ሰጥተው ያሰናብቱታል ። በዚህ ምክንያት ሕዝቡ ሁሉ ባለው አቅም ለፈጠራ ሥራ ይተጋ ነበር ። በሠረገላ ሆነው በሚጓዙበትም ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ ተግባር አይቀርም ነበር ።

ከከተማው ጉብኝት በኋላ ከ11 እስከ 12 ሰዓት ባለው ጊዜ ወደ ቤተመንግሥት ይመለሳሉ ። እስኪጨልም ድረስም ከእንቁላል ቤት በረንዳ ላይ ተቀምጠው ብርዝ ይጠጣሉ ። የእራት ሰዓት ሲደርስ ራት ይበላሉ ። በየሳምንቱ ሐሙስ ማታ ግን ሁኔታው ይለወጣል ። በየሐሙሱ ማታ የተለየ ምሽት ነው ። የአገር ውስጥ መኳንንቶች ፣ ዲፕሎማቶች ፣ የውጭ አገር ሰዎችና የሚጠሩ እንግዶች በሚገኙበት ከእራት በኋላ የሻምፓኝ ግብዣ ይደረጋል ። ግብዣውም እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ይቆያል ።

ምኒልክ ከምግብ የበሬ ሥጋ አይወዱም ነበር ። ስለዚህ የሚሠራላቸው የዶሮ ወይም የበግ ወጥ ነበር ። ከሁሉም የበለጠ ግን የዱባ ወጥ ይወዳሉ ። የዶሮ ዳቦ ፣ አልጫ ወጥ ፣ አይብ ይወዳሉ ። ወተት መጠጣት ስለሚወዱ ለብቻቸው ለእሳቸው የሚሆን ወተት ፣ ቅቤና አይብ የምታዘጋጅ ሠራተኛ አለቻቸው ። በግብር ጊዜ አንዳንዴ ጠጅ ይጠጣሉ ። አንድ መለኪያ አረቂ ወይም አንድ ብርጭቆ ሻምፓኝ ከጠጡ በቂያቸው ነው ። ከኤሮፓውያን መጠጥ በጣም የሚወዱት ክሬም ደ ሜንት የሚባለውን ነበር ።

ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ከምግብ ይልቅ ሻምፓኝ ፣ ኮኛክና አረቂ (ነጭ አረቂ) መጠጣት ይወዱ ስለነበረ ምኒልክ "ሀብቴ እንደ መኰንን መጠጡን ባታበዛ ምናለ" ይሏቸው ነበር ። በመጠጡ በኩል ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ብቻ ሳይሆኑ ራስ አባተም ጠጅና ኮኛክ

መጠጣት ይወዱ ነበር ። በግብር ጊዜ ምኒልክ የመጠጥ አዛዡን ይጠሩና "ከእንግዲህ ወዲህ ለሀብተጊዮርጊስ ቀስ እያላችሁ ቅዱ ። አባተ ግን ጥሬ ሥጋ ሲበላ አይቼዋለሁና አትንፈጉት ፣ ምንም አይለው" ይሉ ነበር ።ራስ አባተ ጥሬ ሥጋ መብላት ይወዱ ነበር ይባላል ።

ምኒልክ እስፖርት አፍቃሪና አበረታችም ነበሩ ። ማርቲኒ በታሪክ መጽሐፉ እንዲህ ይላል ". . . .ንጉሠ ነገሥቱ በፈረስ መሽቀዳደሚያ ቦታ እየተገኙ ይመለከታሉ ። በድምፅም ፣ በጭብጨባም ያበረታታሉ ። አንድ ጊዜ ግን የሚስ ማክሚላንን ዋንጫ ለማግኘት በተደረገው የፈረስ እሽቅድድም ውድድር የሀሪንግተን ፈረስ በማሸነፉ ተበሳጩ ።. . . ."

አንዳንድ ሰዎች ምኒልክ ከሴት ጋር ፍቅር የማያውቁ አስመስለው ያወሩባቸዋል ።ግን እውነት አይደለም ። ውብና ዘንፋላ የሆኑት ፣ በዕድሜ እንደ እናታቸው የሚቆጠሩት ፣ የስምንት ልጆች እናት የነበሩት ወይዘሮ ባፈና የምኒልክን ልብ በፍቅር የነደፉ ሴት ነበሩ ። የመርሐቤቴ ባላባት የነበሩት ወይዘሮ ባፈና ከምኒልክ ጋር የተገናኙት ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው ሸዋ እንደገቡ ማለት በ1858 ዓ.ም. ነው ።ምኒልክ በመምጣታቸውም ወይዘሮ ባፈና ምኒልክን አግብተው ከምኒልክ ጋር ለመንገስ ፈለጉ ። ምኒልክ ግን እናታቸው ከሚሆኑ ሴት ጋር ለመንገሥ ስላልፈለጉ ነገሩን ችላ ብለው በወዳጅነት ብቻ ቆዩ ።

ኢጣሊያዊው አባ ማሳያ አሁን ደግሞ ከምኒልክ ጐን ነበሩና በ1861 ዓ ም አንድ ቀን ወይዘሮ ባፈና አባ ማሳያን ጠርተዋቸው ". . . ምኒልክ በእርስዎ ላይ ትልቅ እምነት እንዳላቸው አውቃለሁ ። ይወዱዎታል ። ያከብርዎታል ። ታዲያ ለምን በሕግ እንዲያገቡኝ አይመክሩዋቸውም ። ቢያገቡኝ ደግሞ ልጅ እወልድላቸው ነበር. . .'" ማለታቸውን ጽፈዋል ። ማሳያ ግን ምኒልክ ወጣት ሴት አግብተው ልጅ ለመውለድ እንደሚያስቡ ያውቃሉና እሺ እያሉ ሳይናገሩ ኖሩ ። ምኒልክ ከባፈና ጋር በወዳጅነት 17 ዓመት ሲቆዩ ባፈና የምኒልክን መንግሥት ለመገልበጥ እስከ መነሳት ደረሱ ። ምኒልክ ግን ይወዷቸው ስለነበር ሁሉንም በይቅርታ ያልፏቸዋል ። ምኒልክ ጣይቱን ካገቡም በኋላ ባፈና ዘንድ መመላለሳቸውን አልተዉም ነበር ። በኋላ ግን ብዙ ተራኪዎች እንደጻፉት ምኒልክ ከመኳንንቶቻቸው አንዱን ጠርተው ባፈናን በሚስትነት አግባት ብለው አዘዙት ። እሱም "ንጉሥ የደረሰባትን ሴት ፣ የእርስዎን የጌታዬን ቅምጥ እንዴት አድርጌ አገባለሁ ?" ቢላቸው "እንደሱ አይደለም ፣ አንተ ከኔ ብትሰርቀኝ ኖሮ ወደሃት ነው የነጠቅኸኝ ይባላል ። አሁን ግን አግባት ብዬ የማ



"...በፈረስ መሽቀዳደሚያ ቦታ እየተገኙ ይመለከታሉ...."

ዝህ የማትፈልጋትን ሴት ነው'' አሉት ። ሰውዬውም መሬት ስሞ ሄደ። ባፈናም በ1879 ዓ. ም. በጥር ወር ሞተው ደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ ። ወይዘሮ ባፈና በ1874 ዓ ም ግድም አንድ ወንድ ልጅ ከምኒልክ ወልደው ነበር ። ልጁ ግን ሲወለድም ጥምልምል ቢጤ ስለነበረ ሳያ ድግ ሞተ ።

ከጉራጌ ሴት የሚወለድ ልጅ ኢትዮጵያን ለብዙ ዘመን ይገዛል የሚል ትንቢት ነበርና በዚህ ሳቢያ መኳንንቱ ሁሉ በጉራጌ ሴት ላይ ሽሚያ በያዘበት ጊዜ ምኒልክም ወይዘሮ ወለተ ሥላሴን ይዘው ነበር። ወይዘሮ ወለተ ሥላሴ የጉራጌ ባላባት የቶሮ ልጅ ናቸው ። ወይዘሮ ወለተ ሥላሴ ለዳግማዊ ምኒልክ ሁለት ልጆች ወልደውላቸዋል ። ያኔ ወይዘሮ ባፈና በሕይወት ነበሩና ምኒልክ በወይዘሮ ወለተ ሥላሴ ፍቅር መያዛቸውን እንዳወቁ ራሴ ዞርዋል አበድኩ ብለው ለጥ ቂት ጊዜ ታመው ቆዩ ።

ከእንኒህ ሁሉ በፊት ምኒልክ መቅደላ ላይ በግዞት በነበሩበት ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ልጃቸውን ወይዘሮ አልጣሽን ድረውላቸው ነበር ከምኒልክ ጋር አብሮ የነበረው እሥረኛው ዎልድ ሜየር "....ጥሩ ወጣት ነበረ ። ፈጣን ፣ ጨዋና ትሑት ነበረ ። ....በዚህ ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱ ልጃቸውን ልዕልት አልጣሽን ዳሩለት...." በማለት ጽፎ ላቸዋል ። ከመቅደላ አምልጠው በወጡ ጊዜ ሚስታቸውን ወይዘሮ አልጣሽን ከዚያው ከመቅደላ ትተዋቸው ነበር የወጡት ።እንደ ኢስ ተርን አጻጻፍ የምኒልክን ማምለጥ "....አልጣሽ ሲሰሙ አለቀሱ ። ....ማምለጣቸውን አልቃወምም ። ነገር ግን እኔን ሚስታቸውን ለምን ትተውኝ ሄዱ ?.... አሉ ።"

ምኒልክ ከመቅደላ ሲያመልጡ አልጣሽን ትተው ይውጡ እንጂ አልረሷቸውም ነበር ።ሳሊምቢኒ በያዘው ማስታወሻ ኦክተበር 1 ቀን 1890 በሚለው ቦታ "....ኢልግ ሲያጫውተኝ እንጦጦ ትግራይ የነበርን ጊዜ ወይዘሮ አልጣሽ ከንጉሥ ምኒልክ ድንኳን ሲገቡ አየሁ ። እንደሰማሁት ባንድ ሞሰብ በሉ ። ሌሊቱንም ከዚያው አደሩ ። ...." ይላል ። ስለ መጨረሻው ጊዜ ሳሊምቢኒ "....የቴዎድሮስ ልጅ የመሸሻ ሹሞች ሁለት ሆነው መጡ ። መሸሻ እንጦጦ የምኒልክ እማች ነበረ ። ሰዎቹ የመጡት የምኒልክ የመጀመሪያ ሚስታቸው ወይዘሮ አልጣሽ መሞታቸውን ለምኒልክ ለመንገር ነበር ።....ያቺ ምስኪን ከምኒልክ ያረገዘችው ሞተች ። የሞተችውም በእቴጌይቱ ትእዛዝ መርዝ ተደርጐ ባት ነው ።...." ይላል ። አልጣሽ ቴዎድሮስ የሞቱት በ1883 ዓ.ም. በጥቅምት ወር ነው ።

ለ ሩ "....ምኒልክ ጠጅ የምትቀዳላቸው አንዲት ወፈር ያለች የደስ ደስ ያላት ሴት ነበረች ። ስሟም ደስላ ነው ።...." ይላል ። የካ

ቶሊኩ ሚሲዮናዊ አባ ጃሮሳቭ እ.ኤ.አ. ሐምሌ 1 ቀን 1910 በጻ ፉት ደብዳቤ ልጅቱ የወሎ ኦሮሞ ናት ይላሉ ።ደስላ የሚለው ስም በኦሮምኛ ውስጥ መኖሩን ለማግኘት አልቻልኩም ። ብዙውን ጊዜ ፈረንጅ ፀሐፊዎች በአገራችን ስም አጠራር ላይ ስህተት ያደርጋሉ ። እንደዚያው ሁሉ ሩ ፣ ደስታን ደስላ ብሎ እንደሆን ወይም ደግሞ ስሟ በእርግጥ ደስላ መሆኑን ለማረጋገጥ ሞክሬ ነበር ። አልሆነልኝም ።

ለ ሩ ከጻፈው እንመልከት "....አንድ ቀን ማታ አንዲት ገረድ በጀሮዋ ነይ ቀስ ብለሽ በጭለማው ውስጥ እንሂድ ።የይሁዳ አንበሳ ለተከበረ አልጋው አብቅቶሻል ....."አለቻት ይላል ። ደስታ መቃ የመ ሰለ አንገት የነበራት ፡ውብ የደስ ደስ ያላትና ብልህ ሴት ስለነበረች ምኒልክ በወዳጅነት ለብዙ ወራት ወደዋት ቆዩ ። እያደር ግን ሆድዋ እየገፋ ይታይ ጀመር ። ነገሩንም ገልጣ ለንጉሡ ለመንገር ፈራች ። በቤተ መንግሥቱ ያሉ ከምኒልክ ለመውለድ የሚመኙ ሴቶች ሁሉ ቀኑባት ። ....እርግዝለች ፣ በማርገዙዋ ይሆናል ንጉሣችን ከእሷ የተ ጣበቁት...." እያሉም ያሟት ጀመር ። እንዳትጠጋቸውም ያባርሯ ታል ። ምኒልክ ወደ ሰሜን ዘምተው በነበረ ጊዜ በሌሉበት ከቤተ መን ግሥቱ እንድትወጣና ዳግመኛም እንዳትመለስ ተነግሯት ተባረረች።

ደስታ እያለቀሰች በእግርዋ ምኒልክ ወደሄዱበት ወደ ሰሜን አቅጣጫ ብቻዋን ጉዞ ጀመረች ። ወርዋ ገብቶ ነበርና የመውለጃ ቀንዋ ሲደርስ በጉዞዋ ላይ ልጅዋን ወለደች ። የተወለደችው ልጅም የምኒልክን መልክ ይዛ በመወለዷ ደስ አላት ። ስሟንም ሸዋረጋ ብላ ሰየመቻት ። ምኒልክንም ለማግኘት ተቸግራ ብዙ ዓመት ልጅዋን ይዛ ስትንከራተት ቆየች ። በየደረሰችበት ቦታ ሁሉ እንጀራ ጋጋሪነት እየተቀ ጠረች ልጅዋን እንዳይገድሉባት ሁሉን ነገር በምስጢር ይዛ ኖረች ። ልጅዋ ሸዋረጋ የሰባት ዓመት ልጅ ስትሆን እናቲቱ ደስታ በሕመም በ1889 ዓ ም በነሐሴ ወር ሞተች ። ከመሞትዋ በፊት ግን ልጅዋን ጠርታ በሚስጥር "....የምቀበረው ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ነው ። ምክንያቱም ለገንዘብ ብዩ እስላም ቤት ተቀጥሬ ስለነበር ነው ። አሁን ክርስቲያን ነኝ ብልም የሚያምነኝ የለም ።እኔ ግን ክርስቲያን ነኝ ። ልጄ ፣ እንቺም ደሃ ነሽና እስክታድጊ ድረስ ማንም የሚሰጥሽን ምግብ ብይ ። ከአደግሽ በኋላ ግን ይሄን በአንገትሽ ላይ በቆዳ ሰፍቼ ያሰ ርኩልሽን ወረቀት ለምታምኚያቸው ሰዎች አሳዪ ። እሱም አባትሽ ማን መሆኑን የሚነግር ወረቀት ነው ።...." ብላት ሞተች ።

ሸዋረጋ አሥር ዓመት ሙሉ በጠባይዋና በመልኩዋ በሁሉ ዘንድ ተወዳጅ ሆና አደገች ። ውብ ጥርሶችዋንና ውብ ዓይኖቿን ይዛ ለአን ዲት እሮጊት ግርድና ተቀጠረች ። እሮጊቷ በበቆሎ ሲሄዱ ተከታይ

በመሆን ፡ ሲወርዱም በመደገፍ ታገለግል ጀመር ። ወታደሮች ወደ ጦርነት በሚሄዱበት ጊዜ ግን የተቀጠረችበትን ቤት እየተወች ከወ ታደሮች ጋር አብራ መዝመትን ትወድ ነበር ። በጉዞም ላይ ሠራዊቱ በሙሉ በአመልዋና በሳቂታነቷ ይወዳታል ። ለአቅመ ሄዋን ስትደርስም አንድ ወታደር አግብቷት ይዟት ወደ ሐረርጌ ሄደ ።

አንድ ቀን ከባልዋ ጋር ሲጫዋወቱ ባልዬው "አንገትሽ ላይ ያለው ድግምት የምንድነው?" ብሎ ጠየቃት ። እሷም የእናትዋን ሚስጥርና አደራ ለመጠበቅ አልናገርም ብላ እምቢ አለች ። ባልዬው መስተፋቅር የያዘች መስሎት ጉዳዩን ለንስሐ አባታቸው ነግሮ እንዲ ጠይቁለት አደረገ ። የንስሐ አባትዮውም ያንን ክታብ ፈትተው ቢያ ዩት ጉዳዩ ሌላ ስለሆነባቸው ደነገጡ ። ባልየውንም "ኑሮህን ለማሳ ደግ ከፈለግህ ይህቺን ልጅ ወደ ንጉሡ ውሰዳት ። የእሳቸው ነች" አሉት ።

ሸዋረጋ ከባልዋ ጋር አዲስ አበባ መጣች ። ጉዳዩም ከእቴጌ ጣይቱ ዘንድ ደረሰ ። ጣይቱም እንዳዩዋት ልጅቱ ምኒልክን በመም ሰልዋና ጥርስና ከናፍርዋ ደግሞ እናቷን በመምሰሉ የዚያች የተባረ ረች ገረድ ልጅ መሆኗን ወዲያው አወቁ ። እንድትታጠብና ጥሩ ጥሩ ልብስም እንድትለብስ አደረጓት ። አንድ ቀን ጣይቱና ምኒልክ ሲጨ ዋወቱ ጣይቱ "ያስታውሳሉ ወይ? ዱሮ ወደስሜን በዘመቱ ጊዜ ያችን የወደዷትን ገረድ ትተው ሄደው ሲመለሱ እንዳጧት ያስታውሳሉ?" ብለው ምኒልክን ጠየቋቸው ።

ምኒልክም "አስታውሳለሁ እንጂ" አሉና "ለምን ሄደች?" ብለው ጣይቱን ጠየቁ ። ጣይቱም ታሪኩን ዘርዝረው ነገሩዋቸውና " . . . .ሴት ልጅ በወለደች በሰባት ዓመትዋ ሞተች" አሏቸው ። ምኒልክ አዘኑ ። ጣይቱንም ልጅቷን እንዲፈልጉ ነገሩዋቸው ። ይሄኔ ጣይቱ ተነስተው ወጡ ። ጥቂት ቆይተውም በብዙ ወጣት ሴቶች ታጅበው ተመልሰው ገቡ ። ይህን ያዩት ምኒልክ ተቆጥተው "ጣይቱ ፡ የነገርኩሽን ነገር ለምን እሺ አትይኝም ። ፈልጊ ያልኩሽን ፈልጊ" አሏቸው ። ጣይቱም "ፈልጌማ አገኘሁሎት እኮ" ብለው መለሱ ።

ምኒልክ ጣይቱን ተከትለው የገቡትን ወጣት ሴቶች ያዩ ጀመር ። ሴቶቹ ሁሉ ተመሳሳይ ልብስ ለብሰዋል ። ሁሉም በተርታ ቆመዋል ። ምኒልክም ተነስተው እየተጠጉ ሲመለከቱ ያቺን ሸዋረጋን ከሠልፉ መሐል ስበው አውጥተው ትኩር ብለው አዩዋትና "ፈገግታዋ ሁሉ ልክ እንደ እናትዋ ነው" ብለው አዘኑ ። ልጅ በማግኘታቸውም ተደ ሰቱ ። "እዚህ ተቀመጭ ፡ ለአንድ መኳንንት እድርሻለሁ" አሏት ።

በ1876 ዓ.ም. ሸዋረጋ ለወዳጅ ዓሊ ተዳሩ ። ወዳጅ ዓሊም አል ፈልግም ብለው ሸዋረጋን ሲፈቱ እቴጌ ጣይቱ ተናደዱ ። ምኒልክ ግን አልተናደዱም ። በኋላም ወይዘሮ ሸዋረጋ ለወሎው ራስ ሚካኤል ተድ ረው በ1888 ዓ.ም. ጥር 25 ቀን በወረሂመኑ ተንታ ውስጥ ልጅ ኢያ ሱን ወለዱ ።

ምኒልክ ወይዘሮ ጣይቱን ሲያገቡ ዕድሜያቸው 30 ዓመት ነበር ። ለጣይቱ 5ኛ ባላቸው ናቸው ። እቴጌ ጣይቱ መሐን በመሆናቸው ከም ኒልክ ልጅ አልወለዱም ። አንድ ቀን ምኒልክ የልጅ ነገር አንስተው ከጣይቱ ጋር ሲጫወቱ "እግዚአብሔር ለምን ልጅ አልሰጠንም፣ ጣይቱ" ብለው ቢሏቸው ፣ ጣይቱ ሲመልሱ "ለምን በዚህ ያዝናሉ ፣ ሁልጊዜ የምናስብላቸው 14 ሚሊዮን ልጆች አሉን አይደለምን" አሏቸው ። የዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት 14 ሚሊዮን ነበር ።

ምኒልክ ከወይዘሮ አብቺው ወይዘሮ ዘውዲቱን ወልደዋል ። የወ ይዘሮ አብቺውን አባት ስም ላገኝ አልቻልኩም ።

ኸርበርት ስላየው ስለ ምኒልክ ሁኔታ ሲገልጥ "... ምኒልክን ልገናኝ ስገባ በወንበራቸው ላይ እግሮቻቸውን አነባብረው ደገፍ ብለው ተቀምጠው ነበር ። በእጃቸውም ሐር መሐረብ ይዘዋል ። በኋላ ግን ከኋላቸው ለቆመው አሽከራቸው ሰጡት ። ንፁሕና ብሩህ ሰማያዊ የሆነ እግር ሹራብ አድርገዋል ። ያደረጉት ጫማ አዲስ ሆኖ የቴኒስ መጫ ወቻ ጫማ ነው ። ጫማው ከአፍንጫው ቀና ያለና ማሠሪያ የሌለው ነው ። በሐርና በወርቅ ዝምዝም የተሠራ ልብስ ለብሰዋል ። ሰፊ እጅጌ ያለው ፣ ወገቡ ላይ በቁልፍ የተያያዘ ሸሚዝ ለብሰዋል ። በወ ርቅ የተዘመዘመ ጥቁር የሐር ካባ ደርበዋል ። ራሳቸው ላይ ነጭ ጨርቅ አስረዋል ። በግራ ጆሮአቸው ላይ የአልማዝ ፈርጥ ያለበት ሎቲ አንጠልጥለዋል ። የሎቲው መደብ ወርቅ ነው ። ይህም ሎቲ የዝሆን ገዳይ ምልክት ነው ።

"በግራ እጃቸው ትንሽ ጣት ላይ ወፍራም ቀለበት አለ ። የቀለ በቱ መደብ ጥቁር ሰማያዊ የሆነ የከበረ ድንጋይ ሆኖ ከላዩ ላይ ሁለት የአልማዝ ፈርጦች አሉበት ። እንዳሰብኩት ፊታቸው በሙሉ በፈንጣጣ የተበላሸ አይደለም ። ከአብዛኛው አበሻ እሳቸው ጠቆር ይላሉ ። ግን እንደ ሌሎቹም ጥቁር አይደሉም ። አፋቸው ጥቁር ይሆንና ከንፈራቸው ትልልቅ ነው ።

"ጥርሶቻቸው ግጥም ያሉ ነጫጮች ናቸው ። ትንንሾቹ አይኖቻ ቸው ደስ ይላሉ ። የዓይኖቻቸው ውስጥም ከነጭነት ይልቅ ወደ ቢጫ ነት ያደላል ። ግንባራቸው ጠባብ ነው ። ትኩር ብለው ሲያዩዋቸው

ደግና የተለያዩ ጠባዮች ያሏቸው መሆናቸውን ፊታቸው ያስታውቃል። ጢምና ሪዛቸው የተጠጋጋ ቢሆንም ግራጫ ሆንዋል ። አነጋገራቸው እንደ ሌላው አበሻ ሁሉ ረጋ ያለ ነው ። ሲናገሩም ምላስና ጥርሳቸው ይታያሉ ። ሲያዳምጡ ደግሞ ራሳቸውን መነቅነቅ ይወዳሉ ። ሲጫወቱ እጃቸውን አያወራጩም ። አንዳንዴ ብቻ ጣቶቻቸውን ያደራርባሉ ። ሁሉንም መናገር አልችልም ። በጠቅላላው ደስ የሚሉና ጨዋ ናቸው ።

“. . . .አንድ ጊዜ ከካፒቴን ሀሪንግተን ጋር ለመነጋገር እኛን አስወጡን ። በዚያን ጊዜ ያልታሰበ ነገር ታየባቸው ። ፊታቸው ልውጥ ውጥ አለ ። ፈገግታቸው ሁሉ ሞተ ። ዓይናቸው ተከፈተና የጎሪጥ ያዩ ጀመር ። ፍፁም የተለዩ ሆኑ ። ድንገት ሰምተው የተቆጡበት ምክ ንያት ፤ በኋላ እንደሰማሁት በእንግሊዝ ሶማሌና በኢትዮጵያ ወሰን ላይ የተተከለውን የኢትዮጵያን ባንዲራ አንድ አገር ጎብኚ እንግሊዛዊ ስላነሳው ነው አሉ ።

“. . . .ሁልጊዜ ፈገግተኛ ናቸው ። የመወደድ ጠባይ አላቸው ። ይህም ቢሆን ሲስቁ የሰሟቸው ወይም ያዩዋቸው ሰዎች በጣም ጥቂት ናቸው ።. . . . ብዙ አልተማሩም ። እንዲያውም በኛ አስተሳሰብ ፈጽ መው የተማሩ አይደሉም ። ሌሎቹ አበሾችም ቢሆኑ ከማንበብና ከመ ጻፍ የበለጠ አይማሩም ።

“. . . .ምኒልክን የሚጠሉዋቸው አሉ ። በኔ አጠራር የወጣት ፓርቲ ያልኳቸው ምኒልክን ያማሉ ። እነዚህ ወጣቶች ምኒልክን የሚጠ ሉዋቸው እሥር ቤት ገብተው የወጡ ናቸው ። . . . .ስለ ምኒልክ ብዙ ወሬዎች ሰምቻለሁ ። አንድ ጊዜ ምኒልክ አንዱን ፈረንሣዊ ወፍጮ እንዲያስመጣላቸው ጠየቁት ። ሰውየውም ዋጋው 20,000 ብር ነውና ይከፈለኝ እንደሆን ነው አላቸው ። እሺ ብለውት ወፍጮው መጣ ። ወፍጮው ከመምጣቱ በፊት የወፍጮው ዋጋ 3000 ብር መሆኑን ምኒልክ ሰምተው ነበርና ያ ፈረንሣዊ አጭበርብሮ 20,000 ብር እንደጠየቃቸው ገብቷቸዋል ። ምኒልክ አጭበርባሪ አይወዱም ነበርና ያ ፈረንሣዊ ወፍጮውን በመጥፎ ቦታ እንዲተክል አዘዙት ። ቦታው ለሥራ በጣም አስቸጋሪ ነበር ። ፈረንሣዊውም በዚያ ቦታ ለመትከል ገንዘቡ ይከፈለኝ አላቸው ። ምኒልክም ወፍጮው 3000 ብር እንደሆነ አውቄአለሁ ። 20,000 ብር ነው ብለህ ልታታልለኝ ፈልገሃልና ዋጋ ከፈለግህ ትከል ። ባትተክል ሁሉም እንዳይቀርብህ አሉት ። ፈረንሣ ዩም ወፍጮውን ለመትከል 10,000 ብር ያህል ያስፈልጋልና እንዴት አድርጌ እተክላለሁ? ቢላቸው ፤ ጥሩ ሰው አይደለህምና እንደምትተክል ትከል አሉት ።

“ከዚህ በኋላ ያ ፈረንሣዊ ራስ መኮንን ዘንድ ሄዶ ገንዘብ ለምኖ 5,000 ብር አበደሩት ። ምኒልክ ይህን ሲሰሙ ቤቱን ክበብልኝ

ብለው በወታደር አዲስ አበባ ውስጥ ያለው ቤቱ ተከበበ ። ፈረንሣዊው ለፈረንሣይ ሚኒስትር ለሙሴ ላጋርድ የአንድ ፈረንሣዊ ውርደት የፈረንሣይ ውርደት ነው ብሎ አመለከተ ። ሚኒስትሩም የነ ጋዴ ጉዳይ አላስቸገረኝም ፤ እኔን ወጥሮ የያዘኝ የፖለቲካው ጉዳይ ነው አለው ። ከዚህ በኋላ እንደገና 5,000 ብር ከጓደኞቹ ተበድሮ ወፍጮ ውን ተከለ ። ምኒልክም የወፍጮውን ሥራ ማለቅ ካዩ በኋላ ፤ ለወደ ፊቱ እንዳትዋሽ መማሪያ ትሆንሃለችና ይቺን 2,000 ብር ውሰድ ብለው ለዚያ ሁሉ ከሣራው 2,000 ብር ብቻ ሰጡት ።

"አንድ ጊዜ ደግሞ አንድ የሩሲያ ሰው መጥቶ ምኒልክ የኤሮጳን ጥበብ ይወዳሉ ሲሉ ስለሰማ ፤ ሰዎች ሰበሰበና የኤሮጳን መዝሙር አስተማራቸው ። ሽልማትና ምስጋና ለመቀበልም አፍተር ዘ ቦል የሚለ ውን መዝሙር ምኒልክ ፊት አዘመረላቸው ። ምኒልክም እኔ የምፈል ገው ሌላ ጥበብ ነው እንጂ ዘፋኝማ ከአገሬ ሞልቷል ብለው ቤሳ ሳይሰጡት ካገር አባረሩት ።

"....ትንባሆ አይወዱም ። ትንባሆ የሚያጨስ ምላስና ከንፈሩ ይቆረጥ የሚል የአጤ ዮሐንስ አዋጅ ነበር ። ምኒልክ ግን የሰውን መብት ላለመንካት አዋጁን ሻሩት ። እንዲያውም ልቅመሰው ብለው እያጨሱ ከሞከሩት በኋላ ስላመማቸው ተዉት ። እሳቸው አያጭሱ እንጂ የሚያጨሱ ሰዎችን አይቃወሙም ። አንድ ጊዜ አንድ እንግሊዛዊ ሲያነጋግሩት ፤ አይዞህ ትንባሆህን አጭስ ብለው እንደፈቀዱለት አውቃለሁ ።

"ብዙ ባይበሉም ጠጅና ጥሬ ሥጋ ይወዳሉ ።. . . .የቀን እንቅ ልፍ አለባቸው ። ይህም ፤ ቀን የሚተኙት ሌሊት አምሽቶ ለመሥራት ያመቻቸዋል ። ወሬን ሁሉ ከሊቃውንት እና ላንድ ነገር አዋቂ ከሆኑ ሰዎች ጋር ነው ማውራት የሚወዱት ። ብዙ ሰላዮች አሏቸው ። እሳቸ ውም ቢሆኑ ልዩ የማስታወስ ችሎታ ያላቸው ናቸው ።. . . ." ብሏል ኸርበርት ።

ስለ ምኒልክ ሥራ ወዳድነትና ታታሪነትም ብዙ ሰዎች ጽፈው ላቸዋል ። ሊ.ሩ እንደጻፈው ". . . .የመጀመሪያው የእንፋሎት መኪና አዲስ አበባ እንደገባ ምኒልክ 15 ቀናት ሙሉ ከእንፋሎቱ መኪና ጋር ሲሠሩ ከርመዋል ። ከዚህም ጊዜ በኋላ ምኒልክ በኩራት መኪናውን ለመኳንንቶቻቸው አስተዋወቁ ።. . . ." ሲል ጽፎአል ።

የመጀመሪያው የብር (ገንዘብ) መሥሪያው መኪና አዲስ አበባ እንደገባ ዶክተር መረብ ሲጽፍ ". . . .ምኒልክ መኪናውን ሲያዩና ሲመረምሩ ብዙ ሰዓት ያሳልፋሉ ። እንዴትም እንደሚሠራ ያያሉ ።

. . . .ዓለም ምኒልክን ያህል ታላቅ እንጅነር ማጣቷንም እመሰክራ ለሁ ። . . .'' ብሏል ። ታላቅ እንጅነር ማጣቷንም እመሰክራለሁ ማለቱ ንጉሥ ስለሆኑ ቁልቁል ወርደው እንጅነር ሊሆኑ አይችሉም ማለቱ ነው ።

ኢጣሊያዊው ደ. ካስትሮ ደግሞ ''. . . .በዓለም ላይ ያሉ ትልቅ ተራማጅ (ፕሮግሬሲቭ) ሰው ናቸው ። . . .ከሰማይ ፕላን ወርዶ ፣ ከመ ሬት ጨረቃ ድረስ የሚያደርስ የመገናኛ ፕላን ነው ቢሏቸው ፣ ንጉሡ የሚቻል ከሆነ እንሥራው የሚሉ ናቸው ። . . . .'' ብሏል ።

መረብ እንደጻፉት ደግሞ ''. . . . የፈረንሣዩ ፕሬዚዳንት ግሬቪ አንድ አሮጌ መድፍና አንዲት የሙዚቃ ሣጥን ስጦታ ላኩላቸው ። ምኒልክም መከፋታቸውን ሳያሳውቁ ደስ ያላቸው መስለው የተላከ ውን ሚኒስትር 'ፕሬዚዳንቱን አመስግንልኝ ። አያቶች ለልጆቻቸው አሻንጉሊት እንደሚልኩ ሁሉ ፣ የእናንተም ፕሬዚዳንት አላላክ እንደሱ መሰለኝ ። ና ወጣ ብለን እንይ' ብለው ሚኒስትሩን ከደጅ አወጡትና በጣም ዘመናዊ የሆኑ መድፎቻቸውንና ጠመንጃዎቻቸውን ለሚኒስ ትሩ እያሳዩ 'ይኸውልህ ፣ የኔ መጫወቻ አሻንጉሊቶች እነኚህ ናቸው' አሉት ። . . . .'' ብለዋል ።

ኬለር ደግሞ ''. . . .በ1877 (እ.ኤ.አ.) በኤደን የሚኖረውን ወዳ ጃቸውን ነጋዴ ፣ ጠቢባን እንዲያመጣላቸው ወደ ስዊስ ላ'.ት ። በ1878 ዓ.ም. ሶስት የስዊስ ቴክኒሽያኖች አዲስ አበባ ገቡ ። አንዱ ብረት ሠራተኛ የሆነው አፔንዚለር ነው ። አንዱ ደግሞ በእንጨት አናጢነት ሥራ እስፔሺያሊስት የሆነው ዚመርማን ሲሆን ፣ ሶስተ ኛው ከዙሪክ ፖሊቴክኒክ ትምህርት ቤት የተመረቀው ኢልግ ነው ።

''. . . .ኢልግም እንዲህ ሲል አጫወተኝ ። . . . .ከንጉሡ ጋር ለመ ተዋወቅ ንጉሡ ዘንድ ገባን ። ንጉሡም መሐንዲሶች መሆናችንን ሰም ተው ነበርና በደስታ ከተቀበሉን በኋላ ፣ አዛዦቸውን ጠርተው ለነዚህ ሰዎች አንድ የሚያድሩበት ክፍል ስጥልኝ ። ከዚያም ቆዳና ወስፌ ሁሉ ስጣቸው ። እናንተም እንግዲህ ለጧት ሁለት ጫማ ሰፍታችሁ እንድታመጡልኝ አሉን ። እኛም ከዚያ ከተሰጠን ክፍል ሆነን የማና ውቀውን የጫማ መስፋት ሥራ እናጠና ጀመር ። ያንዳችንን ጫማ ስፌ ቱን ቀዳድደን በዚያ ልክ ቆዳ ስንቆርጥ አደርን ።

''ጧት ምኒልክ አስጠሩን ። የታለ የሰፋችሁት ጫማ አሉን ። እኛም የኛ ሙያ ታላላቅ መንገዶችንና የባቡር ሐዲዶችን መሥራት ነው እንጂ ፣ ይሄን ትንንሽ ነገር አናውቅበትም አልናቸው ። ምኒልክም 'ራስህ የምትሄድበትን ጫማ መሥራት ያልቻልክ ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሄድበትን መንገድ መሥራት እንዴት ትችላለህ?' አሉንና ጠመንጃ መሥራትስ ትችላላችሁ ? አሉን ።

"እኔም እንዴ ፣ ምን ማለትዎ ነው? ጠመንጃ እኮ የሚሠራው በፋብሪካ ነው ። ፋብሪካው ደግሞ በብዙ ገንዘብ ተገዝቶ የሚመጣ ነው አልኳቸው ። ምኒልክም ይሄን ማወቅህም ደህና ነው ።. . . .አሉኝ ብሎ አጫውቶኛል ። ከዚህ በኋላ ኢልግን ሲያስቀሩ ሌሎቹን መልስ ያልሰጡዋቸውንና ያልተከራከሩዋቸውን አትጠቅሙኝም ብለው ወደ አገራቸው መለሷቸው ።. . . ." ብሏል ።

ከንት ግሊከን ስለ ምኒልክ ሰውነት ሲጽፍ ፡ ". . . .በርዝማኔ ከጫማቸው ሌላ 6 ጫማ ይሆናሉ ። ጠንካራ አካል አላቸው ። ቆዳቸው ጥቁር ነው ። አጠር ያለ ጢምና ሪዝ አላቸው ። ፊታቸው ከባድ ነው ። . . . .አስተያየታቸው የጨዋ አስተያየት ነው ። ፈገግታቸው ማራኪ ነው። ፈገግ ሲሉም ውብ ጥርሶቻቸው ይታያሉ ። አዘውትረውም ግንባራቸው ላይ ከምትታሠረው ነጭ ሐር ሻሽ ሌላ ሰፊ ጥቁር ባርኔጣ ያደርጋሉ። ነጭ የሀገር ልብስ ይለብሱና በላዩ ላይ በወርቅ ክር የተዘመዘመ ጥቁር ካባ ይደርባሉ ።. . . ." ካለ በኋላ ፣ ". . . .ሁልጊዜ በ፫ ሰዓት (በኛ ፱) ሌሊት ከመኝታቸው ተነስተው ወደ ፀሎት ቤት ይሄዳሉ ። በ6 (በኛ ፲፪) ሰዓት ወይም ቀደም ብለው ከየፀሐፊዎቹ የሚቀርብላቸውን ሪፖርት ይሰማሉ ። በሚቀጥሉት ሦስት ሰዓታት የደብዳቤዎች መልስ በመስጠትና የፍርድ ይግባኝ ማመልከቻዎች ሲመለከቱ ይቆያሉ ። ቀኑን ሙሉ በሥራ ተጠምደው ይውላሉ ። ምንም ትንሽ ጉዳይ ቢሆን አገረ ገዥዎችን ስለ አስተዳደር በመምከርና በመቆጣጠር ይውላሉ ። መንግሥታቸው እንዳይጠላባቸውና ተወዳጅ እንዲሆንላቸው ይጥራሉ ። በማንኛውም ሰዓት የሕዝብ አቤቱታ መስማት ይወዳሉ ።" ብሏል ።


እ.ኤ.አ. ኅዳር 13 ቀን 1876 ዓ.ም. ልቼ ከተማ ሆኖ አንቴኖሪ የጻፈው ደብዳቤ እስፒዲሲዮኒ ኢታሊያና በሚባል መጽሐፍ ውስጥ፣ ታትሟል ። በዚያ ደብዳቤ ላይ አንቴኖሪ ስለ ምኒልክ ሁኔታ ሲገልጽ ". . . .ዕድሜያቸው 32 ዓመት ይሆናል ። የጢማቸውም ሆነ የራሳቸው ጠጉር ጥቁር ነው ። ፊታቸው የደስ ደስ ያለውና ልዩ ጠባይ የሚታይበት ነው ። አልጋ ላይ ተቀምጠው ነበር ። ራሳቸውና እግራቸው በምንም ያልተሸፈነ ባዶውን ነበር ። ነጭ ሱሪ ታጥቀው ፣ በላዩ ላይ ቀይ ጥለት ያለው ሸማ ለብሰዋል ።. . . . ከትከሻቸው ላይ ልብሳቸው በመርፌ ቁልፍ ተይዟል ።. . . . በጣም ጥሩ ሰው ናቸው ። ለጦር መሣሪያ ያላቸው ፍቅር የተለየ ነው ።. . . . ጨዋ ናቸው ።. . . ." ብሏል ።

በዚያው መጽሐፍ ቺያሪኒ የጻፈውም ታትሟል ። ቺያሪኒ ". . . .ጨዋና የጦር መሣሪያ የሚወዱ ሰው ናቸው ። ንጉሡ ሲናገሩ ረጋ ብለውና አስበው ነው ። ሲያዳምጡም በፀጥታ ነው ። ጥሩ ወታደር በመሆናቸው የጦር መሣሪያ መያዝ ይወዳሉ ።. . . . ቁመታቸው መካከለኛ

ሆኖ ጡንቻቸው ያፈረጠመ ነው ። ፊታቸው በፈንጣጣ ምክንያት ተጉ ረብርቧል ። ግንባራቸው ሰፊ ነው ። እንደ አፋቸው ሁሉ ደስ የሚሉ ጨዋ ዓይኖች አሏቸው ። . . . . አፍንጫቸው ትክክለኛ ሲሆን ፣ አገጫ ቸው ግን ትልቅ ነው ። . . . . ጥርሳቸው ትክክል ሆኖ የወጣና ነጭ ነው ።. . . .” በማለት ጽፎአል ።



**በጦር ልብስ**



ምኒልክ አሣ ሲያጠምዱ ።



ከመኳንንቶቻቸው ጋር



ከአጃቢዎቻቸው ጋር



የምኒልክ ልጅ ወይዘሮ ዘውዲቱ (በኋላ ንግሥት)



ሜግ መሰቀት ያቃተው ኢልግ ቢትወደድ ድረስ የማዕረግ እድገት አግኝቷል።
ከምኒልክም በአገልግሎቱ ኒሻኖች ተሸልሟል ።

# ሕመምና ሞት

ምኒልክ የሞቱት መድኃኒት ተደርጎባቸው ነው የሚል ወሬ አለ ። ታሪኩ እንዲህ ነው ። በ1901 ዓ. ም. በጀርመን ለጋሲዮን በኩል ፓራላይዝ (ሽባ) ሆነው የታመሙትን ምኒልክን ለማከም ዶክተር እስቴንኩለር መጥቶ ነበር ። ይህ ሐኪም ንጉሡንም መኳንንቱንም በኤሌክትሪክ ሙቀት ያክም ነበር ። ከዶክተር እስቴንኩለር ሌላ ደግሞ ንጉሡን እንዲያማክር ተብሎ ዶክተር ዚንትግራፍ የጀርመን ኮንስለር ሆኖ ተሹሞ መጣ ። ዚንትግራፍ የመጣው የዓመት ደሞዙ 12,000 ብር ሆኖ ካገሩ መምጫ 1500 ብር ተከፍሎት ነው ። ለዕቃ መግገዣም ሁለት ሺህ ብር ከምኒልክ ተሰጥቶት ነበር ።

እነዚህ ሁለት ጀርመናውያን ከበጅሮንድ ሙሉጌታና ከአዛዥ መታፈሪያ ጋር ተጣሉ ። የምኒልክ ሕመም እልሻል እያለ ቢሄድ "....ንጉሡ የታመሙትና ማዳንም ያልተቻለበት መርዝ በልተው ነው ። ያበሏቸውም በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ ናቸው ። ....ብለው በአንድነት ተናገሩ ። ይህን ዜና ድሬዳዋ የነበረው አላዛሪ ስት ሚሲዮን ፣ በነበረው ጋዜጣ ላይ በፈረንሣይኛና በአማርኛ ቋንቋ ዎች አትሞ አወጣው ።

ምኒልክ የታመሙት መርዝ በልተው ነው የተባለው ጉዳይ ከባድ ክርክርና ውዝግብ ያስነሳ ነው ። ውዝግቡ በአገር ውስጥ ብቻ ሣይሆን በውጭ አገር ጭምር ነበር ። ይህን በኋላ እንመለስበታለን ።

ምኒልክ በ1900 ዓ.ም. ግንቦት 10 ቀን እንጦጦ ላይ ከኢጣሊ ያኖች ጋር በዚያን ጊዜ የኢጣሊያ ሱማሌ (ሞቃዲሾ) ይባል የነበረውንና የኢትዮጵያን ወሰን ስምምነት ከፈረሙ በኋላ የደም ብዛት መታቸውና የቀኝ ጐናቸው ፓራላይዝ (ሽባ) ሆነ ። በወሰኑ ጉዳይ ብዙ ክርክር ስለነበር በዚያ ምክንያት የደም ብዛት መታቸው ይባላል ።

ይህም ብቻ ሣይሆን ምኒልክ የልብ ሕመም ነበረባቸው ። ይህ ንንም የልብ ሕመም እንዳለባቸው ያወቀው ቪታሊን የተባለው ሐኪም በ1900 ዓ.ም. ባደረገላቸው ምርመራ ነበር ። ቪታሊን የልብ ሕመም እንዳለባቸው ካወቀ በኋላ ሕመሙ በቅርብ ጊዜ አደጋ የማያደርስ መሆኑን ተናገረ ። ምኒልክ ግን ሕመሙ እየጠናባቸው ሄደ ።

በ1900 ዓ.ም. በግንቦት ወር የመታቸው የደም ብዛት በተደረገ ላቸው ሕክምና በሰኔ ወር ሻል ቢላቸውም እንደወትሮው መናገር ግን ያስቸ ራቸው ነበር ። እግራቸውም ቢሆን እንደተለመደው አይራ መድላቸውም ነበር ። ለምሳሌ ሰኔ 20 ቀን፣ ብሪስን በተቀበሉበት ጊዜ የሚራመዱት በከዘራ እየተደገፉ ነበር ። ይህም ቢሆን ምኒልክ ሕመማ ቸውን ሕዝብ ሳያውቅባቸው የተለመደ ሥራቸውን ይሠሩ ነበር ። ለም ሳሌ በዚያው ዘመን በሐምሌ ወር አዲሱን ማተሚያ ቤት መርቀው ከፈቱ ። ሐምሌ 6 ቀን ችሎት ላይ ውለው በስምንት ሰዎች ላይ የሞት ፍርድ ፈረዱ ።

በዚያው ዘመን ነሐሴ ሁለት ቀን የፖሊስ ኃይል በኢትዮጵያ እንዲቋቋም ፈረንሳይ ለጋሲዮን ከሚሠሩ ፈረንሳዮች ጋር ተነጋገሩ ። በፖስታ ቤት ሰገነትና በገበያው መሐል የተሰቀሉትን ሁለት ሰዓቶች ነሐሴ 9 ቀን እየተዘዋወሩ ጐበኙ ። ነሐሴ 12 ቀን ደግሞ የልደት በዓላ ቸው በሚከበርበት ጊዜ በበዓሉ አከባበር ላይ ፍፁም ጤነኛ መስለው ይታዩ ነበር ። የምኒልክን መታመም የሚያውቀው በኢትዮጵያ ፈረን ሳዩ ሚኒስትር ብሪስ የውጭ ጋዜጦችን ወደ ግቢ ከመላክ አቋርጦ ነበርና ነሐሴ 18 ቀን፣ ብሪስን ጠርተው ለምን ጋዜጦችን እንዳቋረ ጠባቸው ጠይቀው እንዲልክ አዘዙት ። ይህ ሁሉ ሆኖ ጤነኛ እየመሰሉ ቢታዩም ነሐሴ 21 ቀኖ ወገባቸው በጠቅላላው ፓራላይዝ ሆነ ።

ሐኪማቸው ሁኔታውን ሲገልጽ ፡ "...በነሐሴ ወር አመማቸው። ከከተማው መድኃኒት መሸጫ ሱቅ (ፋርማሲ) አትሮፓይን ወስጂ እንዲጠቀሙበት አደረግሁት ። በ1907 ዓ.ም. 84 ኪሎ ግራም ይመዝኑ የነበሩት ምኒልክ በሰኔ ወር 1908 ዓ.ም. 78 ኪሎ ግራም ሆኑ ። አሁን በነሐሴ ወር ደግሞ ክብደታቸው 71 ኪሎ ግራም ወረደ።...." ብሏል ።

ብሪስ ደግሞ ነሐሴ 28 ቀን 1908 ዓ.ም. (በኛ ነሐሴ 22 ቀን 1900 ዓ.ም.) ለወዳጁ ለፒካን ከአዲስ አበባ በጻፈለት ደብዳቤ ላይ "....ነሐሴ 26 ቀን የደም ብዛታቸው ተነሳና ጣላቸው ። ይህ በሆነ በት ጊዜ ባጠገባቸው በጅሮንድ ሙሉጌታ ነበሩ ። በጅሮንድ ሙሉ ጌታም ደንግጠው ምኒልክን በክንዳቸው ተሸክመው መኝታ ቤት ወስ ደው አስተኙዋቸው ።...." በማለት ገልጾለታል ።

በዚያው ዘመን በነሐሴ ወር ከፈረንሣይ መንግሥት ተልኮ ምኒ ልክን ለማከም አዲስ አበባ የገባው ፈረንሣዊው ሐኪም ዶክተር ኽርማይነር ምኒልክን ማከም እንደጀመረ የሰማውን ሲገልጽ "... እን ዲት ዓይኗ የጠፋባት ድመት ፡ ከወገቧ በታች የተሽመደመደች ፡ ጭራዋ የተቆረጠ ፡ አንገቷ ላይ ድግምት ተጥፎ የታሰረባት ፡ ምኒልክ ዙፋን ሥር በሚስጥር ተቀምጣ ተገኘች እያሉ ያወራሉ ።...." ብሏል ። መረ

ብም “....አቡነ ማቴዎስንም እንዲሁ አድርገው ነው የገደሏቸው....” ይላሉ ።

ምኒልክን ለማከም ብዙ ሐኪሞች ከያገሩ መጡ ። ከሶሪያ ሙሣ አሊ ቤይ ፡ ከቱርክ ፖውል መረብ ፡ ከፈረንሣይ ኽርማይነርና ዶክተር ዌክማን ፡ ከጀርመን እስቴንኬለር ፡ የግል ሐኪማቸው ቪታሊን እነኚህ ሁሉ የምኒልክን ሕመም ያጠኑ ጀመር ።

ብሪስ እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 4 ቀን 1908 ዓ.ም. (በኛ መስከረም 24 ቀን 1900) ላገሩ ለፈረንሣይ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በጻፈው ደብ ዳቤ “....ንጉሡ አሁን ተሽሏቸዋል ። ግን ለመደገፊያ ከዘራ እየያዙ ነው የሚሄዱት ።.... ሐኪሞቻቸው ከባድ በሆነ የመንግሥት ሥራ ላይ እንዳይካፈሉ ከልክለዋቸዋል ። ምክንያቱም ጤንነታቸው ስላልተ ረጋገጠ ነው....” ሲል ጽፏል ።

ቪታሊንም “....ምኒልክ ለሐኪሞቻቸው ጥሩ በሽተኛ አይደ ሉም ። አስቸጋሪ ሰው ናቸው ። ጤናቸው በሚታወክበት ጊዜ የሐኪ ሞቹን ትእዛዝ አክብረው ሐኪሞቹ እንዳሉዋቸው ያደርጋሉ ። ሻል ሲላቸው ግን ሐኪሞቹንና የሐኪሞቹን ትእዛዝ ይንቁና እንደፈለጉት ሆነው ከባድ ሥራ መሥራት ይጀምራሉ ።...” ብሏል ።

በደም ብዛቱ ምክንያት ምኒልክ አቋማቸውን ስተው ስለወደቁ በቤተ መንግሥቱና በሌሎችም ዘንድ ምኒልክን ሰይጣን ጣላቸው ተብሎ ታመነ ። ይህንንም ሰይጣን ለማስለቀቅ ጠበል ነው እንጂ ሐኪም አያድንም ተብሎ በ1901 ዓ.ም. በሕዳር ወር ደብረ ሊባኖስ ሄደው ጠበል እንዲጠመቁ ተወሰነ ። በውሳኔውም መሠረት ህዳር 18 ቀን ወደ ደብረ ሊባኖስ ተወሰዱ ።

ወደ ደብረ ሊባኖስ የመሄዳቸውን ጉዞ ብሪስ ለፈረንሣይ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከአዲስ አበባ በጻፈው ደብዳቤ “....እንጦጦ ላይ አራት ቀን ካደሩ በኋላ ንጉሡ ወደ ገዳሙ ጉዞ ጀመሩ ። አብረዋቸው ራስ ወልደ ጊዮርጊስና ሌሎችም መኳንንቶች አሉ ። በጠቅላላው ያጀ ቡዋቸው ሰዎች 8 000 ያህል ሲሆኑ ለጓዝ መጫኛና ለቀለብ የሚጓ ዘው እንስሳ ደግሞ 30 000 ይሆናል ። ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አገሪቱን እንዲመሩ አዲስ አበባ ቀርተዋል ። ሚኒስትሮችና መኳንንት ሁሉ አዝነዋል ። ሕዝቡም በምኒልክ መታመም ተክዟል ። ሐኪማቸው ዶክተር ኽርማይነር ለጥበቃ አብሯቸው ሄዷል ። ኽርማይነር በላከው ሪፖርትም በጉዞው ላይ የምኒልክ ጤንነት ጥሩ ነበር ብሏል ።....” በማለት ዜናውን አስተላልፏል ። በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜም የሬውተር ጋዜጠኛ ንጉሡን ተከትሎ ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄደ ።

ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ በልጅነታቸው ያዩትን የሚ ከተለውን ጽፈዋል ። “. . . .እግራቸውን ስለታመሙ ወደ ደብረ ሊባኖስ ሔደው ጠበል ቢጠመቁ ይሻላል ተብሎ ተመከረና በኅዳር 1 ቀን 1901 ዓ. ም. ከአዲስ አበባ ተነሱ ። ለመጓጓዣ የተሰናዳው አንድ ሲትሮይን መኪና ነበረ ። ይኸውም ከፈረንሣይ አገር . . . . የመጣ አውቶ ሞቢል ነው ። ሾፌሩ መኪናውን ለመፈተሽ እስከ እንጦጦ ድረስ እየነዳ አውጥቶት ነበረና በዚያ ጊዜ እኔ እራሴ መኪናውን አይቼዋ ለሁ ። የራዲያተሩ ውሃ ቶሎ ቶሎ እየፈላ አስቸግሮ ነበር ። እንጦጦ ላይ ከመንደሩ ውሃ እየተወሰደ ሲጨመርበት ያየሁትም ትዝ ይለኛል።

“ከዚህ በኋላ መኪናው ለጃንሆይ ጉዞ የማያመች መሆኑ ስለተገ መተ ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ ሌላ ዘዴ ይፈለግ ጀመር ። የተገኘው ዘዴ በባለ አጐበር ጋሪ እንዲጓዙ ማድረግ ነው ። ባለአጐበሩ ጋሪ ለሰው መቀመጫ ወይም ለመኝታ እንዲስማማ ሆኖ በእናጢዎች ተዘጋጀ ። እርሱም በሁለት ምስንጅር በቅሎዎች ተጭኖ ሊጓዙበት በሚችል ዓይነት ሆኖ ተሠራ ። ከዚህ በኋላ ጃንሆይ በውስጡ ተኝተው ተጓዙበት ። ድካም እንዳይሰማቸውም በቅርብ በቅርቡ ሠፈር እንዲያ ረግ ተወሰነ ።

“ስለዚህም በመጀመሪያ ቀን ከአዲስ አበባ ቤተ መንግሥታቸው ተነስተው እንጦጦ ተራራ ሥር አደሩ ። ይህ ቦታ ዛሬ ቁስቋም የተተከ ለችበት ቁልልታ ነው ። በሁለተኛው ቀን ከዚያ ተነስተው እንጦጦ ማርያም አደሩ ። በሶስተኛው ቀን ከእንጦጦ ተነስተው ሱሉልታ እዘ ብጡ ላይ በባላባቱ በዋቆ ቱፋ ቤት አጠገብ ሠፈሩ ። በዚህ እኳኋን እየተጓዙ ከአሥር ቀን በኋላ ደብረ ሊባኖስ ደረሱ ።. . . .”

እውነተኛው የምኒልክ በሽታ ፓራላይዝ ነው ። እቴጌይቱና ጳጳሱ ፥ ሐኪም እንዳይነካቸውና በጠበል ብቻ ይድናሉ እያሉ በቀዝቃዛ ውሃ ስለሚነከሯቸው የምኒልክ ሕመም እየባሰ ሄደ ። በተለይም ከአዲስ አበባ ደብረ ሊባኖስ ድረስ ባለው መንገድ ጉዞው ራሱ ተጨማሪ በሽታ ሆነባቸው ። ደብረ ሊባኖስ ወርደው ሶስት ወር ያህል ጠበል ሲጠመቁ አብሯቸው የነበረው ሐኪማቸው ኽርማይነር ያ ቀዝቃዛ ውሃ እንደማያድናቸው ቢያውቅም ፈርቶ ዝም አለ ።

በዚያው ዘመን ከጠበሉ ቦታ ደርሶ የነበረው ፈረንሣዊው ተጓዥ ሬሞንድ ሲጽፍ “. . . .አንድ ቀን ጧት ንጉሡ ሊነከሩ ሄዱ ። ሲጠመ ቁም ግርዶሽ ተጋርዶ ፡ ወደ ግርዶሹ መጥፎ መንፈስ እንዳይጠጋ ዙሪ ያውን መስቀል ተይዞላቸው ተጠመቁ ። ጊዜው ጧት ነው ። ውሃው ደግሞ እንደ በረዶ የቀዘቀዘ ነው ። ምኒልክ ተጠምቀው ሲወጡ ፈረን ሣዊውን ሐኪም ጠሩትና ‘እነዚህ ሰዎች ሊገድሉኝ ነው ። ወደ ውሃው

ዳግመኛ እንዳያስገቡኝም እባክህ አድነኝ ። እስከ ሁለት ቀን ከእነኚህ ሰዎች እጅ ካላወጣኸኝ የማደርገውን እኔ አውቃለሁ' አሉት ። ሐኪሙ ኸርማይነርም በዚያ ቀዝቃዛ ውሃ ከመንከር እንዲተዉዋቸው ተማፀነ ። ግን እሺ አላሉትም. . . .'' ብሏል ። ይህን ነገር ካስትሮም ጽፎታል ።

ምኒልክ ከጠበሉ ቦታ በደብረ ሊባኖስ እስከ ጥር ወር መጨረሻ ድረስ ቆይተው የካቲት 5 ቀን አዲስ አበባ ገቡ ። ከደብረ ሊባኖስ ሲመለሱም እንጦጦ ድረስ በመኪና መጥተው ከእንጦጦ በኋላ ሰው ይየኝ ብለው በበቅሎ ሆነው አዲስ አበባ ገቡ ። በመንገድ ላይ የሚያ ያቸው ሕዝብም እልል እያለና እያለቀሰ ተቀበላቸው ። ለቅሶው ''. . . .ልጅ ከእናቱ ሲለይ እንደሚያለቅሰው ነበር ። . . . . በመንገዱ ሁሉ የምኒልክና የጣይቱ ፎቶግራፍ በአበባ እየተከበበ ተደርጐበታል ። አዲስ አበባ ሲገቡም 19 ጊዜ መድፍ ተተኮሰ ።. . . .'' በማለት አለቃ ክንፉ ጽፈዋል። አዲስ አበባ ውስጥ የነበረውም ቦሶዳሪ እ.ኤ.አ. የካቲት 23 ቀን 1909 ዓ.ም. ለንደን ላለው ግሬይ በጻፈለት ደብዳቤ ላይ ''. . . .ምኒልክ የካቲት 13 ቀን (እ.ኤ.አ.) ከጠበሉ ሥፍራ ተመልሰው ጭር ካለችው ከአዲስ አበባ ከተማቸው ገቡ ። ምኒልክ ከቀኝ ጐናቸው ከወገባቸው በታች ፈጽመው ፓራላይዝ ሆነዋል ። የሚጓዙትም ተሽከርካሪ እግር ባለው ወንበር ላይ ሆነው ነው ። አእምሮአቸው ደህና ነው ። ምግብም ይበላሉ ። . . . . በሕዝብ በዓል ላይ ለመገኘት እየፈለጉ ይገኛሉ ። የካቲት 20 ቀን የጀርመኑን ሚኒስትር ሸለር እስቴይን ዋርትስን ተቀ ብለው አነጋገሩ. . .'' ብሏል ።

በአዲስ አበባ ተቀማጭ የሆነውን የጀርመኑን ጉዳይ ፈጻሚ ሚኒ ስትር ያነጋገሩት የጀርመኑ ንጉሠ ነገሥት ሐኪም እንዲልኩላቸው መጠየቃቸው ሳይሆን አይቀርም ። ወይም ደግሞ ''. . . .አንድ የተማረ ሰው እንፈልጋለን ። በምክር እንዲረዳን ። ዶክተር ዚንትግራፍ ከኛ ዘንድ በነበረበት ጊዜ እንዳስደሰተን ሁሉ አሁንም እሱው ወደኛ እንዲዛወር ፈቃድዎን እንጠይቃለን ።. . . .'' በማለት ለጀርመኑ ንጉሠ ነገሥት የጻፉትን ደብዳቤ ለመስጠት አስጠርተውትም ይሆናል ።

ተቀማጭነቱ አዲስ አበባ የሆነው የኢጣሊያኑ ሚኒስትር ኮሊ ለኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባስተላለፈው ሪፖርት ''. . . .ምኒልክ በመሀሉ እየተገኙ ያስለመዱት የአዲስ አበባ ሕዝብ በምኒልክ መጥፋት አዝኗል ። ይህን ያወቁት ምኒልክም አንዳንዴ በሰረገላ ፣ አንዳንዴ ደግሞ በበቅሎ እየሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ መሀል በመዘዋወር ለሕ ዝቡ እንዳስለመዱት አሁንም እየተዘዋወሩ ይታያሉ ። የሚያጅቧቸውም ነጫጭ ልብስ የለበሱ አምስት ወይም 600 ያህል ሰዎች ናቸው ።. . . . አንድ ቀን ምኒልክ በከተማው ውስጥ ሲዘዋወሩ ከገበያው መሀል

ልጅ ኢያሱን አገኙዋቸው ። ምኒልክም በቅሎአቸው ላይ እንደሆኑ ቁል ቁል በመጥፎ አስተያየት አዩዋቸው ። የሸመገለ አንበሳ አስተያየትና ግርማ ፡ እንደሚያስፈራው ሁሉ ሕዝቡ በምኒልክ ሁኔታ ደነገጠ ። ምኒ ልክ በበቅሎዋ ላይ ሆነው መቁነጥነጣቸው ሲታይ ፓራላይዝ የሆኑ አይመስሉም ። ሕዝቡም ሊያውቅ አልቻለም ። ምስጢሩም ከግቢ አልወ ጣም ።. . . .እንደተለመደው በቅሎአቸውን ያቆሙና የሚያጋጥማቸውን ሰው ሁሉ ያነጋግራሉ ። እያንዳንዱንም ሥራ ይቆጣጠራሉ ። እጅ ለሚነ ሷቸውም ሰዎች ፈገግ እያሉ መልሱን ይሰጣሉ ። የሕዝቡንም አቤቱታ እየሰሙ ስለዚያ ጉዳይ መኳንንቱን ያነጋግራሉ ።. . . . ምኒልክ ቢያረ ጁም ዓለምን አርቆ የሚያየው አይናቸው አልደከመም ። . . . .” በማለት ጽፏል ።

ባሮይስ ስለምኒልክ ሕመም ሲገልጽ “. . . .ምኒልክ የታመሙ መስ ለው አይታዩም ። ዕድሜያቸው 64 ዓመት ሆንዋል ። የነበራቸው ውበት ግን አልተቀነሰም ። ቀልዳቸውም አልቀረም ።. . . .ይህ ሕመም የጀመ ራቸው ፣ ሰይጣን ከሠራት አውቶሞቢል ላይ ከተቀመጡ በኋላ ነው እያሉ ቄሶች ያወራሉ ። እሳቸው ግን አሁንም ቢሆን የምዕራባውያንን የቴክኒክ ሥራ ማጥናትና ማየት ይወዳሉ ። . . . .ችግራቸው በቄሶች በኩል ነው ። አሁንም ቢሆን ወደ ደብረሊባኖስ ሄደው እንደገና በጠ በል መጠመቁን እንዲጀምሩ አቡኑ ይወተውታሉ ። ምኒልክ ግን ጠበሉ እንደማያድናቸው ያውቃሉ ። ይህን ሲናገሩም ጣይቱና አቡኑ ይቆጧቸ ዋል ።. . . .” ብሏል ።

ከጀርመን መንግሥት የተጠየቁት አማካሪው ዚንትግራፍ ሐኪሙ ማክስ እስቱንኬለር በ1901 ዓ. ም. መጋቢት 30 ቀን አዲስ አበባ ገቡ ። እስቴይንኬለር ከነሚስቱ አዲስ አበባ ሲገባ በቤተ መን ግሥቱ አቀባበል ተደረገለት ። መኖሪያም ከዚያው ከቤተ መንግሥቱ ግቢ ውስጥ ተሰጠው ። ከዚያም ሆኖ በቀን ሁለት ጊዜ ከምኒልክ ዘንድ እየገባ ያክማቸው ጀመር ። በጥቂት ቀናት ውስጥም ተሻላቸው ።

ጀርመኖች ከመጨረሻው ደረጃ ከምኒልክ ዘንድ ገብተው አማካ ሪም ሐኪምም በመሆናቸው የኢጣሊያ ፤ የፈረንሳይና የእንግሊዝ መን ግሥታት ተቃውሞ አቀረቡ ። እነዚህ መንግሥታት ትሪፓርቲት የተ ባለውን ኢትዮጵያን የሚያከፋፍላቸውን የራሳቸውን የስላም ውል ተዋ ውለው ነበርና የጀርመን መንግሥት ውሉን እንዳፈረሰ ያህል ተቆጠረ ። ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑ የእንግሊዝ ፣ የፈረንሣይና የኢጣ ሊያ ሚኒስትሮችም ተቃውሞአቸውን በግልጽ አዲስ አበባ ላለው ለጀርመን ኤምባሲ አስታወቁ ። በተለይ የኢጣሊያ ጋዜጦች ጉዳዩን

እየተነተኑ የጀርመንን መንግሥት በመወንጀል ይጽፉ ጀመር ። ኤኮ ኤላ እስታምፖ የተባለው የሚላኖ ጋዜጣ ፌብሪዮ 25 ፣ ማርዞ 2 ፣ ማጂዎ 10 ቀን 1909 በወጡት ገጾች ጀርመን የትሪፖርቲን ውል ከፈረመ በኋላ ውሉን አፍርሶ ምኒልክን ሞኖፖል (የግሉ) አድርጎ ያዘ እያለ በተደጋጋሚ ጻፈ ።

የጀርመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቦኤን በጀርመን መንግሥት ላይ ለሚወርደው የጋዜጣ ነቀፋም ሆነ ለየመንግሥታቱ ጥያቄ "....ምኒልክና ዚንትግራፍ በግል ያደረጉት ስምምነት ነው እንጂ ጀርመን መንግሥት በጉዳዩ አልገባበትም ። ዚንትግራፍ ይላክልን ተብሎ በተጠየቀ ጊዜ ለእንዲህ ያለ ትልቅ ቦታ ለመመረጥ ዕድሜው ለጋ ነው ብለን ነበር ። ዓለም ሊያውቅልን የሚገባው የኛ ምርጫ ቢሆን ኖሮ እንዴት ብለን ይሄን ልጅ ልንመርጠው እንችላለን?.." እያለ አሳወቀ ። የዚንትግራፍን በቤተ መንግሥት መግባት ጣይቱም ቢሆኑ አልተደሰቱበትም ። ጣይቱ የዚንትግራፍን መምጣት የተቃወሙበት ምክንያት ለጀርመን ተቃዋሚ መንግሥታት ረድተው ሳይሆን በፊት አዲስ አበባ በነበረበት ጊዜ አይዋደዱ ስለነበር ነው ።

እስቴይንኬለር እና ዚንትግራፍ ምኒልክን ሲያክሙና ሲመረምሩ ቆዩ ። ሻል ብሎአቸው የነበሩት ምኒልክ ግንቦት 3 ቀን እንደገና ሕመማቸው ተነስቶ ጣላቸው ። እስቴይንኬለር የሚያክምበት የኤሌትሪኩ መሣሪያ ጥቂት ቀን ከሠራ በኋላ ተበላሸ ። መሣሪያው አዲስ አበባ ውስጥ ሊጠገን ባለመቻሉ ሁለቱም ጀርመኖች ደነገጡ ።

ዚንትግራፍ ግንቦት 7 ቀን 1901 ዓ.ም. "....ንጉሡ የታመሙት መርዝ በልተው ነው ። በተደረገው ምርመራ በደማቸው ውስጥ መርዝ ተገኝቷል ። ይህንንም መርዝ ያበሏቸው በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ ናቸው ።...." ብሎ ተናገረ ። እነኛ ምኒልክ ያሳደጓቸውና የሚያምኗቸው አገልጋዮቻቸው ይህን ማድረጋቸውን የሰማው መኳንንት ሁሉ ደነገጠ ። የምኒልክ ሠራዊትም ቆራርጦ ሊጥላቸው ተነሳ ። ሁለቱ የታሙት ሰዎች ግን ከምኒልክ መኝታ ቤት ከምኒልክ ጋር ተቀምጠው አልወጣ አሉ ።

ይህ በሆነ በ3ኛው ቀን የሰዎቹን ያለመነካት ወይም ከሹመታቸው ያለመሻር ያየው ዚንትግራፍ ወደ እቴጌ ጣይቱ ዘንድ ገብቶ "....እነ ኚህ ንጉሡን መርዝ ያበሏቸው ሰዎች ከሹመታቸው ተሽረው ካልታሰሩ ንጉሡ አይድኑም ።...." ብሎ በከንቲባ ገብሩ አስተርጓሚነት ተናገረ ። እቴጌ ጣይቱም "....ነገሩ የማይታመን ነገር ሆኖብን ነው ። በውኑ በንጉሡ ላይ ማን መርዝ ያደርግባቸዋል ። ይህስ አይጠረጠርም...." ብለው መለሱ ። ከንቲባ ገብሩም ጣልቃ ገብተው "....እመ



ከንቲባ ገብሩ ።



ፕሮፌሰር
አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ

ቤቱ ይህንንስ አይበሉ ። አሽከር ክፉ ነው ። በገንዘብም በምንም ይገ ዛል ።. . . .'' አሉዋቸው ። እቴጌ ጣይቱም "በአጤ ምኒልክ ላይ እልፍ ወርቅ ቢሰጡት ክፉ ነገር የሚያደርግባቸው የለም'' ብለው መለሱ ። ከዚህ በኋላ ጀርመኑ ምንም ክርክር አላቀረቡም ። የተቻላቸው ሁሉ እንደሚደረግ ተናግረው ወጡ ።

በመሀሉም ምኒልክ ለገነገነው ሕዝብ አዋጅ ነገሩ ። ". . . .ልጆ ቼን ፣ ያሳደግኋቸውን ፣ የማምናቸውን በጅሮንድ ሙሉጌታንና አዛዥ መታፈሪያን እንዳትነካብኝ ። በክፉ አይንህም አትይብኝ ። መርዝ አብል ተውኝ ከሆነ ነገሩ ከተጣራ በኋላ እኔው እቀጣቸዋለሁ ። ነገሩ ተመር ምሮ ሳይጣራ ግን በነሱ አትክፋብኝ ። ቃሌን ጥሰህ ከድሮ ክብራቸው ብታዋርድብኝ ማርያምን አማላጅም የለኝ'' ብለው አወጁ ። በጅሮ ንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያም ከተደበቁበት ወጡ ።

በጅሮንድ ሙሉጌታ ይገዙ በዘመኑ የገንዘብ ሚኒስትር የነበሩና ከምኒልክም ጋር የተቋጥሮ ዝምድና ያላቸው ናቸው ። ከዚንትግራፍ ጋር ደግሞ በገንዘብ ብድር ምክንያት ተቀያይመዋል ። በአሁኑ ጊዜ ከአዛዥ መታፈሪያ ጋር ሆነው ምኒልክን በማስታመም ላይ ናቸው ። በጅሮንድ ሙሉጌታ በ1928 ዓ.ም. ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ የጦር ሚኒስትር ነበሩ ። በጦርነቱ ላይ ተሸረው ከማይጨው ድል መሆን በኋላ ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ኢጣሊያኖች በአይሮፕላን ተከታትለው በመትረየስ የገደሉዋቸው ከኢትዮጵያ ታላላቅ ጀግኖች አንዱ ናቸው ። በአገልግሎታቸውም ራስ ማዕረግ ደርሰዋል ።

አዛዥ መታፈሪያ መልከጼዲቅ ደግሞ በዚያን ዘመን የግቢ ሚኒ ስትር ነበሩ ። አዛዥ መታፈሪያ ከምኒልክ ጋር ምንም ዝምድና የሌላ ቸው የኦሮሞ ተወላጅ ናቸው ። ምኒልክ አዛዥ መታፈሪያን ገና በሕፃንነታችው ከወላጆቻቸው ዘንድ ወስደው በቤተ መንግሥት ውስጥ እያስተማሩ አሳደጉዋቸው ። አዛዥ መታፈሪያ ጀግናና ታማኝ አገ ጋይ በመሆናቸው ከግቢ አዛዥነት ለግቢ ሚኒስትርነት የበቁ ሰው ናቸው ። በ1928 ዓ.ም. ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ ታላቅ ጀብዱ ሠርተዋል ። ኢጣሊያኖችም ማርከው አዚናራ ወስደው እስረ ዋቸው ነበር ። ከነፃነት በኋላም ተፈትተው በ1938 ዓ.ም. በሕመም ሞቱ ። ሁለቱንም በመጠኑ ለማስተዋወቅ ያህል ነው ።

ጀርመኖች የጀርመን መንግሥት ተቃዋሚዎች መሪና ደጋፊ እቴጌ ጣይቱ ናቸው ብለው አምነዋል ። የጣይቱም ሐሳብ ምኒልክን ለመግደል ሳይሆን በሽተኛ አድርገው አስቀምጠው እሳቸው ሥልጣኑን ይዘው ለመምራት ፈልገው መርዙን በቀጥታ ወይም በደጋፊዎቻቸው አማካይነት አበሉዋቸው ተባለ ። በዚህ ምክንያት ልክ ነው ፣ ልክ አይ ደለም በሚል ክርክር መኳንንቱ ሁሉ ለሁለት ተከፋፈለ ።

በመኳንንቱ መከፋፈል ምክንያት አዲስ አበባ ከተማ ሰላም አጣች ። በየአውራጃው ያለው መኳንንት ሁሉ ሠራዊቱን እየያዘ አዲስ አበባ ገባ ። "....ጌታዬ አንድ ነገር ይሁንና እንተያያለን...." እያሉ ፎካሪውም አስፎካሪውም በዛ ። እቴጌ ጣይቱም ለራሳቸው ጥበቃ ሲሉ ወንድማቸውን ራስ ወሌን ከጐንደር አስጠሩ ።

በዚያን ጊዜ የጦር ሚኒስትርና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ የነበሩት ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ከየአውራጃው ወደ አዲስ አበባ የመጣው መኳንንት ሁሉ ሠራዊቱን እየያዘ ከአዲስ አበባ ከተማ እንዲ ወጣና ወደየግዛቱ እንዲሔድ አዘዙ ። ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ የተከ በሩ ታላቅ ሰውና ለምኒልክም ታማኝ ወዳጅ ስለነበሩ የታዘዘው መኳ ንንት ከአዲስ አበባ ከተማ ወጣ ። የአዲስ አበባ ከተማ ፀጥታም ሻል አለው ። የምኒልክ እኅት ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ ራስ ተሰማ ፣ ደጃዝ ማች ለማ ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ ባንድ ነት ሆነው ዚንትግራፍ ጣይቱን መቃወሙን እንዲቀጥልበት አደረጉ። እቴጌ ጣይቱ ይህን ሕዝብ እንዲነሳሳ ያደረገው ምስጢሩን የሚያው ቀው አስተርጓሚው ከንቲባ ገብሩ ነው ብለው ለብቻ አስጠርተው ጠየቁቸው ። "....በምኒልክ ላይ ይሄን መርዝ አበላ የሚባለው በእ ርግጥ ማነው ?" ቢሏቸው ከንቲባ ገብሩ "ንግሥት ሆይ ፣ ባውቀውማ የጌታዬን ጠላት እኔው እይዘው አልነበረምን?" ብለው መለሱ ። ጣይ ቱም "የሐኪሞቹን ወሬ አስፋፍተህ ሕዝብ እንዲሸበር ያወራህ አንተ ነህ" ብለው ስላስፈራሩዋቸው ከንቲባ ገብሩ ደንግጠው ከጀርመን ኤምባሲ ገብተው ተሸሸጉ ።

ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሚኒስትሮችን ፣ የጀርመኑን ቆንሲልና ዚንትግራፍን ሰብስበው በጉዳዩ ላይ እንዲነጋገሩ አደረጉ ። ጀርመኖቹ ለጉባኤው ሲናገሩ መርዙን በምኒልክ ላይ ያደረጉት በጅሮንድ ሙሉ ጌታና አዛዥ መታፈሪያ ናቸው በሚለው እቋማቸው ፀኑ ። ለምን? ለሚለው ጥያቄም ቆንሲሉ መልስ ሲሰጡ "....ጣይቱ ምኒልክን ሽባ አድርገው ሥልጣን ለመያዝ ስላሰቡ ነው ። ለሥልጣኑ አያያዝ እንዲያመቻቸውም ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ተስማምተው በሱዳን በኩል ጦር ሊያስገቡ ነው ።....." ብለው ተናገሩ ። ከዚህ በኋላ ጉባኤው ምኒልክ እልጋ ወራሻቸውን እንዲያሳውቁ ወሰነ ። ይህንኑ ውሳኔውን ለምኒልክ አቀረበ ። ምኒልክም የመጀመሪያ ኑዛዜአቸውን በደብዳቤ አጽፈው ሰጡ ። ሕዝቡና መኳንንቱ ጃንሜዳ ከተሰበሰበ በኋላ ግንቦት 10 ቀን 1901 ዓ. ም. የኑዛዜው ቃል ተነበበ ።

"የአገሬ የኢትዮጵያ ልጆች ፣ ልጆቼ ፣ ወዳጆቼ ፣ እግዚአብሔር የገ ለፀልኝን ምክር ልምክራችሁ ። ምክሬንም እግዚአብሔር በልባችሁ እንዲያሳድርባችሁ ተስፋ አደርጋለሁ ።

“አጼ ቴዎድሮስ የሞቱ ጊዜ ከእሳቸው ጋር የነበረው ሰው ሁሉ ያንዱን አገር አንዱ እያርባለሁ ፡ አንዱን ገድዩ እኔ ጌታ እሆናለሁ እያለ ሁሉም ላይረባ ተላልቆ ቀረ ። ከዚህም በኋላ ያጼ ዮሐንስ ሰው የሆነውን የምታውቁት ነው ። ባገር በሽታ ሳያገባበት ፡ ሌላ የባዕድ ጦር ሳይነሳበት ፣ በምቀኝነት እርስ በርሱ እንደተላለቀ አያታችሁታል ።

“አሁንም ልጆቼ ፣ ወዳጆቼ ። አንዱ ባንዱ ምቀኝነት ይቅር ። ያን ዱን አገር አንዱ እኔ እደርባለሁ እንዳትባባሉ ። እኔ እስከአሁን በፍ ቅር እንዳኖርኋችሁ እናንተም ተስማምታችሁ በፍቅር እንድትኖሩ እለምናችኋለሁ ። እናንተ አንድ ልብ ከሆናችሁ ፣ በምቀኝነት እርስ በር ሳችሁ ተዋግታችሁ ካላለቃችሁ በቀር ፡ አገራችንን ኢትዮጵያን ለሌላ ባዕድ አትሰጧትም ። ከቶም ነገር አገራችንን አያገኛትም ። ነፋስ እን ዳይገባባችሁ አገራችሁን በያላችሁበት በርትታችሁ ጠብቁ ። ወንድሜ ፤ ወንድሜ እየተባባላችሁ ተደጋገፉ ። የኢትዮጵያን ጠላት ተጋግዛችሁ ከድንበር መልሱ ። የኢትዮጵያ ጠላት ባንዱ ወገን ትቶ ባንድ ወገን ቢሄድና ድንበር ቢጋፋ ፣ በኔ ወገን ካልመጣ ምን ቸገረኝ ብላችሁ ዝም አትበሉ ። ያ ጠላት በመጣበት በኩል ሁላችሁም ሄዳችሁ አንድ ነት ተጋግዛችሁ ጠላታችሁን መልሱ ። እስከየቤታችሁ እስቲመጣ ዝም ብላችሁ አትቆዩ ።

“ይህነን ምክር ለእናንተ መስጠቴ እኔማ በእግዚአብሔር ቸርነት ይህን ያህል ዘመን ገዝቼ የለምን ። ነገር ግን ሰው ነኝና እንግዲህ ስንት ያህል ዘመን እቆያለሁ ስል ነው ። አሁንም እኔ እንደተመኘሁት እግዚ አብሔር የተጨመረበትና ፈቃዱ ሆኖ ልጄን ቢያቆምላችሁ ከልጄ ጋር ሆናችሁ አገራችሁን ጠብቁ ። አደራ ብያችኋለሁ ። አደራ የሚያኖሩበት ነው የታመነ ስለሆነ ነው ። አሁንም እኔ እናንተን አምኜ ልጄን አደራ ብዬ እሰጣችኋለሁና አሳድጉት ። በብልሃት ምከሩት ። በጉልበት እግ ዙት ። በምክር ደግፉት ። ልጄን አደራ መስጠቴ ከልጄ ጋር ኢትዮጵያን አደራ ጠብቁ ማለቴ ነው ። እኔም ይኸው በገገሮቹ አለማወቅ ፣ በሕ ዝቡ አለመስማማት የተነሣ ከብዙ ዘመን ጀምራ ተከፋፍላ የነበረችውን አገራችንን ኢትዮጵያን ማስኜ ተጣጥሬ ይኸው አስፍቻታለሁ ። እናን ተም ከልጄ ጋር ሁናችሁ ተስማምታችሁ የኢትዮጵያን ድንበር እንዲ ሰፋ እንጂ አንድም ጋት መሬት እንዳይጠብ አድርጉ ። ጠብቁ ። እልሙ ። የደጊቱ አገራችን የኢትዮጵያ አምላክ ያግዛችሁ ። ይጠብቃ ችሁ ።

“ከዚህ ቃል የወጣ በሰማይም ነፍሱ ፤ በምድርም ሥጋው ፣ ልጅ እስከ ልጅ ልጅ የተረገመ ይሁን ። የኢትዮጵያ ውቃቢ ያጥፋው ። እኔም ሳለሁ ከፍቃዴ የወጣውን እረግሜዋለሁ ።”

ከዚህ ጉዛዜ በኋላ የነ በጅሮንድ ሙሉጌታ ጉዳይ እንደገና አገ ረሸ ። ሐኪሙ ዚንትግራፍ "....እነዚህ ሰዎች ከሹመታቸው ተሽ ረው ካልታሠሩ ንጉሡን እናክምም...." ብሎ በደብዳቤ አሳወቀ ። በሐኪሙ አሠራር ግራ የገባቸው እቴጌ ጣይቱም አዲስ አበባ ላለው ለጀርመን መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የሚከተለውን ደብ ዳቤ ጻፉለት ።

ይድረስ ከሙሴ ሸለር
ሰላም ላንተ ይሁን ።

ትናንትና እኔ በቃሌ ነገርኩህ ። በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ እንኳን ንጉሥ የሚበሉትን ሊያሰናዱ ፣ ሲበሉ እንኳን አይ ተዋቸውም አያውቁም ብዬ ። እናንተም ሐኪሙ የተናገረው እውነት ነው ፣ ከሚበሉት ውስጥ መርዝ ተገኝቷልና ሁለቱ ካልወጡ አይሆ ንም ፣ እነሱ ይውጡና ነገሩ ይመርመር ብላችሁ ይህንኑ ፈርዳችሁ ሌላ ሹም ይሾም አላችሁ ።

ወጥ ቤቱ የኔ ፣ ጠላ ቤቱ ፣ ጠጅ ቤቱ የኔ ፣ እዛዡ የኔ ፣ የማበላቸው እኔ ፣ ሌላ ሰው የለ ። እኔ ከማበላቸው ምግብ ውስጥ መርዝ ተገኝቶ እኔን የሚጠቅም ሌላ ሹም መቀበል ለኔ ታላቅ ሸክም እጅግ የሚከብድ ነው ።

ይህንን ደብዳቤ በውል አይታችሁ በወረቀት አስታውቁኝ ። ይህ ነን ነገር ገልጣችሁ ካላስታወቃችሁኝ ወደ መንግሥታችሁ እመለክ ታለሁ ። በጅሮንድ ሙሉጌታ ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ብር ሰጭ ፣ ብር ተቀባይ ፣ የጭፍራ አለቃ ፣ የውጭ ሰው ባልደረባ ነው ። እውጪ ሲወጡ ከበቅሎ ያወጣል ። ጥላ ይይዛል ፣ ይደግፋል ።

አዛዥ መታፈሪያም አንድ ጊዜ እጅ ነስቶ ጉዳዩን ተማክሮ ከመውጣት በስተቀር ከውስጥ አይገባም ። የሁለቱም ሥራ ልዩ ነው ።

ሐኪሙማ መልካም ሰው ነው ፣ ሌላ ሰው አስነስቶት ነው እንጂ ። እሱን የምጠረጥረው ነገር የለም ። አሁንም ይሄንን ነገር ለኔ እጅግ የከበደ ነገር ነውና ልታገሰው አልችልም ። እሱም ባለ ፍትሐ ነገሥቱ በቀደም አደባባይ ታይቶ ይፈረድ ብሏልና እኔም እለምናችኋለሁ የየ መንግሥቱ ቆንስል ሁሉ ተሰብስቦ ፍትሐ ነገሥቱ ታይቶ ይፈረድ ብዬ ። በገንዘብ ነገርና በሌላ ሥራ ቢጣሉ በዚያው በጥፋቱ መነጋገር ነበር እንጂ ባልዋሉበት ነገር እነሱን እንጉዳለን በማለት እኔን የሚያ ዋርድ ነገር ቢሆንብኝ ነው ይታይልኝ ማለቴ ።

፲፱ ቀን ሐምሌ ፲፱፻፩ ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

እቴጌ ጣይቱ ይህን ደብዳቤ ከጻፉ በኋላ በዘመኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ ደግሞ ዶክተር ዚንት ግራፍ ለጻፈው ደብዳቤ መልስ ጻፉለት ።

ይድረስ ከዶክተር ዚንትግራፍ
ሰላም ለርስዎ ይሁን ።

በራስ ተሰማ እጅ ወደ ጃንሆይ የላኩት ደብዳቤ ደርሶልን ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል እንዳስታውቅዎ ታዝዣለሁ ። ስለ ጃንሆይ ጤና መሠረት ያለው ስጋት ስለኖረበት በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ ወደ ጃንሆይ መቅረብ እንዲከለከሉና እንዲመረመሩ ብለው ስላመለከቱት ቃል ፣ ሐኪሙ ሥራ እንዳይፈቱ ቀድሞ የሳቸውን ነገር ጨርሰን፣ እሳቸው ሥራቸወን ይሥሩ በማለት የሳቸውን ነገር ለመጨረስ ቆየን ። ስለሆነም አልተገኘልንም እንጂ እስካሁንም ውስጥ ውስጡን መመርመራችን አልቀረም ። ወደፊትም አዲስ አበባ ያሉት ሚኒስትሮች ሁሉ እንድነት ተሰብስበው ከኛ ዳኞች ጋራ እንዲመረምሩ አስበናልና እነሱ በሚሰበሰቡበት ቀን ሰኞ በ፬ ሰዓት እስዎም አብረው እንዲቀመጡ ይሁን ።

ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

ዚንትግራፍ በተጠራበት ስብሰባ ሳይገኝ ፣ ከኢትዮጵያ ለመውጣት ፈቃድ እንዲሰጠውና እንዲያሰናብቱት በሚከተለው ደብዳቤ አጤ ምኒልክን ጠየቀ ።

አዲስ አበባ በ፲፰ ቀን ሐምሌ ፲፱፻፩
ይድረስ ኀበ ሥዩም እግዚአብሔር
ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ጃንሆይ

በዚህ ጽሕፈት የሚከተለውን ቃል በትህትና አስታውቃለሁ ። ካሁን በፊት ለጃንሆይ ጤና መሠረት ያለው ሥጋት ስለኖረበት በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ ወደጃንሆይ ከመቅረብ እንዲከለከሉና እንዲመረመሩ ብዬ አመልክቼዎ ነበር ። ጃንሆይም አሁን በመጨረሻ የተገናኘሁዎ ዕለት በቸርነትዎ ይሁን ይመርመር ብለውኝ ነበር ። እነዚህ ሰዎች ግን በዚህ መካከል እኔ ያስታወቅሆን ነገር ገልብጠው እንዳልሆነ አድርገው ለመስተሃቀር የቀናቸው መሰሉ ። እነሱ እስከ ዛሬ ድረስ ከሹመታቸው ከማዕረጋቸው ሆነው ሳይከለከሉም ከጃንሆይ

ይገባሉ ። እኔ ግን ከጃንሆይ ለመገናኘት መላልሼ ብለምን ምላሽ እን ኳን አላገኘሁም ። በዚህ ምክንያት ስለ ኢትዮጵያ መንግሥት ድጋፍና የጃንሆይን ማምከሻ ያጣሁ መሆኑ ነው ። በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ ጋር ሥራዬን አብሮ መሥራት አይቻለኝም ። የጃንሆይ ብልሃት ይፍታው ። ወይም በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ ከጃንሆይ እንዳይደርሱ ወይም ከመንግሥት አማካሪነት ካልወጡ በቸ ርነት መሰናበቴን እለምናለሁ ። የጃንሆይን የቸርነት ምላሽ በጀርመን መንግሥት መልከተኛ እጅ እንዲመጣልኝ የከበሬታ ደጅ እጠናለሁ ።

ዶክተር ዚንትግራፍ
ቆንሲልና የመንግሥት አማካሪ

ሕመምተኛው ምኒልክም ዚንትግራፍ ለጠየቀው የመሰናበት ጥያቄ ሐምሌ 18 ቀን 1901 ደብዳቤ አጽፈው "....በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ ይከልከሉ ያልክበትን ነገር ፤ አንተም ልሰናበት ያልክ በትን ብልሃቱ ካልተገለጠ እንዴት ይሆናል ። አንተም ማከስኸ መጥ ተህ የምርምሩ ነገር እንዲታይ ይሁን" የሚል መልስ ላኩበት ። የም ኒልክ ደብዳቤ በተጻፈ ማግስትም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ አዲስ አበባ ላለው ለጀርመን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒ ስትር ለዶክተር ሻለር "....ከጃንሆይ እጠገብ የነበሩ ጃንሆይን የሚያ ስታምሙ ሰዎች ተለውጠው ሌላ አስታማሚ ይሁንልኝና ጃንሆይን ላስ ታም ብለው ዶክተር ኩላደር ለተናገሩት ነገር ምርምር ፣ እዚህ አገር ያሉትን ሐኪሞች ሁሉ ለነገ በ4 ሰዓት እግቢ ሚኒስትሮች መሰብሰቢያ ቤት ድረስ መጥተው ነገሩን ለማመልከት ፈቃድዎን ሰጥተዋቸው እንዲመጡልን በማክበር እንለምንዎታለን" የሚል ደብዳቤ ላኩላቸው።

በማግስቱ ሐምሌ 20 ቀን በቀጠሮው ቀን መኳንንቱና በአዲስ አበባ ያሉ ሐኪሞች ሁሉ ከሶስት ሰዓት ተኩል ጀምሮ ከተጠሩበት ከሚኒስትሮች ምክር ቤት አዳራሽ ተሰበሰቡ ። በዚህ ጊዜም የመንግ ሥቱ ወይም የአልጋ ወራሹ እንደራሴ ሆነው የኢትዮጵያን መንግሥት የሚመሩት ራስ ቢትወደድ ተሰማ ነበሩና እሳቸውም በስብሰባው ላይ ተገኙ ። ጀርመኖቹ ግን እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ተጠብቀው ሳይ መጡ በመቅረታቸው ጉባኤው ተበተነ ።

ሐኪሞቹ የተፈለጉበትና ጉባኤው የተደረገበት ዋናው ምክንያት በምኒልክ ላይ ተገኘ የተባለው መርዝ እንዴት ሊገኝ እንደቻለ ጉባ ኤው ሰምቶ ፣ በጉባኤው የተጠሩት ሌሎች ሐኪሞች ደግሞ ነገሩን እንዲመረምሩ ነበር ። በአዲስ አበባ ከተማ ያሉ ሐኪሞች እነዚንትግ ራፍ ተገኘ ባሉት መርዝ አልተስማሙም ። ነገሩ ቅጥፈት በመሆኑ ተገኘ የተባለው መርዝ ስያናይድ ኦፍ ፖታሲዮም ነው ። ይህ መርዝ ደግሞ

ኃይለኛ በመሆን ወዲያው ገዳይ እንጂ ሽባ የሚያደርግ አይደለም ። በተለይ የበፊት የምኒልክ የግል ሐኪሞች የነበሩት ፈረንሳዊው ዶክተር ቪታሊን እና ዶክተር ኸርማይነር ይህ የተባለው መርዝ በምኒልክ ላይ እንደማይገኝ አረጋግጠዋል ። እነዚህ ሐኪሞች በጣይቱ ትእዛዝ ምኒልክን እንዳያክሙ ቢከለከሉም ከመከልከላቸው በፊት ምኒልክ "....ሳልሞት አድኑኝ....ገና የምሠራው ብዙ ሥራ አለኝ...." ያሏቸው ትዝ እያላቸው በምኒልክ መጫወቻ መሆን ያዝናሉ ።

ጀርመኖቹ ሐኪሞች በጉባኤው ላይ ያልተገኙትም ጉባኤው በሕክምና ምሁራን የተሞላ ስለሆነ ቅጥፈታቸው በይፋ እንደሚገለጥባቸው አውቀው ነው ። የእነሱ ሀሰተኛነት ከተረጋገጠም ለላኩዋቸ ውለጀርመን ንጉሠ ነገሥትም ሆነ መንግሥት ታላቅ ውርደት መሆኑን ስላወቁ ጭምር ነው ። ከጉባዔው ላይ መቅረት ደግሞ የሚጠረጠሩበትን ውሸታምነት ማመን ስለሆነ ይህንኑ ለማስተባበል ጉባኤው በተሰበሰበ በማግስቱ ዚንትግራፍ ረዘም ያለ የእብሪተኛነት ደብዳቤ በአማርኛ አጻፈ ።

አዲስ አበባ በ፳፰ ቀን ሐምሌ ፲፱፻፩
ይድረስ ከክቡር ወልዑል ራስ ቢትወደድ ተሰማ

እስቀድሜ ለአዲሱ የማዕረግ ስምዎ የዓለምና የዕድሜ የሹመት ያድርግልዎ ብዬ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ። ደግሞ ይህን የሚከተለውን ነገር በማክበር አስታውቃለሁ ። በ፲፰ ቀን ሐምሌ በጃንሆይ ማኅተም እንዲህ የሚል ቃል መጣልኝ ። በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ ይከልከሉ ያልክበት ነገር አንተም ልሰናበት ያልክበት ብልሃቱ ካልተገለጸ እንዴት ይሆናል ። አሁንም አንተ ማክሰኞ መጥተህ የምርመራ ነገር እንዲታይ ይሁን አለ ። ይህን ጽፈት ተቀብዬ ወዲያው ለውጭ ሥራና ለንግድ ሚኒስቴር አደላድለው እንዲልኩብኝ ብዬ እንዲህ ስል ይህን ቃል ላክሁባቸው ። በጃንሆይ ማኅተም ለማክሰኞ የምርምሩ ነገር እንዲታይ እንድትመጣ ተብዬ ታድሜአለሁ ። ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎቼን አስቀድመው ምላሽ ሰጥተው እንዲልኩብኝ እለምናለሁ ። መጀመሪያ ምንጊዜና ወዴት ነው ምርምሩ የሚታየው ። ሁለተኛ በማን ላይ ነው ምርምሩ ። ዳኞችስ እነማን ናቸው ። ሶስተኛ እኔስ ለምስክርነት ነውን ወይስ ለማናቸው እንድመጣ ነው የታደምሁት ። ሐኪሙ እስቴይኬለርም ታድመዋል ወይ ። እንዲህ ብዬ ብልክ ይህን መልክት ያስረከበ መልክተኛ ነጋድራስ ምላሹን እኔ እልካለሁ ብለዋል ብሎኝ እስከአሁን ምላሹን ስጠብቅ ከሁሉም ነገር ሳልደርስ መቅረቱን ለክቡር ራስ ቢትወደድ ማስታወቄ ነው ። ደግሞ ካሁን

ቀደም በእርስዎ እጅ በ፲፭ ቀን ሐምሌ ወደ ጃንሆይ ለላኩት ቃል ቁርጥ ያለው ምላሽ እንዲያስታውቁኝ እለምናለሁ ። የነገር ብዛትና ዋቤ አልባ እንደሆነ ዶክተር እስቴይንኩለርና እኔ ነገሩን ገልጠን አስረግጠን ለምንስትሮችና ለመኳንንት መላልሰን አስታውቀናል ። እንዴት ይሆናል ብልሃቱን ገልፀው ማየት ያስፈልጋል የሚሉ ካሉ. . . . በፊት ተመላልሶ የተነገረውን ነገር ከጃንሆይ ሙሉ ችሎት ላይ ብቻ ለማበርከት የተዘጋጀሁ ነኝ ።

በብዙ ማክበር ታዛዥዎ

ዶክተር ዚንትግራፍ

ቆንሲልና የመንግሥት አማካሪ

ማንም ሰው እንደሚገባውና ራሱም ዚንትግራፍ “. . . . በጃንሆይ ችሎት ላይ ብቻ . . . .” ሲል ሐኪሞችና በሳይንስ መንገድ ተከራካሪ ሰው በሌለበት ማበጣበጫዬን ልናገር ማለቱ ነው ። አሁንም ቢሆን ብጥብጡ ቀላል ነው ለማለት አይቻልም ። በተለይ የሶስቱ መንግሥታት ጋዜጦች በፈረንሳዊኛ ፤ በኢጣሊያንኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ምኒልክን ሊያክሙ የሔዱት ጀርመኖች ምኒልክን ሊገሉ ነው እያሉ ይጽፉ ጀመር ። የጀርመን ጋዜጦችም የጀርመን መንግሥት ተቃዋሚ የሆኑ የአንዳንድ መንግሥታት ዜጎች ከቤተ መንግሥቱ ሰዎች ጋር በመተባበር የጀርመኖችን ስም ለማስጠፋት መርዝ አብልተዋቸው ነው እያሉ ይመልሱ ጀመር ።

የዘመኑ ሶስቱ ኃያላን መንግሥታት በጀርመን ላይ የሚያሳዩት ተቃውሞ በእነሱ እኳያ ሲታይ ትክክለኛ ነው ። የአሁኑን ንጉሠ ነገሥት ምኒልክን ጀርመኖች እስከ መኝታ ቤታቸው ድረስ ገብተው ይዘዋል ። ምናልባት ንጉሠ ነገሥቱ ምኒልክ ቢሞቱ አልጋ ወራሻቸው ኢያሱም በጀርመን ሞግዚት ተይዘዋል ። በዚህ ምክንያት ከምኒልክ ዘንድ መግቢያ ቀዳዳ ያጡት መንግሥታት ለምኒልክ ተከራካሪ መስለው በየጋዜጦቻቸው ጀርመንን ይወቅሱ ጀመር ። መውቀስ ብቻ ሳይሆንም በእቴጌ ጣይቱና በተከታዮቻቸው አማካይነት ወደ ቤተ መንግሥቱ ለመግባት ጥረት ያደርጋሉ ። ይህን የሌሎቹን መንግሥታት ጥረት ያወቁት ጀርመኖች ደግሞ የጀርመን ተቃዋሚ የሚሏቸው እቴጌ ጣይቱና ደጋፊዎቻቸው ከቤተ መንግሥት እንዲወጡ በርትተው በመርዝ ሰበብ ይወተውታሉ ።

ከጀርመን የመጡት ሐኪሞች እንደ አውቃለሁ ባይ ጠንቋይ መርዝ ያበሏቸው በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ ከግቢው ይውጡና ይታሠሩ ይሉ ጀመር ። ይህንኑ ጭብጥ በማጠናከር በኢትዮ

ጵያ የጀርመን መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ስለ እቴጌ ጣይቱ ይዞታ ለምኒልክ ደብዳቤ ፃፉ ። የጀርመን ሚኒስትሩ የፃፉት ተራ የወጥቤት ጉዳይ ስለነበረ እቴጌ ጣይቱ ለዚህ ተራ ደብዳቤ መልስ ለመስጠት ንቀው አዛዣቸው መልስ እንዲሰጡ አደረጉ ። የጣይቱ አዛዥና ፀሐፊ የነበሩት አቶ ወልደ መስቀል ከዚህ የሚከተለውን ደብዳቤ ጽፈው ላኩ ።

ይድረስ ለክቡር ሙሴ ሻለር ።
የጀርመን መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ።
ሰላምና ጤና ለእርስዎ ይሁን ።

እኔ በእቴጌ ቤት ሁሉ በውጭም ፣ በግቢውም ሙሉ ሥልጣን የተቀበልሁ ፀሐፊ ነኝ ። እርስዎ ስለፃፉት ወረቀት ከዚህ ቀጥሎ የተ ፃፈውን ቃል ሥራዬ ነውና በፍቅርና በማክበር ልጽፍልዎ እሰብሁ ።

ወደ ጃንሆይ ከላኩት ወረቀትዎ ላይ እቴጌ በብዙ ጥንቃቄና ባለ መድከም የጃንሆይ ጤና እንዲጠብቁ እናውቃለን ። ነገር ግን የታላቅ ቤት ሥራ ስለሆነ እቴጌ ከንጭ ቤት ፣ ከወጥ ቤት ፣ ከማድ ቤትና ከጠላ ቤት ፣ ከጃንሆይም ዘንድ በመሆን ፣ በዚሁ ሁሉ ላይ አይንም ዙሮ ለመጠበቅ እንዴት ይችላል ያሉትን ፣ እኔም ስለዚህ በማክበር አስታው ቅዎታለሁ ። አይነተኛው ሹም አዛዥ ወልደጻዲቅ ሁሉን በበላይ ያዛሉ። በዚህም በተቆጠረው ቤት ሁሉ የወንድም የሴትም ሹማምንት አለ በት ። እነሱንም የሚረዳ በየቤቱ አምሳም ፣ ስልሳም አገልጋዮች አሉ ።

ደግሞ ከአዛዥ ወልደ ጻዲቅ በታች ለንጉሡ ብቻ አሰናድቶ የሚያቀርብ አዛዥ ተክሉ ነው ። ካዛዥ ተክሉ በታች ሰዲቃና መሶብ የሚያቀርብ አቶ ደስታ የሚባል አለ ። ግብር የሚገባበትም በደረሰ ጊዜ የእልፍኝ አስከልካዩ አቶ ወልደ ገብርኤል እንኚህን ሹማምንቶች ግብር አቅርቡ ይላቸዋል ። ሁሉም በሥራቸው አሰናድተው ያቀርባሉ። አሳላፊዎችም አሳላፊ አብተሚካኤል ፣ አሳላፊ ገብረየስ ተሰናድተው ይቀርባሉ ።

ጠጅ አሳላፊዎቹም እንደዚሁ የተመረጡ አሉ ። ከዚህ በኋላ ጃንሆይና እቴጌ እግብር መግቢያው ይቀመጣሉ ።

ራሶችም ፣ ደጃዝማቾችም ፣ ሌላውም መኳንንት ሁሉ ሴት ወይዘ ሮችም በየማዕረጋቸው ይቀርባሉ ። እነዚህም ሹማምንቶች ሁሉ በየ ሥራቸው ያሰናዱትን ምግብ እየቀመሱ ያቀርባሉ ። እቴጌ ሥራቸው ተቀምጦ ማብላት ነው እንጂ እነጭ ቤት ፣ እወጥ ቤት ፣ እጠጅ ቤትና እጠላ ቤት ሄደው ለማየት ሥራቸው አይደለም ።

በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያም እንደመኳንንቱ ሁሉ ገብተው ከመብላት በቀር ያለ ሥራቸው ከሰው ሹመት አይደርሱም። አዛዥ ወልደጻዲቅም ከበጅሮንድ ሙሉጌታ ሹመት ሄደው አንድ ሙሉ ግምጃ፣ አንድ ሙሉ ሻሽ ስጡ ለማለት አይችሉም ።

በጅሮንድ ሙሉጌታም፣ አዛዥ ወልደጻዲቅ ሹመት ገብተው ይህን ይህን አምጡ፣ ይህን አድርጉ ለማለት አይችሉም ።

ያገራችን ሥርዓት እንደዚህ ነውና የሁሉም ሥራቸው ልዩ ነው ። ይህም ነገር ያልተረዳዎ እንደሆነ ለማየት ቢፈቅዱ እንደዚሁ እንደ ፃፍኩት ሁሉ፣ ሁሉንም በየሥራቸው ለማሳየት የተዘጋጀሁ ነኝ ።

ከዚህ ቀደም የእንግሊዙ ቆንስል ሙሴ ሐሪንቶን የጃንሆይን ቤት አንድ ቀን፤ የእቴጌን ቤት አንድ ቀን እየገቡ አይተው ነበር ።

ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

በዚሁ ቀን የኢትዮጵያ መኳንንት ስብሰባ አድርገው በበጅሮንድ ሙሉጌታና በአዛዥ መታፈሪያ ክስ ላይ ለመነጋገር ወሰኑ ። ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፩ ዓ.ም. የተሰበሰቡት እቴጌ ጣይቱ፣ ወይዘሮ ዘውዲቱ ምኒልክ፣ ራስ ተሰማ፣ ራስ ጉግሣ፣ የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፣ የፍርድ ሚኒስትሩ አፈንጉሥ እስጢፋኖስ፣ የጽሕፈት ሚኒስትሩ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፣ ሊቀመኳስ ብሩ፣ ሊጋባ ወልደ ገብርኤል፣ አዛዥ አየለ፣ ቀኛዝማች ከፈለው፣ ልጅ መኰንን ዋልቴ፣ ልጅ ኃይለሥላሴና ሌሎችም ነበሩ ። እነኚህም ሰዎች ስብሰባ አድርገው ከተወያዩ በኋላ የሚከተለውን መግለጫ አወጡ ።

"ከጀርመን መንግሥት የመጣው ሐኪም ዶክተር እስቴንክለር ጃንሆይን ማስታመም ከጀመረ በኋላ ጃንሆይ ከሚበሉትና ከሚጠጡት ላይ መርዝ ተገኘበት ብሎ ተናገረ ። መኳንንቱም ሠራዊቱም በዚህ ነገር ተጨነቁ ። ዳግመኛ ሁለተኛ በዚህ ምክንያት በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ ከጃንሆይ ግቢ እንዳይገቡ ፈጽሞ ካልተከለከሉ ምንም ቢሆን ለማከም አይቻለኝም አለ ። እኛም የሚከለከሉበትን ምክንያት መጥተህ አስታውቀን ብለን ብንልክበት ሳይመጣ ቀረ ። እኛ ግን እግዚአብሔር በሰጠን እውቀት ብንመረምር ከማገልገላቸው በቀር ክፉ ነገር ስላጣንባቸው ደህንነታቸውን በዚህ ወረቀት እንመሰክራለን ።

ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፩ ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

በአጤ ምኒልክ መታመም ምክንያት ልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽ ሲሆኑ ለኢያሱ ሞግዚትና ለኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን



ራስ ቢትወደድ ተሰማ ።

ተብለው የተሾሙት ቢትወደድ ተሰማ ከዚህ በጅሮንድ ሙሉጌታንና አዛዥ መታፈሪያን ነፃ ከሚያደርገው ውሳኔ በኋላ የሚከተለውን ደብ ዳቤ ፃፉ ። ጉዳዩም ከግል ደረጃ ወደ መንግሥት ደረጃ ተላለፈ ፤

ይድረስ ወደ ክቡር የጀርመን መንግሥት መልእክተኛ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር ።

የተላከ ከራስ ቢትወደድ ተሰማ ።
የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ።

ሰላም ለርስዎ ይሁን ።

ከዚህ ቀጥሎ በፍቅርና በማክበር እስታውቅዎታለሁ ።

ትናንትናም ለነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በቃል ልኬብዎታለሁ ።

ከጃንሆይ ከተላከው ወረቀት ያልተካከለ የሚያዋርድ ቃል አለ በት ያሉትን በውል ባይተረጐም ይሆናል እንጂ የተካከለ መሆኑን አስረዳዎታለሁ ።

ዶክተር ዚንትግራፍ እኛን ሁሉ ሰብስበው በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ ተይዘው ካልተመረመሩ አይሆንም ብለው ነገሩን ። ይህ እንኳን ለርሳቸው ሥራቸው አልነበረም ። ለዚሁ ጃንሆይ ተሰብስ ባችሁ ይመርመር አሉ ። ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስም ወደ ዶክተር ዚንትግራፍ ለምርምሩ በ፰ ቀን ሐምሌ ማክሰኞ ይምጡ ብሎ ጻፈላ ቸው ። ኋላም ጃንሆይ ማኅተም አንስተው ልሰናበት ያልከበት ፣ የኔም ሰዎች አገር ጥለው የሚሄዱበት ካልተገለፀ እንዴት ይሆናል ፤ አሁን ም አንተ እንዳልከው ለምርምሩ ፰ ቀን ሐምሌ ማክሰኞ እንድትመጣ የሚል ቃል ቢላክባቸው ዳኛውስ ማነው ፣ ሥፍራውስ ወዴት ነው ብለው ምላሽ ላኩ ። ዳኛው ማነው ማለት መንግሥታችንን ማዋረድ ይመስላል ።

እንኳን በኛ ፈቃድ ያደሩት ዶክተር ዚንትግራፍ ፤ የየነገሥታቱም ቆንሲል ቢሆኑ የጃንሆይ ማኅተም ሲሄድባቸው መጥተው ይጠይቃሉ እንጂ የሚያስቀር ምክንያት ነገር ካላገኛቸው አይቀሩም ።

ፍረድ ሳይሉ እነዚህ ሰዎች ይሻሩ ፤ ይታሰሩ ማለት በኛ አገር ያልተገባ ነው ። ሁለተኛም እነዚህ ሰዎች ወደ ዳር አገር ሄደው ይሾሙ እንጂ ከዚህ ተቀምጠው አብሮ ለመኖር አይሆንም ማለት ማዘዝ ነው።

ዶክተር ዚንትግራፍም በላኩት ወረቀት ላይ ለመንግሥት የሚበ ጀውን እየተመካከርሁ ለማሠራት ነበር ይላል ። በጅሮንድ ሙሉጌታ

ጃንሆይን የሚጠብቃቸውን ፣ የሚደግፋቸውን ፣ የሚያምኑትን አሽከራ ቸውን ካገሩ ሌላ ከሳሽ ሳይነሳበት አገር ጥሎ ይሂድ ብሎ ማዘዝ ለመንግሥት የሚጠቅምና የሚበጅ መሆኑ ነውን ። እስዎ ባለሙሉ ሥልጣን ነዎ ። እስቲ ይህን ነገር ፍርዱን ይመልከቱት ። ይህ ሁሉ አሁን የፃፍሁልዎ የሚገባ ይሆን ።

ደግሞም ባንድ ሰውና በ፪ ሰው ባሕሪ ያለመስማማት የጀርመንና የኢትዮጵያን መንግሥት ወዳጅነት ያሰናክለዋል ብለን እንጠረጥርም ።

ሐምሌ ፳፱ ቀን ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ።

ነገሩን እንዲከር የሚያደርጉት ጀርመኖች ከኢትዮጵያ ሰዎች የበለጠ ለምኒልክ አሳቢ በመምሰልና የጋዜጦችን አፍ ለመዝጋት ጉዳዩን አዲስ አበባ ላሉ የመንግሥታት እንደራሴዎች አስታወቁ ። ራስ ቢትወደድ ተሰማም የጀርመኖችን ጉዳይ ለማስተባበል የሚከተለ ውን ደብዳቤ ፃፉ ።

ይድረስ ከክቡር ሙሴ ሻርል ብሪስ የፈረንሣይ ሚኒስቴር ባለ ሙሉ ሥልጣን ።

ከሙሴ እስክር ጃንስኪ የመስኰብ መንግሥት ጉዳል ፈጻሚ ።

ከክቡር ኮንት ኮሊ ደፊሊዚአኖ የኢጣሊያ መንግሥት ሚኒስቴር ባለሙሉ ሥልጣን ።

ከክቡር ሎርድ ሐርቤ የእንግሊዝ ጉዳይ ፈጻሚ ።

የተላከ ከራስ ቢትወደድ ተሰማ
የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን

ሰላም ለርስዎ ይሁን ።

ለከበሩ ወዳጃችን ለጀርመን ንጉሠ ነገሥት፣ ሐኪም ይስደዱልን ብለን ብንልክ በቸርነታቸው ሰደዱልን ። ሐኪሙም እኛ ዘንድ በሚ ያዝያ ገብተው እስከ ግንቦት ፲፰ ቀን ድረስ ለጃንሆይ መድኃኒት ሲያደርጉ ቆዩ ። በግንቦት ፲፰ ቀን ግን ሐኪሙ መርዝ አገኘሁ አሉኝ ብለው ዶክተር ዚንትግራፍ ለጃንሆይ ነገሩ ። እኛም በምን ምክንያት መርዝ ተገኝቶ ይሆን ብለን ነገሩን አቅለን ተውነው ።

ደግሞ በ፫ኛው ቀን ሐኪሙ መጥተው ለእቴጌ ነገሩ ። እቴጌም በንጉሡ መርዝ ማን ያደርግባቸዋል ፣ ይህስ አይጠረጠርም ብለው መለሱላቸው ። አስተርጓሚውም ይህንንስ አይበሉ ፣ አሽከር ክፉ ነው ፣ በገንዘብም በምንም ይገዛል አለ ። እቴጌም በአጤ ምኒልክ ላይ እልፍ

ወርቅ ቢሰጡት ክፉ ነገር የሚያደርግባቸው የለም አሉት ። ሐኪሙም ለእንግዲህ ከወኅቤት ዕቃም ከምንም ከምን እድፍ እንዳይገባ መጠን ቀቅ ነው ብለው እንደቀድሞአቸው መድኃኒቱን እያደረጉ እስከ ሰኔ ፲፪ ቀን ድረስ ቆዩ ። ከዚህም ወዲህ ዳግመኛ እንደዚህ ያለ አገኘሁ ፣ የሰዎቹም ስም እንገሌ ናቸው ብለው አልተናገሩም ።

በሐምሌ በ፬ ቀን ግን ዶክተር ዚንትግራፍ ሐኪሙን ይዘው መጥተው መኳንንቱን ሁሉ ሰብስቡልኝ ብለው ሰብስበው በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ እጃቸውን ተይዘው ይመርመሩ ። እና ንተም ብትተዉት ለአለሙ ሁሉ እስታውቃለሁ ብለው በታላቅ ቃል አሰምተው ተናገሩ ።

ደግሞ ዶክተር ዚንትግራፍ ከጃንሆይ ልገናኝ ብለው መጥተው እንደዚሁ እጃቸው ተይዞ ይመርመሩ ሲሉ ፣ ጃንሆይም እነዚህ ሰዎች ምንድነው ኃጢአታቸው ፣ እነሱ ሹመታቸው ሌላ ፣ እኔ ከምበላው ፣ ከምጠጣው አይደርሱ ፣ ምን ባጠፉ እጃቸው ይያዛል አሉ ። ዶክተር ዚንትግራፍም አይሆንም እነሱ ተይዘው ይመርመሩ ። አለዚያ ሐኪሙ አይገቡም አሉ ። እኛም የታመኑትን ፣ የተሾሙትን አሽከሮቻቸውን ይውጡ ማለት ምንድነው ይሆን ብለን ገረመን ። ኋላም እነዚህ ሰዎች ተሽረው ከግቢው ካልወጡ እኔን አሰናብቱኝ ብለው ሁለት ወረቀት ላኩ ። እቴጌም እነዚህ ሰዎች በምን በምን አይደርሱ ፣ የሚበላው ሁሉ የሚሰናዳ ከኔ ቤት ነው ብለው በወረቀት ጽፈው ሰጡ ።

ጃንሆይም እነሱ በምንም በምን ቢሆን አይጠረጠሩም ብለው መሰከሩላቸው ። ከዚሁም ለምርምሩም እነሱው ባሉት ቃል አባታችን አቡነ ማቴዎስ ፣ የኛም መኳንንቶች ፣ ወንበሮችም ፣ በከተማም ያሉት ሐኪሞች ሁሉ ተሰብስበው በሐምሌ በ፳ ቀን ማክሰኞ ነገሩ ይመር መር አልን ። ይህንንም ቃል ለጀርመን ሚኒስቴር ለሙሴ ሻርልና ለዶ ክተር ዚንትግራፍ በጃንሆይ ማኅተም ተላከባቸው ። በዚሁ በቀጠሮው ቀን አቡነ ማቴዎስም ፣ መኳንንቱም ፣ ሐኪሞቹም ተሰብስበው ብዙ ሰዓት ጠብቀው ዶክተር ዚንትግራፍና ዶክተር ሲተይንከለር ሳይ መጡ ቀሩ ። የተሰበሰበውም ሰው ተበተነ ።

ዶክተር ዚንትግራፍ ግን ያልመጡበትን ያለሥራቸው ገብተው እኛንም ሰዎቻችንንም አወኩን ። ሐኪሙም አልገባም ማለት መርዝ አገኘሁ ይሉ ነበር ። የጃንሆይ ሕመማቸው ተለውጦ ፣ ሰውነታቸው ተበሳጭቶ ቢሆን ምን ሆኑብን ብለን ሐኪሙን የምንጠይቅ እኛ ነበርን ።

የቀድሞ ሕመማቸው ሳይለወጥ መርዝ ተገኝቷልና እነዚህ ሰዎች ይውጡ ማለት ይህ ብቻ ነው የጨነቀን ። ባልደረባ የሆነ ሰው ቢያስ

ቀይም ሌላ ባልደረባ ይስጡኝ ማለት ይገባል ። እነሱን አስቀይመዋቸው ፣ በድለዋቸው እንደሆነ እንዲህ አደረጉን ፣ ይህን በደሉን ፣ ይቀጡልን ባሉ ይሻል ነበር ።

ሁላችሁም የመንግሥት ሰዎች ናችሁ ። ሐኪምም በሁሉ መንግሥት አለ ። በጃንሆይ ላይ ያልተደረገውን ነገር የሚያምኗቸውን አሽከሮቻቸውን ከፊትዎ ይውጡና ወደ ሌላ አገር ይሂዱ ማለት ይገባ ይሆን ።

አሁንም እነሱ ስለዚህ ነገር ለእናንተ ማስታወቃቸውን ለእኛም አስታውቀውናልና በኛም በኩል የሆነውን ልንጽፍላችሁ ወደድን ።

ደግሞም ይህንን ሁሉ ቃል መፃፋችን የጀርመን ንጉሥ ነገሥት ወዳጃችን ፣ እነዚህን ሰዎች የሰደዱልን ስለፍቅር ነውና በዚህ ነገር እንዳይቀየሙብን ስለማለት ነው ። ዳሩ ግን በእንደዚህ ባለው በጥቂት ምክንያት የጀርመንንና የኢትዮጵያን መንግሥት ወዳጅነትና ፍቅር ያሰናክለዋል ተብሎ አይጠረጠርም ። አስቀድሞም ከመሰናበት በፊት ዶክተር ዚንትግራፍ መንግሥት የሰጣቸውን ቤት ጥለውት ሄዱ ።

የጀርመን ንጉሥ ነገሥት ስለ ፍቅር ብለው ያዋሱን ሰዎች የናንተን ሰዎች ካላስወጣን እኛ አንኖርም ብለው ቢሄዱ ፣ በዚህ ንጉሥ ነገሥቱ እንዳይቀየሙብን ተስፋ አለን ። ስለዚህ ከኛ ጥፋት እንደሌለብን እናንተ እንድታውቁልን ብለን ነው ። እነዶክተር ዚንትግራፍም እነዚህ ሰዎች ከግቢ ካልወጡ አይሆንልም ብለው የፃፉት ወረቀት አለ ።

ሐምሌ ፴ ቀን ፲፱፻፩ ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ ።

ከዚህ በኋላ በማግስቱ ነሐሴ 1 ቀን 1901 ዓ.ም. የምኒልክ ዋና ሐኪም ኢትዮጵያዊው ዶክተር ወርቅነህ ናቸው ተብሎ በይፋ ተነገረ ።ሐኪም ወርቅነህም ምኒልክ ፣ የሚመገቡት እንቁላል ፣ ወተትና አትክልት ብቻ እንዲሆን አዘዙ ። ጣይቱ ግን“ . . . . አንተ እንደምትለው እንደ ፈረንጅ ሳይሆን እንደ እኛው ይበላሉ . . . . ”አሏቸው ። በማግሥቱ ወርቅነህ ከምኒልክ ዘንድ ሲገቡ ደም ብዛታቸው ግፊቱ ከፍ ብሎ አገኙት ። ምን እንደበሉ ቢጠይቁ በርበሬ የበዛበት ወጥና ጠንካራ ጠጅ መጠጣታቸውን ነገሩዋቸው ። አዘኑ ። መቆጣትም ስለማይችሉ እንደገና ስለምግቡ ጉዳይ ምክር ሰጥተው ሄዱ ። በማግስቱ ደግሞ እንደገና በመታመማቸው ሐኪም ወርቅነህ በለሊት ተጠርተው ሄዱ ። ግን ከምኒልክ ዘንድ እንዳይገቡ ቆዩ ተብለው እኩለ ቀን ድረስ ሲጠብቁ ቆዩ ። ከተሰያት በኋላ ከምኒልክ ዘንድ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ገቡ ። ምኒልክ በጀሮ ግንዳቸው ላይ ፊጠና ሰ

ፍጭ ታስሮላቸው አዩ ። ፌጦና ሰናፍጭ ለምን እንደተደረገላቸው ቢጠይቁ እቴጌ ጣይቱ "....ለግርፋት በሽታ ጥሩ ስለሆነ ነው" አሏቸው ። ዶክተር ወርቅነህም ከቤተ መንግሥቱ ዳግማዊ ምኒልክን ሲጠብቁ አደሩ ። በነጋታው የሐኪሞች ትእዛዝ የማይከበርበት ቦታ ስለሆነ ምኒልክ ይሞታሉ ፤ አይተርፉም ብለው ለራስ ተሰማ ነገሩ ።

ለአጤ ምኒልክ ስለሚደረገው እንክብካቤ ፤ ራስ ቢትወደድ ተሰማ በሚከተለው ደብዳቤ አዲስ አበባ ላሉ የውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎች አሳወቁ ።

ይድረስ ከክቡር ሐፍማን ፊሲን የአታዚኒ ምንሲቴር የአሜሪካው ።

ለክቡር ሙሴ ሻርል ብሪስ የፈረንሣይ ምንስቴር ባለሙሉ ሥልጣን ።

ለክቡር ሙሴ አስከር ጃንስኪ የመስኮብ መንግሥት ጉዳይ ፈፃሚ ።

ለክቡር ሎርድ ሐርቤ የእንግሊዝ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ።

ለክቡር ኮንት ኮሊ ዲፊሊዚአኖ የኢጣሊያ መንግሥት ምንስቴር ባለሙሉ ሥልጣን ።

ሰላም ለርስዎ ይሁን ።

ጃንሆይን ሕመም ከጀመረበት ቀን አንስቶ እስከዚህ ፣ በበጅሮንድ ሙሉጌታና በአዛዥ መታፈሪያ ውስጥ ሆነው የእልፍኝ አሽከሮች ይጠብቅዋቸዋል ። በዚሁ ላይ ከፍ ባለው በእቴጌ ጥንቃቄ ጃንሆይ ተጠብቀዋል ። የጃንሆይም ምግብና መጠጥ እቴጌ ቀደምት እየሆኑ የሚያዘጋጁ የእቴጌ ሰዎች ናቸው ። የከበሩም ንጉሠ ነገሥት በሚመገቡበት ጊዜ እቴጌም ከዚያው ናቸው ።

እንግዲህ የጃንሆይ ሕይወት በዚህ አገር ለማድረግ በሚቻለው በሚሻል ጥንቃቄ ተከቦ ይኖራል ። በዚሁም በተያዘው ጥንቃቄ ለዘለቄታው ይጠቢቃሉ ። የመድኃኒቱም የአደራረግ ትእዛዝ ሁሉ ዛሬም እንደቀድሞው ሆኖ ተፈጽሟል ።

ከዚህ ቀደም ያስታምሟቸው የነበሩ ብዙ ልዩ ልዩ ሐኪሞች መልካም ነው ብለው የፈረዱበትን ነገር አሁን በመጨረሻ የመጣው መጥፎ ሆኖ በማግኘቱና በማከፋቱ ቤተ መንግሥቱ የጥበብ እውቀት የለውምና በነገሩ ሊከራከርበት አይቻለውም ። መጀመሪያ ነገር የበሽተኛውን ሽንት ሲቀዳ ያደራረጉን ሥርዓት በጥበብ ደምብና

ሥርዓት አድርጐ አደላድሎ እሱ ራሱ ሲያረጋግጥ ። ሁለተኛም ቢሆን ግን ፤ ነገር እንዳይሳሳት በረዳት የሚደረገውን ነገር አንድ ባልደረባ ወይም የዚሁኑ ጥበብ ሥራ የተማረ አዋቂ ጨምሮ አደላ ድሎ እራሱ ሳያረጋግጥ ። ቢሆንም ግን የዚህ የታላቅ ክስ ከሳሽ መነሳቱ ለቤተመንግሥቱ ልዩ ነገር ሆኖ ታየው ።

ነሐሴ ፪ ቀን ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ ።

ነገሩ እየከረረ በመሄዱና ከጀርመንና ከሌሎች መንግሥታት ዘንድ ሁሉ በመድረሱ እቴጌ ጣይቱ ለ2ኛ ጊዜ አዲስ አበባ ላለው ለጀርመን ሚኒስቴር የከረረ ደብዳቤ ፃፉ ።

ይድረስ ከሙሴ ሻለር የጀርመን መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር

ሰላም ላንተ ይሁን ።

አንተ ሁሉን የምታውቅ የመንግሥት ሰው ነህ ። በናንተ አገር ፍርዱና ዳኝነቱ የረቀቀ መሆኑ የታወቀ ነው ። አሁን ግን እኔ አጥ ብቄ ተጨንቄአለሁና ይህንን የኔን ደብዳቤ በፍቅር በወዳጅነት እንድ ትመለከትልኝ እለምንሃለሁ ።

መዠመሪያ የኛ ንጉሥ አጤ ምኒልክ ወደ ከበሩ ንጉሣችሁ ልከው ዶክተር ዚንትግራፍንና ዶክተር ስቲያን ኪለርን ያመጣቸው ሐኪምም ያስታምመኛል ፤ ያድነኛል ፤ ዶክቶር ዚንትግራፍም የቸገረ ንን ነገር ስንጠይቀው ለመንግሥታችን ይረዳልናል ብለው ነበር ። አሁን ግን ባልሆነ ነገር ተነስተው ሐኪሙም እነዚህ ሹማምንቶች ካልወጡልኝ አልገባም ብሎ ፃፈ ። ዶክተር ዚንትግራፍም ሰውን ሁሉ ሰብስቦ በንጉሡ መርዝ ተደርጐባቸዋልና በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ ተይዘው ይመርመሩ ብሎ ለዓለሙ ሁሉ አካፈ ለው ። ሐኪም ማለት ምሥጢረኛ ነው ። ንጉሡ መርዝ በሉ ብሎ ለሠራዊቱ መናገር መች ይገባ ነበር ። ሠራዊቱም በዚሁ የተነሣ እው ነት የተደረገ መስሎት ከሁለት ተለያየ ።

እሱ ያነደደው እሳት እስካሁን አልበረደም ። ይህንን ሁሉ አድ ርጐ ሲያበቃ የተቀበለውን ቤት እሱ በፈቃዱ ለቆ ሄደ ። እዚያም ከሄደ በኋላ እነዚህ ሰዎች ካልወጡ አሰናብቱኝ ብሎ ፫ ጊዜ ወረ ቀት ፃፈ ። ንጉሡም እሺ መሄድህን ከወደድህ አሰናብቼሃለሁ ሂድ አሉት ። ከዚህ ወዲህ ዳግመኛ በቃልስ ፤ በወረቀትስ ንጉሡ ምነው መድከማቸው ።

ዶክተር ስታይን ኪለርም ፤ የፊተኞቹም ፤ የነገር ብዛት ድንቅ አይደለምና ነገርም ፤ የወረቀትም ጉዳይ አይብዛባቸው ይረፉ ብለው ተናግረዋል ። አሁን ግን በዚህ ነገር አጥብቀው ደከሙ ። የን ጉሡም ድካም ለኔ ጭንቅ ሆነብኝ ። በቃልም ፤ በማኅተምም ቢልኩ ይህ የንጉሥ ቃል አይደለም ብሎ አለማመን ፤ የውጭ አገሩንም ምንስ ቴር ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስን ቢልኩ አለማመን ፤ እኔ በቃሌ እጠ ይቃለሁ ማለት ሆነ ። የታመመ ሰው ነገር ሲበዛበት እንዲደክም የታ ወቀ ነው ። ንጉሡ የመንግሥታቸውም ጉዳይ ቢሆን ፤ ነገር ድንቅ አይደ ለም በማለት ትተዋል ። በሆነ ባልሆነው ነገር ለምን ይደክማሉ ።

አሁንም ይህ የላክነው ነገር ሁሉ የማይሆንልን ከሆነ እኔ ወደ መንግሥትህ እልካለሁና አንተ የምትልክልኝ የሆነ እንደሆነ ልስደድ ልህ ። ባንተ በኩል ለመስደድ የማይሆንልኝ የሆነ እንደሆነ እኔ እን ድልክ የዚህን ምላሽ በወረቀት እንድታስታውቀኝ ይሁን ። ካንተ ሳላ ስፈቅድ ብዬ ነው ።

መርዙስ ተገኘ አልተገኘም ንጉሥን ሆዳቸውን አላቃጠላቸው ፤ ልባቸውን አልፈጃቸው ፤ ደኅና ነበሩ ። አሁንስ መርዝ ሆኖ ያደከማ ቸው የነገሩ አለማለት ነው ።

ነሐሴ ፱ ቀን ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ ።

ራስ ቢትወደድ ተሰማም ለጀርመኑ ሚኒስትር የከረረ ደብዳቤ "ምላሹን ያለትእግስት እጠብቃለሁ" ብለው የሚከተለውን ፃፉለት ።

ይድረስ ለክቡር ሙሴ ሻለር ። የጀርመን መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ምንስቴር ።

የተላከ ከራስ ቢትወደድ ተሰማ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣን።

ሰላም ለርስዎ ይሁን ።

ሐኪም ስቴይንኪለር ማክሰኞ በ፲፩ እግቢ ውስጥ ሟሉ የመር ዙን ነገር ለምንስቴሮች ያስታወቁበትን ወረቀት በነሐሴ በ፲፪ ቀን እረቡ በ፲ ሰዓት ወደኛ እልካለሁ ብለውን ነበር ። ይልኩልናል ወይስ መቅረቱ ነው ። ምላሹን አለትዕግሥት እጠብቃለሁ ።

ነሐሴ ፲፫ ቀን ፲፱፻፩ ዓመት ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ ።

ለመጨረሻ ጊዜም ራስ ቢትወደድ ተሰማ ለውጭ አገር መንግ ሥታት እንደራሴዎች የሚከተለውን ማስተባበያ ፃፉ ።

ይድረስ ለክቡር ሙሴ ሻርል ብሪስ የፈረንሣዊ ምንስቴር ባለ ሙሉ ሥልጣን ።

ለክቡር ኮንትኮሊ ዲፊሊዚአኖ የኢጣሊያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ።

ለክቡር ሎርድ ሐርቤ የእንግሊዝ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ።

ከክቡር ሙሴ እስክር ጃንስኪ የመስኮብ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ።

ከክቡር ሐፍማን ፍሊፕ የኤታዚኒ ምንስቴር ።

የተላከ ከራስ ቢትወደድ ተሰማ ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን ።

ሰላም ለርስዎ ይሁን ።

የሐኪሙን የዶክተር ስቴይንኪለርን ነገር ካሁን ቀደም የሆነ ውን አውቀውታል ። በየቀጠሮው ቀን እንደቀሩ አሁን ደግሞ በነሐሴ በ፲፩ ቀን የሐኪሞች ጉባዔ አድርገን የመርዙን ነገር ሐኪሞች ይመርምሩ ብንል ዶክተር ስቴይንኪለር ከሐኪሞች ጋር አልነጋገር አሉ ። እኔም ራስ ቢቶደድ መንገሻን ፣ ራስ ጉግሣን ፣ ነጋድራስ ኃይለጊዮርጊስን ይዤ ሥራው የሐኪሞች ነው ምነው አለመነጋገርዎ አልኩ ። ሐኪሞቹም ወረቀቱን ስጠንና እንመርምር ቢሏቸው ለየምንስቴራችሁ ሰጥቻ ለሁና ከነሱ ተቀብላችሁ መርምሩ አሏቸው ። ሐኪሞቹም እንዲህስ ከሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት ይህነን ወረቀት ከጀርመን ምንስቴር ተቀብሎ የሰጠን ጊዜ እንመረምራለን አሉ ።

ዶክተር ስቴይንኪለርም ለምንስቴር ሻለር ነግሬ በነሐሴ በ፲፪ ቀን በ፲ ሰዓት ወረቀቱን ይሰዱላችኋል አሉን ። እኛም በቀጠሮው ቀን ብንጠብቅ ወረቀቱ ቀረብን ። ደግሞ በ፲፫ ነሐሴ እስከ ፲፩ ሰዓት ድረስ ጠብቀን ወረቀቱ ቢቀርብን የመርዙን ነገር ለምንስቴሮች ያስታወቁ በትን ይልኩልናል ወይስ መቅረቱ ይሆን ብለን ለምንስቴር ሻርል ብንልክባቸው የዚህን ምላሽ ሐኪሙ የመርዙ ነገር የተመረመረበት ወረ ቀት የሚገኘው በመንግሥቴ መልክተኛ እጅ ብቻ ነው ብለው ፃፉልን ።

ይህን ወረቀት ለማየት የሚገባን እኛ ነበርን ። ዳሩ ግን ይህ ወረ ቀት ወደኛ ባለመምጣቱ ይገርመናል ። ደግሞም ፊት መርዝ አገኘሁ ያሉ ጊዜ እንደ አሮፓ ሥርዓት ዕለቱን ለሐኪሞች ማሳየት ይገባ ነበር ። ዛሬም የዚሁኑ የመርዙን ነገር ሐኪሞች ይመርምሩ ብንል አይሆንም ሲሉ ጊዜ ስለዚህ የመርዙን ነገር ወደርስዎ የፃፉልዎ አለመተካከሉን እንዲያውቁት ብንል ነው ይህን ወረቀት የፃፍኩልዎ ።

ነሐሴ ፲፬ ቀን ፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ ።

የኢትዮጵያ መኳንንቶች ንጉሡ መርዝ በልተዋል የተባለበትን ጉዳይ ሲመረምሩ መርዝ ያበሉ በጅሮንድ ሙሉጌታና አዛዥ መታፈሪያ ናቸው በማለት ወሬውን ለሕዝብ ያዳርሱ ከንቲባ ገብሩ ስለ ሆኑ ተይዘው እንዲመረመሩ ሲታዘዝ ቀደም ብለን እንዳነበብነው ከን ቲባ ገብሩ ሸሽተው ከጀርመን ለጋሲዮን መግባታቸው ታወቀ ። የከ ንቲባ ገብሩን አምልጦ ከጀርመን ለጋሲዮን መግባት ቢትወደድ ተሰማ እንደሰሙ በኢትዮጵያ ለጀርመን መንግሥት ባለሙሉ ሥል ጣን ሚኒስትር የሚከተለውን ደብዳቤ ፃፉ ።


ይድረስ ከሙሴ ሻለር ፡የጀርመን መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር ።

የተላከ ከራስ ቢትወደድ ተሰማ ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን

ሰላም ለርስዎ ይሁን ።

ይህን ቃል ልጽፍልዎ መንግሥት አዞኛል ።ከንቲባ ገብሩ ዜጋ ችን ነው ። ይልቁንም ሾመን ሥራ አስይዘነዋል ። ከመንግሥታችን ሳይሰናበት ሥራውን ትቶ እናንተ በባንዲራ ወስዳችሁት ከናንተ ዘንድ አስቀመጣችሁት ። አለመንግሥት ፈቃድ ያስያዙትን ሥራ ትቶ የኮበ ለለውን ሰው ማስጠጋት ይህ ሥራት አይደለም ። በፍትሐ ነገሥታ ችሁም የተፃፈ ነው ።አሁንም ይስደዱልን ።ለዚህ ነገር ሰዓት አያስፈ ልግምና ምላሹን በቶሎ ያስታውቁኝ ።”

በአዲስ አበባ ያለው የጀርመን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትርም ከንቲባ ገብሩን ለኢትዮጵያ መንግሥት አሳልፌ አልሰጥም አለ ። ከዚህ በኋላ በዳግማዊ አጤ ምኒልክ ስም የመጨረሻው ደብዳቤ ለጀርመን ንጉሥ ተፃፈ ።



ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩ
መ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ...
ይድረስ ከክቡር [illegible]
[illegible] ንጉሠ ነገሥት ...

ሰላምና ጤና ለርሰዎ ይሁን።

የሰበና ንጉሠ ነገሥት በቻርለተም ሐኪሙን ይዘተርሰቲ ይንክለርን ለምክር የሚረዷቸን ይዘቶር ደንተዓፊቸን ሰጸዷፊን፡ በመምጣ ታቸው እንዲም ሠፊሮቲም ጸሰ ገሎን ነበረ። ነገር ግን ሐኪሙም እንዷን መጸኗቲት ሰጸርን ሊያዷቸኛ በቤዙ ሁለትና በቤዙ ቋክም ከረምሁ።

ሊሽከርቲን ሸመምንቶቺን ከቲየመዪሉቴቲን እቲየማምናቾውን እነሱ ከሌውጡ በሰው ጸዘቶር ጸንተኀፊዎ እኒ ሊልዮርም ሊሰናብቶኝ ሊሉ። ሐከሙም እነሱ ካሌውጡም ዲኗቲቲን ሊላደር ነው ሊሉ ገባም ብሎ ሁለነም ጸፏልኝ። እኔም የነኪሁ ሰዎች ነውራቸው ማይገለጥ ማይረት እንጂች ይወጣሉ፡ ሊሌሉ። እነሱ ግን ካሌውጡ ሊንርርም ሊሉኝ። እነዚሁስ ሊይውጡም በዚ ሊጂ በዚ ሊሰናብቱሁ።

ከበር ወዲጂ መንግሥትዎ የወነትና ረፊዷ ወሮኝን ሊምናለሁና ይሀ ነገር የመርምር ሊንዲነሰማው ነሰፋ፡ ሊሌኝ። ይሆነን ሁሉ ያዲረገና ሁከት ነገር ይመጣ የኒዚጋ የዲርመንን ቋንቋ የሚያውቅ ሰው ነው።

ሊሉንም እኒ እንጂሌመረምረው በግንደፊ ወሰደው ሰጂርመን ሊጋስቶን ዴት ሊሰቀምጠውታል።

ሸሚ ነው ዚጋቶም ነው ወዲሬ ሰጸቋሌኝ ባለው የጂርመን መንግሥት ምንስቲር ጸሰም እሌለው።

የግዴም እንጂሌመጣው የጂርመንን መንግሥት መሰቀየም ይሆን በኛሌ በዚ ሊሰበሁ። እሱም ከነሱው ጋራ ይምጣና፡ ከዚያው ከመንግሥትዎ ሊገር ይመርመር። ይሆነን በዚ መፋቀርና መንን ነገሩ ተገሌጦ እንጂነ

ሰጣው እሰጥ፤ቀንለሁ።
የሆነውን ነገር ሁሉ ገልጦ የጣ ያስረዳ ዓን የአደረ ደብ
ዳቤ ነውና ከዚያ ላይ ይገኛል።
ለሰው እጅግ ጥና ለሐዘ ከም ሰላምና ዕረፍት እን
ዲሰጥ እግዚአብሔርን እለምናለሁ።
ነሐሴ ፳፩ ቀን ፲፱፻፩ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ተጻፈ።

ምኒልክ የጠቀሱት የእቴጌ ደብዳቤ የተጻፈው ከዚህ ከአሁኑ የምኒልክ ደብዳቤ በፊት ነው ። ሁሉንም ነገር ያስረዳል የተባለው እቴጌ ጣይቱ ያጻፉት ደብዳቤ ቀጥሎ ያለው ነው ።

ይድረስ፡ከክቡር፡ወዳጄ ቶን፡ከዲፕሎማቲክ፡ዊልጊ ምስ፡የ
ሺር መንግ፡ንጉ ሠ ነገሥት።
የተላከ፡ከእቴጌ፡ጣይቱ፡ብርሃን፡ዘኢትዮጵያ።

ሰላ ምና፡ጤና፡ለርስዎ፡ይሁን፡

ለጃንሆይ፡መንክብርና፡በትሕትና፡ይዘኸኝ፡ደብዳቤ፡ልጅ ፍል
ም፡እንደብሁ፤እልከዉ፡ይዘኸኝ፡የደረሰብኝን፡የጨ ደ ጣ ዝን
ነገር፡ደፍሬ፡ልጅ ፍልም፡የላጅ፡ሆኔብኝ፡ሊተንሠው፡እለተ
ቻለኝም፤። ለሌ፡አጤ፡ምኒልክ፡ጤና፡መንገዳል፡ጊታቸ
ን፡ወዳጄን፡አጣቸው፡ይሆን፡ብዬ፡እጥብቄ፡ተጨንቄአለሁ።
ለሌቶች፡ካባት፡ከናት፡ከልጅ፡ከወንድምም፡የጨዋ፡ነገር፡
ሞኘት፡እንደሆነ፡የታወቀ፡ነው።

ስለዚሁ፡የጀርመን፡መንግሥት፡ሐኪም፡የምስክር ረቂቅ፡
ካለሃት፡ለመ፡ምሩት፡እስከኔ፡ድርስ፡ገኘው፡ነገሥት፡ተፈ
ውለው፡እንደተደረገላቸው፡ሁለቱ፡ለመሄዱ፡የተቃጠሉ፡ም
ሾቲ፡እንዲፈጸምልኝና፡በግርቱ፡እምብቱ፡ለሮወደቸ
ውም፡ሐዝባቸን፡ገኘሠ፡በሐይወት፡እንደቆዩለት፤
ለመፈወስ፡የሮይስፊልግ፡ነገር፡ሳይደረግላቸው፡እንዲደ
ቀር፡ብለን፡፡ የጀርመኑን፡ለመ፡ምሩ፡የምስክር፡ወረቀት፡ካለ
ሃት፡ረዳትነት፡ለመንገን፡ገኘሠም፡በቸርነቱ፡ሐኪሙን

ም፡ምክር፡የሮፈጸንም፡ይለዩ ዩለንያፈሉን፡ይከቶ
ር፡ደንተቀራቸን፡ወምረው፡ለደጁሉን
እነሱም፡በመምጣታቸው፡እኛንም፡ሠራዊታቸንንም፡እጅ
ግ፡ደስ፡አሉን፡፡
ነገሩ፡ግን፡እንደተመቸነው፡ሳይሆንልን፡ቀረ ሆ
እሰመሆኑንም፡ለማለፈደት፡ከዚሁ፡ቀጥሎ፡በሚደ
ፈው፡ታሪ፡እስታውቃለሁ፡፡
ሐኪሙ፡ደክተር፡ስቲይገኪለር፡በሚድ ንዝይ፡ለዪ
ቀን፡ገበ ከዚየም፡እንስቁ፡እስክ፡ግንቦት፡፲፩ ቀን፡
ጌቱ፡ማን፡ እየተመላለሱ፡ ለገኘሥ፡መዳኒቶን፡
ሊሄድሮጉ፡ ለነበተ፡፡ በሳንበት ባለሎቱን፡ግን፡በገኘ
ሠ፡ነገሥት፡ደም የመርዥ፡ፍለጋ እንደሁ፡ይጠንቀቁ
ካለው፡ለኔ፡ነገሩኝ
እኔም፡በጤ ምኒልክ፡መርዝ ማን፡ይደርግባቸዋል
ይሆ፡ነገር፡እዴ፡ጠረጠርም እልሁ፡
ሐኪሙም ከጠግቢት ዐ ቃም፡ ከምንም፡ከምን፡እዲኛ፡
መጠንቀቅ ነው፡አለ፡፡
የከበሩም እርሲ ኛዊ፡ሐመመዎ፡ከ፳መረቃ፡ቀን፡እን
ሰ፡ እስካሁን፡ይረስ፡የዛሬው፡ሰዓት በኔ፡ዘንደ፡የተወ
ዳዴ ለለሆኑብኝ፡ ያለዕዳረት በባሮቱ ተጋቶና፡ጥንቃቄ
ከብሴ፡ፒታዋን፡የሚስተምም ምዎ እኔ ው፡ፌሊ፡ነኝና፡፡
የሐከመን፡ተእዛዝ፡ሁሉ መፈጸሙን፡ተደላድ ዋ ሚስ
ደቱ የዊ ቻለኝ ለለሆነ፡ ደህነነስ፡እጄ፡የዊ ሰናደውም፡


ምግብ፡ሁሉ፡ከኔ፡ቤት፡ነው፡አሉ።
ከዚ ያም፡ወደ ሁ፡ደግመኛ፡መርዝ፡አገኘሁ ብለው፡አሉኝ
ተኘም፡እንግዲህ ፈትኛው፡ መድኃኒቱን ለደጀርጉ፡ቁጭ።
ደጅ ዙቁር፡ደገተግሬ ፍም፡እለቸው፡ደለተን፡ሁሉ፡እ ጅርግኘ፡
ለሳቸው፡የዘመ ቻቸውን፡ወገሬ ደ፡የተለና ደ፡ቢት፡ለዋ
ተኘ፡ እስከሪን፡ እለመኰተን፡ እኑረና ቸው፡ነበር።
በሐምሌ፡በፉቀን፡ዓን፡ደ ዙቁር፡ደገተግሬ ፍ፡ሐኪ ወን፡ደ
ዘው፡ መፕተው፡የኛ መጓገኘቶችና ሠራዊት፡ከተለ በለበበ
ት፡ለይ፡ለገኙሠ፡ከፋ፡ነገር፡ተደርጕለቸዋሌና፡በብርቱ
የታመኑትን፡እንለንዋቻቸውን፡እጃቸውን፡ተይዘው፡ይ
መርመሩ። ይሀ፡ካልሆነ፡ሐኪሙ፡ገብተው፡መድኃኒት እ
ደጀርጉም፡ብለው፡ከለከሉ።
በበነጋውም፡ደዙቁር፡ደገተግሬ ፍ፡ከገኙሠ፡ሌገናኝ፡
ብለው፡ላኩ፡እኛም፡እኺ፡ብለን፡ሬታቸኑም፡ፈለይ፡ሁነን፡
መሬናቸው፡እለቸውም፡እነዚህ፡ለምኝ፡እጃቸው፡ተይዘ
ው፡ይመርመሩ፡እለ፫ የታመኑ፡እኽ ከሮ ቻቸን፡ናቸ
ው፡እይመረመሩም።እጃቸው ተይዘው፡የዘመረመ
ት። ምግዷነው፡ብገለቸው፡ተይዘው፡ካልተ መረመሩ
ሐኪሙ፡አይገቡም፡አሉ።
ደግሞ፡በበነጋው፡ምገለቲናን፡ውሊ፡ሽለርን፡ጠርቶን
እነዚሁ፡ሬቱ፡ሾውቻቸንን፡ይያዙ፡ደለበት፣ምንድነ
ው፡ነገሩ፡ብለን፡ብንጠይቃቸው፡በገኙሠ፡ምግብ፡ውለ
ጥ፡መርዝ፡ተገኘቷል፡በመብልና፡በወጠጥ ውለጥ፡ሁ
ኖ፡ገኙሠን፡ለልትደቸውም፡እንጂ፡ሐኪሙ፡እያገኙት ዋል
ብለው፡ነገሩን።
እኛም፡ለምገለቲና፡ገኙሠ የዘመገቡ፡ሁሉ፡የዘ

ለዋዲ፡ ክኒ፡ ቢቱ፡ ነው፡ ዓኒ፡ ሹሞች፡ ናቸው፡ የሚደለናዲ።
እነዚህ፡ ለሞች፡ ግን፡ ብሊ፡ ቢቱ፡ በመንግም፡ በምን፡ አደጺር
ሉም፡ ብዬ፡ አለታው፡ ቀሁ።
ንጉሠም፡ እነዚህ፡ ለሞች፡ በዚህ፡ ነገር፡ እይመረመሩም፡
ሠራቸው፡ እይደለም፡ ብለው፡ ተናገሩ።
ሐዝቡም፡ አሜ፡ ምኒሌክን፡ እንደነፍሱ፡ እንደደውም፡
ዘነፍሱ፡ አሌቄ እንደ ደረቀ ሥ ፡ንጉሡም፡ በሐዝቡ፡ እ
ክብሮትና፡ አቀቅሮት፡ ወክስብዎን፡ ተደረጉ ዲ፡ አውታ
ለሁና፡ ደዘነን፡ ሠሉ በሐደ ወታቸው ላይ፡ ሊሠራባቸው፡
ወንም፡ የሚቻሌ፡ ለው፡ ዓለም።
ሚኒሊትሩ፡ ግን፡ ምንም፡ ቢሆን፡ እነዚህ፡ ለሞች፡ ካልወጡ፡
አይሆንም፡ ንጉሡን፡ የሚጠብቁ፡ ሐኪሙ፡ ሊላ፡ ለው፡ ወ
ርጠው፡ ደግቡ፡ አለ።
ሐኪሙም፡ እንደዚሁ፡ እነዚህ፡ ለሞች፡ ካልወጡ፡ እልገባ
ም፡ ብለው፡ ቀሩ፡ እኒም፡ በዚህ፡ ነገር፡ እኒን፡ የሚጠብቁ፡ ሊ
ላ፡ ሹም ወቀበሉ፡ ታላቁ፡ ሹክም፡ ሆነባቸው።
በንጃ ለውነቴ፡ ላይ፡ ወርዝ፡ በወደረግ፡ መጠርጠር፡ አይ
ቻሉምና።
ደግሞ፡ የዚ ደኑ፡ ለቱ፡ ወታ፡ ደክቶር፡ ደንትዋራዊ፡ እነዚ
ህን፡ ለሞች፡ ካልተሾሩና፡ ካልወጡ፡ እኒ፡ አልቀበልም፡ ብ
ለው፡ የለጠናቸውን፡ ቢቱ፡ ለቀው፡ ሄዱ።
እዚ ደም፡ ክዩዲ፡ በኋላ፡ እነዚህ፡ ለሞች፡ ካልወጡ፡ እኒን፡
አለየብቶች፡ ብለው፡ ወደንጉሡ፡ ወረቀት፡ ጻፉ።
ንጉሠም፡ እንተም፡ ፊለናበት፡ ደፊክበት ፤ እነዚህ፡ ለሞ
ች፡ የሚወጡበት፡ ብፊሃት፡ ካልተገለጠ፡ እንደ.ቶ፡ ደሆናፊ
እንተው፡ ደወርወሩ፡ ባፊክበት፡ ነገር፡ በጽሑምሊ፡ ወንክብ

ም፡ እንደተወሰነ፡ ብለው፡ ላከባቸው።
በዴጃው፡ እነሱ፡ ባለንብረቶች ገበሬ፡ ቀን፡ እዳታቸን፡ እበነ፡ም
ቲ ም ለ ም፡ በከተማም፡ ደሴት፡ ሰኪ ሞች።
የኛም፡ መኳንንቶች፡ ሁሉ፡ ተሰብስበው፡ ከ[illegible] ክ፡ ፳ ለፃት፡
ሊ መብት፡ ውለው፡ እነሱ፡ ሰጴ መጡ፡ ተነሡ።
የተሰበሰበውም፡ ሰው፡ ሰየሊ ት፡ገባ፡ ደክ ቆር፡ ደ ገት ባሬ
ና ም፡ ዲኛው ስ፡ ምንው፡ ለናሬ ው ስ፡ ወ ዲ ት ነው፡ ብለው፡
ለ ደ መጡ፡ ቀሩ።
ሎ ከ ሙም፡ እነዚህ፡ ሰዎች፡ ፈጅ መው፡ ካሉት ከእኔ ለ፡ እኔ፡
እሌግባም። ደግ ቁም፡ ሰንባ፡ እኔ፡ የም ወ ደ ውን፡ እለተርጀ
ም፡ ደ ኸ፡ ነው፡ የምንባ ውሊ፡ ደሀ ነው ብለው፡ ወረቀት፡ ደ
ሩ። በዚህ፡ ምክን ደት ወ ደ ፈ ተ ም እንዲ ደለ ታ ምስ መ
ሉን፡ እርዲ ታቸውን ለመሬ ለሣ፡ የም ደ መ ቸን፡ የም ደ ሙ
ለእን፡ ሆነ ብን
ደግ ሞ ርተኛ፡ ኬነዚህ፡ ሰዎች፡ ከዚህ፡ ተከሉ ከለው፡ ወደሊ
ላ፡ አገር፡ ካሉ ጊዜ፡ እኔ፡ እሌኖር ም ና፡ እለና ብቶች ብለው፡
በሬ ስ፡ ቢ ሃ ደ ሂ፡ ተሰ ም እጆ፡ ወሬ ቀ ት፡ ላከ።
ገ ቸ ሠ ም፡ እኔ ም፡ በነዚህ፡ ሰለ ዎ ች፡ በጅ መ ተ፡ ነገር፡ ሊ
ላ፡ የተመቀኛቸው፡ ሰው፡ ተነሱ ቁ፡
እስ ወጡ ሉን፡ ደላቸው፡ ሰው፡ ደኖር፡ ደ ሆን፡ እነዚ ያ
ም፡ ከመጡ፡ ጥቂት፡ ቀን፡ ነው፡ እንዲ ን፡ እደ ው ቂ ት፡ ሰው
ን፡ እለ መ ደ ት፡ ከነሱ ም፡ ጋሬ፡ መብ፡ የላቸው፡ ደሀ፡ ነገ
ር፡ ምን፡ ደ ሆ ን፡ ብለን፡ ፃረ መ ን።
ከዚህ፡ በኋላ፡ ደዘ፡ ካሉሆነ፡ እለናብቶች፡ ብለው፡ ሾ ፚ ዚ፡
ወሬቀት፡ ላኩ።
ከዚ ህ ም፡ ወ ደ ደ፡ እላለና ብተ ም፡ እለች፡ ብለው፡ ወደ
መንግሥታቸው፡ የላኩ፡ እንደ ሆነ፡ የከበሩ፡ ገንዘብ፡ ነገ
ሥት፡ ወደ ዲ፡ የተየ መኛሌ፡ ብለው፡ ለደከቆር፡ ደገትባ
ሬኛ፡ ደ መሮ መ ሩ፡ ብትሉ፡ እኔ፡ ብለን፡ ቀን ቁ ር መን፡ ብና ለ
ታው ቃችሁ፡ ለት መ ጡ፡ ቀሬ ቺ ሁ።
እኔ፡ የም ም ና ቸው ን የለደ ባ ኊ ቸው ን፡ የ አ ም ኊ ቸው
ን፡ እ ም ም ን ቆ ጌ ን ከዚ ህ፡ ወ ጥ ተ ው፡ ወ ደ ሌ ላ፡ አገ ር፡ ካ
ሉ ጊ ዜ፡ ከነሱ፡ ጋሬ፡ ለመኖር እደ ሆነ ሏ ኘ ም ብለሁ፡ መለ
ና ለ ተ ዘ ን፡ ከወ ደ ደ ሁ፡ እለ እለና ብ ቺ ያለሁ፡ ብለው፡ የፉ
ሉ ት፡

በጺሁ፡ በኖ ዘገጹ፡ ጻለት፡ ምኒስቴሩ፡ ሙሴ፡ ሾለር፡ ዓን፡
መልካም ሰው፡ ናቸው፡ ሂሩ፡ ዓን፡ ነገሩን፡ መርምሮ ው፡
ለኛ፡ ባለማስታወቃቸው፡ አዘንን።
ስለሆነም፡ የተመኘነውን፡ ፈቃዳችንን፡ ለመፈጸም፡ ዛለ
ው፡ በታላቅ፡ ቸርነትዎ፡ ለጸረታልን፡ በቶ፡ እጅሩ ዓቅቱ፡ እኔ
ው፡ እሩሲ፡ በኛጹም፡ ሌሲ፡ ዓርመሮ፡ ሰውነት ዋን፡ እመ
ለዓናለሁ። ይህንን ሁሉ፡ ነገር፡ መጻፋችን፡ እነሱን
ለመዋረድ፡ ብለን፡ እጸጸለም፡ የገንዘሡ፡ ሌፎና፡ እንዲ
ያ፡ ተየም ብን፡ ብለን፡ ነው፡ እንጂ፡ ጸሩ፡ ዓን፡ እንጹነት፡ የ
መ ያዋህ ደንን፡ ታላቅነት፡ ፍቅሬ፡ ችንን፡ ለመግለጽ ክሌ፡ ደሀ፡
ተገሸ፡ ነገር፡ ምክንያት፡ ይሆናል፡ ተብሎ እለመጠር
ጠሩ፡ ዓሌዋ፡ ነገር፡ ነው።
የገንሠ፡ ፈቃድዎ፡ ቢሆን፡ ከጺሀ በኋላ፡ ሁሉን ም፡ ነገ
ር፡ ለመጠይቃቸው፡ ምላሽ፡ የመ ናገቱ፡ ከቹ፡ ዘገጹ፡
መልክቶች፡ ለመስሂዱ፡ እንመኛለን።
ነገሩ፡ ብዙ፡ ለሆነ፡ ለወሬቀት፡ እይመቀለልም ና።

ፊት፡ ከሙሴ፡ ሮዥ መዋተው፡ የነበሩት፡ ሐኪም፡ ሀገስ፡ ዮሐ ብሬሸት፡
ለኒም፡ መዋኒነት፡ አዋርገውልኝ፡ አዬነውኝ፡ ነበርና፡ ዛሬም፡ ለ
ጥቂት፡ ቀን፡ እንዲመጡልን፡ እንለምናለን።
የከበሩ፡ የንጉሡ፡ ነገሥተም፡ ለቸርነትዎ፡ ይለዬልናል፡ ስጦለት፡
ተሰፋ፡ እናደርጋለን።
ለኢሰው፡ እጅ ወዷና፡ ጤና። ለሕዝብዎም፡ ለጓምና፡ ዕረፍት፡ እ
ንዲሰጥልን፡ እግዚአብሔርን፡ እንለምናለን።
ነሐሴ፡ ፲፩ ቀን፡ ፲፱፻፬ ዓመተ ምሕረት፡ አዲስ አበባ፡ ተጻፈ።



እቴጌ ጣይቱ ይህን ደብዳቤ ከሸኘው ከምኒልክ ደብዳቤ ጋር ለጀርመን ሚኒስትር ለሻለር ሰጥተው ደብዳቤዎቹ ተላኩ ። ሻለር ደብዳቤዎቹን በሚልክበት ጊዜ የእርሱንም አስተያየት ጨምሮ ፅፎ ላከ ። ሌላ ሐኪም ይምጣ ለተባለው ሻለር በጻፈው ደብዳቤ ላይ የራሱን አስተያየት ሲገልፅ “ . . . .የኢትዮጵያ መንግሥት ለዋስትና የሚሆን ብዙ ገንዘብ ካላስቀመጠ ሐኪም እንዳይላክ. . . . ” ብሎ ፃፈ ።

ምኒልክ ግንቦት 10 ቀን 1901 ዓ. ም. ባደረጉት ኑዛዜ የአልጋ ወራሻቸውን ስም ሳይገልጡ "ከልጄ ጋር" ብቻ የሚል ስለነበር ለማን እንደተናዘዙ ግልፅ አልነበረም ። ይህ ነገር የሕዝቡም ጥያቄ ስለነበር እንደገና ለማናዘዝም በክረምቱ ውስጥ እንደበታቸው ስለተያዘ አልተቻለም ነበርና ክረምቱ ሲወጣ በ1902 ዓ. ም. በጥቅምት ወር ሻል ስላላቸው ጥቅምት 20 ቀን ከቤተ መንግሥት ለተሰበሰበው መኳንንት አልጋ ወራሻቸው ልጅ ኢያሱ መሆናቸውን አሳወቁ ።



ልጅ ኢያሱ ።



ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ ንጉሥ ሚካኤልና ልጅ ኢያሱ ።



ኢያሱ ከነፊርማቸው ።

ምንም እንኳን በከባድ ሕመም ቢያዙም ምኒልክ በታላቅ ሥራ ዎችና በፍርድ ላይ በመግባት ውሳኔዎችን ያዳምጡና መስማማት ያለ መስማማታቸውን በምልክት ይገልጡ ነበር ፡፡ ለምሳሌ በምኒልክ መታ መምና በሌላም ምክንያት ሸፍተው የነበሩት የትግራይ ገዥ ደጃች አብርሃ ጦር ተልኮባቸው ድል ሆነው በ፲፱፻፪ ዓ.ም. በህዳር ወር ከ25 መኳንንቶቻቸው ጋር ተይዘው አዲስ አበባ መጡ ፡፡ በልጅ ኢያሱ መሪነት በተቀመጠው ችሎት ላይ ቀርበውም በደጃች አብርሃና በመኳ ንቶቻቸው ላይ የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው ፡፡ ይህን የሞት ፍርድ የሰ ሙት ምኒልክ አፋቸው መናገር ስለማይችል ራሳቸውን በመነቅነቅ የሞት ፍርዱን መቃወማቸውን ገለጡ ፡፡ ይህን የተመለከተው መኳን ንትም የሞት ፍርዱን በእስራት ለውጦ እነደጃች አብርሃ ወደ ዙዋይ ሐይቅ ተላኩ ፡፡ በኋላም ወደ አንኮበር ተዛወሩ ፡፡

እስቴይንኪለርና ዚንትግራፍ በአዲስ አበባ ጀርመን ለጋሲዮን ተቀምጠው የበርሊንን ውሳኔ ይጠባበቁ ጀመር ፡፡ በርሊን ግን እን ኳን እነሱን ፣ ምኒልክን እንኳ አስታውሳ ለጣይቱ ደብዳቤ መልስ አልሰጠችም ፡፡ በዚህ ሁኔታ የተናደደው ዚንትግራፍ በፈቃዱ በመስ ከረም ወር ወደ ካይሮ ሔደ ፡፡ እስቴይንኬለር ለአገልግሎቱ የተሰጠውን ሶስት ሺ ብር ይዞ እድሌን ልሞክር ብሎ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ክሊኒክ ከፈተ ፡፡ በክሊኒኩ በኩል ገበያ ስላጣ የጀርመን ጋዜጦች ወኪል እሆናለሁ ብሎ ወሬ መላክም ጀምሮ ነበር ፡፡ በመሐሉም ሲያ ጭበረብር ተገኝቶ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ተደረገ ፡፡

ታላቁ አጤ ምኒልክም ፲፱፻፮ ዓ.ም. ታህሳስ ፫ ቀን ሞቱ ፡፡

በርትሊ. እንደፃፈው " . . . . ዶክተር ማርቲን (ወርቅነህ) እንዳጫ ወቱኝ ንጉሡ በመጨረሻው ቀን በጠና ታመው ዶክተር ማርቲን ተጠርተው የተቻላቸውን ሁሉ እንዲያደርጉ ተባለ ፡፡ ዶክተር ማር ቲን ሕክምና ሲጀምሩ ባጠገባቸው ያሉ ታላላቅ ሰዎችና ቄሶች ሕክምናውን ስለከለከሉ ንጉሡ ሞቱ ፡፡ እንደተለመደው እነኚህ መሀ ይምናን ሰዎች በፈረንጅ ሕክምና አናምንም እያሉ ሕክምናውን ባይ ከለከሉ ኖሮ ምኒልክ አይሞቱም ነበር ፡፡ . . . . "በማለት ጽፍዋል ፡፡

ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ደግሞ " . . . በዚህ ዓመት አጤ ምኒልክ ሕመም ፀንቶባቸው ነበርና ታህሣሥ 3 ቀን 1906 ዓ. ም. በዕለተ እርብ ሞቱ ፡፡ ወዲያው እንደሞቱ የግቢ ሥራ ቤቶች የል ቅሶ ድምፅ አሰሙ ፡፡ ነገር ግን የልጅ ኢያሱ ባለሟሎች አገር እንዳ ይሸበር ሰግተው በቶሎ ዝም አሰኙዋቸው ፡፡ አቤቶ ኢያሱ በዚያ ዕለት

ያደሩት ፍልውሃ በሚባለው መታጠቢያ ቤታቸው ነበር ። እዚያው እንዳሉ ማለዳ የአባታቸውን የአጤ ምኒልክን መሞት ሲሰሙ ደንግጠው ወደ ቤታቸው ወጥተው ተቀመጡ ። ሆኖም አገር እንዳይሸበር በማለት ሀዘናቸውን በይፋ አላሳዩም ። እንዲያውም አንዳች ሀዘን እለ መኖሩን ለማስመሰልና ለማሳመን ሲሉ በማግሥቱ ቅዳሜ ወደ ጃንሜዳ ወጥተው ከአሽከሮቻቸው ጋር በፈረስ ጉግስ ሲጫወቱ ዋሉ ። ይህም ለአገር ፀጥታ ሲባል አማካሪዎች ያቀረቡላቸው ዘዴ መሆኑ አይጠረጠርም ። ስለዚህ የአጤ ምኒልክ ሞት ሚስጥር ሆኖ ተደበቀ ።

"የአጤ ምኒልክን አስከሬን አሽከሮቻቸው እንደ ነገሥታት ማዕረግ አምሮ በተሠራ ብረት ሣጥን አድርገው በቤተ መንግሥቱ ግቢ ውስጥ ባለችው በስዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በክብር አስቀመጡት ። ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱና ልጃቸው ወይዘሮ ዘውዲቱ በሣጥኑ እጠገብ ሆነው መሪር ልቅሶ ያለቀሱ ነበር ። ከዚህ በኋላ አጤ ምኒልክ በሕይወት አሉ እየተባለና እየተወራ እስከ ሰገሌ ዘመቻ ድረስ ሁለት ዓመት ከአሥር ወር ተደበቁ ። የመንግሥቱ ሥራም በስማቸው ይካሄድ ነበር ።አጤ ምኒልክ የተወለዱት ነሐሴ ፲፪ ቀን ፲፰፻፴፮ ዓ.ም. ስለሆነ በሞቱበት ጊዜ ዕድሜያቸው 69 ዓመት ከአራት ወር ነበር ።

"አቤቶ ኢያሱ ምንም እንኳ የአጤ ምኒልክን መሞት እንዲደበቅ ቢያደርጉ ወሬውን የከተማው ሕዝብ ሰምቶት ነበርና ሁሉም በየቤቱ በድብቅ እያለቀሰ ሐዘን አደረገ ። አሽከሮቻቸውም የጌታቸውን ስም በፀሎት ለማስጠራትና ተዝካር ለማውጣት ፣ ሰዓተ ሌሊትም ለማስፈታት ተነሳስተው ነበር ። ነገር ግን ሞታቸው በመደበቁ ምክንያት ይህን ለማድረግ ችግር ሆነባቸው ። ስለዚህ በስውር ለማስፈታትና ተዝካር ለማውጣት ልዩ ልዩ ዘዴ ይፈጥሩ ጀመር ። እንዲህ ያደረጉት ሰዎች ብዙ ሲሆን አሁን ለምሳሌ ያህል ያንዱን ስም ከዚህ በታች እጠቅሳለሁ ።

"ቀኛዝማች ገብረ ጊዮርጊስ የተባሉት አሽከራቸው በዚያው ጊዜ ወደ እዲስ ዓለም ማርያም ሄደው ወንድሜ ሞቶብኛልና የሰዓተ ለሊት ፍታት ፍቱልኝ ፣ የክርስትና ስሙ ሣህለ ማርያም ነው ብለው ካህናቱን ለመኑ ።ሣህለማርያም የአጤ ምኒልክ የክርስትና ስም ነበርና ካህናቱ ጥያቄያቸውን ሰምተው ከተመካከሩ በኋላ የወንድምዎ ስም ሣህለ ማርያም ከአጤ ምኒልክ የክርስትና ስም ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ እንፈታም ። ልጅ ኢያሱ እንዳይቀጡን እንፈራለን ። አይሆንልንም ብለው መለሱላቸው ።ይኸውም የካህናቱን ውለታ ቢስነትና የቀኛዝማቹን ቁም ነገራምነት የሚያመለክት ነው ። የሆነው ሆኖ ስም

ተጠርቶ ፍታት አልተፈታም እንጂ ቀኛዝማች ገብረ ጊዮርጊስ ለተዝካር ያሰናዱትን ድግስ ለነዳያንና ለካህናት አብልተውታል ። ሀዘናቸውንና ለቅሶአቸውን በዚህ ዓይነት ዘዴ አብርደውታል።....” ብለዋል ።

ምኒልክ ከሞቱ በኋላ ልጃቸው በኋላ ንግሥት የሆኑት ወይዘሮ ዘውዲቱ የገጠሙት ።

ከሸማው አጥር ውስጥ የግምጃ ድንኳን ፣
ግራ ቀኝ መከዳ ምንጣፍ ዙርያውን ።

ዘውድና ሕለተ ወርቅ ካባና ቀሚስ ፣
ባለወርቅ መጣምር እያለ ፈረስ ፣
ይመስለኝ ነበረ ይሄ የማይፈርስ ።

33 ዘመን የገዛንበቱ ፣ የበላንበቱ ፣ የጠጣንበቱ ፣
የትሣስ ባታ ለት ተፈታ ወይ ቤቱ ።

ብትታመም ልጅህ ፣ እጅግ ጨነቀኝ ፣
ስትሞትስ አልሞትም እኔ ብልጥ ነኝ ።

ወልደውኛል እንጂ እኔ አልወለድሁዎ
እንጀቴን ተብትበው ምነው መያዝዎ ።

አሳዳጊዬ አንቱ አላውቅም እናት ፣
ምነዋ ሞግዚቴ እንዲህ ያል ከዳት ፣

ቀድሞ የምናየው የለመድነው ቀርቶ ፣
እንግዳ ሞት አየሁ አባቴ ቤት ገብቶ ።

ምልክቱ ይህ ነው የንጉሥ ሞት ኀዘን ፣
ጣይቱ ስትጨልም ፣ጨረቃ ደም ስትሆን ።

እጅግ አዝኛለሁ አላቅሰኝ አገሬ ።
የሁሉ አባት ሞተ ተጐዳችሁ ዛሬ ።

አሻግሬ ሳየው እንዲያ በሰው ላይ ፣
መከራም እንደሰው ይለመዳል ወይ ።

## በሕዝብ የተገጠመ

አጤ ምኒልክ ሲሞቱ
ምነው አትሔዱ ከፍታቱ ።
እናንት ሰዎች ከፋታችሁ
አለማስቀበራችሁ ። (ዓለም አስቀብራችሁ)

አጤ ምኒልክ ንጉሡ ፣
አባ ማቴዎስ ጳጳሱ ፣
ቃኘው መኰንን ራሱ ፣
ሄዱ ይላሉ ገሠገሡ ። ፣
እምብዛም አሽከር አልቀራቸው ።
ሁሉም ተከተሏቸው ።

የዓለም መልክ ዥንጉርጉር ፣
ነጭ ጥቁር እንደነብር ።
አይቻታለሁ በሰልፍ ፤
በምኒልክ ጊዜ ስታልፍ ።

ምኒልክ መኳዙን የምትጠይቁኝ ፤
ፊትም አላለፈ ኋላም አይገኝ ።

ምኒልክ ተክላችን ወዴት ጠፉ ካገር ፤
ሸዋ አዲስ አበባ ታይቶባቸው ነበር ።

አርባ ስድስት ዓመት የገዛኸው ንጉሥ ፤
እንዳለህም ስጠኝ ከሌለህም ላልቅስ ።

እንዴት ውላችኋል ፣ንጉሥ ወዴት ዋሉ ፤
እስከ ጊዜው ድረስ ገበያ ነበሩ ።


ዘመዶቼ እንሂድ እንግባ አገራችን ፤
ምኒልክ ከሞተ እንጀራ አባታችን ።

ጌታዬ ምኒልክ ጃኖ አለመንሁም ፥ በቅሎ አለመንሁም ፤
አምና ነበር እንጂ ዘንድሮ የለሁም ።


ምኒልክ ይወቁት ዓይኔ ጠፋልዎ ፤
የፈተፈቱበት ነክቶብኝ ጣትዎ ።

አልጫ መረቁ ወጡ ስለቸኝ ፤
ምኒልክ ተነስቶ ሽሮ ባበላኝ ።

ያ ዳኘው ምኒልክ ሁዳዱን አስፍቶ ፤
በየቦታው ተልሞ በየቦታው ተግቶ ፤
ሳይጨርስ አረፈ አዝመራውን ትቶ



በአዲስ አበባ የምኒልክ መቃብር ያለበት በአታ ቤተ ክርስቲያን



የምኒልክ መቃብር ።

# የምኒልክ ሐውልት

በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን የዳግማዊ ምኒልክን ሐውልት ያሠሩት ልጃቸው ንግሥት ዘውዲቱ ናቸው ። ሐውልቱ የተሠራው ጀር መን ነው ። የተሠራውም ከነሐስ ሲሆን የሠራውም ሐርቲል የተባለ ጀርመናዊ ነው ።

ሐውልቱ ተመርቆ ለሕዝብ የተገለጠው ጥቅምት 22 ቀን 1923 ዓ.ም. ነው ። ንግሥት ዘውዲቱ በዘመናቸው የአባታቸውን ሐውልት ቢያሠሩም ለምርቃቱ ሳይደርሱ በሞት ተቀደሙ ። ይህ ሐውልት ተመርቆ የተከፈተው በአልጋወራሽ ተፈሪ መኰንን የንግሥ በዓል ዋዜማ እለት ነው ።

ኢብሊን ዋህ በአመራረቁ ስነ ሥርዓት ላይ ተገኝቶ ስለነበር የአመራረቁን ሁኔታ ሬሞት ፒፐል በሚለው መጽሐፉ ውስጥ ገል ጦታል ።

"....ጢት ሙዚቀኞች በአደባባዩ እየዞሩ ይጫወታሉ ።.... የምኒልክ ሐውልት የሚመረቅበት ቀን ነው ። ስነ ሥርዓቱ የሚጀመ ረው በ10(በኛ 4) ሰዓት እንደሆነ ተነግሮናል ። ስነ ሥርዓቱ ከሚጀመ ርበት ሰዓት ቀደም ብለን አይረን ራቬንስዳል እና እኔ ከበዓሉ ቦታ ሔድን ። የሰው መስቀያ የነበረው ወርካ ዛፍ ከነበረበት ቦታ የምኒ ልክ ሐውልት ቆምዋል ። ሐውልቱ በከፍት አረንጓዴ ሐር ተሸፍን ዋል ። ዙሪያውንም ትንሽ የአትክልት ቦታ አለች ።....

"ጥቂት ሰዎች መጡና ከመግቢያው ጀምረው ምንጣፍ አነጠፉ። ትልቅና መልኩ ቢጫ የሆነ የጠረጴዛ ግንጥላ ዘረጉና የሆቴል ደጃፍ አስመሰሉት ። ግማሹ በአካባቢው ያለውን ቅጠላ ቅጠል ይጠርጋል ። ባንድ በኩል የእጅ መደገፊያ ያለው ወንበር ተደረገ ። በሌላ ወገን ፎቶግራፍና ሲኒማ አንሺዎች ቦታ ለመያዝ ይጋፋሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ ምንጣፉ ዘንድ ለመጠጋት የሚጋፋውን ሕዝብ ፖሊሶች ዱላ ይዘው ይከላከላሉ ።

"አራትና አምስት የሚሆኑ ኤሮፓውያን ተፈቅዶላቸው ምንጣፉ አጠገብ ቆመዋል ። እኛም ከነሱ ጋር ቆምን ። በየአስሩ ደቂቃ ፖሊስ እየመጣ ዞር በሉ ! እልፍ በሉ ይለናል ። የፍቃድ ወረቀታችንን ስናሳ ይም ሰላምታ ሰጥተውን ይሄዳሉ ።

"ግማሽ ማይል በሚሆነው መንገድ የክብር ዘበኛ ሰልፈኛ ቆም ዋል ። ቤልጂጋዊው ኰሎኔል ፈረስ ላይ ተቀምጦ ሰልፉን ያስተካክ



የምኒልክ ሐውልት

ላል ።. . . ጥቂት ቆይቶ ሻለቃ ሲንክለር የሙዚቃ ባንዱን ይዞ መጣ ። ሜጀር ሲንክለር ወደ ኮሎኔል ተጠግቶ መመሪያ ጠየቀ ። ኮሎኔሉ እንግሊዝኛ አያውቅም ። ሜጀሩ ደግሞ ፈረንሳዊኛ አያውቅም ። ስለ ዚህ ኮሎኔሉ መመሪያውን ለመስጠትና የሜጀር ሲንክለር ሙዚቀኛ በየት በየት እንደሚዞር ኮሎኔሉ ብቻውን በፈረሱ እየዞረ ሁኔታውንና ቦታውን አሳየው ። አልተግባቡም ።

“በኋላ በኤረን አስተርጓሚነት ይነጋገሩ ጀመር ። ለካስ ኮሎኔሉ የሚለው የኔ ባንድ ስላለና የሚዞረውም እንዳሳየሁህ ስለሆነ ፣ የእንግ ሊዝ ሙዚቀኛም ይገኛል ተብሎ ስላልተነገረኝ አታስፈልግም ነው ። ሻለቃው (ሜጀር) ደግሞ ልክ አይደለህም ስነ ሥርዓቱ የሚፈፀመው በ10 (በኛ 4) ሰዓት ስለሆነ ሙዚቀኞቹን ይዘህ እንድትገኝ ተብዬ ታዝዤለሁ ይላል ። ኮሎኔሉ ደግሞ ምንም የማውቀው ነገር ስለሌለ በዚህ አደባባይ ላንተ ሙዚቀኞች የሚሆን ቦታ የለም ይለዋል ።. . . በመጨረሻ እርቅ ወርዶ ያ እንግሊዝ ሙዚቀኛ ባንድ ከኮሎኔሉ ወታደሮች ሰልፍ መጨረሻ ከኮረብታው በታች እንዲቆም ተፈቀደ ለት ። በዚህም አፌሰሩ ተናዶ ሙዚቀኞቹን ይዞ ሔደ ።

“ወዲያው ደግሞ በቆመው ሕዝብና በፖሊሶች መሀል ረብሻ ተነሳ ። ደሌጌሽኖች መምጣት ጀመሩና ወታደሮች በብረት ሰላምታ ሲሰጡ ረብሻው በረድ አለ ። የአገር ተወላጅ የሙዚቃ ባንድም ሙዚቃ ያሰማ ጀመር ።. . .

“ዴሌጌሽኖች በዣንጥላ ሥር በተደረገላቸው ወንበር ተቀመጡ ። ብዙ ጭብጨባ ሲጨበጨብ የአልጋወራሹ መምጣት ታወቀ ። አንድ ጥቁር ሰውየ በራሱ ላይ ወንበር ተሸክሞ መጣና በሌሎች ወንበሮች መሀል አስቀመጠው ። ወዲያው ዩኒፎርም የለበሱ ሰዎች መጥተው መቀመጫውን ያስተካክሉ ጀመር ። ጦር የያዙ ወታደሮች ከአለፉ በኋላ አንዲት አውቶሞቢል ደረሰች ። እንደቆመችም በሐር ዣንጥላ ተሸፈነች ። አልጋ ወራሹም ከወንበራቸው ላይ ሔደው ተቀመጡ ።

“ጥቂት ቆይቶ ሻለቃ ሲንክለር ሙዚቀኞቹን ይዞ መጣና በመሀል አደባባይ ቆመው ሙዚቃ ያሰሙ ጀመር ። ከዚህ በኋላ በፕሮግራሙ መሠረት ሁሉ ነገር ይካሄድ ጀመር ። አልጋወራሹ ንግ ግር ካደረጉ በኋላ ገመዱን ስበው ሐውልቱ የተሸፈነበትን አረንጓዴ ውን ሐር ሲገልጡ ሐውልቱ ያብረቀርቅ ጀመር ።

“ግሪካዊው ኮንትራክተርም መሰላል አቅርቦ ሐውልቱ ላይ ወጣና ሐውልቱ የተሸፈነበትን ጨርቅ በሙሉ አነሳው ። ሙዚቀኞች እየተጫወቱ ሐውልቱ ከተመረቀ በኋላ ሁላችንም ሄድን ።. . .” ብሏል ።

ኢጣሊያ የአዲስ አበባ ከተማን እንደያዘች ሐምሌ 4 ቀን 1928 ዓ.ም. የምኒልክ ሐውልት ካለበት ቦታ ወርዶ ተቀብሮ ነበር ። ነፃነት ከተመለሰ በኋላ ሐውልቱ ከተቀበረበት ወጥቶ እንደገና በድሮው ሁኔታ ቆመ ። እንደገናም ሚያዝያ 27 ቀን 1934 ዓ.ም. ተመረቀ ።

ኒውዮርክ ታይምስ ኤንድ ኢትዮጵያን ኒውስ የተባለው ጋዜጣ እ.ኤ.አ. የካቲት 13 ቀን 1937 ዓ.ም. በወጣው እትሙ "....ኢጣ ሊያኖች የምኒልክን ሐውልት ሲያወርዱ የተመለከተ አንድ ትንሽ ልጅ ጮሆ አለቀሰ ። ኢጣሊያኖችም ለምን እንደጮኸና እንዳለቀሰ ልጁን ጠየቁት ። ልጁም የንጉሡን ምስል ስላወረዳችሁ ነው አላቸው። ኢጣሊያኖችም ከሙሶሎኒ ሌላ ንጉስ እንደሌለው ነግረውና ገርፈው አባረሩት ። ልጁም በዚህ ድንጋጤ ከጥቅምት ወር ጀምሮ ታሞ ተኝ ቷል ።..." በማለት ጽፍዋል ።

ከምኒልክ ሐውልት ግርጌ "ከትልቅ ወይም ከትንሽ ቢሆን መወ ለድ ሞያ አይደለም ። ራስን ለታላቅ ታሪክ መውለድ ግን ሞያ ነው" ይላል ። ሐውልቱ ምኒልክ ጐፈና ለብሰው ፣ ጣምራ ጦር ይዘው ጋሻ ሳይዙ የተሠራ ነው ።



ኢጣሊያኖች የምኒልክን ሐውልት ያወረዱት በጭለማ ነበር ።

## በምኒልክ ታሪክ ውስጥ ያሉ አስደናቂ ታሪኮች

— አጤ ቴዎድሮስ በ1848 ዓ ም የሸዋውን ንጉሥ ኃይለመለኮትን ለመውጋት ሸዋን በወረሩ ጊዜ ጅብ ዋሻ ከሚባለው ቦታ ሲደርሱ እንኮበር ከተማን ይጠብቁ የነበሩ የንጉሥ ኃይለመለኮት ሰዎች "....በጌታችን ቦታ ጠላት አይገባበትም ። ጠጁንም፥ ጠላውንም አይጠጣውም ብለው ጥቅምት 16 ቀን እርብ ዕለት አቃጠሉት ። በዚያን ጊዜም የጠጁ ጋን ሲፈነዳ የከልካዩን ቤት የጠጅ ጐርፍ ከሥሩ ነቅሎ ወሰደው ።...."ገ.ሥ

— አጤ ዮሐንስና ምኒልክ በእርቅ ሰላም ከመሠረቱ በኋላ ወሎ ውስጥ በደስታ ቆዩ ።አጤ ዮሐንስም የምኒልክን ንጉሥነት አፀደቁላቸው ። ከዚህ በኋላ መጋቢት 25 ቀን ሁለቱም ተሰነባብተው አጤ ዮሐንስ ወደ ደራ ሄዱ ። አጤ ዮሐንስ ወደ ደራ በሄዱበት ጊዜ አብሮአቸው የሚጓዝ አንድ ለማዳ አንበሳ ነበራቸውና አልሄድም ብሎ ከመንገድ ላይ ተኛ ። አስልጣኙም ቢደበድበው አንበሳው ከተኛበት አልነሳ አለ ። ግራ የገባው አስልጣኝ ይህንን የአንበሳውን አልሄድ ማለት ለአጤ ዮሐንስ ነገረ ። አጤ ዮሐንስም "እሞት ይሆናልና ተዉት" ብለው አዘዙ ። የአጤ ዮሐንስ ሠራዊት ተጉዞ ካለፈ በኋላ አንበሳው ተነስቶ ወደ ንጉሥ ምኒልክ እየሮጠ ሄዶ ተቀላቀለ ። በምኒልክ ጉዞም ጊዜ ከምኒልክ ፊት ፊት እየቀደመ ያለጠባቂ ብቻውን ይጓዝ ነበር ።—ከገ. ሥ

— አጤ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ ወሎ ውስጥ ሐይቅ በተባለው ደሴት ላይ ያለውን ቤተ ክርስቲያን ሲጐበኙ ቀሳውስቱ የባህሩ ውሃ እየገፋ ደሴትዋን ሊውጥብን ስለሆነ ተቸግረናል ብለው አመለከቱ ። አጤ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ ሠራዊታቸውን ተራ አስገብተው አንድ ቀን የአጤ ዮሐንስ ሠራዊት ፣ አንድ ቀን ደግሞ የምኒልክ ሠራዊት ቆፍሮ ገደሉን ንዶ የባህሩን ውሃ ወንዝ ሆኖ እንዲፈስ አደረጉት።— ከገ.ሥ

— ንጉሥ ምኒልክ ልጃቸውን ዘውዲቱን ለአጤ ዮሐንስ ልጅ ለራስ አርአያ ሥላሴ ሲድሩ የሙሽራይቱ ዕድሜ 6 ዓመት ነበር ።

ጋብቻው ከተፈፀመበት ሥርግ ላይ ምኒልክ ለአዲሱ አማቻ ቸው ለራስ አርአያ ሥላሴ ብዙ ሽልማቶችን ሸልሟቸው ።ከሽ ልማቶቹም መሀል ፣ አንድ መድፍ ፣ 500 ጠመንጃ ፣ 200 ብርሌና ብርጭቆ ፣ 5 000 በግና ፍየል ፣ 5 000 ብር ይገኝበታል ። የሙ ዚዎቹና የአጃቢዎቹ ሽልማት ከዚህ አልገባም ።ለሙዚዎቹ ለእ ያንዳንዳቸው አስር ፈረስና በቅሎ ከነሙሉ ዕቃው ተሰጥተዋል ። ከገ.ሥ

— የእንጦጦ ማርያም የተሠራች ጊዜ ለጧፍ ማብሪያ ተብሎ ከውጭ አገር የመጣ ባለብዙ መስተዋትና የሻማ መሰኪያ ያለ በት ከጣሪያ ላይ የሚንጠለጠል የመብራት ጌጥ ነበር ። ያን ጌጣጌ የመብራት ማስቀመጫ ከጣሪያ ላይ ለመስቀል ሰዎች በመሰ ላል ላይ ይዘው ወጥተው ሳሉ ድንገት እምልጦአቸው ከመሬት ወደቀ ። በወደቀበትም ጊዜ አንዲትም መስተዋት ሳትሰበር ተገኘ። ከገ. ሥ.

— የእንጦጦ ማርያም ተሠርታ ለምረቃው ድግስ ሲደገስ የተዘጋ ጀው ቡሃቃ (የሊጥ ማቡኪያ) እያንዳንዱ እስከ 40 ኩንታል ዱቄት ድረስ የሚያስቦካ ነበር ። የቡሃቃውን ትልቅነት ለማ ወቅ አርባ ኩንታል ዱቄት ለማቡኪያ የሚገባበትንም ውሃ አብሮ ማሰብ ነው ። ሊጡ በሚወጣበትም ጊዜ ሊጥ አውጭዎቹ ከቡሃቃው ላይ በመሰላል እየወጡ ነበር የሚያወጡት ። —ከገ. ሥ

— የእንጦጦ ማርያም ተሠርታ ካለቀች በኋላ በየግድግዳው ላይ መንፈሳውያን ስዕሎች ይሳሉ ነበር ። ሰዐሊው የሚስለው በመሬ ባርብ ላይ ሆኖ ነበር ። አንድ ቀን ሰዓሊው በሚስልበት ጊዜ መረባርቡ ላይ ያለው ፣ ቀለም የያዘው ብልቃጥ ከመሬት ወደቀ ። ብልቃጡ ከመሬት በወደቀበት ጊዜ ቀለሙ ሳይፈስ ብልቃ ጡም ሳይሰበር ቁጭ ብሎ ተገኘ ።—ከገ. ሥ

— የእንጦጦ ማርያም ተሠርታ ለምረቃው ጊዜ ከፍ ያለ ድግስ ተደግሶ ነበር ። ጠጁ በአሸንዳ እየወረደ በጉድጓድ ውስጥ ይከማችና ሕዝቡ ከዚያ የጠጅ ኩሬ እንዲጠጣ ተደርጐ ነበር ። ወደ ጉድጓዱ ጠጅ የሚወርድበት 12 አሸንዳ (ቦይ) ተበጅቶ ነበር ። በግብር ላይ የበላውና የጠጣው መኳንንትና ሠራዊት ከግብሩ ሲወጣ ከዚያ የጠጅ ኩሬ (ባህር) ካለበት ይሄዳል ። በዚያም ኩሬው እንዳይቆሽሽ የሚጠብቁት ዘበኞች ጠጁ የተ ሸፈነበትን ጨርቅ ከፊት እያደረጉ ሕዝቡ በእፍኙ ጠጁን ይጠጣ ነበር ።—ከገ. ሥ

— ለእንጦጦ ማርያም ምረቃ ጊዜ የታረደው ከብት ብዛቱ 5 395 ነው ።—ከገ.ሥ

— ሐረርጌ በአሚር አብዱላሂ ተይዞ በነበረ ጊዜ ደጃች ወልደ ገብርኤል ወደ ሐረር ዘምተው አሚሩን ለማስገበር አስበው ነበር ።በዚያን ጊዜ አሚሩ ብዙ መድፎችና የተለያየ መሣሪያ አለው እየተባለ ይወራ ስለነበር የደጃች ወልደ ገብርኤል መኳንንትና ሠራዊት አንዘምትም ብሎ ከድቶ ወደኋላ ተመለሰ ።በዚያን ጊዜ አጤ ምኒልክ በአርሲ በኩል ዘምተው ነበርና እንጦጦ የቀሩት እቴጌ ጣይቱ የደጃች ወልደ ገብርኤል ሠራዊት መመለሱንና አዋሽ መድረሱን እንደሰሙ "....ከይቱና ከጨርጨር የመጣው ሰው ጠቅሎ ገብቶ ከከተማው እኔን ቢጠብቅ መልካም ነው ። ወዲያ ወዲህ ያለ እንደሆነ እጁን ለኔ ከብቱን ላንተ መርቄልሃለሁ ብለውሃል" ብለው የምንጃሩን ምስለኔ አዘዙ ።

ደጃች ወልደ ገብርኤል ሠራዊታቸውን ተከትለው እንጦጦ ገብተዋል ። በጣይቱ አዋጅ መሠረት የደጃች ወልደ ገብርኤል ሠራዊት ጠቅሎ እንጦጦ ገባ ። ሐረርጌ አልዘምትም ብሎ የፈራው ሠራዊትም ጣይቱ ዘንድ ቀርቦ "ስንቅ አለቀብን" ብሎ አቤት አለ ። ሐረርጌ ባለመዝመቱ የተናደዱት ጣይቱም በየምስለኔው እየሔደ እንዲከርም አቤት ያለውን ሠራዊት አዘዙ ። ለአንኮበር ፥ ለይፍራታ ፥ ለግሼ ፥ ለመራቤቴና ለሌሎችም ምስለኔዎች ደብዳቤ ጽፈው ለእያንዳንዱ የሠራዊቱ ቡድን አንዳንድ ደብዳቤ ሰጡ ። ሠራዊቱም የተሰጠውን ደብዳቤ እያየዘ ሄዶ ለየምስለኔው ሰጠ ። ምስለኔውም ሠራዊቱን በሙሉ እየሰበሰበ አሰረው ። ሠራዊቱ ከጣይቱ ተቀብሎ የወሰደው ደብዳቤ "....እየሰበሰብክ እሰርልኝ ።...." የሚል ነበር ።—ከገ.ሥ

— ምኒልክ የተለየ መጋረጃ ነበራቸው ።መጋረጃው እንደ መስተዋት የሚያብለጨልጭ ነው ።ይህ መጋረጃ በሚጋረድበት ጊዜ ምኒልክ ከመጋረጃው ውጭ ያለውን ሠራዊት ወይም መኳንንት ማየት ሲችሉ ከመጋረጃው ውጭ ያለው ሠራዊት ወይም መኳንንት ግን ወደ ውስጥ ምኒልክን ማየት አይችልም ነበር ። ይህ መስተዋት ዛሬ በአ. አ. ባንዳንድ ሕንፃ ላይ አለ ። ከገ.ሥ

— በምኒልክ ጊዜ ቀንድ ያለው ሰው ነበር ። ይህ ሰው ገንዘብ እየተቀበለ ቀንዱን ለሕዝብ ያሳያል ። ገንዘብ ካልሰጡት ግን ቀንዱን በጨርቅ ሸፍኖ ይውላል ። ይህን ሰው አጤ ምኒልክ አይተው

በቀንድ አበቃቀሉ ተደንቀው እሳቸውም እንደሌላው ሰው ገን ዘብ ሰጥተው ልብሱን አልብሰውታል ።—ከገ ሥ

— በምኒልክ ማድቤት 15 የጠጅ መገልበጫ ጋኖች ነበሩ ።እነኚህ ጋኖች የሚታጠቡት ሰው ከውስጣቸው እየገባ ነው ። እነኚህ የሸክላ ጋኖች እያንዳንዳቸው 1100 ብርሌ ጠጅ ይይዛሉ ። ብርሌ ስንል ይህን ሁላችን የምናውቀውን ሳይሆን የምኒልክን ሹሩቤ ብርሌ ነው ። የምኒልክ ኩባያውም ሆነ ብርሌው ከሁሉ የተለየ ስለ ነበር መለያው የምኒልክ ብርሌ ፣ የምኒልክ ኩባያ እየተባለ ነው ። ለምሳሌ የምኒልክ ኩባያ የሚባለው እያንዳንዱ ርዝመቱ 60 ሣንቲ ሜትር ያህል ነው ።—

— ምኒልክ ወደ አድዋ ሲዘምቱ ታህሳስ 22 ቀን አጠላ ሠፍረው ነበር ። በአምባላጌ ጦርነት የሞተው የጠላት ሬሣ መንገዱን ዘግቶ ስለያዘው በሌላ መንገድ በዋጅራት በኩል ሲጓዙ አንዱን ወንዝ 28 ጊዜ ተሻገሩት ። ወንዙና መንገዱ እየተጠማዘዙ ይገናኙ ስለነበር ነው ። ከገ.ሥ

— ምኒልክ ሰባተኛውን ዓመት የአድዋ ጦርነት መታሰቢያ በዓል በሚያከብሩበት ጊዜ ብዙ የውጭ አገር ሰዎች ሰልፍ እንዲመለ ከቱ ወደ አደባባይ ተጠርተው ነበር ። አሩር የሌለበት ጥይት በተተኮሰ ጊዜ ሠፈሩን እጅግ በጣም አናውጦት ነበር ። በዚህ ምክንያት በዚያ የነበሩት የውጭ አገር ሰዎች“ . . . .ከብዙ ድን ጋጤ የተነሣ አምስት 5 ደቂቃ እየወደቁ የተነሱ አሉ ። አንዳንዶ ቹም እስከ ስምንት ኪሎ ሜትር ድረስ ሸሽተዋል ። . . . .”ገ.ሥ

# ዋቤ መጽሐፍት


| | |
|---|---|
| ኀሩይ ወልደ ሥላሴ (ብላቴን ጌታ) | ከንግሥተ ሳባ እስከ አድዋ ጦርነት (ያልታተመ) |
| መርስኤ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ | ትዝታዬ (ያልታተመ) |
| መንግሥቱ ለማ | ትዝታ ዘ አለቃ ለማ ኀይሉ |
| ተክለ ሥላሴ (አለቃ) | የኢትዮጵያ ታሪክ (ያልታተመ) |
| ተክለ ኢየሱስ (አለቃ) | የኢትዮጵያ ታሪክ (ያልታተመ) |
| ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ | ከአጤ ቴዎድሮስ እስከ ቀ. ኃ. ሥ. |
| አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ (ፕሮፌሰር) | ዳግማዊ አጤ ምኒልክ |
| ወልደ ማርያም (አለቃ) | የአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ |
| ገብረ ሥላሴ (ጸሐፌ ትዕዛዝ) | ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ |
| Alvarez, F. | Narrtative of the Portugues Embassy of Abyssinia |
| Ambrogetti, P. | La Vita Sessuale Nell Eritrea |
| Antonelli, Conte Pitero | Menilik, Imperatore D'Etiopia |
| Audon, Henry | Voyage Au Choa |
| Baratieri , Oreste | Memorie D'Africa |
| Barrois, J. | Impressions De Voyage En Abyssinie |
| Bassi, LT. | Diario La Guerra Italo Abyssina |
| Berkeley George | The Compaign of Adowa and the Rise of Menilik |
| Borelli, J. | Ethiopie Meridionale |
| Capucci, Luigi | In Viaggio Per Lo Scioa |
| Cecchi, A. | La Battalia Di Abba Gagima |
| Cerulli, E. | Una Raccolta Amarica Di Canti Funebri |

| | |
|---|---|
| Chris Prouty | Empress Taitu and Menilik II |
| Clifford Halle | To Menilik in a Motor Car |
| Conti Rossini | Italia Ed Etiopia |
| Coulbreaux, J. B. | Au Pays De Menilik |
| Count Gleichen | With the Mission to Menilik |
| Crispi, F. | La Prima Guerra D'Africa |
| Elets | Emperor |
| Felter, Petro | La Relazione di Pitero Felter sullo Sgombero di Macale |
| Goedorp, Victor | A La Cour du Negus Ménilik |
| Greenfield | Ethiopia |
| Harold G., Marcus | The life and Times of Ménilik II |
| Harris, W. C. | The Highland of Ethiopia |
| Holland & Hozier | Expedition to Abyssinia |
| Johnston, Charles | Travels in Southern Abyssinia |
| Keller, C. | Alfred Ilg. |
| Kolmodin, J, | Traditions de Tsazzega ET Hazzega |
| Lande | UN Voyage Francois Dans L'Ethiopie Méridionale |
| Legean, G. | 1. Voyage in Abyssinie<br>2. Théodore |
| Leontiev, N. | Provinces Equatoriales D' Abyssinie |
| Le Roux, H. | Ménélik ET Nous 1902 |
| Mantegazza, V. | La Guerra D'Africa |
| Massaia, G. | I Miei Trentacinque Anni Di Missione Nell ALTO Etiopia |
| Maydin, H. C. | Simen, Its Heights and Abysses |




@BOOKALEM

| | |
|---|---|
| Mérab | Impressions D'Ethiopie |
| Michel, Charles | De Bonchamps Vers Fachoda |
| Moltedo, G. | L' Assedio Di Maccale |
| Nartini, Sebastiano | Ricordi Ed Escurission in Africa Dal 1878—1881 |
| Nicoletti Altimar | Fra Gli Abyssini |
| Pariset, Dante | Al Tempo Di Menilik |
| Poul De Lavribar | Douze Ans |
| Perhan, M. | The Government of Ethiopia |
| Pétridés, Pierre | Le Héros D'Adoua |
| REY | Un Conquered Abyssinia |
| Richard Pankhurst | Economic History of Ethiopia |
| Rood, Sir James Rennell | Social and Diplomatic Memories |
| Rossi, Adolfo | La Incerta Politica |
| Salimbeni, Augusto | Tre Anni Di Levoro Nel Gojjam |
| Stern | Captive |
| Traversi, Leopoldo | 1/ Let Marefiá<br>2/ Il Conte Pietro Antoneli<br>3/ Gli Eredi Di Menelik<br>4/ Un Pionieri Pietro Felter |
| Waldmeier | Ten Years Life in Abyssinia |
| Wellby, M. S. | Twixt Sirdar and Menelik |
| Wurth, R. | Hygiéne Publique Et Privee En Abyssinie |
| Wylde | Modern Abyssinia |
| Zaghi, C. | 1/ La Missione Del Maggiore Salsa Al Campo Sciona Di Adua<br>2/ Crispi e Menelich Nel Diario Inedito Dell Conte Augusto Salimbeni. |




@BOOKALEM

@BOOKALEM

@BOOKALEM

@BOOKALEM

@BOOKALEM



ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ እንደሆኑ ለእንግሊዟዋ ንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት ደብዳቤ ነው ። ደብዳቤው ዛሬ በለንደን ፐብሊክ ሪኮርድ ማከማቻ ክፍል ውስጥ ይገኛል ። የተጻፈበትም ምኒልክ በአባታቸው ዙፋን ተመልሰው መቀመጫቸውን ያገለጹና ወዳጅነታቸውን እንደገና እንዲታደሱ የሚገልፅ ነው ።

Printed in England by
Percy Brothers Limited,
The Hotspur Press,
Whitworth Street West,
Manchester, M60 1PB,
and 145 Fleet Street
London, EC4A 2BU



በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩፡ አምላክ፡ መልእክት፡ ዘተላከ፡
ከንጉሠ፡ ነገሥት፡ ምኒልክ፡ ዘሸዋ፡ ሪስ ኅበ ንግሥት፡ እጅግ፡ ትኅ፡ እንደምን
ነሽ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር፡ ይመስገን፡ ደህና፡ ነኝ፡ በእግዚአብሔር፡ ብሔር
[illegible]



ሀሌ ማተሚያ ቤት